
# አጤ ቴዎድሮስ



ከጳውሎስ ኞኞ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# አጤ ቴዎድሮስ

ከጳውሎስ ኞኞ

## ማውጫ

ምዕራፍ 1 ............................................................... 6
ትውልድና አነሳስ............................................................6
ምዕራፍ 2 ............................................................... 34
ራስ አሊ እቴጌ መነን ደጃች ጐሹ ዘውዴ ራስ አሊ አሉላ ................. 34
እቴጌ መነን ............................................................ 41
ጐሹ ዘውዴ ............................................................ 43
ምዕራፍ 3 ............................................................... 50
የጐጃምና የሰሜን ጦርነት............................................... 50
ምዕራፍ 4 ............................................................... 56
ደጃዝማች ብሩ ጐሹ - ደጃዝማች ውቤ ብሩ ጐሹ......................... 56
ውቤ..................................................................... 66
ምዕራፍ 5 ............................................................... 82
ንግሥ.................................................................... 82
ምዕራፍ 6 ............................................................... 100
ደጃች ተድላ ጓሉ - አቡነ ሰላማ - ወይዘሮ ተዋበች አሊ - ፕላውዲን - ዮሐንስ ቤልና ደጃች ንጉሤ.............................................. 100
ተድላ ጓሉ ............................................................ 100
አቡነ ሰላማ........................................................... 108
እቴጌ ተዋበች አሊ ................................................... 116
ፕላውዲን (ዋልተር ቺቺሊ ፕላውዲን)............................... 119

ቤል/ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ................................................ 123
ደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤል ...................................... 124
ምዕራፍ 7 ............................................................... 131
የቴዎድሮስ ሰውነት ጠባይ ርህራሄ ጭካኔና ፍርድ ........................ 131
ጠባይ ............................................................... 135
ርህራሄ (ደግነት) .................................................. 142
ጭካኔ ............................................................... 146
ፍርድ ................................................................ 152
ምዕራፍ 8 ............................................................... 157
የአረቦች ጥንስስ ..................................................... 157
ምዕራፍ 9 ............................................................... 162
ልማት ................................................................ 162
ምዕራፍ 10 ............................................................. 182
ፈረንጆቹ ለምን ታሰሩ? ............................................... 182
ምዕራፍ 11 ............................................................. 204
የራሳም መልዕክተኛነት .................................................. 204
ምዕራፍ 12 ............................................................. 227
እስረኞች ተፈትተው ታሠሩ ............................................ 227
ምዕራፍ 13 ............................................................. 259
የእስረኞች የመቅደላ ኑሮ ............................................... 259
ምዕራፍ 14 ............................................................. 278

ጦር መጣ ........................................................ 278
ምዕራፍ 15 ........................................................ 303
ጦርነቱ ተጀመረ ........................................................ 303
ምዕራፍ 16 ........................................................ 338
እቴጌ ጥሩ ወርቅ ውቤ - ልጅ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ...................... 338
ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ........................................................ 341
ዋቢ መጻሕፍት ........................................................ 361
ስለደራሲው በጥቂቱ........................................................ 363

# ይድረስ ከመጽሐፌ አንባቢዎች

## የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ

2ኛ ተሰሎንቄ 3፥ 17

የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ በብዙ ሰዎች ተጽፍዋል። ቴዎድሮስ በመሳፍንት ተከፋፍላ የወደቀች አገራቸውን ለማንሳት የተነሱ ታላቅ አገር ወዳድ ነበሩ። ቴዎድሮስ በብዙ ገዢዎች ተቆራርጣ የነበረችውን ኢትዮጵያን እንደነበረችበት አንድ ለማድረግ ከፍተኛ ድካም ደክመዋል። ያለ እረፍት ሠርተዋል። የግል ዝና እንጂ የአገር ጉዳይ የማይሰማው የዘመናቸው መኳንንት ቢሾሙት እየሸፈተ ቢሸልሙትና ቢያምኑት እየከዳ ስላስቸገራቸው በተፈጥሮአቸው ቁጡ የሆኑት ቴዎድሮስ አይቀጡ ቅጣት እየቀጡ ተቃዋሚዎቻቸውን ለማጥፋት ሞከሩ። ግን አልሆነላቸውም።

ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ከተለያዩ መኳንንት አገዛዝ አውጥተው ባንድ መንግሥት ሥር እንድትተዳደር ለማድረግ የጥርጊያውን መንገድ የከፈቱ ዋናው መሐንዲስ ናቸው። ለአጤ ዮሐንስና ለአጤ ምኒልክ መጓዣቸውን መንገድ በሕይወታቸው የከፈቱ ቴዎድሮስ ናቸው።

የአጤ ቴዎድሮስ ድካም እምብዛም ተዘርዝሮ ባንድነት አልተጻፈ ስለ ነበረ ከየመጻሕፍቱ ለቃቅሜ ዘርዘር ለማድረግ ሞክሬአለሁ። የየተቃዋሚዎቻቸውንም ታሪክና የአገዛዝ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ለመግለጥ ሞካክሬአለሁ። ምኞትና ሓሳቤ አገሩን ወዳድ የሆነው ኢትዮጵያዊ ትልውድ በመጠኑ ቢሆን ታሪኩን እንዲያውቅ ለማድረግ ነው።

ቴዎድሮስ ብዙ ጊዜ የቀረቡልን ጨካኝና ክፉ ሰው ሆነው ነው። ይህ ባህርያቸው ቢኖርም ቴዎድሮስ ጨካኝ ብቻ ሳይሆኑ ደግና ሩህሩህም ነበሩ። አጋጣሚ ክፉ ያደርጋቸዋል። አጋጣሚም ደግ ያደርጋቸዋል። እነኚህም ተለዋዋጭ ባህሬአቸውን ለመግለጥ ሞክሬአለሁ።

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ታሪኩን ሳጠረቃቅም አራት ዓመት ያህል ፈጅቶብኛል። ከሚስቴ ከወይዘሮ አዳነች በስተቀር ማንም የረዳኝ ስለሌለ በዚች ቦታ ላይ የማመሰግነው ሰው የለኝም።

ደህና እንሁን ብቻ

# ምዕራፍ 1

# ትውልድና አነሳስ

ካሣ በ1811 ዓ.ም ጥር 6 ቀን ተወለዱ። የተወለዱትም ከጐንደር ከተማ 12 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ በምትገኝ ዳዋ ከተባለች መንደር ነው። የካቲት 16 ቀንም ጐንደር ከተማ በሚገኘው በአባ አቢየ እግዚእ ቤተ ክርስትያን ክርስትና ተነስተው የክርስትና ስማቸው ገብረ ኪዳን ተባለ።

በኋለኛው ዘመን አጤ ቴዎድሮስ የተባሉት ካሣ አባታቸው አቶ ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ይባላሉ። አቶ ኃይሉ በ1810 ዓ፣ም በመስከረም ወር የእንፍራንዝዋን ተወላጅ ወይዘሮ አትጠገብ ወንድ በወሰንን አገቡ። በተጋቡ በዓመቱም አትጠገብ ለአቶ ኃይሉ ወንድ ልጅ ወለዱላቸው። ልጁም ካሣ ተባለ።

አቶ ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ የመጨረሻ ልጃቸውን እድገት ሳያዩና ናፍቆቱም ሳይወጣላቸው ካሣ በተወለዱ ባመቱ ማለት በ1812 ዓ.ም ሞተው ሰቀልት ወረዳ ባለው ጋጋና ዮሐንስ ቤተ ክርስትያን ተቀበሩ። ካሣም በእርግብ በር አምባ አደጉ።

ካሣ ወይም በኋለኛው ዘመን ቴዎድሮስ የተባሉት የኮሶ ሻጭ ልጅ መሆናቸውን አንዳንድ የውጭ አገር ፀሐፊዎች ጽፈዋል። የአገራችንም ታሪክ ፀሐፊዎች ይህንኑ አምነውበት ቴዎድሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ ናቸው እያሉ ተርከዋል። እናቲቱ ኮሶ ለመሸጣቸው ግን የሚያቀርቡት ማስረጃ የለም። እኔም አላገኘሁም። ወይዘሮ አትጠገብ በምን ምክንያት ኮሶ ይሸጡ እንደነበር በዚያ ዘመን ኮሶ ከየዱሩ በሚሸመጠጥበት ጊዜ የኮሶው ገበያ ምን ያህል የኑሮ መግፊያ ጥቅም ይሰጣቸው እንደነበረም የሚተርክ የለም። የወይዘሮ አትጠገብን የኮሶ ሻጭነት ወሬ ያባዛውና በመጽሐፉ ለዓለም ያዳረሰው ሚስዮናዊው ሄነሪ እስተርን ነው። እሱም የጻፈው ከሰዎች የሰማውን የሐሜታ ወሬ ይዞ ነው።

ካሣን ከድሃ ቤተሰብ አውጥቶ ከሀብታሞች ጉያ ለመጨመር መከራከሬ ሳይሆን እውነተኛውን ወይም እውነት የሚመስለውን ታሪክ ለመከተል ብዬ ነው። የካሣ ወይም የአጤ ቴዎድሮስ አያት ማለት የአቶ ኃይሉ አባት ወልደ ጊዮርጊስ ደጃዝማች ናቸው ይህንንም አቶ ገሪማ ታፈረ በመጽሐፋቸው ውስጥ

በሰፊው ባሳዩት ዘር ቆጠራ አስፍረውታል። በሴት በኩል ደግሞ የካሣ አያት ወዳጀ የራስነት ማዕረግ ያላቸው ናቸው። ራስ ወዳጀ ወንድ በወሰንን ይወልዳሉ። ወንድ በወሰን ደግሞ የእንፍራንዝ ባላባት ልጅ የሆኑትን ወይዘሮ ትሻልን አግብተው ወይዘሮ አትጠገብን ወለዱ። ወይዘሮ አትጠገብ ካሣን ወለዱ። ይህ ከሆነ የካሣ እናት ወይዘሮ አትጠገብ እንዴት ባንድ ጊዜ ደህይተው ኮሶ ከመሸጥ ደረጃ ደረሱ?

አንደኛው ወገን በመንግሥት ተወርሶ ደኸየ ቢባልም በአባትም ሆነ በእናት በኩል የራስና የደጃዝማች የልጅ ልጅ የሆኑት ካሣ በድህነት አደጉ ለማለት አያስደፍርም። በሌላው በኩል ደግሞ አቶ ገሪማ ታገረ ካገር ሽማግሌዎችና ከቆዩ በግዕዝ መጻሕፍት ባገኙት መረጃ እንደጻፉት የካሣ አባት አቶ ኃይሉ ከወይዘሮ ተክሌ ደጃች ክንፉን መውለዳቸውን ይገልፃሉ። በዚህ ገለፃ መሠረት ደጃዝማች ክንፉ ታላቅ ወንድም ደጃዝማች ማሩ አጐታቸው ሆነው እነኚህና ሌሎችም ዘመዶች በህይወት እያሉዋቸው የካሣ እናት ወይዘሮ አትጠገብ ልጃቸውን ኮሶ እየሸጡ አሳደጉ ማለት የማይመስል ትረካ ነው። እነኚህ ዘመዶች ቢኖሩም የካሣን ከኃይሉ መወለድ አልተቀበሉም ነበር እንዳይባል ካሣን በሕፃንነታቸው ወስደው እያስተማሩ ያሳደጉ አጐታቸው ደጃች ማሩና ደጃች ክንፉ ናቸው፡ ይህንንም ታሪክ ፀሐፍት ሁሉ ተስማምተውበታል።



አጤ ቴዎድሮስ

ለኔ እውነተኛ ትረካ አስመስሎ የታየኝና የተቀበልኩትም አቶ ገሪማ ታፈረ የጻፉት አተራረክ ነው። የአቶ ገሪማ ታፈረ መጽሐፍ ትረካው እንዲህ የሚል ነው። ወይዘሮ አትጠገብ በወይና ደጋው ክፍል አውሊድ ማርያም በተባለው ሠፈር ካሉት ዘመዶቻቸው ጋር በመሬት ውርስ ምክንያት ተጣልተው ይከራከሩ ነበር። በኋላም በሽማግሌ እርቅ ተደርጐ ሽማግሌዎች የተጣሉትን ዘመዶች አስታርቀው መሬት ሲያካፍሉ ኮሳ አላየ በሚባለው ቦታ ያለ መሬት ለወይዘሮ አትጠገብ ደረሳቸው። ወይዘሮ አትጠገብም ይህንኑ በዕጣ የደረሳቸውን መሬት ለማሳረስ ደኑን ሲያስመነጥሩ በደኑ መሀል አንድ ያፈራ ቅጠል የኮሶ ዛፍ ስለ ነበር ይህ ዛፍ እንዳይቆረጥ ለደን መንጣሪዎቹ ነግረው ወደ ጐንደር ተመለሱ። በሌላ ጊዜ የዚያ የተመነጠረ የእርሻ ቦት ሥራ ከምን እንደደረሰ ለመመልከት ከጐንደር ተነሥተው ወደ ኮሶ አላየ ሔዱ። ሥራውን ተመልክተው ወደ ጐንደር ቤታቸው ሊመለሱ ሲሉ ያ የኮሶ ዛፍ በብዛት ማፍራቱን ያየች ገረዳቸው ኮሰውን ስትሸመጥጥ አይተው ወይዘሮ አትጠገብ ተይ ምን ያደርግልሻል ብለው ተቆጧት። ገረዲቱም ለቤት የሚሆን ለመያዝ ብዬ ነው ብላ የሸመጠጠችውን ኮሶ ይዛ ጐንደር ገባች።

ይህንን ከተመለከቱት የመሬት ባላንጣዎቻቸው መሀል አንደኛው በሰንበቴ ማህበር ላይ እየተበላና እየተጠጣ ሲጫወቱ «አትጠገብ በአለባበስዋና በሁኔታዋ ሴት ወይዘሮ ትመስላለች። ግን ከዚህ ኮሶ እያስለቀመች ጐንደር ወስዳ ተሸጣለች» ብሎ አወራ። በዚያም የሰንበቴ ማህበር ከጐንደርና ከገጠር የሚመጡ ማህበረተኞች ስለነበሩበት ወሬውን ወይም ሐሚታውን በየቦታው አዳረሱት። እንደ ገሪማ ታፈረ አፃፃፍ ወይዘሮ አትጠገብ ኮሶ ሻጭ አልነበሩም። የኮሶ ሽያጭም ለንግድ ትርፍ ሥራ ምንም የማይጠቅም ነበር። እንኳን በዚያን ዘመንና እኔ በደረስኩበት በኔ ዘመን እንኳ በእልፍኝ እህል የሚለወጠው ኮሶ ለአንድ ቤተሰብ መድኃኒትነት በቂ ነበር። ታዲያ አትጠገብ ምን ትርፍ ያስገኝልኛል ብለው ነው የኮሶ ነጋዴ የሆኑት? በዚያን ዘመን ላልነበርነው ሰዎች ነገሩ እንቆቅልሽ ቢሆንም ለማመንም አስቸጋሪ ነው። አንዳንዶች የውጭ አገር ታሪክ ፀሐፊዎች ማንኛውንም ሐሜትና የእረኛ ወሬ እያጋበሱ ስለ ሚፅፉም እያጣሩ ማመኑ የኛ ድርሻ ይመስለኛል። ወደ ፊት እንደምናነበው ቴዎድሮስ «ከትቢያ ላይ የተነሳሁ ነኝ» እያሉ የሚናገሩት አንደኛ ለትህትና ብለው ነው። ሁለተኛ ዳዊት ደጋሚ ስለነበሩ በዳወኢት መዝሙር ውስጥ የእሥራኤሉ ንጉሥ ዳዊት ስለራሱ ሲናገር

ከትቢያና ከአመድ ላይ የተነሣሁ ነኝ እያለ ስለጻፈ በአገራችን እምነት መሠረት ለትህትና በዚያ መመራታቸው ነው።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ባልታተመው ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በሚለው መጽሐፋቸው «....... ልጅ ካሣ ባላባትነት ካላቸው ውስጥ መወለዳቸው እርግጥ ሆኖ እናትዬዋ በድህነት ምክንያት ኮሶ እየሸጡ ልጅ ካሣን ማሳደጋቸው የታመነ ነው።......» ብለዋል። አትጠገብ በእናት በአባታችው ከባላባቶች ከተወለዱ ውርስ አላቸው። የባላባትነቱ ውርስ ቢቀር ርዝራዥ ኩርማንም ብትሆን የመሬት ውርስ አላቸው። ብዙዎቻችን እንደምናውቀው እንኳን በዚያ ዘመን በቅርቡም ቢሆን ባላባት ብዙ መሬት ያለው ሰው ነው። ይህ ከሆነ ቅድም እንዳልኩት በእናታቸውም በአባታቸውም በኩል በሙሉ ካልተወረሰ እንዴት ሙልጭ ያሉ ደሃ ሊሆኑ ይችላሉ? በባላባት ልጅነታቸው ከተማመንን በዘመኑ እንደነበረው አባባል ዘር ማሰደቢያ የሆነ የግድ እንዴት ሊጀምሩ ይችላሉ? ይህ ጥያቄ በዘመኑ በቴዎድሮስ ዘመን ጐንደር ለነበረው ለእንግሊዛዊ መልዕክተኛ ለሚስተራ ራስምም አልተመለሰም።

ራሳም በ1ኛው ቮልዩም መጽሐፍ ላይ ስለዚሁ ሲፅፍ «......እስተረን እንደፃፈው እናትዬዋ ኮሶ ሻጭ መሆናቸውን ለማጣራት ምክሬ ነበር። አንድም ሰው ኮሶ ሲሸጡ አይቻለሁ የሚል የዓይን ምስክር አላገኘሁም። ያነጋገርኳቸው ሁሉ የሚነግሩኝ የባላባት ዘር መሆናቸውን፤ አባታቸውም የአማራ ሳይንት ራስ መሆናቸውን ነው።....... በአበሻ ውስጥ ታላላቅ ከሚባሉት ሰዎች ዘር መወለዳቸውን ነው ያጣራሁት።



አጤ ቴዎድሮስ ከእናታቸው ጋር

«....... እስተርን በንጉሡ ችሎት ቁሞ ቴዎድሮስ ሲያነጋግሩት የድፍረት ቃል እየመሰለ ጣቱን በማስጮሁ በለው በለው በሽመል ሲመታ ከኪሱ የማስታወሻ ደብተሩ ወደቀች። በዚያችም ደብተር ላይ «ንጉሱ ገዳይ ናቸው» የሚል ቃል በመገኘቱ ዕቃው ሁሉ ተፈትሾ ታሠረ። ከዚህ በኋላ ሲለቀቅ ያን ቂሙን ለመወጣት ያዋረደ መስሎት የኮሶ ሻጭ ልጅ ብሎ ጻፈ።....... » ብሏል። ይህ ይብቃን።

ካሣ በደጃች ክንፉ ቤት በነበሩበት ጊዜ አንድ ቀን ደጃች ክንፉ ለማህበረ ሥላሴ መነኮሳት «አልጋዬ ከልጆቼ እንዳይወጣ እዘኑልኝ። አትርሱኝ» ብለው በዘመኑ በነበረው ልማድ መሠረት ሥጦታ አስይዘው ሁለት የሚስጥር

አሽከሮቻቸውን ወደ መነኮሳቱ ላኩ። መነኮሳቱም «ከልጆችህ አልጋህን የሚወርስ ሰው የለም። ገዢው ካሣ ነውና አደራ ብለህ ንገረው» ብለው መልስ ላኩባቸው። በዚህ ነገር ደጃች ክንፉ ካሣን ጠሉዋቸው። ቂምም ያዙባቸው። ይህን የደጃች ክንፉን ቂም መያዝ የሰሙት ወይዘሮ አትጠገብም ልጃቸን ወስደው ደንቢያ ውስጥ ካለው ቸንከር ተክለሃይማኖት ደብር ተደብቀው እንዲማሩ አደረጉ።

ይህ በሆነበት ጊዜ በጠቅላላው የቤጌምድር ገዢ ራስ ይማም ነበሩ። በደንቢያ ደጃች ማሩ በራስ ይማም ላይ ሸፈቱ። ራስ ይማምም ደጃች ማሩን ለመያዝ ወደ ደንቢያ በዘመቱ ጊዜ ካሣ ይማሩበት የነበረውን ቸንከር ገዳምን በጦር ወረው በዚያ ያሉትን ብዙ ሰዎች ገደሉ። ከተማሪዎችም መሐል 48 ልጆችን ሰልበው ጥለዋቸው ሔዱ። ካሣ ግን ተሸሽገው ያለ ምንም ጉዳት አመለጡ።

ምንም ያህል ሳይቆዩ ደጃች ክንፉ ሞቱ። ደጃች ክንፉ እንደ ሞቱ ልጆቻቸው ልጅ ጋረድ ልጅ መኰንንና ልጅ ይልማ በሥልጣን ውርስ ተጣሉ። ልጅ ካሣ ኃይሉ ለልጅ መኰንን ለመርዳት መጥተው ከልጅ መኰንን ጋር ሆኑ። መኰንንና ይልማ ሁለቱ ወንድማማቾች ዘንጊ በሚባል አገር ላይ ተዋግተው ልጅ መኰንን ክንፉ ወንድማቸው በይልማ ክንፉ ድል ሆኑ። ልጅ ካሣም ተማረኩ። ነገር ግን ከይልማ ክንጉ ጋር የቅርብ ወንድማማቾች ከመሆናቸውም ሌላ አብሮ አደጐች ነበሩና ምርኮኛውን ካሣን ከነፈረሳቸው ነፃ ለቀቋቸው።

ካሣ አቶ ቢተዋ ከሚባሉ መኳንንት ቤት እንደ ዘመኑ ልማድ ወታደር ለመሆን አሽከርነት አደሩ። ካሣ ጋማው እጅግ የረዘመ ድንቅ ፈረስ ነበራቸው። አቶ ቢተዋ ዝሆን አደን ሲሔዱ ካሣም ጌታቸውን አቶ ቢተዋን ተከትለው ከዝሆን አደኑ ሔዱ። አቶ ቢተዋ አንድም ዝሆን ሳይገድሉ ካሣ በዚያ ፈረሳቸው ሆነው ሁለት ዝሆኖች ገደሉ። በዚህ ግዳይ አቶ ቢተዋ እንደተቆጡዋቸውና እንዳኮረፉዋቸው ባወቁ ጊዜ የገዳይነት ምልክት የሆነውን ሰለባ አውልቀው ጥለውላቸው ከእሎሃ ገስግሰው ወፍታ ከሚባለው ሠፈር ገቡ። ከእሎሃ እስከ ወፍታ ድረስ ሁለት ቀን ያስኬዳል ካሣ ግን እንደ ተናደዱ በዚያ ፈረሳቸው ባንድ ቀን ገቡ።

የደጃች ክንፉ ልጆች ተስማምተው ከታረቁ በኋል ባንድነት ሆነው የጐጃሙን ገዥ ብሩ ጐሹን ሊወጉ ወደ ጐጃም ዘመቱ። ይህን የሰሙት ካሣም

አብረው ዘመቱ። የሁለቱ ወገኖች ወታደርም ቸንቲ በር በተባለው ሥፍራ ተጋጥሞ ሲዋጋ የደጃች ከንፉ ልጆች ድል ሆኑ። ካሣም ከጦርነቱ ቦታ ሸሽተው ዘርጊ ከሚባለው አገር ገብተው ካንድ ባላገር ሰው ቤት ተደበቁ። ቀን ቀን ከጫካ እየዋሉ ሌሊት ለአዳራቸው ከዚያ ሰው ቤት እየገቡ እያደሩ ወር ሙሉ ተሸሸጉ። አገርድ እህና ሲሆንም ከዚያ ወጥተው ወደ ዳሞት ሔዱ።

ካሣ ዳሞት ሔደው ለደጃች ጐሹ ሎሌነት አደሩ። ደጃች ጐሹ ከልጃቸው ከብሩ ጋር አንጋጣ ላይ በተዋጉ ጊዜ ካሣ ከደጃች ጐሹ ጐን ነበሩ። በጦርነቱም አንድ ሰው ማርከው ሁለት የጠላት ጦር ይዘው ፈረሳቸው ቆስሎ ተመለሱ። ከጌታቸው ከደጃች ጐሹም ዘንድ ቀርበው በፎከሩ ጊዜ ደጃች ጐሹ ተደስተው አንድ ፈረስ ሸልመው ቀይ ለምድ አስለበሷቸው። እየቆዩ ግን ደጃች ጐሹ ስለ ጠረጠሩዋቸው ወይም ሥልጣን ይቀማሉ በለው ስለፈሩዋቸው ለማሰር ሲያስቡ ይህን የሰሙት ካሣ አምልጠው ወጡ።

ካሣ በጀግንነታቸው ምክንያት ሁሉም ይፈሯቸዋል ይጠሏቸዋልም። ካሣ መሔጃ አጡ። በኋላም አስበው ድሮ ከነበሩበት ቤት ከአቶ ቢተዋ ጋር ይሄን ያህልም ጠብ ስልሌላቸው ተመልሰው ካቶ ቢተዋ ዘንድ ሔዱ። አቶ ቢተዋ በቋራ ላይ የራስ አሊ እናት የእቴጌ መነን ምስለኔ ነበሩ። ካሣ አቶ ቢተዋ ዘንድ የሔዱት አቶ ቢተዋን ለመጠጋት ብቻ ሳይሆን ከተወለዱበት አገር ከቋራ ለመግባት ብለውም ነበር። አቶ ቢተዋ የማይወዷቸውን ካሣን እንደገና በማግኘታቸው ተቆጥተው አሠሩዋቸው። ካሣም ከአቶ ቢተዋ እስረኝነት አምልጠው ቋራ ወደ ተወለዱበት ሠፈር ሔዱ።

ካሣ ወደ ቋራ አምልጠው በወረዱበት ጊዜ 12 ሰዎች ተከትለዋቸው ወረዱ። ይልማ ወሰን የሚባል ከእቴጌ መነን ተጣልቶ ሸፍቶ ቋራ ነበርና ካሣ ወደሱ ዘንድ ሔደው ተደባለቁ። መጠጊያ ቦታ አሳዳሪ ጌታ ያጡት ካሣ ሸፍትነት ጀመሩ።

ካሣ ከይልማ ወሰን ዘንድ በሔዱ ጊዜ በደስታ ተቀብሏቸዋ «አይዞህ የአውራዬ ልጅ። የእንጨት ፍሬ በልተን እንኖራለን» ብሎ አበረታታቸው። ጫቆ በሚባለው ቦታ ላይ ሰባ የሚሆኑ ሽፍቶች ነበሩ። ካሣ ከእነኚህ ሽፍቶች ጋር አንድ ውል ተዋዋሉ። ውሉም አንደኛው ወገን ያገኘውን ከሌላው ቡድን ጋር እንዲካፈል የሚል ነበር። በዚህ ተስማምተው ከተለያዩ በኋላ ካሣ ከክራሆ ገበያ የሚመለሰውን ነጋዴ ዘርፈው በውላቸው መሠረት ለዚያኛው የሽፍታ

ቡድን «ኑና እንካፈል» ብለው ላኩባቸው። እነኚያም የሰረቁትን ሠንጋ አርደው ብቻቸውን ይበሉ ነበርና የካሣ መልዕክተኛ መልዕክቱን በነገራቸው ጊዜ «ወንድሞቹ በግዛት ሲያስጨንቁን ኖሩ። ደግሞ እሱ አሁን የሌባ አለቃ ሊሆን ነው? » ብለው «አንተም ለራስህ ቀማ እኛም ለራሳችን እንቀማለን ብለህ ንገር» ብለው መልዕክተኛውን መለሱት።

ልጅ ካሣም እነኛ ጓዶች ብቻቸውን መብላታቸውንና የላኩትንም መልዕክት ከመልዕክተኛው እንደሰሙ ወዲያውኑ ተነሥተው ያሏቸውን 12 አሽከሮች አስከትለው ሔዱ። እነኛም ዘንድ ሲደርሱ «የተማማልነውን መሐላ የከዳችሁት ለምንድነው? » ብለው ጠየቋቸው። እነኛም «ለየራሳችን እንሥራ ብለን ነው» አሏቸው። ልጅ ካሣም ተናደው እናንተ ሐሰተኞች ብለው ጐራዴያቸውን መዝዘው ያዘው አሉ። እነኚያም ሰባ ሰዎች ሲሸሹ ከመሀላቸው ሰዎቹ እግራቸውን ከጉልበታቸው ላይ እያስቀረጡ ጣሉዋቸው። የመጀመሪያ የቆረጣ ተግባራቸው ይህ ነው።

ከዚህ በኋላ ቱምሐ ወደሚባል ሥፍራ ሔዱ። በዚያም ካለው የጐበዝ አለቃ ከሆነው ከአቶ ደረሰ አቡ ጋር በሕብረት ለመሥራትን ወዳጅ ለመሆን ተማማሉ። ይህን ካደረጉ በኋላ መቀመጫቸውን ፈሮሄ ላይ አደረጉ። በዚያም ሆነው ጐረምሳውን በማባበል ተጨማሪ 30 ሰዎች ተካታይ አገኙ። ይህን ካገኙና ድርጅታቸውን ካጠናከሩ በኋላ 45 የሚሆኑትን ተከታትዮቻቸውን ይዘው ገንዳዋ ቆላ ወረዱ። ልጅ ካሣ ወደ ገንዳዋ ቆላ የወረዱት በጣም ብዙ የሆኑ የሩቅ አገር ነጋዴ በዚያ በኩል እንዲያልፍ አሰልለው ስላወቁ ለመዝረፍ ብለው ነው። ያሰቡትም አልቀረ ከቆላው እንድወረዱ ነጋዲዎቹን በጦር ኃይል መትተው ብዙ ሀብት ዘረፉ። ብዙ ፈረስና በቅሎ ገንዘብም በብዛት አገኙ። ተከታዮቻቸውም በዚህ ድልና ዘረፋ በጣም ደስ አላቸው።

ይህን ድልና ሀብት የቀመሱት ካሣ በነሩት ለመግፋት ሠራዊታቸውን ያጠነክሩና ያበዙ ጀመር። እያደርም ሠርቶ ከማግኘት ይልቅ የሌላውን ሀብት መዝረፍ ያማረው ሁሉ ይገባላቸው ጀመር። ተከታዮቻቸው 300 ያህል በደረሱበት ጊዜ ወደ ወሰን ሔደው በሱዳን ግዛት ውስጥ ከሚኖረው እንድሪስ ከሚባለ ሻንቅላ (ግንጃር) ጋር ወዳጅነት መሠረቱ። አብረው እየተዟዟሩ ለመዝረፍ ተስማሙ።

ከእንድሪስ ጋር ባደረጉት ስምምነት መሠረት አምባ አምበ ላይ ከሚባለው ሠፈር ገብተው ለመዝረፍ ወሰኑ። ዘጠኝ ቀናት ያህል ተጉዘው ከሥፍራው ሲደርሱ ካሣ የራሳቸውንና የእንድሪስን ጦር ባንድነት አስለፉ። ዘራፊው ሠራዊት ወደ ሚዘርፈው መንደር ከመሔዱ በፊት የመንደሩ ነዋሪዎች ኃይለኛ ጦረኞች ስለነበሩ ካሣ ብልሃት ፈለጉ። ያሰለፉትን ሠራዊት መንደሩ አጠገብ አድርሰው ሁሉም ባንድነት ቆሞ እንዲጮህና ወደ መሀል በሚገባበትም ጊዜ እየጮኸ እንዲገባ አዘዙ። ወታደሩ በታዘዘው መሠረት እየጮኸ ወደ መንደሩ ሲገባ የመንደሩ ሰው ድንገተኛ ነገር ስለሆነበት ሠፈሩን እየለቀቀ ሸሸ።

ካሣ ከእንድሪስ ጋር ባደረጉት ወረራ ብዙ ዘረፋ ተገኘ። ፍየልና በግ ላምና፥ በሬ በብዛት ተዘረፈ። ከመንደሩ ነዋሪዎችም 600 የሚሆን ሰው ተያዘ። በነካሣ ሠራዊት ላይ ግን ከሁለት ሰዎች መቁሰል በስተቀር የደረሰ አደጋ አልነበረም። ከዚያ ተመልሰው ሠፈራቸወን አይማ ወንዝ ላይ አደረጉ። ሠራዊታቸወን በአይማ ወንዝ ጥቂት ቀና እንዲቆይና ከድካሙ እንዲያገግም ካደረጉ በኋላ ደለጉ ወደሚባል ስፍራ ተዛወሩ።

ደለጉ ላይ ሠፍረው ሳሉ የአገው ሰዎች መከረውና አድብተው ለሊት መጥተው አደጋ ጣሏብቸው። የካሣም ሰዎች ይህን የለሊት አደጋ ድንገተኛ ነገር ስለሆነባቸው አብዛኛዎቹ ሸሹ። ካሣም ቀን ቀን ከሥርዋ የሚቀመጡባት ዛፍ ነበረችና ከዚያች ሥር ሔደው ቆመው አሽከራቸውን እያሸለሉ እሳቸው እየፎከሩ የሚሸሸውን ወታደራቸውን «ምን ተባብለን ነበር? ጀግና» እያሉ አበረታተው ጐራዴያቸውን መዝዘው ከመጣባቸው ጦር መሀል ገቡ። ወዲያውኑም ከፊታቸው ያገኙዋቸውን ሦስቱን ሰኦች ሲገድሉ ያየው ወታደራቸው ልበ ሙሉ ሆኖ እየተመለሰ ከውጊያው ገባ። ከዚህ በኋላ የካሣ ወታደር ማባረር የአገው ሰው መሸሽ ጀመረ። ካሣም በፈረሳቸው ላይ ሆነው እያባረሩ አራት ሰዎች ገደሉ 360 የሚሆኑ አገዎችም ተማረኩ።

በማግስቱ ካሣ የተማረኩትን ሰዎች አስቀርበው «ምን ብበድላችሁ ነው የወጋችሁኝ?» ብለው ጠየቁ። ምርኮኞቹም «እርስዎ መኖርዎን አላወቅንም። የመጣነው እንድሪስ መስሎን እሱን ልንወጋ ነበር» በለው መለሱላቸው። ካሣም «እንድሪስ ቢሆን የኔ ሰው አይደለምን?» ካሉዋቸው በኋላ እንዲጠበቁ አዘዙ። ለእንድሪስም «ቀንቶኛልና የምሥራች። አንተም መጥተህ እንገናኝ» ብለው ላኩበት።

እንድሪስ በዚያን ጊዜ የሠፈረው ከካሣ ሠፈር የአንድ ሰዓት መንገድ ያህል ከሚርቅ ሥፍራ ነበር። እንድሪስ እንደመጣም መጀመሪያ በአረብኛ አናግረውት ቀጥለው በማርኛ «ወንድሜ እንድሪስ ካንተ ጠላት እኔ ምርቱን አፈስሁ» ብለው ምርኮኞቹ መቶ ሰዎች መርጠው «ያውልህ ግዛቸው» ብለው ሰጡት። 210 ሰዎች ደግሞ አስቀርተው «እኔ ምርቱን እንዳፈስሁ አንተ ግርዱን እፈስ ብለው ሰጡት። እንድሪስም እነኚያን 120 ሰዎች በሙሉ በሰይፍ እያስመታ ፈጃቸው። የቀሩትን አምሳ ምርኮኞች ደግሞ ካሣ አስቀርበው «እናንተስ ብትሆኑ ከኔ ደጅ ደርሳችሁ እንዴት እንዲሁ ትሔዳላችሁ። ንሣ አንዳንድ ጆሮአችሁን እየቆረጥህ ስደዳቸው» ብለው አዘዙ። ጆሮአቸው እንዲቆረጥ ከተፈረደባቸው ሰዎች መሀል አንዱ ከመሞት በመዳኑ ተደስቶ «ከሞት እንዳን እንጂ እንኳንስ አንዱን ሁለቱንም ጆሮ ይቆረጥ» አለ። ካሣም ይህን ሲሰሙ «እንግዲያው እንደ ተናገረው ሁለት ሁለት ጆሮአቸውን እየቆረጥህ ስደዳቸው» አሉ ሁሉም ሁለት ሁለት ጆሮአቸው እየተቆረጠ ተለቀቀ።

በዚህ ጊዜ ካሣ የሚበላ እህል በማጣት ከፍተኛ ችግር ላይ ነበሩ። ወታደሮቻቸውም የሚበሉት እንጨት ፍሬና የዱር ማር እየፈለጉ ነበር። ይህን የተመለከተው ወዳጃቸው እንድሪስ 200 ያህል ግመል እህል አስጭኖ አመጣላቸው። ደለጉ ላይ ከአገዎች ጋር ባደረጉት ውጊያ ያለቀው ሠራዊት ሬሣ እያደር እየገማ አላስቀምጥ ስላለ ደለጉን ለቀ ሻሆ ሔደው ተቀመጡ።

አቶ እንግዳ ወርቅ የሚባሉ የታወቁ ታላቅ ሽፍታ ነበሩ። ካሣ ከእሳቸው ተወዳጅተው ልጃቸውን አገቡ። የአቶ እንግዳ ወርቅን ልጅ እንዳገቡም ወህኒ ወደሚባለው አምባ ሔደው አምባውን በጦር ወግተው ዘረፉት። የወህኒን መወጋትና መዘረፍ የገዢው የራስ አሊ እናት እቴጌ መነን ሲሰሙ ተናደዱ። ካሣን ከገባበት ገብቶ የሚይዝ ጦር ላኩ። ከእቴጌ መነን የተላከው ጦርም ካሣ ካሉበት ሲደርስ ካሣ ወታደራቸውን አሰልፈው ጠበቁት። ከእቴጌይቱ የተላከው ጦር የካሣን ሠራዊት ተሠልፎ ባየ ጊዜ ሁኔታውን አመዛዝኖ ሳይዋጋ ተመለሰ። እቴጌ መነን የካሣን መበርታት የሕዝቡን ማበር በሰሙ ጊዜ ከጦርነት ይልቅ በወዳጅነት መያዙ የሚጠቅም መሆኑን መዝነው ታረቁዋቸው። ቋራንም በምስለኔነት እንዲያስተዳድሩ ተሾሙ።

ካሣ በራስ አሊ ቤት ጥቂት ጊዜ እየታዩ ከቆዩ በኋላ እቴጌ መነን ዘንድ ሔደው ወደ ግዛቴ እንድሄድ ያሰናብቱኝ ብለው ጠየቁ። እቴጌ መነንም እሺ ቆይ አሰናብትሃለሁ ብለው በሌላ ቀን «ቋራ የደጃዝማች አገር ነው። የበላይ ሆኖ የሚያስተዳድር አንድ ባለነጋሪት ደጃዝማች ይዞ መሔድ አለበትና ንገሩት» ብለው ሰው ላኩባቸው። ካሣም እምቢ ቢሉ ወዲያው ተይዘው እንደሚታሠሩ ስለሚያውቁ መልዕክተኛው መልዕክቱን ሲነግራቸው «እሺ መልካም ነው» ብለው እጅ ነሱ። ወዲያውም ወደ ቤተ መንግሥት ሔደው ከእቴጌ መነን ዘንድ ቀርበው «የበላይ ሆኖ የሚመለከት ሹም ስላድረጉልኝ አመሰግናለሁ። በዚህም ተደስቻለሁ። ምክንያቱም አገሩ ክፉ ስለሆነ በጅ ብሎ አይገዛም። ለኔም ቢሆን ታዛቢ ሆኖ የሚያይልኝ በማግኘቴ እቴጌን ከልብ አመሰግናለሁ ብለው እጅ ነሱ። በማግስቱም ቀርበው «አዲስ ሹም ይገቤ ስሔድ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገው እንዲቆዩኝ ለሕዝቡ ሰው መላክ ይገባልና እንድልክ ይፈቀድልኝ» ብለው አመለከቱ። እቴጌም ፈቀዱላቸው።

ካሣ ፈቃዱን ካገኙ በኋላ ፈጣን አሽከር መርጠው ለቋራ ሕዝብ ሁለት ዓይነት መልዕክት ላኩ። አንደኛው ለሚያምኑዋቸው ሰዎች በምስጥር የሚነገር ሆኖ ሕዝቡ ከብትና ፍየሉን ወደማይገኝበት ቦታ እንዲያሸሹ። እህሉንም ከጉድጓድ እየከተተ ሰውም እንዲሸሽ እንዲያደርጉና «......እኔ የወሎን ሕዝብ ይገቤ መምጣቴ ነውና የአሞራ ከቢን ተራራ ስንዘልቅ ተመልክታችሁ ቤታችሁን እሳት ልቀቁበትና በየቦታው ቃጠሎው እንዲታይ ይሁን። ከቃጠሎውም ጋር ኡኡታ እንዲሰማ አድርጉ ብለህ ንገር» አሉት።


ሁለተኛው መልዕክት ደግሞ ሚስጥር ሳይሆን ሕዝብ በተሰበሰበት የሚነገር ነው ብለው «የእቴጌን ደጃዝማች ከብዙ ሠራዊት ጋር ይገቤ ልመጣ ነኝና እንጀራው እንደ ቅጠል ጠጁ እንደ ውሃ ሆኖ ይቆየኝ። ብዙ ፍሪዳም እንዲቀርብ ሰፊ ዳስም እንዲሠራ ይሁን። ይህ ሳይሆን ቢቀር በምን ጠፋን እንዳትሉኝ ብለህ ንገር» ብለው ላኩት።

ይህን መልዕክት ከላኩ በኋላ እቴጌ መነን ዘንድ ሔደው ከኔ ጋር የሚሔደው ለቋራ የተሾመው ሰው ማነው ብለው ጠየቁ። እቴጌም ደጃዝማች በለው ነው አሏቸው። ካሣም እጅ ነስተው ወጡ። እቴጌ መነንም ለደጃዝማች በለው ብዙ ጠመንጃ ሰጥተው እንዲሔዱ አደረጉዋቸው። ካሣም ሁሉን ነገር

በሆዳቸው ይዘው ለደጃዝማች በለው መንገድ መሪ ሆነው ይጓዙ ጀመር። ካሣ የደጃች በለውን ሠራዊት ለማድከም ቅርቡን መንገድ እየተው በሩቅ መንገድ እየመሩ ያጉዝዋቸው ጀመር። ከመንገዱ ርቀትም ሌላ አድካሚና ገደላ ገደል በሆነው መንገድ እየመሩ ወሰዱዋቸው። የደጃች በለው ሠራዊትም ጉዞው ስለደከመው በጉዞው ምክንያት እየተመረረ እየተበታተነ የትም ቀረ። ፈረስና በቅሎውም ገደል እየገባ አለቀ።

ደጃች በለው በመንገዱ መጥፎነትና ርቀት እየተመረሩ «ደህና የተሻለ መንገድ የለም ወይ?» እያሉ ሲጠይቁት ካሣ «ደርሰናል» እያሉ ያጉዙዋቸው ጀመር። በብዙ ድካምና ችግር ተጉዘው ቋራ ደረሱ። በቋራም ወታደሩ በያለበት እንዲሠፍር ታዘዘ። ወታደሩ መስፈር እንደ ጀመረ ሕዝቡ ቤቱን እያቃጠለ እሪ እያለ ይጮህ ጀመር። ይህን የሰሙት ካሣም ከደጃዝማች በለው ሠራዊት ጋር ሆነው እየተታኮሱ ከአገሬው መሐል ገብተው ሕዝቡ ወደ ቆላ ወደ አብ ተጋሆ እንዲሔድ ነግረው ተመለሱ። ደጃዝማች በለው ዘንድም ቀርበው «እዩልኝ ይሄን እርጉም አገር? ዘላለም እንዲሁ በጦርነት ነው የምኖረው። አመለኛ ስለሆነ ምንም ቢደረግለት እሺ ብሎ አይገዛም» አሏቸው። ሰላማዊ ለመምሰል የእራሳቸውን የእህል ጉድጓድ ከፍተው ለደጃች በለው ሠራዊት አደሉ።

የደጃች በለው ሹማምንትና መኳንንትም ካሣን «እዚህ የከፋ አገር እንዳመጡን ወደ ደህናው አገራችን ይመልሱን» አሏቸው። ካሣም «ግድ የለም አሁን የተበታተነውን አገር በግድ እየያዝሁ አመጣዋለሁ። አገሩም ደህና ይሆናል። አንድ ሳምንት ያህል ተቀምጣችሁ ተመልከቱ» አሏቸው። የደጃች በለው የወሎ ሠራዊትም ፈስመን አንከርምም ብለው እምቢ ስላሉ የጐንደር መመለስ ጉዞ ተጀመረ። የመልሱም ጉዞ ቢሆን ሰላምዊና ምቾት ያለው አልነበረም። ካሣ ግማሽ ወታደራቸውን ከፍለው የአመፀ ሕዝብ በማስመሰል በየዱሩ እያደፈጠ የደጃች በለውን የወሎን ሠራዊት በብዛት ፈጀው። ፈረስና በቅሎም እየማረከ ወሰደ። በእንዲህ ዓይነት የመከራ ጉዞ የቋራን ግዛት አልፈው ደንቢያ ሲደርሱ ካሣ ደጃች በለው ዘንድ ቀርበው «እንዳዩት አገሩ የዱር አውሬ ነው። ዘላለም ለምነንና አቆላምጠን ነው የምንኖረው። አሁንም ባላገሩ እሺ ቢለኝ በእርቅ እንዲገባ ለማድረግ ወደ ቋራ እመለሳለሁ። ከእርስዎ ጋርም ሆኜ የደረሰብኝ መከራ ሁሉ ለእቴጌ መእንን ይንገሩልኝ» ብለው ተሰናብተው ተመለሱ።



የንጉሥ ፋሲለደስ ቤተመንግሥት (ጐንደር)

ደጃች በለውም ጐንደር ገብተው የደረሰባቸውን መከራና ሥቃይ ሁሉ ለእቴጌ መነን ነገሩ። እቴጌም «ካሣ የት ቀረ?» ቢሉ «ደንቢያ ድረስ ሸኝቶኝ ወደ ቋራ ተመለሰ» ብለው ነገሩዋቸው። እቴጌም በካሣ ወደ ቋራ መመለስ ተቆጡ። ወዲያውኑም የካሣ እንደገና መሸፈት ተሰማ። ይህ ሲሆን ራስ አሊ ደብረ ታቦ ነበሩና የካሣን መሸፈት እንደሰሙ «እቴጌ በድለውሃል። እኔ እክስሃለሁና ግባ» ብለው የታወቁ ታላላቅ ሽማግሌዎችንና ቀሳውስትን ላኩባቸው። ሽማግሌዎቹ ሁለቱንም ወገኖች በመሀላ አስታረቋቸው። ራስ አሊም ለደጃች ካሣ ግዛታቸውን ቋራን መርቀው ሰጡዋቸው።

ካሣ የቋራ ግዛታቸውን ሰላምዊ ለማድረግ ሲያስቡ በወሰን ያለ ግንጃር (ሻንቅላ) በመተማ በኩል ወሰን እያሰፋ አገር ውስጥ እየገባ በመዝረፍ አስቸገረ። ካሣ ይህን ግንጃር ለመምታት ዘጠና የሚሆኑ ምርጥ አሽከሮቻቸውን ይዘው ወደ መተማ ዘመቱ። አገሩ ባንድ በኩል የወዳጃቸው የእንድሪስ ዘመዶች ያሉበት በመሆኑ ነገሩን በጦር ሳይሆን በሰላም ለመጨረስ አሰቡ። መተማ

እንደደረሱም ወታደሮቻቸውን ሲመክሩ «ግንጃር ብዙ ሆኖ ተሰልፎ ለማስፈራራት ይመጣባችኋል። አትፍሩ። አትንቀጥቀጡም። ዝብ በሉት» አሉ። ካሣ እንዳሉት ሁሉ ግንጃሩ በፈረስ እየሆነ ተሰልፎ መጣ። የካሣ ሠራዊትም እንደታዘዘው አጠገቡ እስቲደርስ ድረስ ዝም ብሎ ቆሞ ጠበቀው። ግራ የገባው የግንጃር ሠራዊትም ከፈረሱ እየወረደ በእግሩ ወደ ካሣ ሠራዊት ተጠጋ። ካሣም ከሠራዊታቸው መሀል ወጥተው በሰላም ከግንጃሮቹ ጋር ተገናኙ። ወደ መተማ ከተማም አብረው በሰላም ገቡ። ጥቂት ቀናት አብረው በመቆየት ጉዳያቸውን በሰላም ጨርሰው ሊመለሱ ሲሉ 12 የዝሆን ጥርስ 200 ብር 8 ባርያ ሁለት ስንና ብርት (የጅ ማስታጠቢያ) አልጋ ምንጣፍና ሌላም ዕቃ ግንጃሮቹ ለካሣ ሰጥተው በሰላም ተለያዩ። ካሣም በደስታ ተመልሰው ይህን ያገኙትን ዕቃ ለእቴጌ መነን በስጦታ ላኩላቸው። እቴጌ መነንም በሥጦታው ደስ አላቸው።

ካሣ በሽፍትነታቸው ዘመን በሱዳን ወሰን በኩል የሚያስቸግረውን በአረቦች የሚታዘዘውን ሠራዊት እየደጋገሙ በመምታት የተደጋገመ ድል አግኝተዋል። የካሣን ዝና በኢትዮጵያም ሆነ በሱዳን በኩል በጣም ከፍ ያደረገው ይሄው የተደጋገመው በሱዳን ወሰን በኩል ያስገኙት ድል ነው። እንዲህ አይነቱንም ጀግና በጦርነት ሳይሆን በወዳጅነት ለመያዝ አስበው እቴጌ መነን የልጃቸውን የራስ አሊን ልጅ ሊድሩላቸው ፈለጉ። «የአቶ እንግዳ ወርቅን ልጅ ትተህ የኔን ልጅ አግባ» ብለው ላኩባቸው። ካሣም በነገሩ ተደስተው በ1840 ዓ.ም የራስ አሊን ልጅ የእቴጌ መነንን የልጅ ልጅ ወይዘሮ ተዋበችን በሕግ አገቡ።



የአጤ ዮሐንስ 4ኛ ቤተመንግሥት (ትግራይ)

ካሣም ምንም እንኳን የመስፍኑ የራስ አሊና የአጤ ዮሐንስ ባለቤት የእቴጌ መነን አማች ቢሆኑም ሶስቱም ታላላቅ መሪዎች የካሳ ጋብቻ የእኩያ ጋብቻ ስላልነበረ ካሣን ይንቋቸው ነበር። ካሣ የወይዘሮ ተዋበችን ካገቡና ለመሪዎቹ ቤተኛ ከሆኑ በኋላ ብዙ ችግር ደረሰባቸው። ግዛታቸው እየተቀነሰ ፍርዳቸው እየተገለበጠ በሕዝብ ዘንድ ንቀት አመጣባቸው። በግዛታቸው ማነስ ምክንያት ገባሪውም እያነሰ በመሔዱ ካሣ ለአሽከሮቻቸው እንኳ የሚያበሉት በማጣት እጅግ ተቸገሩ። ሰዋቸውም ተራበ። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ የካሣን መዳከምና የሠራዊታቸውን መላላት ያወቁት ገዢዎቻቸው ካሣን እስከ ጭራሹ ለማስገደል ስለሚፈልጉ ተዋበችን ባገቡ በሁለተኛው ዓመት ካሣ ወደ ወሰን ሔደው እንዲዋጉ አዘዙዋቸው።

ካሣ ወደ ወሰን ሔደው እንዲዋጉ የታዘዙት ያለ ምክንያት አልነበረም። አረቦች በሱዳን በኩል እያለፉ በመደጋገም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እየገቡ ቤት በማቃጠል፥ በመዝረፍና በመግደል አስቸግረው ስለነበረ ነው። ይህንንም ኃይለኛ ጦር የካሣ ሠራዊት ያለረዳት ብቻውን ሔዶ እንዲጋጠም ታዘዘ። ካሣ አላንገራገሩም። ዘመቱ።


በዘመኑ ዘመናዊ መሣሪያ ከታጠቀው የግብጽ ጦር ጋር የካሣ ሠራዊት ወሰን ላይ ተጋጠመው። በጦር አወጋግና በጐራዴው አመታት ከፍተኛ ውጊያ ተካሔደ በኋላ ካሣ ድል አድርገው የግብጾችን ምሽግ አፈራርሰው በርከት ያለ የጦር መሣሪያ ማረኩ። ወሰን አልፈው ገብተውም የሸሸውን የግብፅ ጦር ራሃድ ከተባለ ወንዝ ላይ ደርሰውበት ያመለጠው ሲያመልጥ የተገኘውን ፈጁት።

በዚህ ጦርነት ላይ ካሣ ቆስለው ነበር። ድሉን እንዳገኙ ወዲያውኑ ገስግሰው መጥተው ለበላይ ገዢዎቻቸው እንደ ዕቃ ለተቀመጡት ለአጤ ዮሐንስም ሆነ ወይም ለመስፍኑ ለራስ አሊ ዝቅም ቢል ለእቴጌ መነን ግዳይ ጥለው አልፎከሩም። ምክንያቱም ቁስላቸው የበረታ ስለነበረ ጨንገር ከተባለው መንደር ካንድ የባህል መድሃኒት አዋቂ ቤት ተኝተው ይታከሙ ነበር። መድኃኒተኛውም ካሣን በሚገባ ሲያክም ከቆየ በኋላ «ቁስሉ በቶሎ እንዲድን በሚገባ መቀለብ አለብዎ» ስላላቸው ድህነት ያጠቃቸው ካሣ ለንጉሱ ለአጤ ዮሐንስ ለመስፍኑ ለራስ አሊ ለእቴጌይቱ እቴጌ መነን ማገገሚያ ስንቅ እንዲልኩላቸው መልዕክተኛ ላኩ።

ንጉሱ አጤ ዮሐንስ ይህን መልዕክት እንደሰሙ አንድ ሰንጋ ብዙ እንጀራና ጠጅ ላኩ። እቴጌ መነን ግን አንድ ብልት ሥጋ፤ 30 እንጀራና አንድ ገንቦ ጠጅ ይላክለት ብለው አዘዙ። ይህን ትእዛዝ የሰሙትን ሰዎችም «ምነው እሜቴ። የካሣን ጠባይ ሁላችንም እናውቀዋለን። ኩሩ ነው። ፍሪዳ አላጣን ምናለ ሲሆን አንድ ፍሪዳ ያለዚያ አንድ የበግ ሙክት ቢላክላቸው አይሻልምን» ብለው አማከሩዋቸው። እቴጌይቱም «ለፍየል ጠባቂ ቆለኛ አንድ ብልት ሥጋ አንሶት ነወይ» አሉ።

ይህን የእቴጌይቱን አነጋገር አንድ ወዳጃቸው ለካሣ ነገራቸው ካሣ ግን ያልሰሙ መስለው ከሁለቱም የተላከውን ሥጦታ አመስግነው ተቀበሉ። ከንጉሱ ከአጤ ዮሐንስ የተላከው ሰንጋ ታርዶ እንዲበላ ሲያዙ እቴጌይቱ የላኩት አንድ ብልት ሥጋ ግን በአገልግል እንዲቀመጥ አደረጉ። ወይዘሮ ተዋበችም ካሣ ከተገኙበት ገብተው «ሲሆን በቤተ መንግሥቱ አዳራሽ ፍሪዳው ታርዶ ማቶቱ በጠጅ ርሶ፥ መጥኑ ተግበስብሶ በተቀበሉን ነበር። በቀረስ ድልቡ ፍሪዳ ቀሚስ ለብሶ ሥጋው በመልከኛ ጠጁ በገንቦኛ በተላከልን ነበር። እንዴት እንደምን ብንናቅ ነው አንድ ብልት ሥጋ የተላከልን? ጀግና ሰው እወዳለሁ። ፈሪ ወንድን ግን እንቃለሁ። ከፈሪ ሰው ጋርም አብሬ መኖር

አልፈቅድም» አሏቸው። ይህን የሚስታቸን ንግግር የሰሙት ካሣም ጥቅምት 5 ቀን 1842 ዓ.ም ሸፈቱ።



## አጤ ዮሐንስ 4ኛ በዙፋን ላይ

የካሣ መሸፈት እንደተሰማ በቤተ መንግሥቱ ታላቅ ድንጋጤ ፈጠረ። ወዲያውኑም እቴጌ መነን ካሣ በሽፍትነት ሳይደራጁና ኃይል ሳያበጁ ቀድመው ለማስመታት አሰቡ። የተደራጀ ጦራቸውን አዘው ካሣ በሸፈቱ በሳምንቱ ማለት ጥቅምት 12 ቀን ካሣን የሚወጋ ጦር ተላከ። የተላከውን ጦር እንደ አመጣጡ ለመቀበል የካሣ ሠራዊት ጫቆ በተባለ ሥፍራ መሽጐ ቆየ። የዚያን ጊዜ ካሣ የነበራቸው ሠራዊት 22 ጠመንጃ ያዥና 400 ጦርና ጋሻ የያዙ ሰዎች ብቻ ነበሩ። ጦሩ እንደመጣባቸው ያወቁት ካሣ፤ ሠራዊታቸውን ሰብስበው «......ጦርነት የምገጥምበት ጊዜው ተቃርቧል። ቢሆንም እኔ የመለከትና የእምቢልታ ድምጥ ሳላሰማህ እንዳትንቀሳቀስ። የመለከት ድምጥ በሰማህ ጊዜ ግን ወደ ኋላ ብትል ለራስህ እወቅ ብለው በአዋጅ ካስለፈፉ በኋላ ከድንኳቸው ገብተው ተኙ። ካሣ ጥቂት እንዳሸለባቸው የጠላት ጦር ፊታውራሪው

(ቀዳሚው) ሲመጣ ባለቤታቸው ወይዘሮ ተዋበች አይተው ካሣ ዘንድ ገብተው ቀሰቀሱዋቸውና «ጦሩ መጥቶልሃል። ተነስ ታጠቅ» አሏቸው። ከዚህም በኋላ የካሣ የፈረስ ስም ታጠቅ ተባለ።

ካሣም ታጥቀው ወጡና የጠላት ሠራዊት ከእሳቸው ሠራዊት አቅራቢያ እስቲጠጋ ድረስ በፀጥታ ቆመው ቆዩ። ከተጠጋጉ በኋላ መለከት ንፉ ብለው አዘዙና መለከቱ መነፋት ሲጀምር «በለው እንግዲህ» ብለው አዘዙ። ከዚህ በኋላ የሁለቱም ሠራዊት ተደበላልቆ ጦርነቱ በጨበጣ ውጊያ ተጀመረ። የካሣ ሠራዊትም በርትቶ በመዋጋቱና የእቴጌንም ሠራዊት ጥይት አላስተኩስ በማለቱ ያልጠበቀው የጦር መላ ስላጋጠመው የእቴጌ ሠራዊት ድል ሆነ። ድሉ ያለማወላወል የካሣ ቢሆንም ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ሞተ። ብዙ መኳንንትና ተራ ሰዎችም በካሣ እጅ ተማረኩ። አንድ መቶ ያህል ጠመንጃም በመማረኩ ደክሞና ወድቆ የነበረው የካሣ ሠራዊት እንደገና ተደራጀ።

ጫቆ የተዋጋው የመንን ሠራዊት ወደ ካሣ ከመዝመቱ በፊት ከእቴጌ መኳንንቶች አንዱ ቀኛዝማች ወንድይራድ የሚባለው ጀግና ለእቴጌ ሲፎክር «ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ አሁን እንደ ሙጭልጭላ አንገቱን አንቄ አመጣልሻለሁ። አይዞሽ» ብሎ ፎክሮ ነበር። ይህን ፉከራውን ካሣ ሰምተዋል። ጫቆ ላይ በተደረገው ውጊያ ድል ካገኙ በኋላ ወንድይራድ ተማርኮ በመያዙ ካሣ ደስ አላቸው። ሠራዊታቸውን ሰብስበውም «ኮሶ የሚመገብ እንግዳ መጥቶብኛልና ኮሶ ሰብስበህ አምጣልኝ» ብለው አዘዙ። ኮሶው መጥቶ ተደቁሶ ከተዘጋጀ በኋላ ካሣ የተበጠበውን ኮሶ አስቀርበው ጦራቸውን ከጭናቸው ላይ አድርገው ሕዝቡን ሰብስበው ቀኛማች ወንድይራድን አስጠሩ። ወንድይራድ እንደቀረቡም «እናቴ ከገበያ ሳይሸትላት የቀረ ኮሶ አለ። አሁን እህል ታጥቷልና ይሄን ኮሶ ተመገብ» ብለው በትልቅ ጥዋ ሙሉ አስጡዋቸው። ቀኛዝማች ወንድይራድም ግማሹን ያህል እንደጠጡ አስታወካቸው። ከዚህ በኋላ ኮሶ እያጠጣህ እሥርልኝ ብለው ሶስት መኳንንት ካሳሰሩ በኋላ ሌላውን ምርኮኛ በምሕረት ለቀቁት።

የተላከው ጦራቸው ድል ሆኖ መበታተኑን እቴጌ መነን እንደሰሙ እንደገና ሕዳር 12 ቀን ከፍተኛ ጦር ሰደዱ። በአሁኑ ጊዜ የካሣ ጦር ቀደም ብሎ ባገኘው

ምርኮ ተጠናክሮ ነበርና ከእቴጌ መነን የተላከውን ጦር ሰቀላ ወርካ ከተባለው ቦታ ገጥሞ በቀላሉ ድል አድርጐ ብትንትኑን አወጣው።

ይህንን የካሣን መጠንከር ያወቁት እቴጌ መነን ልጃቸውን እራስ አሊን ወገራ ላይ ትተው እሳቸው ራሳቸው የጦር መሪ ሆነው ወደ ካሣ ዘመኑ። እቴጌይቱ ልጃቸውን ራስ አሊን ወገራ ላይ የተውበት ምክንያት የሰሜኑ ገዥ ደጃች ውቤ ጐንደርን ይዘው ሊነግሡ ነው እየተባለ ይወራ ነበርና ሁለቱም ከወጡ ውቤ ጐንደር ይገባሉ በማለት ራስ አሊ ጐንደርን ለመጠበቅ ወገራ ላይ ቀሩ። እቴጌ መነንም 20 የሚሆነውን ሠራዊታቸውን እየመሩ በሰኔ ወር ጉዞ ጀመሩ።

በጉዞውም ላይ እንዳሉ እቴጌይቱ «ይህ ቆለኛ ወዴት አባቱ ይገባ ይሆን» ብለው ተናገሩ። የካሣ ጦር ካለበት ሎሃ ከተባለው ቦታ ሲደርሱም የካሣ ሰራዊት ለጦር ተሰልፎ ቆያቸው። እቴጌይቱም የካሣን ሠራዊት ተሰልፎ ሲያዩ «አያፍርም እኮ ይሄ ቆለኛ ከኔ ጋር ሊዋጋ ተሰልፏል» አሉ። ይህን ሁሉ ካሣ ሰምተዋል። ወዲያውም ጦርነቱ ተጀመረ። የእቴጌ መነን ሠራዊትም የካሣን ሠራዊት ምስቅልቅሉን አውጥቶ በጦር ገረፈው። በካሣ አበረታችነት ሠራዊታቸው እንደገና በርትቶ በሚዋጋበት ጊዜ ከጦሩ ጋር ሆነው ያዋጉ የነበሩት እቴጌ መነን በጦር ጭናቸውን ተወግተው ወደቁ። በዚህ ጊዜ የካሣ ሠራዊት የቆሰሉትን እቴጌን አንስቶ ወደ ካሣ ሲወስድ ሌላው የካሣ ሠራዊት ደግሞ በጦሩ መሀል እየዞረ የእቴጌይቱን መማረክ እየለፈፈ ይነግር ጀመር። የእቴጌ ሠራዊት ድል ሆኖ ካሣ ድል አደረጉ። ካሣ ቁስለኛዋንና ምርኮኛይቱን እቴጌን በእስረኝነት ወደ ቋራ ሰደዱዋቸው። በዚያም የተሳደቡትን ስድብ ብድር ለመመለስ ባቄላ ያስፈጩዋቸው ነበር ይባላል።

የእናታቸውን መማረክ ራስ አሊ እንደሰሙ ደነገጡ። ያላቸውን ሰራዊት ይዘው ካሣን ወግተው እናታቸውን ለማስለቀቅ ተዘጋጁ። በመሀሉ ግን ጦር ከመዝመቱ በፊት ይጠየቅ ስለ ተባለ ራስ አሊ «እናቴን ፈትተህ ቶሎ ላክልኝ» ብለው ላኩባቸው። ካሣም ከጐጃም አድባራት ተውጣጥተው የተላኩትን 30 ቀሳውስት በሚገባ ተቀብለው መልዕክቱን ከሰሙ በኋላ «የደጃች ክንፉ ግዛት የነበረውን ሁሉ ይልቀቁልኝና እኔም እናትዎን እለቃለሁ» ብለው መልስ ላኩ።

ራስ አሊ ይህን ቀሳውስቱ ያመጡላቸውን መልስ እንደሰሙ ካሣ በጠየቁት እርቅ አልስማማም ብለው እምቢ አሉ። ከካሣ ጋር ከመታረቅ ይልቅ ከሌላው ጠላታቸ ከደጃች ውቤ ጋር መታረቅና ጦርን ባንድ አቅጣጫ መምራት የተሻለ መሆኑን ያወቁት ራስ አሊ ከደጃች ውቤ ጋር ታረቁ። ለደጃች ውቤ ተሰልፎ የነበረውን ጦርም አቅጣጫውን አስለውጠው ወደ ካሣ አዞሩት። ይህን የአሊን ጦር ማስከተት የሰሙት እስረኛይቱ እቴጌ መነን «ከዚህ መጥፎ ቦታ በሰላም ካላስወጣኸኝ በጦርነት ልታገኘኝ አትችልም» ብለው ለልጃቸው ላኩባቸው።

ራስ አሊም በእናታቸው ምክር ተስማምተው ካሣ በጠየቁት የእርቅ ድርድር መሠረት ፈፀሙ። ካሣም ደጃዝማች ተብለው የሙሉ ደምቢያና ቋራ፤ ከፍርቃ በር እስከ ዳሞት በሰሜንም እስከ አርማጨሆ ድረስ ገዢ ሆኑ። የራስ አሊንም እናት እቴጌ መነንም ከእሥራት ፈትተው ላኩዋቸው።

ካሣ ይህን ጦርነት ከመጀመራቸው በፊት ራሳቸውን ለጦርነት በሚያዘጋጁበት ጊዜ ሴትና ጓዝ ለእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ አስጠቂ መሆኑን ስላወቁ ሚስታቸው ወይዘሮ ተዋበችን ከወዳጅ ዘመድ ቤት ለማስቀመጥ አሰቡ። ለዚህ አደራ ማስቀመጥ ጉዳይ ከሁሉም የተሻለ ሆኖ ያገኙት ታማኝ ወዳጃቸውን አይከል ኮልባን ነው። አይከል ኮልባን አስጠርተው «ወዳጄ ሆይ ወደ ፊት ኃይለኛ ነገር እንደሚገጥመን አውቃለሁ። የጀመርኩትንም ከመጨረሻው ለማድረስ በርትቼ መዋጋት አለብኝ። አሁን የአደራ ዕቃ እንድታስቀምጥልኝ እሰጥሃለሁ። ይህንንም በምድር የሰጠሁህን በሰማይ ትሰጠኛለህ ከዛሬ ጀምሮ ይሄው ልጅህ ናት» ብለው እጅ ለጅ አጨባብጠው ተዋበችን በአደራነት ሰጧቸው።

ከአይከል ኮልባ ሰው የማያውቅቸው ሁለት ዋሻዎች መቀነት ማርያም ከተባለው ሥፍራ መኖራቸውን ያውቃሉ። በነዚያም ዋሻዎች በአንደኛው ተዋበችን አስቀምጠው በሁለተኛው እሳችው ለመቀመጥ ወሰኑ። ይህን ከማድረጋቸው በፊት ልጃቸውን ዘውዴ የሚባለውን ጠርተው ጉዳዩን ሳይገልጡ ምግባቸውን በየቀኑ በገመድ እንዲያቀብላቸው አዘው ተዋበችን ይዘው ከዋሻዎቹ ገቡ። ልጃቸው ዘውዴ ምንም የሚያውቀው ነገር ሳይኖር በታዘዘው መሠረት ብቻ በገመድ በየቀኑ ምግብ ሲያቀብል ኖረ።

ካሣ በጦርነት እቴጌ መነን ድል አድርገው ለሚቀጥለው በሚዘጋጁበት ጊዜ ሚስጥር የሚያውቅ ወታደራቸውን ጠርተው የተዋበች ጤንነት እንዴት

እንደሆነ ጠየቁት። ወታደሩም «እሳቸው ምን አለባቸው። የአይከል ኮልባን ልጅ ዘውዴ አይከልን ወዳጅነት ይዘው ይሽሞነሞናሉ ብሎ ነገራቸው። ካሣ እንኳን ለራሳቸው ለሌላውም የሚቀኑ ሰው ነበሩና ተናደው አይከል ኮልባን የሰጠሁህን ዕቃ ይዘህ አለሁበት ቦታ ድረስ እንድትመጣ ብለው ላኩባቸው።

አይከል ኮልባ ወይዘሮ ተዋበችን ይዘው ወደ ካሣ ለመሔድ ጉዞ ጀመሩ። በዚህን ጊዜ ዘውዴ ከሠፈር አልነበረምና ከሔደበት ሲመለስ «አባትህ ወደ ካሣ ተጠርተው ሔዱ» ብለው ሰዎቹ ነገሩት። ዘውዴም አባቱን ተከትሎ ለመሔድ ወዲያውኑ በግስጋሴ ጉዞ ጀምሮ ከመንገድ ደረሰባቸውና አብረው ወደ ካሣ ሔዱ። ከካሣ ዘንድ ሲደርሱም ካሣ ግብር አገቡላቸው።

ግብር የተዘጋጀው ለሰላም ለፍቅር አልነበረም። ካሣ በግብሩ ጊዜ ጣምራ (ሁለት) ጦር በጭናቸው ላይ አድርገው ተቀምጠዋል። አስተያየታቸውና አነጋገራቸው ሁሉ የቁጣ ነው። ሁሉም በፍርሃት ተመስጦ በሚመገብበት ጊዜ ካሣ በድንገት ወደ ወይዘሮ ተዋበች ዞር ብለው «ተነሺና አንድ ዋንጫ ጠጅ ለዘውዴ አይከል ስጪው» በልው አዘዙ። ወይዘሮ ተዋበች ከቴዎድሮስ ቁጣ ለመዳን ለዘውዴ የሚሰጡትን አንድ ዋንጫ ጠጅ አስቀድተው ይዘው ከመቀመጫቸው ተነሱ። ተዋበች ፈርተው ይነሱ እንጂ ዘውዴ የቱ እንደሆነና የትስ እንደተቀመጠ አያውቁም ነበርና ከመሀል ቆመው ዓይናችወ ይንከራተት ጀመር። ካሣ ግን ጦራቸውን እየነቅነቁ የተዋበችን እርምጃ ይከታተላሉ።

ግብር የገባው ሰው ሁሉ ፈርቶና ደንግጦ እርጭ ብሎ ሲያይና ሲያዳምጥ ተዋበች የባሰ ተደናግጠው ዙሪያውን እየዞሩ ዘውዴ የተባለው የቱ እንደሆነ ይፈልጉ ጀመር። ዘውዴ አይከል ግን የተቀመጠው ከዚያው ከአጠገባቸው ነበር። በሁኔታው ግራ የገባቸው ካሣም የተዋበችን ሁኔታ አይተው «ዘውዴ አይከልን አታውቂውም እንዴ?» ብለው ጠየቁዋቸው። ተዋበችም «እኔ አላውቀውም» ብለው መለሱ። ካሣም ዘውዴ አይከል ማለት እሱ አጠገብሽ ያለው ነው» በለው አሳዩዋቸውና የተነገራቸው ውሸት መሆኑን አውቁ። ወዲያውም ያን የነገራቸውን ወታደር በዓይናቸው ከግብሩ መሀል ቢፈልጉ አጡት። ወታደሩ ቀደም ብሎ ተሾልኮ ጠፍቶ ነበር። ካሣ ጠቅላላ ታሪኩን ከሰሙ በኋላ ለዘውዴ አይከል የአዛዥነት ማዕረግ ሰጥተው ከርብ በላይ ያለው

የበጌምድር ገዢ አደረጉት። በሕመም በሞተ ጊዜም ለተዝካሩ ማውጫ ብለው በግዛታቸው ውስጥ ካሉ ገበያዎች ሁሉ ያንድ ቀን ቀረጥ እንዲሰጥ አዘዙ።

እዚህ ላይ የቴዎድሮስ የምርመራ ዘዴ የሚደነቅ ወይም የሚመሰገን አይደለምን። ሚስታቸውን ወይዘሮ ተዋበችን አደራ የሰጡት ለአይከል ኮልባ ነው። ዘውዱ ደግሞ አባቱ ቤት የሚኖር የአይከል ኮልባ ልጅ ነው። ዘውዴ በአባቱ ዘንድ ታማኝ ሆኖ አባቱ ሚስጥሩን ሊነግሩት ይችላሉ። በታማኝነቱም ወይዘሮ ተዋበችን ሊያስጠብቁት ይችላሉ። አልተደረገም እንጂ ከአይከል ኮልባ ለልጃቸው ሚስጥሩን ገልጠው ቢሆን ኖሮ የንፁሆቹ የወይዘሮ ተዋበችና የዘውዴ አይከል ደም በከንቱ ሊፈስ ነበር። ቴዎድሮስ ሁለት ጦር ይዘው የተቀመጡትም አንዱ ለተዋበች ሌላው ደግሞ ለዘውዴ አይከል መሆኑ ነው። ተዋበች በመንገድ ላይ እንኳን ዘውዴ አይከልን ተዋውቀውት ቢሆን ያን ዋንጫ ጠጅ ለዘውዴ ቢሰጡ ኖሮ የንፁሃኖቹ ሕይወት በከንቱ ሊያፍል ነበር።

ካሣ ከራስ አሊ ጋር ተራርቀው ደጃዝማች ከተባሉ በኋላ አዲሱን ግዛታቸውን ማስተዳደር ጀመሩ። ከግዛታቸውም ሌባና ሽፍታን አጥፍተው ፍፁም ሰላማዊ ግዛት ለማድረግ ተነሱ። በደምቢያ ሽፍተውባቸው የነበሩትን ተቀዋሚዎቻቸውን ሁሉ እያስያዙ እጅና እግራቸውን አስቆረጡ። በግዛታቸው ላይ የበላይ ሳይኖርባቸው ፈላጭና ቆራጭ ሆኑ። ይህን አድራጎታቸውን የሰሙት ራስ አሊ እንድትመጣ ብለው ላኩባቸው። ደጃች ካሣም «አሁን ጊዜው ክረምት ስለሆነ ለመምጣት አያመችኝም» የሚል መልስ ላኩ። ክረምቱ እንደወጣም ራስ እንደ ገና እንድትመጣ ብለው ላኩባቸው። ደጃች ካሣ ከራስ አሊ ጋር የነበረው እርቅ በሁለቱም በኩል ካንገት በላይ ለጊዜው የተደረገ መሆኑን ያውቃሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን እቴጌ መነንን ማርከው በነበረ ጊዜ በእትጌይቱ ላይ የሠሩትን በደል ያውቃሉና ለራስ አሊ «አልመጣም» ብለው ላኩባቸው።

ከዚህ በኋላ ራስ አሊ ደጃች ካሣን ከሹመታቸው ሽረው ግዛታቸውን ለጐጃም ገዥ ለደጃች ጐሹ መስጠታቸውን በሕዳር ወር 1845 ዓ.ም በአዋጅ አናገሩ። ወዲያውም ራስ አሊና ደጃዝማች ጐሹ በአንድነት ሆነው ደጃች ካሣን ሊወጉ ዘመቱ። ካሣም እነዚህን ሁለቱን ታላላቅ መኳንንት በአንድነት ለመውጋት እንደማይችሉ ራሳቸውን ገምተው ደንቢያን ለቀው ወደ ትውልድ

ቦታቸው ወደ ቋራ ሔዱ። ራስ አሊም የደጃች ካሣን መሸሽ እንዳዩ ደንቢያ ላይ የደጃች ጐሹን ገዢነት አውጀውና አደላድለው ተመለሱ።

ደጃዝማች ጐሹም በነበራቸው የጐጃም ግዛት ላይ ደንቢያ ላይ በመጨመሩ በጣም ተደሰቱ። ከደንቢያም ሆነው ጦራቸውን በየግዛቱ ያደላድሉ ጀመር። ራስ አሊ ርቀው ሲሔዱላቸው ደጃች ካሣ ከተደበቁበት ወጥተው ወደ ጉርአምባ መጡ። ይህን የካሣን መነቃነቅ የሰሙት ደጃች ጐሹም ጦራቸውን ሰበሰቡ። ጣፋጭ የሚባል የደጃዝማች ጐሹ አዝማሪም ከተሰበሰበው ሠራዊት መሐል ገብቶ የደጃዝማች ጐሹ አዝማሪም ከተሰበሰበው ሠራዊት መሐል ገብሮ

አያችሁትን የኛን እብድ፥

አምስት ጋሞች ሆኖ ጐር አምባ ሲወርድ።

ያንጓብባል እንጂ ሙች ይዋጋል ካሣ፥

ወርደህ ጥመድበት በሸንብራው ማሳ።

ወዶ ወዶ

በሴቶቹ በነጉንጭት ለምዶ እያለ ተሳደበ።

የደጃች ካሣና የደጃች ጐሹ ጦር ሕዳር 19 ቀን ጉርአምባ ላይ በጦርነት ተጋጠሙ። ሠራዊቱ እንደተጋጠመ የደጃዝማች ጐሹ ሠራዊት አጠቃ። የደጃዝማች ካሣ ሠራዊትም መሸሽ ሲጀምር ካሣ ከጥቂት ወታደሮች ጋር ሆነው ከጦሩ መሀል ገብተው ይዋጉ ጀመር። ደጃዝማች ጐሹም በፈረስ ሆነው ከሠራዊታቸው ፊት ቀድመው ሲያዋጉ በድንገት በጥይት ተመትተው ወደቁ። ድሉም ባለማወላወል የደጃዝማች ካሣ ሆነ። ደጃዝማች ካሣም የደጃዝማች ጐሹን ሬሳ አስነስተው በአሽከርነት አድረውላቸው የነበረ ጊዜ የሠሩላቸውን ውለታ በማሰብ በክብር አስቀብሩዋቸው።

በዚህ ጦርነት ካሣ ብዙ ሀብትና ምርኮ አገኙ። ከተማረኩትም ሰዎች መሀል ጣፋጭ የሚባለው አዝማሪ ተፈልጐ እንዲመጣላቸው አድርገው «እንዴት ብለህ ነው የሰደድከኝ?» ብለው ጠየቁት። እሱም ቢጨንቀው በቀልድ እንዲያምሩት ፈልጐ

«አወይ የእግዜር ቁጣ፥ አወይ ያምላክ ቁጣ፥

አፍ ወዳጁን ያማል ሥራ ሲያጣ፣

ካሣም በፈረደው ፍርድ በሽመል አስደብድበው አስገደሉት።

ደጃዝማች ካሣ ተቀምጠው ግዳይ እየጣለ የሚፎክርላቸውን ሲሰሙና ምርኮ ሲቀበሉ ባላምባራስ ገልሞ የሚባሉት ጀግና አሽከራቸው ቆስለው መጡ። ባላምባራስ ገልሞ በጦር የተወጉት ከጉንጫቸው ላይ ነበር። ጦሩም ባንደኛው ጉንጫቸው በኩል ገብቶ በሌላው ጉንጫቸው የወጣ ስለነበረ ባላምባራስ ገልሞ የጦሩን ዘንግ በጥርሳቸው ነክሰው በፈረስ እየጋለቡ መጡ። ደጃች ካሣም ይህን ሲያዩ ከመቀመጫቸው ተነስተው ባለህበት ቁም ወደ ገልሞ ሔዱ። ከዚያም ከፈረሰ አውርደው ደማቸውን ጠርገው ጦሩ ተሰብሮ ጉንጫቸው እየተቀደደ ጅንፎው ወጣላቸው። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ምን ዓይነት ጀግኖች እንደነበሩ ያሳያል።

ባላምባራስ ገልሞ ከደጃች ጐሹ ጋር የሚደረገው ጦርነት ተሟሙቆ የጐሹ ሠራዊት እያጠቃ ለድል በተቃረበበት ጊዜ ሸሽተዋል ተብሎ ተወርቶባቸው ነበርና አንዲት ዘፋኝ ከደጃች ካሣ ፊት ቀርባ ስታጫውት «አይሸሽም ያልከው ገልሞ እንኳ ሸሸ የደንቢያን ግራር እያበላሸ»

ብላ ገጠመች። ደጃች ካሣም ይህን ገልሞን የሚያሰድበውንና ፈሪ የሚያደርገውን ግጥም እንደ ሰሙ። «አብለሻል እንጂ እውነቱን አላልሽም፥ ብዙበት እንጂ ገልሞስ አይሸሽም»

ብለው መለሱ።

ይህ ጦርነት በተደረገ ጊዜ ራስ አሊ ጐጃም ነበሩ። የጐሹ ሠራዊት ድል በመሆኑና ጐሹም በመሞታቸው አዘኑ። ደጃች ካሣም ይህን ድል በማግኘታቸው ቢደሰቱም በድሉ ሳይኩራሩና አሊንም ሳይንቁ ካህናትን ሰብስበው ከራስ አሊ አስታርቁኝ ብለው ወደ ራስ አሊ ላኩ። ቀሳውስቱም እንደተላኩት ሔደው ራስ አሊን «ይታረቁልን» ብለው ቢጠይቁ እምቢ አሉ። የአሊን እንቢታ የሰሙት ካሣ የራስ አሊን ሰዎች እየሻሩ በነሱ ቦታ የራሳቸውን ሰዎች ይሾሙ ጀመር።

ራስ አሊ የእርቁን ጉዳይ እምቢ ብለው ካህናቶቹን ከመለሱ በሃኡአላ አዲስና ያልተነካ ጦር ያደራጁ ጀመር። ለዚህም ለሚቀጥለው ውጊያ ያላስታው ደጃዝማች ብሩ አሊጋዝ፥ ደጃዝማች በለው ደጃዝማች ውቤ ደጃዝማች ያዘው እነኚህ አራት ደጃዝማቾች ተመረጡ። እነዚህም ጦራቸውን አሰልፈው በሁዳዴ ጦም የካቲት 8 ቀን ደጃዝማች ካሣን ለመውጋት ሔዱ። ለዚህም ጦርም ከሰሜን ከደጃዝማች ውቤ ጦር በሶስት አምበል የሚመራ ሠራዊት እንዲጨመርላቸው ተደርጎ ሁሉም ጉዞውን ወደ ደንቢያ አመራ።

ለዚህ ለሚዘምተው ጦር የካሣ ሠራዊት ተወዳዳሪ እንደማይሆን የታወቀ ነው። ሆኖም ካሣ ከ800 እስከ አንድ ሺ የሚገመት ጠመንጃ የያዘ ጦር ነበራቸው። ካሣ ያላቸውን ጦር አዘጋጅተው ብቸኝ ከተባለው ሥፍራ ሲጠባበቁ ሚያዝያ 5 ቀን ገጣሚያቸው ጦር ደረሰና ብርቱ ጦርነት ተደረገ። በሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ካለቀ በኋላ ደጃዝማች ካሣ ድል አደረጉ። የተላኩት መኳንንትም በሙሉ አልቀው ካሣ ምርኮ አገኙ።

ለዚህም ውጊያ ከትግራይ የመጣው የደጃች ውቤ ወታደር ድል ሆኖ አገሩ ሲገባ

«ራስ አሊ ለቐቑ በለሳ

ፍሩይ ሰብአይ እንከብ ተወልደ ካሣ።

ደጅያት ውበውን ልቀቁ የፀገደ

ፍሩይ ስብአይ ካሣ እንካብ ተወልደ»

እያለ ዘፈነ።

ደጃዝማች ካሣ ይህን ድል ካገኙ በኋላ ገስግሰው ሔደው የራስ አሊን ከተማ ደብረ ታቦርን አቃጠሉት። የሠራዊታቸውን ድል መሆንና የከተማቸውን መቃጠል ተደራርቦ የሰሙት ራስ አሊ አሁን ፍርሃት አደረባቸው። ከእንግዲህ ወዲያም ካሣ በጦር ኃይል እንደ ማይቻሉ ተገነዘቡ። ስለዚህ የሚቻለው መንገድ እርርቅ በመሆኑ ከጐጃም አድራባራት 30 ካህናትን አውጣጥተው «እንታረቅ። ከአባይ ወዲያ ላንተ ይሁን። ወዲህ ለኔ ይሁንና እንታረቅ አባትና ልጅ እንሁን» ብለው ላኩባቸው።

እነኚህ አስታራቂ ካህናት ደብረ ታቦር በደረሱ ጊዜ ደጃዝማች ካሣ ሥራ ላይ ነበሩ። በበጌምድር ያሉትን ብረት ሠራተኞች ሰብስበው አንድ ሺ ማረሻ አስቀርበው አረር ያስቆርጡ ነበር። የድሮው ጠመንጃ ባሩድና ብረት ባንድነት በጨርቅ እየጠቀለለ ይጐርስና በሚተኮስበት ጊዜ የባሩዱ የማስፈንጠር ኃይል አረር የተባለችው ብረት አስፈንጥሮ ስለሚወረውራት ለታለመበት ግብ አደጋ ታደርጋለች። ይህንንም አተኳኮስ እንዴት እንደሚሠራና እንደሚተስኮስ የጥንቱን ጠመንጃ በውርስ ያገኙ ባላገሮች አሳይተውኛል። ይቺን ተስፈንጣሪቷን አረር ነው ካሣ ከማረሻ በየትንንሹ እያስቆረጡ ያሠሩ የነበረው።

አማላጅነት የተላላኩትን ቀሳውስትን ካሣ የተቀበሉዋቸው ከዚያው አረር ከሚያሰሩበት ቦታ ሆነው ነው። አማላጆቹም ከራስ አሊ የተላኩኩትን መልዕክት ነገሩዋቸው። ካሣም መልዕክቱን በሙሉ ካዳመጡ በኋላ «ከእስላም ጋር አገር አልከዳም (አልካፈልም)። እችላለሁ ስትል የአይሻልን ሜዳ የቀበሮውን ጉድጓድ ደልድለህ ሳምረህ ቆየኝ። አልችልም ስትል ቅዱስ ጊዮርጊስን መስጊድ አታድርገው። ጀበናህንና ብረት ምጣህድን፥ እርኮትህን ይዘህ ሰማይ ግንባርህን እስቲመታህ ሽሽ። አትቆየኝ በሉት» አሏቸው። ወዲያውንም ከተናገሩት ቃል መንገር ፈርተው እንዳይቀንሱ ቄስ አስመጥተው አስገዘቷቸው።

ቀሳውስቱም ከራስ አሊ ዘንድ ተመልሰው በቆይታ (በሚስጥር) ያመጡትን መልስ ነገሩዋቸው። ራስ አሊም በመልሱ ደነገጡ። ዘመዶቻቸውን ወረሄመኖችን ሰብስበው «እንሽሽ ወይስ እንዋጋ» ብለው ምክር ጠየቁ። ወረሂመኖችም በሰው አገር ከምንሞት በአገራችን ብንሞት ይሻላል። አሁንም በረንታን ተሻግረን አገራችን እንግባ። ከዚያም ቢመጡ ብዙ ረዳት አለን ብለው አማከሩዋቸው። ራስ አሊ የጐጃምን መኳንንት ደግሞ ሰብስበው እንዲያማክሩዋቸውና የወረሂመኖችንም ሐሳብ ነገሩዋቸው። ጐጃሞችም «ሲገዛ የኖረ ባለአልጋ ጥቂት እንኳ ሳይዋጋ አይሸሽም። ለሰጠው ይስጠው። እንዋጋ» አሏቸው። ራስ አሊም በጐጃሞች ምክር ተስማሙ። ከዚያም ጦራቸውን አስከትተው ወደ አይሻል ሜዳ ሔዱ።

ደጃዝማች ካሣም በዳሞት አድርገው በናዝሬት ወረዱና አይሻል አካባቢ ሲደርሱ የራስ አሊ ጦር ተሰልፎ አዩት። ሠራዊታቸውንም ዙሪያውን እንዲከብ አዘው የራስ አሊን ጦር ዳር ዳሩን አስከበቡ። የራስ አሊም ጦር የካሣን ሠራዊት

አይቶ በማነሱ አዘነ። ያዘነበትም ምክንያት በብዛት ለተሰለፈው ለራስ አሊ ሠራዊት ምርኮው እንደማያዳርስ ገምቶ ነው። ለአስር ሰው አንድ ሰው ምርኮኛ አይደርሰንም እያለ ይጫወት ጀመር። የደጃዝማች ካሣም ሠራዊት ዳርዳሩን እየዞረ ሳይጋጠም በመቆየቱ ፈርቶ ሊመለስ ነው እየተባለም ተወራ። ለምርኮ የታቻኮለው የራስ አሊ ሰው «እግዚአብሔር ይፍታህ» የሚለውን የጦርነት መጋጠሚያውን ትእዛዝ ተቻኩሎ ይጠብቅ ጀመር።

ሰኔ 23 ቀን 1845 ዓ.ም ጧት ጦርነቱ ተጀመረ። ወዲያውኑ ለምርኮ ያሰፈሰፈው የራስ አሊ ሰው እየተቻኮለ ገብቶ የካሣን ሠራዊት ይጠርገው ጀመር። እንደተመኘው ምርኮም እየማረከ መያዝ ሲጀመር የራስ አሊ ጀግና ግራኝ ወልደ ኪዳን ተመትተው ወደቀ። ግራኝ ወልደ ኪዳን የአሊን ሠራዊት እያበረታታ ቀድሞ የሚዋጋ ታላቅ ጀግና ሰው ነበር። ግራኝ ወልደ ኪዳን ተመትቶ እንደ ወደቀ ወዲያው ሞተ። በዚህ ጊዜ የራስ አሊ ሠራዊት ተደናገጠ። የሠራዊቱን መደናገጥ ያዩት ደጃዝማች ካሣ ከሠራዊታቸውን እያደፋፈሩ ከጦሩ መሃል ሲገቡ የድሉ አዝማሚያ እየተለወጠ ይሔድ ጀመር። የተገላቢጦሽ ሆነና የራስ አሊ ሠራዊት በተራው እንደ ቅጠል ይረግፍ ጀመር። የሰውም ሬሳ እየተነባበረ ወደቀ። ደም እንደ ጐርፍ ፈስሶ መሬቱን አጨቀየው። ደጃዝማች ካሣ ድል አደረጉ። ወዲያው ከፍተኛ ዝናብ በመዝነቡ ከጦር የተረፈውን ቁስለኛ ሁሉ ብርድና ቆፈን ጨረሰው።

ራስ አሊም መውጫ ቀዳዳ አጥተው በሚጨነቁበት ጊዜ ደጃዝማች ተሰማ ጐሹ ደርሰው የከበባቸውን የካሣን ሠራዊት እንደ በር አስከፍተው ይዘዋቸው አመለጡ። የራስ አሊን ማምለጥ ያየው የካሣ ሠራዊት ለመያዝ ያባርር ጀመር። ጀግናው ደጃዝማች ተሰማ ግን አሊን አስቀድመው እሳቸው ከኋላ በመከተልና እየዞሩ አባራሪውን እየወጉ ይዘዋቸው የጁ ለመድረስ አበቁዋቸው።

ደጃዝማች ካሣም እያከታተሉ ራስ አሊን የሚይዝ አባራሪ ቢልኩም የራስ አሊ አድራሻ ስለጠፋ መከታተሉን ተዉት። የአይሻል ላይ ጦርነትም የመሳፍንት አገዛዝ የመጨረሻው ሆነ። በታላቁ አሊ የተጀመረው የምሥፍንና ዘመን በትንሹ አሊ ዘመን ተፈጸመ።

ደጃዝማች ካሣ ከአይሻል ድል በኋላ በደጋ ዳሞት አድርገው ሲመለሱ የደጋ ዳሞት ሕዝብ ወጥቶ ከደከመው የካሣ ሠራዊት ፈረስና በቅሎ ይማርክ ጀመር። በየጥሻው እየተደበቀና አፋፍ ላይ እየሆነ «የጐሹን ደመኛ የአሊን

ወረደኛ ትለቀዋለህን» እያለ ብዙ አስቸገረ። ብዙ ሰውም ገደለባቸው። የባላገሩን መበርታትና መዝረፍ ያየው ተራው ባላገር ሁሉ ፈረስና በቅሎ ለመማረክ በብዛት ይወጣ ጀመር። ያላሰቡት ችግር ያጋጠማቸው ደጃች ካሣ ሁሉን ነገር ችለው በሰላማ አልፋለሁ ሲሉ የዳሞት ባላገር አላሳልፍ ስላላቸው ሰገድ ከሚባለው ቦታ ሲደርሱ ሠራዊታቸውን በለው በለው አዘዙ። የደጃች ካሣም ሠራዊት ትእዛዝ በማግኘቱ ብዙውን ባላገር ፈጀው። ከዚህ በኋላም ሰላም አግኝተው ጉዞአቸው ጀመሩ። አንዲት የደጋ ዳሞት ሴት ባልዋ ለዘረፉ ወጥቶ በመገደሉ ስታለቅስ»

«አመጣለሁ ብሎ የካሣን ፈረስ

ሳያርመው ሞተ የዘራውን ገብስ» ብላ አንጐራጐረች።

## ምዕራፍ 2

# ራስ አሊ እቴጌ መነን ደጃች ጐሹ ዘውዴ ራስ አሊ አሉላ

ኢትዮጵያ በመሳንፍት አገዛዝ ሥር በነበረችበት ጊዜ ራስ አሊ አንደኛው መስፍን ነበሩ። የራስ አሊ ምስፍንና ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው ጀምሮ የመጣ እንጂ እንደ አንዳንዶቹ አምባ ገነኖች ምስፍንናውን ከራሳቸው የጀመሩ አይደሉም። የጐንደድርን የመሳፍንት አገዛዝ የጀመሩት ትልቁ ራስ አሊ ልጃቸው ወይዘሮ ከፈይ መርሳ በሬንቱን አግብተው ጉግሣን ይወልዳሉ። ጉግሣ በአባታቸው የምሥፍንና አልጋ ተቀምጠው ራስ ተብለው 28 ዓመት ገዙ። በዚህ 28 ዓመት የምስፍንና የግዛት ዘመናቸውም ሶስት ንጉሦችን አለዋውጠዋል። ያለዋወጡዋቸውም አጤ ጊጋር አጤ ኢዮአስ እና አጤ ጓሉ ናቸው። ራስ ጉግሳ አራት ልጆች ነበሩዋቸው። እነሱም ይማም ማርዬ፥ ዶሪ አሉላ ይባላሉ። ራስ ጉግሣ ሲሞት በአልጋቸው ልጃቸው ይማም ተተክተው የአባታቸውን አጤ መልሰው በአጤ ጊጋር ተቀማጭነት ሶስት ዓመት ገዙ። ራስ ይማም ሲሞቱ ወንድምየው ማርዬ ራስ ተብለው የወንድማቸውን አልጋ


ወረሱ። ራስ ማርዬ ሶስት ዓመት ገዝተው ሲሞቱ ወንድማቸው ዶሪ ራስ ተብለው የምስፍንናውን አልጋ ያዙ። ራስ ዶሪ ለስም መጠሪያ ያህል የሚቀመጡትን አጤ ሰለሞንን በግንብ አስቀምጠው ሶስትወር ከገዙ በኋላ የራስ ጉግሳ የልጅ ልጅ የሆኑት የአሉላ ልጅ አሊ ራስ ተብለው የምስፍንናውን ቦታ ያዙ።

ራስ አሊ በ1822 ዓ.ም የምስፍንናውን ቦታ ሲይዙ ምፅርሐ አምባ በእስር ከተቀመጡት የነገሥታት ልጆች መሀል ገብረ ክርስቶስን አስመጥተው አጤ ገብረ ክርስቶስ አሰኝተው አንግሰው እሳቸው ሥልጣኑን ያዙ። ራስ አሊ ምንም እንኳን ንጉሱን ለስም አስቀምጠው ሥልጣን ቢይዙም እናታቸው ወይዘሮ መነን ደግሞ ራሳቸውን እቴጌ አሰኝተው የሥልጣን ተካፋይ ነበሩ።

በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን የእንግሊዝ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት የፈጠሩበት ዘመን ነበር። በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ስሙ የገነነው ፕላውዲን በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ሆኖ የተሾመው በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን ነው። በፕላውዲን ትረካ ውስጥ ወደ ፊት እንደምናገኘው ፕላውዲን ከኢትዮጵያ ወደ አገሩ ሄዶ የእንግሊዝ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር በወዳጅነት እንዲተሳሰር ባመለከተው መሠረት የእንግሊዝ መንግሥት የጉዳዩን አሳሳቢ ፕላውዲንን በኢትዮጵያ መንግሥት ዘንድ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ብሎ ሾመው።

ፕላውዲን ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ የሹመቱን ደብዳቤ ለማቅረብ ሔዶ በራስ አሊ ቤት ስላየውና ስለ ራስ አሊም ሰውነትና ጠባይ ሰፋ ያለ ታሪክ ጽፏል። ፕላውዲን ከፃፈው ትረካ በመጠኑ እናንብ። «.......ከራስ ቤት ውጪ የተለያየ ማዕረግ ያላቸው ሰዎች ይቀመጣሉ። አንዳንዶቹም በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ናቸው። በድንጋይ ወይም ከመሬት ላይ ከጠሀይም መከለያ ጥላ በሌለበት ቦታ ይቀመጣሉ። ጉዳያቸው እስኪፈፀምላቸው ድረስም ለብዙ ሳምንታት ይቆአያሉ።...... በዚያ ላይ አጋፋሪዎች ማንንም ሳይመሩ በዘንግ እየመቱ ያባርሩዋቸዋል።...... ከሰዎቹም አንዳንዶቹን ስለማውቅ ጉንች ለጉንጨ የተሳሳምን በሩን በሩን አልፌ ከውስጠኛው የችሎት ቦታ ገባሁ። በዚያም ቦታ የማውቃቸውን ታላላቅ ሰዎችን መልዕክት ተላላኪዎችንና ሥራ ቤቶችን ሁሉ አገኘሁ። ከከፍታ ሰገነት

ላይ አፈ ንጉሡ ከሁለት ይሁን ከሶስት ሽማግሌዎች ጋር ሆነው ከበታቻቸው የሚንጫጫውን የሕዝቡን አቤቱታ ይሰማሉ። አልፎ አልፎም አንዳንድ ሁኔታዎችን ለራስ ይነግራሉ። ከሁለት ይሁን ከሶስት ደቂቃ በኋላ እኔና ቤል ገብተን እጅ ነሳን። ከመሬት በተነጠፈ ቆዳ ላይ አንድ ትልቅ አለቃ ተቀምጠው አየሁ።....... ጥቂት የጋላ ልጆች ይጫወታሉ። አንድ አሽከር ቆሞ ትእዛዝ ይጠባበቃል። ራስ እኔን በማየታቸው መደሰታቸውን ገለጡልኝና ውዲያውኑ ምን እንዳመጣሁላቸው ጠየቁኝ። ይህም የተለመደ ጥያቄ ነው። እኔም በጊዜው እንደሚያዩት ነገርኳቸውና ማረፊያ ቤት እንዲሰጡኝ ጠየቅኋቸው። እሳቸውም ወደ እሳቸው ቤት እንድመጣ ነገሩኝ። እኔ ግን አልፈልግም አልኳቸው። አብረን ቁርስ ከበላን በኋላ 200 ያርድ ያህል ከሚርቀው ከአንድ እስላም ባለሥልታን ቤት እንድገባ ታዘዘልኝ። ይህም ቤት ኮረብታ ላይ ሆኖ ደስ የሚልና ዙሪያውን በደህና አጥር የታጠረ ነው። በጣም ደስ አለኝ።




Ritratto di Râs Aly.

# ራስ አሊ አሉላ

«ራስ ቀኑን ሙሉ መልዕክተኛ እየላኩ የመጣሁላቸውን ጠመንጃ ወይም ሌላ ነገር እንዳሳያቸው ይጠይቁኛል። በማግስቱ ዕቃዬን ተሸክመው የመጡትን ሰዎች ሂሳባቸውን ከፍዬ አሰናበትሁና ከሰዓት በኋላ ለራስ ያመጣሁትን ስጦታና ለንጉሱ የተፃፈውን ደብዳቤ ይዠ ሔድሁ።...... ቆሜ ከንግሥታችን የተላከውን ደብዳቤ አነበብኩላቸው። ነገሩ ምን እንደሆነ አልገባቸውም። ከዚህ በኋላ የተላኩላቸውን ስጦታ አቀረብሁ። ተመሰጡ።...... ከዚያም ወጥቼ ሔድሁ።

«በሌላ ቀን እነኚህን ስጦታዎች ለመቀበል ያሳፍረኛል። ምክንያቱም የዚህን ስጦታ መልስ ለንግሥታችሁ የምሰጠው የለኝም። ድሃ ነኝ አሉኝና ሁለት መንደሮችን ሰጡኝ። ሲሰጡኝም ፈረስና በቅሎህን የት ታስቀምጣለህ። እነዚህ ከሌሉህስ ሣርና ቤት የት ታገኛለህ አሉኝ።...... እውነታቸውን ስለሆነ...... እሺ ብዬ ተቀበልኩ።...... መሰንበቻቸውን ራስ በቀን ሶስቴና አራቴ መልክተኛ እየላኩ ያለኝ እየመሰላቸው ተጨማሪ ጠመንጃና ሽጉጥ እንድሰጣቸው ይልኩብኛል።.........በመጨረሻም ያለኝን ጠመንጃና ሽጉጥ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎችንና ድንኳኔን ጭምር እንድሰጣቸው ጠየቁኝ።

«በ1848 ዓ.ም ታላቁ የአበሻ ገዢና በኛ መንግሥት የታወቁትን ራስ አሊን ሁለት ፊውዳል መኳንንት አስቸገሩውቸው። የትግሬው መስፍን ውቤ በሰሜን አመፁባቸው። የጐጃሙ መስፍን ብሩ ደግሞ በደቡብ በኩል ሸፈቱባቸው። ይህም አዲሱ ተዋናይ (አክተር) በሰገነቱ ላይ እስቲታይ እስከ 1853 ዓ.ም ድረስ ቆየ። በ1853 ዓ.ም የቋራው ደጃች ካሣ ተነሣ።.......

«ራስ አሊ ልዩ የሆነ ጠባይ አላቸው። ከእሳቸወ ጋር ተነጋግሮ አንድ ነገር ለመወሰንም በጣም አስቸጋሪ ናቸው። ሥልጣን የያዙት በ12 ዓመት ዕድሜያቸው ገና ልጅ ሆነው ነው።......ሰውን ሁሉ የሚንቁና ራሳቸውን የሚወዱ ሰው ናቸው።....... በራሳቸው ላይ በሚደርስ መጥፎ አጋጣሚ እንኳ የሚስቁ ከግዛታቸው ተቀንሶ አገር ቢወሰድ በጦርነት ድል ቢኮን የጦር አዛዦቻቸው ቢሞቱ እንኳ ጥቂትም የማይቆጫቸውና የማያናድዳቸው ናቸው።...... በተንኮልና በሰላይ መጠቀምን የሚወዱ ናቸው። ጨካኝ

ባለመሆናቸው መቅጣት ስለማይወዱ በግዛታቸው ውስጥ ብዙ ከሥነ ሥርዓት ውጪ የሆኑ ሰዎች አሉ። መበቀልን አይወዱም። ጠላቶቻቸውን እንኳ እየናቁ የሚተዉ ሰው ናቸው።..... በቅርብ ከሚያውቋቸ ይልቅ በሩቅ ሆነው በጥቂቱ የሚያውቋቸው ይወዱዋቸዋል።.......በአካል መካከለኛ ቁመት ያላቸው ኃይለኛና ፈጣን ናቸው።...... ጥሩ ተኳሽ ጥሩ ፈረስ ጋላቢ የታወቁ ጦር ወርዋሪና ሯጭ ናቸው። በአበሻ ውስጥ አሉ ከሚባሉት ጥሩ ፈረስ ጋላቢዎች አንዱ እሳቸው ናቸው። አንዴ ሰው ከወደዱ ግን ይወዳሉ። ከጥሩ ጠባዮቻቸው አንዱ አንዴ ሰውን ከወደዱ ፈጥነው የሚለወጥ (የሚጠሉት) አይደሉም። ጠላቶቻቸው እንኳ ቢሆን ቸርና ደግ ሰው አንቸው።........» በማለት ፅፎላቸዋል።

ራስ አሊ ቀደም ብለን እንዳነበብነው አይሻል ላይ ከደጃዝማች ካሣ ጋር ተዋግተው ድል ከሆኑ በኋላ መውጫ አጥተው ሲጨነቁ የደጃች ጐሹ ልጅ ደጃች ተሰማ ደርሰው ከዚያ ቱማታና ሽብር አውጥተው ከሚያባርራቸው ጋር እየተታኮሱና እየተከላከሉ ደንበጫ አደረሱዋቸው። በደምበጫ እረፍት አድርገው ከአደሩ በኋላ በማግስቱ አመዳሚት ከሚባል ቦታ አደረሱዋቸው። ደጃች ተሰማ አልጋህን ለባዕድ አድርሰው ሲመለሱ ራስ አሊ «.......አልጋህን ለባዕድ አይበለው። ከከፉ እሚታደግ ከጭንቅ የሚያወጣ የተባረከ ዘር ይስጥህ። እኔ መረቅሁህ ዛሬ ብቻ አይደለም። ፊትም በአባትህ ሰንሰለት ተለውጠህ የታሠርክ ዕለትም ነው........» ብለው ደጃች ተሰማን መርቀዋቸው ተሳስመው ተለያዩ።

ከአመዳሚት ደግሞ ይመር ጣሹ የሚባል ሰው እስከ አባይ ወንዝ ድረስ ሸኝቷቸው ማህደረ ማርያም አደሩ። ከማህደረ ማርያም ተነስተው ዋድላ ገቡ። ከዋድላም ደራ ገብተው ከደራው ገጽዥ ከዋቆ ዲቦ ዘንድ ተደብቀው መኖር ጀመሩ። ደጃች ካሣ አገር እያሳመኑ አመዳሚት ሲደርሱ ዋቆ ዲቦ ፈርቶ «ራስ አሊ ከኔ ዘንድ ናቸው» ብሎ ለካሣ ላከ። ራስ አሊም ይህን ሲሰሙ አዝነው ለሸዋ ንጉሥ ለኃይለ መለኮት «አምኜኔው ብመጣና ከእሱ ዘንድ ብጠጋ ዋቆ ዲቦ አሳልፎ ለጠላቴ ሊሰጠኝ ነውና ታደገኝ» ብለው ፈጣን መልዕክተኛ ላኩባቸው። ንጉሥ ኃይለ መለኮትም ጦራቸውን ይዘው ወደ ደራ ሔደው ዋቆ ዲቦን ወግተው ራስ አሊን አውጥተው ወደ የጁ ሰደዱዋቸው።

ራስ አሊ ከትውልድ አገራቸው የጁ ይግቡ እንጂ ካሣን በመፍራት ተዝናንተው አልተቀመጡም። ራያ በረሃ ወርደው በዋሻ ውስጥ ተደብቀው የመከራ ኑሮ መኖር ጀመር። 48 ነጋሪት በአደባባያቸው አብጂር ሲል ይውልበት የነበሩ ታላቅ ጌታ የአውሬ ድምፅ ከሚሰሙበት ዋሻ ገቡ። ባንድ ጉዞ 55 ሺ ወታደር አጅቧቸው ይጓዙ የነበሩት ራስ አሊ በአሁኑ ጊዜ አንድ ታማኝ አሽከር ብቻ ቀራቸው።

ራስ አሊ ጥንቱንም ቢሆን በገና መደርደር (መምታት) ይችሉ ነበርና በዚያ በመከራ ዘመን በዚያ ጭር ባለ ቦታ በዋሻቸው ውስጥ በገና እየመቱ ራሳቸውን ያጽናኑ ጀመር። አንድ ቀን

«የጣቴን ቀለበት አንተ አድርገው ካሣ

«በኔ ማጣት ገብሮ አስጨነቀኝሳ» ብለው አንጐራጐሩ

ቅኔው ሲፈታም «በኔ ማጣት ችግር ገብቶኛል» ማለታቸው ነው። በሌላ ቀን ደግሞ በገና እየደረደሩ ሲያዝኑ

«የውቤን ደመኛ የጐሹን ገዳይ

ያሊን መንግሥት አፍራሽ ያን ዘበናይ።

አደባባይ ቆሞ አበጀሁ ቢላችሁ

ይህን ባለ ጊዜ ምን ትሉታላችሁ» አሉ። በኋላ ታሪኩን የምናመጣው ካሣ የደጃች ጐሹን ልጅ ደጃች ብሩንና የሰሜኑን ገዥ ደጃች ውቤን ድል አድርገው ማሰራቸውንና መንገሣቸውን ከሰሙ በኋላ ተስፋ ቆርጠው የበፊት የበገና ግጥማቸውን በማሻል «የብሩን አሳሪ የጐሹን ገዳይ

የኔን መንግሥት አፍራሽ የውቤን አባታይ።

አደባባይ ቆሞ አበጀሁ ቢላችሁ

ይህን ባለ ጊዜ ምን ትሉታላችሁ» ብለው አለቀሱ። ከግጥሙ መዝጊያ ላይ «ይህን ቢላችሁ ምን ትሉታላችሁ» ያሉ መስለው ምስጢሩ ግን «ይህን ጊዜ የሰጠውን ሰው ጊዜ ያነሳውን ሰው» ማለታቸው ነው።

በበረሃው ዋሻ ሆነው ከፍተኛ ረሃብና ችግር ደረሰባቸው። አንድ ቀን ራስ አሊ ከተደበቁበት ዋሻ ብቅ ሲሉ በዋሻው አጠገብ ያለውን የማሽላ ዘር ከወፎች ይጠብቅ የነበረ አንድ ገበሬ ዝንጀቶ መስለውት ድንጋይ በወንጭፍ እያወነጨፈ ይወረውርባቸው ጀመር። ራስ አሊም ያን አሽከራቸውን ልከው «እኔ አሊ ነኝና ተወኝ። ይልቅስ እባክህ የማሽላ እሸት ስደድልኝ» ብለው ላኩበት። ይህን የአባታቸውን መቸገር የሰሙት ልጃቸው የካሣ ሚስት ወይዘሮ ተዋበች ከባላቸው እየደበቁ ምግብም ልብስም ይልኩላቸው ጀመር። በዚህን ጊዜ ኑሮአቸው በመጠኑ የተሻለ ቢሆንም እኝሁ የሚረዷቸው ልጃቸው ሞቱ። አሊም የልጃቸውን መሞት ሲሰሙ በድንጋጤ ታመሙ። ስለልጃቸው ሞትም በገናቸውን እየደረደሩ።

«ጠጅ አማረኝ ስላት ማሩን ታስጭናለች።

ራበኝም ስላት እህሉን ትልካለች

በረደኝም ስላት ሸማ ትሰዳለች

ሌባዬ ተይዛ ባልጋ ትሔዳለች።» በማለት አለቀዱሱላቸው።

ራስ አሊም ሕመማቸው እየተና ሔደ። ይህን ያየው ያገለግላቸው የነበረው አሽከራቸው ድሮም በገና ደርዳሪ ነበርና በገናውን እየደረደረ

«አንተንም አፈር የበላሃል

እኔንም ጐንደር ይሸጡኛላ።

ከአሊ በፊት

እኔ ልሙት።

አሊ ሲሞት ያለብኝ አሣር

የሽማግሌ ማጭድ የአዋሌ ምሳር።

አሊ ሲሞት

መጠጤ አተላ ሙብሌ ጉበት።

ከአሊ በፊት እኔ ልሙት» እያለ አንጐራጐረ። ራስ አሊም ከልጃቸው ሞት በኋላ ምንም ያህል ሳይቆዩ ሞተው ወሎ ውስጥ ሐይቅ ደሴት ተቀበሩ። በሥልጣን ላይ የቆዩት 22 ዓመት ነበር።

## እቴጌ መነን

መነን የራስ አሊ እናት መሆናቸውንም በጦርነትም ምን ያህል ተዋጊ ሴት እንደነበሩ አንብበናል። ማርክሃምም «......ዝነኛ የሴት ጦረኛ ሴት። አሻንጉሊቱን ንጉሰ ሸማግሌውን አጤ ዮሐንስን አግብታ በልጅዋ ስም ደንቢያ ትገዛ ነበር.......» ይላል። እቴጌ መንነ የበፊት ስማቸው ሐሊማ ነበር ይባላል። ራስ አሊ ሥልጣን ከያዙ በኋላ የእናታቸው ስም ሐሊማ መባሉ ቀርቶ መነን እንዲንባሉ በአዋጅ አስነገሩ። ሐሊማ የሚል ሰው ቢገኝ አይቀጡ ቅጣት እንደሚቀጣ አስነገሩ። ጐንደሮች በግጥም አመስጋኝ መስለው መሳደብን የሰደቡ መስለው ማመስገንን ወይም ደግሞ ግልፅ ባልሆነ መንገድ ሚስጥር ማውጣትን ይችላሉ። በዚህም ቅኔያቸው ጐንደሮችንና ጐጃሞችን የሚስተካከል የለም። ራስ አሊ የእናታቸው ስም መነን እንጂ ሐሊማ እንዳይባል ባወጁበት ጊዜ በራስ አሊ አዳራሽ ሕዝቡ ግብር ገብቶ ሲበላና ሲጠጣ በመሀል ሆኖ ያጫውት የነበረው አዝማሪ

«አሊ ምን ይላታል እናቱን

እኛስ የምንላት እቴጌ መነን» ብሎ አንጐራጐረ ይባላል የቅኔው ትርጉም ያልገባቸው ራስ አሊም ተደስተው ሸለሙት ይባላል። አዝማሪው ግን «ሐሊማ ይላታ እናቱን» ማለቱ ነው።

ሲቭሮ ሮቢንሰን እንደጻፉት እቴጌ መነን ኢትዮጵያን እየከፋፈለሉ ሊሸጡ ካስማሙ ባላባቶች አንደኛይቱ ናቸው። በአሌክሳንድርያ የቤልጅንግ መንግሥት ቆንስል የነበረው ኤድዋርድ ብሎን ዲል ከእቴጌ መነን ጋር በመነጋገር አጋሚኔንና እንጣሎን በ15.000 ማርትሬዚያ ብርና በሶስት ሺህ ጠመንጃ ለመግዛት ተስማምተው ነበረ። ለዚህም ጉዳይ ኢትዮጵያዊው አባ ገብረ ማርያም ለኢትዮጵያ መንግሥት ኃላፊ ሆነው ለሽያጩ ተግባር ዋና ደላላና ተዋዋይ ነበሩ።

አባ ገብረ ማርያም ካይሮ ውስጥ ከቤልጅጉ ቆንሲል ከብሎንዲል ጋር የተዋዋሉት ውል እንዲህ የሚል ነበር። «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም። እኔ ገብረ ማርያም የኢትዮጵያ እጨጌ በኢትዮጵያ ገዥ በራስ አሊ ስም የሚከተለውን ተስማምቻለሁ። ለቤልጅግ ንጉሥ ግርማዊ ቀዳማዊ ሊዎፖልድና ለእሳቸውም ወራሾች ሁሉ እንዲሆን የአጋሜን አውራጃ በሙሉ ከአዲግራት እስከ ባህሩ ድረስ ሰጥተናል» የሚል ነበር። አባ ገብረ ማርያም በመስፍኑ በራስ አሊ ስም ውሉን ይጻፉ እንጂ ጉዳዩን የፈፀሙት እቴጌ መነን ናቸው ይባላል።

ነገሩን ከሥሩ ለማምጣት ያህል በግብፅ የቤልጅግ ቆንሲል የነበረው ኤድዋርድ ብሎን ዴል እ.ኤ.አ በ1837 ዓ.ም ለቤልጅግ መንግሥት አንድ ሪፖርት ልኮ ነበር። ሪፖርቱም ብዙ መንግሥታት የቀይ ባሕር አካባቢ ሲሻሙበት የቤልጅግ መንግሥት ለምን ዝም እንዳለ የሚገልፅ ነበር። በኋላም የእንግሊዙ ብሪትሽ ኢስት እንዲያ ካምፓኒ ዘይላን ይዞ ፊቱን ወደ አርጊጐ ባዞረበት ጊዜ ብሎንዴል ደግሞ የአገሩ የቤልጅግ መንግሥት ከዙላ ምሥራቅ ያለውን እንፊላን እንዲይዝ መከረ። እ.ኤ.አ በ1842 ዓ.ም ወደ ቤልጅንግ መንግሥት ባስተላለፈው ሪፖርትም የፈረንሳይ መንግሥት ኢድ የተባለውን ቦታ ከገዛበት ዋጋ ትንሽ ጨመር አድርጐ በሁለት ሺህ ብር ከኢትዮጵያ መሬት ቦታ ለመግዛት እንዲችል ከ25.000 እስከ 30.000 ድረስ የቤልጅግ ፍራንክ ግብፅ ድረስ ቢላክለት ለቤልጅግ የመጀመሪያውን የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት ለማስገኘት እንደሚችል አስታወቀ። ኢድ በዛሬው ጂቡቲ ውስጥ ያለች ሥፍራ ስትሆን በዚያን ጊዜ ለፈረንሳይ የተሸጠችው በ1800 ማርትሬዚያ ብር ነበር።

የቤልጅግ መንግሥትም እንፊላን ቢገዛ ምን ጥቅም እንደሚያገኝ እንዲገልፅለት ቆንሲሉን ብሎንዴልን ጠየቀ። ብሎንዴልም በሰጠው መልስ «........ዛሬ ከምፅዋ ወደብ በያመቱ ሁለት መቶ ሺ ፍራንክ ያህል ገቢ ይገኛል። የእንፊላን የባህር ዳርቻ ገዝተን ወደቡን ብናስፋፋው በምፅዋ የሚገኘውን ገቢ ወደ እፍኒላ ማዞር ይቻላል።.......» ብሎ አሳአወቀ። ቀጥሎ ባስተላለፈው ሪፖርትም ኢትዮጵያ በምሥራቅ በኩል ጤናማ አገር መሆንዋን ሀብታምና ሀብቷም ያልተነካ ሕዝቡም ዘመናዊ መሣሪያ ስለሌለው አገሪቱ በቀላሉ ያምትያዝ መሆንዋን ገልጾ «.......አንድ አጥኚ ወኪል ወደ ቀይ ባህር ቢላክ

የእንፊላን ሁኔታና ጠቅላላው ኢትዮጵያን ሊያጠና ይችላል። የእንፊላ ገዢዎችም በቀላሉ በጥቃቅን ድለላ የሚዋዋሉን ናቸው። በዳርቻው ላይ ተቆናጠን መብቻን የሆነ መሬት ከያዝን በኋላ የሚያስፈልገው ነገር 500 የታጠቁ ሰዎች ወደ ሥፍራው ብንልክ በቂ ይሆናል። እነኚህም የሚላኩት የታጠቁ ሰዎች ይዞታችንን ለማጠናከር ጠረፉን ለመጠበቅ በቂ ናቸው።....... እንፊላ ደግሞ የኢትዮጵያን ደጋ ቦታዎች ለመያዝ አመቺ ሥፍራ ነው።...... እንፊላ የምጠቁመው በኔ አስተያየት ለመጀመሪያ ጊዜ ለመቆናጠጫ ጠቃሚ መሆኑን በማወቄ ነው። እሱ ከተያዘ መላውን አገር በቅኝ ግዛት ለመያዝ መንገዱ ቀላልና ክፍት ነው የሚሆነው........» ብሎ ምኞትና ዓላማውን ገለፀ። በዚያው ላይ ደግሞ ሪፖርቱ በሚስጥር እንዲያዝ ይጠይቃል።

የቤልጅግ መንግሥት ጉዳይ እንዲጠና አደረገ። በጥናቱ መሠረት የቤልጅግ ቅኝ ገዢነት የቀይ ባህርን አካባቢ መያዝ እንደማይጠቅም ታወቀ። የማይጠቅምበትም ምክንያት በኔ የስዊዝ ቦይ አልተቆፈረ ስለነበረ በመከርብ ወደ ቀይ ባሕር ለመምጣት በደቡብ አፍሪካ ዞሮ በመሆኑ ብዙ ወጪ እንደሚያስወጣና ጉዞውም ረጅም በመሆኑ አያስፈልግም ተብሎ ተወሰነ። ከውጭ በእንዲህ ያለ ሁኔታ እንዲቀር ሲደረግ በአገር ውስጥ ደግሞ የቴዎድሮስ መነሳት የእቴጌ መነንም ሆነ የአባ ገብረ ማርያምን ምኞት አጨናገፈው።

## ጐሹ ዘውዴ

ቀደም ብለን እንዳነብነው ከካሣ ጋር ሲዋጉ የሞቱት ደጃች ጐሹ የጐጃሙ የደጃች ዘውዴ ሥልን ልጅ ናቸው። አለቃ ተክለ ኢየሱስ ስለ ደጃች ጐሹ አወላለድ ሲተርኩ የመርድ «.....የእህቱ የድንቅነሽ ባል የዳሞት ደጃች ዘውዴ ጉልበት ተሰምቶ በዳሞት ላይ ጐጃምን ደርቦ ሊገዛ ከጅሎ ነበረ። ግን ራስ መርድ ቶሎ ነቃበትና በምክንያት ይዞ ሊያስር እቴን ድንቅነሽን ልያት ይዘሃት ና ብሎ ምላሽ ጠራው። ደጃዝማች ዘውዴም የተንኮል መሆኑን ሳያውቅ ወይዘሮ ድንቅነሽን ይዞ ገባ። ራስ መርድም ደጃች ዘውዴን ይዞ በቀራንዮ ዋሻ አስሮ እቱን ድንቅነሽን እጅ አደረገ። ከብዙ ቀን በኋላ ምሽቱ ስትናፍቀው ጊዜ ዘውዴ መድኃኒት ታጠጣኝ ብሎ ወደ ራስ መርድ ላከ። ራስ መርድም ታማኝ ገረድ ስደጅለት ብሎ አዘዘ። ደጃች ዘውዴም በሌላ እጅ አልጠጣም ብሎ

እምቢ አለ። ራስ መርድም ዘበኛ ጨምሮ ምሽቱን ሰደደለት። ደጃች ዘውዴም መድኃኒት ይጠጣ መስሎ እንደታሰረ ተገናኙ። ያን ቀን ደጃች ጉሹ ተፀንሶ አደረ.......» ይላሉ

ደጃች ዘውዴ ከደጃች መርድ ጋር ታርቀው በሥልጣናቸው ተመልሰው ነበርና ደጃች ዘውዴ ሲሞቱ ጉሹ በአባታቸው ሥልጣን ተተኩ። ራስ ጉግሣም ጉሹን ገብር ቢሏቸው ደጃች ጉሹ አልገብርም ብለው እምቢ አሉ። ራስ ጉግሳ ሊወጓቸው ወደ ጐጃም መጡ። ጉሹ ሸሽተው ንብረታቸውን ከጅብላ ዋሻ ከትተው እሳቸው ወደ አሞሮ ሔደው ተደበቁ። ራስ ጉግሳም በጐጃም ላይ ደጃች ጉበናን ሾመው ወደ በጌምድር ተመለሱ። የራስ ጉግሳን መመለስ ጉሹ እንደሰሙ ከአሞሮ ጦር ይዘው መጥተው የደጋ ዳሞትን ጦር ጨምረው ደብረ ዘይት ውስጥ አምስትያ ከሚባል ቦታ ከደጃች ጉበና ጋር ጦርነት ገጥመው ጉሹ ድል አደረጉ። ለራስ ጉግሳ አልገበርም እንዳሉ ሳይገብሩ በጐጃም ግዛታቸው ላይ ተቀመጡ።

ከራስ ጉግሳ በኋላ የምስፍንናውን ቦታ ራስ ማርዬ ሲይዙም ጉሹ አልገብርም ብለው እምቢ አሉ። ራስ ማርዬም ሊወጓቸው ወደ ጐጃም ሲመጡ ጉሹ እንድተለመደው ከጅብላ ገቡ። ራስ ማርዬም የጅብላ ምሽግ ጠንካራ መሆኑን አይተው በአገሩ ላይ ደጃች ማጠንቱን ሾመው ተመለሱ። ራስ ማርዬ ወደ ጐንደር እንደተመለሱ ጉሹ ከምሽጋቸው ወጥተው ማጠንቱን ሊወጉ ወደ ቤቡኝ ሔዱ። በዚያም ሆነው

«ተጠናከር ጐጃም ተጠናከር ዳሞት

አይተንም አናውቅ በአረፋ ነጋሪት»

ብለው ለአዝማሪ ግጥም ነገሩ። ይህን ለአዝማሪ የተነገረውን ግጥም ደጃች ማጠንቱ እንደ ሰሙ ሰሙ እሳቸውም አዝማሪ አቁመው

«በል አንዳችም እቲ በል አይጐዳም

እግዚአብሔር ከሰጠ የሰው ልጅ አይነሳም።» ብለው ነገሩ።

ሁለቱም ደጃዝችማ በግጥም ከተመላለሱ በኋላ በቤቡኝ ቀበሌ ሰበዝ ከሚባለው ቦታ ጦርነት ተጋጥመው ጉሹ ድል ሆነው ተያዙና ቋሚ ጨርቅ ከሚባለው ቦታ ታሠሩ። ከደጅች ጉሹም ጋር የታወቁት ጀግኖቻቸው

ፊታውራሪ ገለታ እና ፊታውራሪ ባርያው አብረው ተይዘው ታሰሩ። ከዚህ ድል ብኋላ የደጃች ማጠንቱ ገረድ ስትዘፍን

«ከተያዘ ገለታ

ደሞዜን የኔታ

ከተያዘ ባርያው

አገሬን ልየው» አለች።

የደጃች ጐሹ ልጅ ደጃች ብሩ የአባታቸውን የደጃች ጐሹን መታሰር እንደሰሙ ሠራዊታቸውን አስከትተው መጥተው ሰጉዲት ከሚባል ቦታ ከደጃዝማች ማጠንቱ ጋር ጦርነት ገጠሙ። በዚህም ጦርነት ደጃዝማች ማጠንቱ ድል ሆነው ሸሽተው ከደጃች ውቤ ዘንድ ገቡ። ደጃች ብሩም አባታቸውን ደጃች ጐሹን በሥልጣናቸው መለሱ ደጃች ጐሹ ለጐንደር የመሳፍንት መንግሥት አልገብርም ብለው ራሳቸውን ችለው ሲኖሩ ራስ ማርዬ ሞቱ። ከራስ ማርዬ በኋላ ራስ ዶሪ በምስፍንናው ቦታ ተተከተው አጤ ሰለሞንን በግምብ አኑረው በሚያስተዳድሩበትም ዘመን ደጃች ጐሹ አልገብርም አሉ። ራስ ዶሪም ሠራዊታቸውን አስከትተው ጐጃምን ለመውረርና ደጃች ጐሹን ለማስገበር ዘመቱ። ደጃች ጐሹ ከልጃቸው ከደጃች ብሩ ጋር ሆነው አመዳሚት በተባለው ቦታ ላይ ጦርነት ገጠሙዋቸውና ራስ ዶሪን ድል አድርገው መለሱዋቸው።

ራስ ዶሪ ሞተው ሥልጣኑን ለራስ አሊ ሲይዙ ጐሹን ገብር ብለው ላኩባቸው። ጐሹም እንደተለመደው እምቢ አሉ። ራስ አሊ በጐጃም ላይ ማለት በደጃች ጐሹና በደጃች ብሩ ግዛት ላይ ሌሎችን ሾሙባቸው። የየጁውን አዶዮ ባቡን በአገው መሸሻ ባቡን በዳሞት ሥዩም በቃኸኝን በጐጃም ሾመው ግዛታችወን እንዲይዙ ሰደዱዋቸው። ይህን ሲሰሙ ጐሹ የዳሞትን ጦር ደጃች ብሩ ደግሞ የጐጃምን ጦር አስከትተው ደረቤ ሜዳ ስኩት ከሚባል ሥፍራ ጠበቋችወ። አዲስ ተሿሚዎቹም የበጌምድርንና የየጁን ጦር ይዘው ደጋ ዳሞትን እየዘረፉ መጡ። ስኩት ሲደርሱም የሁለቱ ወገን ጦርነት ተጋጠሙ። ጦርነቱ ተፋፍሞ ብዙ ሰው ከአለቀ በኋላ የደጃች ጐሹ ጦር ድል አደረገ። ሥዩም በቃኸኝ በጀግንነት ተዋግተው ፊቴን አዞሬ አልሸሽም ብለው በዚያው በጦሩ ሜዳ ላይ ሞቱ። መሸሻ ባቡና አዶዮ ባቡ ግን ሸሽተው አጋምና ጊዮርጊስ

ቤተ ክርስትያን ገብተው ምህረት እንዲደረግላቸው ተማፀኑ። ደጃች ብሩ ግን ተከትለው ቤተ ክርስትያኑ ውስጥ ገብተው ሁሉንም እያረዱ ፈጁዋቸው። አልቃሽም

«መሸሻ ባቡ አዶዮ ባቡ ያስነሱበቱ

ሥዩም በቃኸኝ የሞቱበቱ

ሣር አላበቀለም ስኩት መሬቱ።

የውሃም አይደል የሥዩም ደም ነው

የስኩት መሬቱ ሳሩ ለምለም ነው።

ሥዩም በቃኸኝ የወረደበት

አምስት መቶ ላም የተነዳበት።

ሥዩም በቃኸኝ የሞተው ዝሆን

ጦር መጣ በሉት ይነሳ እንደሆን» ብላ ገጠመችላቸው።

ለደጃች ጐሹም «ጐሹ የኢያሱ ልጅ ዓለም የማይውቀው፥

ዘውዴ አባቱ ነው ቢነግስ ምነው»

እየተባለ ተዘፈነላቸው።

ይህም የሹማምንቶቻቸውን ማለቅ ራስ አሊ ሲሰሙ ደነገጡ። የጐሹንም የኋላ ታሪክ አጥንተው በወዳጅነት መያዙ እንደሚሻል አውቀው በመሐላ ተራርቀው ወዳጅ ሆኑ። ወዳጅነታቸውን ለማጠናከርም ራስ አሊ ልጃቸውን ወይዘሮ የወብዳርን ለደጃች ጐሹ ልጅ ለብሩ በሚስትነት ዳሩላቸው።

ደጃች ጐሹ ከጐንደር መሳፍንት ጋር በጀግንነት እየተዋጉ ኖረው በራስ አሊ ዘመን ወዳጅ ሆነው እፎይ ብለው ለመኖር ሰላማዊ ኑሮ ሲጀምሩ ልጃቸው ደጃች ብሩ ተነሱባቸው። ደጃች ብሩ ሠራዊታቸው እየበዛና እየደረጀ በመሔዱ ኩራትና ጉልበት ተሰማቸው። የአባታቸውን ግዛት ዳሞትን በጐጃም ላይ ደርበው ለመያዝ ፈለጉ «ግዛቱን ለኔ ልቀቅልኝና ዝም ብለህ ተቀምጠህ ተጠባ (ተጦር)» ብለው ላኩባቸው። ወደ ደጃች ጐሹ የተላኩት መልእክተኞች

መልሱን ይዘው ሳይመለሱና እሺም እምቢም ማለታቸው ሳይታወቁ ደጃች ብሩ በአባታቸው ግዛት በደገሞና በመቻከል በፊጠበዶኝ የራሳቸውን ሰዎች እየሾሙ የጐሹን ሹሞች አባረሩ።

ይህን ጥንሰስ የፈሩ ያገር ሽማግሌዎች በነገሩ መሀል ገብተው አባትና ልጁን ለማስታረቅ ጥረት አደረጉ። ደጃች ብሩ «እስታሁን የገዛው ይበቃዋል። አገሩን ለኔ ለቆልኝ እኔ እየገዛሁ እሱን እጦረዋለሁ። በዚህ ካለ ተዋግቼ በጉልበቴ ግዛቱን እወስዳለሁ እንጂ ምንም ቢሆን እንደ ጥንቱ ይሁን ብዬ አልታረቅም» አሉ። ሽማግሌዎቹም ወደ ደጃች ጐሹ ሔደው «እርስዎ ይሸነፉ (እሺ ይበሉ) እሱ ጉልበቱ እንደመራው ይያዝ» ቢሏቸው ጐሹ «ወልጄ እርስዎ አልል። ጋሻ አንግቤ አንተ አልል። ሰው ካልሳቀበት ያሰበውን ያድርግ» ብለው እርቁን እምቢ አሉ። ከዚህ በኋላ ሁለቱም አባትና ልጅ ሊዋጉ ለጦርነት ተሰላለፉ። ደጃች ብሩ ለጦርነት ከተሰለፈው ሠራዊታቸው መሀል ተገኝተው «አባቴን ማርኩ እንጂ እንዳትገድሉ?» ብለው በአዋጅ አስነገሩ። የሁለቱም ወገን አንጋጣ በሚባል ሜዳ ላይ ተጋጥሞ የደጃች ብሩ ሠራዊት ድል አድርጐ አባትየው ደጃች ጐሹ ድል ሆነው ሸሹና ኢጋምና ጊዮርጊስ ቤተ ክርስትያን ገብተው ምሕረት ጠየቁ። ከዚህ በኋላ እንደገና የሁለቱም ወገን መኳንንቶች አባትና ልጁን አስታርቀው በሰላም መኖር ጀመሩ።

ይህን የአባትና ልጁን መዋጋት ራስ አሊ እንደሰሙ ከደብረ ታቦር ወደ ጐጃም መጡ። አዴት ከሚባል ቦታ ሠፈር አድርገውም ደጃች ጐሹንና ደጃች ብሩን እንዲመጡ ላኩባቸው። ደጃች ብሩ አልመጣም ብለው ሶማ አምባ (ምሽግ) ገቡ። ደጃች ጐሹ ግን «በፊት የማልኩትን መሀላዬን አላፈርስም» ብለው ወደ ራስ አሊ ሔደው ተገናኙ። ራስ አሊም የበፊቱንና ያሁኑን ጦርነት ተርከው ተቆጡና ጐሹን አሠሩዋቸው። የደጃች ጐሹ ሌላው ልጃቸው ተሰማ ጐሹ የሚባሉት የአባታቸውን መታሰር ሲሰሙ ራስ አሊ ዘንድ ቀርበው «በአባቴ ስነሰለት እኔ ተለውጬ ልታሠርና እሳቸው ይፈቱ» ብለው ለመኑ። ራስ አሊም ተሰማ ጐሹን አመስግነው በአባታቸው ምትክ አሰሩዋቸውና አባታቸውን ደጃች ጐሹን ፈተው ለቀቁላቸው።

አዝማሪም «እኛ የተማርነው ሊቃውንቱ ሳናውቅ

ተሰማ ለአባቱ ተሰዋ እንደ ይስሐቅ።» ብሎ ገጠመላቸው። ራስ አሊም ጥቂት ቆይተው ተሰማ ጐሹን ፈትተው ለቀቁዋቸው። ደጃዝማች ብለውም በቡሬና በአገው ላይ ሾመዋቸው። በኋላም ራስ አሊ ከደጃች ካሣ ጋር ተዋግተው ድል ሆነው ማምለጫ ቀዳዳ አጥተው በተጨነቁበት ጊዜ ከዚያ ጭንቅ አውጥተው የጁ ድረስ ሸኙዋቸው።

ጐጃሞች በአስማት ተግባር እውቅ ነበሩ ይባላል። አለቃ ተክለ ኢየሱስ እንደጻፉት በጐሹ ዘመን የተፈፀመ ለማመን የሚያስቸግር አንድ አስደናቂ ታሪክ አለ። አለቃ አርአያ የሚባል አስማተኛ ይልማ አማኑኤል ከሚባል አገር ጐጃም ውስጥ ይኖር ነበር። የውላ ከሚባል አገር የአንድ ሰው ሚስት በውሽምነት ይዞ አስማት እየደገመ ማታ ማታ ወደ ቤቱ ያመጣት ነበር። አንድ ቀን አውሬ እንዳይበላት የሚከላከለውን ድግምት ሳይደግምባት ቀርቶ በጭለማ ወደ አለቃ አርአያ ዘንድ ስትመጣ ሳሴ ከሚባል መንደር ስትደርስ ጅብ በላት። አባትና እናትዋ፤ ባልዋም ሆነው ደንበጫ ሄደው ለደጃዝማች ጐሹ አቤት አሉ። ደጃች ጐሹም «ተጩሆብሃልና መጠተህ መልስ ስጥ» ብለው ወደ አለቃ አርአያ መልዕክተኛ ላኩ። አለቃ አርአያም በአስማታቸው ኮርተው «አልመጣም» ብለው መልስ ሰጡ።

ደጃች ጐሹም «አስማቱ ሲያድነው አያለሁ» ብለው እጃቸውን ይዞ የሚያመጣ ጭፍራ ላኩባቸው። ይህን ነገር አለቃ አርአያ በሰሙ ጊዜ በቤታቸው አጥር ዙርያውን እፀ መሰውር መድፍነ ዓይን ገደሙና ረጩ። ከደጃች ጐሹ የተላኩት ወታደሮችም የአለቃ አርአያን ቤት ማየት አቅቷቸው ባላገሩን ሁሉ አሳዩን እያሉ ሲገርፉና ሲያምታቱ ቆይተው ቀኑ ሲመሽ ወደ ደጃች ጐሹ ተመለሱ። «ከነቤቱ ተሰውሮ ጠፋብን» ብለውም ነገሩ። ደጃች ጐሹም «እርስ በርሳችሁ እየተስማማችሁ ነው እንጂ ቤቱ ተሰውሮ አይደለም» ብለው ራሳቸው ለመሔድ ተነሱ።

«የደጃች ጐሹ መኳንንትም «ያዋርደናልና አንሒድ። ባይሆን ባይሆን ታማኝ ሰው ሔዶ ይያዘው» ብለው ቢያማክሯቸው «አይሆንም። ሰምው አላምንም» ብለው ጉዞ ጀመሩ። አማሬ ኢየሱስ ከሚባል ቦታ ሲደርሱ አለቃ አርአያ እንደመጡባቸው ሰምተው የደጃች ጐሹ ነጋሪት እንዳይጮህ ድምጥ የሚዘጋ አስማት ደገሙ። ነጋሪት እያስመቱ መለከት እያስነፉ የሚጓዙት ደጃች ጐሹ ድንገት ነጋሪቱም የመለከቱም ድምጥ ዝም አለ። ሠራዊታቸውም

ደንገጠ። መኳንንቱም ደጃች ጐሹ ዘንድ ቀርበ «ይሄን ጉድ አየን። ሌላ ሳይመጣ ይህን ጊዜ እንመለስ። በሌላ ቀን በድንገት አዘንግተን ለሌት እንይዘዋለን» ብለው መክረው ተቆጡና አስይዘው ገርፈው ዋሚት ዋሻ ከሚባለው ቦታ አሰሩዋቸው። አለቃ አርአያም በዚያ በታሰሩበት ቦታ ሆነው የሰው ሚስት ቀምተው አውሬ ባስበሉበት ተፀፀቱ። የአስማታቸውንም መዘገብ በእሳት አቃጥለው ሞቱ። «......የአለቃ አርአያ ደቀ መዛሙርት አለቃ አስረስ ደብተራ ሕፃነ ማርያም የሚባሉ ብዙ አስማተኞች ተተክተው ይልማ አማኑኤል ነበሩ......» በማለት አለቃ ተክለ ኢየሱስ ይተርካሉ።

በዚሁ በደጃች ጐሹ ጊዜ ብላታ አይከል ዲዱ የሚባሉ ሀብታም ሰው ነበሩ። እኚህ ሰው ሞገስ የሚባል ሥልጣን አሽከር ነበራቸው። አንድ ቀን ሞገስ ከውጭ መጥቶ ምሳውን ሊበላ ሲል ጌታው ብላታ አይከል ጠሩትና ምሳውን ሳይበላ አፍጥነው ወደ ደጃች ጐሹ ወደ ቡሬ ላኩት። ሞገስም ምሳውን ሳይበላ በመላኩ ተናዶ ጌታውን ሊጐዳ ፍለገ። ደጃች ጐሹ ዘንድ ሲደርስ ይላተላከውን «መጥተው ድግሴን ይብሉልኝ ብለዋል» ብሎ ነገረ።፡ ደጃች ጐሹም እውነት መስሏቸው «ምን አሳሰበው። እሺ እመጣለሁ» ብለው መለሱለት። ሞገስም ወደ ጌታው ተመልሶ «ደጃች ጐሹ ሊመጡ ነውና ተሰናዱ»ብሎ ነገረ። ብላታ አይከል ያላሰቡትን ነገር ሲሰሙ ደነገጡ። የሞገስንም ተንኮል አውቀው «ሞገስ? አንድ እንጀራ ብነፍህ ሺ እንጀራ ልታስከፍለኝ ነው? «ቢሉት ሞገስ ተንኮለኛ ነበርና «የላኩኝን ነው የተናገርሁት እንጂ ሌላ አልተናገርኩም» አለ። ብላታ አይከልም የተናገርሁት እንጂ ሌላ አልተናገርኩም» አለ። ብላታ አይከልም ቢቆጡትም ሆነ ቢገርፉት ደጃች ጐሹ የሰሙ እንደሆነ እንደሚጣሉዋቸው አውቀው «ሲበሉ የላኩት ማለት አንተ ነህ። ፍርድ የለብህም። በደለኛው እኔ ነኝ። ምሳህን ሳላበላህ መላኬ ጥፋቱ የኔ ነው» ብለው ለደጃች ጐሹ ግብዣ ድግሳቸውን መደገስ ጀመሩ።

ደጃች ጐሹ እመጣለሁ ያሉት በቅርብ ቀን ስለ ሆነ ብላታ አይከል ጠላም ሆነ ጠጅ ለማስጠመቅ ጊዜው አጭር ሆነባቸው። ከዘመድ ከወዳጅ መላክተኛ እየላኩ ጠላና ጠጅ አሰባሰቡ። በቤታቸውም አምሳ ምጣድ አስጥደው ቶሎ ቶሎ እየተባለ አንድ ሺ እንጀራ ተጋገረ። የተሰበሰበውም ጠጅ ሶስት ጋን ሞላ። አምስት ሰንጋ አሳርደው ደጃች ጐሹ ሲመጡ ታላቅ ግብር አበሉ። ደጃች

ጐሹም ከዚያው ከብላታ አይከል ቤት አድረው በማግስቱ ሊሔዱ ሲነሱ «ምን ፈለገህ እንው እንዲህ አስበህ የጠራኸኝ?» ብለው ብላታ አይከልን ጠየቁ ብላታ አይከልም የሞገስን ተንኮል አጫውቷቸው። ደጃች ጐሹም ስቀው በድንገት ይሄን ያህል ድግስ በመገኘቱ ተደንቀው ብላታ አይከልን ሸልመው ሔዱ።

ደጃች ጐሹ ደግ ሰው ስለ ነበሩ አዝማሪ

«የደጃ ጐሹ ሞግዚት፥

እህል አታቀምስ በጊዜያት።

ይተዋት ትቅርብዎ፥

ኣንትም አትሆንዎ።» ይላቸው ነበር።

# ምዕራፍ 3

# የጐጃምና የሰሜን ጦርነት

ወደ አላማችን ወደ ደጃች ካሣ ትረካ እንመለስና ካሣ አሁን የቀሩዋቸው ጠላቶች የሰሜኑ ደጃች ውቤ የጐጃሙ፥ ብሩ ጐሹ የሸዋው ኃይለ መለኮት ናቸው። እነኚህም ታላላቆቹ ጠላቶቻቸው እንጂ ሌላው ትናንሹ በብዛት ነበር። ካሣ አይሻል ላይ ራስ አሊን ድል ካደረጉ በኋላ ብሩ ጐሹን ግባ ብለው ላኩባቸው ደጃች ብሩም ስቀው ከዚያ በፊት በደጃዝማች ላይ የደረሰውን መጉላላት ያውቃሉና «ለካስ ተዘንብሏል ይሄ ሁሉ ጠጅ» የሚል አንድ መስመር የግጥም ስንኝ ወደ ደጃች ካሣ ላኩ።

ደጃዝማች ካሣም የግጥሙን አንድ መስመር እንደ ሰሙ «እኔ ተጠጥቷል መስሎኝ ነበር እንጂ»። ማለቱ ነውኮ ብለው ባለፈው ተግባር ያለ መፀፀታቸውን ለመግለጽ ጭምር፥

«አይዋጋም እንጂ ጠመንጃ ተኩሶ

አይዋጋም እንጂ ዘብ ይዞ ገስግሶ

ወትሮም ልማዱ ነው ጐጃሜ ለለቅሶ» ብለው ወደ ደጃች ብሩ ላኩ።

ከዚህ በኋላ ብሩ ጐሹን ለመፈለግ ወደ እነብሴ ሔዱ። ቋሚ ጨርቅ ከተባለ ቦታ ሠፍረው ሳለ አንድ ቀን ግብር ላይ ደስታ የሚባል አሽከራቸው ተነስቶ ፎከረ ደስታ በብዙ የጦር ሜዳዎች ብቹ የጀግንነት ተግባር የሠራ ነው። ሲፎክርም «እንኳን ያንተን ፊት እኛን የአሽከሮችህን ፊት የሚያይ አለን?» ባለ ጊዜ ደጃች ካሣ በአነጋገሩ ልባቸው ተነክቶ ጠጅ ይጠጡበት የነበረውን ብርሌ ወረወሩት ብርሌዋም ከፊታቸው ካለ የእንጨት ገበታ ጋር ተጋጭታ ሳትሰበር ዳነች ገበታው ግን ተሰበረ። ወዲያውኑ ተነስተው «እኔ የክርስቶስ ባርያ። ክርስቶስን ከያዝሁ ግን ማን ከፊቴ ይቆማል» ብለው ፎከሩ። ፉከራቸውን ጨርሰው ሲቀመጡም አሽከር ብርሌ አንስቶ ጠጅ ሞልቶ ሰጣቸው።

ደጃች ካሣ የብርሌይቱን ያለመሰበር አይተው ከተቀመጡበት ተነስተው «ማና ይቻልሃል ጌታዬ ሆይ ቸሩ እግዚአብሔር የሚሰበረውን አድነህ የማይሰብረውን ሰበርክ ኃያል አንተ ነህ» ብለው ሰግደው ተቀመጡ። በብርሌዋም የተቀዳላቸውን ጠጅ ጠጡ። ይህን የብርሌዋን ያለመሰበር ያዩት ካሣ የኃይል ብዛት ዋጋ እንደሌለው አስበው ሠራዊታቸውን እየመሩ ወደ ደብረ ፋራን ተሻገሩ። ካሣም ጐጃም ገብተው ሁለት ወር ያህል ተቀምጠው የብሩን ሁኔታ ይከታተሉ ጀመር። ደጃዝማች ብሩ ጐሹም ስንቃቸውን አዘጋጅተውና ይዘው ሶማ ገቡ።

ደጃዝማች ካሣ ሶማን ከበው ተቀመጡ። አንድ ቀንም አሽከራቸውን ወደ ደጃች ብሩ ልከው «የፈረስዎን ስም አባ ዳምጠውን ለኔ ይተውልኝ። ይህ ባይሆን ደግሞ ሌላ መልካም ስም ለፈረሴም ያውጡልኝ» ብለው በአክብሮት ላኩባቸው። ደጃዝማች ብሩም ትዕቢተኛ ነበሩና «ተንጓለል በለው» መልሱን ላኩ። ካሣ ይህን ሲሰሙ ተናደዱ። ጠጉራቸውንም ነጩ ሶማ የገቡትን ደጃች ብሩን ለመያዝም ሆነ ጦርነት ለመግጠም ስፍራው ፈጽሞ የማያመች ስለነበር ካሣ ሶማን ትተው ወደ ሜጫ ሔደው ይጠባበቁ ጀመር። ብሩ ጐሹም የካሣን መራቅ እንደሰሙ ከሶማ ወጡ። የብሩ ጐሹን ከሶማ መውጣት የሰሙት ካሣ ሌሊት በጨረቃ እየገሰገሱ ሲደርሱባቸው ደጃች ብሩ አምልጠው በቻልቃት

ተሻግረው በደራና በጃርሶ አድርገው ብሩ አምልጠው ደጃች ካሣም ተከታትለው በድብቅ አልባሶ ደረሱ።

ደጃች ብሩ በኩታይ ወደጃቸው የሆነ አንድ ኦሮሞ ነበርና «ደጃዝማች ካሣ የት እንደደረሱ ሰልለህ ንገረኝ» ብለው ላኩበት። በዚያ ያለው የኦሮሞ ብሔረሰብ በሙሉ በካሣ መወረሩን ፈርቶ ነበርና የደጃች ብሩ ወዳጅ የነበረው ኦሮሞ ከደጃዝማች ካሣ ጋር ተባብሮ ለተላከበት መልዕክተኛ «ጦርም የለ። ደጃች ካሣም አልመጣም» ብለው መልስ ላከላቸው። ደጃች ብሩ ይህን ሲሰሙ አገር ሰላም ነው ብለው ሲዝናኑ ደጃች ካሣ ድንገት ደረሱባቸው። ደጃች ብሩ የሠፈሩት ጀንዳና ጨንገር መሀል ነበር። ካሣ ምርጥ የሆኑ ጥቂት ወታደሮች ይዘው ባካባቢው ካለው የበቆሎና የማሽላ ሰብል ውስጥ ገብተው ተደበቁ። በዚያም አድፍጠው ሲጠባበቁ የደጃች ብሩ የጦር መኮንን (አዛዥ) አምባው ስላም ነው ብሎ የማዕርግ ልብሱን ለብሶ በፈረስ ሆኖ ታጅቦ ካሣ በተደበቁበት ሰብል አጠገብ ሲያልፍ ካሣ በድንገት ከተደበቁበት ወጥተው በሽጉጣቸው ጥይት ራሱን መትተው ጣሉት። የጦሩ አዛዥ እንደ ወደቀ ካሣ ቶሎ ብለው የአዛዡን በደም የተነከረ ልብስ ገፍፈው በጦራቸው ላይ ሰክተው ይዘው በደጃች ብሩ ሠራዊት መሀል ገብተው «አዛዥህ ሞቷልና ተማረክ» እያሉ አሸበሩት። ሠራዊቱም የአዛዡን በደም የተነከረ ልብስ በማየቱና አዝማቹ መሞቱን ባወቀ ጊዜ አብዛኛው ሳይዋጋ ሲሸሽ የተቀረውም ተማረከ። በተለይም የደጃች ብሩ ድል መሆን ዋና ምክንያት የሆነው የደጃች ብሩ ሠራዊት ከደጃች ካሣ በመሸሽ ጌታውን እየተከተለ አገር ለአገር መዞሩ ሰልችቶት ነበርና ከካሣ ጦር ጋር ምንም ሳይዋጋ ለግንቦት 19 ቀን ጌታውን አስያዘዘ።

ደጃች ብሩ እንደ ተያዘ ካሣ ወደ ጐጃም ተጓዙ። የብሩ ጐሹ ሚስት ወይዘሮ የውብዳር ጅብላ ከሚባለው አምባ መሽገው ነበርና ካሣ የየውብዳርን ወንድሞች ደጃች ኃይሉን ደጃች ይማምን ባላቸውን ደጃች ብሩን ጐሹን ከፊት አስቀድመው «አምባውን ልቀቁ አለቅም ካልሽ ያው ከፊት ናቸውና ወንድሞችሽን ግደያቸው» ብለው ላኩባቸው። ወይዘሮ የውብዳርም «ለባሌ ለብሩ አይሰጡኝ እንደሆነ አምባአውን ይቀበሉኝ» የሚል መልስ መለሱ። ካሣም በየውብዳር ጣያቄ ተስማምተው አምባውን ተረከቡ። ከአምባውም ብዙ ጠመንጃና ምንጣፍ ብርሌና ሌላም ዕቃ ሁሉ ተገኝቶ ተማረከ። ደጃች ካሣም በአምባው ብላታ ደስታን ሾመው ደጃች ብሩን ይዘው ጉዞ ጀመሩ።

አምባ ጫራ ሲደርሱም ደጃች ብሩን ሣር አምባ እንዲታሰሩ አደረጉ። በጐጃምም ተድላ ጓሉን የጦር አዛዥ ባላምባራስ ወልታን ምስለኔ አድርገው ሾሙ። ይህን ካደረጉ በኋላ ካሣ ወደ ደብረ ታቦር ጉዞ ጀመሩ። በጉዞውም ጊዜ የጐጃም ባላባት ልጆች የሆኑትን የደጃዝማች ጐሹን ልጆች የሌምቱ ጐሹን ይልማ ጐሹን ንጉሴ ጐሹንና ተሰማ ጐሹን በዘበኛ እያስጠበቁ ፊት ፊት አስቀድመው ይጓዙ ጀመር። ይህን ጉዞ የተመለከተው ሸናሻ አብተው የተባል አቅራሪ

«አምባ ቢጠበው ሰንሰለት ቢያንሰው
አንድ አርጎ አጓዘው የጐጃምን ሰው።
ብሩ ጨው አድርገህ ከመነዘርከው

ውቤን ጫማ አድርገህ ሸዋን ክፈተው» ብሎ አቅራሪ ይህ ግጥም ውቤን ረግጠህ ጣልና ወደ ሸዋ ዝመት ለማለት ነው። ምክንያቱ በአሁኑ ጊዜ የቀሩት ታላላቅ ጠላቶች የሰሜኑ ወይም የትግራይ ገዢ ደጃች ውቤና የሸዋው ኃይለ መለኮት ብቻ በመሆናቸው ነው።



የአጤ ቴዎድርስ ምሽግ (መቅደላ)

ደጃዝማች ካሣ ወደ ደጃች ውቤ ለመዝመት በሐሳብ ላይ ሳሉ በጐጃም የሾሙዋቸው ደጃዝማች ተድላ ጓሉ የካሣን መራቅ አይተው ሸፈቱባቸው ተድላ ጓሉ የሸፈቱበት ምክንያት ካሣ የጐጃምን የባላባት ዘሮች ሁሉ ሊያስሩ ነው የሚባል ወሬ ስለ ተሰማ ነው። በዚህ ባልተረጋገጠ ወሬም ተድላ ጓሉ ሊሸፍቱ አላሰቡም ነበር። አንድ ቀን ግን በመኳንንቶች ዘንድ ሁሉ በአዝማሪቱ ተዋቂ የሆነው ጐጃሜው ሊቀ መኳስ መርሻ ከደጃዝማች ተድላ ጓሉ ሠፈር ሌሊት ገብቶ

«እናንተ የጐጃም መኳንንት

ጭቃ አይነካችሁ በክረምት።

በአገራችሁ በወንዛችሁ

ወየው ወየው እብራችሁ።

አልተከልኩ እንኳ ተጓሮዬ

ዱብ አለ መከራዬ» እያለ በማሲንቆ በማዝመሩ ተድላ ጓሉ ጉዳዩ ገብቷቸው ከዱ። «ወየው በራችሁ» ማለቱ እንደ ጧፍ ልትነዱ ነው ማለቱ እንው። ተድላ ጓሉም ዛሬ ደብረ ማርቆስ ከተባለው ከተማ መንቆረር ገብተው ሠፈሩ። ዕድሌን ልሞክር ብለውም ራሳቸውን ደጃዝማች ብለው በጐጃም የበላይ የሌለባቸው መሆኑን አሳወቁ። ደጃዝማች ካሣ የሾሙዋቸውንም ሾሞች እየዞሩ የራሳቸውን ሰዎች ሾሙ።

ደጃች ተድላ ጓሉ ሸፍተው በጐጃም ሹም ሽር ቢያደርጉም የደጃዝማች ካሣ ድንገተኛ አመጣጥ የማይታወቅና አደገኛም ስለሆነ በግዛታቸው ዙርያ በየበሩ ጠባቂ አስቀምጠው ነበር። እነኚህም ጠባቂዎች ከካሣ ጋር እንዲዋጉ ሳይሆን የካሣን መምጣት ጠብቀው እንዲነግሩ የተዘጋጁ ነበሩ።

ካሣ ግን የተድላ ጓሉን ሸንፈትና የጐጃምን መያዝ ቢያውቁም ተድላን አቆይተው ትልቁን ተቀናቃኛቸውን ደጃች ውቤን ለመምታት አሰቡ። ደጃች ውቤን መጀመሪያ በሰላም መንገድ ለመጠየቅ ብለው ጐንደር ላይ እንደሆኑ እንዲገብሩላቸው አስጠየቋቸው። ደጃች ውቤም «ኧረ አንተ ማነህና ነው እኔ የምገብርልህ?» ብለው መልስ ላኩባቸው። ደጃዝማች ካሣም ለተላከባቸው

መልዕክት ሲመልሱ «የጐልያድንና የዳዊትን ታሪክ ይመልከቱ። ጥጋብዎን ለማብረድ በቅርብ ቀን እመጣለሁ» ብለው ላኩ።

ደጃዝማች ካሣ ሠራዊታቸውን በሚገባ ካደራጁ በኋላ የግዛት ወሰናቸው ወደ ሆነው ወደ ሰሜን ተራራ ተጓዙ። ደጃች ውቤም ጀግና የሆነ ሠራዊታቸውን አስከትለው ሰሜን ተራራን ወጥተው ኃይለኛ ብርድ ካለበት ቧሒት ተራራ ላይ ሠፈሩ። ደጃዝማች ካሣ የካቲት 3 ቀን 1845 ዓ.ም ሰሜን ተራራ ደርሰው ሠፈር እንደተደረገ ባጠገባቸው ያለውን ጆን ቤል የተባለውንን እንግሊዛዊ «እስቲ በመነጥር አይተህ ንገረኝ» አሉት። ቤልም «የሸማ ድንኳን ተተክሎ ይታየኛል» አላቸው። ደጃዝማች ካሣም «አያሳድረኝ ባሳድረው» ብለው ፎክረው ተነሥተው ሠራዊታቸው ተነስ አሉ። ሠራዊቱም ተነስቶ ሲሰበሰብ ካሣ ከፍ ካለ ሥፍራ ቆመው «እንኳን ይህን ቁርጥማታም ወሎ መትቼ ተሻግሬ የሸዋን ንጉሥ እይዘዋለሁ። ሰሜን ሰሜን እነግርሃለሁ ያልሁህ ስሜ ቴዎድሮስ ነው አይዞህ የውቤ ነፍጥ የውቤ ነፍጥ ቢሉህ አትፍራ። የተለጐመው ጨርቅና ባሩድ ነው። አይነካህም። እኔ የክርስቶስ ባርያ ሁሉንም አሳይሃለሁ።» ብለው ሠራዊታቸውን ሸኙት። ሠራዊቱም ከደጃች ውቤ ሠራዊት ጋር ገጥሞ ከፍተኛ ውጊያ ተደረገ። በመጨረሻም ድሉ የቴዎድሮስ ሆኖ ደጃች ውቤ ተያዙ። የተረፈው የደጃች ውቤ መኳንንትም ደረስጌ ማርያም ገብቶ ተማጠነ። ቴዎድሮስም «ደረስጌ ማርያም የገባውን የደጃች ውቤን ሰው ምሬዋለሁ» ብለው አዋጅ ነገሩ።

ይህ ጦርነት ከተካሔደ በኋላ የደጃች ውቤ ልጅ ደጃዝማች ጓንጉል ሠራዊቱን አሰልፎ ነጋሪቱን እያስመታ አባቱን ለመርዳት ደረሰ። መኳንንቶቹ ቀርበው «አሁን ሁሉም ነገር አልቋልና እንመለስ» ቢሉት «የጫንኩትን አረር እንደ በረዶም ሳላራግፍበት ፈርቼ አልመለስም» ብሎ ጦርነት ገጠመ። ግን ውጊያው ብዙም ሳይቆይ ጓንጉል ድል ሆኖ ሸሸ።

ቴዎድሮስ ደጃች ውቤን አስረው «ገንዘብዎን ያምጡ» ቢሏቸው «ገንዘቤ ሁሉ የደረስጌ ማርያምን በመሥራት ጨርሻለሁ ከየት አመጣልሁ» አሏቸው። ቴዎድሮስም የደጃች ውቤ ዕቃ ወዳለበት ሀይ ወደተባለው አምባ ሔዱ። የደጃች ውቤ ዕቃ የተቀመጠው ቤቴል ከሚባለው ሥፍራ ነበር። ከዚያ ሲደርሱ የውቤ ልጅ ደጃዝማች ጓንጓል በአባታቸው መታሰር ምክንያት አዝነው

ስለ ነበር ቴዎድሮስ መምጣታቸውን ባወቁ ጊዜ «አባቴን ከእስራት ይፍቱልኝ እንጂ ገንዘባቸውን አስረክባለሁ» ብለው ቀርበው አመለከቱ። ወዲያው ዕቃውም የተቀመጠበትን አምባ አስረከቡት። በዚያም «እጅግ በጣም የበዛ ወርቅና ብር ብርጭቆ ብርሌ ሁለት መድፍ ከነጥይቱ 500 ጠመንጃ ሁለት ጋን ሙሉ የልብስ መስፊያ መርፌ ተገኘ» ብለው አለቃ ወልደ ማርያም ሲጽፉ ዱፍተን ግን 40.000 ጥሬ ብርና 7.000 ጠመንጃ መማረኩን ጽፏል። ከዚህ ከተገኘው ገንዘብ ለመኳንንቱና ለወታደሩ እንደየማዕረጉ ከአሥር ብር እስከ ሽህ ብር እያንዳንዱ ተሰጠው። ደጃች ውቤ «ገንዘቤን ሁሉ የደረስኜ ማርያምን በመሥራት ጨርሼዋለሁ» ያሉት እውነታቸውን ነው። ቤተ ክርስትያኒቷን ያሠሩዋት ሹምፐር በሚባል ጀርመናዊ ነው። የውስጡን ስዕሎች የሳለው ዛንደር የሚባል ጀርመናዊ ሰዓሊ ነው።

## ምዕራፍ 4

# ደጃዝማች ብሩ ጐሹ - ደጃዝማች ውቤ ብሩ ጐሹ

ስለ ደጃዝማች ብሩ ጐሹ ፕላውዲን ሲጽፍ «.......አፍንጫው እንደ ሮማውያን ቀጥ ያለ ሲሆን ጠጉሩ ከግንባሩ ገለጥ ብሎ መሀል ራሱ ድረስ ነው። እንደሚሉትም እንዲህ ያደረገው ሽቶ ነው። ሌላው ጠጉሩ ግን ጥቁር ሆኖ ያጐፈረና ውበት የሚሰጥ ነው።....... አመለካከቱ ኃይለኛ ነው........ ሲናገርም ረጋ ብሎ ነው። ፊቱ ጥቁር ሆኖ ጨፍጋጋ ነው።........» ይላቸዋል።

ፕላውዲን ከአገሩ እንደመጣ ከበሩ ዘንድ ደርሶ በዚያ ከርሞ ነበር። ከእሳቸው ዘንድ በነበረበት ጊዜ ያየውን ሲጽፍ «......ከድንኳኑ ውስጥ ስገባ ብሩ ከመሬት ቁጭ ብሎ አየሁት። ከእርሱ ጋር አንድ ጠጉራቸው ነጭ የሆነ ሽማግሌ ሰው አሉ። አጠገቡ ለመድረስ አምስት ያርድ ያህል ሲቀረኝ አጋፋሪው በያዙት አጭር በትር እንድቆም አመለከቱኝ። ብሩም እንደተቀመጠ በፀጥታ ይመልከተኝ ጀመር።

«.......ስለንግሥታችን አንዳንድ ነገር ጠይቆኝ ስመልስለት በጣም ሳቀ። የሳቀውም በተሰባበረ በአማርኛ አነጋገሬ ነው። እንድቀመጥም ጋበዘኝ።

.......ለሱ ያመጣሁትን አሮጌ የፈረሰኛ ሰይፍ፥ ያስያዝኩት አሽከሬ እንዲያመጣ አዘዝሁት። ብረቱ ግን በጣም ሩ ብረትና የተወለወለ ነበር።.......ሲያየው ተደሰተ። በእጁ ግን አልነካውም።........ ምግብ ቀርቦልኝ ስበላም ብሩ አበላሌ ደካማ መሆኑ ገባው። ጠጅ መጥቶልኝ ስጠጣ አይቶ እንደ ሰው ትጠጣለህ አለኝ።........ ለሌሊት የሚሆነኝም አንድ ገንቦ ጠጅ አዘዘልኝ።....... ሁለት ባልደረቦችም ሰጠኝ። አንደኛው ባልደረባዬ አዛዡ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አጋፋሪው ነው። አዛዡ ለምግብና ለአስፈላጊዬ ነገር ሁሉ እንዲሆን የተሰጠኝ ሲሆን አጋፋሪው ደግሞ ወደሱ ዘንድ ስሔድ ለማስገባትና መልዕክት አስልከውም እንዲነግርልኝ ነው።

«......በማግስቱ ተጠርቼ ወደ ድንኳኑ ሔድሁ ድንኳኑን 70 ጫማ ያህል ርዝማኔ ኧልው። ያ የሰጠሁት ሰይፍ ተመዝዞ ተቀምጦ አየሁ።...... እንደተቀመጥሁ አንድ ብርሌ ጠጅ ተሰጥቶኝ ስመለከተ ጥበበኛው ሠራተኛ እሳት አያይዞ የሰይፉን እጀታ አወለቀው። የተሻለ ከአውራሪስ ቀንድ የተሠራ እጀታም አገባለት። ይህ ሁሉ ተግባር የተከናወነው በአምስት ደቂቃ ውስጥ ነው።...... በሳምንቱም ፈረስ ጉግስ ጨዋታ ላይ ያን ሰይፍ ይዞ ለሕዝብ ሁሉ አሳየ።

«አረብ ወይም ቱርክ አለመሆኔንና እንግሊዛዊ መሆኔን ነገርኩት። እሱም ይህን ባለማወቁ ይቅርታ ጠየቀኝና ‹ታዲያ ስምህን ማን ብዬ ልጥራህ› አለኝ። እኔም ስሜን ነገርኩ። በትትክል ለመጥራት ስሜ አስቸጋሪ መሆኑን ነገረኝና እንዲያው «እንግሊዝ» እንዲለኝ ተስማማን።

«......አንድ ቀን ማታ በጭለማ ተጠራሁ። ደርዘን ከሚሆኑ ሹማምንቶች ጋር ተቀምጦ መጠጥ ሲጠጣ ደረስሁ። ተራራ ላይ አስሮት የነበረው ደጃች መርሶ (የአሊ ሹም) ከታሰረበት ከተራራው መጥተዋል።........ መርሶ ወጣትና ቆንጆ መልክ ያለው ነው። ቁመናውም ደስ የሚል ነው። ቀኝ እጁን በሰንሰለት ታስሮ ግራ እጁን ከታሠረ ከአንድ ታማኝ አሽከር ጋር አንድ ያርድ ያህል ርዝመት ባለ ሰንሰለት ተቆራኝተዋል። ይመር ሣህሉንም ከዚያው አገኘሁት። ሆዳምና በአገሪቱ ያለ መልከ ጥፉ ሰው እሱ ብቻ ነው። የድንኳኑ ውስጥ መብራት ደብዛዛ በመሆኑ ብዙም አይታየኝም። የሚበራው ሁለት ጧፍ ነው።

እያንዳንዱም ባንዳንድ ሰው ተይዞአል።....... ጥቂት ቆይቼ ቀስ ብዬ ሹልክ ብዬ ወጣሁ።

«በማግስቱ ብሩ በደህና መንፈስ ነበር። በዕለቱ የጉግስ ጨዋታ ነበርና በዚያ ቦታ ሁላችንም ተገኝተን ነበር። ብሩ በፈረስ እንደመጣ የጉግሥ ጨዋታው ተጀመረ። ጨዋታው አልቆ በፈረሱ እንደሆነ ወደ ድንኳኑ ሲሄድ ሌሎችም ተከትለውት ሔዱ። በአዳራሽ ግብር ተዘጋጅቷል። በብሩ ድንኳን ውስጥም ገበታ ተዘርግቷል። በገበታዎቹ ላይ በሺ የሚቆጠር የጤፍና እይ ሌላም እህል እንጀራ ተደርጓል። እኔ ስገባ ታላላቅ መኳንንቶች ከመስፍኑ አጠገብ ከመሬት ተቀምጠዋል። እሱ ግን የተቀመጠው ድንክ አልጋ ላይ ነው። ጕራዴውን የያዘው አሽከር ከኋላው ቆሟል። ሌላው አሽከር ደግሞ ጋሻውን ከጣምራ ጦሮች ጋር ይዞ እሱም ከበሩ ኋላ ነው።

«አምስት ይሁን ስድስት የሚያማምሩ የመኳንንት ልጆች በአንገታቸው ዙሪያ የብር አሸን ክታብ ያደረጉ ዙሪያውን ቆመዋል። አንድ ትልቅ ሰው ብሩ ከተቀመጡበት አልጋ አጠገብ ሆኖ ዝንቦች እንዳያርፉበት ጭራ ይዞ ይከላከላል። ብርሌውን የሚቀበልና ትእዛዙን የሚነግር አንድ አሽከር ደግሞ ከአጠገቡ አሉ። ሁለት ይሁን ሶስት አለቆች ዘንጋቸውን ይዘው ግብር በይውን ያጋፍራሉ። በትልልቅ ጋን የተቀመጠውን ጠጅ ሴቶች ይሰጣሉ። አሳላፊዎች በብዙ መቶ የሚቆጠሩ መጠጫ ዕቃዎች ያድላሉ። ከጐሽና ከሌላ ቀንድ የሚሠራው ዋንጫ ለወታደሮች ይሰጣል። ለታላላቅ ሰዎች የሚሰጠው ግን ብርሌ ነው። የወጥ ቤት ሴቶች እያንዳንዳቸው ድስት እየያዘ ገብተው ለማቅረብ የተዘጋሁ ሥጋ ቤቶችም 30 ይሁን 40 ከብት አርደዋል።

«በግብሩ ላይ መጀመሪያ የደረሰው ሥጋ ለመኳንንቶች ቀረበ። ቢለዋም ሁሉ ተሰጠ። እያንዳንዱ ሰውም ሥጋውን ይዘው ከቆሙበት አሽከሮች ላይ የቻለውን ወይም የሚያስፈልገውን ያህል ይቆርጣል። እንጀራውና ጥሬ ሥጋው ተበልቶ እንዳበቃ ጥብስ ሥጋ ቀረበ። ተበልቶ ሲጠገብ ወይም ሊጠገብ ሲል ጠጅ ታደለ።.......ይህም የወታደሩ የመግቢያ ጊዜ መድረሱን ማሳወቂያ ነው። .......ወታደሩ በተራው ገባ። ለወታደሩ ሥጋ መብሊያ ቢለዋ አይሰጥም። ጥሬ ሥጋ የሚበሉት ወታደሮች በያዙት ሾተል ወይም ጕራዴ ነው። ሥጋ የሚቆርጡት የሚያስገርመው ነገር ሥጋውን በአፋቸው ይዘው ሲቆርጡ አፍንጫቸውን ያለ መቁረጣቸው ነው።

«በዚህ ጊዜ ሁሉ ቂላቂል የሆኑ አጫዋች ሰዎች እየገቡ ታላላቆቹን ያስቁ ነበር። አዝማሪዎችም ራቅ ብለው ከዳር ሆነው ያጫውታሉ። ከውጭ ነጋሪት ይጐሸማል። የእምቢልታና መለከት ድምፅም ይሰማል። ፈረሰኞች ጦራቸውን ይዘው የጦር ልብሳቸውን ለብሰው በፈረስ ላይ እንደ ሆኑ እየሸለሉና እየፎከሩ ድንኳኑ በር ድረስ እየጋለቡ ደርሰው ይመለሳሉ።

«ፈረሰኞቹ ድንኳኑ ድረስ እየጋለቡ መመለስ ሲጀምሩ የድንኳኑ በር በሰፊው ተገለጠ። ፈረሰኞቹም እየጋለቡ ድንኳኑ ውስጥ ይገቡና ጦራቸውን ወርውረው አለቃቸው ፊት ከመሬት ይተክሉታል። ከዚያም ፈረሳቸው ላይ እንደሆኑ እንደሆኑ ጐራዴያቸውን መዝዘው ፈረሳቸውን እያንጐራደዱ ወይም ከውጭ ወደ ውስጥ ከውስጥ ወደ ውጭ እየጋለቡ ድንፍታ (ፉከራ) ይጀምራሉ። ፎካሪው ፎክሮ ሲያበቃም እጅ ነስቶ ይመለሳል። እንዲህ እያለም ተራ በተራ ይካሔዳል። በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ የጦር አለቆች የሚቀመጡት ከውጭ ነው።.......

«አንድ ቀን ጧት ማለድ ብዬ ወደ ብሩ ዘንድ ሔድሁ። ቀኑ የጦም ቀን ነበር። ብሩ ፊቱን አኮሳትሮ አየሁት። አልተደሰተም። የጅራፍ ድምፅ እሰማለሁ። ጅራፍ ባንድ ጥፋተኛ ጀርባ ላይ እንደ ሽጉጥ ይጮሃል። ጥፋተኛውም የቤት ውስጥ ሠራተኛ ወጣት (ባርያ) ሊያመልጥ ሲል ተይዞ ብሩ ዘንድ ቀርቦ 40 ጅራፍ እንዲገረፍ ተፈርዶበት ነው።....... ፍርፋቱን የሚቆጥረው ራሱ ብሩ እያየ ነው።.......የተፈረደው ግርፍ እንዳለቀም ወጣቱን ከብሩ ፊት አቀረቡት። ብሩ ከወጣቱ ጀርባ ላይ ያለው ስንጥቅጥቅ በቂ ስላልመሰለው እንደ ገና አስር ጅራፍ በተጨማሪ እንዲገረፍ አዘዘ።...... ይህም ሲያልቅ በኩርኩምና በጡጫ እየተደበደቡ ከድንኳኑ ውስጥ ተባረረ።....... ብዙ ብዙ የጭካኔ ሥራዎችን ይሠራል።.......

«ነገ ጉዞ እንደሚጀመር ተነገረን። ወዴት እንደምንሔድ ግን አልተነገረንም። እኩለ ለሊት ሲሆን የብሩ ሚስት በብዙ አጀብ ታጅባ ዓይነ ወጐችን ለመከላከል ፊቷን በልስብ ተሸፍና ጉዞ ጀመረች። የእሷም ድንኳን መነቀል ለሌላው ሁሉ የጉዞውን መጀመር የሚያበስር ነበር። ከመንጋቱ በፊት ፊታውራሪዎች ነጋሪት እያስጐሰሙ ጉዞ ጀመሩ። ከእነሱ በኋላ ብሩ ቀጠል። ጓዙ በሙሉ ከተነሳ በኋላ ደጀን የሚሆነው ሠራዊት ተነሳ። ወታደር ሴቶች

ልጆች ሽማግሌዎችና በጣም ብዙ የሆኑ ከብቶች ሁሉ በአንድነት መንገዱን ይዘው ይጓዛሉ።

«ማረፊያችን ቦታ ስንደርስ ትተነው ከመጣነው መንደር ጀምሮ እስከ አዲሱ መንደራችን ድረስ ተጓዡ የተቀጣጠለ ነበር። እኔም ከቀዳሚው ተጓዥ ጋር ነበርኩ። ከመንገዱ ዳር አንዲት ጥሩ ምንጭ አየሁና ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም አልኩ። ዓይኔን አሻግሬ ሳይ አምስት ወይም 600 የሚሆን ከጧቱ ፀሐይ ጋር እያብለጨለጨ አየሁት።

«የብዙ በቅሎዎች ኮቴ ይሰማ ጀመር። የነጋሪቱም ድምፅ እየቀረበኝ ሲሔድ በልዑሉ ዙሪያ የሚመታ መሆኑን አወቅሁ። ወዲያውም ልዑሉ መጣ። ግሩም የሆነ ሐር ቀሚስ ለብሷል። በራሱም ላይ ሻሽ አስሯል። ጉዞው ረጋ ያለ ነው። ሌሎች በቅሎዎች ከፊት ይሄዳሉ። አራቱ ተወዳጅ ፈረሶች ከኋላው ይከተላሉ።...... ዙሪያውን መኳንንቶች ጀግኖችና የሚያቀርባቸው ወዳጆቹ አሉ። አንዳንዶቹ ፈረሶቻቸውን ከፊት እያሳቡ እነሱ በሚያማምሩ በቅሎዎች ተቀምጠዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ በፈረስ ሆነው ጋሻ የያዙ  አሽከሮቻቸው በየበቅሎአቸው እየሆኑ ይከተሏቸዋል። አብዛኛው ጋሻ ከብር በተሠራ ጌጥ ያጌጠ ነው። ጊዜው የዓመቱ ጥሩ ወራት በመሆኑ አየሩ ግሩም ነው። ቀኑ እጅግ በጣም ጥሩ ቀን ነበር። ጧት ስለ ሆነ አልፎ አልፎ ከሳሩ ላይ ጤዛ ይታያል። .......

«ከሰፈራችን ደረስን። ከኛ ቀደም ብለው የደረሱት በሥራ ላይ ናቸው። ሁሉም የጌቶቻቸውን ድንኳን ይተክላሉ። አንዳንዶቹ ጐጆ መሥሪያ የሚሆን ሣርና እንጨት ያግዛሉ። እያንዳንዱ ሹም ድንኳን የብሩን እንኳን ከብቦ ከተተከለ በኋላ እያንዳንዱ ጭፍራ ሠፈሪ የት እንደሆነ ያውቃል። ሁሉም የየጌታውን ድንኳን የእከበበ ጐጆውን ይሠራል። በአካባቢው ያለው እርያና አውሬ ሁሉ ይባረራል። ለእሳት ማንደጃ የሚሆን እንጨት ይመጣል። ከጥቂት ሰዓታት በኋላ አዲሱ ሠፈራችን ልክ እንደ አሮጌው ሠፈራችን ሆነ።

«ሴቶችና ልጆች የያዙዋቸውን ድስቶች ምጣዶች የውሃ መቅጃ እንስራዎች ወፍጮዎችን እየያዙ ደረሱ። ወታደሮችም እንደ ታላላቅ አዳራሽ የሚያስቡዋቸውን ጎጆአቸውን ቁርበት በማልበስ ሠሩ። እንደ ደረስን ከልዑሉ ጋር ቁርስ በላሁ። እንደ ተለመደው ቁርሱ ጠጅና ጥሬ ሥጋ ያለበት ነበር።

ከዚያ በኋላ የኔ ሠፈርም ሶስት ጐጆዎች ተሠርተውባት አገኘኋት። ትልቁን ጐጆ መርጬ ያዝኩ።....... ማታ በየትናንሿ ሠፈራችን እሳት እያነደድን አደርን። በነገታው በዚያው ሁኔታ ጉዞው ተጀመረ። ጉዞአችንም ወደ ደቡብ አቅጣጫ ነበር። ስንጓዝ ቆይተን አባይ ወንዝ አጠገብ ካለ መንደር ሰፈር አደርን። ብሩ በአካቢው ላለ የጋላ አለቃ መልዕክተኛ ላከ። በሳምንቱም ለሳሳ ፈረሰኛ አምጥተው ገበሩለት።.......በጉዞ ላይ ትልቁ ድንኳን ከተተከለ በዚያ ቦታ ጥቂት ቀናት እንደሚቆይ ምልክት ነው።.......» ብሏል።

ደጃች ብሩ ያደጉት ራት አሊ ቤት ነው። አባታቸው ደጃች ጐሹ ከራስ አሊ ወዳጅ ነበሩና ብሩን በልጅነታቸው ለራስ አሊ ሰጡ። በዚያም በጥሩ ይዞታ ተይዘው ሳለ ጉርምስና ሲሰማቸው ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት ይመኙ ጀመር። ፕላውዲን እንደ ፃፈው በዚህ አሳባቸው «.......ጓደኞቻቸው ሁሉ ይስቁባቸው ነበር። ወይዘሮ የውብዳርን ዳሩላቸው። የባለነጋሪቱንም አገር ነፍሴን በግዛትነት ሰጡዋቸው።

አንድ ቀን በራስ አሊ ሠፈር ከራስ አሊ ጋር ጉግሣ ጋር ሲጫወቱ ዘንግ ወርውረው ራስ አሊን በዘንጉ ወጉዋቸው። በጉግስ ጨዋታ ደንብ በዘንግ መወጋት የሚችለው እኩያ ወይም የበታች ሲሆን እንጂ በማዕረግ የበላይ ከሆነ ወጋሁ ለማለት ዘንግን ዝቅ አድርጐ ማሳየት ነበር። ደጆች ብሩ ግን ዘንድ ወርውረው መስፍኑን ራስ አሊን ስለወጉ ራስ አሊ ተቆጡ። ብሩም ከቤታቸው ሔደው ታምሜአለሁ ብለው ተኙ።

ብሩ ታምሜአለሁ ብለው የተኙት ለምክንያት ያህል ስለነበር ማታ የሚያምኑዋቸውን ጓደኞቻቸውን አስጠርተው ሁሉም ባንድነት ለመጥፋት ተስማሙ። 21 ዓመት ዕድሜ የነበራቸው ብሩ ለኢሊቱን ከጓደኞቸው ጥቂቶቹ የብሩን ሚስት ይዘው በሌላ መንገድ ሲሔዱ ብሩ ደግሞ በሌላ መንገድ ወጥተው አመለጡ። በጨረቃ እያገሰገሱ ሔደው ከግዛታቸው ነፍሴ ገቡ። የብሩ መጥፋትና መሸፈት እንደታወቀ ራስ አሊ ሠራዊታቸውን አስከትለው ተከተሉዋቸው። ብሩ ግን ወደ ኦሮሞ አገር ገብተው ተደበቁ። ራስ አሊ ሲመለሱም ብሩ ጐጃም ገብተው ለማንም የማይገብሩ የጐጃም ገዢ መሆናቸውን አወጁ።

ራስ አሊም ጐጃም ድረስ ተከትለው ሔዱ። የራስ አሊን መምጣት ብሩ እንደ ሰሙ ከአባታቸው ምሽግ ሶማ አምባ ገቡ። የራስ አሊ ሠራዊትም ሶማ

አምባን ከብቦ የብሩን ሠራዊት መውጫና መግቢያ አሳጣው። በዚህ መሀል የደጃች ብሩ አሽከር የነበሩት ጀግናው ረምሐ ክንፉ ከሶማ አምባ ወርደው ከራስ አሊ ሠራዊት ጋር ገጠሙ። በጦርነቱም ከራስ አሊ ሠራዊት ብሩ ሰው አለቀ። ጀግናው ረምኃ ክንፉም በዚያው በጦርነቱ ሜዳ ላይ ሞቱ። ሬሳቸውንም የሚያነሳውን ጠፍቶ በዚያው በጦርነቱ ሜዳ ላይ ስላደረ ሌሊት ሬሳቸውን ብዙ ጅብ ተሰብስቦ ሲበላው አደረ።

ይህን የጀግናውን የረምኃ ክንፉን መሞትና በጅቦች መበላት ደጃች ብሩ ሲሰሙ አዘኑ። አምርረውም አለቀሱ። በገናቸውን አንስተው እየደረደሩ (እየመቱ) በለቅሶ ዜማ ቅኔ ተቀኙላቸው።

«ትናንት በገናውን እየደረ

ረምኃ ክንፉ በጅማት አደረ» ብለው አንጐራጐረ። ቅኔው በጅብ መዓት ተበላ ለማለት ነው። ሶማ አምባ ምሽግ ጠንክሮ የተሠራው ስለ ነበረ የራስ አሊ ሠራዊት አንድ ዓመት ያህል በከበባ ቆይተው ያለ ምንም ውጤት ወደ መጣበት ተመለሰ። የራስ አሊ ሠራዊት እንደተመለሰ ደጃች ብሩ ከምሽጋቸው ወጥተው ሕዝቡን ግብር በማብላት ሠራዊት እየሰበሰቡ ማደራጀት ጀመሩ። ጉልበታቸው የበለጠ እየተጠናተከረም ዝናቸው ገነነ።

ራስ አሊ ይህን የብሩ ጐሹን መጠናከርና ጉልበት ማበጀት እንደ ሰሙ የምርጥ መኳንንቶቻቸውን ጦር አዘው እንዲዋጉዋቸው ላኩ። በውጊያው ደጃች ብሩ አሸንፈው የራስ አሊን ሰባት መኳንንት ማረኩ። ከእነዚህ ተማራኪዎች ውስጥ አንዱ የራስ አሊ ወንድም ነበሩ። በዚህም በተደረገው ውጊያ ደጃች ብሩ 2000 ጠመንጃ በምርኮ ስላገኙ ጉልበታቸው የበለጠ በረታ። የግዛት ወሰናቸውንም አባይ በመለስ አደረጉ። ከዚህ በኋላ ካሣ ተነሱ።

ደጃች ካሣ አልበገር ብለው ያስቸገሩዋቸውን የጐጃሙን ደጃች ብሩን ከያዙ በኋላ ጭልጋ ውስጥ ካለው አርባ ከሚባለው ቦታ በእስር አስቀመጡዋቸው። ደጃች ብሩ አርባ አምባ ታስረው ከቆዩ በኋላ ሚስታቸው ወይዘሮ የውብዳር ከእልፍኝ አሽከሮች አንዱን መርጠው ውሽምነት ያዙ። ይህን የእልፍኝ አሽከራቸውን ውሽምነት መያዝ ደጃች ብሩ በእስር ላይ እንዳሉ በሰሙ ጊዜ አዘኑ፥ በገና እየመቱም አንጐራጐሩ።

«መከራን በሰው ላይ እንዲያ ሳቀለው፣

ምንኛ ከበደኝ እኔ ብይዘው።

መከራ ሲመጣ አይነግርም አዋጅ፥

ሲገሰግስ አድሮ ቀን ይጥላል እንጅ።

ዘሃው ለሰለሰ ሸማኔው ተቆጣ፥

እስተወዲያው ድረስ መጠቅለያው ታጣ።

የኔታም አይምጡ እኔም አልመለስ፤

ዋ ቢቸና ቀረ እስተወዲያው ድረስ።

ከእልፍኝ ሰው አይገባ ሚስቴን ሰው አይያት አይሉም አይሉም

ፈረሴን ሰው አይጫነው በቅሎዬን ሰው አይጫነው አይሉም፥ አይሉም፥

ጠጁ ቀጠነብኝ ሥጋው ጐፈየብኝ አይሉም አይሉም፥

ቀን የጣለ ለታ፥ የጨነቀ ለታ ይደረጋል ሁሉም።» አሉ።

ይህን የደጃች ብሩን ኀዘንና እንጉርጉሮ አጤ ቴዎድሮስ በሰሙ ጊዜ «ሎሌዎ ብድሎታል ብለዋልና ልቅጣልዎ» ብለው ለደጃች ብሩ ላኩባቸው። ደጃች ብሩም «መንግሥትዎን ያበርክትልኝ። ቃልዎ ደረሰኝ። ግን የጮሁለት ሰው አለና የዚያን ቁርጥ ሳውቅ ይሁን» ብለው መለሷልቸው። ይህን መልዕክት የያዘው አሽከር መልዕክቱን ይዞ ቴዎድሮስ ዘንድ ሳይደርስ ያን የወይዘሮ የውብዳርን ውሽማ መብረቅ ገደለው። ደጃች ብሩም ይህን ሰምተው ተደሰቱ። ለአጤ ቴዎድሮስም «ክርስቶስ ሰማኝ። ፍርዱን ፈረደ። ባላጋራዬ ሞተ» ብለው ላኩ። ቴዎድሮስም በነገሩ ተደነቁ።

አጤ ቴዎድሮስ የደጃች ብሩን ማዘንና በወይዘሮ የውብዳር ውሽማ ላይ የደረሰውን ተአምር አመዛዝነው ፈታችሁ አምጡልኝ ብለው አዘዙ። ደጃች ብሩም ከታሠሩበት ተፈትተው መጥተው ከቴዎድሮስ ፊት ቀረቡ። ከቴዎድሮስ ፊት በሚቀርቡበት ጊዜ ራሳቸውን ተከናንበው ነበር። በዘመኑ ይደረግ እንደነበረው ይማሩኝ ለማለትም ሎሚ የምታህል ድንጋይ በትከሻቸው ላይ ይዘው ቀረቡ። አጤ ቴዎድሮስ ይህን ሲያዩ ተቆጥተው «አሁን ትዕቢትዎ አለቀቅዎትምሳ» አሏቸው። ደጃች ብሩም «ከንንቡ እንደሆነ የጭልጋ በረሃ

ጠጉሬን ጨርሶት ባርፍ ነው» ብለው መለሱላቸው። ቴዎድሮስም «ከብራዳው ሥፍራ ከመቅደላ ይቆዩ። እኔ ልፈታዎ ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ ማቆያ የትዕቢት ምክንያት አመጣብዎ። ፈቃዱ ሲሆን ይፈታሉ» ብለው በ1846 ዓ.ም ወደ መቅደላ ሰደዱዋቸው።

አንድ ጊዜ እንግሊዞች ለአጤ ቴዎድሮስ ሱላድ የሚባል ጠመንጃ በስጦታ ላኩላቸው። ቴዎድሮስ ጠመንጃውን ተቀብለው ተኩሰው ለመሞከር ሲሉ ጠመንጃው ባሩዱ በዝቶበት መጉረሱን የተመለከቱት ጳጳሱ አቡነ ሰላማ «አይሆንም። አንተ መጀመሪያ አትተኩሰው። በፊት በሌላ ሰው እጅ ይፈተን» አሏቸው። አጤ ቴዎድሮስም እተኩሳለሁ ብለው ሲነሱ ጳጳሱ አትተኩስ ብለው ገዘቱዋቸው። አጤ ቴዎድሮስም ጠመንጃውን ለጋሻ ጃግሬአቸው ሰጥተው ተኩስ አሉት። ሲተኮስም ከባሩዱ ብዛት የተነሳ ጠመንጃው የኋልዮሽ ተራግጦ ጋሻ ጃግሬአቸውን ገደለው። አጤ ቴዎድሮስም በጋሻ ጃግሬአቸው መሞት በጣም አዘኑ። ለደጃች ብሩም «የምወደው አሽከሬ ሞቶብኛልና የለቅሶ ግጥም ያበርክቱልኝ» ብለው ላኩባቸው። ደጃች ብሩም ቅን የማይናገሩ ትዕቢተኛ ነበሩና ስለተላከባቸው መልዕክት ሲመልሱ፥

«አቡን ባይገዝቱ ያ ባርያ ባይኖር

ያበሻ መከራ ያልቅለት ነበር። ብለዋል ብለህ ንገርልኝ» ብለው መለሱ። አጤ ቴዎድሮስም «ዕድሜዬ ይፍታዎ። ራስዎ ጐዱት እንጂ እኔን አልጐዱኝም» ብለው ላኩባቸው።

ደጃች ብሩ በመቅደላ እንደታሠሩ እስከ ቴዎድሮስ ዕድሜ ማለቅ ድረስ 14 ዓመት ቆይተው የእንግሊዝ ጦር የመቅደላን እስረኞች በፈታበት ጊዜ ተለቀቁ። ማርክሃም ስለ መለቀቃቸው ሲጽፍ «.....ከታሠረበት ሲፈታ አጐንብሶ እጅ ነሳ።....... ወዲያውንም ፈጥኖ ወደ አገሩ ሔደ።......» ይላል። ለቴዎድሮስ አጐንብሰው እጅ ነስተው ቢሆን ኖሮ 14 ዓመት የእስራት ምርቃት (ተጨማሪ) አያገኙም ነበር።

ደጃች ብሩ በሥልጣናቸው ዘመን ሕዝብ አይወዳቸውም ነበር። በሚሠሩት ግፍ ምክንያት የጐጃም ሕዝብ እንዳለቀሰ ነበር የሚኖረው። አለቃ ተክለ ኢየሱስ እንደጻፉት ብዙ ግፍ የሠሩ ሰው ናቸው። አንድ ጊዜ በምሽጋቸው

በሶማ አምባ ምስጥ አስቸገረ። «ጉንዳን ቢኖር ኖሮ ምስጥ አይኖርም ነበር» የሚል ውሬ ደጃች ብሩ ሲሰሙ በደረቤ ሕዝብ ላይ የጉንዳን ግብር ጣሉበት። በየወረዳው ያለው የደረቤ ሕዝብ አስር እንስራ ጉንዳን እንዲያመጣ ብለው አዋጅ አነገሩ። ይህ አዋጅ የተነገረበት የደረቤ ሕዝብም በሥጋ ላይ ጉንዳን እየሰበሰበ በእንስራ ሲከት ከረመ። እንስራው ሲሞላም በቅጠል እየወተፈ በትከሻው እየተሸከመ ባላገሩ ወደ ሶማ ይጓዝ ጀመር። ጉንዳንም ከእንስራው ውስጥ እያፈተለከ እየወጣ ተሸካሚውን እየነከሰ ቢያስቸግርም የባሰ ቅጣት የሚመጣበት ባላገር እንደምንም እያለ ሶማ አደረሰ።

ባለገሩም «ከመከራው ሁሉ የጉንዳኑ ባሰ፥

የተሸካሚውን ጀሮ፥ እየተናከሰ» አለ።

አንድ ጊዜ ደግሞ የደጃች ብሩ በቅሎዎች በሆድ ቁርጠት በሽታ እየታመሙ በሠፈር የበቅሎ በሽታ ገባ። «ለዚህ ለበቅሎ የሆድ ቁርጠት መድኃኒት የሴት ብልት ጠጉር ነው» ብለው ለደጃች ብሩ ነገሩዋቸው። ደጃች ብሩም «አምስት መቶ ጉንዲ የሴት ብልት ጠጉር አግባ» ብለው በግዛታቸው ሁሉ አዋጅ አስነገሩ። ባላገር የሴት ብልት ጠጉር ከሴቱ እያሰባሰበ ከርሞ ሚዛን አልሞላ ቢለው የራሱን ጠጉር እየላጨ ሚዝና እየሞላ ይወስድ ጀመር። የሴት ብልት ጠጉር ግብር ተቀባዮችም «ይሄ የራስ ጠጉር ነው አንቀበልም። የሴት ብልት ጠጉር አምጣና ሙላ» እያሉ ድሃውን አስለቀሱት። ድሃውም ጠጉር ስለማይገኝለት ገንዘብ እየሰጠ ያመልጥ ጀመር። በዚያን ዘመን ሴት ዘመድ የሌለው ተቸግሮ እንደነበረ አለቃ ተክለ ኢየሱስ ጽፈዋል።

አንድ ጊዜ ደግሞ ደጃች ካሣ ወደ ጐጃም ለመዝመት ማሰባቸው እንደተሰማ ደጃች ብሩ የሶማንም ምሽግ እያጠናከሩ ያሰሩ ጀመር። ለምሽጉ መሥሪያ የሚሆን ንግድ ሕዝቡ ወደ ተራራው ሲያግዝ አንዱን ትልቅ ግንድ ሰላሳ ሰዎች ሆነው በሕብረት ተሸክመው ወደ ተራራው ሲወጡ ከጠባብና ከዘወርዋራ ቦታ ደረሱ። ያቺንም ቦታ ለማለፍ ሲሞክሩ ግንዱ ወደ አንድ በኩል አዘንብሎ ሰላሳውን ተሸካሚ ይዞ ገደል ገባ። ተሸካሚዎቹም በሙሉ ሞቱ። ይህን ነገር ቆመው ይመለከቱ የነበሩት ደጃች ብሩ የሰዎቹን በሙሉ መሞት ሲሰሙ» ገበሬ ምንኛ የሚዋደድ ነው? በአንድነት ወርዶ አለቀ ወይ» ብለው ቀለዱባቸው።

## ውቤ

ደጃች ውቤ የሰሜኑ የራስ ገብርዬ የልጅ ልጅ ናቸው። አባታቸው ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ይባላሉ። ደጃች ውቤ በካሣ ሠራዊት ድል ሆነው እስከ ተያዙበት ድረስ ለ24 ዓመት ያህል ትግራይን በመልካም ሁኔታ አስተዳድረዋል። ደጃች ውቤ በቴዎድሮስ እጅ ለብዙ ዓመት ከታሠሩ በኋላ በ1859 ዓ.ም ሞቱ። የደጃች ውቤ ሁለት ልጆችም መቅደላ ላይ በቴዎድሮስ ታስረው እንግሊዞች ድል አድርገው በገቡ ጊዜ ፈትተው በነፃ ለቀቋዋቸው። ውቤ ለብዙ ዘመን በቴዎድሮስ ታስረው የቆዩት፥ ልጃቸው እቴጌ ጥሩነሽ የአጤ ቴዎድሮስ ሚስት ሆነው ነው።

ደጃች ውቤ በዘመናቸው ሰፊ ግዛት የነበራቸው ታላቅ ሰው ነበሩ። ግዛታቸው ከጐንደር አካባቢ ከወልቃይት ጀምሮ ቀይ ባህር ድረስ ነበር። በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል የሆነው ፕላውዲን ስለ ደጃች ውቤ በጻፈው ታሪክ ስለ ግዛታቸው ሰፊነት ሲገልጽ «.....ከላስታ እስከ ሻንቅላ ወደ ግብጽ ግዛትም እስከ ሲናር ይደርሳል......» ይላል «......የውቤ ጦር አዛዥ በአካለ ጉዛይና በሀማሴን ተራራዎች ላይ ሲጓዝ የሠራዊቱ ብዛት ጥቁር ደመና ያለበት ይመስላል።.......እኚህ ታላቅ ሰው ደጃች ውቤ 40.000 የጦር ወታደር አላቸው። ከእነዚህም 8.000 ብር ይገብራሉ.......» ብሏል።

ስለ ደጃች ውቤ ደግነት ሲጽፍም «.......የውቤ እጅ ቸር ስለ ሆነ በባልደረባ አማካይነት ለማንኛውም እንግዳ ብዙ ነገር ይደርግለታል።...... በቀን መቶ እንግዳ ቢመጣም ለሁሉም ባልደረባ ተሰጥቶ ድርጐ ይታዘዝለታል።......ለኔም አንድ ሠንጋ እንጀራ፥ ጠጅ፥ ጠላ የሚነድ እንጨት ለበቅሎ ሣርና ምግብ ታዘልኝ ይህንንም የሚያዘጋጁ ሠራተኞች ጭምር ወዲያው ተሰጡኝ።...... እኔም አሞኝ ነበርና አንደኛይቱ ወጥ ሠሪ መታመሜን ለጌታዋ ነገረች በአብሾች ባሕል አንድ የማይበላና የማይጠጣ ሰው ሊሞት የተቃረበ በሽተኛ ነው ብለው ያምናሉ። በነጋታው በማለዳ ጌትዬው ብዙ ነገሮችንና ለእራሳቸው የተዘጋጀላቸውን ብርዝ ላኩልኝና «በሞቴ ይህቺን ጠጣልኝ ብለውሃል» አለኝ። እኔም በመከበሬ ደስ ብሎኝ ጠጣሁ ወዲያውኑም ሻል አለኝ። በሶስተኛው ቀን ውቤ ሊያዩኝ እንደሚፈልጉ ተነገረኝ። አልጠናሁም። ተቅማጡም ቢሆን አልቆመልኝም። ለባብሼ ወደ ግቤ

ሔድሁ። ግቢው ትልቅ ነው። አስር ጫማ ያህል ከፍታ ባለው ግንብ ተከቧል። አንዳንድ ክፍል ብቻ ብዙ የሆኑ ቤቶች አሉ። ግማሹ በደንብ የተሠራ ሲሆን ግማሹ ደግሞ በእንጨት የተሰራ ነው።........ይህን ሁሉ አልፌ ውቤ ካሉበት ክፍል ገባሁ። ጭር ብሏል።.......ጥቂት ሰዎች ቆመዋል። ሁለት ሽማግሌዎች ተቀምጠዋል። አማካሪዎች ናቸው እንደ ገባሁ ከውቤ አልጋ አጠገብ ካለ ምንጣፍ ላይ ተቀመጥሁ። እሳቸውም ሐር ጨርቅ የተሸፈኑ ሁለት መከዳዎች መሀል ተቀምጠዋል። ህለት አለቆች ከአልጋው ራስጌና ግርጌ ቆመው በጭራ ዝንቦች እንዳይጠጉዋቸው ይከላከላሉ። በክፍሉ መሀል ባለው ትልቅ ምድጃ እሳት ይነዳል። ከክፍሉም በለምለም ሣር ጉዝጓዝ ተጐዝጉዟል።

«.........ደጃዝማች ውቤ የተከበሩት ጦረኛ የኃይለ ማርያም ልጅ ናቸው። ........ አባታቸው የሞቱ ጊዜ ሕፃን ነበሩ። በዚያን ጊዜም አባታቸው ከትግራይ ገዢዎች ያስለቀቁትን ወልቃይትን ይገዙ ነበር። አባትየው ሲሞቱ ወንበራቸውን (ሥልጣናቸውን) ለትልቁ ልጃቸው ተናዘው ነበር።




ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ




ደጃች ውቤ

«ውቤ ወደ ጉርምስናው ሲደርሱ ሞግዚታቸው ማጂ ወልደ ኪዳን በወንድማቸው ላይ እንዲያምፁ ገፋፉዋቸው። ከዚያም ውቤ ያሏቸውን አሽከሮች አስከትለው ሌትና ቀን እየተሰገሱ ሔደው ከእኘሁ ከአሳዳጊያቸውና ረዳሃለሁ ካሏቸው ከማጂ ወልደ ኪዳን ጋር ተደባለቁ። በማግስቱም ወደ ወንድማቸው ሠፈር ሔደው በጥቂት ተከታዮች ያለምንም ተከላካይ ወንድማቸውን ይዘው የአባታቸው ወራሽ መሆናቸውን በአዋጅ አሳወቁ። ታላቅ ወንድምየው ደካማና የዋህ ቢጤ ስለነበሩ ሥልጣናቸውን በሰላም ለቁላቸው። ውቤም ታላቅ ወንድማቸውን ሳያስሩ በሰላም አብሮ ለመኖር በነፃ ለቀቁዋቸው።

«ውቤ ሥልጣን እንደያዙ የጠለምቱ ባላባት ሽፈተባቸው። ይህም ሰው ጥሩ ወታደሮችና አንድ ሺ ያህል ጠመንጃ ያለው ነበር። ጥቂት ፈረሰኞችም አሉት። ሰባት ነጋሪት እያስጐሸመ ታላቅ መሪ መሆኑን አሳወቀ። ውቤ ያላቸው ኃይል 16 ጠመንጃዎችና ሶስት ፈረሰኞች ብቻ ነበሩ። በዚያችው ኃይላቸው የተነሳባቸውን ሽፍታ ለመግጠም ሲሉ ማጂ ወልደ ኪዳን በቅድሚያ ሰዎችን መሰብሰብና ጥሩ ወታደሮችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል ብለው መከሩ። ውቤም የአባቴን አገር ከመልቀቅ መሞት ይሻለኛል ብለው ጥቂት ሠራዊት ይዘው ዘመቱ። በጦርነቱም ድል አድርገው ብዙ ወታደሮች ገድለው ነጋሮቶቹንና ብዙ ጠመንጃ ማረኩ። የሽፈቱባቸውንም ማርከው በሰንሰለት አስረው የአባታአቸው ታማኝ አሽከሮች ወዳሉበት ተራራ እንዲጠበቅ ላኩት።

«........በወጣትነት ዘመናቸው ሀብትና የጦር መሣሪያ በዛላቸው። የወታደሮቻቸውን ጥራትና ጉልበት ካረጋገጡ በኋላ ሌላ ዘዴ ይወጥኑ ጀመር። ራስ ይማምን ወግተው ጋላን አስገበሩ። ከዚያ ተመልሰው የንጉሱን መሞት እንደሰሙ ራሳቸውን ነፃ አድርገው አወጁ። ከራስ ማርዬ ጋር ሾዳ ላይ ጦርነት ገጥመው ድል ሆነው ወደ ሰሜን ሸሹ። ታላቁና ጀግናው የጋላ ተወላጅ ራስ ማርዬም ከውቤ ጋር በጦር ሳይሆን በሰላም አብረው ለመኖር አስበው ከታረቁ በኋላ አማች አድረጉዋቸው።

«.......ውቤ ከቋራው ገዥ ከደጃች ክንፉ ቁርቋሶ ጀመሩ። ክንፉ አበሻን ሊወር የመጣውን ቱርክ አሸንፈው በመመለሳቸው በግብጽ ውስጥ ታላቅ ዝና ያላቸው ሰው ናቸው። በዚያም ጦርነት የሚረኩት ብዙ ጠመንጃ ስላላቸው ጦራቸው የጠነከረ ነው። ውቤ ከክንፉ ጋር ለመግጠም በሚያስቡበት ጊዜ

ደጃች (ራስ) ማርዬ የሰሜንን አውራጃ በመዝረፍና በማቃጠል ያስቸገሩትን ገዥ ደጃዝማች ሰባጋዲስን ሊወጉ ተነሱ። እሳቸውም ከሸዋ ወሰን በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የጋላ ፈረሰኛ ሰብሰብው በውቤ መሪነት ዝነኛውን አስቸጋሪ መንገድ የሊማሊሞን ተራራ አልፈው በትግራይ ውስጥ መዝረፍና ቤት ማቃጠል ጀመሩ።.......በመንገዳቸው ላይ አንድም የሚያቆማቸው ሳያጋጥማቸው ተከዜን አቋርጠው በትግራይ ውስጥ የሚያቆማቸው ሳያጋጥማቸው ተከዜን አቋርጥው ተሻገሩ። ማይስላን ሲደርሱ የካቲት 7 ቀን 1823 ዓ.ም በአበሻ ምድር የተደነቀ ታላቅ ጦርነት ተደርጐ ራስ ማርዬ ሞቱ። ራስ ማርዬ የተገደሉት በሰባጋዲስ ልጅ በደጃች ሐጐስ ነው። ደጃች ሐጐስም ተማረኩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ተገደሉ። ጌታው የተደሉበት የጋላ ጦርም ተበረታቶ በመዋጋቱ ድል አግኝቶ ሰባጋዲስን ማረከ። በማግስቱ በደጃች ውቤ ትእዛዝ የራስ ማርዬን ደም ለመቀበል ተብሎ ተገደሉ። ውቤም በትግራይ ላይ ራስ ዶሪን ሾሙ።

«.......ደጃች ውቤ የትግራይን ግዛት ለማደላደል አስበው ወደ ፊት ቢገፉም የሸፈቱት የሰባጋዲስ ልጆች ኃይላቸውን አጠናክረው መለሱላቸው። ውቤም ወደ ሰሜን ተመልሰው ኃይላቸውን በደንብ ካደራጁ በኋላ እንደ ገና ወደ ትግራይ ዘመቱ። ከዚያም በአገር ሽማግሌዎች ከሰባጋዲስ ልጆች ጋር ታርቀው ሰላም ከወረደ በኋላ ውቤ የሰባጋዲስን ልጅ ካሣይን በትግራይ ላይ ሾሙ። ካሣይ ግን ከዳቸው። ውቤም ጦራቸውን ሰብስበው ፈረስ ማይ ከተባለ ቦታ ከካሣይ ሠራዊት ጋር ተዋግተው ድል አደረጉ። ካሳይ ግን አምልጠው ከተራራ ወጥተው መሸጉ። ውቤም የተራራውን ዙሪያ አስከብበው ውጊያ ገጠሙና ድል አድርገው ካሳይን ማረኩ። ከዚህ በኋላም የትግራይ ባላባት በጠቅላላው ገበሩላቸው።



የላስታ መንደር

«ውቤ ትግራይ በንቡረ ዕድ ወልደ ሥላሴ እንዲተዳደር አድርገው አዲስ ያስመጡዋቸውን ጳጳስ አቡነ ሰላማን ይዘው ወደ በጌምድር ተመለሱ። በጌምድርም እንደገቡ በራስ አሊ ላይ መሸፈታቸውን በአዋጅ አሳወቁ። በአዋጃቸውም «.......የጐንደርን ነገሥታት ማዕረግ ሳላፋልስ እገዛለሁ።...... ራስ አሊ በልባቸው የእስልምና እምነት ያልተው በመሆአንቸው ሃይማኖታችንን እየበጣበጡና እያበላሹ ናቸው።......» ብለው አሳወጁ። ይህም የደጃች ውቤ አዋጅ በሕዝብ ዘንድ የታወቀ ትክክለኛ ነገር በመሆኑ ብዙ ደጋፊ አገኙ። አቡነ ሰላማም ይህንንኑ አዋጅ አጠናክረው ገዘቱ።......» በማለት ጽፈዋል።

ደጃች ውቤ የራስ አሊን ከተማ ደብረ ታቦርን ለመውረር ተጓዙ። ራስ አሊ ጐጃም ውስጥ ነበሩና የውቤን መዝመት እንደ ሰሙ ሠራዊታቸውን አሰባስበው በግሥጋሴ ደብረ ታቦር ደረሱ። እንደ ደረሱም በጧት ጦርነት ተጋጥመው

ሲዋጉ የውቤ ሠራዊት ብዙ ነበርና ጦርነቱ ብዙም ሳይቆይ ወደ ረፋዱ ገደማ አለቀ። በጦርነቱ ድል የሆኑት ራስ አሉም ሸሽተው ወሎ ውስጥ ወረሂመኑ ገቡ።

በጦርነቱ ድል ያገኙት ደጃች ውቤም ድል በማድረጋቸው ተደስተው ከድንኳናቸው ገብተው መዝናናት ሲጀምሩ ብሩ አሊ ጋዝ የተባለ የራስ አሊ ሰው በግርግሩ መሀል ሳይታወቅ ከጥቂት ወታደሮች ጋር ከደጃች ውቤ ድንኳን ገባ። በድንኳኑም ውስጥ ጳጳሱና መኳንንቶቹ ከደጃች ውቤ ጋር ሲጫወቱ ብሩ አሊጋዝ በድንገት ደርሶ ሁሉንም ማረካቸው። በጦርነቱ የተማረኩትን የራስ አሊን ሠራዊትም አስለቀቀ። ዙሪያውንም ላስደፈታቸው አስደፈጣቸው አሽከሮቹ ድል የራስ አሊ መሆኑን አስለፈፈ።


ብሩ አሊጋዝ የማረካቸውን ደጃች ውቤን ጳጳሱንና መኳንንቱን ይዞ ለራስ አሊ ለማቅረብ ራስ አሊን ቢፈልግ አጣቸው። ወረሂመኑ መግባታቸውንም ሰማ። መልክተኛም ልኮ ከወረሂመኑ ራስ አሊን አስመጥቶ በሸሹ በሰባተኛው ቀን እንደ ገና ለዙፋናቸው አበቃቸው። ውቤና አሊም በእርቅ ተለያዩ። ይህ ጦርነት በተደረገ ጊዜ አንድ ባላገር በጦር ሜዳ የዋለ ወታደር አግኝቶ «ጦርነቱ እንዴት ሆነ» ብሎ ጠየቀው። ወታደሩም «ራስ አሊ ድል ሆነው ሸሹ። ደጃች ውቤም ተማረኩ» አለው። ባላገሩም ድል ሆነው ሸሹ። ደጃች ውቤም ተማረኩ» አለው። ባላገሩም ግራ ገብቶት «ኧረ ተው በወግ በወግ አርገህ አውጋኝ» ቢለው «እነሱ በወግ ያላደረጉትን እኔ እንዴት ላድርገው» አለው።

ፕላውዲን ስለደጃዝማች ውቤ ጠባይና ሁኔታ ሲገልጽ «......ዝምተኛና ጨዋ ሰው ናቸው። ተፈሪነትም አላቸው።.......በሥራቸው ፈጣን ናቸው። ወሳኝና ቆራጥ ናቸው። አጭር መልስ የሚወዱ ረጅም ደብዳቤ የማይወዱ....... ናቸው። ለጠላቶቻቸው የማይተኙ ወዳጆቻቸውን የሚጠይቁ ናቸው።........አንዴ የሚናገሩት እንዲጸና ይፈልጋል። ትንሽም ጥፋት ብትሆን ይቅርታ የሚያደርጉ ናቸው።....... በጦር ሜዳ ጥሩ የጦር እንጂ ጥሩ ተዋጊ አይደሉም። ፈጣን ሳይታሰብ አጥቂ ናቸው።..... ቁመናቸው አጭር ከንፈራቸው ስስ ሲሆን ድምፃቸው አስፈሪ ነው። ፈጣንና የንግግር ተሰጥኦ ያላቸው ናቸው።........ አንፍጫቸው ቀጥ ያለ ነው።........» ብሏል።

ፖርኪንስ ደግሞ «.......ወደ ታላቁ አስደናቂው የውቤ አዳራሽ ገባን። ቤቱ ዙርያ ክብ ነው። መሀል ለመሀል ሲለካም 30 ጫማ ያህል ይሆናል።

በመሀል በትልቅ ምድጃ እሳት ይነዳል። የመሬቱን መጥፎነት ለመሸፈን ከዳር እስከ ዳር ሣር ተጎዝጉዟል።.......ወደ ቤቱ ውስጥ ብርሃን የሚገባው በበርዋ ብቻ ነው።.......ውቤ እንዴት ናችሁ ብለው ጠየቁን። መልሱም እጅ መንሳት ነበር። እንድንቀመጥ ስለነገሩን ሁላችንም መሬት ላይ ተቀመጥን። በቤቱ ውስጥ እሳቸው ከተቀመጡበት መቀመጫ በስተቀር ሌላ የለም። .......የተቀመጥኩበት ቦታ እንጨት ከሚነድበት ከእሳቸው ምድጃ አጠገብ ነው። ከምድጃው አንድ ያርድ ያህል ብንርቅ ነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በጭሱ ምክንያት ዓይኔ ውሃ ያመነጭ ጀመር ሊያሳውረኝም ደረሰ።......ዓይኔ ቀልቶ እምባዬ ሲፈስ ውቤ አይተው ይስቁብኝ ጀመር።......ውቤ የተቀመጠበት የሲምርና (ቱርክ ውስጥ) ምንጣፍ የተነጠፈበት አልጋ ላይ ነው። በተዥጎረጎረ ጨርቅ የተሸፈኑ ሁለት መከዳዎች በመቀመጫቸው ላይ አሉ።

«.......ውቤ ቀጭንና መልከ መልካም ናቸው። ዕድሜአቸውም 45 ዓመት ያህል ነው። ጠጉራቸው ጥቅጥቅ ያለ ነው። አልፎ አልፎ ነጫጭ ጠጉር ጣል ጣል አድርጎበታል።.......» ይልና አንድ ጊዜ ደጃች ውቤ ሞቱ ተብሎ ስለተነገረ ሁኔታ ሲገልጽ «.......ውቤ ሞቱ የተባለ ጊዜ በቦታቸው ሰው እስኪ መረጥ ድረስ መሞታቸው ምስጢር ነው ተባለ። በኋላ ግን ነገሩ ከወታደሮቻቸው ዘንድ በመድረሱ ውቤ ጨቋኝ ገዥ ነበሩና ወታደሩ ሁሉ በመሞታቸው ተደስቶ ይሳሳም ጀመር። ግማሹም ወታደር የውቤን ወራሽ አንቀበልም እያለ በሐውዜን ምድር ክርክሩ ተሟሟቀ። .......ወታደሩ ሌላ ለመሾም በሚዘጋጅበት ጊዜ ላካስ ውቤ ሞቻለሁ ያሉት ሕዝቡን ለመሰለል ኖሮ ሳይታሰብ በድንገት ከድንኳናቸው ውስጥ ተቀምጠው ታዩ። እንዲያውም ከተለመደው የተሻለ ጤናማ ሆነው ተገኙ። ወዲያውም በየገበያው አዋጅ እንዲነገር አዘዙ።.......» በማለት ጽፈዋል።



# የእንጣሎ ገበያ

ደጃች ውቤ አስደናቂም አስቂኝም ታሪክ ያላቸው ናቸው ፖርኪንስ ስለ ደጃች ውቤ የሰማውንና ያየውን አንዳንድ ታሪክ ጽፏል። እነኛንም ታሪኮች በቀጥታ ትርጉም ሳይሆን ባጫጭሩ ለአንባቢያን ለማቅረብ ፈለግሁ።

ሁለት ልጆች የሾላ ፍሬ ለመብላት መንደራቸው ውስጥ ካለ የሾላ ዛፍ ዘንድ ሔዱ። አንዱ ዕድሜው አምስት ዓመት ሲሆን ትልቅዬው ደግሞ ስምንት ዓመቱ ነው። ከሾላው ዛፍ ዘንድ እንደደረሱ ትልቅዬው ልጅ ከዛፉ ላይ ወጥቶ ለራሱም የሾላውን ፍሬ እየበላ ከታች ለሚጠብቀው ጓደኛው ፍሬ ይጥልለታል። የበሳሰለ ፍሬዎችን እያየ እነኝያን ለመልቀም ትልቅየው ልጅ በዛፉ ላይ ከፍ እያለ ወጣ። ከአንድ ቦታ ሲደርስ አዳልጦት ከዛፉ ላይ አንሸራቶት ቁልቁል ወርዶ ከሥሩ ካለው ልጅ አናት ላይ ወደቀበት። ያም ከሥሩ የነበረው የአምስት ዓመት ልጅ ወዲያው ሞተ። ከዛፉ ላይ የወደቀው ልጅ ግን ደህና ነበርና ጓደኛውን ቢያገላብጠውም ቢያናገረውም መልስ የማይሰጠው ሆነ ይህም የተረፈው ልጅ ደንግጦ ወደ ቤቱ እየሮጠ ሔደና ሁኔታውን ለእናቱ ተናገረ።

የሁለቱ ልጆች ወላጆች ተካሰው ውቤ ዘንድ ቀረቡ። በመጨረሻው ልጁ ልጁን የገደለው አውቆ ሳይሆን በአጋጣሚ ሲጫወቱ ነውና የሟች ወገኖች የደም ዋጋ (ዋጀ) ተቀበሉና ተለያዩ ቢባሉ የሟች እናት ልጄን እንደገደለ ይህም ልጅ ይገደልልኝ እንጅ የድመ ዋጋ አልቀበልም ብለው እምቢ አሉ። በዚያን ጊዜ የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ብለው እምቢ አሉ። በዚያን ጊዜ የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ፍርድ «ገዳይ በገደለበት ሁኔታ ይገደል» የሚል ስለ ነበር ደጃች ውቤ ሲፈርዱ «.......እንግዲያውስ የሟች ወንድም ስላለ ገዳዩ ከዛፉ ሥር ይቁምለትና ወንድምየው ከዛፉ ላይ ወጥቶ ተወርውሮ ከገዳዩ ላይ ይውደቅበትና ይግደለው» ብለው ፈረዱ። በዚህ ጊዜ የሟች እናት «የቀረኝ አንድ ልጅ ነው። ይህ ይገደል የተባለው ልጅ ከዛፉ ላይ ተወርውሮ በሚወርድበት ጊዜ ከመሬት ያረፈ እንደሆነ ይሞትብኛል። ወይም ይሰባበርብኛልና ይቅርብኝ» ብለው ያለምንም ግድያ በሰላም ተለያዩ።

አንድ ቀን ደግሞ አንዲት አሮጊት ከደጃች ውቤ ድንኳን ፊት ለፊት ሆነው ጮሁ። ደጃች ውቤም አቅርቧት ብለው አዘዙ። አሮጊቷ ከደጃች ውቤ ዘንድ እንቀርቡ «ልጄ ሻንቅላ አገር ዘምቶ በነበረ ጊዜ አንድ የእርስዎ ወታደር የገዛ ጓደኛው የሆነ ገደለው ይህም የልጄ ገዳይ የእርስዎ ወታደር ሻንቅላ የገደለ አስመስለሎ ግዳይ ጥሎ ስለ ፎከረ ተሸለመ። አሁን የልጄን ደም ይወጡልኝ። » ብለው አመለከቱ። ውቤም ያስመስክሩ አሉዋቸው። አሮጊቷም ወሬውን የነገሩዋቸውን ከልጃቸው ጋር አብረው የዘመቱትን ወታደሮች አቅርበው ተመሰከረላቸው።

ደጃች ውቤ የምስክሮቹን ቃል አዳምጠው ከጨረሱ በኋላ «ነገርዎ ያሳዝናል። የልጅዎን ደም ለመበቀል እርስዎ አርጅተዋል። ፍርዱ ደግሞ ገዳይ እንደገደለበት ይገደል ነው የሚለው። እርስዎ ሌላ ልጅ ወይም ዘመድ የለዎትም። እንደሰማሁትም ልጅዎ ከሞተ ወዲህ የሚረዳዎ ሰው እንኳን አላገኙም። የልጅዎ የደም ዋጋ (ዋጀ) ይቀበሉ። 150 ብር አስከፍልዎታለሁና ይጠቅምዎታል። ይህም ገንዘብ እስከ ዕድሜ ልክዎ መጦርያ ይሆንዎታል። ይህም ሴትዮዋም «መጥቀስም ይጠቅመኛል። ልጄ ከመሞቱ በፊት በሕይወት እያለ ሲያበላኝ ኖረ። ከሞተ በኋላ ደግሞ ደሙን አልበላምና የልጄ ገዳይ ይገደልልኝ» ብለው አመለከቱ። ደጃች ውቤም «ነገርዎ ትክክል ነው። እርስዎ በዚህ አገር ዘምድ የለዎትም። ማን ይገድልልዎታል?? እርስዎ መግደል

ይችላሉ? ብለው ጠየቋቸው። ሴትዮዋም «እኔ መግደል ባልችል እግዚአብሔር የልጄን ደም የሚበቀልልኝ ይሰጠኛልና ይፈረድልኝ» አሉ። ይሙት በቃ ተፈረደላቸ። ሴትዬዋም ከሠፈራቸው የሁለት ቀን መንገድ ተጉዘው የተቋጥሮ ዘመድ አምጥተው የልጃቸውን ገዳይ ሰባት ቦታ በጦር እያስወጉ አስቆስለው በመጨረሻ በጥይት አስገደሉት።

አንድ ሰው 19 ዓመት ዕድሜ ያለውን አሽከሩን ጋሻውን አስይዘና አስከትሎት ወደ ጫካ ሔዱ። ሰውዬው ጦር ሜዳ ውሎ አያውቅም። በጦር ሜዳ ባለመግደሉም ገዳይ ከሆኑት ጓደኞቹ ሁሉ ክብሩ ያነሰ ነው። ከአሽከሩ ጋር በጫካው ውስጥ ሲሔዱ ድንገት ዞር ብሎ በያዘው ጦር አሽከሩን ወጋው። አሽከሩም ቆስሎ እንደ ወደቀ «ጌታዬ ከልጅነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በታማኝነት አገልግያለሁ። ሰባት ዓመት ሙሉ ሳገለግልዎትም አንድም ደሞዝ አገልግያለሁ። ሰባት ዓመት ሙሉ ሳገለግልዎትም አንድም ደሞዝ ተከፍሎኝ አያውቅም። እኔም አልጠየቅዎትም። ይሄን ያህል ዓመት በታማኝነት አገልግዬ አሁን ምን ባጠፋሁ ይገሉኛል?» አለ። ጌትዬውም «ያልከው ሁሉ እውነት ነው። እንዳልከውም በታማኝነት አገልግለኸኛል። ሰባት ዓመት ማገልገልህንም ምን ጊዜም አልረሳውም። አሁን ደግሞ በሞትህም ምናልባት ደግሞ ሰባት ሹመት እሾምብህ ይሆናል።» ብሎ አሽከሩን በጦር ደጋግሞ ወግቶት ጥሎት ሄደ።

ከሠፈር ገብቶም በጫካ ውስጥ ሽፍቶች እንዳጋጠሙት ከእነኛ ሽፍቶች ጋርም ሲከላከል አሽከሩን እንደገደሉበት እሱም ከሽፍቶቹ አንዱን እንደገደለና ሌሎች ግን ሸሽተው እንዳመለጡት አድርጐ ለጓደኞቹ አወራ። ጓደኞቹም ፈሪ መሆኑን ያቃሉና የነገራቸውን አናምንም ብለው «ይህም ያረግህበትን ቦታ ውሰድና አሳየን» አሉት። እሱም «ቦታው ሩቅ ነው። ምናልባትም ደግሞ እነኝያ ሸሽተው የሄዱት ሽፍቶች የጓደኛቸውን ሬሳ ለማንሳት ሲመጡ ድንገት የተገናኘን እንደሆነ ጦርነት ይነሳል» ብሎ አልሔደም አለ። ሌሎቹ ሲቀሩ የሟች አሽከር ጓደኞች የሆኑ ጥቂት ሰዎች የእግር ፈለግ እየተከተሉ ከጫካው ውስጥ ገብተው የሟቹን ጓደኛቸውን ሬሳ ይፈልጉ ጀመር። ተለያይተው በጫካው ውስጥ ሲፈልጉ አንደኛው የሚያቃስት ድምጽ ሰማ። ቢሔድ ጓደኛቸው አልሞተ ኖሮ ሲያቃስት አገኘው። ሌሎች ፈላጊ ጓደኞቹን ጠርቶ ያን የቆሳሰለ ጓደኛቸውን ተሸከመው ከደጃች ውቤ ዘንድ ሔዱ። ደጃች ውቤም

ጉዳዩ ፈጽሞ እንዳይወራና ማንም እንዳይሰማ አስጠንቅቀው ቁስለኛው በሚገባ ታክሞና ተመግቦ እንዲያድን አዘዙ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልጁ ቁስለኞቹን ዳነ።

ደጃች ውቤ ታላቅ ግብር አስደግሰው ለጀግኖች የሚሰጠው ሽልማቶች አዘጋጅተው ወታደር ሁሉ ለግብር ተጠራ። ጀብዱ የሠራ ወታደር ሁሉ ከውቤ ፊት እየቀረበ እየፎከረና ግዳዩን እያስመሰከረ ይሸለም ጀመር። ያም አሽከሩን እያቆሰለ ሰው ከደጃች ውቤ ፊት ቀርቦ ታሪኩን እየዘረዘረ እንዴት እንደገደለና እነሱም አሽከሩን እንደገደሉበት ዘርዝሮ ተናግሮ ፎከረና ሲያበቃ እጅ ነሳ። ደጃች ውቤ ያንን ከቁስሉ የዳነ ልጅ አጠገባቸው አለ መጋረጃ ኋላ ደብቀው ከመጋረጃው ውጭ ሽልማቶችን አስቀምጠው ከዚያ እያነሱ ነበር የሚሸልሙት። ሽልማቱም ከአነስተኛ ጨቤ እስከ ጐራዴ ድረስ ነበር። ያ ሰው ፎክሮ እንዳበቃ ውቤ ለስጦታ የተቀመጠ ዕቃ የሚያነሱ መስለው እጃቸውን ዘረጉ። ሰውዬውም ደስ ብሎት ጓደኞቹን ሁሉ እየተዟዟረ በኩራት ተመለከተ። የሰውየውን መገለማመጥ ያዩት ውቤም «ወዳጄ ሆይ ጠጋ በል አትፍራ። እንዳንተ ያለ ጀግና እወዳለሁ። መሸለም የምወደውም ለጀግና አሽከር ነው። አይዞህ ጠጋ በል» ሲሉት ሰውዬው ተጠጋቸውና ቆመ።

ሰውዬው ተጠግቶ እንደ ቆመ ደጃዝማች ውቤ አጠግባቸው ያለውን መጋረጃ ድንገት ገለጡት። ሰውዬው ገድየዋለሁ ያለውን ልጅ ከዚያ ቆሞ ሲያየው ደነገጠ። ለመሸሽም ሞከረ። ግን ብርክ ይዞት ወደ ኋላው በጀርባው ተንጋሎ ወደቀ። የውቤም አሽከሮች ፈጥነው እዚያው እወደቀበት እጅና እግሩን አሰሩት። ውበኢ ግን ምንም ፈገግታ ሳያሳዩ ኮስተር ብለው ይመለከቱታል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ «ወዳጄ አንተን ለመሰለ ጀግና የምሸልመው ብቂ ሽልማት የለኝም። ያ ገድየዋለሁ ብለህ የጣልከው ሟች ልጅ እሱ የሚሰጥህን ተቀበል» ብለው ወደ ልጁ ዞር አሉና «አንተ ድሃ ለደጉ ጌታህ የምትሰጠውን ሽልማት ስጠው» አሉት። ልጁም እጅ ነስቶ አጠገቡ የተቀመጠለትን ጦር አነሳ። በጀርባው ወደተኛው ጌታው ሔዶ ጦሩን በሁለት እጁ ይዞ ከጌታው ሆድ ላይ ሰካው። ከዚያም ባለው ኃይል ሁሉ ጦሩን ቁልቁል ይገፋው ጀመር። እንደገና እየነቀለም ከሌላ ቦታ እየተከለ ሲያቆስለው ሳለ ልጁ አዞረውና ወደቀ። በደጃች ውቤ ትእዛዝ አሽከሮች ያን ሰው አንገቱን በሰይፍ ብለው ገደሉት።

አንድ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ነጋዴ አንዲት የደስ ደስ ያላትን የአሥራ ስድስት ዓመት ልጅ በግርድና ቀጠራት። በግርድና ሲቀጥራት እሱ በሚሔድበት ሁሉ አብራው እንድትሔድ ነው። በተለይ ለንግድ ሥራ ብዙ ጊዜ ወደ ጠረፍ ወደ ምፅዋ ስለሚሔድ ልጅቱ እንድትከተለው አስቦ ነው። በዚህ ምክንያት ደሞዝዋ በአገር ደንብ ሳይሆን ከፍ ያለ ነበር። በዚህ ሁኔታ ከተቀጠረች በኋላ አንድ ሁለት ጊዜ ከየቅርብ ቦታ እየሔዱ ተመለሱ። ልጅቷ ውብ በመሆንዋ ብትሸጥ ደህና ዋጋ እንደምታወጣለት ስላወቀ በመጨረሻው ወደ ምፅዋ አብረው ተጓዙ። ከጠረፍ እንደ ደረሱም ነጋዴው ልጅቷን በደህና ዋጋ ሸጦ እሱ ወደ ሌላ የኢትዮጵያ ክፍል ተሰውሮ ገባ።

የልጅቷ ዘመዶች ነጋዴው መመለሱንና ልጅቷ ግን አብራው እንደ ሌለች ጭምጭምታ ወሬ ሰሙ። ቢጠብቁም ልጅቷ ልትመጣ ስላልቻለች ወደ ደጃች ውቤ ዘንድ ሔደው አመለከቱ። ደጃች ውቤም የነጋዴውን የቅርብ ጓደኞችና የእስልምና ሃይማኖት መሪ የሆኑትን ሰዎች አስጠርተው ልጅቷን ካለችበት አምጠው ለዘመዶችዋ እንዲሰጡ አዘዙዋቸው። እነሱም «ልጅቷ የተሸጠችው ከጠረፍ ስለሆነ እንዴት ማግኘት ይቻላል? ጊዜውም ስለ ቆየ ባሁኑ ጊዜ ካንዱ ወደ አንዱ እየተሸጠች ምናልባትም አረብ አገር ወይም ግብፅ ገብታ ሊሆን ይችላል። እንዴት እናገኛታለን?» ብለው አመለከቱ። ደጃች ውቤም «ይቻላል አይቻልም የሚለው አነጋገር በኔ ቁርጥ ቃል ተናገሩ። ቀኑንም ቆርጠው ባንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያመጡዋት ወሰኑላቸው፡ ለመያዣም «ልጅቷ ባትመጣ ግን ከሃይማኖት መሪዎቻቸው ሁለት ይገደላሉ» ብለው አስጠንቅቀው ሰዎቹን ያዙ። የውቤ ቃል እንደማይታጠፍ ያውቃሉና እነኛ ሰዎች ቶሎ ብለው የገንዘብ መዋጮ አሰባስበው በየአቅጣቸው ልጅቷን ለመፈለግ ተሰማሩ። ሳውዲ አረቢያ ውስጥ ጅዳ መደስዋ ተሰማ። ከዚያም የሚከፈለውን ከፍለውና ከስረው ልጅቷን በማምጣት የሃይማኖት መሪዎቻቸውን ከመገደል አዳኑ።

ደጃች ውቤን የጐን ውጋት ሆኖ ቀስፎ ይዟቸው የነበረ የዲ የሚባል ሰው ነበር። የዲ በደጃች ውቤ ላይ አምፀው የነበሩት የደጃች ካህሣይ አሽከር ነው። ደጃች ውቤ ጠላታቸውን ደጃች ካህሣይን ይዘው አሠሩዋቸው። የጌታውን መታሰር ያየው የዲ ከፍቶት ሸፈተ። የዲ ከድሮውም ቢሆን ጋሻው በብርና በወርቅ ያጌጠ ቢለዋው (ጪቤው) ከብር የተሠራ በራሱ ላይ የሚያደርገው የአንበሳ ጐፈርም እንደዚሁ ያጌጠ ነበር። የፈረሱ ዕቃ ውበት እንኳ ከጌታው

የሚወዳደር ነበር። ስለየዲ የዘመኑ የትግራይ ሰዎች ሲያወሩ «ጠላቱን በሚያጠቃበት ጊዜ ሰው መሆኑ ቀርቶ እንደ ፀሐይ በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ይወድቃል» ይሉታል።

የዲ - በጌታው መታሰር ምክንያት በውቤ ሰፈር አደጋ እየፈጠረ አስቸገረ። የደጃች ውቤ ሰዎችም በየዲ ምክንያት የከብት መኖ ሣር ለማጨድም ሆነ ውሃ ለመቅዳት ተቸገረ። ሲመሽ በሠፈር አጠገብ አድፍጦ ይተኛል። ከሠፈር አንድ ሰው ብቅ ሲል ይይዝና ያለ ምሕረት አርዶ ይጥለዋል። ልጅ፥ ሴት ሽማግሌ፥ አሮጊት ማንንም አይመርጥም። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መኳንንቱ ጉግስ እስቲጫወቱ ይጠብቅና የጉግስ ጨዋታ በሚጀመርበት ጊዜ እየጋለበ ከመሀከላቸው ገብቶ ሁለት ሦስት ሰዎች ይገድልና ወደ ተራራው ወጥቶ ከምሽጉ ይገባል። አንዳንዴም ደግሞ መነኩሴ መስሎ ወደ ሠፈር ይመጣል። ከመኳንንቱ ደጅ ይቆምና እራቱን እንዲያበሉት ከለመነ በኋላ ከውጭው በር ሰብሰብ ብሎ ይተኛል። እኩለ ለሊት ላይ ይነሳና የተኙትን ወታደሮችና ባለቤቱን ገድሎ በፈረስ ሆኖ አሸባሪ ጩኸት እየጮኸ ያመልጣል።

እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ለጥቂት ዓመታት ሲያከናውን ቆይቶ ተያዘ። ዘመዱን እናት አባቱ የተገደለበት ሁሉ ተሰብስቦ እንዲገደልላቸው ከደጃች ውቤ ዘንድ እየቀረቡ ይጮሁ ጀመር። ውቤ ግን ጀግና ሰው ይወዱ ነበርና «እንዲህ ዓይነቱ ጀግና አይገደልም» ብለው በነፃ ለቀቁት። የሚገዛውም አገር ሰጥተው ሾሙት። የዲ አንድ ቀን ከሰዎች ጋር ቆሞ ሲያወራ አንድ አባቱን የገደለበት ልጁ ካንድ ወታደር የጐረሰ ጠመንጃ ተቀብሎ ተኩሶ ገደለው። የደፋሩ ጀግና መጨረሻው ሆነ። የትግራይ ሰዎችም ለጀግኖች አቀባበር በሚደረግበት የክብር ሥርዓት እያለቀሱ ቀበሩት። ይህን የየዲን ታሪክ የጻፈው ፕላዊን ነው።

ከፕላውዲን መጽሐፍ ሌላም ነገር አለ። አቶ ውርካ የሚባል አርመናዊ አድዋ ከተማ ይኖር ነበር። የአድዋ ጅብ ብዙ ስለሆነ ውርካ ጅብ መግደል ይወዳል። አንድ ቀን አንድ አህያ ሞቶ ከገበያው ላይ ወደቀ። ማታም ያን አህያ ለመብላት የሚመጣ ጅብ ለመግደል አቶ ውርካ ሲጠባበቅ ነገር አየና ጥይት ተኮሰ። ጅብ መስሎት የተኮሰው ጥይትም ያ ነገር ሰው ኖሮ ገደለው። አቶ ውርካ ሰው መግደሉን ሲያውቅ ከቤተ ክርስትያን ገብቶ ተደበቀ። ሕዝቡም

አቶ ውርካን በማጣቱ ትልቁን ልጁን ይዞ በሰንሰለት አሠረው። የልጁን መታሰር የሰማው አቶ ውርካ ከተደበቀበት ወጥቶ ክርክር ቀጠሉ።

በደጃች ውቤ ችሎት ላይ ውርካ «.......ሳላውቅ በስህተት ጅብ መስሎኝ በተኮስኩት ጥይት ነውና የገደልኩት ምህረት ይደረግልኝ........» አለ። ፈራጅ ሁሉ ሰው ከገደለ ይገደላል እያለ ፈረደ። ደጃች ውቤ ፍርዱን እንዲያፀድቁ የመጨረሻው ተራ ሲደርሳቸው «.......ሰውና የሞተ አህያ በሌሊት ምንም ግንኙነት የለውም። ቡዳ ከሆነ ግን ያን ጥንብ አህያ ለመብላት ስለሚሔድ ግንኙነት አላቸው። ስለዚህ እሱ ተኩሶ መግደሉ ጥሩ አድርጓል» ብለው ፈረዱ። የሟች ዘመዶች ይህን ሲሰሙ ደንግጠው ከውርካ ጋር ታርቀው 40 ብር ብቻ የደም ዋጋ ተቀበሉ። የደም ዋጋ ደንቡ እስከ 250 ብር ነበር።

ደጃች ውቤ ጥሩ ጥሩ ጦር ወርዋሪ አሽከሮች ነበሩዋቸው። ከአምሳ ሜትር ርቀት በጦር ኢላማ የሚወጉ ነበሩ። ጦራቸውንም በረጃጅም ዛፍ አናት ላይ ወርውረው ማሳለፍ ይችሉ ነበር። በተለይ ንቡዕረድ ወልደ ሥላሴና ሊቀ መኳስ ደስታ እባክሱም ረጅሙ ሐውልት አናት ላይ ጦር ወርውረው ማሳለፍ የሚችሉ ሰዎች ነበሩ።

ደጃች ውቤ የአጤ ቴዎድሮስ አማች ቢሆኑም መቅደላ ላይ ታስረው ቆይተው ሞቱ። ከዚያን አስቀድሞ ማንም ዘመድ የሞተበት ሰው እንዳያለቅስ በአዋጅ ተከልክሎ ስለ ነበር ደጃች ውቤ ሞተው ልጃቸው የቴዎድሮስ ሚስት እቴጌ ጥሩ ወርቅ ከተረዱ በኋላ ለቅሶ በአዋጅ ተፈቀደ። ሕዝቡም ለደጃች ውቤ በማስመሰል አስቀድሞ ለሞቱበት ለየዘመዱ አለቀሰ። አንዲት አልቃሽም፥

«የኔታ ደጃዝማች ሁልጊዜ ደግነት

ዛሬ እንኳ ለድሃው እንባ አተረፉለት» ብላ አንጐራጐረች።

ደጃች ውቤ አገራቸውን ኢትዮጵያን የሚወዱ ታላቅ ሰው ነበሩ። አንድ ጊዜ ለዲ - አባዲ ሲያጫውቱት «.......እናንት ፈረንጆች የአገሪነ አፈር እንዳትነግዱበት ተጠንቀቁ። እንግሊዞችና እናንተ (ፈረንሳዮች) የመሬታችንን አፈር ትቆፍራላችሁ። ጤናማ አየራችንን ያለ ፈቃዳችን ትጠቀሙበታላችሁ። አንዱ ዕፀዋታችንን ሲቀነጣጥብ ሌላው ድንጋያችንን ይሰበስባል። ምን እንደ

ምትፈልጉ አላውቅም። ያን የምትፈልጉትም ነገር ከአገሬ ውስጥ እንድታገኙ አልፈቅድም።.........» በለውታል።

# ምዕራፍ 5

# ንግሥ

ደጃዝማች ካሣ ደጃች ውቤን ድል ካደረጉ በኋላ በዚያው በየካቲት ወር 1845 ዓ.ም አጤ ቴዎድሮስ ተብለው በደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስትያን በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ እጅ ነገሱ። ቴዎድሮስ የነገሱበትን ዘመን ደብተራ ዘነበና አለቃ ወልደ ማርያም በጻፉት ታሪክ በ1847 ዓ.ም ነው ይላሉ። አለቃ ተክለ ኢየሱስ ግን በ18545 ነው ብለው ዕፈዋል። በእነዚህ መፃሕፍት የሁለት ዓመት ልዩነት አለ። እንደነደብተራ ዘነበና አለቃ ወልደ ማርያም ዘመን አገላለፅ ከሆነ ቴዎድሮስ የነገሱት 13 ዓመት መሆኑ ነው። አለቃ ታዬ አጤ ቴዎድሮስ 15 ዓመት ነገሱ ስለሚሉ የነገሱበት ዘመን ከአለቃ ተክለ ኢየሱስ ትረካ ጋር ይጋጠማል። አቶ መንግሥቱ ለማ የአባታቸውን የአለቃ ለማን ትረካ በፃፉበት መፅሐፍ ትዝታ ውስጥ ቴዎድሮስ በ1845 ዓ.ም ነግሰው በ1860 ዓ.ም ሞቱ ይላሉ። ባላንባራስ ማህተመ ሥላሴም በዝክረ ነገር መፅሀፋቸ በ1845 ዓ.ም ነገሱ ይላሉ። ስለዚህ እኔ አብዛኛዎቹ በተናገሩት በ1845 ዓ.ም ነገሱ ብያለሁ።

ደጃዝማች ካሣ ስማቸውን ለውጠው አጤ ቴዎድሮስ ተብለው ከነገሱ በኋላ የዘመነ መሣፍንት ፍጻሜ ሆነ። ስማቸውን ቴዎድሮስ ተብለው የነገሱበትም ምክንያት «ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ሲነግሥ ኢትዮጵያን እስከ ባሕር ያሰፋታል፥ ፍርድና አስተዳደርንም ያስተካክላል» የሚባል ትንቢት ስለነበረ ሕዝቡ «ይህ ትንቢት የርስዎ ነው» እያሉ ስላሞካሿቸው ስሜን ቴዎድሮስ በሉ ብለው አወጁ።

አጤ ቴዎድሮስ እንደነገሱ ደጃች አርአያን ለትግሬ ሾመው ወደ አምባ ጫራ ተመለሱ። ከዚህ በኋላ ደግሞ ሸዋን ለማስገበር ይዘጋጁ ጀመር። ዝግጅታቸውን አጠናቀው ወደ ሸዋ ጉዞ ጀመሩ። ገራገራ ከተባለ ቦታ ሠፈር

አድርገው ሳለ ትግሬዎች የዓመት ግብራቸውን ለመገበር መጡ። እንደመጡም በትግራዩ ገዥ በደጃች አርአያ ላይ ከሳሽ ተነስቶ ወነጀላቸው። አጤ ቴዎድሮስም ደጃች አርአያን ሽረው በምትካቸው ደጃች ካሣን ሾሙ።

ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ለመዝመት በተነሱ ጊዜ የሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለኮትና የወሎዋ ባላባት ወይዘሮ ወርቂት የጦርነት ውል ተዋዋሉ። ውሉም ቴዎድሮስ በጐጃም በኩል አቋርጠው ወደ ሸዋ ሲመጡ ኃይለ መለኮት ፊት ለፊት ሲገጥሙ ወርቂት ደግሞ ሠራዊቷን ይዛ በጐን በኩል ልትወጋቸው ነበር። ወርቂት ከጨጨሆ እስከ ሸዋ ድንበር ትገዛ ነበር። ይህን ምክር ቴዎድሮስ ሲሰሙ ነገሩ እንደማያዋጣቸው አውቀው የጦር መላቸውን ለወጡ። ሁለቱን ባንድ ጊዜ ከመግጠም ተራ እብተራ መግጠሙ እንደሚሻል አውቀው የሸዋ ዘመቻውን ትተው ወደ ወሎ ለመዝመት ይገሰግሱ ጀመር።

ደላንታ ሲደርሱ ሠራዊታቸው ተርቦ ነበርና «እህል ዘርፈህ ብላ። ልብስና ከብት አትንካ» ብለው አወጁ። ቴዎድሮስ ይህን አዋጅ ቢያውጁም ሠራዊታቸው ግን አዋጃቸውን ጥሶ ከብት እየዘረፈ እያረደ ይበላ ጀመር። ቴዎድሮስም በወታደሩ ተግባር በጣም ተቆጥተው «የድሃውን ገንዘብ እንዳረድኸው ባንተም እግዚአብሔር አለብህ» ብለው ደላንታን ለቀው ወደ በሸሎ ተጓዙ። ከበሸሎ ወንዝ ሲደርሱ ወታደር ሳይታዘዝ ተከፍሎ ወደዘረፋ ሔደ። በዚያም ያሉ ኦሮሞዎች በርትተው በመዋጋት ብዙ ወታደር ገደሉ። ብዙ ጠመንጃም ማረኩ። ለምርኮ ሔዶ ከነበረው የተረፈው ወታደራቸው እየሸሸ ሲመጣ ቴዎድሮስ ሁሉንም አስይዘው አንዳንድ እጁንና አንዳንድ እግሩን እያስቆረጡ ጣሉት። ከዚህ በኋላ በወታደሮቻቸው መሀል ስነ ሥርዓት ሰፈነ።



የደቡብ ትግሬ ዕይታ

በሐምሌ ወር ቴዎድሮስ ቆቃ ከተባለ ቦታ ሠፍረው ሳለ የሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለኮት በውላቸው መሠረት ወይዘሮ ወርቂትንና አሊ አደራን ለመርዳት መምጣታቸውን ሰሙ። በዚህ ጊዜ ከቆቃ ተነስተው ወደ አያታ አዋ ሜዳ ከተባለው ሥፍራ ሠፈሩ። የቴዎድሮስን መጠጋት የሰሙት ኃይለ መለኮትና የኦሮሞቹ ባላባቶች ባንድነት ተሰብስበው «ይህን ሰው አንችለውምና እንበታተን ብለው መከሩ። በዚህ ምክር ተስማምተው ኃይለ መለኮት ወደ ሸዋ ተመለሱ። ሲመለሱም በክረምቱ ምክንያት ብዙ ከብትና ሰው አለቀባቸው። አሊ አደራም ለጋጐራ ገቡ። ቴዎድሮስ የአሊ አደራን ወደ ለጋጐራ መሔድ እንደ ሰሙ እጁን ለመያዝ ገሰገሱ። እንደደረሱም ነሐሴ 5 ቀን ውጊያ ገጥመው አሊ አደራ በጀግነንት በመዋጋቱ ከቴዎድሮስ ሠራዊት ብዙ ሰዎች አለቁ። ቴዎድሮስም ፈረሳቸው ላይ ሆነው ከጦሩ መሀል ገብተው ሲያዋጉ ውጊያው ጠንቶባቸው ከሰልፉ መሀል በከፍተኛ ችግር ሊወጡ ቻሉ። ከብዙ እልቂት በኋላ ቴዎድሮስ ድል አድርገው አሊ አደራ በእርቅና በሰላም ገባላቸው። ቴዎድሮስም አሊ አደራን በአባቱ አገር ላይ ሾሙት።

የአሊ አደራን ጉዳይ ካጠናቀቁ እብኋላ እንደ አሊ አደራ ጉልበት የሚሰማውንና የሚያስቸግረውን ሰዲቅ ዳንቃ የሚባለውን ለማስገበር ቆራቆራ

ወደ ተባለ አገር ሔዱ። ሰዲቅ ደንቃም ጦርነት ገጥሞ አሰቃቂ የሆነ ውጊያ ተዋጋቸው። ከቴዎድሮስ ሠራዊትም ብዙ ሰው አልቆ ብዙ መሣሪያም ተማረከ። ነገሩ እንደ ጠና አይተው የተረፈ ሠራዊታቸውን ይዘው ቴዎድሮስ ተመለሱ። ከሁለት ዓመት በኋላ ግን አሊ አደራ አዘንግቶ ሰዲቅ ደንቃን ይዞ ለቴዎድሮስ ሰጣቸው። እሳቸውም ግቤን ላይ አስረውት ሳለ ታሞ ሞተ።

ከሰዲቅ ደንቃ ውጊያ በኋላ ቴዎድሮስ ወደ ጊምባ ዘመቱ። ጊምባ ሲደርሱም የሰባት ቤት ኦሮሞዎች ዙርያቸውን ከበው መሔጃም ሆነ መመለሻ በማሳጣት አወኳቸው። ጳጉሜ እንዳገባም ጥኑ ውጊያ ገጠማቸው። ሠራዊታቸውም በርትቶ እየተዋጋ ምርኮ ማምጣት ጀመረ። ቴዎድሮስ ከመጀመሪያው የመጡትን 47 የጊምባ ምርኮኞችን አስቀርበው ሁለት ሁለት እጆቻቸውን እያስቆረጡ በገመድ ካንገታቸው ላይ እያሰሩ ወደ ዘመዶቻቸው ሒዱ ብለው ለቀቁዋቸው። ከዚህ በኋላ ይህን ያየ ወሎዬ በሙሉ ሸሽቶ መንገዱን ከፈተላቸው። የወሎዎችን እጅ መቆረጥ ያየ ቀልደኛም «እራቱንስ ሚስቱ ታጉርሰው ኧረ ቂጡን በምን ያብሰው (ይጥረገው)» ብሎ ተናገረ።

በሰላምም ሆነ በቅጣት ወሎ ከገበረ በኋላ ወደ ሸዋ ተጓዙ የቴዎድሮስን ወደ ሸዋ መምጣት ንጉሥ ኃይለ መለኮት እንደ ሰሙ እሳቸውም ለጦርነት ተዘጋጁ። ቴዎድሮስ ከሸዋ ድንበር ግዜ ሲገቡ የመንዝ ገዥ አቶ ሀብተ ማርያም ጥር 7 ቀን 1847 ዓ.ም ከግድሙ ገዥ ከአቶ ሰሙ ንጉሥ ጋር ሆነው ውጊያ ገጠሙዋቸው። በጦነቱም ሙሉ ቀን ሲዋጉ ውለው በሁለቱም በኩል መሸናነፍ ሳይኖር ውጊያውን ምሽት ገላገለው። በማግስቱ ውጊያው ቀጥሎ የቴዎድሮስ ኃይል በመበርታቱ አቶ ሀብተ ማርያም ተማርከው ሲያዙ አቶ ሰሙ ንጉሥ ግን አመለጡ። በዚያ ታላቅ ውጊያ የአቶ ሀብተ ማርያም ድል መሆን በሸዋ ድንጋጤ ፈጠረ።

ንጉሥ ኃይለ መለኮት ከወሎ ሲመለሱ ሕመም አድሮባቸው ነበርና በሕመም ላይ እንዳሉ መኳንንቶቻቸውን ሰብሰበው ምክር ጀመሩ። በዚህም ምክር ላይ የይፍራታው ገዥ አቶ በድሉ ከመዋጋት ይልቅ እጃችንን ብንሰጥ ይሻላል የሚል ሐሳብ አቀረቡ። በመረሐቤቴው ገዥ በአቶ ሰይፉ ሣህለ ሥላሴ የሚመሩት መኳንንት ግን ሳንዋጋ እጃችንን መስጠት የለብምና መዋጋት አለብን እንዋጋ አሉ።

አስተርን እንደ ፃፈው በዚህ ጊዜ ሸዋ የነበረው የተዘጋጀ ጦር 50.000 ወታደር ይሆን ነበር። ፕላውዲን ደግሞ የአጤ ቴዎድሮስን ሁኔታ በመግለፅ ለአርል ከላሬንደን በፃፈው ደብዳቤ የቴዎድሮስ ጦር 50 እስከ 60 ሺ ወታደር እንደ ነበርና ከጐንደር ጀምሮ በየመንገዱ ያለቀው ወታደራቸው ሲቀነስ አሁን ሸዋ የገባው 40.000 ወታደር ቢሆን ነው ይልና ወታደራቸው ግን የተሻለ መሣሪያ ያለውና ስነ ሥርዓት አክባሪ መሆኑን ይገልፃል። በተለይም ከሽፍትነታቸው ጊዜ ጀምሮ ቴዎድሮስን ያገለግሉ የነበሩት አንድ ሺህ ያህል ወታደሮቻቸው ጥሩ ተዋጊዎች እንደ ነበሩም ይናገራል።

እንደተባለው ሁሉ በመሣርያ በኩል የቴዎድሮስ ኃይል ተወዳዳሪ የሌለው ነው። ጥንት ራሳቸው በነበራቸው ላይ ከደጃች ውቤ የማረኩት ሰባት ሺ ጠመጃና ሁለት መድፎች ተጨምረውላቸዋል በዚህም ባላቸው ኃይል ቴዎድሮስ መንዝን፥ ግድምንና ይፍራታን አስገብረው ጉዞአቸውን ወደ ፊት ቀጠሉ። የይፍራታው ገዥ አቶ በድሉም ከኃይለ መለኮት ከድተው ለቴዎድሮስ ገቡ። እሳቸውም ቴዎድሮስን መንገድ በመምራት ጌታቸውን ኃይለ መለኮትን ለመውጋት መጡ።

ቴዎድሮስ ጅብ ዋሻ ከተባለ ቦታ ሲደርሱ አንኮበር ያለውን የኃይለ መለኮትን ቤተ መንግሥት የሚጠብቁ ሰዎች «በጌታችን ቦታ ጠላት አይገባበትም። ጠጁንም ጠላት አይጠጣውም» ብለው ጥቅምት 16 ቀን አርብ ዕለት የአንኮበርን ቤተ መንግሥት አቃጠሉት። ንጉሥ ኃይለ መለኮትም ሕመማቸው እየጠናባቸው ስለሄደ ለጦርነት ከተሰለፉበት ቦታ ጥቅምት 30 ቀን 1848 ዓ.ም ሞተው በማግሥቱ ሕዳር 1 ቀን በደብረ በግዕ ተቀበሩ። ንጉሥ ኃይለ መለኮት እንደሞቱም የሸዋውን ጦር የኃይለ መለኮት ወንድሞች አቶ ዳርጌና አቶ አንዳርጋቸው (በኋላ ሁለቱም ራስ የተባሉት) ይመሩ ጀመር። እነኝህም የጦር መሪዎች የኃይለ መለኮትን ልጅ ሕፃኑን የአስራ አንድ ዓመቱን ምኒልክን ቡልጋ ውስጥ ደብቀው ለመዋጋት ሲያስቡ የቴዎድሮስ ጦር ደረሰባቸው። ከዚያም ምኒልክን ይዘው ወደ ምንጃር ሸሹ።

አጤ ቴዎድሮስ ጓዛቸውን ቁንዲ ላይ ትተው እሳቸው ጦራቸውን ይዘው ወደ ጠምቂ መጡ። በዚያም በሰፈሩ ጊዜ የአገሬው ብዙ ነፍጠኛ ገባላቸው። ከዚያን ተጉዘው መገዘዝ ሲደርሱ ራስ እንግዳን ቢትወደድ ብሩንና፥ ቢትወደድ ውቤን ባንድነት አድርገው ምኒልክን እንዲይዙ ላኩዋቸው። እነኚህም

የተላኩት መኳንንት በረከት ከሚባለው ሥፍራ ምኒልክን ከሚያሸሸው ሠራዊት ጋር ተገናኝተው ውጊያ ገጠሙ። ከሁለቱም ወገን ጥቂት ሰው ካለቀ በኋላ አቶ ናደው (በኋላ ራስ) ዳርጌ እና አቶ ሀብቱን ልጅ ምኒልክን ይዘው በፈረስ አመለጡ። በኋላ ግን ከሚያባርራቸው ከቴዎድሮስ ኃይል ለማምለጥ ያለመቻላቸውን ባወቁ ጊዜ «እንግባ በከንቱ አንከራተት» ብለው መከሩና ምኒልክን ይዘው ከአጤ ቴዎድሮስ ታርቀው ገቡ። ቴዎድሮስ የሸዋን አስተዳደር አደላድለው ከሾሙት በኋላ ተድላ ጓሉን ለመያዝ ወደ ጐጃም ዘመቱ።

ቴዎድሮስ አባይን መሻገራቸውን ተድላ ጓሉ እንደሰሙ ጅብላ ገብተው መሸጉ። አጤ ቴዎድሮስም መንቆረር ላይ ሠፍረው ጅብላ የሚሰበርበትን ብልሃት ይፈልጉ ጀመር። የጅብላ ምሽግ ጠንካራ በመሆኑ ለቴዎድሮስ ጦር አስቸገረ። ይህን ችግር የተመለከቱት ቴዎድሮስ ጅብላን ትተው አራ መንኮራከር ላይ ሔደው ሠፈሩ። አገሩንም እንዲዘረፍ አዘዙ። በዚህ ጊዜ ተድላ ጓሉ ምርጥ የጦር መሪ የነበሩት ፊታውራሪ ቸኰል በዱር ነበሩና የቴዎድሮስ ወታደር ለጋበዲስ ከተባለው ቦታ ይዞአቸው ለቴዎድሮስ አቀረባቸው። ቴዎድሮስም ፊታውራሪ ቸኮልን ከወንድ ልጃቸው ጋር ባሶ ገበያ ላይ ሰቀሉዋቸው። ያንጊዜም አልቃሽ ብልታቸ ያያች አስመስላ

«ፊታውራሪ ቸኰል ሸማው አልቆበት

እንደተንጠለጠለ ግንዱን አየሁት።

አለች። የፊታውራሪ ቸኰል ሚስት ባላቸውና ልጃቸው ባንድነት ስለተሰቀሉባቸው

አባትና ልጁ ተጣልተው በገመድ

እኔ ልቅደም አለ ወይ እንዳሻ መልመድ።

ምን ብትንደግጥ ግንዱ ሲበጃጅ

ምን ብትደነግጥ ቀንበሩ ሲበጅ

እናቴ ሔድሁልሽ አይልምወይ ልጅ «ብለው አለቀሱ።

አጤ ቴዎድሮስ በዱር የሸፈተውን ሁሉ እያስያዙ ብዙ ሰዎችን ሰቀሉ። ከነዚህም መሀል የታወቁት መሪዎች ወንዴ ገብረ ወልድና ካሣ ቢሰውር

የተባሉት ነበሩ። ብዙ ሰው መሰቀሉ ያየች የጐጃም አልቃሽ የመሳለሚያ መስቀል አስመስላ

«ወይ አልተባረከ ይሄ ሁሉ ሰው

ንጉሥ መስቀልዎን ቢተውት ምነው።» አለች ከነዚህ ከተሰቀሉት ሰዎች ሌላ የደጃዝማች ተድላ ጓሉ ቁባት የነበሩት ወይዘሮ ጣይቱ ኤልያስ ተይዘው በእሳት አቃጥለው ገደሉዋቸው። የጣይቱን መቃጠል ያየች አልቃሽም

«እንኳን የሰገራ የሰንበት ልትደርስ

ነዳጥራ ቀረች ጣይቱ ኤልያስ» ብላ ገጠመች። የሰገራ የሰነብት እና ነዳጥራ የአገር ስም ነው። በአገር ስሙ አስመስላ ነደደች ለማለት ነው።

አጤ ቴዎድሮስ በጐጃም ላይ ይህን የመሰለ ጥፋት ቢያደርሱም ሙሉ በሙሉ ተግባሩ ብቻ ያተኮሩ አልነበሩም። አንድ መነኩሴ ከሽፍቶች ጋር ተባብሮ ነእብር ተብሎ ተማርኮ ከቴዎድሮስ ፊት ቀረበ። ቴዎድሮስም የተናደዱበት ጊዜ ነበርና ያን መነኩሴ እንዳዩ «በል በልልኝ» ብለው አዘዙ። መነኩሴው የታዘዘበትን ትእዛዝ ሲሰማ «ጃንሆይ እግዜር ያሳይዎ ቄስ ነኝ ቄስ ነኝ» እያለ ጮኸ። ቴዎድሮስም «ቄስ ከሆንክ እስቲ ዳዊትን ቁጠር። ስንት ነው?» አሉት። መነኩሴውም በዳዊት ውስጥ ስንት መዝሙሮች እንዳሉ አያውቁም ነበርና «ጃንሆይ እንዲያው ትይማሩኝ እንጂ የሜዳ ቄስ ነኝ» አላቸው። በንዴት ላይ የነበሩት ቴዎድሮስ በመነኩሴው አመላለስ ስቀው መማራቸውን ሩሴላ ያስታሙት ደራሲ ያልታወቀው ታሪክ ፀሐፊ ገልጾታል።

በዚህ ጊዜ ደግሞ አጤ ቴዎድሮስ ደጃዝማች ተድላ ጓሉን አድፍጠው አረሳስተው ለመያዝ አስበው ወደ ሸዋ የሔዱ መስለው ሠራዊታቸውን ሁሉ ዱር ውስጥ ደበቁት። የተድላ ጓሉን ሁኔታ እያሰለሉ ሲጠብቁ አንድ ቀን ማታ ራሳቸው ቴዎድሮስ ተራ ልብስ ለብሰውና ተራ ሰው መስለው አንድ አሽከር አስከትለው መንቆረር ከተማ ገቡ። ከያኔው መንቆረር ከዛሬው ደብረ ማርቆስ ከተማ እንደ ገቡ በየመንደሩ ሲዘዋወሩ ቆዩና በመጨረሻው ገደማ ካንዲት ባልቴት ቤት ገቡ። እንደገቡም ሴትዮዋ «እንዴት ዋልሽ» አሉዋት።

«እግዚአብሔር ይመስገን። አንተስ እንዴት ዋልህ?» አለቻቸው።

«እርቦኛልና እስቲ እንጀራ ስጭኝ» አሉዋት። ባልቴትዋም

«ለመሆኑ አንተ የማን ወታደር ነህ?» አለች።

ቴዎድሮስም «የተድላ ጓሉ ነኝ እንጂ የማን ብለሽ?» አሉዋት። ሴትዮዋ ይህን እንደሰማች ተነስታ እንጀራ በእርጐ አድርጋ ሰጠቻቸው። ቴዎድሮስ የሰጠቻቸውን እንጀራ በእርጐው እየማጉ መብላት ሲጀምሩ ሴትዮዋ ወደ አጠገባቸው ቀረብ ብላ ተቀምጣ «ብላ» ትላቸው ጀመር።

ሴትዮዋ ንጉሱ አጤ ቴዎድሮስ መሆናቸውን አላወቀችም። ቴዎድሮስም እንዲታወቁ አልፈለጉም ነበርና ከሴትዮዋ ጋር ጭውውት ጀመሩ። «ያ እብድ ንጉሥ ወዴት ደረሰ ይባላል? ወሬውን አልሰማችሁም?» አሏት።

ሴትዮዋም የንጉሱን መሰደብ ስትሰማ ተናደደችና «እብዶችስ የተድላ ጓሉ ወታደሮች ናችሁ እንጂ የተቀባ ንጉሥ እብድ አይባልም። አሁን ሸዋ መሔዱን ብትሰሙ አገር ለማጥፋት ደስ ብሏችኋል። ያ እብድ የምትሉት ንጉሥ ቢዘልቅባችሁ ደግሞ ድምጣችሁ ከአምባው ለመሽጐጥ ነው» አለች።

ቴዎድሮስም ቆጣ ብለው «ምነው ትሰድቢናለሽ። እንጀራሽን አንሺ አሉዋት። ሴትዮዋም ምነው አትጐርሰውም» ብትላቸው «ይበቃኛል፣ ደህና ሁኝ» ብለው ወጡ።

ተድላ ጓሉ ከምሽጋቸው አልወጣ ብለው ስላስቸገሩ አጤ ቴዎድሮስ ጐጃም እንዲዘረፍ አዘው ወታደሩ በሚዘርፍበት ጊዜ የዚያች ሴትዮ ቤትና ንብረት እንዳይዘረፍ ዘብ አቁመው እንድትጠበቅ አዘዙ። ዘረፋው ጋብ ሲል ቴዎድሮስ ያቺን ሴትዮ አምጡ ብለው አዘዙ።

የታዘዙ ወታደሮችም ሴትዮዋን ይዘው ወደ ቴዎድሮስ ሲሔዱ ሴትዮዋ ከመፍራትዋ የተነሳ እያለቀሰች እየተንቀጠቀጠች ቴዎድሮስ ዘንድ ደረሰች። ቴዎድሮስም ቆጣ በልው «በይ አንቺ ሴት? ትናንትና የተድላ ጓሉ ወታደሮች ከቤትሽ ገብተው ነበር? ሰምቻለሁና እውነቱን ንገሪኝ። በቀረ ከሳሽ ሊመጣብሽ ነው» አሏት።

ያልታወቀው ኢትዮጵያዊው ደራሲ ሩሲላ ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ የሴትዮዋን መልስ ሲገልፁ እንዲህ ይላል። «እግዜር ያሳይዎ ጃንሆይ። ከንጉስና

ከእግዜር ፊት እውነት መናገር ነው መልካም። ትናንትና እውነት በሀሰት አለውጥም። አንድ ጉበዝ ከቤቴ እባክሽ እርቦኛልና እንጀራ ስጭኝ አለኝ። የማን ወታደር ነህ ብዬ ብጠይቀው የተድላ ጓሉ ነኝ እንጂ የማን ልታደርጊኝ ነው አለኝ። እኔም ፈርቼ እንጀራ በእርጎ አቀረብሁለትና አልበላውም እንኳ አልሞጽሙጾ ጥሎልኝ ሔደ። የተናገረውንስ ለራሱ ይጥቀመው እኔ አልናገረውም። እኔ ግን የተቀባ ንጉሥ ሲመጣ ድምጣችሁ ሊጠፋ ዛሬ ንጉሱ ሸዋ ሔደው ሰምቻለሁ ድሃ ለማጥፋት ደስ ብሏችኋል ብዬ ተናገርሁትና ደህና ሁኝ ብሎኝ ጦሩን አስንቶ ወጥቶ ተጓዘ። ከዚህ ሌላ የተናገርሁት የለኝም። ካለ አንድ ጉበዝ ሌላ የገባብኝም የለ። ከሳሽ ይቁምብ» አለችና እጅ ነሳች።

ቴዎድሮስም ስለ እሳቸው የተከራከረችውን አስበው አምሳ ላምና አምሳ በሬ ሰጥተዋት «እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ ድረስ አትከሰስ አትወቀስ» ብለው አዘዙላት።

አጤ ቴዎድሮስ የሸፈተባቸውን አገር እየዘረፉና ሰውንም እየቀጡ በጌምድር ገቡ። የቴዎድሮስን ጐንደር መግባት ተድላ ጓሉ ሲሰሙ ከጅብላ ምሽጋቸው ራስ እንግዳን ለመውጋት ተሰለፉ። ጉሊት ከተባለው ቦታ ላይ ሁለቱም ወገኖች ጦርነት ገጥመው ራስ እንግዳ ድል አድርገው። ደጃች ተድላም ፈረሳቸው ላይ እንደ ሆኑ እየተዋጉ ወጊያውን ይመሩ ነበርና በመጨረሻው ጊዜ በሽጉጣቸው ተኩሰው ቢስቱ ሽጉጣቸውን አምዘግዝገው በመወርወር አንድ ሰው ገደሉና በፈረሳቸው እየጋለቡ አምልጠው ጅብላ ገቡ። የጐጃም አዝማሪ «ደጃች ተድላ መች ገንዘብ ወደደ ተኩሶ አምዘግዝጐ ጥሎላቸው ሔደ» ብሎ ገጠመላቸው። ራስ እንግዳም ከተድላ ጓሉ ሠራዊት ብዙ ሰው ማርከው ነበርና ምርኮኛውን ሁሉ በነፃ ለቀቁት። የምርኮኛውን በነፃ መለቀቅ ቴዎድሮስ ሲሰሙ ተቆጡ። ራስ እንግዳም «እንዴት ሳትቀጣ ትለቃለህ» በልው አስጠርተው አሰሩዋቸውና በእሳቸው ቦታ ራስ ውቤን ሾመው ሰደዱ።

በ1849 ዓ.ም በታህሣሥ ወር የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ወደ ኢትዮጵያ መጡ። አጤ ቴዎድሮስም በታላቅ ክብር ተቀበሏቸው። ሊቀ ጳጳሱ የመጡበት ዋናው ምክንያት አጤ ቴዎድሮስና በኢትዮጵያ የተሾሙት ጳጳስ አቡነ ሰላማ ስምምነት አልነበራቸውም። ከጳጳሱ ጋር ብቻ ሳይሆን ከቀሳውስትም ጋር ጠብና ክርክር ስለ ነበር ይሄን ነገር በሰላም ለመፍታትና ለማስማማት ብለው ነበር ይባላል። ቴዎድሮስን ከቀሳውስት ጋርም ሆነ

ከየመኳንንቱ የሚያጣላቸው ጳጳሱ አቡነ ሰላማ ነበሩ። አቡነ ሰላማ ጠባያቸው የመንፈሳዊነት ሳይሆን ዓለማዊነት ያጠቃው ነበር። ከቴዎድሮስም በፊት እቴጌ መነን ጋር ከፍተኛ ጠብ ተጣልተው ነበር። እቴጌ መነን በጳጳሱ አድራጎት ተናደው «ጳጳስ ባርያ ነው። በወርቅ ተገዝቶ መጥቷልና። ደግሞ ባርያ ጌታው እመቤቱ የወደዱትን ያዘዙትን ይሠራል እንጂ የርሱ ፈቃድ አይሆንም» ብለው ወቀሷቸው። ጳጳሱ አቡነ ሰላማ እኔ ባርያ ሆኜ በወርቅ በሺ ብር ተገዛሁ። አንቺ ግን በአገሬ አስር ብርም አታወጭ» ብለው መለሱላቸው። ይህን የጳጳሱን የስድብ መልስ ስንመለከት ከዓለማውያን አንደበት እንጂ ካንድ መንፈሳዊ አባት ሊነገር የማይገባው ነበር። የጳጳሱን ታሪክ ወደፊት አቡነ ሰላማ ከሚለው አርእስት ሥር ይመለከቱታል።

አጤ ቴዎድሮስ ምንም እንኳን ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ቢደክሙም የሚሸፍተው እየበዛ አልሳካልቸው አለ። በጐጃም አልበገርም ብለው ያስቸገሩ ደጃዝማች ተድላ ኋሉ በሸዋ መሸሻ ሰይፉ፥ በሰቆጣ ዋግሹም ገብረ መድህን በትግሬ ደጃዝማች ንጉሴ በአጠገባቸው በጐንደርም ጋረድ ክንፉንና ግንባሮ ካሣ ሸፍተው ቴዎድሮስን እረፍት አሳጥተዋል። ከእነኝህ ከታወቁት ታላላቅ ሰዎች ሌላ በየጉጡና በየአምባአው እየሸፈተ ያስችገራቸው ባላባትም ብዙ ነው። እነኝህ ሁሉ ቴዎድሮስ አምነው የሾሙዋቸው ሹማምንቶቻቸው ነበሩ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY



የጐንደር ከተማ ዕይታ

ከዚህም ሌላ በጳጳሱ በአባ ሰላማና በቀሳውስቱም ጭቅጭቅ ቴዎድሮስ ሰላም አላገኙም። ቀሳውስቱ የሚወጣባቸውን ደንብ በመቃወም ሁልጊዜ አቤቱታ ያቀርባሉ ጳጳሱ አባ ሰላማ ጥቅማቸ በተነካ ቁጥር በተራው ነገር ሁሉ ቴዎድሮስን ይገዝቷቸዋል። የመኳንንቱ መሸፈት የቀሳውስቱ ጭቅጭቅ የአባ ሰላማ ግዝት ከሌላው ከድሃው አቤቱታ ጋር ተዳምሮ ቴዎድሮስን የነገር ብዛት በጥብጧቸዋል። ቤተ ክህንትና መኳንንቱ መሬቱን ተካፍሎ በመያዙና የሚያርሰውና የሚያመርተውም ለየራሱ በመሆኑ ቴዎድሮስ ጦረኛ ሠራዊታቸውን የሚቀልቡት በማጣት መቸገራቸው ሌላው የቴዎድሮስ ችግር ነበር። ሠራዊታቸው ዘርፎ እንዲበላ ሲያዙም ባላገሩ ይነሳባቸዋል። ይህን የመሰለው ችግር ተደራርቦ የደረሰባቸው ቴዎድሮስ መኳንንቱ እንዲገብር ቤተ ክህነት የያዘው መሬት ተቀንሶ በይዞታውም እንዲገበር በማድረጋቸው መሬትን በመውረሳቸው ሽፍታውም ሆነ በጥባጩ እየበዛ ሔደ። ቴዎድሮስም እልህ ለእህል ተያይዘው አዋጃቸውን ሁሉ በኃይል ለማስፈጸም ቢጥሩም ተያይዘው አዋጃቸውን ሁሉ በኃይል ለማስፈጸም ቢጥሩም ቅጣታቸውን ፈርቶ ከሚያብርላቸው ኃይል የሚሸፍተው እየበዛ ሄደ። «ሰዎችን ከማጥፋት ሰዎችን

የሚጠሉብህን አጥፋ» የሚለው ምሳሌም በቴዎድሮስ ዘንድ ትክክለኛ አባባል አልነበረም። ሁሉን በኃይል ሁሉን በግድ የሚሉት ቴዎድሮስ የግዛት ዘመናቸው እየረዘመ በሔደ ቁጥር ችግራቸውም እየበዛ ሔደ።

ከችግራቸው በመጠኑ ብንመከለት በ1849 ዓ.ም ካህናት ተሰብሰበው ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርበው «ጃንሆይ ለሕዝቡ እንደ አባትህ በልው እንዳወጁት እኛንም እንደ ጥንት እንደ ነገሥታቱ ያኑሩን» ብለው አቤቱታ አቀረቡ። አቤቱታው የቀረበበት ምክንያት የጣሉባቸውን ግብር እንዲያነሱላቸውና የወሰዱባቸውን መሬት እንዲመልሱላቸው ነበር። ይህን አቤቱታ የሰሙት አጤ ቴዎድሮስም «እኔ ምን ልብላ? ሠራዊቴንስ ምን ላብላው? እኩሌታውን የመስቀል መሬት እኩሌታውን እሪም ገዳም እያላችሁ ወሰዳችሁት» አሏቸው።

የቀሳውስቱ አፈ ጉባኤም (ተናጋሪ) «አራት ወር በጐንደር ተቀምጠው አርማጨሆን ጠገዴን ወልቃይንት ስሜንን ትግሬን ይብሉ። አራት ወር በአሪንጉ ተቀምጠው በጌምድርን ላስታን፥ የጁን ወረሂመኑን ወሎን ሸዋን ይብሉ። አራት ወር ይባባ ላይ ተቀምጠው ሜጫን አገውን ዳሞትን ጐጃምን ይብሉ። እንደ ጥንቱ ነገሥታቱ ይሁኑ» አሏቸው። ይህን አባባል ስንመለከተው ንጉሡ ከቀሳውስቱ ራስ ላይ ተነስተው ባላገሩ ራስ ላይ እንዲሠፍሩ የሚጠይቅ ነው።

አጤ ቴዎድሮስም ለቀሳውስቱ ጥያቄ መልስ ሲመልሱ በሴት አጠራር እየተናገሩ «እኔ ብቻዬን በሆንሁልሽ ጊዜ እንደ አጤ ኢያሱ በሻሽ አንቀሽ ልትገድሊኝ ነው?» አሉና በፍትሐ ነገሥት እንዲወሰን አዘዙ። ፍትሐ ነገሥቱ በቀሳውስት የተዘጋጀ የሕግ መጽሐፍ በመሆኑ ለቀሳውስቱ ያደላልና የፍትሐ ነገሥቱ ውሳኔ ለቀሳውስት ሆነ። ይህን የሰሙት ቴዎድሮስም «አንድሽ አንባቢ አንድሽ ተርጓሚ» ብለው ተቆጥተው «የወደዳችሁንት ባልጋው አስቀምጡበት። እኔ እንደጋሎች እየዘረፍሁ እበላለሁ» ብለው ለመሄድ ከተቀመጡበት ጃንተከል ከተባለው ግንብ ሥር ተነሱ። ቴዎድሮስ ተነስተው መንገድ ሲጀምሩ በዚያ የነበረው ሕዝብ በሙሉ ተነስቶ መንገድ ሲጀምሩ ነገር ለካህናት ለጐንደር ከፍ ያለ መከራ እንደሚያመጣ የተገነዘቡት የአገር ሽማግሌዎች በቴዎድሮስ እግር ላይ ወድቀውና ለምነው መለሱዋቸው። ከጳጳሱና ከካህናትም ጋር አስታረቋቸው። ቴዎድሮስም ካህናት ፈሰስ

እንዲገብሩና የዳኝነት ገቢ ለንጉሱ እንዲንሆን ሌላ እንደ ጥንት እንዲያድሩ ብለው አወጁላቸው።

ወደ መኳንንቱ ብንመለስ ቴዎድሮስ ሁሉንም ተራ በተራ ለማስገበርና የከዳቸውንም ለመቅጣት ተዘጋጁ። በመጀመሪያም የላስታውን ዋግሹም ገብረ መድህን ለመምታት ከመነሳታቸው በፊት በግብር ላይ ለሚያዘምረው አዝማሪ፥

«ጐጃም ብንቆጣው በእሳቱ ተቀጣ

ወሎን ብንቆጣው በነፍጡ ተቀጣ፥

ይብላኝ ለወራሄ ይብላኝ ለሰቆጣ»

ብለው ለራሳቸው ግጥም ነገሩ። ከዚህም በኋላ ወደ ላስታ ተጓዙ። ዋግዙም ገብረ መድህንም ተጋጥመው ከተዋጉ በኋላ ዋግሹም ድል ሆነው ተማረኩ። ከእሳቸው ጋር ቢትወደድ ብሩና አባ ጫጉ የተባሉት የጦር መሪዎች ተያዙ። ቴዎድሮስም ሶስቱን መኳንንት አስረው ጦረኛውን የወጋቸውን ሠራዊት ግን ማሩት። መኳንንቶቹን ማለት ዋግሹም ገብረ መድህንን ቢትወደድ ብሩንና አባ ጫጉን ከጐጃም የተያዙትን አሰነኢ ደረሰን፥ ጉለም ወልደ ሚካኤልን ማሩ ሰሎሞንንና ሌሎች ሶስት ሰዎች በጠቅላላው ዘጠኝ መኳንንቶችን ረጅም ግራር ከሚባለው ሥፍራ በግንቦት ወር 1850 ዓ.ም ለመቀጣጫ ብለው እጅና እግራቸውን እየቆረጡ ሰቀሉዋቸው። ቴዎድሮስ በስቅላት ብቻ ለመቀመጫ ማድረጉ ሲበቃቸው ብዙውን ጊዜ ሰዎችን በስቅላት የሚገሉት በመጀመሪያ እጅና እግራቸውን ካስቆረጡ በኋላ ነበር። ይህም ምሕረት የሌለውና ድርብርብ ቅጣታቸው በቴዎድሮስ ላይ ጠላት አበዛባቸው እንጂ አልጠቀማቸውም።

ወደፊት እንደምናነበው ይህን የቴዎድሮስን ጭካኔና መጥፎ አቀጣጥ የሚያዩትና የሚሰሙት ሚስታቸው እቴጌ ተዋበች ብዙውን ጊዜ ጭካኔያቸውን እንዲተውና ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲያድርባቸው ይመክሩዋቸው ነበር። ቴዎድሮስ ግን የሚስታቸውን ምክር በሰላሙ ጊዜ ተቀብለው በንዴታቸው ጊዜ የሱታል። ቢሆንም እቴጌ ተዋበች በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የሚቀጡት ቅጣት እቴጌ ተዋበች ከሞት በኋላ እጅግ በጣም የተለየ የበረታ ቅጣት በመጀመራቸው

ቴዎድሮስን በምክር ይዘዋቸው የነበሩት እቴጌ ተዋበች እንደነበሩ ሕዝቡ ሁሉ አወቀ።

አጤ ቴዎድሮስ የከዱ ጠላቶቻቸውን ረጅ ግራር ከተባለው ሥፍራ ከሰቀሉ በኋላ ወደ ጐንደር ተመለሱ። በሸዋ የሾሙዋቸው የንጉስ ሣህለ ልጅ አቤቶ ሰይፉ በቴዎድሮስ ላይ ሸፍተው ምሥራቅ ሸዋ ነፃ መውጣቱን አውጀው አንኮበር ተቀመጡ። ይህን የሰሙት ቴዎድሮስም በግስጋሴ ወደ ሸዋ ዘመቱ። አቤቶ ሰይፉም ሰራዊታቸውን ይዘው ሙቅምድር ከሚባለው ቦታ ጦርነት ተጀመረ። ጦርነቱ እንደተጀመረ የሸዋ ሠራዊት በርትቶ በመዋጋቱ የቴዎድሮስ ጦር ወደ መሸነፉ አዘንብሎ ነበር። በኋላም አቤቶ ሰይፉ ተዋጊው ቴዎድሮስ መሆናቸውን ነገራቸው። አቤቶ ሰይፉ መጀመሪያ የተዋጉት የቴዎድሮስ ሹም ከሆነው ከአቶ በዛብህ ጋር መስሏቸው ነበር። በኋላ ግን የቴዎድሮስ መኖር ሲሰሙ ከጦራቸው መሀል በድብቅ ወጥተው ሸሹ። ሠራዊቱም የአለቃውን መሸሽ እንደሰማ እጁን ሰጠ። አጤ ቴዎድሮስም ይህን የወጋቸውን ሠራዊት በጀግንነቱ አድንቀው 500 ያህል ሰዎችን ቀኝ እጃቸውንና ግራ እግራቸውን እየቆረጡ ጣሉዋቸው። በዚህ ጊዜ አንዲት ባሏ የተቀረጠባት ሴት

«አጤ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ

የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነስተውት ሔዱ» ብላ ገጠመች።

አጤ ቴዎድሮስ በሰላም እጁን የሰጠውን ሠራዊት እጅና እግሩን ይቁረጡት እንጅ የሸዋው ሠራዊት ከእሳቸው ሠራዊት 1700 ያህል ወታደሮች ገድሎባቸዋል።

ቴዎድሮስ ከሸዋ ድል በኋላ ወደ ጐንደር ተመለሱ። ጥቂት ዕረፍት ካደረጉ በኋላ በወሎ ተበታትኖ የሸፈተባቸውን ባላባት ለማስገበር ከሚስታቸው ከእቴጌ ተዋበች ጋር ወደ ወሎ ጉዞ ጀመሩ። እቴጌይቱም አሟቸው ነበርና አርብ ገበያ ከተባለው ሥፍራ ሲደርሱ ለመጓዝ አቃታቸው። ከዚያ ጀምረው በአልጋ ላይ ተኝተው በሸከም ይጓዙ ጀመር። ክረምት የመግቢያው ጊዜ ተቃርቦ ነበርና በሰኔ ወር ወደ መቅደላ ሲጓዙ እቴጌ ተዋበች በ1850 ዓ.ም ነሐሴ 13 ቀን ረቡዕ ማታ ግራኝ ሜዳ በተባለው ሥፍራ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

አጤ ቴዎድሮስም የሚስታቸውን ሬሳ ከግራኝ ሜዳ ወደ መቅደላ ለመውሰድ ጉዞ ጀመሩ። ሠራዊታቸው ግን ጥቂት እንደ ተጓዘ በክረምት ውሃ

ሙላት ሊያስወስዱ ነው እያለ አንጐራጐረ። ቴዎድሮስም ይህን ሰምተው የእቴጌ ተዋበችን ሬሳ ከሠፈር አስመልሰው በሣጥን አድርገው ይዘውት የሚዞሩት ታቦት ካለበት ድንኳን ውስጥ አስቀመጡት። አጤ ቴዎድሮስ ሚስታቸውን እቴጌ ተዋበችን በጣም ይወዱዋቸው ነበርና ከታመሙበት ጊዜ ጀምሮ ለሚስታቸው ጸሎት ይዘው አዳራቸው ከቤተ ክርስቲያን ነበር። ምግባቸውም ሽንብራ ብቻ እንደነበረ የቅርብ ታሪክ ጸሐፊያቸው ደብተራ ዘነበ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ክረምቱ ሲወጣ የሚስታቸውን ሬሳ በሣጥን አስይዘው ደሴ ገቡ። ሬሳውን ከደሴ አኑረው የሸፈተባቸውን አመዴ በሽርን ለመውጋት ወደ እርቂ ሔዱ። አመዴ በሽርም የንጉሱን መምጣት ሰምተው ሸሹ። ከዚያ ተመልሰው ተሁለደሬን ዘረፉት። ቴዎድሮስን ተሁለደሬን ሲያዘርፉ ጐንደር በሽፍታ ተያዘ የሚሉ ወሬ መጣላቸው። ደሴ ከሚስታቸው ሬሳ ዘንድ አቡኑንና እጨጌውን ግራዝማች፥ ዓለሜንና ሌሎች የጦር መሪዎችን ትተው እሳቸው ጥቂት የዋድላን ጦር ይዘው ወደ ጐንደር ተመለሱ። ጐንደር ይዘው የነበሩት ሽፍቶችም የንጉሱን መምጣት ሲሰሙ ሸሹ። ከዚያ በግስጋሴ ተመልሰው የወሎው አመዴ በሽር ሠራዊቱን ይዞ ቢፈታ ከተባለ ቦታ መስለፉን ሰምተው በጥቅምት ወር 1851 ዓ.ም ደረሱበት። አመዴ በሽርም የንጉሱን መምጣት ሲሰማ ሖተላ ወደ ተባለ ሸሽቶ ሔደ። ቴዎድሮስም ተከታትለው ቢሔዱ አመዴ በሽር ኩሎ ወደ ተባለ ሥፍራ ሸሽቶ አመለጠ ቴዎድሮስ ግን ባላገሩን ያለ ርህራሄ ፈጁት።

ቴዎድሮስ የሚስታቸውን ሬሳ ሳያስቀብሩ በድንኳን ውስጥ ሣጥን አስቀምጠው ሁለት ወር ያህል እየተዘዋወሩ ከተዋጉ በኋላ ጥቅምት 11 ቀን 1851 ዓ.ም የሚስታቸውን ሬሳ ግሼን አስወጥተው አስቀበሩ።

አጤ ቴዎድሮስ የሚወዷቸውን የሚስታቸውን አስከሬን ግሼን ካስቀበሩ በኋላ ወደ በጌምድር ተመልሰው በኀዘን ተቀምጠው ሳሉ የደጃዝማች ክንፉ ልጅ ደጃች ጋረድ ሸፈተባቸው። ጋረድ አገር እየዘረፉና እየገደሉ አስቸገሩ። ጋረድ በሸፈቱበት ጊዜ የአጤ ቴዎድሮስ ታማኝ ወዳጃቸውንና በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል የነበረው ፕላውዲን ወደ እንግሊዝ አገር ለመሔድ ከቴዎድሮስ ተሰናብቶ ጉዞ ጀመረ። የካቲት 25 ቀን 1852 ዓ.ም ጐንደር ከተማ አካባቢ ቀሃ ወንዝ አጠገብ ሲደርስ የደጃች ጋረድ ሰዎች በጦር

ደረቱ ላይ ወግተው ያዙት። ይህንንም ቴዎድሮስ እንደሰሙ ሕይወቱን ለማዳን ብለው አንድ ሺ ብር ለጠላታቸው ለጋረድ ከፍለው ቁስለኛውን ወዳጃቸውን ፕላውዲንን አስለቀቁ። ፕላውዲንም በቃሬዛ ሆኖ ሰዎች ተሸክመውት ወደ ጐንደር መጣ። በጦር የተወጋው ቁስሉ ከፍተኛ ነበርና ፕላውዲን ጐንደር በደረሰ በዘጠኝ ቀኑ በተወለደ በ40 ዓመቱ ሞቱ።



የእቴጌ ጥሩ ወርቅ ሥርዓተ ቀብር

የወዳጃቸውን የፕላውዲንን ሬሳ በታላቅ ሥነ ሥርዓትና ክብር በጐንደር ከተማ ካስቀበሩ በኋላ ደሙን ለመበቀል ሰራዊታቸውን አስከትተው ወደ ጋረድ ዘመቱ። ደባርቅ ከሚባለው አካባቢ ጦርነቱ ተጀመረ። ጦርነቱ ተጀመረ። ጦርነቱ ተፋፍሞ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰዎች ወደቁ በዚህ መሀል ደጃች ጋረድ አጤ ቴዎድሮስን ነጥለው ለመግደል እያደቡ ሲደርሱ አጤ ቴዎድሮስ አጠገብ ቤል ዮሐንስ የተባለው እንግሊዛዊ ነበርና ጋረድን በጠመንጃ መትቶ ጣላቸው። ጋረድ ወዲያውኑ ሲሞቱ ይህን ያየው ወንድም ደግሞ የወንድሙን ገዳይ ሊቀ መኳስ ቤልን ወዲያውኑ ገደለው። አጤ ቴዎድሮስ ደግሞ የወዳጃቸውን የሊቀ መኳስ ቤልን ገዳይ የጋረድን ወንድም ገደሉ። ይህ ከሆነ በኋላ የጌታውን

መሞት ያወቀው የጋረድ ሠራዊት መሸሽ ሲጀምር የቴዎድሮስ ሠራዊት እያባረረ ይገድልና ይማርክ ጀመር። ከሞተው በስተቀርም 1500 ያህል የጋረድ ሰዎች ተማረኩ። አጤ ቴዎድሮስም ይህን የተማረከውን ሠራዊት ከደባርቅ ከተማ አስገብተው በሙሉ አስገደሉዋቸው። ማስገደሉ ብቻ ሳይበቃቸውም ጭንቅላቱን እያስቆረጡ እንደ ካብ እንዲካብ አዘዙ። ጭንቅላቱ በሚካብበት ጊዜም እየተቆጠረ ስለተካበ 1500 ጭንቅላት ተቆጥሮ መካቡን አለቃ ወልደ ማርያምና አለቃ ተክለ ኢየሱስ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ደጃች ጋረድን ድል ካደረጉ በኋላ ሌላውን ሽፍታ ደጃች ብሩ ኃይሉን ሊወጉ ወደ ጣና ሔዱ። ብሩ ኃይሉ ጣና ሐይቅ ደሴት ውስጥ ገብተው ቴዎድሮስ ሲርቁ እየወጡ እየዘረፉ፥ ቴዎድሮስ ወደ አካባቢያቸው ሲቀርቡ ደግሞ ከደሴት እየገቡ አስቸግረው ነበር። በዚህ ድርጊት ቴዎድሮስ በጣም ይናደዱና ይበሳጩ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ቴዎድሮስ ብሩ ኃይሉ የሚያዙበት ብልሃት አዘጋጅተው ወደ ጣና ዘመቱ። በጣና አካባቢ ያሉትን ጦርና ጐራዴ እያስያዙ በየጀልባው ላይ አሳፈሩት። የብሩ ኃይሉም ሠራዊት በየጀልባው እየሆነ ወደ መጣበት ጠላት ወደ ቴዎድሮስ ሠራዊት ተጓዘ። የሁለቱም ሠራዊት በባሕር ላይ ተገናኝቶ ውጊያው ጀመረ። የቴዎድሮስ ሠራዊት በባሕር ላይ ተገናኝቶ በጦሩ ላይ ገመድ እያሰረ ጦሩን ወርውሮ የጠላቱን ጀልባ ይወጋል። ጀልባው በጦር ሲወጋ ገመዱን እየጐተተ ጀልባውን ከነሰዎቹ በማቅረብ በጦርና በጐራዴ እየደበደበ የብሩ ኃይሉን ሠራዊት በዚህ ዓይነት ዘዴ ፈጀው። ብሩ ኃይሉም ድል ሆነው ተያዙ።

አጤ ቴዎድሮስ በአሁኑ ጊዜ የቀራቸው ኃይለኛውና ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር የወዳጅነት ውል እየተዋዋሉ ያስቸገሩዋቸው የትግራዩ ደጃዝማች ንጉሴ ናቸው። ደጃዝማች ንጉሴ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ እያሳደሙ ከውጭ አገር መንግሥት ጋር እንዴት ይዋዋሉ እንደ ነበረ ወደ ፊት በምዕራፍ 6 ውስጥ በሚነበበው በደጃች ንጉሴ ታሪክ ውስጥ ያገኙታል።

አጤ ቴዎድሮስ ደጃች ንጉሴን ለማጥፋት እየደጋገሙ ቢዘምቱም ሊያገኙዋቸው አልቻሉም። የደጃች ንጉሴን ከፈረንሳይና ከኢጣሊያ መንግሥታት ጋር አገር ቆርሶ የሚሰጥ ውል መዋዋላቸው አጤ ቴዎድሮስ እንደሰሙ ይህ ውል በሥራ ላይ ሳይውል ለማጥፋት በግስጋሴ ተጉዘው ትግራይ ገቡ። የአጤ ቴዎድሮስ በድንገት መምጣት እንደተሰማ በትግራይ

ሕዝብ ዘንድ ድንጋጤን ፈጠረ። ደጃዝማች ንጉሴንም ከፈረንጆቹ በተሰጣቸው ተስፋ ተማምነው ለጊዜው ባላቸው መሣሪያና ሠራዊት ቴዎድሮስን ለመግጠም አክሱም አጠገብ ሳጋሞ (?) ከተባለ ቦታ ሠራዊታቸውን አሰልፈው ቴዎድሮስ ጠበቋቸው። አጤ ቴዎድሮስም ከቦታው ደርሰው ጊዜው መሽቶ ነበርና የሁለቱም ሰራዊት ፊት ለፊት ተሰላልፎ ለበነገታው ውጊያ አሰፍስፎ ይጠባበቅ ጀመር።

ከአጤ ቴዎድሮስ ሠራዊት መሀል ሰባኪዎች ወጥተው ከደጃች ንጉሴ ሠፈር በስውር ገቡ። እንደገቡም «ንጉሱ አጤ ቴዎድሮስ እናንተን ወታደሮቹን ምረዋችኋል። ድሮም ቢሆን በግድ ታዛችሁ የወጣችሁ በመሆናችሁ በእናንተ ላይ ቂም የለም ብለዋልና ወደ ንጉሥ ሰፈር በሰላም ግቡ» እያሉ ሰበኩ። ይህን የሰሙት የደጃች ንጉሴ ወታደሮችም ሌሊቱን ከደጃች ንጉሴ ሠፈር እየከዱ ወደ ቴዎድሮስ ገቡ።

ደጃች ንጉሴ በማግስቱ ሠራዊታቸው እየከዳ መሔዱን ሰምተው አዘኑ። በተረፋቸው ሠራዊትም ቴዎድሮስን ለመግጠም እንደማይችሉ ገምተው ወደ ቴምቤን ተራራ ሸሹ። አጤ ቴዎድሮስም ተከታትለው ደረሱባቸውና ጥቂት ውጊያ ከተደረገ በኋላ ንጉሴ ድል ሆነው ተማረኩ። አጤ ቴዎድሮስም ደጃን ንጉሴንና ወንማቸውን ሌላውንም ተባባሪ መኳንንት ሁሉ እጅና እግሩን እየቆረጡ ጣሉዋቸው። አለቃ ወልደ አምርያም ከድሉ በኋላ ስለነበረው ወይም ስለ ደጃች ንጉሴ አሟሟት ሁኔታ ሲፅፉም «.......ከወደቁበት እህል ውሃ የሚሰጥ አልነበረምና ውሃ ጥም ቢጠናበት አገው ንጉሴ ይህን የወርቅ ድሪዬን ላትተርፍ ምን ያደክምሃል ብሎ ወዲያው ሁለቱም ሞቱ። እንዲህም በተደረገ ጊዜ ንጉሱ እጅግ ደስታ አድርገው በምገዛው አገር ህዩሉ ያልዘፈነልኝ ጠላቴ ነው በለው አዋጅ ነገሩ። በዚህም አዋጅ ቃል እሰይ ንጉሱን ቀናዎ እያለ ያልዘፈነ የለም.......» ብለዋል።

እርግጥ ደስ የሚያሰኝና የሚያዘፍንም ነበር። ምክንያቱም ቴዎድሮስ ከተነሱባቸው ጠላቶች ሁሉ ከውጭ መንግሥት ጋር ተዋውሎ የውጭ ጦር ሊያመጡባቸው የተዘጋጁት አገው (ደጃች) ንጉሴ ነበሩ። ሌላው ምክንያት ደግሞ የግል ጠላታቸውን ወይም የሥልጣን ተቀናቃኛቸውን ለመጣል በማሰብ ለውጭ አገር መንግስት አገር ቆርሶ ለመስጠር በአገር ላይ የሚፈጸም ትልቅ በደል ስለሆነ ነው።

አጤ ቴዎድሮስ አገው ንጉሴን ድል አድርገው በታላቅ ደስታ ወደ ጐንደር ሲመለሱ ከደጃች ውቤ በብር ደረስጌ ላይ ሠፈር አደረጉ። ከዚያም ሠፈር አድርገው ሳለ አንድ ወታደር የደጃች ውቤን ልጅ ወጣትዋን ጥሩነሽን አየ። ያም ወታደር በጥሩነሽ ውበኢት ተደንቆ ወደ አጤ ቴዎድሮስ መጥቶ «ጃንሆይ ለእርስዎ ለንጉስ የተገባች መልኳ እንደ ፀሐይ የምታበራ ሴት አገኘሁ» ብሎ ነገራቸው። አጤ ቴዎድሮስም ደህና ደህና ሰዎች ልከው ጥሩነሽን አስመጥተው ሲያዩ በውበቷ ደነገጡ። እንደ አለቃ ወልደ ማርያም አጻጻፍ ከእግር እስከ ራስ ቆጥረው አይተው ይህቺስ ጥሩ ወርቅ ናት አሉ ቴዎድሮስ ባወጡት ጥሩ ወርቅ ተባለ።

## ምዕራፍ 6

# ደጃች ተድላ ጓሉ - አቡነ ሰላማ - ወይዘሮ ተዋበች አሊ - ፕላውዲን - ዮሐንስ ቤልና ደጃች ንጉሤ

### ተድላ ጓሉ

ተድላ ጓሉ የራስ መርድ የልጅ ልጅ ናቸው። ደጃች ብሩ በጐጃም ሆነው ለማንኛውም መስፍን ወይም የበላይ ነኝ ባይ አልገብርም እያሉ በተቀመጡበት ጊዜ አንድ መነኩሴ «አልጋህን የሚወርሰው ተድላ ጓሉ ነው» ብሎ ነገራቸው። ያንጊዜ ተድላ ጓሉ ደረስጌ ይማሩ ነበር። የመነኩሴውን ትንቢት የሰሙት ደጃች ብሩ ከደረስጌ ትምህርት ቤት ተድላ ጓሉን አስይዘው ቋሚ ጨርቅ በሚባል አምባ አሠሩዋቸው።

ተድላ ጓሉ እንደታሠሩ ያ በፊት ትንቢት የተናገረው መነኩሴ ወደ ደጃች ብሩ ዘንድ መጥቶ «ብታስረውም ብትገርፈውም የክርስቶስ ትእዛዝ አይቀርምና ይልቅ ፍታው» ብሎ ነገራቸው ደጃች ብሩም ተድላ ጓሉን ፈትተው «እኔ በምገዛበት አገር እንዳትቀመጥ» ብለው አባረሩዋቸው። ተድላ ጓሉም ወደ አማራ ሳይንት ሔደው ከደጃች ትኩ ዘንድ አሽከርነት ገቡ። ይህን ነገር

ደጃች ብሩ እንደሰሙ «ጠላቴን ደብቀህ አኑረሃል አሉ። እሺ ብትል አባረው እምቢ ብትል ታጠቅ መጣሁ» ብለው ለደጃች ትኩ ላኩባቸው። ደጃች ትኩም ፈርተው ተድላ ጓሉን አባረሩዋቸው።

ተድላ ጓሉ ወደ ደራ ሔዱ። ደራ ሔደውም ከኦሮሞዎቹ ከነቦሩ ቱሪ ዘንድ ገቡ። ደጃች ብሩም ይህን ሲሰሙ የፊተኛውን ዓይነት እያስፈራሪያ ቃል ለቦሩ ቱሪ ላኩ። ቦሩ ቱሪም ፈርቶ ተድላ ጓሉን ከባላባትነቱ ግዛት ውስጥ አባረረ።

ተድላ ጓሉ ወደ ጃርሶ ሔዶ። ከጃርሶም ከኦሮሞው ባላባት ከነገዎ ገመዳ ዘንድ ገቡ። ይህን የተድላ ጓሉን ጃሮስ መግባትና ነገዎ ገመዳ ዘንድ መጠጋታቸውን ደጃች ብሩ ሲሰሙ ያንኑ የማስፈራሪያ ቃል ለነገዎ ገመዳ ላኩባቸው። ነገዎም የተድላ ጓሉን ጓይ ሲያጠና ደጃች ብሩ የሚያባሩዋቸው ንግርት ስላለ መሆኑን አጠና። ነገዎ ገመዳ ጉልበት ያለውና እንደ ደጃች ብሩ ሁሉ ትዕቢተኛ ነበርና ደጃች ብሩ ለላኩበት መልክት «አትችለኝምና አትምጣ። ግድ ያለህ እንደሆነ የምትወደውን የምታምነው ሎሌህን አስቀድመህ ሰደህ የሠራዊቱን ብዛት የልቤን ብርታት አሰልለህ ናብኝ። ብሎ መልሱን ላከ።

ደጃች ብሩ መልሱን እንደሰሙ ወደ ነገዎ ገመዳ አገር ሰላይ ወይም ተመልካች ላኩ። ነገዎ ገመዳም የተመልካቹን መምጣት እንዳወቀ የሰላሌንና የጃርሶን ኦሮሞ በሙሉ በሜዳ ላይ አሰልፎ ጉግሳ ጨዋታ በማስመሰል የፈረሱን የጦሩን ብዛትና አወራወር አሳየ። ከደጃች ብሩ የተላከው ሰላይ ተመልሶ «አንችለውምና እንቅር» ብሎ ነበረ። ደጃች ብሩም «እኔ የዳምጠው ጌታ የጋላ ፈረስ ነወይ ከፊቴ የሚቆም? ቂጥ ለቂጥ ነው የማማታው» ብለው ፎከሩ። የጐጃም መኰንንቶችም «አሳዳጅ እስከ ደጅ አንሁን በከንቱ ሰዎቻችን አይለቁ» በማለት መክረው ደጃች ብሩን ከውጊያው አስቀሩ።

ተድላ ጓሉ ከነገዎ ዘንድ ከከረሙ በኋላ ደጀን ካሉት ዘምዶቻቸው ጋር መላላክ ጀመሩ። ከዘመዶቻቸውም መልካም ምላሽ እንዳገኙ ነገዎ ዘንድ ቀርበው «አገሬ ናፍቀኝ። ዘመዶቼን ለማየት ልሂድ» ብለው ፈቃድ ጠየቁ። ነገዎም በአሳቡ ተስማምተው እስከ አባይ ወንዝ ድረስ በሸኚ አደረሳቸው ተድላ ጓሉ ከዘመዶቻቸው አገር አሳይ ዳርቻ ቢደርሱም የቆላው ሕዝብ ደጃች ብሩና ፈርቶ ተድላ ጓሉ እንዳይገቡ ከለከለ። በዚህም ምክንያት ቆለኛና ደገኞቹ ተጣሉ። በረብሻውና በግልግሉ መሀል የቅርብ ዘመዶቻቸው ተድላ ጓሉን

በድብቅ ወስደው ፊታውራሪ ፀጋ ቤት አስቀመጡዋቸው። ይህም ነገር ሚስጥሩ እያፈተለከ የተድላ ጓሉ መደበቅ ተሰማ። አድገህ ግኑሴ የሚባሉት ሰው ከሳሽ ሆነው ተነስተው «የደጃች ብሩን ጠላት ደብቀህ አኑረሃል» ብለው ፊታውራሪ ፀጋን ከስሰው ስለረቱ አድን ሺ አሞሌ ጨው እንዲከፍሉ ተበየነባቸው። ፊታውራሪ ፀጋም የተፈረደባቸውን ቅጣት በሙሉ ከፈሉ። በዚህም ጊዜ በደጃች ብሩ ላይ ራስ አሊ ጦር ስላወጁባቸው የተድላ ጓሉ ጉዳይ ቀዘቀዘ።

ደጃች ብሩ ከደጃች ካሣ (ቴዎድሮስ) ጋር ተዋግተው ድል ሆነው መያዛቸውን ተድላ ጓሉ ሲሰሙ ከተደበቁበት ከደጀን ወጥተው ለደጃች ካሣ አሸከርነት ገቡ። ቅድም እንደተባለው ደጃች ካሣም የደጃች ጓሉ ልጅ መሆናቸውን ባወቁ ጊዜ የጐጃም ጦር አዛዥ አድርገው ሾመዋቸው በበላያቸው ግን ባላምባራስ ወልታን የጐጃም ምስለኔ ብለው ሾሙ።

ተድላ ጓሉ በሰላም መኖር እንደጀመሩ በፊት እንደተባለው አዝማሪው ሊቀ መኳስ መርሻ በገጠሙላቸው ግጥም ምክንያት በካሳ ላይ ሸፈቱ። መንቆረር (በዛሬው ደብረ ማርቆስ) ላይ ሆነው ራሳችወን ደጃዝማች ብለው ደጃች ካሣ የሾሙዋቸውን ሰዎች እየሻሩ የእሳቸውን ወገኖች ይሾሙ ጀመር።

የተድላ ጓሉን ሹም ሽር አንዳንድ የጐጃም ክፍል አልቀበል አለ። ተድላ ጓሉ በበረንታና ሸበል ላይ የሾሙዋቸው ፊታውራሪ ወንድ አወክ የተባሉትን ነበር። ሕዝቡ ግን አንቀበልም ብሎ ባንድነት ተነስቶ ፊታውራሪ ወንድ አወክን አባሮ ጋትአነስ ከተባላው ቦታ አድርሷቸው ተመለሰ ሲመለስም።

«ሰርጉደው ሰርጉደው ሰርጉደው በጨሬ፥

ግድ ብሎ ተመጣ ባገሬ።

ፊታውራሪ ወንድ አወክ የጪስ ጨው ወዳጅ፥

የጐበዝ ሚስ ወዳጁ፥

አፈረሰው አፈረሰው በጁ» እያለ ጨፈረ።

ግጥሙ ፊታውራሪ ወንድ አወክ እንደ ተሾሙ በሕዝቡ ላይ የጪስ ጨው ግብር እንዲከፍል አውጀውበት ስለነበርና የሰው ሚስት መቀማት በመጀመራቸው የተጠማቸው ነው። የጪስ ጨው ማለት በመኖሪያ ቤት ሁሉ አንዳንድ አሞሌ ጨው ግብር መቀበል ወይም መክፈል ነው። ተድላ ጓሉ

ለጉብያ ሕዝብ ደግሞ ኃይሌ ወልደ ዮሐንስ ሾመው ነበርና የዚያም አገር ሕዝብ አንቀበልም ብሎ ኃይሌ ወልደ ዮሐንስን አባረረ። በተራውም

«እንደ ሊበን እንደ ኮሳሴ

እኛ አንከፍልም ፈሰሴ» እያለ ዘፈነ። ፈሰሴ ግብር ነው። በደጀን ሕዝብ ላይ የተሾሙት ደግሞ ባላምባራስ አድገህ ንጉሴ ነበሩ። የደጀን ሕዝብ በባላምባራስ ላይ አድሞ ተነሥቶ አባረራቸው በእሳቸው ላይ

«ያውለኛል ያውለኛል፥ ጦሬ

አድገህ ንጉሴ የተድላ ጓሉ አትድረስ ባገሬ

እንደቅማቱ እንደ አያቱ

ደጀን ነው ሞቱ» እያለ ዘፈነ። ይህን ሁሉ የሰሙት ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ተናደዱ። መጀመሪያም በበረንታና ሸበል ላይ ዘመቱ። የበረንታንና ሸበል ቆለኞችም ተሰባስበው ጫነፌቆ በተባለ ሜዳ ከተድላ ጓሉ ጋር ተጋጥመው ተድላ ጓሉ ድል አደረጉ። በዚህም ጦርነት ላይ የተማረከውን ሁሉ ተድላ ጓሉ ቀኝ እጁንና ግራ ጆሮውን እያስቆረጡ ለቀቁት። የተድላ ጓሉ ወታደርም ብድሩን ለመመለስ ሲዘፍን።

«ሰርጉድ ሰርጉድ ብሎ ሰርጉድ መነመነ፥

ቀኝ እጄን ገብሮ በግራው ለመነ» እያለ በተራው በበረንታና በሸበል ሕዝብ ላይ ዘፈነበት። ተድላ ጓሉም ከዚያ አልፈው በረጭ በሚባል ቦታ ሠፍረው የጉብያን ሕዝብ «ግባ» ብለው አወጁ። የገብያ ሕዝብም በበረንታ ላይ የደረሰውን ያውቃልና በጥሪው መሠረት በብዛት ተሰልፎ

«ቢገዛን መች ጠላሁ የራስ ኃይሉ ልጅ

የኋላውን ካሣ ብፈራው ነው እንጅ» እያለ እየዘፈነ ገባ ታላቁ ራስ ኃይሉ የተድላ ጓሉ አያት ናቸው። ደጃች ተድላም የጉበያን ሕዝብ በሰላም ካስገበሩ በኋላ ወንታ ሔደው ሰፈሩ። በዚያም ሆነው የደጀንን ሕዝብ ግባ ብለው ላኩበት። የደጀንም ሕዝብ በበረንታና ሸበል የደረሰውን ሰምቷልና በነቂስ ወጥቶ ገብረላቸው። ቆቃር ከተባለ ሠፈር ሲደርሱም የጁቤና የገሞ ሕዝብ

በሕብረት ሆኖ ወጋቸው። ደጃች ተድላ ድል አደረጉ። ከዚያም ምርኮኛ አሰባስበው በሙሉ ገርፈው ለቀቁዋቸው።

ቀረር ኤውስጣጤዎስ በተባለው አምባ የአሞራው ኃይሉ ልጆች የደጃዝማች ዘውዴ የአጐት ልጆች ዶሪ ኃይሉ ጀምበሬ ኃይሉ ወሌ ኃይሉ የሚባሉ ጀግኖች ነበሩና ተድላ ጓሉ ደንበጫ ላይ ሠፍረው «አታመልጡኝምና ግቡልኝ» ብለው ላኩባቸው መልዕክተኛው ደርሶ ይህን መልዕክት ሲነግር ዶሮ ኃይሉ ተነስቶ ፎከረ። ወዲያውም አቅራሪ አስጠርቶ

«ላሚቱ እንቦሳ፥ ጥጃውም ተኩላ ነው፥

አላቢዋ ዘንዶ ጋዲውም እባብ ነው፥

ቀጨሞን ተሻግሮ መካሪው ሰው ማነው» ብሎ ግጥም ገጠመ። ጋዲ ማለት ላሞች ሲታለቡ እግራቸ የሚታሠርበት ጠፍር ነው። የዶሪ ኃይሉን ግጥም የሰሙት የዶሪ ኃይሉ አማች የሆኑት ጀግናው ጓሉ አደሩ የተባሉት ደግሞ

ከተምጬ ወዲህ እንዳትሻገሩ

አፋው ነብር ነው የጓሉ አደሩ፥

እንደ ደጋን ምት ካንገት ካንገቱ

የጓሉ አደሩ ባፉ አመታቱ። እያሉ ግጥም ነገሩ። ባፉ ማለት የጐራዴ ስም ነው። ይህን ቀረርቶ ከአሳባቂ የሰሙት ተድላ ጓሉ ፎከረው ዘመቱባቸው። ዶሪ ኃይሉም በተድላ ጓሉ ሠራዊት ላይ ለሊት አደጋ ጥለው ብዙ ሰው ፈጅተው እሳቸውም በዚያውም በጦሩ ሜዳ ሞቱ። ወንድሞቻቸው ጀንበሬ ኃይሉና ወሌ ኃይሉ ግን አመለጡ። ደጃዝማች ተድላ የዶሪ ኃይሉን ሬሳ እንዳይቀበር ከልክለው ከመንገድ ላይ ተጥሎ ሕዝብ እንዲያየው አደረጉ።

ይህን የሰሙት የዶሪ ኃይሉ ሚስትም

«ተውት አትቅበሩት ይኑር ከመንገዱ

ምን ወንዝ አብቅሎታል እያሉ ይሂዱ» ብለው አንጐራጐሩ። አገው ያሉት የዶሪ ኃይሉ ወንድሞች የወንድማቸውን ድል መሆንና አሟሟት ሰምተው በአገው ውስጥ ተፈሪና ታዋቂ የሆነውን ሽፍታ አቶ እርጥቦ ወልደ አምላክ

የሚባለውን በገንዘብ ገዝተውና ሌላም ኃይል ጨምረው ተድላ ጓሉን ሊወጉ ተጓዙ። የፎዳ ከሚባለው ሥፍራ ላይም ከደጃች ተድላ ሠራዊት ጋር ጦርነት ገጥመው ተድላ ጓሉ ድል አደረጉ። አዝማሪው

«አገው የወደቁትን ያንን መብላት ትተው

እርጥቡን አጨዱት ደጃዝማች ቸኩለው።» ብሎ ገጠመላቸው።

ተድላ ጓሉ መንቆረር ተመልሰው ቤት ያሰሩ ጀመር። ወታደራቸው ግን ባለመሸለሙና ባለመሾሙ ቅሬታ ተሰምቶት በያለበት ያማቸው ጀመር። የወታደራቸውን ማጉረምረም የሰሙት ደጃች ተድላም በግብር ላይ ቆመው አዝማሪ

«ታንገራግር ወታደር፥

መልአክ በፈታው ጦር» ብለው ግጥም ነገሩ። ይህም ቢሆን ደጃች ተድላ በወታደር አያያዛቸውና እብግብር አበላላቸው ሠራዊቱ ይወዳቸው ስለ ነበር በጐጃም ላይ ተንሰራፍተው መቀመጥ ጀመሩ።

አጤ ቴዎድሮስ ሸዋን ወግተው ወደ ጐንደር ለመመለስ አባይን ተሻግረው ተድላ ጓሉ ከመንቆረር ወጥተው ከምሽጋቸው ገቡ ቴዎድሮስም ጅብላንብሬ ተድላ ጓሉን ሳልይዝ አልሔድም ብለው መንቆረር ላይ ሠፈር አደረጉ። የጅብላ ምሽግም ባለመሰበሩ ቴዎድሮስ በአገሩ ላይ ራስ እንግዳን ሾመው ጐንደር ገቡ

ቅድም እንዳነብነው ቴዎድሮስ ራስ እንግዳን ሽረው ለጐጃም ራስ ውቤን ሾሙ። ቴዎድሮስ ራስ ውቤን ይዘው ወደ ጐጃም ሔደው ግዛቱን አደላድለው ተድላ ጓሉን ለመያዝ መንገድ ሲጀምሩ የእንግሊዙ መልዕክተኛ ሚስተር ራሳም በመምጣቱ ቀሩ።

የደጃች ጐሹ ልጅ ደጃች ተሰማ አርባ አምባ ከሚባል ቦታ ታስረው ነበርና ልጃቸውን አዳልን አደራ ሰጥቼሃለሁ ብለው ለደጃች ተድላ ላኩባቸው። ልጅ አዳል በኋላ በአጤ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ተክለ ሃይማኖት የተባሉት ናቸው። ደጃች ተድላም ልጅ አዳልን ተቀብለው ከልጃቸው ከንጉሤ ጋር ይማር ብለው ጅብላ አስቀመጡዋቸው። በጅብላም ከሊቀ ካህናት ወርቄ ዘንድ እየተማሩ ዳዊት ከደገሙ በኋላ ከደጃች ተድላ ቤት መኖር ጀመሩ።

ደጃች ተድላ ወይዘሮ ጉዳዬ የተባሉት ቁባት (ውሽማ) አሉዋቸው። ልጅ አዳል ዕድሜያቸው ከጉርምስና ሲደርስ ተሽሽገው ከወይዘሮ ጉዳዬ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀሙ። ደጃች ተድላም ሰምተው ተቆጡ። ሊያስሩዋቸው ሲሉም ይህን ሐሳባቸውን የሰማ ፈንታ ወዳጆ የሚባል ሰው ልጅ አዳል ዘንድ ሔዶ «ልጅ አዳል ነህ እንዴ? ምነው እስታሁን? ኧረ ወዲያ ኧረ ወዲያ» እያለ ተናገረ። ልጅ አዳልም ፈንታ ወዳጆ እንዲሸሹ መምከሩ መሆኑ ገብቷቸው ያሏቸውን አሽከሮች አስከትለው ከደጃች ተድላ ቤት ጠፍተው ሔዱ። ጠለዛም ከሚባል አገር ገብተው ከብላታ ክብረ አብ ዘንድ ተቀመጡ።

ከብላታ ክብረ አብ ቤት የተቀመጡት በግልጽ ሳይሆን ቀን ቀን ከጫካ እየዋሉ ማታ ለአዳራቸው ከብላታ ቤት ያድሩ ነበር። ወይዘሮ ጉዳዬንም ደጃች ተድላ ገርፈው ብዙ ሥቃይ አሳዩዋቸው። ልጅ ዳልንም ቢያስፈልጉ አጡዋቸው። ደጃች ተድላ የሸፈቱባቸውን ገላቴ ኮልባንና ተሰማ ደረሶን ሊይዙ ወደ ሜጫ ዘመቱ። የደጃች ተድላን መዝመት ልጅ አዳል ሲሰሙ የጓደኛ አሽከሮቻቸውን መርሻ ፀዳሉንና ተሰማ አሉላን አጽቁ ደረሶን መሸሻ እንግዳን ወደ መንቆረር ልከው ወይዘሮ ጉዳዬን አስመጡ። ጉዳዬን በእጃቸው ካደረጉ በኋላ የደጃች ተድላን ከተማ መንቆረርን አቃጠሉት።

ደጃች ተድላም የከተማቸውን መቃጠል የቁባታቸውን መወሰድ ሲሰሙ ተናደዱ። ዘራፊዎቹ ያሉበትንም ቦታ ሲያጠያይቁ ደግሞ በረሃ መሆናቸውን አወቁ። ከሜጫ ተነስተው በደጋ ዳሞት ወጥተው በደገም ጫካ ውስጥ ወራሪ (ቀዳሚ ጦር) ሰደዱበት። ልጅ አዳልና ወይዘሮ ጉዳዬ ሲያመልጡ ተሰማ አሉላ ግን ዝንብል ከሚባል ደን ውስጥ እንደተደበቁ ተያዙ። ደጃች ተድላ ተሰማ አሉላን ሀብትና ንብረቱን በሙሉ ከወረሱ በኋላ «ከተማዬን ባቃጠልህበት እቁባቴን በወሰድህበት ተፋረደኝ» ብለው የተለያየ ፍርድ አስፈረዱባቸው። ደጃች ተድላ ግን ገርፈው ጅባል አሰሩዋቸው። ወይዘሮ ጉዳዬ ከልጅ አዳል ከበፊቱ በስርቆሹ ጊዜ ፀንሰው ነበርና ወንድ ልጅ ወለዱ። የተወለደው ልጅ በዛብህ ተባለ በዛብህ በኋለኛው ዘመን ራስ በዛብህ የተባሉት የራስ ኃይሉ ታላቅ ወንድም ናቸው።

ደጃዝማች ተድላ በየጥቃቅኑ ሽፍታ ቢረበሹም ብዙውን ጊዜ በሰላም አሳለፉት። አጤ ቴዎድሮስም የደጃች ተድላን መረጋጋት ሲያውቁ በሐምሌ ወር ሌትና ቀን ገስግሰው አጅባራ ከሚባል ቦታ ላይ ደርሰውባቸው ደጃች ተድላ

ለጥቂት ሲያመልጡ ሠራዊታቸውን ግን ቴዎድሮስ ፈጁባቸው። ከባላገሩም ሆነ ከወታደሩ የተማረከው ስምንት ሺህ ያህል ሰው ነበርና አጥር አሳጥረው ያን ሁሉ ሠራዊት በአጥር ውስጥ አጉረው በጐራዴና በጥይት ጨረሱት።

ደጃች ተድላ ጓሉ 12 ዓመት ገዝተው በ1860 ዓ.ም ሕዳር 6 ቀን ሞቱ። አጤ ቴዎድሮስም የተድላ ጓሉን መሞት ሲሰሙ አዘኑ፥ ደነገጡም። ምክንያቱም አዋቂዎች «ተድላ ጓሉ ሲሞት አንተ ተከትለህ ትሞታለህ» ብለዋቸው ስለነበር ነው። ተድላ ጓሉ በይፋ አልተቀበሩም። በይፋ የተቀበሩ እንደሆነ ቴዎድሮስ መጥተው ይወጉናል በሚል ፍራቻ በድብቅ የውሽ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስትያን ተቀበሩ።

አልቃሽ

«አጥር ቀደው ወጡ ነውረኛ መስለው፥

እረኛ ሳይሰጡት ለዚህ ሁሉ ሰው።

ተንግዲህ ወዲህ የልቤን ልናገር፥

አባ መላክ ተድላ ጠጁ ውሃ ነበር።

በሸዋ ተላካ ዋናው ሊመጣ ነው፥

በጎንደር ተላከ ዋናው ሊመጣ ነው፥

ተድላ ጓሉ ሞቶ ጐጃም ሊፈታ ነው።

አልሞተም ይሉናል ደጃዝማች ተድላን

አሁን እሑድ ሲቀር የምናውቀውን፥

እሻሻ ነው እንጂ የእሥራኤል ሞት፥

እንዲያልቅ ሰው ተድላን ለምን ቀበሩት» አሉላቸው።

## አቡነ ሰላማ

ደጃች ውቤ ታላላቅ ሊቃውንቶችን መርጠው አለቃ ሀብተ ሥላሴን የበላይ አድርገው ከግብጽ ጳጳስ እንዲያመጡላቸው ወደ ካይሮ ላኩዋቸው። መልዕክተኞቹ ከመሔዳቸው በፊትም ደጃች ውቤ «……ሃይማኖቱን ከዚያው ወስናችሁ በማናቸውም ተስማምታችሁ ከዚህ እንደ ቀድሞ ጠብ እንዳይሆን ቀዋሚ ነገር ይዛችሁ ጳጳሱንም የተገባ ባለ አእምሮ ሰው መርጣችሁ ይዛችሁ ኑ» ብለው መከረውና አስጠንቅቀው ሰደዱዋቸው። ደጃች ውቤ ጳጳሱ እንዲመጣላቸው የፈለጉበት ምክንያት ራስ አሊን አሸንፈው እሳቸው የመንገስ ፍላጎት ስለነበራቸው ነው።

አድዋ ላይ ይኖር የነበረውን ኢዘንበርግ የተባለውን ሚስዮናዊ በሃይማኖት ስብከት ምክንያት ደጃች ውቤ ተጣልተው ካገር እንዲወጣ አድርገውት ነበር። ኢዘንበርግ በዚህ ጊዜ የሚኖረው ካይሮ ነበር። የደጃች ውቤ መልዕክተኛ መላካቸውን በሰማ ጊዜ ወደ ሊቀ ጳጳሱ ዘንድ ሒዶ 1700 ብር (አንዳንዶቹም 7000 ይላሉ) እጅ መንሻ ሰጥቶ አንድራዎስ የሚባለው የ25 ዓመት ወጣት ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ያደርጉ እንድ ለመናቸው። ኢዘንበርግ ይሄን ያህል ስጦታ የሰጠበት ምክንያት ወዳጁ አንድራዎስ ወደ ኢትዮጵያ ቢላክ የበለጠ ገንዘብ እንደሚከፍለው ሰለሚያውቅና ስለተነጋገሩም ነው። ሊቀ ጳጳሱም በኢዘንበርግ ሐሳብ ተስማሙ።

ኢትዮጵያውያኖቹ መልዕክተኞች ከሊቀ ጳጳሱ ዘንድ ቀርበው የተላከውን እጅ መንሻ ከሰጡ በኋላ ሊቀ ጳጳሱ ከአንድራዎስ አገናኝተው «እሱን ነው የምሰጣችሁ» አሏቸው። የአባ አንድራዎስን የመጀመሪያ ታሪክና ሁኔታ ብተወውም በዚያ ባሉ መነኮሳት ዘንድ በመጥፎ ምግባር የታወቁ ሰው ነበሩና አንዳንድ መነኮሳት በምስጢር በደጃች ውቤ መልዕክተኞች የተመራጩን ጳጳስ ታሪክ ነገሩዋቸው። መልዕክተኞቹም ከሊቀ ጳጳሱ ዘንድ ቀርበው «…….የ25 ዓመት ወጣት እንዴት አቡን ሆኖ ያንን ሁሉ ሕዝብ ሊመራና ሊጠብቅ ይችላል።…….40 ዓመት የሆነው ሌላ ሙሉ ሰው ይፈልጉልን…… ብለው አመለከቱ። ሊቀ ጳጳሱም አስብበታለሁ ብለ መለሱላቸው።

ከደጃች ውቤ በተላኩት መልዕክተኞች መሐል ያለመግባባት ተነሳ። ከመልዕክተኞቹ አንዱ የሆኑት አለቃ ኩላሊት ኪዳነ ማርያም «ይህን ወጣት

ጳጳስ ብንወስድ ልጅ ነውና ብዙ ዘመን ይቆይልናል» የሚል ሐሳብ አቀረቡ። የመልዕክተኞቹ መሪ አለእቃ ሀብተ ሥላሴ ደግሞ «ሞት በሰው ልጅ ሆነንን? አሮጌ ሳለ ልጅ ሲሞት አላየህምን?» ብለው መለሱ። ይህ ያለ መግባባት በመልዕክተኞቹ መሀል እንዳለ ወደ ሮም ሊሄዱ ተነሱ። መልዕክተኞቹ ወደ ሮም የሚሔዱበት ምክንያት ገና ከትግሬ ከመነሳታቸው በፊት ደጃች ውቤ በትግራይ ይኖሩ የነበሩትን ካቶሊካውያን አባ ያዕቆብን አስጠርተው «እነዚህን መልዕክተኞቼን ጠብቀህ ውሰድልኝ» ቢሏቸው አባ ያዕቆብ በነገሩ ተስማምተው እሳቸውም በተራቸው «ይህን ከታዘዝሁ እኔም አንድ ነገር ልለምንዎ። በዘመዶቼ ዘንድ ክፉ እንዳይሆንብኝ እነዚህ ሰዎች ከጴጥሮስ መቃብር ከጳውሎስ ዝህር ሮማ ደርሰውልኝ ይምጡ ቢሏቸው ደጃች ውቤ «እሺ ይድረሱልህ። እኔ አገር ቢያዩልኝ እወዳለሁ» ብለው ሮማ ሄደው አገር አይተው እንዲመጡ አዘዋቸው ስለ ነበረ ነው።

መልዕክተኞቹ ወደ ሮማ ለመሔድ መርከብ ተከራይተው ገንዘብ ከፍለው ከጨረሱ በኋላ የአንድራዎስ ጳጳስ መሆን የተስማሙት አለቃ ኩላሊት ኪዳነ ማርያም በመጨረሻዋ ሰዓት ላይ ወደ ሮማ አልሔድም ብለው ቀሩ። ሌሎቹ ግን በመርከብ ተሳፍረው ወደ ሮም ሔዱ። መልዕክተኞቹን ወደ ሮም መሔድ ያረጋገጡት አለቃ ኩላሊት ኪዳነ ማርያም ከሊቀ ጳጳሱ ዘንድ ቀርበው «ይህን የተባለውን ሰው ወደነዋልና ጳጳስ አድርገው ይስጡን» ብለው ስለጠየቁ ሊቀ ጳጳሱ እሺ ብለው አንድራዎስን የጵጵስና ስማቸውን ሰላማ ብለው ሾመው ሰጡዋቸደው። ወደ ሮም ሔደው የነበሩት መልዕክተኞችም ከሮም ተመልሰው ጳጳሱ እንዲሰጣቸው ሊቀ ጳጳሱን ቢጠይቁን «ያንኑ እናንተ የጠላችሁትን ወንድሞቻችሁ ተባብረው ወደው ስለመረጡት እርሱን ሾሜ ሰድጃለሁና ሒዱ ተከተሉ» አሏቸው። አቡነ ሰላማ በዚህ ዓይነት የመጡ ሰው ናቸው። ይህን ታሪክ እዚህ ያመጣሁት አጤ ቴዎድሮስ አባ ሰላማን ማስርና መፍታታቸው፥ ማጉላላታቸው ብቻ በአገራችን ስለተጻፈ አንዳንድ ሰዎች ያለቦታው የቴዎድሮስን ክፋት እያጋነኑ በማውራታቸው እውነተኛውን ለማሳወቅ ያህል ነው።



ABOONA SALAMA, METROPOLITAN OF ETHIOPIA.

አቡነ ሰላማ

ሰላማ ተብለው ከእስክድንርያ የመጡት ግብሳዊ ጳጳስ ገና አስመራ ሲደርስ ከውቤም ሳይተዋወቁ «አሊን ያልወጋ ውጉዝ ነው» እያሉ ሕዝቡን አወገዙ። ራስ አሊና ደጃች ውቤ ጦርነት ተጋጥመው ራስ አሊ ድል ሲያደርጉ አቡነ ሰላማ ተማርከው ከራስ አሊ ዘንድ ቀረቡ። ራስ አሊም «ፍየል ከመድረስዋ ቅጠል መበጠስዋ። ዛሬ በእንግድነት ይህን የሠራ ቆይተህስ ምን ትሠራ ይሆን። ጳጳስ ታረቁ አትዋጉ እያለ ለምኖ ገዝቶ ያስታርቃል አንጂ ተዋጉ ብሎ ያስተላልቃልን። እኛን ለመዋጋት ማነው የላከህ። ሰላማስ ብሎ ማነው የሰየመህ። ሰላም አጥፊ የሰላም ጠር እንጂ። ወየው አቡን ባልሆንክ፤ እንደ ግብርህስ ሞት ይገባህ ነበር። ምንም ሥራህ የሰይጣን ቢሆን ስምህ ጳጳስ ነውና አንተን ገድዬ ስሜን አላከፋም። አሁን ጐንደር ወርደህ ከአቡን ቤት ተቀመጥ። ከዚህ አትናወጥ» ብለው መውቀሳቸውን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ጽፈዋል።

ራስ አሊ የያዙባቸውን ቂም ለማሻር በዚያን ጊዜ ለራስ አሊ ይገብሩ እንጂ ራሳቸውን ችለው የሚኖሩበትን የሸዋን ንጉሥ ሣህለ ሥላሴን አቡነ ሰላማ ማውገዝ ጀመሩ። «ሣህለ ሥላሴ ውጉዝ ነው» እያሉ በይፋ በአደባባይ ይናገሩ ጀመር። ይህን የሰሙት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴም ከየአድባራቱ ሊቃውንት ሰብስበው የሊቃውንቱም የበላይ መሪ አለቃ አሥራትን አድርገው ጠይቁልኝ ብለው መልዕክተኞቻቸውን ወደ ጐንደር ላኩ። መልዕክተኞቹም ከራስ አሊ ዘንድ ቀርበው «ንጉሣችን በምን ምክንያት ይወገዛሉ። ይዳኙን።» ብለው አመለከቱ። ራስ አሊም «ነገር እንዳለው በሥርዓት ይባላል ይከራከር። እንደሌላውም ግዝቱን ይፍታ ብለው ጨምረው ወደ እናታችሁ ወደ እቴጌ መነን ሰደዷዋቸው።

እቴጌ መነንም ጳጳሱን «ቀርበህ ተባባል። ወይም ግዝት ፍታ» ቢሏቸው አልዳኝም ብለው ተከታዮቻቸውን ጦር አስነስተው ብዙ ሰው አለቀ። ከዚህ በኋላ ራስ አሊ እንዲህ ያለ ጳጳስ አያስፈልገኝም ብለው ከጐንደር እንዲወጡ አደረጓቸው። ያንጊዜ ደጃች ውቤ ከራስ አሊ ጋር ታርቀው በግዛታቸው ነበሩና አባ ሰላማ እንደገና ተመልሰው ወደ ደጃች ውቤ ገቡ። በዚህ ጊዜም የጐንደር ሊቃውንት በእኙሁ በጳጳሱ በሃይማኖት ምክንያት ቂም ይዘው ነበርና

«ግድግዳው ቤታችሁ ያው ይሻላችኋል
ካቡን አትጠጉ ይናድባችኋል።

መናዱ እንኳ ቢቆይ ከዚህ ከእርጉዝ ካብ፥

አይታጡምና ዳሞትራና እባባ» እያሉ ገጠሙባቸው። የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ መልዕክተኞችም ከጐንደር ተመልሰው አንኮበር ሲገቡ ደብተራ ጉልቴ የተባሉ ሊቅ

«እንዳሥራት ማን አለ የሚያውቅ ድጓውን

ትግሬ መርቶት መጣ ያን ረዥም አቡን» ብለው ገጠሙ።

አጤ ቴዎድሮስ ገና በሽፍትነት ሳሉ ራስ አሊን ድል ካደረጉ በኋላ የደጃች ካሣን ኃይል መበርታት ያዩት አቡነ ሰላማ ከደጃች ውቤ ዘንድ እንደሆኑ «እኔን ብትቀበለኝ ቀብቼ አነግስሃለሁ» እያሉ በምሥጢር ይላላኩ ጀመር። ደጃች ካሣም ውቤን ድል ሲያደርጉ በቃላቸው መሠረት አቡነ ሰላማ ደጃች ካሣን ቴዎድሮስ ብለው ቀብተው አነገሱ።



ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ

አቡነ ሰላማ በጐንደር ሊቃውንቶች ዘንድ እንደማይወደዱ አጤ ቴዎድሮስ ያውቁ ነበርና የጐንደርን ሊቃውንቶች ሰብስበው «አባቴን ተቀበሉልኝ። ታረቁልኝ» ብለው ለመኑ። ሊቃውንቱም «የሃይማኖት ነገር በሥርዓት እንጂ በልመና አይሆንም። የእንግዜር ሃይማኖት ለሰው ብሎ በሰው ልመና መካድና ማስካድ ለኛም ለእርስዎም አየባምና በዚህ ነገር እሺ ልንልዎ አንችልም።» ብለው መለሱ። በዚህም ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ተናደው በአጠገባቸው የቆሙትን ወታደሮች «በል በልልኝ» ብለው አዘዙ። ወታደሩም የሊቃውንቱን ልብስ እየገፈፈ ጥምጥማቸውን እያወለቁ በሚጫወትባቸው ጊዜ አቡነ ሰላማ ከዚያም ነበሩና በአድራጐቱ ተደስተው ሊቃውንቱን የሚያሰቃየውን ወታደር «እግዚአብሔር ይፍታህ» አሉት። ይህን የአቡነ ሰላማን «እግዚአብሔር ይፍታህ» ማለት የሰማው ወታደር የሊቃውንቶቹን ቀሳውስት ቤት ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ጭምር ከተማዋን በሙሉ ዘረፋት።

አቡነ ሰላማ ከግብጽ አገር ሲመጡ የተከፈለው አሥር ሺ ብር ነው። የዋሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ያህል ገንዘብ ከፍሎ ጳጳስ ማስመጣቱ በያገሩ እየዞሩ ድቁናም ቅስናም እየሰጡ ሃይማኖቱን እንዲጠብቁለትና እንዲያስፋፉለትም ነበር። ቴዎድሮስ ዎልድ ሜየር እንደጻፈው አባ ሰላማ ግን አገር ላገር አልንከራተትም ብለው ትንፋሻቸውን በስልቻ እየሞሉ ለሸዋና ለጐጃም ይልኩ ነበር። አንድ ሰው ለመቅሰስ በሚፈልግበት ጊዜ ከስልቻው መጠነኛ ትንፋሽ በራሱ ላይ ይነፋበትና ቄስ ሆነ ይባል ነበር።

ከአጤ ቴዎድሮስ ጋርም ቢሆን በፍቅርና በሰላም አልኖሩም። የጠብ መነሻ የሆነውም ሚስዮናውያኖቹ ከራፍ እና ፍላድ የመጡ ጊዜ ነው። እነኚህ ሁለት የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ከኢትዮጵያ እንደ ገቡ ደርበ ታቦር ሔደው ከራሳቸው ጳጳስ ከጉባት የተጻፈላቸውን ደብዳቤ ይዘው አቡነ ሰላማ ዘንድ ቀረቡ። አቡነ ሰላማም በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት ሚስዮናውያኖቹ ስብከታቸውን እንዲሰብኩ ፈቀዱላቸው። በማግስቱም ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ሲያገናኙዋቸው አጤ ቴዎድሮስ «የምፈልገው ጥበበኛ እጅ ሥራ አዋቂ ነው። ጠመንጃና ሌላም የሚሠራ እንጂ ሰባኪ ለአገሬ ምን ይጠቅማታል» ቢሉ አቡነ ሰላማ «በሥራዬ በሃይማኖት ጉዳይ አትግባ» ብለው ቴዎድሮስን ገሰጡዋቸው። ቴዎድሮስም ከዚያን ቀን ጀምሮ ቂም ያዙ።

አባ ሰላማ ከቴዎድሮስ ጋር በነበሩበት ጊዜ የጐንደርና የጐጃም የሸዋም ቀሳውስት ጳጳሱን አይወዱዋቸውም ነበር። ከክህነት በስተቀር ለጳጳሱም አይታዘዙም ነበር። ይህን የቀሳውስቱን ያለመታዘዝና መጥላት ያወቁት አባ ሰላማም ቂጭታቸውን በቴዎድሮስ በትር ለማስመታት እያሉ ቀሳውስቱ ሥርዓት የሌለው በመሆኑ በሥርዓት እንዲያድር እንዲያደርጉ ለቴዎድሮስ ይነግሩዋቸው ነበር። አጤ ቴዎድሮስም እውነት እየመሰላቸው ከቀሳውስቱ ጋር በየጊዜው ይጣሉ ነበር። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተሰምቶ የማይታወቅ ትእዛዝም ቀሳውስቱን ያዙ ነበር።

በ1849 ዓ.ም በመስከረም ወር አጤ ቴዎድሮስ ማንኛውንም ቄስ ጥምጥም ጠምጥሞ ከእሳቸው ዘንድ እንዳይቀርቡ የሚል አዋጅ አወጡ። ይህን ምን ጊዜም ተደርጐ የማያውቅ ነገር ነውና ካህናቱ ጥምጥም ማውለቅ የክብራቸው መዋረድ መሆኑን አውቀው ከንጉስ ዘንድ ቀርበው «ጃንሆይ ጥምጥም ክብራችን ነውና ይበይኑልን» ብለው አመለከቱ።

አጤ ቴዎድሮስም «ከታቦት በገባችሁ ጊዜ ስለምን ጥምጥማችሁን ታወልቃላችሁ? ቢሏቸው እግዚአብሔር አድሮበታል ብለን ነው» አሏቸው። ንጉሡም «በኔ እግዚአብሔር አላደረብኝምን። እግዚአብሔር በኔ አድሮ አይደለም የሚያስገዛኝ?» አሏቸው። ካህናቱም አዎን አሉ። ቴዎድሮስም «እንግዲያው ምነው እኔ ሥራት አስተምራችሁ ብዬ ነው። ጠምጥሙ» ብለው አዋጁን ሻሩላቸው። ይህ አዋጅ ቴዎድሮስ አምነውበት ያወጁት ያለመሆኑን ብዙም ሳይቆይ በመሻራቸው ያስታውቃል። በኋለኛው ዘመንም ቴዎድሮስ በቀሳውስት ዘንድ ከፍተኛ ጥላቻ መነሳቱን ካወቁ በኋላ ያበቁዋቸውን ጳጳሱን አባ ሰላማን መቅደላ ወስደው አሰሩዋቸው።

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ኢትዮጵያ መጥተው በነበረ ጊዜ ከኢትዮጵያ ጳጳስ ከአቡነ ሰላማ ጋር ተማክረው ለንጉሥ ቴዎድሮስ ሳያማክሩ ወደ ግብጽ መሪ ሠራተኛ እንዲልክ ደብዳቤ ጽፈው ነበር። የደብዳቤውን መጻፍ ቴዎድሮስ እንደሰሙ «ከኔ ሳትማከሩ እኔ ሳልፈቅድ እንዴት ለግብጽ ንጉሥ ደብዳቤ ጻፋችሁ?» ብለው ቢጠይቋቸው ሁለቱም ኃይለ ቃል ተናገሩዋቸው። በዚህ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ የሁለቱም ጳጳሳት ቤት በእሾህ አጥር አሳጥረው ከዚያ እንዳይወጡ በዘበኛ እንዲጠበቁ አደረጉ። አጤ ቴዎድሮስ

እንኳን ከውጭ አገር መንግሥት ጋር መጻጻፍ ቀርቶ በአገር ውስጥም ቢሆን ሁሉን ነገር ለማወቅ የሚፈልጉ በመሆናቸው ሁለት የግብጽ ጳጳሳት በራሳቸው ሥልጣን በሰው አገር ጉዳይ በምስጢር መጻጻፋቸው ጥፋት ነበር። ሆኖም ቀሳውስትና የአገር ሽማግሌዎች በነገሩ ገብተው ቴዎድሮስን ከጳጳሳቱ ጋር አስታረቋቸው።

በ1850 ዓ.ም የጁ ውስጥ ኢየላ ከተባለው ቦታ ሠፍረው ሳለ አንድ ሰው ወደ ንጉሥ ጮኸ። የሰውየውን ጩኸት የሰሙት ቴዎድሮስም አቡነ ሰላማን «ለምን ያስጮሁብኛል?» ቢሏቸው አቡነ ሰላማ «አንተ በኔ ግዛት ምን አገባህ» ብለው የተገላቢጦሽ ንጉሱን ተቆጡ። ንጉሱም ተናደው ቢቆጡ ጳጳሱ ብሰው በኃይል ተቆጥተው «ታቦት ያነሳ ይህን ሰው የተከተለ ውጉዝ ይሁን» ብለው ገዘቱ። ንጉሱም ግዝቱን እንደሰሙ ያዘው በልው ቄርሎስ አስያዙዋቸው። የጳጳሱን መያዝ ያዩት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ግዝቱን ፈቱ። አባ ሰላማ ግን ለምን የገዘትኩትን ይፈታሉ ብለው ከሊቀ ጳጳሱ ከቄርሎስ ጋር ተጣሉ። በእነኝህ ሰዎች መጣላት ምክንያት ታላቅ ሽብር ሊነሳ ሲል ቴዎድሮስ ነገሩን አብርደው ታረቁዋቸው። ይህን በመሳሰለ በጥቃቅኑ ነገር ሁሉ ቴዎድሮስን የሚያበሳጫቸው ብዙ ነበር።

አቡነ ሰላማ አምስት ዓመት ያህል በግብፅ ከሠሩ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ብዙ መንገላታት አድርሰውባቸው በመጨረሻው እንደ ገና ከ62 ተከታትዮቻቸው ጋር ከመቅደላ ተራራ አስገብተው አሠሩዋቸው። ከዚያም ሆነው ከሸዋው ንጉሥ ከዳግማዊ ምኒልክ ጋር በሚስጥር «ከዚህ አውጣኝና አነግስሃለሁ» እያሉ ሲጻጻፉ አራት አመት እንደታሰሩ በሞት ተለዩ።

አቡነ ሰላማ ከቴዎድሮስ ቁጣና እጅ ድነው በ1860 ዓ.ም ጥቅምት 15 ቀን ባደረባቸው የሳንባ (ሳል) በሽታ አርብ ዕለት ከቀኑ 9 ሰዓት ሞቱ።

## እቴጌ ተዋበች አሊ

ቀደም ብለን እንዳነበብነው እቴጌ ተዋበች ሞተው አጤ ቴዎድሮስ ሬሳውን አጅበው በሚሔዱበት ጊዜ

«እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሔድ፥

እቴጌ ተዋበች ሚስትና ገረድ» ብለው ተቀኙላቸው። ትርጉሙም እቴጌ ተዋበች ሚስት፥ ገረድ ነች ለማለት ነው።

አጤ ቴዎድሮስ ለሚስታቸው የተቀኟልት ቅኔ ትክክለኛ አባባል ነበር። ተዋበች ለቴዎድሮስ ተንከባካቢ ሚስታቸው፥ መካሪ እህታቸው አሳቢ እናታቸው እና አገልጋይ ገረዳቸው ነበሩ። ከቅርብ ሁኔታውን ያጠናው ውልድሜየር ሲጽፍ «......ንጉሥ ቴዎድሮስን ሚስታችወን እቴጌ ተዋበች ይጠብቋዋል።...... እቴጌይቱ እንደ አበሾች ባህል ሁሉ ንጉሱን በምግባቸው በኩል ይንከባከቡዋቸዋል። ንጉሱ የሚበሉትንም ሆነ የሚጠጡትን የሚቀበሉት ከእቴጌይቱ እንጂ ከሌላ ሰው አይቀበሉም። ሴትዬዋ ብልህና ጠቢብ ስለሆኑ ንጉሱ ብዙ መጠጥ በሚጠጡበት ጊዜ ወይም እየደጋገሙ ሲጠጡ ሲያዩዋቸው «ንጉስ አስካሪ መጠጦችን ደጋግሞ ስይጠጣም» በማለት ይመክሩዋቸዋል። በዚህም ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ያነቡላቸዋል «ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲያድርባቸው ይነግሩዋቸዋል።......» ብሏል።

ዶክተር ብላንክ እንደጻፈው ደግሞ «.......ጅግናና ተወዳጅ የሆነች ሚስታቸውን አጡ። እጅግ በጣም ታማኝ የሆነች አማካሪያቸውን እንደ እሳቸው ሰፊ ምኞትና ዓላማ የነበራት ጓደኛቸው በመሆንዋ በጣም ይወዷት ስለ ነበረ በሕይወታቸው ሳሉ ትዝትዋ ምንጊዜም ከአእምሮአቸው ውስት አልጠፋም ነበር። በ1860 ዓ.ም አንድ ብረት ቀጥቃጭ (ሠራተኛ) የሆነ ሰው ከቴዎድሮስ ፊት ቀርቦ ሚስትቱ በጠና መታመምዋን ገልጦ ለጥቂት ቀናት ለመሞት በምታጣጥር ባለቤቱ አጠገብ ለመቆየት እንዲፈቀድለት ስለጠየቀ አጤ ቴዎድሮስ በዚህ አነጋገር ልባቸው ስለተነካና የሚወዷትንም ባለቤታቸውን በማስታወስ ራሳቸውን አቀርቅረው ማልቀስ ጀመሩ......» ብሏል።

ተዋበች ለቴዎድሮስ እጅግ በጣም ደግና አዛኝ አፍቃሪና አሳቢ የሆኑበት ምክንያት ነበራቸው። ቴዎድሮስ ከመሞት ያዳኑዋቸው ሕይወታቸውን ለተዋበች ሕይወት የለወጡ ሰው ነበሩ። ሜጀር ፖሰን ኒው ማን የተባሉት ታሪክ ፀሐፊ እንደሚተርኩት አያታቸው እቴጌ መነን ከቱርክ ጦር መሪ ከመሐመድ አሊ ጋር ለመግጠም ወደ ወሰን ሲሔዱ ወይዘሮ ተዋበችም

አብረው ሔደው ነበር። የዚያን ጊዜ የተዋበች ዕድሜ 15 ዓመት ነበር። በጦርነቱ ላይ ተዋበች ተማርከው ተወሰዱ።

የዚያን ጊዜው ካሣ የኋላው ቴዎድሮስ ከእቴጌ መነን ጦር ጋር ነበርና የተዋበችን መማረክ እንደሰሙ ብቻቸውን አሸምቀው ወደ ጠላት ሠፈር ገብተው ተዋበች ከታሠሩበት ቦታ ደረሱ ተዋበችም በመሐመድ አሊ ዘቦች ይጠብቁ ነበር። ካሣ ዘቦቹን እንደምንም ብለው አልፈው ገቡ። ሲገቡም ተዋበች ራሳቸውን ለመግደል አካላቸውን እብጥተው (ቀደው) መርዝ ሲጨምሩ ደረሱባቸው። ካሣም ተዋበችን ሲያዩ በውበታቸው ቢደነግጡም ቶሎ ብለው አጐንብሰው መርዝ የተደረገበትን የተበጣውን ቦታ በአፋቸው እየመጠጡ መርዙን ያወጡላቸው ጀመር። መርዙን መጥጠው አውጥተው ከጨረሱ በኋላ ተዋበችን በድብቅ አውጥተው ጐንደር ወስደው ለወላጆቻው መስጠታቸውን ዝርዝረው ጽፈዋል።

ቴዎድሮስን ከተራ ሽፍተንት ጀምሮ እስከ መንገስ ድረስ ያደረሱ ተዋበች ናቸው። እንዴት እንደሆነም ከዶክተር ብላንክ ትረካ ጥቂት እንመልከት። በኋላ ቴዎድሮስ የተባሉት ካሣ ገዳሪፍ ላይ ከቱርኮች ጋር በተደረገው ጦርነት ቆስለው ቁስላቸወ እስቲሻላቸው ድረስ ደንቢያ ተኝተው ስለ ነበረ ለማገገሚያ ፍሪዳ እንዲላክላቸ ለአማቻቸው ቢልኩ እቴጌ መነን አንድ ብልት ሥጋ ከስድብ ጋር ስለላኩላቸው «......መንፈሱ ጽኑ የሆነችውናን የምትወዳቸው ሚስታቸው ቆስሎ ከተኛው ጀግና ባለቤቷ አጠገብ ያልተለየች ስለሆነ ይህን አሰቃቂ የንግስቲቱን ንግግር በሰማች ጊዜ ትኩስ የሆነው የጋለ ደሟ ሲፈላ ኩራት በተመላው አነጋገር ከመቀመጫዋ ተነስታ እየተንቆራጠጠች «ደፋሮችን እወዳችዋለሁ። ፈሪዎችን ግን እንቃቸዋለሁ» ብላ ከዚህ ሁሉ ውርደት በደሉን በደም የማይበቀሉ ቢሆን ከጐናቸው የማይወደውን የካሣን ልብ የመበቀል ሀሳቡ ጠነሰሰችበት። ወዲያው ቁስላቸው እያገገመ ሲሔድ ወደ ቋራ ተመልሰው ነፃነታቸውን በግልጽ አወጁ።......» ይላል በሌላ ጊዜ ደግሞ «......ካሳ ከጠነከሩ የበላይነቱን ቦታ ለማግኘት ምንም የሚያቆማቸው ነገር ያለመኖሩን ሚስታቸው ደጋግማ ስትገፋፋቸው የጥርጣሬ መልክ ስላሳዩዋት አሁንም በዚህ ሐሳብ የማይቀጥሉ ከሆነ አብራ ለመኖር እንደሚያዳግታት ስላስፈራራቻቸው ወደ ጐጃም ቀጥለው ሁሉንም ድል መቱት......» በማለት ጽፈዋል።

## ፕላውዲን (ዋልተር ቺቺሊ ፕላውዲን)

እ.ኤ.አ ኦገስት 3 ቀን 1820 ዓ.ም ተወለደ። በኛ አቆጣጠር ሐምሌ 27 ቀን 1812 ዓ.ም መሆኑ ነው። በ19 ዓመት ዕድሜው ወደ ሕንድ ሔዶ ካልካታ ውስጥ አከር ታጉር ከተባለ ኩባንያ ዘንድ ተቀጠ። እ.ኤ.አ በ1843 ዓ.ም ከሕንድ ወደ እንግሊዝ አገር ለመመለስ ጉዞ ጀምሮ ስዊዝ ሲደርስ ከቢል ጋር ተገናኙ በዚያም ሆነው የአባይን ምንጭ እንፈልጋልን በማለት ተስማምተው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። በዚህ ጊዜ የፕላውዲን ዕድሜ 23 ዓመት ነበር።

በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ 1847 ዓ.ም ድረስ አራት ዓመት ቆይቶ ወደ አገሩ ተመለሰ። በእንግሊዝ አገርም ለእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሎርድ ፖልመር እስቶን የእንግሊዝ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ ቆንሲል ቢያቋቁም ጠቃሚ እንደሚሆን አሳወቀ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም በአሳቡ ተስማምተው «አገሩን ሕዝቡንም ቋንቋውንም ታውቃለህና አንተው ሁን» ብለው ፕላውዲን በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል አድርገው ሾሙት።

ፕላውዲን ከእንግሊዝ የወጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሾመበትን ደብዳቤ ይዞ በ1848 ዓ.ም ምጽዋ ደረሰ። ከዚያም መሀል አገር ገብቶ ከራስ አሊ ጋር የቆንሲልነቱን ሥራ ጀመረ። ራስ አሊና ደጃች ካሳ በሚዋጉበት ጊዜ ፕላውዲን ታሞ ስለ ነበረ ወደ እንግሊዝ አገር ለመሔድ ምጽዋ ነበረ። በምጽዋም ሕመሙ ስለጠናበት እስኪሻለው ድረስ በዚያው ቆየ። ሕመሙን ሻል ሲለው ራስ አሊ በደጃዝማች ካሣ ድል መሆናቸውን ሰማ። ይህም ለውጥ እሱን የሚመለከተው በመሆኑ የእንግሊዝ አገር ጉዞውን አቋርጦ ወደ አዲሱ ንጉሥ ወደ ቴዎድሮስ ዘንድ ተመለሰ።

ፕላውዲን ወደ ጐንደር እንደ ተመለሰ ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ተገናኝቶ ከራስ ጋር የነበረው የሰላም ውል እንዲጠና ቢጠይቃቸው ቴዎድሮስ በወሉ ውስጥ ያለው የእንግሊዝ መንግሥት የፍትህ ጠባቂነት የሚለው ቃል እያለ ውሉ አይጠናም ብለው እምቢ አሉ። ፕላውዲንም ይህን የውል ቃል አስቀርቶ በውሉ ቴዎድሮስ ሲሰማ የእሱንም ቆንሲልነት አወቁለት። ቆንሲልነቱን ለማወቃቸውም ቀጥሎ አየልውን ደብዳቤ ለእግንሊዝ መንግሥት ጻፉ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩
አምላክ። የእግዚአብሔር ፍጡር ባርያው
የዳዊት የሰሎሞን ልጅ። ንጉሠ ነገሥት
ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ አቶ ፍላጥን በአይሮጳ
ልኬ ሰድጄዋለሁ። ብልህ ሠራተኛ
ፈልጌአለሁ። ከኔ የሚመጣን ሠራተኛ ሁሉ
በደስታ እቀበለዋለሁ ቢኖርም ደስ አሰኝቸ
አኖረዋለሁ። ብልሀቱንም አስተምሮ ወደ አገሬ
እመልሰሳለሁ ቢል ደመወዙን ሠጥቼ። ደስ
አሰኝቸ ሸኝቼ እሰደዋለሁ። በእግዚአብሔር
ኃይል የእግዚአብሔር እምነት ይሁንብኝ
ክርስቶ በተወለደ በሽህ ፰፻፶፰ ዘመን በዘመነ
ማርቆስ በሚዝያ በ፲ ቀን ዘጊ ላይ ተጣፈ።



ፕላውዲን የበፊት ሕመሙ ሲሻለው ከፈረስ ወድቆ እግሩ ተሰበረ። ጥቂት ቀን ቆይቶ ለመታከም ወደ አገሩ ለመሄድ ከጐንደር የካቲት 25 ቀን 1852 ዓ.ም ተነስቶ ጉዞ እንደ ጀመረ ጐንደር ከተማ አጠገብ ቀሃ ከሚባለው ወንዝ ሲደርስ በድንገት የደጃች ጋረድ ሰዎች ደርሰው ደረቱ ላይ በጦር ወጉት። ማርከውም ወሰዱት። ቴዎድሮስም ከሽፍቶቹ ጋር በተደረገው ድርድር መሠረት አንድ ሺ ብር ከፍለው ፕላውዲንን አስለቀቁት። ፕላውዲንም በጦር የተወጋው ከፉኛ ነበርና በቃሬዛ ሆኖ ጐንደር ገባ። በጐንደርም ለዘጠኝ ቀናት በሕመም ሲሰቃይ ቆይቶ በጥር ወር 1853 ዓ.ም ሞተ።

የፕላውዲን ሬሳም ነገሥታት ከሚቀበሩበት ሥፍራ የጐንደር ሕዝብና መኳንንት ባለበት ጉዞ ፍታት ተፈትቶ ተቀበረ። በጐንደር ያሉት ዕቃዎችም ለወንድሙ ትሬቫልስ ቺቺሊ ፕላውዲን ተሰጠው። ከዕቃውም ጋር ፕላውዲን በሕይወት በነበረ ጊዜ በደረቅ እርሳስ ይጽፈው የነበረው ማስታወሻና የመጽሐፍ ረቂቅ ድርስቱ ተገኝቶ ለወንድሙ ተሰጠ። ይህም ድርሰቱ ፕላውዲን ከሞተ ስምንት ዓመት በኋላ ወንድምየው «ትራቫልስ ኢን አቢሲኒያ ኤንድ ጋላ ካንትሪ» በሚል ርዕስ አሳተመው።

ፕላውዲን እንዳሁኖቹ አምባሳደሮች ወይም ቆንሲሎች የሚሠራው ሥራ አልነበረውም። ራሱ በመጽሐፉ እንደገለፀው «በስም ብቻ ቆንሲል ነኝ። የቆንሲልነት ተግባር ግን የለኝም። የውጭ ንግድ ጉዳይ የለም። የንግድ ትርፍም ጉዳይ የለም። የምጠብቀውም የእንግሊዝ መንግሥት ነገር የለም» ብሏል።

አጤ ቴዎድሮስ ፕላውዲንን የገደሉትን ሰዎች እነጋረድን ከነወታደሩ ካጠፉ በኋላ የሚቹን የፕላውዲን ደም መበቀላቸውን የፕላውዲን ረዳት ወይም ምክትል ሆኖ ምጽዋ ለተቀመጠው ለራፋኤል ባሮኒ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ
ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ከአት ቦረኒ
እንዴት ሠነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን
ደኅና ነኝ የምሥራች በእግዚአብሔር ኃይል ቀና
ወዳጆች ዮሐንስን የገደሉን ሠዎች ፈጇቸው
በእግዚአብሔር ኃይል ከሤት በቀር በሠልፍ
ያገኝሁትን ሁሉ ፈጀሁት አንድ አልተውሁም
ወዲያው ተከታትዬ ተሻግሬ ሌባ ንጉሴን
በእግዚአብሔር ኃይል ከነሠራዊቱ ፈጀሁት
አኰሱም ከሜዳው ላይ። አንተም ቶሎ ናልኝ
ከዕንግሊዝ ንግሥት ከወዳጀ እግዚአብሔር
ያደረገልኝን የደስታየን ወሬ የምልክ ሰው
የምሠድ ነኝና ቶሎ ናልኝ ይዘህልኝ የምትሄድ
ነህና የሊቀ መኳስ ዮሐንስን። የአቶ ቡላዲን
ሰዎች እስታሁን ያቆየኋቸው ከኔ ሰው ካንተ ጋራ
ይሄዱ ብየ ነው።



ይህን ደብዳቤ መቼ እንደጻፉት ቀኑ ባይገለጽም ለራፋኤል ባሮኒ የደረሰውን ግን እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 23 1863 ዓ.ም ነው በኛ አቆጣጠር ጥር 15 ቀን 1855 ዓ.ም መሆኑ ነው።

## ቤል/ሊቀ መኳስ ዮሐንስ

ጆን ቤል በሞቱበት ጊዜ ስለነበረው የቴዎድሮስ ሁኔታ ዱፍተን ሲጽፍ «.......ከጐናቸው ሆኖ ይዋጋ የነበረውን የወዳጃቸውን ሬሳ ባዩ ጊዜ እጅግ በጣም አምርረው አለቀሱ። ወዳጄ ቤል ድሃው ቤል በወዳጅነት ክፍያ ህይወቴን ያዳንኸው» እያሉ ሬሳው ላይ ተደፍተው ጮሁ። ከሬሳው ላይ ሲነሱም የገዳዩም ሬሳ ከዚያ ወድቆ ነበርና» አንተ አንተ የማትረባ ከወዳጄ ካንዱ ወዳጄ የለየኸኝ» ብለው የያዙትን ጦር በሬሳው ላይ ሰኩበት።.......» ብሏል።

ጆን ቤል በእንግሊዝ ባህር ሀይል ውስጥ የመቶ አለቃ ነበር። በኋላም ጊዜ በቱርክ ቅኝ ገዢዎች ስር በነበረች አሌፖ በተባበረችው የአረብ አገር የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ሆኖ ተሹሞ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ለራስ አሊ አሽለርነት አደረ። ራስ አሊም የባሻነት ማዕርግ ሰጥተውት ነበር። ጆን ቤል በራስ አሊ ዘንድ አይወደድም ነበር። መኖርም የቻለው በፕላውዲን ደጋፊነት ነበር። ቤል አንዲት ኢትዮጵያዊት በፕላውዲን ደጋፊነት ነበር። ቤል አንዲት ኢትዮጵያዊት አግብቶ ሁለት ሴቶችና አንድወንድ ልጅ ወልዳለታለች። ሴቶች ልጆችም በኋለኛው ጊዜ ሁለት የቴዎድሮስን ጥበበኛ ፈረንጆችን አግብተው ከባሎቻቸው ጋር በቴዎድሮስ እጅ ታስረው ነበር። እስረኞቹ ሲፈቱም አብረው ተፈትተው ከባሎቻቸው ጋር ወደ ኤሮፓ ሄድዋል። አንዲቱ ልጅ ያገባችው ምልድሜየርን ነበር።

ራስ አሊና ደጃች ካሣ (በኋላ ቴዎድሮስ) የመጨረሻውን ጦርነት በተጋጠሙ ጊዜ ቤል ከራስ አሊ ወገን በመሆን ተዋግቷል። ራስ አሊ ድል ሲሆኑም ጆን ቤል ካንድ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ተደብቆ ሳለ ቴዎድሮስ ይህንኑ ሰምተው ምህረት አድርገውለት ወደ ቴዎድሮስ ገባ። ቤል በኑሮውም ሆነ በአለባበሱ ከኢትዮጵያውያኖች የተለየ አልነበረም። የሚለብሰው ልብስ አበሾች የሚለስቡትን ሲሆን ለእግሩ ጫማ ለራሱ በርኔጣ አያደርግም ነበር።

አጤ ቴዎድሮስ በጥሩ ሁኔታ ስለሚመክራቸውና በተለይም በፍርድ ጉዳይ መልካሙንና እውነተኛውን መንገድ ስለሚመራቸው ቤልን ይወዱትና ያከብሩት ነበር። በሕዝቡም ዘንድ በዚሁ በምክሩና በአማላጅነቱ የተወደደና የተከበረ ሰው ነበር። የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል የሆነው ፕላውዲን እንኳን በአጤ ቴዎድሮስ ሞገስ ዘንድ አግኝቶ በኢትዮጵያ መኖር የቻለው በጆን ቤል ድጋፍ እንጂ ቴዎድሮስ ፕላውዲንን አይወዱትም ነበር። ብዙ ጊዜም ከመታሰርና ከመጉላላት ያዳነው በቤል አማላጅነትና ስለሱ መልካም ነገር በመናገሩ ነበር።

## ደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤል

ደጃዝማች ንጉሴ በአባታቸው የአገው ተወላጅ ስለሆኑ ብዙ ጊዜ አገው ንጉሴ እየተባሉ ይጠራሉ። ደጃች ውቤ ድል ሆነው ሲያዙ ደጃች ንጉሴ የአጎታቸውን የደጃች ውቤን ሥልጣን ለመያዝ ወራሽ ነኝ በልው በቴዎድሮስ ላይ ሸፈቱ። ደጃች ንጉሤ የደጃች ውቤ እህት ልጅ ናቸው። ደጃዝማች ንጉሴ በትግራይ ውስጥ ሸፍተው ሲነሱ ብዙ ተከታይ በማግኘታቸው አቅማቸው ወዲያውኑ ደረጀ።

ደጃዝማች ንጉሤ በቴዎድሮስ ላይ የሸፈቱት እንደሌሎች ጠላቶቻቸው ሁሉ ራሳቸውን ችለው አልነበረም። የካቶሊኩን መነኩሴ አባ ያዕቆብን ወዳጅ አድርገዋቸው ስለ ነበረ በአባ ያዕቆብ አገናኝነት ከፈረንሳይ መንግስት ጋር መወዳጀት ጀመሩ። አባ ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር የመጣሁ ነኝ በማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ለእግራቸው ጫማ ሳይኖራቸው ፍፁም ባህታዊ መስለው የሚሰሩ ነበሩ። በዚህም ተግባራቸው በሕዝቡና በመኳንንቱ ዘንድ ሁሉ የተከበሩ ስለ ነበሩ ደጃች ንጉሴ እንደ ሸፈቱ ፈረንሳዊ አባ ያዕቆብ ወዳጅነታቸውን አጠናከረው ከመንፈሳዊነቱ ወደ ዓለማዊነቱ አዘነበሉ።

የእንግሊዝ መንግሥት ቀደም ብሎ በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን በዲፕሎማቲክ ደረጃ ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነት መሥርቶ ፕላውዲንን ቆንሲል አድርጐ በመሾሙ ለአገራቸው መንግሥት ይቀረቀሩ የነበሩት አባ ያዕቆብ የእንግሊዝ መንግሥት በኢትዮጵያ ያለውን ተፈላጊነት አስጥለው በምትኩ የፈረንሳይ መንግሥት እንዲሆን ያስቡ ነበርና ደጃዝማች ንጉሴ በቴዎድሮስ ላይ ሸፍተው ሲነሱ «የቴዎድሮስን መንግሥት ለመጣል የበለጠ ኃይል መያዝ

አለብዎት ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ግንኙነት ቢጀምሩ የፈልጉትን ያህል የጦር መሣሪያ ማግኘት ይችላሉ» ስላሉዋቸው ደጃዝማች ንጉሴ ለፈረንሳይ ንጉስ ናፖሊዮን 3ኛ ደብዳቤ ጻፉ።


ሰኔ 2 ቀን 1848 ዓ.ም ለናፖሊዮን የተጻፈው ደብዳቤ «.......አባቴ ይሁን እኔም ልጅዎ እሆናለሁ። አሁን አንድ ሽፍታ ንጉሥ ተነስቶ እኔን በማጥቃት ላይ ነው። ክርስትያኖችም እያጠፋ ነው። እንደ እውቀትዎ ይርዱኝ። ቢቻል በነሐሴ ባይቻልም በመስከረም። እስከዚያም እቆያለሁ ከወዲያ ወዲህ እያልኩኝ። አቡነ ያዕቆብን አባቴ አርጌሃለሁ። የእርስዎንም ፈቃድ የማልጥስ ነኝ» የሚል ነበር።

ይህ የደጃች ንጉሤ ደብዳቤ በተጻፈ በዘጠኝ ቀኑ ለፈረንሳይ መንግሥት ደረሰ። የፈረንሳይ መንግሥትም ደብዳቤውን ካየ በኋላ የሚጣሩ ነገሮንች እንዲያጣራ ምጽዋ የተቀመጠውን ጉዳይ ፈጻሚውን ቢላርድን አዘዘ። ቢላርድም ለፈረንሳይ መንግሥት በላከው መልስ ደጃዝማች ንጉሤ እስካሁን ድረስ ከመሐል ኢትዮጵያ የሚባረቱን ካቶሊኮች እያሰባሰቡ ማስጠጋታቸው ካቶሊኩን ፈረንሳዊ አባ ያዕቆብንም (ጃኮቢስ) ኢትዮጵያ ጳጳስ ብለው መሾማቸውን የፈረንሳይ መንግሥት ባንዲራም በደጃች ንጉሴ ትእዛዝ በትግራይ ምድር እንዲውለበለብ መፍቀዳቸውን ሁሉ ዘርዝሮ አሳወቀ።

ይህ የፈረንሳይ መንግሥት ባንዲራ በኢትዮጵያ ምድር መሰቀል ወይም መውለብለብ በዚያን ጊዜ በነበረው አስተሳሰብ ከፍተኛ የፖለቲካ ስሜት ነበረው። አጤ ቴዎድሮስም የማንኛውም የውጭ አገር መንግሥት ባንዲራ በኢትዮጵያ ምድር እንዲውለበለብ አይፈቅዱም ነበር። በቴዎድሮስ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ዱፍተን ሲጽፍ «......ጋፋት ደረስን። ከዚያም ሙሴ ሌዝጎን ተቀበለን።..... ሙሴ ሌዝጎን በድንጋይ ላይ ሶስት ቀለም የሆነውን ባንዲራውን ሰቅሎ ነበር። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ንጉሱ እንዳማይወዱ ከተነገረው በኋላ ቶሎ አነሳው።...... የሱ ሀሳብ በዚያ ግዛት ቆንሲል በመሾሙ የቆንሲሉን መመሥረት ለማሳወቅ ነበር። የንጉሱ አሳብ ደግሞ በዚያ አገር ማንኛውም ኃይለኛ መንግሥት እንዲገባ አይፈልጉም።.......ብሏል። የአንድ የውጭ አገር መንግሥት ባንዲራ በኢትዮጵያ ምድር ላይ እንዳይተከል ወይም እንዳይውለበለብ የሚፈልጉት መሪዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ሕዝቡም ጭምር ነበር።

ዶክተር ብላንክ በመጽሐፉ እንዲህ ይላል። «.......አንድ ጊዜ ሚስተር ፕላውዲን የአገሩን ሰንደቅ ዓላማ ለመስቀል (ራስ አሊን) ፈቃድ ቢጠይቃቸው በደስታ መፍቀዳቸውን አረጋግጠው......እንድጠብቅልህ አትጠይቀኝ። እንደዚህ ስላለው ነገር እኔ ብዙ አልጨነቅለትም። ዳሩ ግን ሕዝቡ የሚወደው አይመስለኝም ስላሉ ፕላውዲን በቆንስላው ግቢ የእንግሊዝን ሰንደቅ አላማ ሰቅሎ ማውለብለብ እንደጀመሩ ከጥቂት ሰዓት በኋላ ቁጥሩ የበዛ ሕዝብ መጥቶ ሰንደቅ ዓላማውን አውርዶ ቀዳዶ ጣለው። ይህን ሁኔታ ራስ አሊ ስምተው ከፕላውዲን ጋር ሲነጋገሩ «አልነገርኩህም ነበርን» የሚል ቃል ብቻ ነበር።.....» በእንዲህ ዓይነቱ ዘመንና ወቅት ነው ደጃች ንጉሤ የፈረንሳይ ባንዲራ በትግራይ ምድር እንዲውለበለብ ያደርጉት።

ቢላርድ ሪፖርቱን ያቅርብ እንጂ አባ ያዕቆብና ቢላርድ ተስማምተው ሌሎች የሚጣሩ ነገሮችን ከደጃች ንጉሴ ዘንድ ሔደው እንዲነጋገሩ ኢትዮጵያውያን ካቶሊካዊ መነኩሴ አባ እምነቱ (እምነተ ማርያም) የተባሉትን ላኩዋቸው። አባ እምነተ ማርያም (እምነቱ) ወደ ደጃች ንጉሤ የተላኩበት ሌላው ምክንያት የደጃች ንጉሴ የቅርብ ዘመድ ስለነበሩ ነው። አባ እምነቱም ከደጃች ንጉሴ ዘንድ አንድ ወር ያህል ከርመው ሲመለሱ ንጉሴ የትግራይ ሙሉ ገዥ መሆናቸውን ያላቸውም የጦር መሣሪያ ከሶስት እስከ አራት ሺ ጠመንጃ ብቻ በመሆኑ በዚህም ከሶስት እስከ አራት ሺ ጠመንጃ ብቻ በመሆኑ በዚህም መሣሪያ ቴዎድሮስን ለመቋቋም እንደማይችሉ አስረዱ። የዚያን ጊዜ የትግራይ ገዥ ወሰኑ እስከ ቀይ ባሕር ድረስ ነበር።



ጥንታዊት የአክሱም ከተማ

ከፈረንሳይ መንግሥት የተጠየቀው የጦር መሣሪያ እርዳታ በመዘግየቱ ደጃች ንጉሤ ቢላርድንና አባ ያዕቆብን ይጠይቁ ጀመር። ምንም እንኳ መልሱ ከፓሪስ ባይመጣ የንጉሤን ተስፋ ላለማጨለም ቢላርድ በካቶሊክ ቀሳውስት ታጅቦ 15 ጠመንጃ ስጦታ አስይዞ ከንጉሤ ጋር ለመገናኘት ከምጽዋ ወደ ትግራይ መጣ። ከደጃች ንጉሤም ጋር ተገናኝተው በሚነጋገሩበት ጊዜ ደጃች ንጉሤ የፈረንሳይ መንግሥት መድፎች እንዲሰጣቸውና ወደ ደምቢያ እንዲዘምቱ አሁን ያላቸው ወታደር ግን አራት ሺ ያህል ጠመንጃ ያዥና አስር ሺህ ያህል ጦረኛ ሠራዊት መሆኑን አሳወቀ። ከዚያም በቀር ስለንግድና በሌላም ጥቃቅን ነገሮች ተነጋግረው ቢላርድ ወደ ምጽዋ ተመለሰ።

የፈረንሳይ መንግሥት ጉዳዩን እንዳጠናው ደጃዝማች ንጉሤ የጦር መሣሪያ የሚሰጣቸው ሰው ሆነው አላገኛቸውም። ቢላርድም ሆነ አባ ያዕቆብ በዚህ ጉዳይ ቃል እንዳይገቡ ትእዛዝ ተላልፈላቸው። ይህ ከሆነ በኋላ አባ

ያዕቆብና ቢላርድ ተነጋግረው ጉዳዩን የሚያስረዳ የመልክተኛ ቡድን ወደ ፓሪስ እንዲላክ ተስማሙ። የሚላኩትም ሰዎች አባ እምነቱና ልጅ ጠጋዬ እንዲሆኑ ተወሰነ። ፈረንሳዊው ለፔር ደምን ፀሀፊና አስተርጓሚያቸው ሆኖ አብሮ እንዲሄድ ተመረጠ። ይህ ካለቀ በኋላ ደጃዝማች ንጉሤ ደብዳቤ ጽፈው ለመልክተኞቹ ተሰጥቶ መልክተኞቹ ጉዞአቸውን ጀመሩ።

መልክተኞቹ ከመሔዳቸው በፊት ከነአባ ያዕቆብ ጋር በምክር ይደጋገፉ የነበሩት ካቶሊካዊው የአላዛሪስቱ ሚስዮን መሪ የነበሩት አባ ጁሴፔ ሳፔቶ በዚሁ ጉዳይ ለሮማው ፓፓ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ለፈረንሳይ ንጉሥም በላኩት መልዕክት የፈረንሳይ መንግሥት የንጉሴን ጥያቄ ቢፈጽም ንጉሥ ንጉሤ ካገራቸው ዳርቻ ለፈረንሳይ መንግሥት ግዛት ለመስጠት መዘጋጀታቸውን በኢትዮጵያ የሚኖረው የፈረንሳይ ቆንሲል በሁሉም ነገር ባለሙሉ ሥልታን እንደሚሆን በአድዋም ቆንሲሉ መቀመጫ ከ500 እስከ 600 ሰዎችን ሊያኖር የሚችል መሬት ለመስጠት መወሰናቸውን አሳውቀው ነበር። የያኔው የትግራይ ዋና ከተማ አድዋ ነበር።

ደጃዝማች ንጉሤም ለፈረንሳይ መንግሥት መሪ ለንጉሥ ናፖሊዮን የጻፉት ደብዳቤ «.......የአገሬን ነፃነት እንዲጠብቁልኝ አምናለሁ። ከዘራፊውና ከዓመፀኛው ከቴዎድሮስ እጅ ይጠብቁኝ። ይህንንም ለማድረግ ሁለት ነገሮች ያስፈልጋሉ። መጀመሪያ ከናንተ ተወካይ ቢላክ ከዚህ በፊት እንደጠየቅሁት ይጠብቁኝ። ይህ በአገሬ ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ እንዲመለከት። እሱንም በአገሬ እንደራሴ አድርጌ እጠብቀዋለሁ። የፈረንሳንም ባንዲራ እተክላለሁ። ሁለተኛ የምፈልገው ሁለት መድፎች ከተኳሾቻቸው ጋር ነው። ለደረጉልኝና ለአገሬም ለሚያደርጉት እርዳታ ከባህር ዳርቻ ራስ ድሜራ የሚባል ዙላን እሰጥዎታለሁ» የሚል ነበር። ደብዳቤው የተጻፈው ጥቅምት 22 ቀን 1851 ዓ.ም ነው።

በፈረንሳይ በኩል ያለውን በዚህ እናቁመውና መልክተኞቹ እነ አባ እምነቱ ወደ ኤሮፓ በሚሔዱበት ጊዜ በአባ ጁሴፔ ሳፔቶ ውትወታ ለኢጣሊያ መንግሥትም ደብዳቤ እንዲፃፍና ይዘው እንዲሔዱ ተደርጎ ነበር። ኢጣሊያዊው አባ ጁሴፔ ሳፔቶም በኢጣሊያ አገር ላለው ጉዳይ እንዲረዱ ተብሎ ወደ ሮም ሔደው ነበር። መልክተኞቹ ሮም ደርሰው በኢጣሊያው ንጉሥ ለዳግማዊ ቬቶር አማኑኤልና ለፓፓው የተፃፈው እሳቸው ለአገራቸው

ለኢጣሊያ የሚበጀውን ይሠሩ ጀመር። የተላኩት መልክተኞችም ተመልሰው የማይጨበጥ ተስፋ ይዘው ኢትዮጵያ ገቡ።

የኢጣሊያ መንግሥት ጉዳዩን ለመጨረስ መልክተኞች ወደ ኢትዮጵያ እንደሚልክ ሲነግራቸው የፈረንሣይ መንግሥት ደግሞ ጉዳዩን አጥንቶ መልሱን እንደሚሰጥ ነግሮአቸው ተመለሱ። የኢጣሊያ መንግሥት በገባው ቃል መሠረት መልክተኞቹን አፋጥኖ ወደ ደጃች ንጉሤ ዘንድ ላከ። የተላኩትም መልክተኞች ከደጅዝማች ንጉሤ ጋር ተገናኝተው የጦር መሣሪያውን እለምስጠት ድርድር አቀረቡ። በቀይ ባሕር ዳርቻ በዙላና በአንፊላ መሀል ያለውን አንዳዳ የተባለው አገር እንዲሰጣቸው ጠየቁ። ደጃዝማች ንጉሤም በአሳቡ ተስማምተው የኢጣሊያ መንግሥት መልክተኛኖች ወደ አገራቸው በሚመለሱበት ጊዜ ለኢጣሊያው ንጉሥ ነገሥት «.......የተጠየቀውን ጉዳይ ሁሉ ተስማምተንበታል። ይህንንም ስምምነት በአስቸኳይ እንድንፈራረም እጠይቃለሁ........» የሚል ደብዳቤ ጽፈው ላኩ።

የኢጣሊያኑ ንጉሥ ነገሥት ዳግማዊ ቪክቶሮ አማኑኤልም ለደጃዝማች ንጉሤ በላኩት ፌብራሪ 10 ቀን 1859 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ሲመልሱ «......የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ በመስማቴ በጣም ተደስቻለሁ። በዚህም ላይ አወዳጅነታችንን አጠንክረን የንግድን ጉዳይ ሁሉ እንመሠርታለን። አሁንም የእርስዎ ወኪል በፍጥነት ይምጣና ይህን ጉዳይ በቶሎ እንጨርስ።.......» አሉ። ይህ ደብዳቤ ሎፒሪማ ጉየራ ዲ. አፍሪካ (የአፍሪካ የመጀመሪያው ጦርነት) በተባለው መጽሐፍ ከገጽ 58 እስከ 66 ላይ አለ። ከዚህም ሌላ ጁሊዮ ባሳተሙት ኢትዮጵያ ማር. ሮቦ (የኢትዮጵያ ቀይ ባህር) ከተባለው ቮሊዩም 1 ገጽ 56 ላይ ይገኛል ፡

ይህ የኢጣሊያአው ንጉሥ ነገሥት ደብዳቤ ለደጃዝማች ንጉሤ ሲደርሳቸው ተደሰቱ። ጁሴፔ ሳፔቶ ስለዚሁ ጉዳይ በመጽሐፋቸው ሲገልፁ «.......ደጃች ንጉሤ......ማህተሜን ይውሰዱ። የፈለጉትን ጥሩ ነው የሚሉትን ነገር ሁሉ ጽፈው ይውሰዱ። ልቤን ከፍቼልዎታለሁ.......አለ፤.......» ብለዋል። የኢጣሊያ አገር ጋዜጦችም በኢትዮጵያ ያሉ ካቶሊኮች ችግር ስለደረሰባቸው የኢጣሊያ መንግሥት አስቸጋሪውን ንጉሥ ጥሎ የሚስማማውን ለማንገስ ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ ነው እያሉ ይጽፉ ጀመር። ይህ

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የርስ በርስ ሽብር የሰሙ የኢጣሊያ ነጋዴዎችም የጦር መሣሪያ ለደጃች ንጉሤ ለመሸጥ ሩጫ ጀመሩ። ከኢጣሊያ መሣሪያ ነጋዴዎች አንዱ የሆነው ባሮኒ የተባለው ሰው አፕሪሌ 24 ቀን 1859 ዓ.ም ለወዳጁ ለኮግላን በጻፈው ደብዳቤ «......ለዚህ የካቶሊክን እምነት ለሚያስፋፋው ቅዱስ ጦርነት ከአስር ሺህ እስከ ሃያ ሺ ጠመንጃ አቀርባለሁ......» የሚል ቃል ነበረበት።

በኢጣሊያ በኩል ያለው የደጃዝማች ንጉሴ ጉዳይ ተፋፍሞ የፈረሳይ መንግሥት ደግሞ በአልጄሪያ የፈረንሳይ መንግሥት ተወካይ ኮንት እስንታሌ ሩሴል ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ለፈረንሳይ መንግስት ወደብነት የሚጠቅመውን ሥፍራ ከምፅዋ እስከ ታጁራ ድረስ እንዲያጠና ታዘዘ። ሩሴል በታዘዘው መሠረት ታህሳስ 2 ቀን 1853 ዓ.ም ምፅዋ ሲደርስ አባ ያዕቆብና አባ እምነቱ ተቀበሉት። ወዲያውም ሐውዜን ለነበሩት ለደጃዝማች ንጉሤ የሩሴል መምጣት ተነገረ። ወታደሮች ታችቦ ሹማምንት በሚመሩዋቸው የባህር ኃይል ወታደሮች ታጅቦ በአባ ያዕቆብና በአባ እምነቱ መንገድ መሪነት መሪነት የወደብ ፍለጋ ጉዞ መጀመራቸውን ራሱ ሩሴል በጻፈው ኡን ሚስዮን በተባለው መጽሐፍ ገልጦታል።

የሁለቱ መንግሥታት በኢትዮጵያ ዘልቆ እምግባትና ከንጉሤ ጋር መዋዋል ለቴዎድሮስ ሚስጥር አልነበረም። አጤ ቴዎድሮስ ደጃች ንጉሤን ለማጥፋት ቢዘምቱም ሆነ ቢያደፍጡም ሊያገኙዋቸው አልቻሉም። ይህን የንጉሤን ሁኔታ የሚያጠናው የሚመለከተው አገሩን የሚወድና ለባዕድ አሳልፎ ላለመስጠት ሲዋጋ የኖረው የትግራይና የሐማሴን መኳንንት ተማክረው ባስነሱት አድማና ስብከት የደጃች ንጉሤ ሠራዊት እየከዳ በመለየቱ መነመነ።

የሩሴል ምፅዋ መግባት ለደጃዝማች ንጉሤ እንደተነገረ ደጃዝማች ንጉሤ በአንድ ከፍተኛ የሚመራ ሠራዊት ልከው በእሳቸው ስም ታላቅ አቀባበል ተደረገለት። ይህም የተላከው ሠራዊት ሩሴል ከኢትዮጵያ እስኪወጣ ድረስ ከማንኛውም አደጋ እንዲጠብቀው የታዘዘ ነበር። ደጃች ንጉሤ ይህን ሠራዊት ለጥበቃ ያዘዙበት ምክንያት ቅድም እንደተባለው አገር ወዳዱ መኳንንት ሩሴልን ይዞ ለቴዎድሮስ ለማስረከብ መስማማቱን ደጃች ንጉሤ አውቀው ስለነበረ ነው። ሩሴልም ቢሆን ይህን የመኳንንቱን አድማ ሰምቶ ሰግቷል። ይህን ስጋቱን ያወቁት አባ ያዕቆብም ምንም ነገር እንደማይደረግ እኔ ኃላፊ

እሆናለሁ እያሉ የመኳንንቱን ኃይል እያንቋሸሹ ቢነግሩትም ሩሴል ግን ሁሉም ነገር ገብቶት ነበርና ለሊት የጀመረውን የወደብ ፍለጋ ጉዞ አቋርጦ ምፅዋ ገባ።

ሩሴል ምፅዋ እንደገባ የደጃች ንጉሤ ተወካይና ባለሙሉ ሥልጣን ከሆኑት ከአባ እምነቱ ጋር ውል ተዋዋለ። አባ እምነቱ ውሉን ሊዋዋሉ የቻሉት ከደጃች ንጉሤ የተሰጣቸውን ባለሙሉ ሥልጣን ወኪል መሆናቸውን የሚያስረዳ ባለማኅተም ደብዳቤ ካሳዩ በኋላ ነበር። ከውሉ ውስጥ አንዳንዱን ለመጥቀስ የፈረንሳይ መንግሥት ዙላንና የዲሴን ደሴቶች ከዊዳ እስከ ዘይላ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያን ቀይ ባህር በር እንዲይዝ የሚል ነበር። በውሉ አንቀፅ 5 ላይ ደግሞ በደጃች ንጉሤ ስም «........ይህ ለእናንተ የሰጠሁት ስጦታ ለፈረንሳይ ንጉሥ እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል። ከባህር የሚመጣብኝን ከአገር ውስጥ የሚነሳብኝን ጠላት (የፈረንሳይ መንግሥት) እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ይጠብቁኛል........» የሚል ነበር።

የኢጣሊያና የፈረንሳይ መንግሥታት ሁለቱም ከደጃች ንጉሴ ጋር ባደረጉት ውል የኢትዮጵያን ቀይ ባህር ዳርቻ መሬቶች ተከፋፍለው ቴዎድሮስ የሚጠፉበትን የጦር መሣሪያ ለደጃች ንጉሴ ለመስጠትና ለማድረስ በሚዘጋጁበት ወቅት አጤ ቴዎድሮስ ቀደም ብለን እንዳነብነው ደጃች ንጉሤን ድል አድርገው ቆራርጠው ጣሉዋቸው። ደጃች ንጉሤ ቢሞቱም ሃያ ዓመት ያህል የተለፋበት የባህር በር የመያዙ ጥንስስ ተደፋ።

## ምዕራፍ 7

# የቴዎድሮስ ሰውነት ጠባይ ርህራሄ ጭካኔና ፍርድ

ቴዎድሮስ እንዴት ያሉ ሰው ነበሩ? ብንል ሁሉንም ጠባይ አሟልተው የያዙ ሰው እንደነበሩ እንረዳለን። ይህም ማለት ደግ ናቸው ክፉም ናቸው። ሩህሩህ ናቸው ጨካኝም ናቸው። ፍርድ አዋቂ ናቸው ፍርድ ገምድልም ናቸው። ሁሉንም በየተራቸው እናነባለን። ቀድመን ግን አካላቸው ምን ዓይነት ወይም እንዴት እንደነበር እንመልከት።

ያያቸው ዱፍተን ሲፅፍ «........ወደ ጥቁረቱ የሚያደሉ ናቸው። ሻንቅላ ግን አይደሉም።.......ራሳቸው ጥሩ ቅርፅ ያለው ነው። ጠጉራቸው ከግንባራቸው ወደ ኋላ የተጐነጐነ ነው። ግንባራቸው ወጣ ያለ ነው።......

«ዓይናቸው ጥቁር ነው።.......አፍንጫቸው በመጠኑም ቢሆን የሮማውያን ቅርፅ አለው።......አፋቸው ውብና ፈገግተኛ (ሳቂታ) ነው። ......ጢማቸውም ሆነ ሪዛቸው በጣም ትንሽ ነው። ተባያቸው ደስ የሚልና ትሁት ናቸው።..... ኤውሮፓውያኖች ሠራተኞች ለመጨረሻ ጊዜ የሚሠሩትን መድፍ ለመመልከት ንጉሱ መጡ። በራሳቸው ላይ ምንም የለም። እግራቸው ባዶ ያለ ጫማ ነው። እቢዝህ እሾህና ቁጥቋጦ በበዛበት መጥፎ መንገድ ባዶ እግራቸውን ኮረብታውን ወጡ።.......እሳቸው በእግራቸው እየሄዱ እኛን በየበቅሎአችን ላይ እንድንቀመጥ ነገሩን። እኛም ለክብራችን ስንል እምቢ ብለን እሳቸው እሔዱበት ድረስ እበግራችን አብረን እንጓዝ ጀመር።

«.......ታቦር ተራራ ሥር ስንደርስ ቴዎድሮስ ፈረሳቸው ላይ ተቀመጡ። ፈረሱ ላይ በወጡበት ጊዜ ከመሬት ዘለው ተቀመጡበት እንጂ እርካብ አልረገጡም። በፈረስ ግልቢያና አቀማመጥ ጥሩ ችሎታ አላቸው። ፈረስ እየጋለበም ከፈረሱ ላይ መውረድ ይችላሉ......»



አጤ ቴዎድሮስ (በጦር ልብስ)

ዶክተር ብላንክ ጽፎት አቶ ዳኜ ወልደ ሥላሴ እንደተረጐሙት ደግሞ «......በ1852 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስን ስንገኛ ዕድሜያቸው 48 ዓመት ይሆን ነበር። መልካቸውም ከብዙዎቹ አበሾች ጠቆር ያሉ ጠይም አፍንጫቸው ደፍጣጣ አፋቸው ሰፊ ከንፈሮቻቸው ትንንሽ ጠጋጋ ቀጠን

ያሉ........በፈረሰኛነታቸው በጦር አወራወር ስልታቸውና በወታደርነታቸው የተመሰገኑ ጠንካራ የሆነውን ጭፍራቸውን ለማሸነፍ ችሎታ ያላቸው ሰው ነበሩ። ጐድጐድ ያሉት ጥቋቁር ዓይኖቻቸው አገላለጥ የሚያሰኙ ለስላሳ ሆነው በተቆጡ ጊዜ ደግሞ በርበሬ መስለው የሚያስደነግጡ የሚያሸብሩ እሳተ ገሞራ የሚወርውሩ ነበሩ። በድንገት ሲቆጡ መላ አካላቸው የሰውን ልጅ ከፍ ካለ ድንጋጤ ላይ ይጥላል። ጠይሙ ገላቸው ሲኮሰኩስ ስሱ ከንፈራቸው ሲንቀሳቀስና ጠጉራቸው ሲቆም በጠቅላላው ሰውነታቸው የአንበሳነት ጠባይ የያዘ አስደንጋጭ ይሆናል።

«......በተከታዮቻቸው ለመወደድ የሚችሉ የጦር ዘዴና መላ ያላቸው ሰው ነበሩ። ሕይወታቸው ከማለፉ ከጥቂት ቀናት በፊት ባገኛቸው ጊዜ ሙሉ የመሪነት ባሕሪያቸውና ክብራቸው ከመልካም ቤተሰብ የወረሱት ባሕል ያልተለያቸው የመኳንንት ጠባያቸው አብሯቸው ነበር። ከአንደበታቸው የሚወጡት ቃላት የሚጣፍጡ ሲስቁ የሚማርኩ ለዛ ያላቸውና በጠቅላላው ደስ የሚያሰኙ ክብር የተመላቸው ንጉሥ መሆናቸውን ለመረዳት አዳጋች አልነበረም። ቴዎድሮስ በሚያደርጉት በደልና የጭካኔ ሥራ ሁሉ ተገቢ ነው ተብሎ እንዲደገፍላቸው የሚጥሩና ምክንያት የሚፈጥሩ ሰው ነበሩ።.......» ይላል።

ብላንክ እንዳለው ሰውነታቸው የአንበሳነት ጠባይ ያለው ብቻ ሳይሆን ቴዎድሮስ የሚያጫውቷቸው ለማዳ አንበሶችም ነበሩዋቸው። ራሳም በሁለተኛው ቮልዩም መጽሐፉ ላይ በደብረ ታቦር ስላየው ስለ አንበሶቹ ጉዳይ ሲገልፅ «......አድን ቀን አራት አንበሶች አስይዘው እንድመለከታቸው ወደ አለሁበት መጡ። ከአጠገቤም ሲደርሱ የአንበሶቹ ጠባቂ አንበሶቹን እየፈታ እንዲለቃቸው አዘዙትና ‹ምን ያህል ለማዳ እንደሆኑ አያቸው› አሉኝ። እነኚህ አንበሶች ሲለቀቁ ውሎአቸው ከከብቶች ጋር ነው። ሁልጊዜም ፈረሶችን እየተከተሉ ይሔዳሉ። ንጉሡ ጥቂት ቆይተው ለአንበሶቹ ጠባቂ ምልክት ቢሰጡት ጠባቂው ሁሉንም ጠራና በማሰሪያቸው ያዛቸው።......» ብሏል። አንዳንድ ሰዎች ቴዎድሮስ በአንበሶች መሀል ሆነው የተሳሉትን ስዕል ሲያዩ ሰአሊው በልበወለድነት የሳለው የሚመስላቸው አሉ። ነገሩ ግን እርግጥ ነበር።



አጤ ቴዎድሮስ ከአንበሶቻቸው ጋር

## ጠባይ

አጤ ቴዎድሮስ ጠባያቸው ተለዋዋጭ ነበር። በሚያስቆጣ ነገር ይቆጣሉ፥ ይበሳጫሉ፥ ይቀጣሉ። በሚያስቆጣው ነገር ደግሞ ይስቃሉ ይምራሉ ወይም ዝም ይላሉ። አለቃ ተክለ ኢየሱስ «.......የአጤ ቴዎድሮስ ነገር ያስቸገረ ነበረ። ለምሕረት የተባለው ለመዓት ለመዓት የተባለው ለምሕረት ይሆን ነበረ» ብለው ይጽፉና ይህንኑ ሲያብራሩት «አንዱ ያልታሰበ መዓት በመቅደላ የነበረው እስር ገደል ሲጥል ክርስቶስ የፈረደበት አንድ መነኩሴ አላገደደው መጥቶ ይህን ታሪክ አይቼ ልሂድ ብሎ በንጉሡ ትይዩ ቆመ እርሱ ሊመከር አስቦ ነበር። ንጉሱ ግን ተቋጭቷልና እርሱንም አብረህ ጣለው አሉ። ደግሞ የተበደለ ሰው ቢጮህለት ፍርድ አዛብቶ ባፉ አረደው። የዚህ ጊዜ ሚስቱ ስታለቅስ

«አንተ እየተሚገትህ ዳኛው እያደላ፥

ባፋረዱህ እንጂ እኔ ምን ልበላ» አለች። ደግሞ ያልታሰበ ምሕረት እናት አባትዋ እት ወንድሟ በእሳቸው ተቃጥለውባት የቆሜት የነደዳት አበራሽ የምትባል ሴት ስታለቅስ

ሺ ፈረስ በኋላው ሺ ፈረስ በፊቱ፥

ሺ ነፍጥ በኋላ ሺ ነፍጥ በፊቱ

ይህን ሳታይ ሞተች ኮሶ ሻጭ እናቱ።

በሸዋ በትግሬ የተቀመጣችሁ፥

በጐጃም በላስታ የተቀመጣችሁ፥

አንድ ዛላ በርበሬ መንቀል ቸሮአችሁ።

በሉ እንዲህ ቆጥቁጦ ለብልቦ ይፍጃችሁ። ብላ ተሳደበች። ይህን ስድብ ንጉሱ በሰማ ጊዜ ፈከረ። ካሣ አንድ የናቱ የሀበሻ ባል የኢየሩሳሌም ውሽማ አለና አስመጣት። እርስዋም ተጨነቀች። ተንቀጠቀጠች። ሰውም ልትቀጣ ነው ብሎ ቁርጥ አወቀ።

እርስዋ ግን አይስማም ብዬ እንዴት በጉድ ወጣሁ፥

መንጠልጠያ ባገኝ ከሰማይ በወጣሁ

መውረጃ ባገኝ ከምድር በገባሁ እያለች አለቀሰች። ምሕረት የታዘዘበት ቀን ሆኖ ማራት። ወዲያው ሸለማት። ብርም ባርያም ሰጣት።......በማለት ጽፈዋል። አለቃ ወልደ ማርያም ይህንኑ የቴዎድሮስን የጠባይ መለዋወጥ ባጭር ቃል ጽፈው ሲያስረዱ «.......ሰውም ከሰው ተጣልቶ ከቴዎድሮስ መዓት ይጣልህ እያለ ሲረግም፣ ሲመርቅም ከቴዎድሮስ በረከት ይክፈልህ ይል ነበር......» ብለዋል።

አለቃ ወልደ ማርያም ስለዚሁ ስለ ቴዎድሮስ ጠባይ ሲገልጡ «.......በጉዞ በሄዱ በጭንቅ ሥፍራ ከመንገድ ላይ ወታደር ከባልደረቦቹ ብቻውን ተለይተው አንድ ፈረስ ሁለት አህያ ሲነዳ ፈረስ ለብቻ ወደቀ። አህያ ጭነቱን ጣለ። ይህን ጊዜ ያ ወታደር ለማናቸው ይሁን? ተቸግሮ ጨንቆት ፈጣሪውን ሲያማርር ንጉሱ በኋላው ደርሰው ቢሰሙት ‹ለምን ፈጣሪህን ታምርረዋለህ።

ይህን ንጉሥ ግደልልኝ እንዳርፍ ብለህ ለምነው እንጂ› አሉት። እርሱም ሲመልስ ‹ጃንሆይ አልሰማም አለኝ እንጂ እኔስ ሁልጊዜ ለመንሁት› አለ። ቴዎድሮስም እውነትህን ነው ብለው ዝምብ ብለውት ሔዱ።.......» በማለት ጽፈዋል። የእንግሊዝ ቆንሲል ፕላውዴንም «......መጥፎ ባሕሪያቸው ሳይታሰብ ድንገት ቱግ ብለው የሚቆጡት ነው።.......» ሲል ጽፏል።

አንዲት ሴት ባሌ ሽፈተ ብላ ብትነግራቸው ተናደው። «ስትማከር ከርማ ነውኮ። መቶ አምሳ ግረፍልኝ» ብለው አስገረፉዋቸው። ከዋድላ አንድ ሽፍታ አለቃ ከሁለት ተከታዮቹ ጋር ተይዞ መጥቶ ሽፍቶቹ ይቅር ይበሉን እያሉ ሲለምኑ ገበያ ሲለምኑ ገበያ ላይ በጥይት አስደበደቡዋቸው። ሚስቶቻቸውም ከወገቡ በላይ ራቁት ሆነው ለግርፍ በወታደሮች ተይዘው ቀርበው ሊገረፉ ሲተኙ ቴዎድሮስ «ተው አትንካቸው። ሚስቶች ምን ያውቃሉ። ጥፋተኞቹ ባሎቻቸው ናቸው» ብለው በነፃ መልቀቃቸው ራሳም ጽፏል።

የቴዎድሮስን ጠባይ መለዋወጥ ያዩት አጫዋቻቸው የነበሩት ብላታ በቀቱ የተባሉት ሰው ፈርትወ ከቴዎድሮስ አጠገብ መጠጋቱ ተዉ። ቴዎድሮስም አንድ ቀን ወደ ብላታ በቀቱ መላክተኛ ልከው «ምነው እንደወትሮህ አታጫውተኝም፥ ምነው ጠፋህ» ብለው ቢልኩባቸው ብላታ በቀቱ ሲመለከቱ «ቀድሞ በዋዛው ጊዜ አውቅ ነበረ። አሁን ግን ረሳሁት» አሉ።

ዶክተር ብላንክ ጽፎት አቶ ዳኘ ወልደ ሥላሴ ከተረጐሙት ደግሞ «......አጤ ቴዎድሮስ በከተማ የሚኖሩትን ሁሉ ይጠሉዋቸዋል። በልዩ ልዩ ቦታ እየሠፈሩ የሜዳዎችን ንፁህ አየር ማግኘት ስለሚወዱ በሚመርጡት ኮረብታ ላይ ሠራዊቱ ዙሪያውን ይሰፍራል።......ውብ በሆነ በአበሻ አገር በየሌሊቱ መንቀሳቀስን ይመርጣሉ።

«......ቴዎድሮስ በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ ለቅርብ አገልጋይነት አዘውትረው የሚቀጥሩዋቸው ከኤሮፓውያን ጋር የሠሩትን ሰዎች ነበር። .......ዘወትር በአጠገባቸው ከማይለውየው ከአሽከራቸው ሌላ ብዙ ጊዜ የቴዎድሮስን ጠመንጃ፥ ጐራዴ፥ ጦርና ጋሻ፥ በጥንቃቄ የሚጠብቁ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የሚኖሩ የቤት አሽከሮች ነበሩ።

«.......አጤ ቴዎድሮስ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ንጉሥ መሆናቸው ቢታወቅም በብዕራቸው ከማንም ሰው ጋር ተጻጽፈው አያውቁም። ነገር ግን በማንኛውም ጊዜ ብዙ ፀሐፊዎች ስለሚያስከትሉ ደብዳቤ ለመጻፍ ሲያስቡ በቃላቸው እየነገሩ ያፅፏቸዋል። የቴዎድሮስ አንጐል አስገራሚ በሆነ ሁኔታ የማስታወስ ችሎታ ስላለው የደብዳቤዎች መልስ በሚፅፉበት ጊዜ ከሳምንት ከወር ወይም ከብዙ ዓመታት በፊት ለደረሷቸው ደብዳቤዎች መልስ መስጠት ባስፈለጋቸው ጊዜ የተደረገውንና የሆነውን ሁሉ በትክክል እያስታወሱ የሚፈለገውን መልስ መስጠት ይችላሉ።

«.......አጤ ቴዎድሮስ በጀግንነታቸው የማይጠረጠሩ ንጉስ ቢሆኑም በሚሠፍሩበት ጊዜ ሙሉ ጥንቃቄ እንዲደረግ ያዛሉ። ድንኳኑ የሚተከልበት ኮረብታ ሁልጊዜ የተጣራ ነፍጥ በያዙ ወታደሮች ሲጠበቅ ያድራል። ቴዎድሮስም ሽጉጣችወን ከትራሳቸውና ብዙ የተለጐሙ መሣሪያዎች ከአጠገባቸው ሳያስቀምጡ እንቅልፍ አይወስዳቸውም።......መርዝ ከምግብ ጋር ተቀላቅሎ እንዳይሰጣቸው እጅግ ስለሚፈሩ ማንኛውንም ዓይነት ምግብ ንግሥቲቱ ወይም ምትኳ እንዲሠሩትና በሚቀርብላቸው ጊዜ ብዙ ሴቶች ቀምሰው የምግቡን ንፁህነት ማሳየት ይኖርባቸዋል። የሚጠጣውም ሁሉ ውሃ ይሁን ጠጅና አረቄ በዚሁ ዓይነት መንገድ መጠበቅ ስላለበት መጠጥ የያዘውን ዋንጫ ወይም ብርሌውን የሚያቀርበው አሳላፊ ከንጉሡ ነገሥቱ ፊት ቀምሶ ማረጋገት አለበት።

«.......አጤ ቴዎድሮስ በጣም ቀናተኛ የሆኑ ባል ነበሩ። ........ለንግሥቲቱ በጣም ስለሚጠነቅቁ ምንጊዜም ቢሆን ከሠራዊቱ ጋር አብረው እንዲጓዙ አያደርጓቸውም። ንግሥቲቱ ደህና ሆነው ተሻፋፍነው በሌሊት በብዙ ጃንደረባዎች ታጅበው መጓዝ ይኖርባቸዋል። በጉዞ ላይ ሳሉ ዓይኖቹን በንግሥቲቱ ላይ የማያሳፍፍር ወንድ ከፍ ካለ መከራ ላይ ይወድቃል። አንድ ቀን ንግስቲቱን አጅቦ የሚጓዝ ወታደር ወደ ንግስቲቱ ድንኳን ተደብቀው ከተጠጋ በኋላ ደንገጡራ (ገረዲቱ) ጠጅ እንድትሰጠው ለምኖ ሲጠጣ ባለ መታደል አንድ ጃንደረባ ስላየው ተኩሶ ከንጉስ ነገስቱ ፊት ቀርቦ ወንጀሉ ከተነገረ በኋላ ቴዎድሮስ በመልካም ስሜት ላይ ስለነበሩ ወታደሩ ጠጅ ይወድ እንደሆነ ስለጠየቁት በፍርሃት ይርበደበድ የነበረው ወታደር የጠጅ ዓመልተኛ መሆኑ ስለተረጋገጠ ንጉሱ አከታትለው ለወደፊቱ

ወደ ንግሥቲቱ ድንኳን እንዳይጠጋ ትምህርት እንዲሆን አምሳ ጅራፍ እንዲገረፍ አዘዙ። አንድ ቀን መቅደላን በጐበኙ ጊዜ በአምባው አዛዥ ባቀረበው ክስ አንዱ የአምባው መኰንን ከሚስቱ መኖሪያ ቤት ገብቶ መያዙን ስለገለፀ ቴዎድሮስ ስቀው «ምን ቂል ነህ። እኔ ንጉሥ ነኝ ነገር ግን ሚስቴን በሚገባ አልጠብቅምን?» ሲሉ ተናገሩ።

«.......ማልደው መነሳት ይወዱ ነበር። በመጠኑ እንቅልፍ ይወዳሉ። ከቀኑ ሁለት እስከ አሥር ሰዓት ድረስ የሚቀርባቸውን ጉዳይ ሁሉ እያጠኑ ይፈርዳሉ። ከሰዓት በኋላ ጠባያቸው የሚለወጥ ስለሆነ በተለይም የቤተ ክህነት ሰዎች በሚቻላቸው ሁሉ ከፊታቸው ይሠወራሉ። ቴዎድሮስ የጥንት ልማዳቸውን ያልረሱ ሰው ስለነበሩ ሊነጋጋ ወገግ ሲል ብቻቸውን ከድንጋይ ላይ ተቀምጠው በአሳብ ባህል እየዋኙ በፀጥታ ሲፀልዩ ይታዩ ነበር። በምግብ በኩል ብዙ የማይስገበገቡና የእህል ወጥ በፍስክም፥ ቀን እንጀራና የአሳ ወይም የስጋ ወጥ ይበላሉ።

«......አጤ ቴዎድሮስ ተራ የሆነ ልቦስችን ኩታና በአገር ውስጥ የተሠራ ሱሪና እጀጠባብ ይለብሳሉ። ጫማና ባርኔጣ ግን አይወዱም። በጣም ረጅም የሆነው ጠጉራቸው በሶስት ረድፍ ተሠርቶ ከአንገታቸው ላይ ይደርስ ነበር። ወደ መጨረሻው ግን ስለ ጠጉራቸው የነበራቸውን ጥንቃቄና መንከባከብ በመተዋቸው ጠጉራቸው ብዙ ተጐሳቁሎ ይታይ ነበር። በህዝቡ ብስጭት ምክንያት የተሰማቸውን ሀዘን ለመግለፅ ሲሉ በአበሻ ልማድ መሠረት ቅቤ በመቀባት የሚያደርጉትን የጠጉር መከባከብ ትተው ነበር። አንድ ቀን ሲያነጋግሩን ልብሳችወ በጣም ተራ በመሆኑ ይቅርታ ጠይቀው ለጥቂት ጊዜ አገራቸውን አበሻን በሰላም ሊገዙ ችለው ስለነበረ ለንጉሥ የሚገባውን የክብር ልብስ እየለበሱ ንጉስነታቸውን ይገልፁ እንደ ነበረ አንስተው አሁን ግን በሕዝቡ ብስጭት ምክንያት በየጊዜው ለጦርነት ተሰናድተው ስለሚኖሩ እንደ አንድ ተራ ወታደር መልበስ መምረጣቸውን አስረዱን። ቢሆንም ቴዎድሮስ የዘመነ መንግሥታቸው ፍጻሜ እንደተቃረበና የሚወድቁ መሆኑን ስለተገነዘቡት ብዙ ጊዜ በንጉሳዊ ልብሳቸውና ጌጣቸው እያሸበረቁ መታይት ጀምረው ነበር። ይህንንም ማድረጋቸው ለሕዝቡ በስልጣን ላይ መኖራቸውን ለማሳየት አስበው ይሆናል......» በማለት ፅፈዋል።

ዱፍተን ደግሞ «.......እኛ የደረስን ጊዜ ንጉሱ አልነበሩም። ወደ ደቡብ የሶስት ቀን ጉዞ ሄደው ነበረ። ከሳምንት በኋላ ይሆናል ደብረ ታቦር ተመልሰው መጡ።......ባልደረባዬ ዎልድሜየር ንጉሱን እንኳን ደህና መጡ ብሎ እጅ ከነሳ በኋላ አንድ ወጣት እንግሊዛዊ ከእርስዎ ጋር ለመገናኘት ከውጭ ይጠብቃል ብሎ ነግሮኝ ኖሮ ተጠራሁ። እንደታዘዝሁት ባርኔጣዬንና ጫማዬን አውልቄ ከደጅ አስቀምጬ ገባሁ።...... ዝነኛው ቴዎድሮስ የታወቀው ጦረኛ የታላቁ አገር የበላይ ከጥጥ የተሠራ ሸሚዝና ሱሪ ለብሰዋል። እነሱም ቢሆኑ በጣም ንፁህ አይደሉም። በዙፋን ላይ አልተቀመጡም ከመሬት አንድ ጫማ ያህል ከፍ በምትል ድንክ ላይ ተቀምጠዋል። በመጀመሪያ ጊዜ ንጉሱ አይደሉም ብዬ አስቤ ነበር። እጅ የነሳሁትም ያለ ቦታዬ ለሌላ ሰው ነው ብዬ ነበር። እንድቀመጥ አዘዙኝ። እግሬን አጣምሬ ተቀመጥሁ። በመጠጥ በኩል አረቄና ጠጅ መጥቶ በሚገባ ተጋበዝን። በምግቡም በኩል የጤፍ እንጀራና ስጋ እንደ ቁርስ ተብሎ በልተናል። ንጉሱም እየደጋገሙ አረቄ ይጠጣሉ።......ይህን ያህል አብዝተው ጠጪ አይደሉም። ደጋግመው ይጠጁ እንጂ ካንድ የተወሰነ ደረጃ ሲደርሱ ያቆማሉ። አብዛኛውን ጊዜም የሚጠጡት ከቴምርና ከማር የሚሠራውን የሱዳን አረቄ ነው።.......» ብሏል።

በሌላ ጊዜ ስለሆነው ሁኔታ ዱፍተን ሲፅፍ «.......በማግስቱ ለፈረንሳዩ ቆንሲል ለሌዣን ይፋ አቀባበል አደረጉለት። ለአቀባበሉም ስርዓት መድፍ ተተኮሰ በዙፋናቸው ተቀምጠው ተቀበሉት። የተቀበሉትም ቤት ግድግዳው ረጅም ሆኖ የሚያማምሩ ምንጣፎችና ኸንጉርጉ ጨርቆች ተደርገውበታል። መሬቱም እንደዚሁ ሙሉውን ተነጥፏል። ከናፖሊዮን የተላከውንም የወዳጅነት ደብዳቤ ከሌዣን እጅ ተቀበሉ።

«.......ሌዣን አሽከሩን የስጦታውን እቃ እንዲያቀርብ አዘዘ። ሽጉጦች፥ ውብ የሆኑ ዕቃዎች በብዙ ሳጥን የተያዙ የሀር ልብሶችን አቀረበ። ......ለስጦታው ጓጉተው በተመስጦ አይመለከቱም።........አንዷ ብቻ አንዱን ሽጉጥ አነሱና ወደ አይናቸው አስጠግተው እያነጣጠሩ ተመለከቱ። ምንም ነገር ሳይናገሩም አጠገባቸው ለቆመው አሽከር ሰጡት። ሀር ጨርቆቹንማ መለስ ብለውም አላዩዋቸውም። ከሳጥኑ መጨረሻ ያለው እስቲወጣም አልጠበቁም። «እንዲህ ዓይነቱ ነገር የሴት ስለሆነ ለእቴጌይቱ ይሁን» አሉ። ከሀሩ ልብስ

ይልቅ በሳጥኑ መከደኛ ላይ የተለበዱት ባለቀለም ስእሎች ስሜት ሰጡዋቸው......በማለት ፅፈዋል።

ቴዎድሮስ በሴት በኩል ያላቸው ጠባይ እንደ አብዛኛው ወንድ ሁሉ ቢሆንም እንደሌላው ጠባያቸው ሁሉ ቆንጆ ካዩ የማያትመልጣቸውና የሚንቁም ወንድ ነበሩ። በዚህ በኩል ያላቸውንም ጠባይ እንዲህ ዓይነቱ ናቸው ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ነው። አንዳንዱን ሁኔታ እንመልከት።

ወይዘሮ የተመኙ የየጁ ተወላጅ ሲሆኑ ባላቸውም የየጁ ኦሮሞ ነበር። ወይዘሮ የተመኙ በእስልምና ሃይማኖት የሚያምኑ ሴት ነበሩ። ቴዎድሮስ የእኚህን ሴት ቁንጅናና ዘንፋላነት እንደሰሙ ከባላቸው ነጥለው አስመጡዋቸው። ክርስትና አስነውተውም ስማችወን የተመኙ ብለው አስቀሩዋችው። ባልዬውም ይገሉኛል ብሎ አገር ጥሎ ጠፋ። ቴዎድሮስ ግን እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ የተመኙን ወደዱዋቸው ይኖሩ ነበር።

ቴዎድሮስ የደንቢያዋን ወይዘሮ ሒሩትን በቁንጅናቸው አድንቀውና ወደው ቁባት አድርገው አስቀምጠዋቸው ነበር። ወይዘሮ ሒሩት በቴዎድሮስ ተግባር ይበሳጩና ያዝኑ ነበር ጠፍተው ከታና ደሴት ደቅ ከሚባለው ገዳም ገብተው ተቀመጡ። ቴዎድሮስም በያለበት አያስፈልገው ስ9ለጠፉባቸው አዝነው ተቀመጡ። አቶ ገሪማ ታፈረ እንደጻፉት ይህን ምስጢር የሚያውቀው የቴዎድሮስ አዝማሪ በግብር ላይ ሲዘፍን «ወድቃ ተሰብራ ያለ ውሉ፥

ሒሩት ደቃለች አሉ» ብለው በቅኔ ግጥም በመናገሩ ቴዎድሮስ ወይጦዎችን ሰብሰበው በጀልባ ሰው ልከው ወይዘሮ ሒሩትን አስይዘው አስመጡዋቸው።

ይህን የመሳሰለውን ሰናይ ቴዎድሮስ ለውበት ያላቸውን አድናቆትና ፍቅር እንረዳለን። በሌላው ሁኔታዎች ደግሞ ያን የመሰሉት ውበት አፍቃሪ ወንድ፥ መነኩሴ መስለው እናገኛቸዋለን።

በጐንደር ከተማ አቅራቢያ ቀሃ ወንዝ አጠገብ አጤ ሰቀላ ከተባለው ኮረብታ ላይ ቴዎድሮስ የቁንጅና ውድድር እንዲደረግና አዘዙ። ቴዎድሮስ ትእዛዙን ይስጡ እንጂ ነገሩ የመጣው ከኤሮፓውያኖቹ ከነቤል ይመስላል። የምርጫው ወይም የቁንጅና ውድድሩ ሊቀ መናብርት ኢትዮጵዊው ገብርዬና እንግሊዛዊው ጆን (ዮሐንስ) ቤል ነበሩ።

ራሳቸው አጤ ቴዎድሮስ ባሉበት የቁንጅና ውድድር ተካሒዶ 1ኛ ጣይቱ ይልማ ሆነች። ጣይቱ ይልማ ለውድድር የቀረበችው ከሰቀልት ወረዳ ከመቋቋሚያ ማርያም ሲሆን የደጃዝች ይልማ አሰፋ ልጅ ናት። 2ኛ የወጣችው ወይዘሮ ተዋበች የተባለች ናት። ተዋበች እስላም ስትሆን ባልዋም መሐመድ ኩርማን ይባል ነበር። ተዋብች 2ኛ ለመውጣት የቻለችው በጠጉርዋ ማማር በቁንዳላዋ አወራረድ በሹርባዋ አረዛዘም ነበር። እነኚህን የመሳሰሉት ከማንም የሚበልጡ ወብ ሴቶች ተመርጠውላቸው ሳለ ቴዎድሮስ ከጉዳይም ሳያገቡዋቸው ተዋቸው። አቶ ቢወጣ ኪዳኑ በዘመኑ ቢያዙት ማስታወሻ እንደገለጡት ጣይቱ ይልማን በጋፋት የመድፍ ሠራተኞች አለቃ የነበረው ወርመር (አርማኤል) አብቷት ብዙ ልጆች ወልዳለታለች።

## ርህራሄ (ደግነት)

ቴዎድሮስ ደስ ሰው ነበሩ። ወዳጃቸው የነበረው ዎልድሜየር ሲጽፍ «.......አንድ ቀን ከንጉሥ ቴዎድሮስ ጋር በየባላገሩ ስንዘዋወር አንዲት ድሃ ሴት አጋጠመችን። ሴትዮዋ ምንም ልብስ ያለበሰች ፈፅማ ራቁትዋን ነበረች። ንጉሱ ከበቅሎአቸው ወረዱና የለበሱትን ሻማ ከላያቸው ላይ አንስተው ሴትዮዋን አለበሷት። ከኢዝያም በኋላ ገንዘብ ሊሰጧት ፈልገው ገንዘብ አጡ። ወደኔም ዞር ብለው እስቲ ጥቂት ብር እንዳለህ አበድረኝ አሉኝ። እኔም ‹እሺ ጃንሆይ አሁን ለግዜው አምስት ብር አለኝ። እሱን ልስጦት› ብዬ ሰጧኋቸው። እሳቸውም ገንዘቡን ከኔ ወስደው ለድሃይቱ ሴትዮ መቶ ብር ስጡኝ። እኔም ‹ጃንሆይ እኔ የሰጠሆት አምስት ብር ነው ለምን 95 ብር አስበልጠው ይሰጡልኛል?› አልኳቸው። እሳቸውም ‹የመለስኩልህና የሰጠሁህ እንደ ንጉስነቴ ነው።› አሉኝ። አመስግኜም እኔም እንደተደሰትኩ ወደ ቤቴ ሄድሁ...... ብሏል።

በሌላ ቀን ስለሆነው ነገር ደግሞ ሄደው ዎልድሜየር ሲጽፍ «......አንድ ቀን ከንጉሱ ጋር በጋማ ከብት ተቀምጠን በአገር ውስጥ እንዘዋወር ነበር። አንድ ሰው ከመንገዳችን ላይ ቆመና ጃንሆይ ጃንሆይ እያለ ጮኸ። ንጉሱም ‹ምን ሆነሃል ተናገር› አሉት። ሰውየውም ‹ከመንገድ ላይ ሃያ ብር አገኘሁ። ይህ ገንዘብ የማን እንደሆነ እኔ አላውቅም። በዚህ ምክንያት ገንዘቡን ወደ ጃንሆይ

አመጣሁት› አላቸው። ንጉሱም ‹ይሄ ያንተ የዋህነት ነው። አሁንም ገንዘብ የጠፋው ሰው እስቲገኝ ድረስ ገንዘቡን አንተጋ አስቀምጠው። ስላንተ ታማኝነት ግን እኔ ሌላ ሀያ ብር እሰጥሃለሁ› ብለው ሰጡት። ሰውዬውም እየተደሰተ ሔደ። ይህን ወሬ አንድ ሌላ ሰው ሰምቶ እንዲህ በቀላሉ ገንዘብ የሚገኝ ከሆነ የቀበርኩትን አርባ ብር አውጥቼ ለንጉሱ ላቅርብ ብሎ ይዞ መጣና ‹ጃንሆይ ይሄንን ገንዘብ ከመሬት አገኘሁት። የማን ገንዘብ እንደሆነ ስላማላውቅ ወደ እርስዎ አመጣሁት› አላቸው። ንጉሱም የሰውየው አታላይነት ገብቷቸው ‹ገንዘቡን ወስደህ ለኔ ገንዘብ ያዥ ስጥ› አሉት። ሰውዬውም እያዘነ ገንዘቡን ለንጉሱ ገንዘ ያዥ አስረክቦ ወደ ቤቱ ሐሔ.......› በማለት ጽፏል።

ድፍተን ስለ ቴዎድሮስ አዛኝነት ሲስፍ «......ድሆችን እራሳቸው እየተቆጣጠሩ ይጠብቃሉ። ድንኳናቸው በተተከለበት ቦታ ሁሉ የድሆችን አቤቱታ መስማት ይወዳሉ። ሁልጊዜ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የድሆችን ጉዳይ ይሰማሉ። በጉዞም ላይ በሳምንት በሺዎች የሚቆጠር ብር ለድሆች ይሰጣሉ። ይህንንም ስጦታ በሚሰጡበት ጊዜ «ድሆችን ባልረዳ ለእግዚአብሔር ያሳጡኛል። እኔም እራሴ ድሃ ነበርኩ ይላሉ።......» ብሏል።

ፕላውዲን እንደጻፈው ደግሞ «.....አንድ ቀን ለጉዞ ልንነሳ ስንል ስጦታ ሰጡኝና አልቀበልም ብላቸው ‹አንተ ልጄ ነህ። ከኔ የምትፈልገውን ነገር ስሰጥህ ለምን አትቀበልም?› አሉኝ። እኔም የታዘዝኩት ነገር እንደሆነ ብነግራቸው ‹ግድ የለም። መልክተኞች ሁሉ ከመንግሥታቸው እንደሚከፈላቸው አውቃለሁ። አገሬ ግን እንግዶችን እንድትቀበል ትጠቅይቀናለች። የእግንዶችን እግር ማጠብ ይገባናል።........ክፍያ የምከፍልህ አይደለም ሀብታምም መሆንህን አውቃለሁ። ይሄ ግን አሁን ብድር ነው አንተ ደሞ በተግባር ትከፍለኝ ይሆናል። ባንተም ረዳትነት ብዙ ቤቶችን እገነባለሁ። › አሉኝ። እኔም ‹ምንም አይደለሁም። ለእርሶ የሚጠቅሙ የኔ ንግሥት ናቸው›። አልኳቸው እሳቸውም ‹ስማኝማ። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የምድር ነገሥታት ሁሉ በኔ ላይ ተቃውመው ለመነሳት አይችሉም። ስለዚህ አልፈራቸውም። ግን ያንተ ንግሥት አንተን ወደኔ ልከውልኛልና ክርስቲያን ናቸው። እምነታችንም ያስተሳስረናል። ክርስቶስ ወዳጅነታችንን ፈቅዷል።

እግዚአብሔር በዚህ መልካም መንገድ ምራኝ› አሉኝና ለብቻዬ ወስደው አንድ ሺ ብር ሰጡኝ። ከዚያም እጄን ይዘው ሰው ሁሉ ሟች ነው። አንድ ነገር በኔ ላይ ቢደርስ ልጄ ወዳጄ ሁነኝ። ወደ አገርህም ሁላችሁንም የሚወድ ሰው ብለህ ጻፍ።...... እወድሃለሁ። አምንሃለሁ። በል ሂድ። ደህናዋል አሉኝ......» ብሏል።

ፕላውዲን ጁን 25 1855 ወደ ሃገሩ ባስተላለፈው ሪፖርት «.....ንጉሥ ቴዎድሮስ በዕድሜ ወጣት ናቸው።......ትሁትና ደስተኛ ናቸው። የባርያ ንግድን አጥብቀው የሚቃወሙ ናቸው። የተሸጡትን ባርያዎች እሳቸው እንደገና የተገዙበትን ዋጋ እየከፈሉ በማስለቀቅ ነፃ ያወጡዋቸዋል። .......ወታደሩንም ከሚከፈለውና እየሠራ ከሚያገኘው ገቢ በስተቀር ከገበሬው ዘንድ እናይደርስ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥተዋል።......» በማለት ለሕዝቡ ያላቸውን ርህራኄ ገልጿል።

ዎልድ ሜየር ስለ ባርያቸው ጉዳይ በጻፈው በጐንደር አካባቢ ባርያ ነጋዴዎች የሚወስዷቸውን አስጥለው በብዙ መቶ የሚቆጠሩ በነጻ ከለቀቁ በኋላ ጥቂቶቹን ለዎልድሜየር ሲልኳቸው በጻፉት ደብዳቤ «......እነኚህን ወጣት ልጆች ጥበብና ሃይማኖቶች እንድታስተምራቸው ይሁን። እንደእነኝህ ያሉትንም ያልታደሉ ፍጥረቶች ባገኘሁ ጊዜ እልክልሃለሁ። ደስ እንዲላቸው። የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ የምችለው እኔ ነኝ......» ብለውታል።

ቀደም ብለን እንዳነበብነው የደጃዝማች ክንፉ ልጆች መኮንንና ይልማ የጐጃሙን ገዥ ብሩ ጐሹን ቸንቲ በር ከተባለው ሥፍራ በተዋጉ ጊዜ ያን ጊዜ ካሣ ይባሉ የነበሩት ቴዎድሮስ ከደጃች ክግኑ ልጆች ጋር አብረው ነበሩ። የደጃች ክንፉ ልጆች ድል ሆነው ጦራቸው በተበታተነ ጊዜ የያኔው ካሣም አምልጠው አለፋላይ ካንድ ሰው ቤት ተደብቀው ወር ሙሉ መቀመጣቸውን አንብበናል። ብዙ ቆይቶ የያኔው ካሣ ከእቴጌ መነን ጋር ተዋግተው ድል ካደረጉ በኋላ ሠራዊታቸውን በየባላገሩ ቤት ምሪት ሰደዱት። ምሪት ከገባባቸው ባላገሮች መሀል ያ ድሮ ሰውሮ ወር ሙሉ ከደበቃቸው ሰው ቤት 12 ወታደሮች ገብተው ሠፈሩበት። ይህ ሰው ሊቀለቡ የገቡበት ሰዎች ስለበዙበት በለሊት ተነስቶ ወደያኔው ካሳ ዘንድ ሔዶ ጮኸ። ደጃች ካሣም ሰውየውን በድምጡ አውቀው ወታደር ልከው አስይዘው አስመጡት። እንደመጣም አንተ እገሌ የምትባለው

ሰው አይደለህም? ብለው ቢጠይቁት አዎን ነኝ አለ። ከዚያም የሠራላቸውን ውለታ ሁሉ ነግረው ከእልፍኝ አስገብተው ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ተዋበች ጋር አስተዋውቀው ጋበዙት። በመጨረሻም አንድ ወታደር እንዳይገባበት አድርገው ሃያ ብር ስምንት በሬ ስምንት ላም ሴትና ወንድ ባርያዎች ሰጥተው አገሩን የሱ ግዛት ጉልት አድርገው ሰጥተው ሰደዱት። ይህም ቴዎድሮስ አስታዋሽ አእምሮና ብድር መላሽ መሆናቸውን ያሳያል።

በሽፍትነት ዘመናቸው ስማቸውም ካሣ በነበረበት ጊዜ ከወዳጃቸው ከሌላው ሽፍታ ከእንድሪስ ጋር ሆነው አምበለይ ከሚባል ከሻንቅላ አገር ዘመቱ። ከዚያም ብዙ ዘረፋ አግኝተው 600 የሚሆን ሻንቅላም ተማረከ። የተዘረፈው ፍየልና በግም ለቁጥር አስቸግሮ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ከካሣ በኩል ሁለት ወታደሮች ሻንቅላ ሲያባርሩ በጦሩ ተወግተው ወድቀው መቅረታቸውን ካሣ ሰሙ። እንደ ሰሙ ሰባት ያህል አሽከሮቻቸውን አስከትለው ሁለት ወታደሮቻቸው ወደ ወደቁበት ቦታ ሔዱ። ከቦታውም ሲደርሱ ሁለት ወታደሮች ክፉኛ ተወግተው ወድቀው አገኙዋቸው። አንዱን የቆሰለ ወታደር አሽከሮች ሲሸከሙ አንዱ ግን እሳቸው ተሸክመው ይጓዙ ጀመር። በጉዞው ጊዜ ካሣ የተሸከሙት ወታደር ከሚፈሰው ደም ብዛት የተነሳ ደሙ ከሣ ጀርባ እየተንቆረቆረ በእግራቸው እያለፈው ይወርድ ጀመር። አለቃ ዘነበ እንደ ጻፉት በደም የተበከለው የልጅ ካሣ እግር «......በክረምት እንደሚሔድ ሰው ብዙ ጭቃ አነሳ»። ካሣ እንዲህ ለፍተው ከሠፈር ያደረሱዋቸው ሁለት ወታደሮች ከሠፈር ሲገቡ ሞቱ።

ወሎ ውስጥ ለጋምቦ ላይ ጮቄ ጨሜ በተባለው ቦታ ሠፍረው ሳለ በኤሮፓ እንደሚዘንበው በረዶ ዓይነት ዋእይም እንደ አመድ የሚበን በረዶ ዘነበ። ይህም በሰውም በከብቱም ላይ ሁሉ እየወረደ እንደ ጭቃ እየተመረገ ተቀመጠ። አቅመ ቢሶችና ሐመምተኞች በበረዶው ምክንያት ብዙዎቹ ሞቱ። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ ድንኳናቸው ውስጥ ነበሩ። መጠጊያ ወይም መከለያ የሌለው ሕዝብ በበረዶው መመታቱን ያዩት ቴዎድሮስ ሕዝቡ እንደዚህ ያለ ሥቃይ ላይ ሆኖ እኔ ድንኳን ውስጥ ተጠልዬ አልቀመጥም ብለው ከደጅ ወጥተው በረዶው ከሚወርድበት ውስጥ ቆሙ። ሠራዊቱንም እግዚአ በሉ ብለው አዘው እግዚአታው ሲጀመር በረዶው ቆመው ፀሐይ ወጣ።

## ጭካኔ

አጤ ቴዎድሮስ የበፊት ሚስታቸው እቴጌ ተዋበች ከሞቱ በኋላ ጠባያቸው ተለዋውጦ ጨካኝ ሆኑ የሚሉ አሉ። ፈረንጅ ፀሐፊዎችም መካሪያቸው ጆን ቤል ከሞተ በኋላ መካሪ በማጣት የጭካኔ ሥራ ጀመሩ እያሉ ፅፈዋል። እንደተባለው የተዋበችና የቤል መሞት ቴዎድሮስን ከብስጭት ላይ ቢጥልም አጠቃሎ የቴዎድሮስን ጠባይ ለወጠ ለማለት አይቻልም። ገና በሽፍትነት ሳሉ ቀደም እንዳነበብነው በህብረት እየዘረፉ አብረው ሊበሉ የተሰማሙዋቸው ሽፍቶች ለየራሳቸው ያገኘነውን እንብላ ቢሏቸው ተቆጥተው የተያዙትን ሰባት ሽፍቶች ጉልበት ጉልበታቸውን ቆርጠው ጣሉዋቸው። ከእንዲህ ዓይነቱ ቅጣት መግደል የተሻለ ነው። ከዚያም ሌላ የሱዳኑን ወዳጃቸውን የእንድሪስን ጠላቶች ድል አድርገው ከማረኩ በኋላ የእሳቸው መጨረስ አንሶ 210 ኢትዮጵያውያኖች በፈለገህ መንገድ ግደላቸው ብለው ለእንድሪስ ሰጡት። እንድሪስም ሁሉንም በሰይፍ ፈጃቸው። ራሳቸው ካሳም በዚሁ ጊዜ ከተማረኩት ሰዎች መሀል አምሳዎቹን ሁለት ሁለት ጆሮአቸውን እያስቆረጡ ግፍ ከሰሩ በኋላ ለቀቁዋቸው ከመጀመሪያው ጀምሮ እንጂ ከተዋበችና ከቤል ሞት በኋላ አይደለም።

ወይዘሮ ተዋበችን ካገቡ በኋላ ቢሆን ብዙ የጭካኔ ተግባሮችን ፈፅመዋል። ቀኛዝማች ወንድይራድን ራትና ምሳህ ኮሶ ይሁን ብለው በእንስራ ሙሉ የተበጠበጠ ኮሶ ሰጥተው እያጠጡ በጭካኔ የገደሉዋቸው ወይዘሮ ተዋበች ሳይሞቱ በፊት ነው። ጊምባ ላይ የተማረኩ 47 አሮሞዎችን ሁለት ሁለት እጃቸውን እየቆረጡና ቁራጩን በያንገቱ ላይ በገመድ ላይ በገመድ እያሰሩ አገርህ ግባ ብለው የሰደዱት እቴጌ ተዋበችም ቤልም እያሉ ነው። ይህን የመሳሰለውን ብዙ ቅጣ ስናይ ቴዎድሮስ ከተዋበችና ከጆን ቤል ሞት በኋላ ጠባያቸው ተለወጠ የሚባለው አባባል ትክክል አይመስልም። ምናልባት ከሁለቱ ሰዎች ሞት በኋላ የበለጠ ጨካኝ ሆኑ ቢባል ይሻላል።

አለቃ ገብረ ሥላሴ እንደ ፃፉት ደግሞ ቴዎድሮስ ጭካኔ ያበዙት የሸዋው ምኒልክ ካመለጡ በኋላ ነው ይላሉ። ይህንንም ሲያብራሩ «......ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ጋር......ከዕለታት ባንድ ቀን ሲነጋገሩ «አባቴ በሀገርዎ ሳሉ የኔን ወሬ ይሰሙ ኖርዋልን?› ብለው ጠየቋቸው። እሳቸውም ‹ቸር ነህ፥ ጀግና ነህ ይሉሃል። ነገር ግን የሸለመውን

የሾመውን ያስራል፥ ይገድላል ይቆርጣል፥ ይሉሃል› አሏቸው። አጼ ቴዎድሮስም መልሰሉ ‹በሽፍትነቴ በረሃ ለበረሃ ስሔድ መነኩሴ አገኘሁ። ያም መነኩሴ ትነግሣለህ ነገር ግን ያሳደግኸው ሰው ከቤትህ ከወጣ ዕለት መንግሥት ያጥራል ብሎ ነገረኝ። ይህን የማደርገው ስለዚህ ነው» አሏቸው። አቡነ ቄርሎስም ‹እግዚአብሔር የሚያነግሰውን ሽፍኖ ይጠብቀዋል እንጂ አንተ መቼ ታገኘዋለህ›.......አሏቸው.......» ይላሉ ይህም እውነት ቢሆን እንኳ ቴዎድሮስ ጭካኔ የጀመሩት ምኒልክ ከመማረካቸው በፊት ገና በሽፍትነት ሳሉ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ቴዎድሮስ ጨካኝ የሆኑት የአገሪቱን አንድነት ለማስከበር ሲሉ ነው ይላሉ። ይህም እውነት ቢመስልም ሕዝብ የሚያብረው በሰላም መንገድ እንጂ በኃይልና በጭካኔ አይደለም የኃይል ሥራ ለጊዜው ላይ ላዩን መልካም ውጤት የሰጠ ቢመስልም ውስጡ ግን የሚያመረቅዝ ነው። ለቴዎድሮስም በሰላም የገቡላቸው ሁሉ የኃይል ሥራቸውን በመመልከትና በመስማት ነግ በኔ እያለ ከዳቸው እንጂ ለጥ ሰጥ ብሎ አልተገዛላቸውም። ኢትዮጵያን አንድ አድርጌ እገዛለሁ ያሉት ቴዎድሮስ በመጨረሻው ሰዓት የእንግሊዝ ጦር በመጣ ጊዜ ሳላምጌ ላይ ሆነው «.....ወደ አምባው አመልክተው ‹ግዛቴ ያ ብቻ ነው። ስለዚህ ከዚህ እቆያቸዋለሁ። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ያለው ይሆናል......» ብለው መናገራቸውን ዶክተር ብላንክ ጽፏል።

የቴዎድሮስን አስተዳደር ሁኔታ እያየ ሠራዊቱና መኳንንቱ ባይከድዳቸው ኖሮ የኢትዮጵያ ወሰን ለእንግሊዝ ጦር ክፍት ሊሆንለት ባልቻለ ነበር። እንግሊዞችም ቢሆኑ እስረኞቻቸውን ለማስፈታት ለመግባት የደፈሩት የመኳንንቱን መለያየት በማየትና ምቹ ክፍት ጐዳና በማግኘታቸው ነው እንጂ በጉልበታቸው ብቻ ተመክተው ቢመጡ ኖሮ ምናልባትም በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍ ያለ የደም መፋሰስ ይደርስ ነበር። ግን የሁሉም በቴዎድሮስ ላይ ማደምና የሁሉም መከፋፈል የቴዎድሮስን መንግሥት አዳከመ። ዶክተር ብላንክ ሲጽፍ «......አጤ ቴዎድሮስ ከጥቂት ወራት በፊት ይገዙት የነበረው ግዛት ሁሉ ቀረቻቸው። በሰኔ ወር 1859 ዓ.ም ያለ ግዛት ንጉስ ያለ ጦር ሠራዊት ጀኔራል ሆኑ። መቅደላና ዙርአምባ በእርሳቸው ወታደሮች እንደተጠበቁ ነበሩ። ከእነዚህ ቦታዎች በስተቀር ግን የኔ ነው የሚሉት አንድም ቦታ አልቀረ.......»

ብሏል። ያኔ በቴዎድሮስ ጐን ጥሩ አማካሪዎች ቢኖሩና ቴዎድሮስም ተቀባይ ቢሆኑ ኖሮ የቴዎድሮስ መንግሥት ቶሎ ለመውደቅና በየጊዜው ከመዋጋት ባደረሱ ነበር። ነገር ግን ዙርያቸውን የከበቧቸው ወዳጆቼ የሚሉዋቸው ሁሉ የእለት ጥቅማቸውን ፈላጊዎችና መስሎ አዳሪዎች በመሆናቸው ለቴዎድሮስ አወዳደቅ መስላል ዘርጣጮች ሆኑ። ቴዎድሮስም ቢሆኑ «የሚጠሉህን ሰዎች ከማጥፋት ይልቅ የሚጠሉብህን ነገር አጥፋ» የሚለውን የምሥራቃውያንን ምክር አልተከተለም።

ቴዎድሮስ ከሠሩዋቸው የጭካኔ ተግባሮች ጥቂቶቹን እንመልከት። የሸፈተባቸውን ቸኮልን ለመውጋት ወደ ደንበጫ ሔደው ሳለ ቸኮል አመለጣቸው። ከአሽከሮቹም ስድስት ሰዎች ተማርከው ስለ ነበረ እነሱን በገበያ ላይ ሰቀሉዋቸው። አንደኛው ከቴዎድሮስ አሽከር ጠመንጃ ሲቀማ ተይዞ ነበርና ያንን ሰው ከመድፍ አፍ ላይ አስጠግተው አስቁመው የመድፉ ጥይት እንዲተኮስ አዘዙ። ሲተኮስም ሰውዬውን ብትንትኑን አውጥቶ ገደለው በማለት ጸሐፊ ትእዛዛቸው አለቃ ዘነበ ጽፈዋል። ከአለቃ ዘነበ መጽሐፍ የምናነበው ሌላም አለ።

ግራዝማች ዓለሜ የሸፈቱ ጊዜ አንዱ አሽከራቸው ተይዞ መጣ ከንጉሱ ችሎት በቀረበ ጊዜም ቴዎድሮስ የሞት ፍርድ ካስፈረዱበት በኋላ «......መቅደላ ወረሂመኖ ደላንቴ፥ ዳውንቴ፥ ዋደሌ ጦርህን ከዚህ ሰው ደም ያላስነካህ ጠላቴ ነህ......» ብለው በመናገራቸው ያ ሁሉ ሕዝብ በንጉሱ ትእዛዝ መሠረት ሁሉም በጦር ሲወጋው ብትንትኑ ወጥቶ ለምልክት እንኳ የሚታይ ሥጋው ከመሬት ላይ ጠፋ።

አለቃ ወልደ ማርያም እንደ ጻፉት ደግሞ ቲዝባ ከሚባለው አገር ሕዝብ መሀል ጥቂቶቹ ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርበው «ጃንሆይ ሁሉንም እንደ አባትህ እደር ብለውታል። እኛም ያባታችን ማደሪያ ሌሊት ገስግሰን በረት ከፍተን ላም ነድተን፥ ሰው ሲተኛ ግድግዳ ምሰን ያገኘነውን ወስደን እንኖራለንና ይሄው ይፈቀድልን ብለው አመለከቱ። ቴዎድሮስም «አሁን ያላችሁት ጥቂቶች ናችሁና ሁላችሁም አንድ ሁናችሁ ንገሩኝ» ብለው በቀጠሮ መለሱዋቸው። በቀጠሮው ቀን ሽማግሌና ሕፃን ሁሉ ሳይቀር ሕዝቡ በሙሉ መጣ። ቴዎድሮስም በለው ብለው ሲያዙ ወታደሩ ያን ሁሉ ሕዝብ በጦርና በጐራዴ ፈጀው። በፊት የቀረቡት ተንኮለኞች ወይም አላጋጮች ብቻ መቀጣት

ሲገባቸው ምንም የማያውቀው ባላገር ሁሉ በማስጐምጀት አሰብስበው ማስፈጀቱ መልካም ድርጊት አልነበረም።

ደጃች ተድላ ጓሉን ለመያዝ አጤ ቴዎድሮስ ገስግሰው በድንገት ደርሰው በተዋጉ ጊዜ ስምንት ሺ ሰዎችን ማረኩ። ይህን ሁሉ ምርኮኛ እንጅባራ ላይ ሰብስበው ራስኑ ሲያስቆርጡ ውለው ጊዜው ሲመሽ የተረፈው ሰው ተቆጥሮ አደረ። ሲነጋጋ ንጉሡ ተነስተው ያደሩትን ሰዎች አምጣ ብለው አስቀርበው ሁሉንም አስደብድበው ፈጁት። ያን ሁሉ ክምር ሬሳ እየተዘዋወሩ ሲያዩ ከሬሳዎቹ መሀል አንዱ አልሞተ ኖሮ ሲንፈራገጥ አዩት። ቴዎድሮስም «ሁሉንም እንዲሁ ሳትገድሉ ነው የጣላችኋቸው» ብለው ያን የሚንፈራገጠውን ራሳቸው ገድለው ሌላው ሁሉ እየታየ ያልሞተው እንዲገደል አዘዙ። ሁሉም ካለቀ በኋላ «ይህን ሁሉ ጠላቴን በጅጄ ጥሎ እንዲህ አስተኝቶ ያሳየኝ እግዚአብሔር ይመስገን» ብለው መሬት ስመው ከድንኳናቸው ገቡ። አልቃሽም

«አንጥረኛው ብዙ ከንጉሱ ቤት

ባል አልቦ አደረጉት ይህን ሁሉ ሴት» ብላ ገጠመች

በ1859 ዓ.ም የአማራ ሳይንት ሰዎች ሊከዱ ነው ብለው ስለነገሩዋቸው ቴዎድሮስ ከአማራ ሳይንት መኳንንት 400 ሰዎች አስይዘው ሁሉንም በጐራዴ አስደብድበው ፈጁዋቸው። አንድ ሰው ከዋድላ ሰዎች ጋር ቢጣላ ከቴዎድሮስ ዘንድ መጥቶ ዋድሎች ሊከድዎት ነው ብሎ ነገራቸው። ቴዎድሮስም «ለዋድላ ሰዎች ገንዘብ እሰጣለሁና ሁሉም ተሰብስቦ ይምጣ» ብለው አዋጅ አስነገሩ። ይህንንም አዋጅ የሰማው ሕዝብ እረኛ እንኳ ሳይቀር በሙሉ ተሰብስቦ መጣ። አጤ ቴዎድሮስም በራስ አዲሉ የሚመራውን የየጁን ጦር ዙሪያውን አስከብበው ስድስት መቶ ሰዎንች በጐራዴ አስደብድበው ፈጁዋችው። ይህን የግፍ አገዳደል ያዩት ራስ አዲሉ ለሊቱን አምልጠው መሸፍታቸውን አለቃ ተክለ ኢየሱስ ጽፈዋል። ከአለቃ መጽሐፍ ሌላም እናነባለን።

የሜጫ የአገው ሰዎች ሊሸፍቱ ነው ብሎ አሳባቂ ነገራቸው ቴዎድሮስም አራት መቶ የሜጫና የአገው መኳንንት ሰብስበው ዙሪያውን በሾህ አጥር አጥረው ሱሪ ብቻ እየታጠቁ ራቁታቸውን እንደ ከብት አጐሩዋቸው። እህልና ውሃም እንዳይሰጣቸው አዘዙ። በረሃብና በውሃ ጥም የሚሰቃየው ሕዝብም

ከአሥር ቀን በኋላ መሞት ጀመሩ። በ15ኛው ቀን ግን ሁሉም በረሃብና በውሃ ጥም አለቁ። ወሰን ቢሰውር የሚባሉት የሜጫ መኮንንም «ጃንሆይ አምስት መቶ ብር ልክፈልና አንድ ዋንጫ ውሃ ይስጡኝ» ቢሏቸው ቴዎድሮስ ሰምተው ዝም ብለውት አለፉ። ወሰን ቢሰውር ከሞቱም በኋላ ሚስትየዋ «ጌታ የጌታውን ልጅ ወሰን ቢሰውር

ውሃ ልግዛ ይላል በአምስት እምቶ ብር» ብላ ገጠመች።

ቴዎድሮስ ቃሮዳ ከሚባል አገር ሔዱ። ቃሮዳ በአትክልት አብቃይነቱ በተለይ በወይን ሰብል የታወቀ አገር ነበር። ቴዎድሮስ ቃሮዳ እንደ ደረሱ ሕዝቡን ሰበሰቡልኝ ብለው ሕፃናት ሳይቀሩ 1700 ሰዎች ተሰበሰቡ። ይህን ሁሉ ሰው ቤት እስከቻለ ድረስ በየቤቱ እያሰገቡ ሁሉንም በእሳት እያቃጠሉ መጨረሳቸውን አለቃ ወልደ ማርያም ፅፈዋል። ሌላም አለ።

ማህደረ ማርያም በወረዱ ጊዜ ካህናቱ ንጉሱን ለመቀበል ከለቻ ከሚባል ሜዳ ላይ ቆመው በፀናፅልና በከበሮ እያመሰገኑ አቀባበል አደረጉላቸው። ይህን ያዩት ቴዎድሮስ በልልኝ ብለው ወታደሩን አዝዘው 450 ካሃንት በጐራዴ ተደብድቦ አለቀ። ከዚያ ተመልሰው ደብረ ታቦር በወጡ ጊዜ ከርብ ጀምሮ እስከ ፍርቃ በር ወታደራቸውን አሰማርተው ሲቆፍርም በመንገድ ሲሔድም የተገኘውን ሁሉ 7700 ሰዎችን አሰበሰቡ። ይህን ሁሉ ሰብስበው በየቤቱ ውስጥ እያጐሩ የታጐሩበትን ቤት በማቃጠል ሲያስፈጁዋቸው ዋሉ። ሰው ተቃጥሎ ሲያልቅ ጊዜው ስለመሸ ተራፊውን ከሜዳ ላይ እየተጠበቀ ራቁታቸውን እንዲያድሩ አዘዙ። ለሊቱንም ዝናብ ስለዘነበ ሕፃናትና እመጫት ሳይቀሩ በዝናብ ሲደበደቡ አደሩ። በማግስቱ ቴዎድሮስ ያደረውን ሕዝብ ለማቃጠል መጥተው ሰው ከሚቃጠልበት ቤት እየተከፈለ ሲገባ አንድ የአምስት ዓመት ልጅ እናቱን እየጐተተ «ናይ እንደትናንቱ ዝናብ እንዳይመታን ቶሎ ከቤት እንግባ» እያለ ሲያለቅስ እናቱም ስታለቅስ ቴዎድሮስ አይተው «ለምን ያለቅሳሉ» ብለው ጠየቁ። ልጁ የተናገረውን ቢነግሯቸው «ፈጣሪዬ ምነው እንዲህ ታደርገኛለህ። ወይ እኔን ቶሎ ግደልና ፍጥረትህ ይረፍ በልው አልቅሰው ሊቃጠሉ የቀረቡትን ሁሉ ማሩት። ይህ ከሆነ በኋላ ጣና ሐይቅ ውስጥ ከምትገኘው ምፅርሐ ወደ ምትባለው ደሴት ሔደው በደሴቲቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች በሙሉ በቤት ውስጥ እያስገቡ ቤቱን በማቃጠል ጨረሱት።

ዶክተር ብላንክ ስለ ቴዎድሮስ የጭካኔ ተግባር ጽፎት አቶ ዳኘ ከተረጐሙት ብንመለከት «ህዳር 21 ቀን 1859 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ አጤ ቴዎድሮስ የተመረጡ ጥቂት ፈረሰኛና እግረኛ ወታደሮች አስከትለው ጐንደርንና ከጐንደር ግንብ ውስጥ እየተደበቁ የሚያስቸግሩዋቸውን ሽፍቶች ለማጥፋት መገስገስ ጀምረው አስራ ስድስት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሰማንያ ማይልስ ርቀት ያለውን ጐዳና አንድ ጊዜ እንኳ ሳይቆሙ ሲጓዙ አድረው ወገግስ ሲል የጐንደር ከተማ ከሚገኝበት ተራራ ስር ደረሱ። ምንም እንኳ በድንገት ለመድረስ አቅደው የመጡ ቢሆንም የጐንደር ነዋሪ ሕዝብ ወሬውን ሰምቶ ስለ ነበረ በመጨነቅና በመሸበር ሴቶች ወጥተው በእልልታና በደስታ ሲቀበሉዋቸው በፋሲል ግምብ ውስጥ ተሰግስጐ የነበረውም ሽፍታ ሸሽቶ ከጐንደር ወጣ። ወደዚያውም ሽፍቶችን ለማግኘት ሠራዊቱ ቤቱንና ቤተ ክርስትያኑንም ሳይቀር መበርበር መዝረፍ ያዘ። ዳሩ ግን ሽፍቶቹ ባለመገኘታቸው አስር ሺህ በላይ የሆነውን የከተማውን ነዋሪ ሕዝብ እንደ ከብት ሰብሰበው ነዱት። ከዚህም በኋላ የጥፋት ሥራቸውን ጀምረው ሕዝቡን ቤቱን ቤተ ክርስትያኑንና ቤተ መንግሥቱንም ጭምር በእሳት አቃጠሉት። ከቀሳውስት መካከል አንዳንዶች የደፈሩ አጉረምርመው የንጉሡ ነገሥቱን አፈጻጸም በግልፅ ተቃውመው ስላወገዙ ብዙ መቶ ሽማግሌ ቀሳውስት ወደ እሳቱ ተወርውረው ተቃጠሉ። የማቃጠሉ ነገር ከዚህ እብላይ ሳይቆም «እልል እያሉ የተቀበሉት ሴቶችስ የት አሉ? እነርሱ እልል ባይሉ ኖሮ ሽፍቶቹ መምጣታችንን የት ያውቁ ነበር?» በማለት ሴቶቹ ሁሉ ተይዘው እንዲመጡ አጤ ቴዎድሮስ በማዘዛቸው ሁሉም ከነ ሕይወታቸው ወደተቃጠለው ቤት እየተወረወሩ ነደዱ።.......» ብለዋል።

ይህን የመሳሰለውን የቴዎድሮስን የጭካኔ አስተዳደር ስንመለከት ቴዎድሮስ ጠላት ሳይኖርባቸው በራሳቸው ላይ ጠላት የሚፈጥሩና የሚያበዙ ሰው ነበሩ። ብዙ ፀሐፊዎች እንደ ጻፉት ቴዎድሮስ የሚፈፅሙት የጭካኔ ተግባር ሁሉ በትክክል የተፈፀመ ትክክለኛ ተግባር ይመስላቸው ነበር። ሲናገሩም «ለአገሬ እድገት ብዬ ነው» ይሉ ነበር።ወዳጃቸው ፕላውዴን እንደጻፈው «......ባንድ አጋጣሚ ንጉሡ ሲያጫውቱኝ «አንተና ቤል ብቻ ትወዱኛላችሁ። አበሾች ግን የሚገዙት በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ግን ገና ብዙ የምሠራው አለ። ዛሬ ማታ ብሞት ወይም ብመነኩስ እንንኳ ይህ የሚሆነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በዚህ ቤት ሙሉ ወርቅ ብትሰጠኝ

ጥቅሙ ምንድነው? እምመኘው ጥበብን ነው። ቅጣት የማበዛውም አገሬ በሥርዓት እንድትተዳደር ለማድረግ ነው።......ለእኔ ለአንድ ድሃ ይህን ዙፋን የሰጠኝ እግዚአብሔር ጥበብን ደግሞ ይሰጠኝ» አሉ።......» ብሏል። ቴዎድሮስ በንዴት ወይም በሌላ ጊዜ የጭካኔ ተግባራቸውን ይፈፅሙ እንጂ በጥሞናው ጊዜ ባለፈው ተግባራቸው ይፀፀቱ እንደነበር ብዙዎች ጽፈዋል። ብዙ ንፁሃን ሰዎች ፈጅተው ከጨረሱ በኋላ «እኔን ግደለኝና ሠራዊትህ ይፍረድ» እያሉ ይፀልዩ ነበር። ፕላውዲንም «......ባንድ አጋጣሚ ደግሞ እንደሚወዱኝ ነግረውኝ እግዚአብሔር ጥሩ ልብ እንዲሰጣቸው እንድፀልይላቸው ለመኑኝ.......» ይላል።

አጤ ቴዎድሮስ ሁሉን ነገር በኃይል አስፈጽማለሁ ወይም፥ በኃይል ሥራ ፀጥታውን አስከብራለሁ እያሉ ነገሩን ሁሉ አበላሹት እንጂ ለአገራቸው ፈጣን ዕድገት አሳቢና ለሥውም ታታሪ ነበሩ። በተለይም ወይዘሮ የተመኙን ቁባት ካስቀመጡ በኋላ ከወይዘሮ የተመኙ ዘንድ እየቆዩ ብዙ አረቄ መጠጣት ስላበዙ በሞቅታ በሚመጡት ፍርድና ተፈጻሚነት ጠላታቸው እየበዛ ሔደ። ይህ ባይሆንና ቴዎድሮስ ሁሉንም ነገር በጥሞና ነገር በመቻልና በማሳለፍ አገሪቱን ቢመሩ ኖሮ ለአገሪቱ የፈለጉት እድገትና ሥልጣን ሁሉ በሰላም በተከናወነላቸው ነበር።

## ፍርድ

ቴዎድሮስ ከነገሱ በኋላ በ1846 ዓ.ም ደብረ ወርቅ ላይ ሠፍረው ሳለ ሁለት ሰዎች ተከሰው ለፍርድ ቀረቡላቸው። ከሳሽ ሹምዬ ጃሎ ሲባል ተከሳሽ ደግሞ ጠቦ ወልደ ሚካኤል ይባላል። ሹምዬ ጃሎ አንድ ፈረስ ለጠቦ ሰጥቶታል። ሹምዬ ጃሎ የራስ አሊ አሽከር ነበረና ከራስ አሊ ጋር ሆኖ የወጋ ሰው ነው። አሊ ድል ሲሆኑ ሰዋቸው ሲዘረፍ ሹምዬም ልብሱን ሳይቀር ተገፎ ከባድ ድህነት ላይ ወደቀ። ሀብት ባለው ጊዜ ፈረስ ከሰጠው ወዳጁ ከጠቦ ዘንድ ሒዶ እባህክ ልብሴን የምገዛበት አንድ ብር ስጠኝ ብሎ ለመነው። ጠቦም አልሰጥህም አለው። ውለታውን ቆጥሮ ቢለምነውም እምቢ አለው።

ከዚህ በኋላ አቶ ሹምዬ የደህና ቀን ወዳጁን ጠቦን ከስሶ ከቴዎድሮስ ዘንድ አቀረበው። ከዚያም ቀርበው ሲማገቱ ሹምዬ በደህናው ቀን ፈረስ መስጠቱን

አመልክቶ አሁን ተዘርፎ ድህነት ሲጫነው ለልብስ መግዣ አንድ ብር ቢለምነው እምቢ ማለቱን አመለከተ። ጠቦ ወልደ ሚካኤልም ነገሩን ሸፈጠና ፈረስ አልሰጠኝም ብሎ ካደ። ሹምዬ ጃሎ ሲመልስ ፈረስ «ለመስጠቴ ምስክር አለኝ። ምስክሬም እግዚአብሔር ነውና እግዚአብሔርን ምስክር እጠራብሃለሁ» አለው። የዚህ ጊዜ ጠቦ ወልደ ሚካኤልን ደነገጠና «እግዚአብሔርን ምስክር ከጠራህስ አዎን ሰጥተኸኛል» ብሎ አመነ። ይህን እግዚአብሔርን መፍራቱን የሰሙት ቴዎድሮስ «እግዚአብሔር ፈርተህ እውነቱን ስለተናገርክ እኔ እከፍልልሃለሁ» ብለው ለሹምዬ ጃሎ አስር በር አንድ ፈረስ አንድ በቅሎ ሰጥተው ገላገሉዋቸው።

ቴዎድሮስ ጋይንት ላይ ሠፍረው ሳለ ወታደሮቻቸውን በባላገሩ ላይ ተሰሪ አገቡ። ባላገሩ እንዲቀልብ በየቤቱ ማስገባት ማለት ነው። ተሰሪ ከገቡት ወታደሮች መሀል አንዱ ወታደር አንዱን ባላገር ገደለው። የሟች ወገንም ከቴዎድሮስ ዘንድ መጥቶ አመለከተ። ቴዎድሮስም ወታደራቸውን ሁሉ አፈርሳታ አስቀምጠው ገዳዩን አውጣ ብለው ያዙ። ወታደሩም በመላው አድሞ ገዳዩን አላየንም እያለ በቁስ እየተገዘተ ወጣ። የሟች ገዳይ ወታደር በመጥፋቱ ቴዎድሮስ ተናደው «ወታደር ብላ ባላገር አብላ ያልሁ እኔ ነኝ። ደመኛህም እኔ ነኝና እኔን ግደል» ብለው ተነስተው ለከሳሹ ነገሩት። ከሳሹም «እኔ ንጉሥ መግደል አይቻለኝም» አለ። ቴዎድሮስም እንግዲያውስ ደም በከንቱ አይቀርም ብለው ለሟቹ ወገን የደም ዋጋ ሰጥተው ሸኙት።

አቶ ገሪማ ታፈሰ አንዳንድ የቴዎድሮስን ፍርዶች ጽፈዋል። አንድ ጊዜ ቴዎድሮስ አንድ ታማኝ ወታደራቸውን ጠርተው «በፍርቃ በር በኩል እርጉዝ ሴት እንኳ ብትሆን እንዳታልፍ ጠንክረ ጠብቅ» በልው አዘዙት። በሌላ ቀን ደግሞ ሌላውን ወታደር ጠርተው «ፈረስ እያለዋወጥህ ይህን ወረቀት የጁን ሰጥተህ በአስቸኳይ በስድስት ቀን ውስጥ ተመልሰህ እንድትመጣ ብለው ላኩት። ይህ የታዘዘው ወታደር በፈረስ እየጋለበ ሔዶ ፍርቃ በር ደረሱ። የፍርቃ በሩ ጠባቂ በፈረስ አታልፍም ብሎ ከለከለው። የተላከው ወታደር ደግሞ «ከንጉሱ ተልኬ ነው። በስድስት ቀንም የጁ ደርሼ እንድመለስ ለአስቸኳይ ጉዳይ ማህተም እንዳለህ አሳየኝና ታልፋልህ እንጂ ያለዚያ

አታልፍም» ብሎ ከለከለው የተላከው ወታደር በግዴታ አልፋለሁ ብሎ መንገድ ሲጀምር ዘበኛው ጥይት ተኩሶ ገደለው።

የሟች ወገኖች የንጉሱ መልክተኛ ወንድማቸ ንጉሱ ልከውት ሲሔድ በመገደሉ ጉዳዩን ከሰሰው ቴዎድሮስ ዘንድ አቀረቡት። ቴዎድሮስም ችሎት አስችለው ፍርድ እንዲፈረድ አደረጉ። በችሎቱ ላይ የተቀመጠው ፈራጅ ሁሉ እየተነሳ ገዳዩን «በደለኛ ነህ። እምቢ አልፋሁ ቢልህስ ለንጉስ ታሰማ ነበር እንጂ ራስህ ፈርደህ እንዴት የንጉስ መልክተኛ ትገድላለህ? አሁንም ስትሞት ይታየናል» እያሉ ፈረዱ። አንድ ፈራጅ ከተቀመጠበት ተነስተው «.......ማየት የሚገባን በመጀመሪያ ከንጉሱ የተሰጠውን ትእዛዝ ነው። አንዱን ጠርቶ በዚህ በር ያለኔ ፈቃድ ወንድ ይቅርና የፀነሰች ሴትም ብትሆን እንዳታልፍ ብሎ ማዘዝ፣ እንደገና ሁለተኛውን ወታደር ጠርቶ ቀንና ለሊት ሳታርፍ በስድስት ቀን የጁ ደርሰህ እንድትመለስ ብሎ ማዘዝ አግባብ ስላልሆነ ጥፋቱ የሚመለከተው ንጉሡ ነገሥቱን ነው። ነገር ግን ብርሃን ናቸውና ምን ይደረግ» ብለው ተቀመጡ።

አጤ ቴዎድሮስ ይህን ንግግር ሲሰሙ ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው «እንዲህ ነው መሸምገል ሁለት ጠጉር ማብቀል። በደለኛው እኔ ነኝ። ፍረዱብኝ» ብለው በተከሳሹ ወታደር ቦታ ወርደው ቆሙ። ወዲያውም ፈራጆቹ በፈረዱት ፍርድ መሠረት ለሟች ወገኖች 500 ብር የደም ዋጋ በቴዎድሮስ ላይ የተፈረደው 500 ብር አጠፌታ ዋጋ መሆኑ ነው።

አንድ ቀን ደግሞ አንድ ሌባ ከአንድ ሀብታም ቤት ሊሰርቅ ገባ። ከበረት ገብቶ ሲያንኰዳጉድ ባለቤቱ ነቃና ወጣ። ባለቤቱ ሲወጣ ሌባው ሸሸ። ሰውዬውም ሌባውን እያባረረ ሲደከመውና መድረስም ሲያቅተው «በቴዎድሮስ አምላክ ቁም» ብሎ አወገዘው። ይህ ሲሰማ ሌባው ቆሞ ጠበቀው። ሀብታሙ ሰውዬም ከሌባው ዘንድ እንደ ደረሰ በያዘው አንካሴ ሌባውን ደጋግሞ ወጋውና ጥሎት ሄደ።

ሌባው አልሞት ኖሮ እየጐተተ አርዋ ሚካኤል ደብር ገብቶ ተኛ። ሌባው ሻል ሲለው ቴዎድሮስ እንፍራንዝ መጥተው መስፈራቸውን ሲሰማ እያዘገመ ሔደ። ታሪኩን ለቴዎድሮስ ተናገረ። ቴዎድሮስንም ታሪኩን በጥሞና አዳምጠው «የለሊት ጅብ ከሰው በረት ምን ልታደርግ ገባህ? አበጀ። ደግ

አድርጓል» በልው አስደነገጡትና በሚስጥር ሀብታም ሰውዬ ተይዞ እንዲመጣ አዘዙ።

ሀብታሙ ሰውየ እንደመጣም ቴዎድሮስ በፈገግታ «እህእ አንተ ጐበዝ ይህን ሌባ እንዴት አድርገህ ወጋኸው?» ብለው እየሳቁ ጠየቁት። ሰውዬውም ደስ ብሎት «በረቴን ከፍቶ ገብቶ ከብቶቼን ሊነዳ ሲል ነቃሁና ምዝራጤን (አንካሴየን) ይዞ ልወጋው ስል ኮቴዬን ሰምቶ አብለክ አለ (ሮጠ) እኔም ተከታትዬው ብሮጥ የማልደርስበት መሆኔን ስላወቅሁ በቴዎድሮስ አምላክ ብለው መሮጡን ትቶ ቀጥ ብሎ ቆመልኝ። እንደ ደረስኩም በያዝኩት ምዝራጥ ወደወድኩት (ወጋሁት) ብሎ ተናገረ።

አጤ ቴዎድሮስ የሰውየውን ንግግር ሰምተው ሲጨርሱ «ወንጀለኛ ነህ። እንዴት በስሜ ቆሞልህ ትገድለዋለህ። መሞት ይገባህ ነበር። ግን ምሬሃለሁና ያለህን ሀብትና ንብረት በሙሉ ለወጋኸው ትለቃለህ» ብለው ፈረዱ።

አንድ ነጋዴ ወገራ ዳባ ከተባላ ውሎ ሲመለስ አንድ አይጠጣሽ ከሚባል ቦታ ሲደርስ ወንበዴ ቀማኛ ይዞ ይደበድበው ጀመር። ነጋዴውም «ገንዘቤን ውሰድና ልቀቀኝ። እየነገድሁ ልጆቼን ላሳድግበት ተወኝ» እያለ ቢለምነውም እምቢ ብሎ ገደለው። ይህን ነገር ተደብቆ ይሰማ የነበረው ሰው ሁኔታውን ለሟች ሚስት ነገራት። የሟች ሚስትም ለቴዎድሮስ አመለከተች። ወንበዴው ተይዞ ሲመጣ ቴዎድሮስ በሽማግሌ ይታይለት ብለው አዘዙ። ሽማግሌዎቹም ሰማንያ ብር ካሣና አርባ ብር የዳኝነት በወንበዴው ላይ ፈረዱበትና ውሳኔውን ለመንገር ቴዎድሮስ ዘንድ ቀረቡ። ቴዎድሮስ ውሳኔውን ሰምተው ሴትዮዋን ቢጠይቋት በውሳኔው መስማማቷን ነገረች። ቴዎድሮስም «ወይ ሴት መሆን? ገንዘቤን ውሰድና ለቀኸኝ ልጆቼን ላሳድግ ሲለው በጭካኔ ይገደለውን ሰው በገንዘብ ትታረቂያለሽ?» ብለው ሰማንያውን ብር ከራሳቸው ሰጥተው ወንበዴንው አስለቀቁት።

አንድ ገበሬ ሞተ። ሚስቱ የቤቱን ኃላፊነት ወስዳ ስታስተዳድር ያላት አንድ ወይፈን ብቻ ነበርና ወይፈኑ ሴት ፍለጋ እያእል አላርስ አለ። የመንደርዋን ሰዎች አኮላሹልኝ ብላ ብትለምንም የመንደሩ ሰዎች የወይፈኑን ቁመና አይተው ለርቢ ስለሚሆን ለጥቅማቸው ሲሉ አምቢ አሏት። ከዚህ በኋላ ያ ወይፈን እየዞረ የሠፈሩን ላሞች ሁሉ ሲያስወልድ ከረመ። አንድ ቀን

ካንድ ብሬ ጋር ሲዋጋ ያን በሬ ገፍቶ ገደል ጨመረውና በሬው ሞተ። በሬው ገደል የገባበት ሰው የወይፈኑን ጌታ ያቺን ሴት ከሰሳት። «ተዋጊ በሬን ተናካሽ ውሻህን ያዝ ይላልና የበሬዬን ዋጋ ትከፍይኛለሽ» አላት።

ሴትዮዋ በሽማግሌዎችም በዳኞችም ስለተፈረደባት ቴዎድሮስ ዘንድ ሔዳ ጮኸች። ቴዎድሮስም «ሕጉ ያዛልና መክፈሉን ትከፍያለሽ» በልው ፈረዱና «ለመሆኑ ከዚህ ወይፈንሽ የተወለዱትን ከብቶች ታውቂያቸዋለሽ?» ቢሏት አዎን አውቃቸዋለሁ ብላ መለሰች። ቴዎድሮስም አጋፋሪያቸውን ጠርተው «ንሳማ፥ እሷ የምታሳይህን ከብቶች ሁሉ እየያዝህ አንድ ለሷ፥ አንድ ለባለ ላም እያደረግህ አካፍላቸው» ብለው አዘዙ። ሴትዮዋም በአንድ ጊዜ ሀብታም ሆነች።

ከደብረ ታቦር ተነስተው ሲሔዱ ጊዜው ብርድና ንፋስ ሆኖ አላስኬድ ስላለ ጉና ከሚባለው ሠፈር ሲደርሱ ሠፈር ሆነ። ቴዎድሮስ የሚያድሩበት ቤት አልነበረምና ከድንኳን ይሻላል ተብሎ ካንድ ቄስ ቤት ገብተው አደሩ። ለሊቱን የዚያ ቄስ ቤት ትኋን ሲበላቸው አደረ። በማግስቱ ቴዎድሮስ ከውጭ ሆነው ቤቱን ጌታ ቄሱን አስጠርትወ ከአልጋህና ከመቀመጫህ በስተቀር ሌላውን ዕቃን አውጣ በልው አዘዙና ዕቃው እንደ ወጣ ቤቱ እንዲቃጠል አዘዙ። ቤቱ ሲቃጠልም እያዩ «ትኋን እንዳንገበገብሺኝ አገበገብኩሽ እያሉ ቆይተው ለቄሱ ቤት ሥሩለት ብለው አዘዙ። ወዲያውም ሠራዊታቸው ተረባርቦ በጣም ደስ የሚያሰኝ ቤት ባንድ ቀን ተሠርቶ ተሰጠውና ዕቃውን አስገባ።

አንድ ቀን ሴትዮ አርባ ክንድ ርዝመት ያለው መቀነት አሠርታ ለቴዎድሮስ ስጦታ ሰጠች። ቴዎድሮስም ስጦታውን ተቀብለው «እንዴት በአባ ክንድ መቀነት ወሰንሺኝ። እንደ ተራ ሰው ቆጥረሺኝ ነው?» ቢሏት «አይደለም ጃንሆይ። ድሃ ብሆን ነው እንጂ ለእርስዎ መቶ ክንድም አይበቃዎ» አለቻቸው የሴትዮዋን መልስ የሰሙት ቴዎድሮስ ተደስተው ሽልማት ሸልመው ሰደዷት።

ይህን ታሪክ የሰማች ሌላ ሴት ለዚያች መልከ ጥሩ ያን ያህል የሸለሙ የኔንማ ቁንጅና ሲያዩ የበለጠ ይሸለሙኛል ብላ ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርባ እጅ ነሳች። ቴዎድሮስም «ሙያሽ ምንድነው እቱ?» ብለው ጠየቋት። ሴትዮዋም «የከተማ ቅሬ (ሴተኛ አዳሪ) ነኝ እንጂ ሥራ የለኝም» ብላ መለሰች። ቴዎድሮስም «እግዚአብሔር ሁለት እጆች የፈጠረልሽ እንድትሠሪባቸው

ነበር። ለመብል ብቻ ከሆነ አንድ እጅ ይበቃሻል» ብለው አንድ እጅዋን አስቆረጧት።

የዘመኑ ዘፋኞችም

«ማረስ ይሻላል መገበር፥

እጅ እግርን ይዞ ለመኖር።

አላርስም ያሉ አለንግድ

ተመለመሉ እንደ ግንድ።» እያሉ ይዘፍኑ ነበር።

# ምዕራፍ 8
# የአረቦች ጥንስስ

ግራኝ መሀመድ በኢትዮጵያ ላይ በሽፍትነት ተነስቶ በአረቦች በተለይ በቱርኮች እርዳታ በመላ ኢትዮጵያ ከተንሰራሩ በኋላ ቱርኮች በኢትዮጵያ ዳርቻ በተለይ በምፅዋና ባካባቢዋ አገር መያዝና መስፈር ጀመሩ። የቱርኮች ኃይል በሚደክምበት ጊዜ ግብጾች እየተረከቡ በመፈራረቅ ይይዙ ጀመር።

ይህን የአረቦችን በኢትዮጵያ ዳርቻ ላይ መስፋፋት የኢትዮጵያ ነገሥታት በነገሩ ቢቆጩበትም የባህር ላይ መዋጊያ መርከብ ስለሌላቸው ብቻ መርከብ ላላቸው መንግሥታት እያመለከቱ ውጤቱን ይጠባበቁ ጀመር። የሚጠበቀው የባለ መርከብ አገር እርዳታም ውጤቱ አጥጋቢ ባይሆንም በየጊዜው የተነሱ ነገሥታትና መሳፍንት ከመለመን ያቋረጡበት ጊዜ አልነበረም። እንዲያውም ከአረቦች መስፋፋት ይልቅ ሌላ ክርስትያን የሆነ መንግሥት ቢይዘው ይመኙ እንደነበረ ለማስረጃ ያህል ከትግራዩ መስፍን (ገዢ) ከደጃዝማች ሰባጋዲስ ደብዳቤ መረዳት እንችላለን።

በ1820 ዓ.ም ግድም ዊልያም ኮፊን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ወደ አገሩ በሚመለስበት ጊዜ ለእንግሊዙ ንጉሥ ለጆርጅ 4ኛ ደጃዝማች ሰባጋዲስ አንድ ደብዳቤ ልከው ነበር። ደብዳበኢውም «.......የምፅዋን ወደብ እርስዎ

ይውሰዱና ለኛ ይሰጡናል። ባይሆንም ደግሞ በእርስዎ በንጉሥ እጅ ቢሆን ይሻለናል......» የሚሉ ቃላት ይገኙበት ነበር።

ከዚያም በፊት የትግራይ ገዥ (መስፍን) የነበሩት ራስ ወልደ ሥላሴ በ1802 ዓ.ም ግድም በሚያዝያ ወር ለእንግሊዛዊው ለሶልት ሲያጫውቱት «......በመሬት ላይ ስላለው ጉዳይ አታስቡ። ምፅዋን ስለያዙት ቱርኮች ግን አስቡበት። እንግሊዞች ምፅዋን ቢይዙና መርከቦቻቸው አካባቢውን ቢጠብቁ ከዳርቻው ወዲህ ላለው አገር እኔ ጠባቂ እሆን ነበር.......» ማለታቸውን ራሱ ሶልት ፅፎታል።

መሐምድ አሊ ግብፅን ማስተዳደር እንደ ጀመሩ በግራኝ መሀመድ ጊዜ በጀሃድ ጦርነት እስከ ሰሜን ኢትዮጵያ ድረስ በአረቦች (በእስላሞች) ተይዞ እንደ ነበረ አስታውሰው አረብን ሁሉ አጠቃልዬ እግዛለሁ በሚለው ሐሳባቸው መሠረት ኢትዮጵያንም ደርበው ለመያዝ ፈለጉ።

መሐመድ አሊ ግብፅን በገዢነት ይያዙ እንጂ በትውልድ ግብፃዊ አልነበሩም። ቱርካዊ ናቸው። መሐመድ አሊ በ1769 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ከቱርክ ወላጆቻው ቱርክ ውስጥ ተወለዱ። የቱርክ ጦር በ1799 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ግብፅ ሲገባ መሐመድ አሊ ገና የሰላሳ ዓመት ጐረምሳ ስለ ነበሩ በፈቃደኝነት ከጦሩ ጋር ዘምተው ግብፅ ምር ገቡ። ግብፅ ምድር በገቡ በአራተኛው ዓመት ማለት በ1803 ዓ.ም የግብፅን መንግሥት ያዙ። የግብፅን መንግሥት አመራር ሲይዙ በቀላል ሁኔታ አልነበረም። አስር ሺ አልባናውያን ወታደሮችና ሌሎችም ነበሩዋቸው። እነዚህንም ወታደሮች በበላይነት የሚመሩላቸው ከ95 ልጆቻቸው መሀል ከመጀመሪያ ሚስታቸው የተወለዱት ሦስቱን ልጆቻቸው ማለት ኢብራሂም፥ ትኩን፥ እስማኤል፥ የተባሉትን የጦር ትምህርት አስተምረው የወታደሩ የበላይ አድርገዋቸው ነበር።

መሐመድ አሊ ተቃዋሚዎቻችውን እያጠፉ ሥልጣን ቢይዙም ሥልጣን ከያዙም በኋላ ብዙ ተቃዋሚዎቻቸው ኃይለኞቹ ማምሉኮች ከባድ ምሽግ እየሠሩ የማይገብሩ ሆኑባቸው። ነእኝህንም ማምሉኮች በእርቅና በሰላም ለመስማማት ብለው ሰላም ከመሠረቱ በኋላ ታላቅ በዓል አዘጋጅተው 500 የማምሉክ አለቆች በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ጥሪ አደረጉ። ማምሉኮችም እውነት ሰላም የወረደ መስሏቸው 1811 ዓ.ም በዓሉን ለማክበር ተሰበሰቡ። በዓሉ

ተከብሮ ካለቀ በኋላ በትልቁ ልጃቸው በኢብራሂም የሚታዘዙትን ወታደሮች አዘው አምስት መቶዎቹን ማምሉክና በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን በጥይትና በሰይፍ አሳርደው ባንድ ቀን ሁሉንም ፈጁዋቸው። ይህ ከሆነ በኋላ በዚሁ በኢብራሂም የሚታዘዘው ወታደር እስከላይኛው አባይ ድረስ ዘምቶ የተረፉትን ማምሉኮች ሁሉ ጨረሳቸው።

ተቃዋሚዎቻቸውን በዚህ ሁኔታ ከጨረሱ በኋላ መሐመድ አሊ ታላቁን ሕልማቸውን እውን ለማድረግ አሰቡ። የመጀመሪያ አሳባቸው ቀይ ባህርን ከዳር እስከ ዳር መያዝ ነበር። ቀይ ባህር ከተያዘ የአረብን አገር በሙሉ ለማስገበርና የባህሩም መንገድ ለንግድ እስከ ሕንድና ሩቅ ምሥራቅ ድረስ እንደሚያዘልቃቸው በማሰብ ነበር። ሁለተኛው ሕልማቸው ወይም አሳባቸው በጥቁርና በነጭ አባይ (ናይል) ሸለቆ ያሉትን አገሮች በሙሉ ለመያዝ ነበር። እነኝህም አገሮች በሚያዙበት ጊዜ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ገብቶ ጣናን ለመያዝ ጐንደር መድረሻ በመተማ በኩል እንዲሆን ተወጠነ።

በዚያው ዘመን የነበረው ዋዲንግተን ያን ሐሳብ ሲተነትን «......የመሐመድ አሊ አሳብና ምኞት በናይል አካባቢ ያሉ አገሮችና ደሴቶች ሁሉ በእጁ እንዲገቡለት ነው። ከአበሻ ምድር ጀምሮ እስከ ሜዲትራኒያን ባህር ድረስ ያሉ የናይልን ውሃ የሚጠጡ ሰዎች ሁሉ የእሱ ተገዢ ሆነው እሱ ጌታቸው እንዲሆን ነው።....... በማለት ጁርናል ኦፍ ኤ ቪዚት ቱ ሰም ፓርትስ ኦፍ ኢትዮጵያ በሚል ርእስ ገልጾታል።

በዚህ ሐሳብና ውጥን መሠረት መሐመድ አሊ 3ኛ ልጃቸው እስማኤልን በ25 ዓመት ዕድሜው አባይን ለማስገበር ሾሙት። አባይ ስል የኛን ጥቁር አባይ ነው። ናይል ግን ከነጭ አባይ እስከ ሜዲትራኒያን ባህር ድረስ ያለው የኛንም አባይ ጨምሮ ነው።

የአባይ ዳርቻን እየያዘ ኢትዮጵያ ድረስ ለማስገበር የታዘዘው እስማኤል ወታደሮቹን በሚገባ አደራጀ። የቱርክና የአልባኒያ ተወላጆች የሆኑት ወታደሮቹ ቀይ ወይም አረንጓዴ ባርኔጣ ያደርጉና ወርቃማ ከፈፍ ያለው አጭር ኮት ይደርባሉ። በወገባእው ላይ ነጭ ሐር ታጥቀው ቁምጣ ሱሪ የሚለብሱ ነበሩ። ጫማቸው ቀይ ነበር። እነኝህንም ወታደሮች እያንዳንዳቸውን አንድ ባርያና አንድ አህያ እንዲከተላቸው ይደረጋል። ሌሎቹ ወታደሮቹም ቢሆን እንደ ነኝህ በጣም ያጌጡ አይሁኑ እንጂ አለባበሳቸው አንድ ዓይነት ነበር።

ከእነኝህ ከታወቁት ወታደሮች ሌላ ለዝርፊያና ለምርኮ ሲል ብቻ የሚዘምተው ሲቪል ሕዝብ በጣም የበዛ ነበር።

እስማኤል ጦሩን አዘጋጅቶ ለመዝመት በሚነሳበት ጊዜ አባቱ መሐመድ አሊ ጦሩን እንዲያሰናብቱለት አደረገ። መሐመድ አሊም ጦሩን በሚያሰናብቱበት ጊዜ አንድ የሰው ጆሮ ላመጣ ወታደርም ሆነ ሲቪል የዘመኑን ገንዘብ 50 ፒያስተር እሰጣለሁ ብለው አወጁ። እስማኤል መሐመድም ጦሩን እየመራ ወደ ላይኛው አባይ ወደ ሱዳን ጉዞውን ጀመረ። አቅም ያላቸው የሱዳን ባላባቶችም መጠነኛ ቁርቋሶ እያደረጉና እያለቁ የእስማኤል ወታደር ተጓዘ ወደ ኢትዮጵያ ጠረፍ በሚቃረብበት ጊዜ ግን ሻንያቸው ያላቸውን ጦር አዘጋጅተው በሴትዋ ሜህራ አቡድ መሪነት ተሰልፈው ጠበቁ። በ1822 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የእስማኤል ወታደሮች ቆርቲ (ኮርቲ) ከሚባል ቦታ ሲደርሱ ሜህራ ከግመልዋ ላይ ሆና ጦርዋ እንዲገጥም አዝዛ ታላቅ ጦርነት ተደረገ። 800 ያህል የጥቁር ሬሳዎች አንዳቸውም ጆሮ አልነበራቸው። ከቆርቲ ጦርነት በኋላ በነበረው ዘረፋና ግድያ ሶስት ሺ ጆሮዎች ባንድነት ሆነው ወደ ካይሮ ተላኩ። አምሳ ፒያስተር ለማግኘት ጆሮዎቹ የሚቆረጡት ከሞተ ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን በሕይወት ካለም ሰው ላይ ነበር።

የእስማኤል ወታደሮች በሱዳን ውስጥ ታላቅ ድል ካገኙ በኋላ የሱዳኑ ንጉሥ (ሜክ) ኒምር የመጣበት ጠላት እንደማይበገር አውቆ ሰላም እንዲወርድ በእርቅ ለመግባት ተስማማ። ይሄው የኒምር አሳብ ወደ ካይሮ ተልኮ ከመሐመድ አሊ የመጣው መልስ 30.000 ጥሬ ብር ስድስት ሺ ባርያዎች በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ እንዲገብር ካልገበረ ግን ጦርነቱ እንዲቀጥል የሚል ሆነ።

ኒምር ሥልታን የያዘው በ1806 ዓ.ም ግድም ነው። ቁመቱ 6 ጫማ ርዝማኔ ያለው ሲሆን የላይ ልብሱ የነብር ቆዳ ነው። ይህም የአባይ ዳርቻ ሹማምንት ምልክት ነበር። ወደ ውጭ ሲሔድም ታላቅ ዛንጥላ ተይዞላቸው ነው። ጠባቂዎቹም ሶስት መቶ ፈረሰኞች ይሁኑ እንጂ ያላቸው ጠመንጃ ከሃያ አይበልጥም። ከሻንያዎች ጋር ሁልጊዜ በውጊያ ስለሚኖር የእስማኤል ጦር ጉረቤቶቹን ሻንያዎች እያረደ ሲጨርስ ኒምር በሱ የማይደርስ መስሎት ሳያግዝ ቀረ። ሻንያዎች ድል ሲሆኑ ሻንያዎችን የደበደበው በትር ወደሱ ሲዞር ከሻንያዎች ባገኘው ትምህርት ልገብር አለ።

ኒምር ከካይሮ ከመሐመድ አሊ የመጣውን የግብር ጥያቄ ለሕዝቤ ላስረዳ ብሎ በእስማኤል እጅ ከወጣ በኋላ ሕዝቡን ሰብስቦ አማከረ። ሕዝቡም እንኳን ባንድ ቀንና ለሊት ባመትም ቢሆን ያን ያህል ግብር ለመስጠት ባለመቻሉ ከመገበር ይልቅ ተዋግቶ መሞቱን መረጠ። ሌሊት ሲሆንም ሕዝቡ እስማኤል የሠፈረበትን ሠፈር በእሳት አቃጠለው። እስማኤልም ከዚያ ለመውጣት ሞክሮ ሳይሆንለት ቀርቶ ሞተ። የአሁኑ ትረካ በመተማ በኩል ስላለው ብቻ ነው።

እስማኤል እንደ ሞተ በቦታው መሐመድ ቤይ ተተክቶ ሱዳኖችን ፈጁዋቸው። በተለይ የቁም ሥቃይ ለማሳየት በማለት ወንዱን እየሰለቡ ሴቶቹን ጡታቸውን እየቆረጡ ለቀቁዋቸው። ኒምርም ሸሽቶ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ገብቶ በተራሮች ውስጥ ተደበቀ። እነ መሐመድ ቤይም ወደ ፊት እየገፉ መተማ ድረስ መትተው ኒምርን ቢያጡ መተማ ከተማን አቃጠሉት። በጠቅላላው አምስት ሺ ሱዳኖችንም ገደሉ።

ይሄው ከግብፅ የመጣው ጦር የኢትዮጵያን ወሰን አልፎ ገባ። ለአገባባቸው ሰበብ ያገኙት ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ የተደበቀው ኒምርን እንይዛለን በማለት ነው። በግብፅም ጦር ከኢትዮጵያ ምድር ገብቶ ማስገበር ጀመረ። ይህን ነገር ገዳች ውቤ እንደሰሙ የግብፅን ጦር ከኢትዮጵያ ምድር ለማስወጣት አስበው ትግራይ ውስጥ በተነሳባቸው የተቃዋሚዎቻችው የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት ሳይዘምቱ ቀሩ። ኒምር ግን ወልቃይት ሆኖ የተቻለውን ያህል የግብፅን ጦር አላስገባ ብሎ ሲከላከል ቆየ። በኋላም የደምቢያ ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ክንፉ ደርሰውለት የግብፅን ጦር ከወሰን አርቀው አባረሩ።

ደጃዝማች ክንፉ ይህን ወሰን አልፎ ገብቶ የነበረውን ጦር አባርረው ወደ ግዛታቸው ሲመለሱ በሱዳኑ ቅኝ ገዥ በአህመድ ቃሲምና ከካይሮ በመጣለት ረዳቱ በረሺድ የሚመራ ጦር ባንድነት መጥቶ በኢትዮጵያ ግዛት በመግባት እየዘረፉና እያስገበሩ ስላስቸገሩ ደጃዝማች ክንፉ እንደ ገና በ1829 ዓ.ም በሚያዝያ ማለቂያ ዘምተው ዋድ ቃልተቡ በተባለ ሥፍራ ጦርነት ገጥመው ታላቅና ዝነኛ ያደረጋቸውን ድል አገኙ።

የደጃዝማች ክንፉ ድል ማድረግ በካይሮ ከተማ በተሰማ ጊዜ አሊ ቀርሽድ ፓሻ የሱዳን ገዥ እንዲሆን ተሹሞ ጥሩ መሣሪያ የያዘ አዲስ ጦር ይዞ በግስጋሴ

ድል ስለሆነ ሠራዊቱ ደርሰለት። ይህም አዲስ ጦር መተማ አካባቢ ደርሶ ወሰን ሳያልፍ ሠፈረ። ደጃች ክፍኑም እንደገና ጦራቸውን ይዘው ለመዝመት ሲሉ ወሬው ከግብጾች ዘንድ ስለ ደረሰ በአስቸኳይ ኢትዮጵያን ለመውረር ያለመምጣታቸውንና አሁንም የሰፈሩት ወሰን ሲያልፍ መሆኑን የሚነግር መልክተኛ ልከው ደጃች ክንፉን ከመዝመት አስቀሩዋቸው። ከዚህ የተረፈው በቴዎድሮስ ትረካ ውስጥ አለ። ትንሽ ለመጨመር ቢያስፈልገው አጤ ዮሐንስ ሕይወታቸውን እስከ መሰዋት የደረሱቱ በዚሁ ወሰን በኩል ከመጣው የአረብ ጦር ጋር ሲዋጉ ነው።

# ምዕራፍ ፱

# ልማት

አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው የነበሩትን ፈረንጆች አሰባስበው ለኢትዮጵያ እድገት የሚሆን ተግባር በውዴታ ብቻ ሳይሆን በግዴታም ጭምር እንዲሠሩ አደረጉ። እነኝህም ሚስዮናውያን እና ለአገር ጉብኝት የመጡት ፈረንጆች በእጅ ጥበብ በኩል እምብዛም እውቀት ስላልነበራቸው የቴዎድሮስን ፍላጎት እንደምኞታቸው ሊፈፅሙላቸው አልቻሉም።

ከሚስዮናውያን አብዛኞቹ ደጃች ውቤ ትግራይን በሚገዙበትና በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ናቸው። የፕሮቴስታንት ጳጳስ ጐባት በ1823 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የአገሪቱን ሁኔታ ካጠኑ በኋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው ሔዱ። በ1827 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ሲመጡ ሶስት የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ማለት ክራፍ ኢሰንበርግ እና ብሎም ሐርት የተባሉትን ይዘው ገቡ። እነኝህንም ሚስዮናውያን ከቀሳውስት ጋር በተነሳው ያለመግባባትና ጭቅጭቅ ምክንያት ትግራይን ለቀው እንዲወጡ ታዘዙ። ሔንሪ ዱፍተን በደቡብ ኢትዮጵያ ያሉትን ሕዝቦች ወንጌል ለማስተማር የመጣ ነበር።

ሚስዮናውያኖቹ ከትግራይ ወጥተው ወደ ሸዋና ጐንደር በሔዱበት ጊዜ ማለት በ1830 ዓ.ም የታወቀው የጀርመን የተፈጥሮ ተመራማሪ ሩፔል

ከፍራንክፈርት ተነስቶ ኢትዮጵያ ገባ። ከሩፔልም ቀጥሎ ጀርመናዊው የእፅዋት ተመራማሪ ዶክተር ሼምተር ለእፅዋት ምርመራ ጥናት ተግባር ወደ ኢትዮጵያ መጣ። ከ1831 – 1835 ባለው ዘመንም ለፈብሬዠር እና ፔቲ የተባሉት ሳይንቲስቶች ለሳይንስ ምርመራና ጥናት ተግባር ኢትዮጵያ ገቡ።

ፈረንሳዊዎቹ ኢንጅነሮች ፌሬ እና ጋሊነየር በምፅዋ በኩል አድርገው በትግራይ አልፈው ጐንደር ገቡ። ማንስፊልድ ፓርኪንስ ከ1835 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1840 ዓ.ም ትግራይን እየጐበኘ የኢትዮጵያን ታሪክ ሲያጠና የቆየ ሰው ነበር። አጤ ቴዎድሮስ እነኝህንና ሌሎችንም አሰባስበው ያለ እውቀታቸውን የእጅ ሥራ እንዲሠሩ አዘዙዋቸው። እነኝህ ሰዎች ግን ጥቃቅን ነገሮችን ከመሥራት በስተቀር የቴዎድሮስን ሐሳብ ሊያሟሉ አልቻሉም።


ከሚስዮናውያኖቹ አንዱ ፍላድ የሚባለው ታሞ ስለነበረ ወደ ውጭ አገር ሔዶ ታክሞ እንዲመለስ ቴዎድሮስን ፈቃድ ጠይቀ። ፍላድ ለቴዎድሮስ ወዳጅ ነበርና ሕመሙን ታክሞ በሚመለስበት ጊዜ የጅ ሥራ አዋቂዎች ይዞላችወ እንዲመጣ ቴዎድሮስ ለመኑት። ፍላድም ፈቃደኛ ሆኖ በመገኘቱ አጤ ቴዎድሮስ አድራሻ የሌለው ለፍላድ የምስክር ወረቀት የሚሆን የእሳቸው መልክተኛ መሆኑንና ጠቢባን እንዲያመጣላቸው መታዘዙን የሚገልጽ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ሰጡት።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩
አምላክ። የእግዚአብሔር ፍጡር ባርያው
የዳዊት የሰሎሞን ልጅ። ንጉሠ ነገሥት
ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ አቶ ፍላጥን በአይሮጳ
ልኬ ሰድጄዋለሁ። ብልህ ሠራተኛ
ፈልጌአለሁ። ከኔ የሚመጣን ሠራተኛ ሁሉ
በደስታ እቀበለዋለሁ ቢኖርም ደስ አሰኝቸ
አኖረዋለሁ። ብልሀቱንም አስተምሮ ወደ አገሬ
እመልሰሳለሁ ቢል ደመወዙን ሠጥቼ። ደስ
አሰኝቸ ሸኝቼ እሰደዋለሁ። በእግዚአብሔር
ኃይል የእግዚአብሔር እምነት ይሁንብኝ
ክርስቶ በተወለደ በሸህ ፰፻፶፰ ዘመን በዘመነ
ማርቆስ በሚዝያ በ፲ ቀን ዘጊ ላይ ተጣፈ።



ፍላድ ይህን ደብዳቤ ይዞ ወደ ኤሮፓ ሔደ። ሕመሙን ድኖ ሚስት አግብቶ በዓመት ከመንፈቁ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ዎድሜየር ቤንደር ኪንስሌ ሚየር ሳልሙለር እና እስኮርዝ ከነልጁ ሆነው አብረውት መጡ። ዎልድማየር ለወንጌል ስብከት ሥራ ከጳጳስ ጐባት የተላከ ቢሆንም ሌሎች ግን የእጅ ሥራ ሞያ የነበራቸው ነበሩ። ሆኖም በጉዞ ላይ እንዳሉ የእስኮርዝ ልጅ ሞተ። ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ወጭኔ ላይ ሲደርሱ መንገደኞቹ በሙሉ ታመሙ። ከጥቂት ቀናት በኋላ እስኮርዝ በያዘው ሐመም ምክንያት ሲሞት ሌሎቹ ድነው በሰላሳ ሁለት ግመሎች የተጫነውን ጓዛቸውን ይዘው ጐንደር ገቡ። ከግመሎቹ ጭነት አብዛኛው መጽሐፍ ቅዱስ ነበር።

በጆን ቤል አማካይነት ከቴዎድሮስ ጋር ተገናኙ። አጤ ቴዎድሮስም በደስታን በአክብሮት ተቀበሉዋቸው። በመንገድ ስለሞቱትስ ሰዎችም በጣም ማዘናቸውን ገልፀው «እግዚአብሔር የኔን ኃጢአት ቆጥሮ ነው እነዚህን ሰዎች ከኔ የወሰዳቸው» ማለታቸውን ዎልድሜየር ጹፏል። ከዚያም የእያንዳንዳቸውን ችሎታ ጠይቀው በችሎታቸው መሠረት እንዲሠሩ አዘዙ። ቴዎድሮስ የሚመጣውን የውጭ አገር ሰው ሁሉ ሲገናኙ ዋናው ጥያቄያቸው «ምን ሥራ ታውቃለህ? » ማለት ነበር። ምንም አላውቅም ካለ ዳግመኛ አያነጋግሩትም። ፈጥኖም ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ያዛሉ። ለምሳሌ ኸንሪ ዱፍተን የመጣ ጊዜ ከቴዎድሮስ ጋር ተገናኘው ራሱ ኸንሪ ዱፍተን እንደጻፈው «የባሩድንና የእርሳሱን አሠራር ትችላለህ? » ቢሉት «የለም። እንዲህ በማለቴ አዝናለሁ እንጂ አላውቅበትም። በአገሬም ቢሆን በጉምሩክ ጽሐፊነት እሠራ የነበርኩኝ ነኝ «አላቸው። አጤ ቴዎድሮስም «ይሄም መልካም ነው። አንድ የእንግሊዝኛ ፀሐፊ እንዲኖረኝ ብዙ ጊዜ አስብ ነበር። አሁን አንተ በዚያ በኩል ታገለግለኛለህ» አሉት።




# የጋፋት መንደር (ደብረታቦር)

ቴዎድሮስ የሰበሰቡዋቸውን ፈረንጆች መቅደላ አስቀመጡዋቸው። በዚያም ያለው ብርድና ሌላውም ሁኔታ ለፈረንጆች አልመች ስላለ ጆን ቤል ከቴዎድሮስ አስፈቅዶላቸው ከመቅደላ ተራራ ላይ እንዲወርዱና ጋፋት እንዲኖሩ አስደረገ። ጆን ቤል በዚህ ልመና የገባው ከኢትዮጵያዊነት የወለዳት ሴት ልጁ ዎልድ ሜየርን አግብታ ከባሏ ጋር መቅደላ ስለነበረች በሱማ ውትወታ ጭምር ነው። ከቴዎድሮስ ፈቃድ እንደተገኘም በሰኔ ወር 1852 ዓ.ም ፍላድ ከነሚስቱ ዎድሜየር ከነሚስቱ ቤንደር ሳልሙለር ኰንዝላን ሜየር ከነሚስቱ (ቴዎድሮስ በትርጉሙ ከንቲባ ይሉት ነበር) ወደ ጋፋት ሔዱ። በዝናብና በጭቃው ምክንያት እየተጉላሉ ከሰባት ቀን በኋላ ጋፋት ደረሱ። ከዚያ በህብረት እየሆኑ 12 ትናንሽ ቤቶች ሠሩ። በህብረት ሥራውም አንዱን ቤት ሠርተው የሚጨርሱት በአምስት ቀን ነበር። በዚህ ዓይነት የህብረት አሠራር እያንዳንዳቸው ሁለት ጐጆ አገኙ። አንዱ ቤት የመኝታና እልፍኝ (ሳሎን) ሲሆን አንደኛው ማድቤት ነበር። ጋፋትም የኤሮፓውያን ሠፈር ሆነ።

አንድ ቀን ንጉሡ ውልድሜየርን (እናንተ የኤውሮፓ ሰዎች በጣም ብልሆች ናችሁ። ግን ችሎታችሁን ደብቃችኋል። አሁን በጣም ትልቅ የሆነ መድፍ እንድትሠሩልኝ እፈልጋለሁ። መሥራቱን አናውቅበትም ብትሉ ሁላችሁም ዋሾዎች መሆናችሁን እረዳለሁ። እነኝያን ያናደዱኝን ምን እንዳደረግኋቸውም ታውቃለህ» ብለው በድንገት ማዘዛቸውን ራሱ ዎልድሜየር ጽፎታል።

ዎልድሜየር ስለ ራሱ አስተሳሰብ ሲጽፍ «አናውቅበትም ብል ሁላችንንም ይገድሉናል። እናውቅበታለን እሺ እንሠራለን ብልም ካልሠራን ያው መገደላችን ነው ብዬ ጥቂት አሰብኩና ለመሥራት የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ እንሞክራለን አልኳቸው» ብሏል ቴዎድሮስ በዎድልሜየር አመላለስ ተደሰቱ። ሥራው እንዲጀመርም አዘዙ። አንዳንድ ሰዎች እየመጡ «ንጉሱ መድፉ ከተሠራ በኋላ እነኚህን ባሪያዎች ደብረ ታቦር ተራራ ላይ እገላቸዋለሁ ሲሉ ሰማን» ሰማን እያሉ ለፈረንጆቹ ይነግሩዋቸዋል። ፈረንጆቹም ንጉሡ ምን ዓይነት ተለዋዋጭ ጠባይ እንዳላቸው ያውቃሉ። ከፈረንጆቹ ጋር ተማሪዎችን ያስተምሩ የነበሩትን ደብተራ ሣህሉን ያለ ምንም ጥፋትና ጥየቃ ጠርተው እጅና እግራቸውን ቆርጠው ጥለዋቸዋል ይህ ከፈረንጆቹ አእምሮ አልጠፋም። የፈረንጆቹንም አሽከሮች እያስጠሩ አስገደሉዋቸው። አስረዋቸዋልም። ይህን ሁሉ የሚያውቁት ፈረንጆች ሰዎቹ እንደነገሩዋቸው መድፉ ከተሠራ በኋላ ይገድሉናል ብለው ሲሰጉም ባይሠራም ደግሞ ያው መገደላቸው ስለሆነ ሥራውን ሞክረው የሚመጣውን መጠባበቅ እንደሚሻል ወሰኑ። በውሳኔውያቸው መሠረትም የመድፉን ሞዴል በወረቀት ላይ ሠርተው ዎልድ ሜየር ለቴዎድሮስ አቀረበ። ንጉሱም ስዕሉን አይተው ከተስማሙ በኋላ በአስቸኳይ እንዲሠራ አዘዙ። የጉልበቱን ሥራ የሚረዱዋቸውም በሺ የሚቆጠሩ ሰዎንች ሰጡዋቸው።

ኸንሪ ዱፍተን በመጽሐፉ ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልፅ እንዲህ ይላል። ……ለዚህ ለመድፉ ሥራ ምንም ዓይነት ችሎታ ቀርቶ አሳብም የሌላቸው ስለ ነበረ…… ከንጉሱ ዘንድ ቀርበው መድፍ መሥራት ቀርቶ ሁኔታውን እንደማያውቁ አስረዱ። በእንግሊዝ በጀመርን፥ ወይም በፈረንሳይ አገር በፋብሪካ ስለሚሠራ በንግድ ልውውጥ ማስመጣት ስለሚቻል በዚያ በኩል እጠያይቀው ለማስፈፀም እንደሚችሉ ነገርናቸው። ንጉሱ በዚህ መልስ

አልተደሰቱም። ምኞታቸው በአገራቸው ውስጥ መሥራት እንደሚቻልና ከሌላ ጥገኝነት ለመውጣት መሆኑን ተናገሩ። ኤውሮፓዉያኖቹ እያቅማሙ ስላስቸገሩ የኤሮፓውያኖቹን አሽከሮች በሙሉ ሰብስበው በሰንሰለት አሠሩዋቸው። ይህም ጌቶቻቸው የንጉሱን ምኞች እስከፈፀሙ ድረስ መሆኑ ተነገሯቸው።

«......ከሁሉም የተሻለ እውቀት ያለው ሞርዝ ነው። የብረት ማቅለጫውም ምድጃ ከሸክላ እንዲሠራ ተወሰነ።......ከዚያ ስለሚቀጥለው ሥራ እውቀት የላቸውም ነበርና እየተሰበሰቡ ራሳቸውን ገጥመው ከየመጽሐፉ መረጃ ይፈልጉ ጀመር።.......በአሸዋ በተደባለቀ አፈር ሸክላ (ጡብ) ሠርተው ምድጃውን ካበጁ በኋላ አፈር ለማቅለጥ ቢማከሩ ብረቱ ቢቀልጥም አልወርድ አለ። አሁን የቀራቸው ዕድል እንደገና በሌላ ዘዴ መሞከር ነው። በየባላገሩ እየዞሩ ለሸክላ መሥሪያ የሚሆን ሸክላ እንደገና ምድጃው ተሠራ። አሁን ከማቅለጫው ብረቱ እየቀለጠ ይወርድ ጀመር። አሁን ሁሉም ተደሰቱ። ንጉሱም እየተመላለሱ በማየት ውጤቱን ይጠባበቁ ነበርና ከዚያ ወዲያ ልጆቼ እያሉ ይጠሩዋቸው ጀመር።.......» ይላል ሞርዝ በፊት የራሽያ ወታደር የነበረና በኋላም የፖላንድ ወታደር የነበረ ነው። ወደ ኢትዮጵያም የመጣው ለጉብኝት አገር ለማየት ነበረ።

ምንም እንኳን ኸንሪ ዱፍተን እንደገለፀው በብረቱ መቅለጥ ምክንያት ገና በውጥኑ ቴዎድሮስ ቢደሰቱም በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ ጦር እስረኞቹን ለማስለቀቅ ወደ ኢትዮጵያ ሊመጣ ነው እየተባለ በሰፊው ይወራ ነበርና ቴዎድሮስ እየተበሳጩ ብዙ ሰዎችን ይገድሉ ጀመር። ይህን የግድያ ብዛት ያዩት ፈረንጆችም በፍርሃት ሥራቸውን ያጣድፉ ጀመር። ቴዎድሮስም በየቀኑ እየተመላለሱ የምድጃዎቹን የብረት ማቅለጥ ሥራ ይመለከታሉ ይቆጣጠራሉም። አለቃ ተክለ ጊዮርጊስ እንደጻፉት «.......መድፉ የተሠራው ከጐንደር በተዘረፈው ንዋየ ቅድሳት ነቅኅ ባለው መስቀልና ቃጭል፤ በሰንና በብረት ነሐስ ነው.......» ይላሉ።

ብረቱ በብዛት ቀልጦ ከመጨረሻው ደረጃ በደረሰበት ጊዜ ቴዎድሮስ መጥተው ከጐልቱ ምድጃዎች መሀል ከቆሙት ፈረንጆች አጠገብ ሆነው የዎልድሜየርን እጅ ያዙና «አሁን ምን እንደ ሚደረግ ንገረኝ። ትእዛዝ እንደጥላችሁ» አሉ። ዎልድሜየር ራሱ እንደጻፈው ንጉሡ በድንገት እንጄን

ሲይዙት በጣም መደንገጡን ገልጿል። ከምድጃው ይጨምሩኛል ብሎ አስቦም ነበር። በዚያን ጊዜ ደግሞ ዎልድሜየር ሥራ ባይሳካም «......ብረቱን ካቀለጡት ምድጃዎች ውስጥ ይጨምሩናል.......» እያለ ያስብ ነበር።

ብረቱ ደህና ሆኖ መቅለጡን ያየው ዎልድሜየር ወደ ቴዎድሮስ ጠጋ ብሎ የምድጃዎቹ እንዲከፈቱ እንዲያዙ ነገራቸው። በቴዎድሮስ ትእዛዝ ሲከፈትም የቀለተው የብረት ወንዝ ሃያ ደቂቃ ያህል ከወረደ በኋላ የሞዴል ጉዳጓድ ሞላ። ንጉሱም ተደስተው የመዱን ስም ሰባስቶፖል ብለው ሰየሙት። ብረቱ ቀልጦ የገባበት ሞዴል ቦታ ከሶስት ቀን በኋላ ሲከፈት ጥሩ ፎርም ይዞ ተገኘ።

ይህ መድፍ ተሠርቶ ካለቀ በኋላ ስላለው ሁኔታ ዎልድሜየር በጻፈው መጽሐፍ እንዲህ ይላል። «.......ሥርተን እንደጨረስን አንዱ ሹማቸው «ጃንሆይ አሁን የምንፈልገውን ሁሉ አገኘን እርስዎም ትልቅ ታሪክ መሠረቱ። እንዲህ ያለ ነገር ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ አልተሠራም። ለመሥራት የበቃው በእርስዎ ዘመነ መንግሥት ነው። ከእንዲህ ወዲያ ከእነኝህ አህዮች የምንፈልገው የለም አላቸው።.......» ይላል የሰውየው አስተሳሰብ ፈረንጆቹን ለማስገደል ነበር። ቴዎድሮስ ግን ዎልድሜየር እንደጻፈው «.......ይቆዩ። በፊት ለመድፉ መሔጃ ጋሪ ይሥሩ» አሉ። በመድፉ ሥራ ላይ ለተካፈሉት ኤሮፓውያንም የክብር ቀሚስ በወርቅና በብር ዕቃ ያጤጠ ፈረስና በቅሎ ሸለሙዋቸው። ለእያንዳንዳቸውም አንዳንድ ሺህ ብር ሰጡዋቸው። የመጡበትንም የሚስዮን ሥራ እንዲሠሩና እንዲያስተምሩ እየተሰበሰቡም እንዲፀልዩ ፈቀዱላቸው።

ቴዎድሮስ ፈረንጆቹን በሽልማት ካስደስቱ በኋላ ለመድፉም ሆነ ለሌላ ዕቃ ማጓጓዣ የሚሆን ጋሪ እንዲሠሩ ጠየቁዋቸው። እነሱም ተረባርበው አስራ አራት ጋሪዎችን ሠሩ። የጋሪዎቹን ሥራ ከጨረሱ በኋላ ቴዎድሮስን ወደ መጥፎ ተግባር መሚመሩዋቸው እወደድ ባይ ሰዎች አንዱ ቀርቦ «ከእንግዲህ እይምንፈልገው ነገር የለምና እነኝህ ነጭ አህዮች ይገደሉ» ብሎ እንደገና ቢያስታውሳቸው «ልጅ። መድፉ የሚሔድበትን መንገድ ማን ሊያሠራው ነው?» ብለው መለሱለት።

ቴዎድሮስ መድፉ ተተኩሶ ምን ያህል ርቀት ለመምታት እንደ ሚችል ለማየት ፈለጉ። መድፉና ጥይቱ በሚሞከርበት ቀን ቴዎድሮስ ወደ ጋፋት

መጡ። ከደብረ ታቦር ያለው የመንገ ርቀት አምስት ኪሎ ማየት ያህል ይሆናል። ስለመድፉ አተኳኮስ ሁኔታ ዱፍተን ሲናገር «.......እኛም ሚስተር ሳልሙለር ግቢ ሆነና ተእቅበልናቸው። ግቢው አርቆ ለማየትም አመቺ ነእብር። ምንጣፍ ወጥቶ ተነጠፈና ንጉሠ ነገሥቱ ተቀመጡ። ሙሴ ሌዠን አጠገባቸው እንዲቀመጥ ፈቀዱለት ሌሎቻችንም በያገኘንበት ቦታ ተቀመጥን። ......ይህ ጥይት በተተኮሰበት ጊዜ ንጉሡ በአሳብ ተመስጠው ነበር። ራሳቸውንም ደፍተው ከማንም ጋር አይነጋገሩም።......እስተናካቴውም ከንፈራቸው ከማንም እንኳ ሲከፈት አላየሁም።.....ሁኔታቸው ተኩሰው እስቲሳካ ድረስ አልተለወጡም። ከተተኮሰ በኋላ ዞሪያቸውን ተመለከቱ። አጠገባቸው በተቀመጠውም ላይ ዓይናቸው ፈዝዞ ቀረ። ኤሮፓውያኖቹም ፈዘዙ። ንጉሱም ከዚህ የበለጠ ጥይት እንዲሠራላቸው ጠይቀው የተሻለ ትልቅ መሥሪያ ቤት እንደ ሚሠራና የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ ሁሉ እንደሚቀርብላቸው ነገሩዋቸው። ይህ ሁኔታ በሚካሄድበት ጊዜ ቴዎድሮስ ከምንጣፉ ላይ ካጠገባቸው ከእሳቸውና ከሙሴ ሌዠን መሀል ከተቀመጠው ከሙሴ ቡርጋርድ ልጅ ጋር ይጫወቱ ነበር። ይህም እንግዳ ነገር ነበር። .......የዚህ ጦረኛ ሰው ክንድ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን የገደለ አስር ሺህ ሰዎችን ያህል ገደለ የጨመረ ክንድ ካንድ ትንሽ የነጭ ልጅ ጋር ሲጫወት ማየት ድንቅ ነገር ነው.......» ብሏል።


አለቃ ወልደ ማርያም እንደጻፉት ደግሞ «.......በተጨረሰም ጊዜ ንጉሱ ሰሪዎቹ እነዎልድሜየርን ተኩሱትና ድምፁን ልስማው የአረሩንም መንገድ ልየው ቢሉ እነዚያም በተንኮል ጥበብ ሲያታልሉ አሁን ብተኩሰ በከተማ ሀገር መካከል የድምፁ ኃይል የቀረበች እርጉዝ ያስወርዳል። የደከመ በሽተኛ ይገድላል እያሉ እውነት አስመስለው ሳይተኮስ ቀርቶ.......ከደብረ ታቦር ተነስቶ በሰባት ወር በብዙ ድካም ሰውም እየተሞተበት እስከ መቅደላ ደረሰ ይላሉ።

እዚህ ላይ ዱፍተን ተተኩሶ መልካም ውጤት አሳየ ሲል አለቃ ወልደ ማርያም ደግሞ የሙከራው ተኩስ ያለመተኮሱን ይገልጻሉ። ግን ማንኛውንም ገማች እንደሚገምተው ቴዎድሮስ ያንን ያህል በጉጉት የጠበቁት ለአገሬ ትልቅ ሥራ እሰራላታለሁ ብለው ያስቡለትና ያሠሩት መድፍ ሥራው ካለቀ በኋላ ሳይሞከር ቀረ ብሎ ለመገመት አስቸጋሪ ነው። ቴዎድሮስን የመሰለ ሰው ቀርቶ

ሌላውም ቢሆን ያን የመሰለ ሥራ አሠርቶ ለእርጉዝና ለበሽተኛ አስቦ አይሞከር የሚል የለም። ዶክተር ብላንክ እንደጻፈውም «......በሚገባ በመተኮሱ አጤ ቴዎድሮስ በጣም ተደስተው ለሠራተኞቹ የሚያስደስት ሽልማት ስጦታ አድርገው መድፉን ከእሳቸው ጋር ይዘው ለመሔድ መሰናዳት ጀመሩ.......» ይላል። ይህም አስተማማኝ የሆነ ምስክርነት ነው። ምክንያቱም የእንግሊዝ ጦር መጣ እየተባለ በሚወራበት ጊዜ ቴዎድሮስ ያን መድፍ ሲያስሞክሩ የእንግሊዝን ጦር ሊገጥሙበት ወደ መቅደላ አፋፍ በብዙ ችግር አያስግዙትም ነበር። ተተኩሶ በውጤቱ ባይደሰቱም ኖሮ አንድ መቀጫ የመሰለ ድብልብል ከባድ ብረት በታላቅ ችግርና መከራ ወደ መቅደላ ባልተጓዘ ነበር። የመድፉ ክብደት 80 ኩንታል ወይም 8000 ኪሎ ግራም ነው።

የእንግሊዝ ጦር ዙላ ወደብ መከማቸቱን ቴዎድሮስ ሰሙ። ይህን እንደሰሙም ያን ያሠሩትን ታላቅ መድፍ ወደ መቅደላ ለማስጓዝ ጀመሩ። ወደ መቅደላ የሔደበት ዋናው ምክንያት መቅደላ ተራራ ዙርያውን ሙጥጥ ያለ ገደል በመሆኑ ጠላት ከዚያ ቦታ በቀላሉ ለመድረስ እንደማይቻል ታስቦ ነው። ወደ ተራራው ለመውጣትም ለመድረስ እንደማይቻል ታስቦ ነው። ወደ ተራራው ለመውጣት ያለው በር አንድ ብቻ ነው። ይህም በመሆኑ አጤ ቴዎድሮስ የእንግሊዝን ጦር መቅደላ ተራራ ላይ ሆነው ለመግጠም አስበው ነው።

መስከረም 21 ቀን 1860 ዓ.ም መድፉ በጋሪ ላይ ተጭኖ የመቅደላው ጉዞ ተጀመረ። ከጋፋት እስከ መቅደላ ድረስ ያለ የመንገድ ርቀት 320 ኪሎ ሜትር ያህል ይሆናል። ይህ ርቀት ደግሞ እንኳን 8000 ኪሎ ግራም የሚከብድ መድፍ የጫነ ጋሪ የሚጐተትበትና ሌጣ የሆነ ሠራዊት የሚጓዝበት መንገድ የለም። ይህን ሁሉ ቴዎድሮስ ያውቃሉ። በመንገዱ ምክንያት ችግር እንደሚደርስዎ ተገንዝበውታል። ቢሆንም ቴዎድሮስ ደፋርና ችኩል በመሆናቸው ሠራዊቱ እየቀደመ መንገድ ሲሠራ መድፉ ከኋላ እንዲከተል አዘዙ።



የቴዎድሮስ መድፍ (ሰባስቶፓል)

መሰንበቻውን ለመድፉ መጐተቻ የሚሆን ገመድ ከጭራና ከበግ ጠጉር በወፍራሙ ሲገመድ ከርሟል። ጋሪው በቁልቁለት እንዳይሽከረከር በዳገት ወደ ኋላ እንዳይመለስ ማገጃ ወይም የፍጥነት መቆጣጠሪያ አለው። ብዙ ገመዶች ከጋሪው ፊት ከታሠሩ በኋላ 800 ጋሪ ጐታች ሰዎች ተመደቡ። አብዛኛው እየጐተተ ጥቂቱ ከኋላ እየገፋ ያ ታላቅ አስቸጋሪ ጉዞ ተጀመረ። ችግሩ የመንገድ ብቻ ሳይሆን በዚያን ጊዜ ቴዎድሮስን ብዙ ሰዎች ከድተዋቸው ስለ ነበረ መንገዱ በሙሉ በሽፍቶች የተሞላ ነበር። ስለዚህም ጉዞው ከሽፍቶች ጋር ጦርነት እየገጠሙ መንገዱን ማስለቀቅም ነበር በዚህ ምክንያት በቀን ውስጥ ረጅም ጉዞ ተደረገ የሚባለው የሶስት የአራት ኪሎ ሜትር ርቀት ብቻ ነበር። ሌላው ችግር ደግሞ ጊዜው ገና ሰብል ያልተሰበሰበበት ወቅት በመሆኑ ለሠራዊቱ በቂ ስንቅ አልነበረውምና ደክሞ እየዋለ የምግብ ችግር ሠራዊቱን ያጋጥመው ነበር። ይህን ችግር ለመፍታትም አጤ ቴዎድሮስ ያገኙት

ያጋጥመው ነበር። ይህን ችግር ለመፍታትም አጤ ቴዎድሮስ ያገኙት ዘዴ ራሳቸው በሰብል መሀል እየገቡ እሸት እየቆረጡ በመመገብ ለሠራዊታቸው አርአያ ሆኑ።

እስከ ጨጨሆ ድረስ ያለው መንገድ እምብዛም አስቸጋሪ ባይሆንም ከዚያ በኋላ ግን ያለው መንገድ የተራራ መውጣት ነበር። በዚያም ከባድ የሆነ የመንገድ ሥራ ችግር አጋጠመ ከንጋቱ ጀምሮ እስከ ምሽቱ ድረስም ሠራዊቱ በሙሉ መንገድ በሥራት ይውላል። የአገሬው ባላገርም እየታዘዘ በመውጣት ይረዳል። አጤ ቴዎድሮስም ከሠራዊቱ መሐል ሳይለዩ ድንጋይ በመፈንቀልና አፈር በመደልደ ሥራ ሲያግዙ ይውላሉ። ይህን መንገድ ከመነሻው እስከ መድረሻው ሔጀበት እንዳየሁት በዚያ ዘመን በእንደዚያ ያለ ጥሩ ምሕንድስና ይሠራል ተብሎ የማይታሰብ ነው። ምንም እንኳን እኔ በበቅሎ በምጓዝበት ጊዜ መንገዱን ጢሻ ወርሶት አንዳንዱም ዘንድ ጐርፍ በርብሮ ያበላሸው ቢሆንም የአግድመት አያያዝና የመጠምዘዣው ፕላን ለኔ አስደንቆኛል።



አጤ ቴዎድሮስ በመንገድ ሥራ ላይ

ዓዙ ተንታ በደረሰ ጊዜ ወዳጃቸውና የሚወዱት ዎልድሜየር ከእንግሊዝ ጦር ጋር መዋጋቱ እንዲቀርና ነገሩ በሰላም እንዲያልቅ ወደ ናፒር መልክተኛ እንዲላክ አጤ ቴዎድሮስን አማከራቸው። ቴዎድሮስ ባቀረበው አሳብ ተናደው ሽጉጣቸውን መዝዘው ዎልድሜየርን ሊገድሉት ካነጣጠሩበት በኋላ ሽጉቱን መልሰው ከቦታው ከተቱ። ወዲያውም የያዙትን ጦር ቢወረውሩበት ለጥቂት ስቶት ከመሬት ገብቶ ተቀረቀረ። ከዚህ በኋላ ለዎልድሜየር ይቅርታ ቢያደርጉለትም ዳግመኛ በቴዎድሮስ ፊት የሰላም ሁኔታን የሚያነሳ ጠፋ። በዚያን ጊዜ ግን የእንግሊዝ ቀዳሚ ጦር ከበሽሎ ሸለቆ ደርሶ ነእብር። አንድ ቀንም ቴዎድሮስ ዎልድሜየርን ጠርተው የሩቅ ማመልከቻ መነጥራቸውን ሰጡትና «.......የበሽሎን ወንዝ አካባቢ ተመልከትበት እነኝያ እኔን ለመግደል የተላኩትን መልክተኞች ታያቸዋለህ? የለበሱትን ቀይ ልብሶች በማየቴ ተደስቻለሁ የተደሰትኩበትም ዋናው ነገር ያ ቀጣፊ ካሜሮን ያመጣልኝን መልስ ለማምጣት የእንግሊዝን አገር በሙሉ በማንቀሳቀስ ነው» አሉት።

መድፉ ከስድስት ወር ተኩል ጉዞ በኋላ ሰላምጌ ደርሰ። ሰላምጌ ከመቅደላ ግርጌ ያለ ሰፋ ያለ ቦታ ነው። ወደፊትም ቢሆን ስማቸው የሚጠሩት ፉላ፥ አሮጌ ስላሴ እነኝህን የመሳሰሉትን ሁሉ በመቅደላ ተራራ ወገብ ላይ የቦታቸው ስም ናቸው።

መድፉ እየተጐተተ ሰላምጌ ከደረሰ በኋላ ስለነበረ ሁኔታ ዶክተር ብላንክ ሲፅፍ «......መጋቢት 16 ቀን 1860 ዓ.ም ጋሪዎቹን መድፎቹንና አዳፍኔውን ይዘው ሰላምጌ ተራራ ስር ሠፈር አድርገው ወደ አምባው ለመውጣት የሚያስፈልጋቸውን እምንገድ ማሠራት ጀመሩ።........ከሰላምጌ ተራራ ላይ የተሠራው መንገድ ስፊ ሆኖ ቀጥ ያለ ተራራና ከግማሽ መንገድ ላይ በኃይል ሰለሚጠመዘዝ ምናልባት ከባድ ጋሪዎችን ለማዞር የሚያስቸግር መስሎን ሰጋን። አጤ ቴዎድሮስ የሥራውን አካሔድና አመራር አተኩረው ይመለከቱ ስለ ነበር ብዙ ንግግር አላደረጉም። ኋላ ግን ትልቁ አዳፍኔ መድፍ እየተጐተተ ብቅ ሲል እንድናይ አመልክተው የሚስተር ራሳምን አስተያየት ጠየቁ። ያን ትልቅ ነገር ሁላችንም አደነቅነው። ሚስተር ራሳምም አድናቆትን ከምሥጋና ጋር ከገለፀላቸው በኋላ በቅርቡ የመጡት ሰዎችም ተመልክተው እንደሚያደንቁት ስለተናገረ።........ አጤ ቴዎድሮስ ስቀው ሣሙኤል ወደ ዎልድሜየር እንዲወርድና ራሳም ያለውን እንዲነግረው አዘዙት።......ከዚህ

በኋላ አጤ ቴዎድሮስ አስቸጋሪ ቀጥተኛ ወደ ሆነው ቦታ ወርደው ሠራተኞቹን መምራት ያዙ።......... ያን የመሰለ ከባድ ዕቃ እንደዝያዘ ካለ ተራራና ገደል ሥፍራ ጐትቶ ለማውጣት ከቴዎድሮስ አመራር በስተቀር ሌላ ሰው ሊያደርገው እንደማይችል በፍፁም አምናለሁ መጐተቻው መጫኛ ጠፍሩ ብዙ ጊዜ የሠራ በመሆኑ አሁንም ቅድምም ስለሚቆረጥ በዚህ በመጨረሻው ሰዓት ላይ አደጋ ደርሶ ይህ የደከሙበት ትልቁ ሰባስቶፐል ገደል ሲገባ ግርማዊነታቸውን ሊያበሳጭና ሊያሳዝናቸው እንደሚችል በመገመት ሁኔታው እኛንም ከአደጋ ላይ ሊጥለን ስለሚችል እግዚአብሔር በሰላም እንዲያወጣው መፀለይ ግድ ሆነብን። አጤ ቴዎድሮስ ከአንድ ትይዩ ከሆነ ድንጋይ ላይ ጦራቸውን ተደግፈው ቁመው በሥራው ላይ ሆነው ጠፍሩን ለሚስቡት አምስትና ስድስት መቶ ለሚሆኑ ሰዎች መልከት እየላኩ ሥራውን ላይ ሆነው ጠፍሩን ለሚስቡት አምስትና ስድስት መቶ ለሚሆኑ ሰዎች መልክት እየላኩ ሥራውን መምራት ያዙ። አንዳንድ ጊዜ የሠራተኞቹ ድምፅ ሲበዛ ወይም መምሪያ ለመስጠት ሲፈልጉ እጃቸውን ወደ ላይ ብድግ ባደረጉ ጊዜ ያ ሁሉ ድምፅ ባንድ ጊዜ ፀጥ ስለሚል ከዚህ በኋላ ግልፅ በሆነ ድምፃችወ መናገር መምራት ይጀምራሉ።

«በመጨረሻ ትልቁ አዳፍኔ መድፍ በሰላም ሰላምጌ ደረሰ። በፍጥነት ወጥተን ግርማዊነታቸው ላከናወኑት ትልቅ ሥራ ምሥጋናችንንና አድናቆታችንን እንደገለፅን ወደ መድፉ ሔደን እንድመለከት ታዘዝን። ሶስታችንም ከመድፉ መጐተቻ ጋሪ ላይ ወጥተን አድናቆታችንን በቃለ አጋኖ ስለገለፅን በዙሪያው የነበሩት ሁሉ ተገረሙ። ግርማዊነታቸውም ያስደስታቸውን መሣሪያ እኛም ስላደነቅንላቸው ከተቀመጡበት ከሰላምጌ አፋፍ ላይ ቀረብ ብለን እንድንቀመጥ አዘዙን።.......» በማለት ሁኔታውን ገልጿል።



ዶክተር ብላንክ እንደጻፈው «ሶስታችንም» ብሏል። እነሱም ራሳም ራሱ ብላክና ፐሪዲውክስ ነበሩ። ብላንክ እንደጻፈው ሶስቱም ከቴዎድሮስ አጠገብ እንደ ተቀመጡ ቴዎድሮስ ወደራሳም ዘወር ብለው ስለ እንግሊዞች መድፍ ሁኔታ ይጠይቁ ጀመር። ጥያቄያቸው የመድፎቻቸው ኃይል ምን ያህል ነው? ምን ያህል ርቀትስ ይተኩሳሉ? ወታደሮቻቸውስ እንዴት ናቸው? እያሉ ነበር። ራሳምም ራሱን ከመከራ ለማዳን ሲሉ ባጭሩ ስለወታደር ነገር ምንም እንደማያውቅ መናገሩን ራሱ ጽፎበታል። አጤ ቴዎድሮስ የራሳምን መልስ ችላ ብለው «.......እነኝህን የኔን የማይረቡ ወታደሮች እንዴት አድርጌ የእናንተን ጥሩ የለበሱትን ወታደሮች ላሳያቸው እችላለሁ?......አንድ ጊዜ ኃይለኛ እንደነበርኩበት ጊዜ ቢሆን ኖሮ በርግጥ የእናንተን ወታደሮች ለመገናኘት ካረፉበት ከጠረፉ ቦታ ድረስ እሔድ ነበር። ወይም ደግሞ መልክተኛ ልኬ በአገሬ ውስጥ ምን እንደሚፈልጉ አስጠይቃቸው ነበር። ሆነና አሁን አበሻን በሙሉ አጥቻለሁ። አሁን የቀረኝ ይሄ ድንጋይ ብቻ ነው። አሉት። ያን መድፍ ያሠሩትንም እንግሊዞችን ለመውጋት ሳይሆን የአገራቸውን ሽፍታ ለማጥፋት እንደነበረ ገለፁለት።

ምንም እንኳ በዘመናቸው ባለ ሞተር መኪና ቀርቶ ሕዝብ የሚመላለስበት ሠረገላ እንኳ በኢትዮጵያ ውስጥ ባይኖርም ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን በሙሉ በመንገድ ለማገናኘት ከፍተኛ ምኞትና ሐሳብ ነበራቸው። ኸንሪ ዱፍተን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሚስዮናውያንን መንገድ እንዲሠሩ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ረዳት መንገድ ሠሪዎች መስጠታቸውን በመጽሐፉ ይገልፅና ይህም ሊሆን የቻለው ሚስዮናውያኖቹ «.......አንድ ቀን ከንጉሱ ጋር በአጀብ ሲሔዱ ብዙ ድንጋይና ቋጥኝ ካለበት ቦታ ደረሱ። በዚያም ሆነው ኤውሮፓውያኖቹ በኤሮፓ መንገድ ላይ ያለ መሰናከል ያለመኖሩንና መንግሥት መንገድ ማሠራቱን ነገሩዋቸው። ቴዎድሮስም ወዲያው ከበቅሎአቸው መውረዳቸውንና ድንጋይ ማንሳታቸውን ያየ ሁሉ ከበቅሎና ከፈረሱ እየወረደ ድንጋዮቹን ያነሳ ጀመር ወዲያውንም ድንጋዮችም ሆኑ ቋጥኞች ተንስተው ጥቂት ማይሎች ርዝመት ያለው ሥፍራ ጥሩ መንገድ ሆነ። «.......አንድ ቀን ደግሞ በመንገድ ሲሔዱ መሬቱ ተሰነጣጥቆ ፈረስና በቅሎ አላስኬድ ሲል ተመልክተው ያንጊዜ በእግራቸው ነእብርና የሚጓዙት ቆም ብለው በያዙት ጦር መሬቱን እየቆፈረ ሲያስተካክሉ ያየው ሠራዊት ባንድ ጊዜ መንገዱን ደልድሎ

ጥሩ መንገድ አደረገው።.........» ይላል እንዲያው ለአብነት ያህል ያህል ጠቀስኩት እንጂ የቴዎድሮስ የመንገድ ሥራ በዚህ የተገታ አልነበረም።

መኪናም ሆነ ሠረገላ በሌለበት አገር መንገድ ለመሥራት ቴዎድሮስን ምን አሳሰባቸው?። ቴዎድሮስን መንገድ ለመሥራት ያሳሰባቸው። «........መንገድ ሁሉ በያቅጣቸው በየዱሩ ውስጥ በመሆኑ ሽፍታውና ሌባው ነጋዲዎችን እየዘረፉ በማስቸገሩ ደንበኛ መንገድ በሚስዮናውያኖቹ ለማሠራት ፈለጉ። ዋናውን ከተማቸውን ደብረ ታቦር ጋር እንዲገናኝ ለማድረግ ወጡኑ። ከጐንደር ከጐጃምና ከመቅደላ ጋር በአውራ ጐዳና ለመገናኘትና ከእነዚህም መንገዶች ቅርንጫፍ ከሌሎች ከተሞች ጋር እንዲገናኝ እንዲደረግ ፕላን አወጡ።» ሲል ኸንሪ ይገልጣል። ቴዎድሮስ ወደ ዋድላ ሲሔዱ ከሚስዮናውያኖቹ አንዱ ሳልሙለር የሚያሠራውን የቤተሐራን መንገድ ሊጐበኙለት ሔዱ። ከዚያም እንደ ደረሱ ሳልሙለር «የሚረዳኝን አጥቼ ብቻዬን ሆንኩ» ብሎ ለአጤ ቴዎድሮስ አመለከተ ይህን የሰሙት ቴዎድሮስ በጣም ተቆጥተው «ይሄ ከሩቅ አገር መጥቶ ሲሠራ ያገሬ ሰው እምቢ ሊል» ብለው ብለው የዋድላውን ምስሌነ ይመር ጐዳና የተበለውን ገርፈው እንዲታሠሩ ማድረጋቸውን አለቃ ዘነበ ጽፈዋል። ለላርሙለርም የራሳቸውን የሚቀመጡበትን በቅሎ ከነሙሉ ዕቃው ሸለሙት። የጨጨሆን መንገድ ለሚሠሩት ለፍላድ 300 ብር ለቤንደር፥ ለኪስሌ ይህን ስናስብ ቴዎድሮስ ለአገራችወ እድገት ምን ያህል አሳቢ እንደነበሩ እንገምታለን።

ሚስዮናውያኖቹን በግዴታ ይዘው ያሠሩዋቸው በነበረ ጊዜ ለሚስዮናውያኖቹ ረዳት የሚሆኑ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያኖችን ሰጥተዋቸው ነበር። ሚስዮናውያኖቹም መንገድ ከመሥራታቸውም ሌላ በሠሩት መንገድ ዕቃ የሚያመላልስ ጋሪም ሠርተው ነበር። ይህም ብቻ ላይሆን በውሃ ኃይል እየዞረ ልዩ ልዩ መንኮራኩሮችን የሚያዞር መኪናም ተሠርቶ ነበር። በዚያ ዘመን የቅጥቀጣና ልዩ ልዩ ሞያ አላቸው የሚባሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በሚስዮናውያኖቹ ዘንድ ተሰብስበው እንዲሠሩና እንዲማሩም ተደርገው ነበር። ሳልሙላር እና ዎልድሜየር ኢትዮጵያውያንን በሚገባ በጅ ሥራ በማሥተማራቸው ቴዎድሮስ ተደስተው በየጊዜው ሥራው ወደሚሠራበት ወደ ጋፋት እየተመላለሱ ይጐበኙዋቸው ነበር። አዳዲስ ሥራዎች ተሠርተው በሚያዩበት ጊዜም ዎልድሜየር እንደጻፈው «የሚያላዝኑ እጆች። አሁን

እነኝህንም አፈር ይበላቸው ይሆናል» እያሉ የዎልድሜየርን እጅ ይስሙ እንደነበረ ጽፈዋል።

ወዳጃቸው የነበረው ፕላውዲን እንደ ኤሮፓ አቆጣጠር ሰኔ 25 ቀን 1855 ዓ.ም ወደ እንግሊዝ ወዳገሩ ባስተላለፈው ሪፖርት ላይ ሲገልጽ «......የአበሾችን አለባበስ እንኳ ለመለወጥ ጀምረዋል። ሰዎቻቸው ሁሉ ከጋሎች በወሰዱት አለባበስ ግማሽ ራቁት መሆናቸው ቀርቶ ሙሉ ልብስ እንዲለብሱ አዘዋል።......በያውራጃው ያለውን ወታደር ሁሉ ባንድ አዛዥ ሥር እያደረጉ ለመፍረድና ለመቅጣት ሥልጣን በሌላቸው በታማኞቻቸው ሥር እንዲታዘዝ አድርገዋል።.......ለወታደሩም ገንዘብ በመስጠት በደሞዝ እንዲተዳደር ወስነዋል። ለሹማምንትም እንደየደረጃቸው ከሙቶ ብር እስከ ሺህ ብር ቋሚ ክፍያ ወነውላቸዋል።......... ይህም ቢሆን እንደሚያስቡት በሚገባ ሆኖ አልተቋቋመላቸውም።....... ወታደሩም በጠመንጃ ብቻ እንዲሰለፍ እንጂ በጦርና በጐራዴ እንዳይሆን ያስባሉ። ጦርና ጐራዴንም ወደማረሻነት ለመለወጥ ይመኛሉ።.......» ብሏል።

መጋቢት 6 ቀን 1858 ዓ.ም ቴዎድሮስ ለራስም በጻፉት ደብዳቤ «.......ቱርኮች አገሬን ይዘውብኝ ባለጋራ ሁነውብኛልና መርከብ የለኝ በባህር አልችላቸውም.......» ብለው ነበር። በዚህ ምክንያት የእንግሊዝ እስረኞችና ሚስዮናውያኖቹ መርከብ እንዲሠሩላቸው ትእዛዝ ሰጡ። ስለዚሁ ጉዳይ ዶክተር ብላንክ ሲጽፍ «.......የጋፋት ሰዎች መርከብ መሥራት እንዲጀምሩ ቢታዘዙ ስለመርከብ ሥራ ምንም እንደማያቁ ገልፀው ነገር ግን ችሎታ ያለው ሰው ከመራን ለመሥራት ፈቃደኛ ነን ብለው በተጨማሪም ለመርከብ ሥራ ችሎታ ያለው ሰውና መሣሪያ ከእንግሊዝ አገር ሚስተር ራሳም እንዲያመጣላቸው እንዲጠይቁት....... የሚጠይቁትንም ሚስተር ራሳም በደስታ እንደሚፈጽም አረጋገጡ።

«.......ከጥቂት ቀናት በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ለሚስተር ራሳም ደብዳቤ ጽፈው የመርከብ ሠራተኞች ከእንግሊዝ አገር እንዲያስመጣላቸውና ሠራተኞቹ እስኪመጡ ድረስ እንዲቆይ አለጠየቁት......ሚስተር ራሳምም.......ወደ እንግሊዝ አገር ቢመለስና የግርማዊነታቸውን ፍላጎትና

ጥያቄ ለንግሥቲቱ አስረድቶ ለማስፈፀም የሚቀለው መሆኑን ካስረዳ በኋላ ግርማዊነትዎ ከዚሁ እንዳለው ደብዳቤ እንድጽፍ ልጻፍ ሲል መስል ሰጠ።

ቴዎድሮስ በዚህ የረጅም ጊዜ ሐሳብ አልተስማሙም። የእንግሊዝ እስረኞችም ተጠይቀው መርከብ መሥራት ያለመቻላቸውን ገልፀዋል። ሚስዮናውያኖቹም አናቅበትም ብለዋል። ለዚህ መድኃኒት ወይም መፍቻው ቁልፍ ራሳችው ቴዎድሮስ በመሆናችወ ለመስራት ሥራውን መጀመር እንዳለባቸው ተገንዝበው ቴዎድሮስ የመርከብ ስራቸውን ጀመሩ። ሐሳባቸውም እሳቸው ሥራውን ቢጀምሩ ሌሎች ኤውሮፓውያንም ስለሚረዱ ሥራው ከፍጻሜ እንደሚደርስ በመተማመን ነው። ብላንክ ሲጽፍ «......ራሳቸው ወርደው መርከብ መሥራት ጀመሩ።.......» ይላል። ሌሎችም ኤውሮፓውያን በመረባረብ ስለረዷቸው ታላቅ መርከብ ተሠራ። «እንዲያውም» ይላል ብላንክ። «እንዲያውም ፓድል እስቲመር ፈልስፈው ሠተው ነበር።ድ አሩ ግን ሎኮማቲቩ ሳይሠራ ቀረ።....... ጀልባዋን የሚያንቀሳቅሰው ጐልቱ መንኮራኩር በጣም ትልቅ ስለነበር ወደው ሃው ውስጥ ጠልቆ እንዲገባ ለማድረግ በመቶ የሚቆጠር ሰው ያስፈልገው ነበር። በዚሁ ጀልባ ሥራ መንፈሳቸው በጣም ተመስጦ ስለነበረ ጊዜያቸውን በሙሉ ለዚህ ተግባር ስላዋሉት ከሠፈራቸው አራት ማይልስ ርቆ ከሚገኝ ሥፍራ ላይ ኃይለኛ ጠላት ተነስቶ ሳይሰሙ ቆይተዋል...... ይላል።

ይህ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በሞተር የሚንቀሳቀስ ጀልባ የተሠራው በ1858 ዓ.ም በሚያዝያ ወር ነበር። ራሳም ስለነዚሁ መርከቦች ሥራ ሲገልጽ «......በሥራው ቴዎድሮስም ተካፋይ ነበሩ። 60 ጫማ ርዝማኔና 20 ጫማ ስፋት ያላቸው ሁለት ጀልባዎች ተሠሩ።...... እነዚህ 2 ጀልባዎች እያንዳንዳቸው አንድ መቶ ሰዎች ሲጫኑበቸው ጀልባዋ ወደ ባህሩ ውስጥ ያዘቀጠችው አራት ኢንች ያህል ብቻ ነበር።.......ሚስዮናውያኖቹና ሕዝቡ ተሰብስቦ በአድናቆት ጀልባዎቹን ሲመለከት ቴዎድሮስ ደግሞ በጣም ደስ ብሏቸው ነበር። ጀልባዋ በምትሞከርበት ጊዜ እኛን ይዘውን አልሔዱም። መልክተኛ ልከውም እናንተን የተውኩበት ምክንያት ምናልባት ጀልባዋ የሰጠመች እንደሆነ ውሃ ውስጥ ትገቡና ትበሰብሳላችሁ (ትረጥባላችሁ) ብዬ ነው አሉን።......በደህና ከተመለሱም በኋላ አንድ የባህር ኃይል እንድናቋቁም ጠየቁን።.....ብሏል።

በቴዎድሮስ ታሪክ ውስጥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ጎልቶ የሚታየው መድፍ ማሥራታቸው ብቻ ነው። ግን ብዙ ሥራ አሠርተዋል።

# ምዕራፍ 10

# ፈረንጆቹ ለምን ታሰሩ?

አጤ ቴዎድሮስ ፈረንጆቹን ያሰሩበት ምክንያት ምንድነው? በእብሪት ተነሳስተው ነው ወይስ ምክንያት አላቸው? የአንድን መንግሥት ያውም በዚያን ዘመን የሚፈራውን የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል የሆነውን ሰው ማሠር የማይገባ ቢሆንም ቴዎድሮስ ያሠሩበት ዋናው ምክንያት ግን በኢትዮጵያ ላይ ጠላት ስለበዛና ኤሮፓውያንም እየናቋቸው ስላስቸገሩዋቸው ነው።

ቱርኮችና ግብጾች ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ለመያዝ በያሉበት ይራወጣሉ። በባህርም ሆነ በምድር የኢትዮጵያን ወሰን እያለፉ አገር ይዘዋል። በዚህ ላይ የካቶሊክ ሚስዮናውያን እበሳቸው ላይ ሌላ ፕሮፓጋንዳ ይሠራሉ። ፈረንሳዮች ከኢትዮጵያ ጠአልቶች ጎን ተሰልፈው ለኢትዮጵያ ጠላቶች የመሣሪያም ሆነ የማበረታታ ዕርዳታ ያደርጋሉ። ፈረንሳዮች ለኢትዮጵያ ጠላቶች የሚረዱበት ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያ ኃይል ሲዳከም በደከመው ጉልበት ላይ በአዲስ ኃይል ዘምተው ኢትዮጵያን ለመያዝ ባላቸው ጉጉት ነው። ይህም ጉጉት በቴዎድሮስ ዘመን የተጀመረ ሳይሆን የቆየ ነው።

ቴዎድሮስ ገና ከመንገሳቸው በፊት ደጃች ካሣ ይባሉ በነበረበት ጊዜ የሮማ ካቶሊክ ሚስዮን የላካቸው ያዕቆብ (ጃኮቢስ) በአገር ጉዳይ እየገቡ ስብከትና ስለላ ስለጀመሩ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ አዘዙዋቸው። ያኔ የካሣ ግዛት ኢትዮጵያን በሙሉ አያጠቃልልም ነበርና ካሣ ያባረሩዋቸው አቶ ያዕቆብ ወደ ትግራይ ሔደው ከደጃች ውቤ ዘንድ ተቀመጡ። ቴዎድሮስ ደጃች ውቤን ድል አድርገው ከነገሡ በኋላ ያዕቆብ ኢትዮጵያን ትተው ወጡ።

አባ ያዕቆብ የደረሰባእችውን በደል እየጨማመሩ በቫቲካን ላሉት የካቶሊክ ሊቀ ጳጳስ አመለከቱ። ጳጳሱም አንድ ዜጋችን ያለምክንያት ስለተባረረ ጉዳዩ ይታይልኝ ሲሉ ለኢጣሊያ መንግሥት አመለከቱ። የኢጣሊያ መንግሥትም በዚያው ጊዜ በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል እያለ አለሁ አለሁ

የሚለው ለፈረንሳይ መንግሥት ጉዳዩን አመልክቶ ግብጽ አገር ባለው አምባሳደርና ምጽዋ በተቀመጠው የፈረንሳይ ቆንሲል አማካይነት ጉዳዩ እንዲጨረስ ጠየቀ። በኢትዮጵያ እግራቸውን ለማስገባት ይመኙ የነበሩት ፈረንሳዮች ይህን ምክንያት በማግኘታቸው የቴዎድሮስን መንግሥት መቃወማቸውን በይፋ ገለፁ።

አባ ያዕቆብ ቴዎድርሶን ለመጣል እነእከሌን እንርዳ እያሉ የኢትዮጵያን መኳንንት ስም እየጠሩና ከቴዎድሮስ ጋር ያላቸውን ጥል እያብራሩ ለፈረንሳይ መንግሥት ይጽፉ ጀመር። ሌላው ቀርቶ ፌብረዋሪ 24 ቀን 1856 ለሳልሳዊ ናፖሊዮን በጻፉት ደብዳቤ ከቴዎድሮስ በፊት በራስ አሊ ጊዜ የነበሩትን አጤ ዮሐንስ እንደገና ወደ ዙፋናቸው ቢመለሱ በካቶሊክ ሃይማኖት ሊገቡ ቃል ገብተውልኛል እያሉ ጻፉ። በዚህና በሌሎች ምክንያቶች ቴዎድሮስ የውጭ አገር ሰዎችን እየጠሉ የሚስዮናውያንንም ስብከት ከለከሉ።

አጤ ቴዎድሮስ ሚስዮናውያንን በኢትዮጵያ ውጽት መንፈሳዊ ስብከት እንዳይሰብኩ የከለከሉት የካቶሊክ እምነት የሚሰብኩትን ሚስዮናውያን ብቻ አይደለም። የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮችም ቢሆኑ መንፈሳዊ ስብከት እንዳይሰብኩ ከልክለዋል። ወደ ፊት እንደምናነበው አንድ ጊኤ በሌዠንና በባርዴል ጉዳይ ጐንደር ውስጥ ጉባኤ ተደርጐ ጉዳዩ በሚመረመርበት ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ሲናገሩ «.......በሚገባ አውቃለሁ።.........የኤውሮፓ መንግሥታት አንድ አገር ለመያዝ ሲፈልጉ መጀመሪያ ሚሲዮናውያንን ይልካሉ። ቀጥለውም ሚስዮናውያኖቹን የሚያጠናክር ቆንሲል ብለው ይሾማሉ። ከዚያም በኋላ ቆንሲሉን የሚጠብቅ ብለው የጦር ወታደሮችን ይልካሉ። እኔ እንደ ሒንዱስታን ራጃ ቂል ሆኜ እንደዚያ እንዲደረግ የምፈቅድ አይደለሁም።........» ብለዋል።

አጤ ቴዎድሮስ እንዳሉት ሁሉ ፈረንሳዮችም ሆኑ እንግሊዞች ኢጣሊያኖች፥ ጭምር ስለሚስዮናውያኖቹ ኑሮ ጉዳይ የሚከራከሩበት በእርግጥ ለእግዚአብሔር መንግሥት የወንጌል ትምህርት እንዲስፋፋ ብለው አይደለም። አብዛኛዎቹ ሚስዮናውያን አንድ አገር የሚገቡት ለወንጌል ስብከት ሥራ ሳይሆን የአገሩን ሁኔታ የመንግሥቱን ጥንካሬና ድክመት ለመሰለል ጭምር ነው። ውስጠ ምሥጢሩን ግን በወንጌል ልባስ ይሸፍኑታል። ይህም

ሁሉ እንዲህ ያደርጋሉ ማለት ሳይሆን እንዲያ የሚያደርጉ እንዳሉባቸውም ለማሳወቅ ነው።

ለምሳሌ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የሆኑት ሉዊስ ክራፍ እና ሔንሪ እስተርን ለወንጌል ሥራ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ኖረው ከወጡ በኋላ የጻፉዋቸውን መጽሐፍት ብንመለከት የኢትዮጵያ ብሔረሰብ የሚያደርገውን የርስ በርስ ግጭት በመንግሥት ላይ ያየሉትን ሽፍቶች ታሪክና ዝና የትኛው አገር ለምና የትኛው በረኛ ክፍል እንደሆነ በጠቅላላው አገሪቱን ቁልጭ አድርጐ የሚያሳይ ትረካ ነው የንጉሱን ወይም የየመኳንንቱን ደካማና ጠንካራ ጐን ሁሉ ይጠቅሳሉ። ይህ እንዲህ ከወንጌል ሥራ ወይም ትእዛዝ ጋር የማይገናኝ ነገር ነው።

በተለይ እስተርን አጤ ቴዎድሮስን ሰካራም ናቸው ሴሰኛ ናቸው፥ የአንዲት ተራ የኮሶ ሻጭ ልጅ ናቸው እያለ በመስደብ የጻፈባቸው የትኛው ወንጌል ነው ሐሜታ አሙ ወይም ተሳደቡ የሚል? ወደፊት እንደምናነበው አጤ ቴዎድሮስን ከመጠን በላይ ያናደዳቸውና ሚስዮናውያኖችን ያስጠላቸው አንዱም የእስተርን አጻጻፍ ነው። እነኝህ ሰዎች ለወንጌል ሥራ ሳይሆን ለታሪክ ፀሐፊነት ገብተው እንደዚያ ያለ ቢጽፍ ባልተነቀፉ ነበር። ወንጌልና ስድብ አብረው አይሄዱም።

ወደ እንግሊዞች ብንመለስ ወደ ኢትዮጵያ እግራቸውን ለማስገባት ባሰቡበት ጊዜ መጠቀሚያ ወይም መንገድ ቀዳጅ አድርገው መጀመሪያ የላኩዋቸው የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያንን ነበር። ይህን ያወቁት ቴዎድሮስም ሚስዮናውያኖቹ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ አደረጉ። ይህንንም የቴዎድሮስን ውሳኔ ለማስለወጥ የእንግሊዝ መንግሥት ቴዎድሮስ የሚወዱትን የጦር መሣሪያ ሊልክላቸው አሰበ። ይህንንም ሐሳብ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አፕሪል 8 ቀን 1858 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለፕላውዲን ገለፀለት።

ፕላውዲን ይህ ደብዳቤ እንደደረሰው መልሱን ኖቬብመር 15 ቀን 1858 ዓ.ም ጻፈ። በጻፈውም መልስ ቴዎድሮስ ትግራይን እስኪይዙ ድረስ የሚላከው መሣሪያ ኤደን እንዲቀመጥ ቴዎድሮስ፥ በእንግሊዝ መንግሥት ሐሳብና ፍላጐት መሠረት እንዲሠሩ እንዲደረግ ፈቃደኛ ሆነው ተባብረው ባይሠሩ ግን «.......የግብፁ ገዥ ባለው ኃይል ሥነ ሥርዓት እንዲያስተምራቸውና ሥልጣኔ

እንዲያሳያቸው ቢደረግ ይሻላል.......ይህም አዲስ ገና የተቋቋመው ሕፃን መንግሥት ማንኛውንም ኃይል መቋቋም የሚችል አይደለም። ስለዚህ ግብጾች ቢመቱዋቸው ጉዳዩ ቀላል ይሆናል......» ብሎ ነበር።

ፕላውዲን እንዳመለከተ ቴዎድሮስ እየተደጋገሙ ቢጠየቁና ብዙ ማስፈራሪያ ቢቀርብላቸውም ኤውሮፓውያንን የሚፈልጉዋቸው ሀገሪቱን በማልማት በኩል ብቻ መሆኑን እየገለፁ ያውም ቢሆን በእሳቸው ትእዛዝ መሠረት እንጂ ማንንም የበላይነትም በስብከትም እንደማይቀበሉ አስታወቁ። ይህንንም የቴዎድሮስን ገታራነት ያየው ፕላውዲን ጉዳዩን እየዘረዘረ ወደ አገሩ አስታወቀ። የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም ያሰበውን ለማድረግ እንዲያመቻቸው መጀመሪያ ቆንሲሉን ማንሳት ስላለበት ጃንዋሪ 1860 ለፕላውዲን በአፈው ደብዳቤ ፕላውዲንም በታዘዘው መሠረት በሕመም አሳቦ ከኢትዮጵያ ለመውጣትና ወደ ሐገሩ ለመሔድ ጉዞ ሲጀምር በጋረድ አሽከሮች በጦር ተወግቶ ወደ ተያዘ። ፕላውዲንም ከሞተ በኋላ ቴዎድሮስ ለንግስት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ «........እነ አቶ ቡላዲን እነ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ.......የጠሉኝ ሰዎች እኔን ይከፋው ሲሉ ገደሉዋቸው። እኔም በእግዚአብሔር ኃይል ደመኞቼን አንድ ሳልተው ፈጀኋቸው። የገዛ ዘመዶቼን በእግዚአብሔር ኃይል የርስዎን ዝምድና ስለምፈልግ.......» በሚሉ ቃላት ለጊዜው ይነሳ የነበረውን የእንግሊዝን ድንፋታ ገቱት።

ቴዎድሮስን ከውጭ መንግሥት ጋር በማበር እጅግ ያበሳጫቸዋል የነበሩት የካቶሊክ ወይም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ብቻ አልነበሩም። የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ደግሞ አገርዎን ይልቀቁ በሚለው አሳብ ከሁሉ የበለጠ ያሳዝኑዋቸውና ያበሳጩዋቸው ነበር። የፈረንሳይ መንግሥት ለደጃች ንጉሴ ዕርዳታ ሰጥቶ አገር ለመቀበል ከመስማማቱ በፊት ሌላ ውጥን ነበረ። የአሌክሳንድርያው የኦርቶዶክስ ሊቀ ጳጳስ ወይም ፓትርያርክ የሆኑት አቡነ ቄርሎስ ወደ ሃይማኖት ልጆቻቸው ወደ ኢትዮጵያ ሔደው መሔድም ባይችሉ መልክተኛ ልከው የኢትዮጵያውን ግብጻዊ ጳጳስ አቡነ ሰላማንና ቴዎድሮስን መክረው የካቶሊክ ሚስዮናውያን በኢትዮጵያ ውስጥ እንደፈለጉ እንዲሰብኩ እንዲያስደርጉ ጠየቁ። አቡነ ቄርሎስም እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 2 ቀን 1853 በተጻፈ ደብዳቤ አቡነ ሰላማ የካቶሊክ ሚስዮናውያንን እንዳይቃወሙ አዘዙዋቸው። ይህም ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሚስዮናውያን ጥላቻ አልበርድ አለ፥

ይህን የአማላጅነት ምክንያት ያገኙት አቡነ ቄርሎስ እንደ ጂሴፔ ሁሉ እሳቸውም ለአገራቸው ለግብፅ ማሰብ ወይም ነገሩን ማዞር ጀመሩ። ቴዎድሮስ ከመንገሳቸው አንድ ዓመት ያህል ቀደም ብሎ መሐመድ ሰይድ ፓሻ የግብፅ ገዢ ሲሆን በሱዳን በኩል ያለው ሁኔታ ተለወጠ። መሀመድ ሰይድ ፓሻ በሱዳን በኩል ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ወሰን አልፎ ስናር በጐስ መንሳ ሐልመሐል ሐባብና ሌሎችም የግብፅ ግዛት ናቸው ብሎ አወጀ። ይህንንም ለማስፈፀም በወሰን ላይ ከኢትዮጵያውያን ጋር ብዙ ጦርነቶች ተደርገው ኢትዮጵያውያን እያሸነፉ የግብፅን ጦር መልሰዋል።



ግብፃዊው ፓሻ

ይህን የሚያውቁት የኦርቶዶክስ ሊቀ ጳጳስ ግብጻዊው አቡነ ቄርስሎስ በፈረንሳይ በኩል ለማላጅነት ሲመረጡ ይህን የወሰን ጉዳይ በሰላም

ለማስጨረስ መንገድ ለማዘጋጀት እንደሚሹ ለመሐመድ ሰይድ ፓሻ አመለከቱ። ሰይድ ፓሻም ለፈረንሳይ አማላጅነት አስመስለው ይህን ጉዳይ ለማስፈጸም ወደ ኢትዮጵያ እንዲሔዱ ጠየቃቸው። እሳቸውም ጥያቄውን በደስታ ተቀብለው በታህሳስ ወር 1849 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ምናልባት የማያውቁ አንባቢዎች ቢኖሩ በዚያን ጊዜም ሆነ ከዚያም በፊት ለኢትዮጵያ ጳጳስ የሚመጣለት ከግብፅ አገር ግብፃዊ የሆነ ሰው በፓትርያርኩ እየተሾመ ነበር። ስለዚህ የፓትርያርኩ የአቡነ ቄርሎስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታ ነበረው።

አቡነ ቄርሎስ እንደ መጡ አጤ ቴዎድሮስና ሕዝቡ ታላቅ አቀባበል አደረጓልቸው። ከአቀባበሉም ስነ ሥርዓት በኋላ አቡነ ቄርሎስ ከግብፁ ገዥ ከመሐመድ ሰይድ ፓሻ ለአጤ ቴዎድሮስ የተላከውን ደብዳቤ አቀረቡ። የመጡበትም ምክንያት በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የጠበቀ ወዳጅነት ለመመሥረት እንደሆነ በማስታወቃቸው ቴዎድሮስ በጣም ተደሰቱ። ይህንንም የሁለቱን አገር ወዳጅነት ቴዎድሮስ በጣም እንደሚፈልጉት ገልፀው ለሰይድ ፓሻ የሚላከውን የወዳጅነት ደብዳቤ መልስ እንደሚፅፉ ገለፁላቸው።


አቡነ ቄርሎስ ለሰይድ ፓሻ የሚላከውን የወዳጅነት ደብዳበኢ ቀደም ብለን ታሪካችን ካነበብነው ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ጳጳስ ለማዘጋጀት ቢፈቀድላቸው ለማዘጋጀት ፈቃደኛ መሆናቸውን ለቴዎድሮስ ገለጡ። አጤ ቴዎድሮስም ጉዳዩን በቅን ልቦና ተመልክተው ቴዎድሮስ ስም የሚላከውን ደብዳቤ እንዲያዘጋጁ ፈቀዱላቸው።

በሁለቱ ጳጳሳት የተረቀቀው ደብዳቤ ለአጤ ቴዎድሮስ ቀረበ። አጤ ቴዎድሮስም የደብዳቤውን ረቂቅ ቃሉን ሰምተው ጉዳዩን በጉባኤ ለማስፈቀድ መኳንንቱና ሕዝቡ እንዲሰበሰብ አዘዙ። መኳንንቱና ሕዝቡ በተሰብሰበት ጉባኤ ለሰይድ ፓሻ የተፃፈው ደብዳቤ ተነበበ። ደብዳቤው ባጭሩ የሚለው ጥበበኞች እንዲላኩላቸው በሶስት የቱርክ መኮንኖች የሚመሩ የግብፅ ወታደሮች በኢትዮጵያ ገብተው የኢትዮጵያን ወታደር እንዲያሰለጥኑ በኢትዮጵያ ያሉት የእንግሊዝና የጀርመን ዜጎችም እንዲወጡ የሚልና ወሰኑንም በሰልማ በፓሻው አስተሳሰብ ለመጨረስ ፈቃደኛ መሆናቸውን የሚገልፅ ነበር። ይህም አስተሳሰብ ኢትዮጵያ ባዶዋን ሆና ከውስጥ የቱርክና የግብፅ ወታደሮች ገብተው ማንኛውንም የኃይል ሥራ ለመሥራት እንዲችሉ

የታሰበ ነበር። አጤ ቴዎድሮስ ደብዳቤውን ካስነበቡ በኋላ ፓትርያርኩ በቃል የነገሩዋቸውን ጭምር ለተሰብሰበው ሕዝብ ነግረው «የእግዚአብሔር መንገድ ከማስተማር ትታችሁ ለገዢያችሁ ለስይድ ፓሻ አሽከር ከሆናችሁ እኔም በአገሬ ገዢያችሁ ነኝና በመንገዴ አስራችኋለሁ» ብለው ፓትርያርኩንም ጳጳሱንም አብረው አሰሩዋቸው። የዚያን ዘመን ኢትዮጵያውያን ታሪክ ፀሐፊዎች የቤተ ክህነት ሰዎች በመሆናቸው ከአቡነ ቄርሎስና ከአቡነ ሰላማ መታሰር ላይ ሲደርሱ የታሰሩበት ምክንያት ብዙ ነው እያሉ ያልፉታል። አንዳንዶቹም ቴዎድሮስ ስላበዱ ነው ይላሉ። ቴዎድሮስ ግን እንደዚያ የሚያደርጋቸው የአገር ፍቅር እንጂ እብደት አልነበረም።

ቅድም እንደተባለው ቱርኮች እስከ ባብ ኤልመንደብ ያለው የኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ ለኛ ይገባል እያሉ በያለበት የኢትዮጵያን የባህር ጠረፍ ይዘዋል። ግብጾች በሰሜናዊ ምዕራብ ያለው የኢትዮጵያ ግዛት ለኛ ይገባል እያሉ አደጋ በመጣልና በመያዝ ላይ ናቸው። ሕዝቡንም በሃይማኖት ስብከት ገብተውታል። ወሰን እያለፉም ይዘርፋሉ፥ ቤት ያቃጥላሉ። ሴትና ወንዱን እየማረኩ ባርያ ያደርጋሉ። በቁርአን ትምህርት ያላመነውንም በሰይፍ ይቀጣሉ። አጤ ቴዎድሮስ ይህን ሁሉ በመመልከትና ዙርያውን የከበቡት ጠላቶችም በሙሣሪያ በኩል ከአቅም በላይ በመሆናቸው ክርስትያኑን የእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ ጠየቁ።

የቴዎድሮስ የእርዳታ ጥያቄ የደረሰው የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ሎርድ ክላሬንዶን ግብጽ አገር ላለው የእንግሊዝ አምባሳደር ደብዳቤ ጻፉ። ጁን 30 ቀን 1845 የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለግብፁ አምባሳደር በጻፉት ደብዳቤ «.......ለፓሻው አጥብቀህ የምትነግረው....... በማንኛውም ነገር ቢሆን በወደብም ሆነ በማንኛውም የአበሻ ወሰን እንዳይደርስ። የግርማዊት ንግሥት መንግሥት በዚያ አገር ያሉትን ክርስትያኖች ለመጠበቅና ጥቅማቸውን ለማስከበር ይገደዳል። ስለዚህ በአጐራባች ያሉት እስላማውያን ከዚህ ተግባር እንዲታገዱ አድርግ........» የሚል ነበር።



አቡነ ቄርሎስ

ደብዳቤው ቢጻፍም የተሻለ ውጤት አላስገኘም። ይህ በዚህ እንዳለ በ1852 ዓ.ም ኧርል ሩሴል የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ተሾመ። በተሾመ ባመቱም ካሜሮንን የኢትዮጵያ ቆንሲል ብሎ ሾመው። ካሜሮን በኢትዮጵያ የተሾመበት ዋና ምክንያት ለኢትዮጵያውያኖች ጥቅም ሳይሆን ለራሳቸው ለእንግሊዞች ጥቅም ተብሎ ነው። የፈረንሳዩ ንጉሥ ቀዳማዊ ናፖሊዮን ቦናፓርት በ1807 ዓ.ም ግድም (1815 በኤሮፓ) ወተርሉ ላይ በተደረገው ጦርነት ከተሸነፈ በኋላ እንግሊዝ አፍሪካን በሚከቡ ውሃዎች ሁሉ በተለይ በሕንድ ውቅያኖስ ላይ የበላይነቱን ቦታ ይዞ ትቆጣጠር ጀመር። ያኔ የስዊዝ ካናል ስላልተከፈተ ዋናው የመርከቦች መንገድ ሕንድ ወቅያኖስ ነበር። አፍሪካን ከሚከቡ ውሃዎች ከሚዋሰኑት አገሮች አንዷቱ ኢትዮጵያ ስለሆነች የእንግሊዝ መንግሥት መልክተኞችን ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት በመላክ ወዳጅነት መሥርቶ ቀይ ባህርን ይቆጣጠር ነበር።

በቴዎድሮስም ጊዜ እንግሊዞች ይሄው በቀይ ባህር ላይ ያላቸውን የበላይነት ሌላ መንግሥት ገብቶ እንዳያደናቅፋቸው በማሰብ ከአዲሱ የቴዎድሮስ መንግሥት ጋር ወዳጅነታቸውን ለመቀጠል ፈለጉ። በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን በአበሻ አገር ቆንሲል ተብሎ ተሹሞ የነበረውን ፕላውዲንን በቆንሲልነት ቴዎድሮስ እንዲቀበሉት አደረጉ። ፕላውዲን ከሞተ በኋላ እንግሊዞች የባህር ጥበቃቸውን ለማጠናከርና ኢትዮጵያን ከሌላ ከእንግሊዝ ተቀናቃኝ መንግሥት በተለይም ከፈረንሳይ ጋር ተወዳጅታ የበላይነቱን እንዲያጡ ያኔ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት በነበረችው በሕንድ አገር ይሠራ የነበረውን ካፒቴን ቻርልስ ዱንካን ካሜሮንን የኢትዮጵያ ቆንሲል ብለው ሾሙት።

ካሜሮን በ1852 ዓ.ም ጐንደር ገባ። ካሜሮን በመጣበት ጊዜ ቴዎድሮስ ደጃች ተድላ ጓሉን ለመውጋት እየፈለጉዋቸው ይዟዟሩ ስለነበር ጐንደር አልነበሩም። ካሜሮንም ቴዎድሮስ እስቲመጡ ድረስ ክምረቱን ጐንደር ላይ አሳልፈው ቴዎድሮስ ጐንደር በተመለሱ ጊዜ ታላቅ የክብር አቀባበል አደረጉለት። ካሜሮንም ከእንግሊዝ መንግሥት የተላኩ ናቸው በማለት አንድ ጠመንጃና ሁለት እጀታቸው ብር የሆኑ ሽጉጦችን በስጦታ አቀረበ። «ለበሻው ንጉሥ ለቴዎድሮስ ከእንግሊዝና ለአይርላንድ ንግሥት ለአሽከርዋ ለፕላውዲን

ለተደረገለት ቸርነት የተሰጠ። 1861» የሚል የእንግሊዝኛ ጽሑፍ ያለበት ስጦታም ሰጠ።

አጤ ቴዎድሮስ በተላከላቸው ስጦታና በተለይ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት በመመሥረቱ ተደስተው መልክተኞቻቸውን በቅርቡ ወደ እንግሊዝ አገር ልከው የበኩላቸውን ምኞትና አሳብ ለእንግሊዝ ንግሥት እንደሚያሰሙ ተናገሩ። ከካሜሮንም ጋር ፈረንሳዊ ባርዴል አብሮ መጥቶ ነበርና ቴዎድሮስ ከፈረንሳይ መንግሥትም ጋር ጥሩ ወዳጅነት ለመመሥረት ፍላጐት እንዳላቸው ተናገሩ። ከካሜሮንም ጋር ፈረንሳዊው ባርዴል አብሮ መጥቶ ነበርና ቴዎድሮስ ከፈረንሳይ መንግሥትም ጋር ጥሩ ወዳጅነት ለመመሥረት ፍላጐት እንዳላቸው ተናገሩ። ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥት መልክተኞች እልካለሁ በማለታቸው ካሜሮን ተገረመ። «አንድ የአፍሪካ ትንሽ ንጉሥ እንዴት ዓለምን ከምታስተዳድር ከእንግሊዝ ንግሥት ጋር መልክተኛ ልኮ ለመነጋገር ያስባል?» በማለት ተገርሞ ጉዳዩን ናቀው።

በራስ አሊ የምስፍንና ዘመን ፕላውዲን በእንግሊዝ መንግሥት ስም ሆኖ የተዋዋለውን ውል እንደገና እናድሰው ብሎ ካሜሮን አጤ ቴዎድሮስን ጠየቀ። አጤ ቴዎድሮስም «ቆይ ላስብበት» አሉት። ካሜሮን ግን በየቀኑ እየደጋገመ በመጠየቅ ውትወታ ስላበዛ አጤ ቴዎድሮስ አንድ ቀን ቀቆጥተው «ቆይ ስልህ ቆይ። እኔ ቴዎድሮስ እንጂ አሊ አይደለሁም። ስለመንግሥቱም ሳስብበት» ብለው ቁርጡን ስለነገሩት ካሜሮን የመጣበት ቁም ነገር እንዳይበላሽበት ቁጣና ኩራቱን ትቶ ወደ መለማመጡ አዘነበለ።

ፕላውዲን በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል በነበረ ጊዜ በአገሩ መንግሥት ስም ከራስ አሊ ጋር ያደረገው ውል የኢትዮጵያና የእንግሊዝ መንግሥታት በወዳጅነት በንግድ ልውውጥና የሁለቱም አገር ዜጎች አንዱ በሌላው አገር ውስጥ እንደፈለገው የሁለቱም አገር ዜጎች አንዱ በሌላው አገር ውስጥ እንደፈለገው የመዘዋወርን ነፃነት የሚሰጥ ነበር። ይህም ውል ከ1841 ዓ.ም እስከ 1847 ዓ.ም ወይም እ.ኤ.አ. ከ1849 እስከ 1855 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ ነበር።

ውሉ የሁለቱን መንግሥታት ወዳጅነትና የንግዱ ልውውጥ የሚጠቅም ቢሆንም የአንዱ አገር ዜጋ በሌላው አገር እንደፈለገው መዘዋወር መብት

መስጠቱ ግን ጥቅሙ ለእንግሊዞች ብቻ እንጂ በዚያን ዘመን ለነበሩ ኢትዮጵያውያን እንግሊዝ አገር ውስጥ ገብተው እንደፈለጉ ሊዘዋወሩ አይችሉም። እንደዚያ ለማድረግ እውቀቱም ገንዘቡም የላቸውም። እንግሊዞች ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ሊዘዋወሩ ይችላሉ። ገንዘብም እውቀትም ያላቸው ናቸው። ከዚህም ሌላ በስለላ ወይም እርስ በርስ ለማጋጨት ተግባር ሊገቡ ይችላሉ። እንግሊዞች አብዛኛዎቹን ቅኝ ግዛቶቻቸውን የያዙትም በዚሁ ዓይነት ዘዴ ነበር።

አጤ ቴዎድሮስ በራስ አሊ ዘመን ምስፍንና የነበረውን ውል ላጥናው እያሉ ያቆዩት ከላይ በተተነተነው አኳኋን መሆን ያለመሆኑ አይታወቅም። በኔ አስተያየት ግን ካሜሮን ውሉን እናድስ እናድስ በሚልበት ጊዜ ባርዴል ደግሞ የጦር እምሣሪያ ነጋዴ ነበርና አጤ ቴዎድሮስም ዘንድ እየቀረበ ለራሱ ንግድ እንዲያመቸው ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር ቢወዳጁ የጦር መሣሪያ የሚፈልጉትን ያህል መግዛት ይችላሉ እያለ ይነግራቸው ስለ ነበረ አጤ ቴዎድሮስ የሁለቱንም መንግሥት ወዳጅነት ለመፈለግ አስበው ይሆናል። ባርዴል አጤ ቲዎድሮስን ምን ያህል ይጨቀጭቃቸው እንደ ነበረ ወዳገሩ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ገልጾታል። ባርዴራ የታወቀው የጦር መሣሪያ ነጋዴ ቢሆንም በውጭ ግን ሲያስወራ ራሱን የካሜሮን ረዳት አድርጎ ነበር።

ሌላውም ምክንያት ካሜሮን ኢትዮጵያ ውስጥ ገብሮ ሶስት ወር ያህል ከቆየ በኋላ ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሩሴል ዘንድ ፌብሩዋሪ 22 ቀን 1862 ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ መጣለት ለቴዎድሮስም በተጻፈው የሰላምታ ደብዳቤ ላይ አድራሻው «ለክቡር ቴዎድሮስ» የሚል ስለ ነበር ምናልባትም ቴዎድሮስ የእንግሊዝ ንግሥት ንጉሥነታቸውን አውቀው «ንጉሥ ቴዎድሮስ» እያሉ ሲጽፉ አንድ የበታች ሚኒስትር «ለክቡር» ብሎ በመጻፉ ቴዎድሮስ ቂም በመያዛቸው ሊሆን ይችላል።

አጤ ቴዎድሮስ ለእንግልዚ ንግስትና ለፈረንሳዊው ሳልሳዊ ንጉሥ ለቻርለስ ሎዊስ ናፖሊዮን ቦናፓርት የወዳጅነትና የእርዳታ መጠየቂያ ደብዳቤ ጽፈው ካሜሮን ወደ እንግሊዝ አገር ባርዴልን ደግሞ ወደ ፈረንሳይ አገር ላኩዋቸው። አጤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥት የጻፉት ደብዳቤ የዘመኑን የአጻጻፍ ስልት ለማሳየት ከእንግሊዝኛው ትርጉም ጋር የሚከተለው ነው።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ባንድነት
በሶስትነት እግዚአብሔር መርጦ ያነገሰው ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ
ዘኢትዮጵያ ይድረስ። ከዕንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ።እንዴት አሉ
እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። እስተ ዛሬ ድረስ አባቶች
ነገሥታቱ ፈጣሪአችነን ብበድሉት መንግሥታቸውን ለጋላና ለቱርክ
አሳልፎ ሰጥቶባቸው ነበረ ዛሬ ግን እኔ ከተወደድሁ ፈጣሪየ ካመድ
አንስቶ ኃይል ሰጥቶ ባባቶች መንግሥት አቆመኝ በእግዚአብሔር
ኃይል ጋሎችን አስለቀቅኋችው ቱርኮች ግን ያባቴን መሬት ልቀቁ
ብላቸው እምቢ ብለውኝ በእግዚአብሔር ኃይል ነው ልታገል ነኝ።
እነአቶ ቡላዲን እነ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ የክርስቲያን ንጉሥ ታላቅ
ሰው ክርስትያን የሚወዱ ሰው አሉ እናስተዋውቅህ አለን እያሉኝ
እጅግ እወዳቸው ነበረ የርሰዎን ወዳጅነት ያገኘሁ እየመሰለኝ።
ሞት ይቀርምና የጠሉኝ ሰዎች እኔን ይክፋው ሲሉ ገደሉአቸው
እኔም በእግዚአብሔር ኃይል ደመኞችን 1 ሳልተው ፈጀኋቸው የገዛ
ዘመዶቹን። እግዚአብሔር ኃይል የርስዎን ዝምድና ሥፈልግ።
ቱርኮች ከባርህ ላይ ሁነው መልክተኛየን እናሳልፍም ብለው ቸግሮኝ
ሳለ ቁንስል ኪምሮን መጣልኝ ወረቀትና የፍቅር በረከት ይዞ
በእግዚአብሔር ኃይል እጅግ ደስ አለኝ። ደህንነትዎንና ፍቅርዎን
ብሰማ የሠደዱልኝም የፍቅር በረከት ተቀበልሁ እግዚአብሔር
ይሥልጥልኝ። አሁንም መልክተኛየን ከቁንስል ኬሜሮን ጋራ የፍቅር
በረከት ይዞ እንዳልሰደው ቱርኮች በባህር ላይ የማያስተላልፉኝ ሆነ
አሁንም እንዲህ ባለ ስፍራ እከሌ ይቀበለው ብለው ይላኩብኝ
ምላሹን ኰንስል ኬሜሮን ይዞልኝ ይምጣ።

እናንተም ተገፉልኝ ክርስቲያኑን እስላም አጠቃህ ሲለኝ። ተጻፈ
በ፯ሺ ተ፫፻፶፮ ዘመን በሉቃስ በወርኃ ጥቅምት በ፳ ቀን ጐጃም
በይባባ ከተማ።



አጤ ቴዎድሮስ ይህን ደብዳቤ ለካሜሮን ሰጥተው እሱም ለእንግሊዝ መንግሥት አቅርቦ ከዚያ የሚያገኘውን መልስ ይዞላቸው እንዲመጣ አደረጉ። ለፈረንሳዩ ንጉሥ ለ፫ኛ ቻርልስ ሎዊስ ናፖሊዮን ባናፓርትም ተመሳሳይ የሆነ ደብዳቤ ጽፈው ባርዴል እንዲያደርስና መልሱን ይዞ እንዲመጣ ላኩ። ሁለቱም በሚልኩበት ጊዜ ለሁለቱም ለመንገዳቸው ስንቅ የሚሆን ገንዘብ ሰጥተው ነው።

ባርዴል ምፅዋ ሲደርስ በመርከብ ተሳፍሮ በግብጽ በኩል አድርጎ ወደ ፈረንሳይ ሔደ። ካሜሮን ምፅዋ ሲደርስ ደብዳቤ ስለያዘ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመጣ እንዲፈቀድለት የአገሩን መንግሥት ቢጠይቅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች አንድ ትንሽ መንግሥት የታላቁን እንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ለመላክ በማሰቡ ተገርመረውና ስድብ ነው ብለው ካሜሮን ደብዳቤውን እንዲልክላቸውና እሱ ግን ወደ ሱዳን ግዛት ሔደ በዚያ ያለውን የጥጥ አዝመራ እንዲያይና የባርያ ገበያውን ሁኔታ እንዲያጠና ትእዛዝ ደረሰው። የጥጥ አዝመራውን እንዲያይ የታዘዘበት ምክንያት እንግሊዝ ጥጥ የምትገዛው ከአሜሪካ ነበርና በዚያ ጊዜ በአሜሪካ አገር በተነሳው የርስ በርስ ጦርነት ምክንያት የጥጥ ገበያ በመቋረጡ ጥጥ ተወዶ ስለነበረ ነው።

ካሜሮን እንደታዘዘው ደብዳቤውን ወደ እንግሊዝ አገር ልኮ ቦጐስ፥ መንሳ፣ ከረንና ወደ ሌሎችም ቦታዎች ሊጐበኝ ሔደ። ቴዎድሮስ በባርያ ገበያ ላይ ባላቸው የክልከላ አመራር ምክንያት በሱዳን ውስጥ በግብጽ የሚቃወሙዋቸው ባርያ ፈንጋዮች ነበሩና ካሜሮን ከእነሱም ጋር ተገናኝቶ ተነጋገረ። ቴዎድሮስ የካሜሮንን ሂደት ይከታተላሉ። አብሮህ ይሂድ ያሉትን ፀሀፊያቸውን አቶ ሣሙኤልን ምጽዋ ላይ እንዲቀር አድርጐ እሱ ወደ ሱዳን መሔዱን ሰምተዋል። ሱዳን ውስጥ ገብቶ ከጠላቶቻቸው ከባርያ ፈንጋዮችና ከሌሎችም ሹማምንቶች ጋር ተገናኝቶ መነጋገሩ ወሬው ደርሷቸዋል። «....... ወዳጅ ነኝ ብሎ እንዴት ነው ጠላቶቼ ይሔዳሉ? » እያሉም አጠገባቸው ላሉት መኳንንቶችና ፈረንጆች ያወራሉ። በፈረንጆች ላይም ያላቸው እመንት በቋፍ ሆነ።

ካሜሮን አጤ ቴዎድሮስ ለላኩት ደብዳቤ የሚመጣውን መልስ ሲጠብቅ ቆየ። የደብዳቤው መልስ ግን አልመጣለትም። የደብዳቤው መልስ ግን አልመጣላቸውም። የደብዳቤው መልስ በመዘግየቱና በሱዳን አገርም የወባ

በሽታ መነሻው ጊዜ ስለተቃረበ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ። የደብዳቤውን በመናቅና በተለይ አንድ ትንሽ መንግሥት የእንግሊዝ ቆንሲል እንደ አሽከሩ በመላኩ ተናደው ስለነበር ክብራቸውን ለመግለጽ ሲሉ መልሱን እንዳይጻፍ ወሰኑ። ንግስቲቱ ቪክቶሪያ ግን ለደብዳቤው መልስ እንዲሰጥ ፈልገው ነበር። ምክር ቤቱ ባለመስማማቱ ቀረ።

ካሜሮን ከአጤ ቴዎድሮስ ሲገናኝ የደብዳቤ መልስ ያለመምጣቱን ተናገረ። አጤ ቴዎድሮስም ተበሳጩ። መበሳጨታቸውን ያየው ካሜሮንም «ጃንሆይ። እስከ ሁለት ወር ድረስ የደብዳቤዎ መልስ ይመጣል። ባይመጣም ግን አንገቴን እሰጣለሁ (I WILL GIVE MY HEAD) አላቸው። ቴዎድሮስም እሺ በልው ሲጠብቁ የደብዳቤ መልስ ሳይመጣ የቀጠሮው ጊዜ ሁለት ወር አለፈ። ከዚህ በኋላ በቴዎድሮስና በኤውሮፓውያን መሀል የመጀመሪያ ጠብ (ያለመግባባት) ተፈጠረ።

ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ ፈረንሳዊው ሙሴ ጉላሜ ሌዣን የፈረንሳይ መንግሥት መልክተኛ ነኝ ብሎ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የንግድ ሁኔታ ሊያጠና መጣ። ቴዎድሮስም ሌዠንን በክብርና በደስታ ተቀበሉት። ሌዠንም ለቴዎድሮስ ያመጣውን ስጦታ አቅርቦ ሲጨዋወቱ ቴዎድሮስ «……በዓለም ላይ ካለው ስጦታ ሁሉ ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር መወዳጀቱ የበለጠ ነገር ነው……. » አሉ ሌዠን ስለመጣበት ጉዳይ ከቴዎድሮስ ጋር ተነጋግሮ ካበቀ በኋላ «ከዚህ ከኔ አገር ከኔ ጋር ትቆያለህ ወይስ ፈጥነህ ትሔዳለህ? » ብለው ጠየቁት።

ሌዠንም «ጃንሆይ ከተፈቀደልኝ መቆየት እፈልጋለሁ ብሎ መለሰ።

«ጥሩ ብለሃል» አሉ ቴዎድሮስ «የአገርህን ሰው ወዳጄን ሙሴ ባልዴርን ወዳገርህ መንግሥት ለወዳጅነት ነገር ስለላክሁት እሱ እስቲመለስ ድረስ መቆእይት አለብህ» አሉት። ሌዠንም ይህን የቴዎድሮስን መልስ በደስታ ተቀበለው።

ሶስት ሳምንታት ከቆየ በኋላ የቴዎድሮስ ዓይነውሃ አላምር ስላለው ሌዠን ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርቦ ወደ አገሬ ለመመለስ እፈልጋለሁና ይፍቀዱልኝ ብሎ ጠየቃቸው። ቴዎድሮስም «ሙሴ ባርዴል እስቲመጣ ድረስ ቆይ ብየሃለሁ

ቆይ» አሉት። ሌዠንም «ጃንሆይ። ባርዴል የማይረባ ቀጣፊ ሰው ነው። እሱ ንጉሡም» ቀጣፊው ማን እንደ ሆነ ለማረጋገጥ ይበጀኛልና ባርዴል እስቲመለስ ድረስ ከዚሁ ቆይ። አትሔድም» አሉት።

ሌዠን የመቆየቱ ጉዳይ አስግቶት ወደ አገሩ ለመሔድ እንዲፈቅዱለት ክርክር ሊጀምር ሲል ቴዎድሮስ አቋርጠው «……ያገርህ መንግሥት ለፍቅርና ለወዳጅነት ነገር ልኮህ እንደሆነ በኬንዝለንና በልጆቹ ፊት ነግሬሃለሁ ባርዴል እስቲመለስ ድረስ አርፈህ ተቀመጥ። ለጭቅጭቅ ለድብድብ መጥተህ እንደሆን ንገረኝ። እሰማሃለሁ።» ብለው ሲቆጡት ሌዠን ደንግጦ አንገቱን አቀርቅሮ ዝም አለ።

ሙሴ ባርዴል በመስከረም ወር 1856 ዓ.ም ተመልሶ መጣ። ባርዴል ሲመጣ ቴዎድሮስ ለፈረንሳዩ ንጉሥ ሳልሳዊ ናፖሊዮን ቻርልስ ቦናፓርት ለጻፉት ደብዳቤ ከፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሙሴ ድሩይን የተጻፈውን የምላሽ ደብዳቤ ይዞ መጣ። የመጣው መልስ ቴዎድሮስን አላስደሰታቸውም።

የመጣው ደብዳቤ መልስ ባጭሩ የሚለው 1ኛ. የፈረንሳይ መንግሥት በዓለም ያሉትን ካቶሊካውያንን ሁሉ የመጠበቅ ኃላፊነት ስላለበት የእነሱን መልካም ሁኔታ ከመስማት የበለተ የሚያስደስተው ነገር ያለ መኖሩን ይገልፅና ፪ኛ ቴዎድሮስ በመጥፎ አማካሪዎች ምክር እየተገፉፉ ምንም በማያገባቸው ጉዳይ ከጎረቤቶቻቸው ኃይለኛ መንግሥት ጋር ጦርነት መጀመራቸው የማያዋጣቸው መጥፎ ነገር መሆኑን የሚገልፅ ነበር። ይህ ደብዳቤ እንኳን በዚያን ዘመን በወቅታዊው ሁኔታ ላይ ላሉት ቴዎድሮስ ይቅርና በሐሳብ ወደዚያ ዘመን ለምንሔደው ሰዎች እንኳ የፈረንሳይ መንግሥት አመላለስ የሚያናድድ ነው። ቴዎድሮስ የጠየቁት ስለ አገር እድገት ጉዳይ እንጂ ስለ ሃይማኖት የቱ ይሻላል የሚል ጥያቄ አልነበረም። ለካቶሊኩ የክርስቲያን ሃይማኖት ጋሻ ሆኜ የቆምኩ ነኝ የሚለው የፈረንሳይ መንግስት እስላም ስላጠቃኝ የሙሣሪያ እርዳታ ሰጡኝ ላሉት ለቴዎድሮስ ምን አግብቶዎት ይዋጋሉ ያገርዎንም ወሰን አርፈው ይልቀቁ የሚል መልስ መስጠቱ የሚያሳዝን ነው።

ቴዎድሮስም ቢሆኑ የዋዛ ሰው አልነበሩም። ከፈረንሳይ መንግሥት የተላከው ደብዳቤ ኤውሮፓውያኖቹ በሙሉ ባሉበት ሜዳ ላይ ጉባኤ ተደርጐ ከተነበበ በኋላ «ይህን የወዳጅነት መልስ እንው ብዬ አልቀበለውም። የፈረንሳይ መንግሥት ለጻፍኩለት ደብዳቤ ምላሽ እንዳልሰጠ አድርጌ እቆጥረዋለሁ» ብለው ደብዳቤውን ከመሬት ላይ ጣሉትና ከላዩ ላይ ቆመው እየረጋገጡ በእግራቸው አሽተው መቅደዳቸውን ሩቤንሰን ጽፎታል። ደብዳቤውን በእግራቸው አሻሽተው በላዩ እንደቆሙም ከፈረንሳይ ጋር ሊያደርጉት የወጠኑት ወዳጅነት መቅረቱን ገልፀው የጐንደሩን ጉባኤ በተኑ።


የባርዴልን መመለስ በናፍቆት ይጠባበቅ የነበረው ሌዣን ከቴዎድሮስ ዘንድ በሌላ ቀርቦ ወዳገሩ ለመመለስ እንዲፈቅዱለት ጠየቁ አጤ ቴዎድሮስም «ባርዴል አይመጣም ውሽታም ሰው ነው ብለኸኝ ነበረ። አሁን እሱ ስለመጣ ውሽታምና ቀጣፊው አንተ መሆንህን አወቅሁ። በአገሬ ደግሞ ብዙ ውሽታሞች ስላሉ እነሱ ይበቁኛል አንተ ካገሬ ውጣልኝ» ብለው ወቅሰው ወደ አገሩ እንዲሔድ ፈቀዱለት። ሌዣንም ከኢትዮጵያ ወሰን ሲደርስ ከንጉሱ እጅ ማምለጡን ስላወቀ መጥፎ የስድብ ደብዳቤ ፅፎ ለቴዎድሮስ ላከላቸው። ይህም የስድብ ደብዳቤ ቴዎድሮስ በኤሮፓውያን ላይ የነበራቸውን ጥላቻ እያበዛው ሔደ።

ቴዎድሮስ ኤሮፓውያኖችን እንዲጠሉ ያደረጋቸው እነኝህ ምክንያቶች ብቻ አይደሉም። የዶክተር እስተርንና የአቶ ሮዚንታልም ጉዳይ አለበት። ሮዚንታል ለወንድሙ በጻፈው ደብዳቤ «ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ጨካኝ ንጉሥ ከሚገዙ ይልቅ በባዕድ በግብጾች ቢገዙ ይሻላል» የሚል አስተያየቱን ጽፎለት ደብዳቤው ተያዘ። ደብዳቤው አቶ ሣሙኤል ጊዮርጊስና አቶ ብሩ ጴጥሮስ ለቴዎድሮስ ተርጉመው ስድባቸውን አሰሙዋቸው።

ሚስዮናዊው እስተርን በሃይማኖት ስብከት ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ጐንደር አጠገብ ካሉት ፈላሻዎች ዘንድ ከርሞ አገሩ ሲመለስ ዎንደሪንግ አሞንግ ዘ ፈላሻስ ኦፍ አቢሲኒያ በሚል ርእስ አንድ መጽሐፍ አሳተመ። በመጽሐፉ ውስጥ ባለፈው ገጽ እንዳልኩት ቴዎድሮስን የሚሰድቡ ቃላት አሉበት።

እስተርን ይህን መጽሐፉን ካሳተመ በኋላ እንደገና ተመልሶ ወደ ኢትዮጵያ መጣ። በሰላም በመኖር ላይ እያለ ካሽከሮቹ ጋር በተፈጠረው ያለመግባባት ተከሶ ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ቀረበ። በዚያም በሙግት ላይ እንዳሉ እንደ ዎልድሜየር አጻጻፍ በንዴት በንጉሱ ፊት አሽከሮቹን ስለተማታ ንጉሱን ደፈረ ተብሎ እንዲታሠር ተደረገ። በታሠረ በማግስቱ ሙሴ ባርዴልን አስጠርቶ «ዎንደሪንግ አሞንግ ዘ ፈላሻስ ኦፍ አቢሲኒያ የተባለው መጽሐፍ ከሣጥኔ ውስጥ ስላለ እባክህ አምጣልኝ። ይህ መጽሐፍ በእምኖሩ የተገኘበት እንደሆነ ብዬ ፈርቻለሁ። ምናልባት በንጉሱ የተገኘብኝ እንደሆነ ንጉሱን የሚያስደስት ነገር አለበት ብሎ አጫወተውና ሰውሮ እንዲያመጣለት ለመነው።

ባርዴል በተለመነው መሠረት መጽሐፉን ከደራሲው ከእስተርን ሣጥን ውስጥ አውጥቶ እንደተጠየቀው ለእስተርን በመስጠት ፈንታ እያነበበ ንጉሱን ቴዎድሮስን የሚነካውን ክፍል ይተረጉም ጀመረ። ሲጨርስም ያን የተረጐመውን ስድብ ከመነጽሐፉን ለአጤ ቴዎድሮስ አቀረበው። አጤ ቴዎድሮስ ስድባቸውን ሲሰሙ እንደገና በባሰ ሁኔታ ተበሳጩ። በፈረንጆች ላይ ያላቸውም ጥላቻ በዛ። የእስተርን አጻጻፍም ባጭሩ ቴዎድሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ እንጂ የነገሥታት ዘር የሌላቸው መጥፎ ሾካካ እንደ ዱር አውሬ፥ ደም የጠማቸው መሆናቸውንና ሌላ ሌላ ሁሉ የሚገልፅ ነበር።



አጤ ቴዎድሮስ በሄነሪ እስተርን ላይ ሽጉጥ ደግነው

ይህ የእስተርን የስድብ ጽሑፍ ከደረሳቸው በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ጉዳዩ በችሎት እንዲታይ ወሰኑ። በችሎቱ እለት በሺ የሚቆጠሩ ተመልካቾችና በኢትዮጵያ ያሉ ፈረንጆች ሁሉ ቀረቡ። አጤ ቴዎድሮስም ችሎቱ ላይ «.......እናንተ የኤሮፓ ሰዎች ወደ አገሬ ስትመጡ አፍቅሬ አክብሬ እቀበላችኋለሁ። አኖራችኋለሁም። ይህንንም የማደርገው የኤሮፓ ሰዎች ሁሉ እንደምወደው እንደ ዮሐንስ ቤል እየመሰለኝ ነው። እሱ እውነት ተናጋሪ ነበር። እናንተ ግን ውሸታሞች ቀጣፊዎች ናችሁ። መልካም ሳደርግላችሁ እናንተ ግን በመጥፎ መለሳችሁልኝ። ወደ አገራችሁ በምታስተላልፉት ነገር ሁሉ እኔን የሚያጥላላ ነገር ትናገራላችሁ። ትጽፉላችሁም። በዓለም ላይ መጥፎ ስም አሰጣችሁኝ። በእኔና በእናንተ መሀልም እግዚአብሔር ፍርዱን ይስጥ» ብለው ችሎቱን አስጀመሩ።

ችሎቱ የተሰበሰበው ጐንደር ከተማ ውስጥ ከሰፊ ሜዳ ላይ ነበር። ወዲያው ክርክሩ ከተሰማ በኋላ ሊቃውንቶቹ ፍትሐ ነገሥቱ ምን እንደሚል

እንዲያነቡ ተጠየቁ። ፍትሐ ነገሥቱ ከተነበበ በኋላ ችሎቱ በአንድ ድምፅ አቶ እስተርንና አቶ ሮዜንታል በስቅላት እንዲቀጡ ፈረደ። ወዲያውም የመስቀያቸው እንጨት ተሰቃዮች እየተመለከቱ ይዘጋጁ ጀመር።

አጤ ቴዎድሮስ የሚወዱትና የሚያከብሩት ሚስዮናዊው አቶ ዎልድሜየር በኀዘንና በትካዜ ወደ ንጉሱ ዘንድ ተንበርክኮ እያለቀ ምሕረት እንዲደረግላቸው ንጉሱን ለመነ። ቴዎድሮስም የዎልድሜየርን እጅ ይዘው ከተንበረከከበት አስነሱትና «አይዞህ አትፍራ ወዳጅጄ። ላንተና ለዮሐንስ ቤል ስል አልገድላቸውም።.......አንተ ወዳጄ ነህ። ይህቺን ጣቴን እንኳን ቆርጠህ ስጠኝ ብትለኝ እሰጥሃለሁ። ምክንያቱም እውነተኛ ሰው ነህና እወድሃለሁ።» አሉት።

ከዚህ በኋላ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ሰዎች ፍርዱ እበስራት ተውለጠባቸው አቶ እስተርንና አቶ ሮዜንታል ወዲያውኑ በግር ብረት ታሠሩ። ቴዎድሮስ በኤሮፓውያን ላይ የነበራቸው ፍቅርና አክብሮት ተሟጦ ስለነበረ ቂም የያዙባቸውን ፈረንጆች ሁሉ እንዲታሰሩ አደረጉ። ማርቲን ፍላድ እስቲገር እና ብራንዲስ ወዲያውኑ በሰንሰለት ታሰሩ።

ጥቂት ቀደም ብለን እንዳነበብነው ቴዎድሮስ የጐንደሩን ችሎት ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር «ወደ አገራቸው በምታስተላልፉት ነገር ሁሉ እኔን የሚያጥላላ ነገር ትናገራለች።.......» ያልቱ እንዲያው ከልባቸው አቅንተው ወይም ሳይሆን አይቀርም በሚል አስተሳሰብ አይደለም። ምፅዋ ይኖሩ የነበሩት ሚስዮናዊ አባ (ፓድሬ) ደልሞ የተባሉ ሰው የእንግሊዝና የፈረንሳይ ጋዜጦች ስለ ኢትዮጵያ ስለ ቴዎድሮስ የሚፅፉትን ሁሉ ጋዜጣውን ለቴዎድሮስ ይልኩ ነበር። ለአጤ ቴዎድሮስም ጋዜጣውን እየተረጐመ ያሚያነብላቸው ባርዴል ስለ ነበረ ሁሉንም ነገር አጣርተው ያውቁታል።

በካሜሮን እጅ የተላከው ደብዳቤ ዓመት ካለፈው በኋላ በ1856 ዓ.ም ኬራስን የተባለ የአይርሽ ሰው ለካሜሮን ከእንግሊዝ መንግሥት የተጻፈውን ደብዳቤ ይዞ ጥቅምት 21 ቀን ጐንደር ገባ። ቴዎድሮስም የደብዳቤያቸው መልስ መጥቶ እንደሆነ ቢጠይቁም የእሳቸው ደብዳቤ መልስ ያለመምጣቱን አስረዳ። ኬራንስ ይዞ የመጣው ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለካሜሮን የተፃፈለት ትእዛዝ ነበር።

ደብዳቤውም «.......በመሀል ኢትዮጵያ የግርማዊት ንግሥት መኪል ሆነው ብትቀመጥ ምንም የሚጠቅም ነገር የለም። ወደ ነበርክበት ወደ ምፅዋ ብትመለስ ግን የተሻለና የበለጠ ሥራ መሥራት ትችላለህ።........ይህንንም ፈጥነህ አድርግ። ሌላ ትእዛዝ እስኪመጣልህ ድረስም በምፅዋ እንድትቆይ.......» የሚል ነበር። በሩቅ ላለው ለእንግሊዝ መንግሥት ጉዳይ ቀላል መስሎ ቢታየውም በቅርብ ላለው ለካሜሮን ግን ይህን ትእዛዝ ተቀብሎ ለቴዎድሮስ ማሳወቅ ጭንቁ ነበር።

ካሜሮን ከዚህ በፊት ከአገሩ በደረሰው ትእዛዝ መሠረት ሱዳን ውስጥ ገብቶ በመሰንበቱ ቴዎድሮስ ከጠላቶቹ ከደርቡሾች ጋር ቆየህ በማለት ከፉኛ ቂም ይዘውበታል። አሁን ደግሞ ቱርኮች ከኢትዮጵያ አስለቅቀው ወደ ያዙት ወደ ያዙት ምፅዋ ለመሔድ ከቴዎድሮስ ፈቃድ መጠየቅ በሕይወቱ ላይ መፍረድ ነበር። ካሜሮን ይህ ሁሉ በማመዛዘንና በመፍራት የመንግሥቱን ትእዛዝ ቸል ብሎ ቆየ። የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግን እየደጋገመ ትእዛዙን አስተላለፈለት።

ያሁኑ ጊዜ ደግሞ ቴዎድሮስን ያናና ጥሩ ጊዜ አልነበረም። ግብጾች ከፈረንሳዮች ጋር ተባብረው በሱዳን በኩል ወደ ኢትዮጵያ ለመዝመት የመዘጋጀታቸው ወሬ ይወራ ነበር። ወሬም ብቻ ሳይሆን ኮንት ራውል ዱ. ቢሶን ከሱዳን ወይም ከኢትዮጵያ የጥጥ መትከያ መሬት እንድፈልግ ታዛዥ መጥቻለሁ እያለ ካርቱም ገብቷል። ከእሱም ጋር 400 ጠመንጃና አራት መድፎች ያለው የፈረንሳይ ጦር ሠራዊት ሠራዊት አጅቦታል። «......በሱዳን ውስጥ የጥጥ መትከያ ሰፊ መሬት የማይገኝ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውስጥ ገብቼ እንድፈልግና እንድይዝ ከፈረንሳይ መንግሥታት ታዝዠ ነው የመጣሁት......» እያለ ለጋዜጠኞች ተናግሮ ታትሟል። ቴዎድሮስም ይህን ሰምተዋል። በዚሁ አጣብቂኝ መሀል የገባው ካሜሮን ታህሳስ 24 ቀን 1857 ዓ.ም ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርቦ ወደ ምፅዋ እንዲዛወር መታዘዙን አስረዳ። አጤ ቴዎድሮስም ይህን ሲሰሙ ተበሳጭተው መላው የኤሮፓ ሠራዊት በእሳቸው ላይ መነኮሳቱን ተገንዝበው እሰርልኝ በለው ካሜሮንን አሠሩ። ካሜሮንን ብቻ ሳይሆን ፈረንጅ የተባለውን ዘር ሁሉ እሰርልኝ ብለው ከኢትዮጵያውያን ሴቶች የተወለዱትን የፈረንጅ ዘሮች ሁሉ አሳሰሩ።

የእነኝህ የኤሮፓውያን መታሠር ወሬው ኤደን ተሰማ። በኤደን የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት የፖለቲካ ኃላፊ የሆነው ኮሎኔል ሜልዌዘር የዜጎችን መታሰር እንደሰማ ለቴዎድሮስ ደብዳቤ መልሱ በአስቸኳይ እንዲሰጥ ሲል የበኩሉን አስተያየት ጨምሮ ወደ እንግሊዝ አገር ላከ። የእንግሊዝ መንግሥት ግን በቴዎድሮስ ድፍረት ቢገረምም ለደብዳቤያቸው መልስ መስጠት ግን ውርደት መሆኑ ተገነዘበ። የደብዳቤያቸውን መልስ ሰጥቶ ጉዳዩን በሰላም በመጨረስ ፈንታ ግብፅ ያለው የእንግሊዝ ዋና ቆንሲል የታሠሩትን ኤውሮፓውያንንና ካሜሮንን እንዲያስፈታ ትእዛዝ አሳለፈ።

ግብፅ አገር ባለው ቆንሲል በኩል እስረኞቹን ለማስፈታት የማይቻል መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ እስረኞቹን ለማስመለጥ እንዲሞከር ሰላዮች ወደ ኢትዮጵያ ተልከው ገቡ። ሰላዮቹም ከካሜሮን ጋር ባደረጉት የምስጢር ግንኙነት ካሜሮን «......ለንጉሡ ደብዳቤ መልስ ካልተሰጠ በቀር የእኔ አምልጦ ከእስር መውጣት የማይታሰብም የማይሞከርም ነው.......» በማለት ለመልዕክተኞቹ እምልስ መስጠቱን አላን ሙርሄድ ጽፎታል። ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሰላይ አስመላጮች የአገሪቱንና የእስረኞቹን ሁኔታ አጥንተው ወደ አገራቸው ተመለሱ። እነሱም እስረኞቹ ያሉት በመሀል ኢትዮጵያ ስለሆነ ለማስመለጥ የማይቻል መሆኑን በሪፖርታቸው አሳወቁ።

ሌላ ምርጫ እንዲሞከር ታሰበ። ሌላውም ምርጫ የቴዎድሮስን መንግሥት ማስገልበጥ ነበር። በዚህም እንዲሞከር ተወሰነ። ቴዎድሮስ በጭካኔያቸው ሕዝብ የጠላቸው መሪ በመሆናቸው አንድ ገልባጭ ኃይል ቢነሳ ሕዝቡ እንደሚከዳቸው ተጠንቶ ተረጋገጠ፥ ለዚህም ግልበጣ ተግባር በጊዜው ኃይል ያላቸውና ለዳርቻውም ቅርብ የሆኑት በኋላ አጤ ዮሐንስ ተብለው የነገሡት የትግራዩ ካሣ በእንግሊዞች ተመረጡ።

ካሣ ከቴዎድሮስ ጋር ጠበኛ በመሆናቸው ትግራይን በአዋጅ ነፃ አውጥተው በቴዎድሮስ ላይ ሸፍተዋል። ግዛታቸው፣ ከመረብ እስከ ተከዜ ሆኖ መቀመጫ ዋና ከተማቸው አድዋ ላይ ነበር። የእንግሊዝ መልክተኞች በሚስጥር ገብተው ከካሣ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ እንግሊዞች ያልጠረጠሩዋቸውና ያላሰቧቸው ጣሰው ጐበዜ ተነስተው ዋልድባን ወልቃይትን አርማጨሆን ወገራንና ሰሜንን ያዙ። የጣሰው ጐበዜ አነሳስም ለትግራዩ ካሣ ጭምር የሚያሰጋ ሆነ። የሸዋው ምኒልክም ሥልጣን ለኔ እንጂ

ለጣሰውም ለካሳም አይገባም ማለታቸው ተሰማ። በዚህ ምክንያት ግራ የገባው የእንግሊዝ መንግሥት የማስገልበጡን ነገር ትቶ ሌላ ዘዴ መፈለግ ያዘ።

የእንግሊዝ መንግሥት ያደረገው ሙከራ ሁሉ የማይጠቅም መሆኑን ከተገነዘበ በኋላ ጉዳዩን ካፒቴን እስፒዲ እና ኮሎኔል ሜርዌዘር እንዲያጠኑ አዘዙ። እነሱም ባጠኑት ጥናት እስረኞቹን ለማስለቀቅ የሚያዋጣው ቴዎድሮስ ለጻፉት ደብዳቤ ምላሹን በንግሥቲቱ ፊርማ መመለስ ብቻ መሆኑን አስረዳ። ከዚህ በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት እስረኞቹ እንዲለቀቁ በንግሥቲቱ ስም የልመና ደብዳቤ እንዲጻፍ ተወሰነ።

ለአጤ ቴዎድሮስ የሚላከው የንግሥት ቪክቶሪያ ደብዳቤ ሜይ 26 ቀን 1864 ዓ.ም ወይም በኛ አቆጣጠር ግንቦት 17 ቀን 1856 ዓ.ም ተጻፈ። ደብዳቤውንም የሚወስድ ሰው ሲመረጥ ቆይቶ በመጨረሻው ሆርሙዝ ራሳም እንዲላክ ጉባኤው ተስማማ። ራሳም የተመረጠበት ምክንያት አንድ ንፁህ እንግሊዛዊ ወደ ቴዎድሮስ መላክ ክብር እንደሚዋረድ ተቆጥሮ በዜግነት እንጂ በትውልድ እንግሊዛዊ ያልሆነ ሰው ይፈለግ በተባለው ውሳኔ መሠረት ነበር።

ራሳም ትውልዱ አረባዊ ነው። የተወለደውም ሶሪያ ውስጥ ከሚኖሩ ክርስትያን ቤተሰቦች ነው። ለትምህርት ወደ እንግሊዝ አገር ሔዶ በዚያ ከኦክስፎርድ ትምህርት ቤት አርኪዎሎጂ ተማረ። ትምህርቱን እንደ ጨረሰ ዜግነቱን ለውጦ እንግሊዛዊ ሆነ።

ከራሳም ጋርም ዶክተር ኸንሪ ብላንክ እና ከቦምቤይ ጦር ሠራዊት መቶ አለቃ ፕሪዲውክስ አብረውት እንዲሔዱ ታዘዘ። ዶክተር ብላክን የታዘዘበት ዋናው ምክንያት በኢትዮጵያ ያሉትን እስረኞች ጤንነት እንዲመረምርና እንዲያክም ተብሎ ነው። ኤደን ያለ ሜርዌዘርም በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ እንዲረዳቸው ታዘዘ። መልክተኞቹም ከእንግሊዝ አገር ወደ ኤደን ሔዱ። ከኤደንም በጀልባ ተሳፈው በሐምሌ ወር 1856 ዓ.ም ምፅዋ ገቡ።

# ምዕራፍ ፲፩

# የራሳም መልዕክተኛነት

በሚስተር ራሳም የሚመሩት የእንግሊዝ መልክተኞች ምፅዋ ከደረሱ በኋላ ብላንክ ስለነበረው ሁኔታ በመጽሐፉ ሲገልጥ «.......ንጉሠ ነገሥቱን ለማግኘት የጓጉለትንና ሰዎቹንም ለማሠር ምክንያት የሆነውን የንግሥቲቱን ደብዳቤ ለማድትርድ የነበረው ትረት ብርቱ ነበር። የአበሻው ንጉሠ ነገሥት ለእንግሊዝ ንግሥት ልከውት ልከውት ለነበረው ደብዳቤ መልስ የያዙ መልክተኞች ምፅዋ መግባታቸውን ለግርማዊነታቸው የሚያስታውቁ መልክተኞች ለማግኘት ምፅዋ በደረስንበት ቀን ወዲያውኑ ሙከራ ጀመርን። ነገር ግን የአጤ ቴዎድሮስን ስምና ዝና የሰማ ሁሉ ፈጽሞ የሚሸበር ስለሆነ ለዚህ ተግባራዊ የምናውላቸው ሰዎች ለማግኘት ከፍ ያለ ችግር ገጠመን። ብዙ የገንዘብ ስጦታ እንከፍላለን በማለት ተስፋ ሰጥተን ማግኘት ቻልን......» ይላል። ትርጉም አቶ ዳኘው ወልደ ሥላሴ።

ራሳም በጻፈው መጽሐፍ ላይ እንደሚገልጠው ለቴዎድሮስ የተጻፈው ደብዳቤ በአረብኛ ፊደልና ቋንቋ ነበር። ደብዳቤውም «.......እናንት ከዚህ ወደብ መድረሱን ለግርማዊነትዎ ላስታውቅ ክብር ይሰማኛል። የመጣሁትም ግርማዊነት የእንግሊዝ ንግሥት ለግርማዊነትዎ የጻፉትን ደብዳቤ ለማድረስ ነው። ይህንንም ያመጣሁትን ደብዳቤ በእጅዎ ለመስጠት እችል ዘንድ መልስዎን እጠባበቃለሁ።

«......ክብር አግኝቼ እርስዎን ለማየትና ከታላቁ ችሎትዎ ለመቆም በጉጉት እጠብቃለሁ። በዚህም ምክንያት ከከተማዎ የሚያደርሰኝ አጃቢ እንዲላክልኝ ፈቃድዎን እጠይቃለሁ። የዝናሙ ወራት ደርሶ መንገዱ አስቸጋሪ ከመሆኑ በፊት ፈቃድዎ ይፈጸምልኛል ብዬ እመኛለሁ። ቆንሲል ካሜሩንንና ሌሎቹንም እስረኞች በፈቃድዎ ፈትተው እዚሁ ቦታ ድረስ እንደሚልኩልኝ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ።

«ይህ ከሆነም ግርማዊነትዎ የሚመኙትን ምኞት ሁሉ የሚያስፈጽም አንድ የመልዕክተኛ ቡድንዎ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲሔድ እናደርጋለን። ንግሥታችንም መልዕክተኛዎን ለመቀበል ደስተኛና ፈቃደኛ ናቸው። ወደ

ኤደን ከመመለሴ በፊትም ይህ የሚላከው ቡድን ቢመጣ እንግሊዝ አገር በኔ ጠባቂነትና ኃላፊነት አደርሳለሁ። ከዚህም ደብዳቤ ጋር ሶስት ደብዳቤዎችን ልኬአለሁ። አንደኛው ከግብፅ የኮፕት ፓትርያርክ ለግርማዊነትዎ የተጻፍ ነው። ሁለቱ ግን ለኢትዮጵያው ጳጳስ ለአቡነ ሰላማ የተላኩ አንቸው። ......ለነዚህም የሚሆን መልስ ቢልኩ እኔ ተርጉሜ በየአድራሻው ለማድረስ እችላለሁ። ግርማዊነትዎ በመልስዎ እንደሚያስደስቱኝ ተስፋ አለኝ።......» የሚል ነው።

ሚስተር ራሳም ለአጤ ቴዎድሮስ የጻፈውን ይህን ደብዳቤና ለእስረኛው ለካሜሩን ስንቅ የሚሆን ገንዘብ ጨምሮ ላከና ምላሽ እስኪመጣ ምፅዋ ሆነው ይጠባበቁ ጀመር። የደብዳቤው ምላሽ ሳይመጣ በመዘግየቱ መልክተኛው በሽፍታ ተገድሎ ወይም ተወርሶ ይሆናል ተብሎ ስለታሰበ ለሁለተኛ ጊዜ ኦክቶበር 17 (በኛ ጥቅምት 7) ቀን አሁንም በአረብኛ ቋንቋ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፈ።

«......እዚህ ከደረስኩ አሁን ሶስት ወር ገደማ እንደሆነኝ በግርማዊነትዎ ይታወቅልኝ። የመጣሁትም ከታላቋ የእንግሊዝ ንግሥት ለግርማዊነትዎ ለተላከው ደብዳቤ ለማድረስ ነው። እዚህ እንደደረስኩም ይህንኑ ለግርማዊነትዎ የሚያስታውቅ ደብዳቤ ጽፌ በሁለት መልክተኞች ልኬ ነበር። መልክተኞቹም መሐመድ አባዋስ እና መሐመድ ስኡድ ይባላሉ። እስካሁን ድረስ ግን አንዳችም መልስ አላገኘሁም።

«እዚህ ስለቆየሁበት ምክንያት በየቀኑ የተለያዩ ወሬዎችን እሰማለሁ። አንዳንዱ ወሬ መልክተኞቹ ከእርስዎ ዘንድ ባይደርሱ ነው ይሉኛል። ይኸውም በመንገድ ላይ ከእርስዎ ዘንድ እንዳይደርሱ የሚያደርጉ አስቸጋሪ ሰዎች እንዳሉ ይነግሩኛል። አንዳንዱም ውሬ ደብዳቤው ለሌሎች ሰዎች ተሰጥቶ እነኛ ሰዎች ለግርማዊነትዎ ሳያደርሱት ጥለውት ይሆናል የሚል አለ። በእነዚህ ምክንያቶች አሁን እንደገና ይህን ደብዳቤ ጻፍኩልዎ። ከዚህም ጋር ከዚህ በፊት ጽፌልዎት የነበረውን ደብዳቤ አልደረሰዎት ይሆናል ብዬ ግልባጭ ጨምሬ ልኬአለሁ።


«ናአብ መሐመድ ቢን አብዱልራህማን ለግርማዊነትዎ ታማኝ ወዳጅ መሆኑን ስለነገረኝ ይህን ደብዳቤ በእርሱ በኩል ላኩልዎት።......እርሱም በደህናና በሰላም እንደሚያደርስልዎ ተስፋ አለኝ። መልሱን በቶሎ በመላክ

እንዲያከብሩኝ እለምንዎታለሁ። ከእንግሊዝ መንግሥት ለተላኩበት መልዕትም የግርማዊነትዎ አስተያየት ምን እንደሆነ ባውቅ ደስ ይለኛል። በሁሉም ነገር የግርማዊነትዎ ፍጹም ታዛዥ ነኝ......»

ራሳም ይህን ደብዳቤ ከጻፈ በኋላ ለኤሮፓውያኖቹም ደብዳቤ ጽፎ ነበር። እንግሊዛውያኖቹ ሳይሆኑ ሌሎቹ የተያዙት ኤሮፓውያኖች ምን ዓይነት ቋንቋ ይናገሩ እንደሆነ ስላልታወቀ እነራሳም በእንግሊዝኛ በፈረንሳዊኛና በጀርመንኛ ቋንቋዎች ደብዳቤ ጽፈው እስረኞችን ለማስፈታት የሚቻልበትን የተሻለ መንገድ እንዲያማክሩዋቸው ጠየቁ።

ሁለተኛው ደብዳቤ ቢሆን ውጤት አልነበረውም። በምፅዋ ሐሩር ይቃጠል የነበረው ብላንክ «......የተላኩት ሰዎች ከልዩ ልዩ ክፍል ከተራው ወገን ከናይብ ተከታዮችና የንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ አሽከርና ዘመድ የተባለ ሰው ሁሉ ቢሆንም ውጤቱ እንደ ሆነ። ችግሩ ከንጉሠ ነገሥቱ መልስ መምጣቱ ሳይሆን አንዳቸውም ሳይመለሱ መቅረታቸው ነበር።........» ይላል። በዚህም ምክንያት እንደገና ለሶስተኛ ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ደብዳቤ ጻፈ። ራሳም ሶስተኛውን ደብዳቤ በእንግሊዝኛ የጻፈበት ምክንያት በአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ እንግሊዝኛና አማርኛ የሚያውቁ ኤሮፓውያንና ኢትዮጵያውያንም መኖራቸውን ስለሰማ ነው። ይህን ሶስተኛውን ደብዳቤ የላከው ኢብራሂም በተባለ ሰው እጅ ነበር። ኢብራሂም የተመረጠበትም የንጉሱ ባለሟል የሳሙኤል ወንድም ነኝ ብሎ ተናገረ ነበር። ማርች 30 በኛ መጋቢት 21 ቀን የተጻፈው ሶስተኛው ደብዳቤም እንደሚከተለው ይላል።

«.......ግርማዊነትዎ እስረኞቹን ይቅርታ አድርገውላቸው በነፃ እንደሚለቋቸው በዚህ ለሶስተኛ ጊዜ በጻፍኩልዎት ደብዳቤ ስገልጽልዎ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል። ከስምት ወሮች በፊት በጻፍኩልዎ ደብዳቤ ከእንግሊዝ መንግሥት የተጻፈልዎትን ደብዳቤ ለማድረስ ተልኬ መምጣቴን ገልጬ ነበር። ሶስት ወር ሙሉ መልሱን ስጠብቅን ቆየሁ በኋላ የመጀመሪያዎቹ ሁለት መልክተኞች ባያደርሱልኝ ይሆናል በማለት እንደገና በሐረርጌው ናኢብ በኩል ጽፌ ልኬ ነበር።



ናአቤ ሐሰን

«ለመጀመሪያውም ሆነ ለሁለተኛው ጊዜ ለጻፍኩልዎ ደብዳቤ እስከአሁን መልስ አላገኘሁም። እንደማስበውና እንደምገምተውም ሁለቱም ደብዳቤዎች እንደደረሰዎት አድርጌ ነው። ነገር ግን የእርስዎ ዝም ማለት እኔን በጣም አሳስቦኛል።

«ለግርማዊነትዎ ለመግለጽ የምወደው የመጣሁበት ዋና ተግባር ከንግሥታችን የተጻፈልዎትን ደብዳቤ ለግርማዊነትዎ ለማድረስ ነው። ይህን ደብዳቤ ለእርስዎ ከማቅረብ ሌላ የማደረገው ምንም ነገር የለም።........

«ክፉ አሳቢ ሰዎች የእንግሊዝና የኢትዮጵያ መንግሥት በመልካም ወዳጅነት እንዳይገናኙ ስለሚመኙ የተላኩበት ሥራ እንዳይሳካ የሚያደርጉ አሉ። የእንግሊዝ መንግሥት የጠበቀ ወዳጅነት እንደሚፈልግ አረጋግጥልዎታለሁ። በሁለቱም መንግሥታት መሀል የሚደነቀረውን መሰናከል እያስወገድን መልካም ግንኙነት እንዲኖረን እንጥራለን።

«የመዘግየቱ ጉዳይ የበለጠ እያሳሰበኝና እያስጨነቀኝ ሔደ። ምክንያቱም ለላከኝ መንግሥት ምን መልስ ልመልስ እያልኩ ነው። ሌላው ደግሞ የዝናቡ ወራት አሁን መቃረቡ ነው። ስለዚህ ግርማዊነትዎ ፈቃድዎ ሆኖ መልስ ፈጥነው ካላኩልኝ ወደ ሥራ ቦታዬ ወደ ኤደን ለመመለስ የምገደድ መሆኔን እገልጣለሁ።

አጤ ቴዎድሮስ የሚጻፉላቸው ደብዳቤዎች ሳይደርሳቸው ቀርተው ሳይሆን ሁሉም ደርሶዋቸዋል። መልሱን ፈጥነው ለመስጠት ግን የእሳቸው ደብዳቤ መልስ እንደተናቀ እሳቸውም የንግሥቷን ደብዳቤ በመናቅ ብድር ለመመለስ ብለው ነው። ለራሳም ደብዳቤ መልስ መከልከል ብቻ ሳይሆን የተላኩት መልክተኞች እንኳ ተመልሰው እንዲሔዱ አልፈቀዱላቸውም ነበር።

ከመልዕክተኞቹ አንዱ አቶ ወልደ ማርያም የሚባለው ከመቅደላ ተመልሶ ምፅዋ ገባ። ከእሱም ጋር በመቅደላ የታሠሩት የትግራይ እስረኛ የደጃች መርድ ሁለት አሽከሮች አብረውት መጡ። ነኝህም ሰዎች ከቴዎድሮስ የተጻፈ ደብዳቤ ባይዙም ከቆንሲሉ ከካሜሩንና ከወንጌላዊው እስተርን የተጻፈ ደብዳቤዎች ይዘው መጡ። ካሜሩን ለራሳም በጻፈው ደብዳቤ «......ምክሬ ልለግስህ የተከበርከው ራሳም ሆይ...... ይህን ነገር ከመፍትሔ ለማድረስህ የተከብርከው ራሳም ሆይ...... ይህን ነገር ከመፍትሔ ለማድረስ ጠንከር ያለ ደብዳቤና ተግባር ያስፈልጋል። እንዳሁኑ ያለው ልመና አያዋጣም። እርግጥ ይህ ይደረግ ብለን መንግሥታችንን መጫን እንደማይገባን እናውቃለን። የእንግሊዝ መንግሥት ጥቅምና የአገሪቱ ደህንነት በቅድሚያ ትኩረቱ የሚገባ ነው።

«......እሳቸው ነገሩ በሰላም እንዲያልቅ ይፈልጋል። ግን እንዴት እንደሚሆን አያውቁም። እባክህ ስለ እግዚአብሔር ብለህ ወደዚህ እንዳትመጣ። እንደሚያስሩህ እርግጠኛ ነኝ። እንደሚያስቡት እኛ በእጃችን እስካለን ድረስ ምንም ጥቃት እንደማይደርስባቸው ይገምታሉ። እንዳንተ ያለው ደግሞ ሲጨመርላቸው ለእሳቸው የበለጠ መልካም ነገር የሚሆንላቸው ይመስላቸዋል። እንደ እሳቸው አስተያየት ማለቴ ነው።.......» የሚሉ አረፍተ ነገሮች ነበሩበት።

ራሳም እነኝህን ከመቅደላ የመጡትን ሰዎች ስለ ቴዎድሮስ ሁኔታና ስለ እስረኞቹ ይዞታ ሲጠይቃቸው ንጉሡ የውጥር መያዛቸውን ነገሩት። ሸዋ ዘምተው ሲመለሱ ወታደራቸው በረሃብና በበሽታ እንደተጐዳባቸው፤ የወሎ ሰዎች ሸፍተው ማስቸገራቸውን የወልቃይቱ ጣሰው ጐበዜ ዋናው ከተማ ጐንደርን መያዙን ምስራቃዊው አውራጃ ላስታ አገውና ተምቤን እስከ ትግሬ ድረስ በዋግዙም ጐበዜ እጅ መሆኑን ዋግዙም ጐበዜም ለቴዎድሮስ ዋና ጠላታቸው መሆኑን ሁሉ ነገሩት።

ከራስም ዘንድ እየተላኩ የሔዱት ሰዎች ሁሉ ለምን መልስ ይዘው አልመጡም? ለምንስ በዚያው ይቀራሉ? እነኝን የመሳሰሉ የአንባቢ ጥያቄዎች ይኖራሉ። ለእነኝህ መልስ መጠነኛ ማብራሪያ የሚሰጠን የመሐመስ ሰይድ ደብዳቤ ነው። መሐመድ ሰይድ ሐምሌ 17 ቀን 1856 ዓ.ም የመጀመሪያዋን የሚስተር ራሳምን ደብዳቤ ለአጤ ቴዎድሮስ ለማድረስ የተላከ መልዕክተኛ ነው። መሐመድ ሰይድ የቆየበትን ምክንያት ሪፖርት እንዲያቀርብ ራሳም ባዘዘው መሠረት የጻፈው ደብዳቤ (ሪፖርት) እንዲህ ይላል።

«.......እኔና ጓደኛዬ መሐመድ አባዋሶ ወደ አበሻው ንጉሥ ዘንድ ተልከን በ16 ቀናችን ደረስን። ጐንደር እንደደረስን ወዲያውኑ ደብዳቤውን ለንጉሱ በእጃችን ሰጠን። እሳቸውም ደብዳቤውን ከማንበባቸው በፊት «ይሄን ደብዳቤ የሰጣቸው ባሻ የሚባለው ምን ዓይነት ሰው ነው? አብረውትስ ወታደሮች አሉ? ብለው ጠየቁን። ምንም የለም ብለን መለስንላቸው። ደብዳቤው እንዲነበብ አረብኛ ማንበብ የሚያውቅ እንዲጠራ አዘዙ ሌላ ሰው ደግሞ ጠርተው ለኛ ምግብና ማረፊያ እንዲሰጠን አዘዙት።

«በማግሥቱ መልክተኛ ልከው አስጠሩን። እንደረስንም ይህን ወረቀት የሰጣቸው ሰው ወደዚህ ለመምጣት የሚፈልግ ነው? ብለው ጠየቁን። እኛም አዎን ወደዚህ ለመምጣት በጉጉት ይጠባእብቃል ብለን ነገርን። እሳቸውም በአርባ ቀናት ውስጥ መልሱን ይዛችሁ ትሔዳላችሁ። አሁን ሂዱና ጠብቁ ብለው ንጉሱ አሰናበቱን። በሣሙኤል በኩል መልዕክተኛ ተልኮ መልሱን እስቲነግረን ድረስ ሳንፈራ እንድንቆይ ተነገረን።

ከሁለት ወር በኋላ ወደ ደብረ ታቦር ሔዱ። ኤሮፓውያን ሁሉ ተሰብስበው ቆንሲል ካሜሩንንና ሌሎችንም እስረኞች እንዲፈቱ

ለመኑዋቸው። ንጉሱም ነገ ኑ ብለው መለሱላቸው። ማታውኑ መልክተኛ ልከው ልመናቸውን እስቲፈጸም ድረስ ከፊታቸው እንዳይቀርቡ አስነገሩዋቸው። እኛም ሣሙኤል እንደገና ወደ ንጉሱ እንዲያቀርበን ጠየቅነው። ወደ ምፅዋ ለመመለስ አስበን ነበርና ነው። የኛ ሥራ ደብዳቤውን አምጥተን መስጠታ መልሱን ይዘን መመለስ ነው አልነው። በማግስቱ ወደ ንጉሱ ድንኳን ተወሰድን። ወደ ድንኳኑ ከመግባታችን በፊት ሣሙኤል መጥቶ ጥቂት ቆዩ ብለዋቸዋል ብሎ ነገረን።

«ከሐረር ጊዮ ናአቢ የተላኩት የእርስዎን ደብዳቤ የያዙት ሌላዎቹ መልዕክተኞች መቅደላ መድረሳቸውን ሰማን። የያዙትንም ደብዳቤዎች ተቀብለው ከተነበበና ጉዳዩን ከሰሙት በኋላ መልዕክተኞቹ ከኛ ጋር እንዲቀላቀሉ ታዘው እኛ ወዳለንበት ሠፈር መጡ።

«ንጉሱ እኛን ያኖሩን ልክ የእሳቸውን ተከታዮች እንደሚይዙት ነበር። የሚያስፈልገንን ሁሉ እየጠየቅን በየጊዜው ይሟላልናል። ይህም በጦርነት ላይ ከሚውሉበት ቀን በስተቀር ነው። የጐንደሩ ነጋዴ ወልደ ሥላሴ ጐበዜ በሐምሌ ወር መጀመሪያ ገደማ ከምፅዋ መጣ። ከንጉሡ ዘንድ ቀርቦም ሰለኛ መቆየት አመለከተልን። እሱም ከእርሶ ጋር መገናኘቱን ገልጾ የዘገዩት የሚሰጣቸውን መልስ ሲጠብቁ ነውና ሲሆን መልሱን ይዘው ያለዚያም እንደዚሁ እንዲሔዱ ቢደረግ መልካም ነው አላቸው። ይህን በሚናገርበት ጊዜ ጓደኛዬ መሐመድ አባዋሶ ከዚያው ቆሞ ነበር። ንጉሱም ፈጥነው እንደሚመልሱን ተስፋ ሰጥተዋል ተብሎናል።




ኢሚር አብዱላሂ

«ሰኔ 27 ረቡዕ ዕለት ኢብራሂምና መሐመድ ሺሃዊ ሶስተኛውን የእርስዎን ደብዳቤ ይዘው መጡ። በማግስቱ ሁላችንም ከንጉሱ ዘንድ ተጠራን። ያንጊዜ በመቅደላ ምሽግ ነበሩ። እዚያም እንደደረስን ወደ ምፅዋ ለመመለስ ዝግጅት እንድናደርግ ተነገረን። በዚያን ቦታ የንጉሱን የአማርኛና የአረብኛ ፀሐፊዎቻቸውን አየናቸው። ሙአሊም ማታና (ማታ የአባቱ ስም ነው ጨለመ መሸ ለማለት አይደለም)። አለቃ ተክሌ ናቸው። እነሱም ለእርስዎ የሚላከውን ደብዳቤ ይጽፉ ነበር።

«ንጉሱ በየትኛውም መንገድ ወደ ምጽዋ ለመመለስ እንደምንፈለግ ጠየቁን። እኛም በላስታ በኩል ያለው መንገድ ሰላማዊ (ደህና) መሆኑን ነገርናቸው። ደብዳቤዎቹ ለሣሙኤል ተሰጡት እኛም ወደ ሰፈራችን ሔደን እንድንዘጋጅ ተነገረን። በመጨረሻው ደብዳቤዎቹ ለኢብራሂምና ለመሐመድ ሲሃዊ ተሰጡ። በዚያው ቀን በተሰያት ገደማ መቅደላን ለቀን የምፅዋ መንገዳችንን ቀጠልን።

«ከንጉሡ ዘንድ ተሰናብተን ከሔድን በኋላ ቆንሲል ካሜሩን መፈታቱን ሰማን። ኢብራሂምና መሐመድ ሲሃዊ እግር ብረቱ በሚወልቅበት ጊዜ ከዚያው ከአጠገቡ ነበሩ። እኔና ጓደኞዬም ቆንሲሉን ብዙ ጊዜ አይተናቸዋል። አንድ ጊዜ ልብሳችንን የምንገዛበት ገንዘብ ለከውልናል። ከተፈቱት በኋላ ግን ለማየት ጊዜ አልነበረንም። ለምፅዋው መንገዳችን ተቻኩለን ነበርና ነው። ከምሽጉም በደረስን ጊዜ የንጉሡ ኃይል ብዙ ነበር። እየቀነሰ ሔዶ አሁን የበፊቱን በየቦታው ከሽፍቶች ጋር በሚያደርገው ውጊያ እየሞተ አልቋል። እኛ መቅደላ በለቀቅንበት ጊኤ እንኳን ንጉሱ ትልቁን አመፀኛ ዋግ ሹም ጐበዜን ለመውጋት ሊዘምቱ ነው እየተባለ ይወራ ነበር። ተከዜ ወንዝ ስንደርስ እንዳየነው የንጉሱ ሹማምንት ለዘመቻቸው ስንቅ የሚሆን በግና የቀንድ ከብት ይሰበስቡ ነበር።





እሥረኞች

«ጓደኞዬ አባዋሶ ተምቤን አጠገብ ፋናራ ስንደርስ ተለያይተን በሰራዊ ውስጥ ጉዱ ፈላሴ ያሉትን ዘመዶቹን ለማየት ብሎ ሔደ። ምፅዋ ላይ እንገናኝ ብሎን ቀረ።»

ለሶስተኛ ጊዜ ራሳም ለአጤ ቴዎድሮስ የጻፈውን ደብዳቤ መጋቢት 21 ቀን 1857 ዓ.ም ይዘው የሔዱት ኢብራሂም ወለድ ሹም እና መሐመድ ሲሃዊ በደብዳቤ ያቀረቡት ሪፖርት ደግሞ እንዲህ ይላል።

«ከእርስዎ እንደተለየን ወደ አበሻው ንጉሥ ዘንድ ለመሔድ በትግሬ በተንቤንና በላስታ አድርገን ጉዞ ጀመርን። በጉዞውም ከመጨረሻው ቦታ ለመድረስ አንድ ወር ያህል ፈጀብን። የምንጓዘውም ሽፍቶችን እየፈራን በሌሊት ነእብር። አንዳንዴም አንድና ሁለት ቀን ያህል ጉዞአችንን እያቋረጥን ውሎ እናደርግ ነበር። ሰቆጣ ስንደርስ በሰቆጣና በደብረ ታቦር መሃል ያለው መንገድ ሰላማዊ ባለመሆኑ ብዙ ቀን ተቀመጥን።

«ደብዳቤውን በሣሙኤል በኩል ለመስጠት አሰበን። እሱም የንጉሱ ባለሟል ሰቆታ እንደደረሰን ስንጠያይቅ እሱ ያለው ደብረ ታቦር መሆኑ አጣራን። እኛም የመጣንበትን ጉዳይ ገልፀን እንዲረዳን መልዕክተኛ ላክንበት። እሱም ግድ የለም እንድትመጡ ሲል ላከብን። እኛም በቀጥታ ወደ ደብረ ታቦር ተጉዘን በ12 ቀናችን ደረስን። እሱም የንጉሱን የጦር መሣሪያዎች ጠመንጃዎችንና ጥይቶችን ወደ መቅደላ በማስጫን ሥራ በዝቶበት አገኘነው። በዚያውም አስር ቀናት ከቆየን በኋላ ሳሙኤል ቀድሞን ወደ መቅደላ ያውም አስር ቀናት ከቆየን በኋላ ሳሙኤል ቀድሞን ወደ መቅደላ ሔደ። እኛንም ለንጉሱ ከሚጫነው ጓዝ ጋር እንድንሔድ አደረገን።

«ጁላይ 4 (ሰኔ 27) ቀን በዘጠኝ ቀናችን ረቡዕ ዕለት መቅደላ ደረስን። ደብረ ታቦር ሆነን ሳሙኤል ስላመጣነው ደብዳቤ ለንጉሱ ሊነግርልን ተስፋ ሰጥቶን ነበርና መቅደላ ካለው ከሳሙኤል ቤት እንደደረስን መልዕክተኛ መጥጦ ከንጉሱ ዘንድ እንደምንፈልግ ነገረን። እኛም ፈጠንን ጉዞ ጀመርን።

«ደብዳቤውን ለግርማዊነታቸው ከመስጠታችን በፊት ግን እንደላክን ጠየቁን። እኛም እርስዎ እንደላኩን ተናገርን። እሳቸውም ‹ይሄን የሽፍታውን ነገር እንዴት አለፋችሁት?» ብለው ቢጠይቁን እኛም ‹በርስዎና በእንግሊዝ መንግሥት ውቃቤ ልናልፍውቻልን ብለን መለስን። ደብዳቤ ይዘን እንደሆነና የተጻፈውም በምን ቋንቋ እንደ ሆነ ጠየቁን። አንደኛው የተጻፈው በአረብኛ ሲሆን ሌላው ደግሞ በእንግሊዝኛ ነው አልናቸው።

«ደብዳቤውን ከመቀበላቸው በፊት የምንናገረው ሌላ መልዕክት እንዳለ ጠየቁን። እኛም ‹ጃንሆይ መጀመሪያ ደብዳቤው ይነበብና ከዚያ በኋላ የምናገረው ይኖረናል› አልናቸው። እሳቸውም ‹ግድ የለም። ደብዳቤውን በኋላ አነበዋለሁ። በመጀመሪያ የምትናገሩት እንዳለ ልስማው› አሉን። እኛም ‹የእንግሊዙ ወኪል ለእርስዎ ከፍተኛ ሰላምታ እንድናደርስ ነግሮናል። የመጀመሪያዎቹ ደብዳቤዎች ሞገስ እንዳላገኙ ሰግቷል። በዚህም በእንግሊዝኛ በአበሻ መሀል መልካም ወዳጅነት እንዳይኖር የሚፈልጉ ሰዎች እንዳሉ ጠርጥሯል። እሱ የመጣበትንም ጉዳይ እያጣመሙ የሚያስረዱ እንዳሉ አድርጎ ያስባል። የእንግሊዝን መልካም ወዳጅነት ግን ግርማዊነትዎ ተመራምሮ እንዲደርስበት ይመኛል። ይህንንም ከእንግሊዟ ንግስት ለግርማዊነትዎ

በተጻፈው ደብዳቤ ላይ ያገኙታል። የያዘውንም ይህን ደብዳቤ ለግርማዊነትዎ ለመስጠት ቸኩለዋል› ብለን ተናገርን።

«እሳቸውም ‹ለመምጣት ከፈለገ ለምን እናንተ ጋር አይመጣም ነበር?› አሉን። እኛም ስንመልስ ‹እንዴት አድርጎ ያለ ግርማዊነትዎ ፈቃድ መምጣት ይችላል?» ስንላቸው ሳቁና ‹እሺ ያንን የምትሉትን ፈቃድ እልክለታለሁ› አሉን። ከዚያም ወደ ሠፈራችን እንድንሔድና ደብዳቤውን ካነበቡ በኋላ እንደሚያስጠሩን ነገሩን።

«ወደሠፈራችን እንደ ተመለስን ራሳቸው ንጉሡ ከሚበሉት ምግብ ተላከልን። ከበላንም በኋላ እንድትመጣ ተነገረን። ከፊታቸው ስንቀርብም ሶስቱን ደብዳቤዎች ፀሐፊያቸው ሙአሊም ማታ እንደገና እንዲያነባቸው ነገሩት። እሳቸው ከመጀመሪያዎ ደብዳቤ ይልቅ ሁለተኛው የተሻለ መሆኑን ከሁለተኛው ደግሞ ፫ኛው ደብዳቤ የተሻለ መሆኑን ተናገሩ። በተለይ ፫ኛው ደብዳቤ ላይ በጣም እንዳስደስታቸው ገለጹልን። ሲናገሩም እንግሊዝና አበሻ ወዳጅ ከሆኑ ጊዜ የቆየና አሁንም ወዳጅ መሆናቸውን ተናግረው ቆንሲሉ ግን በሁለቱ አገሮች መሀል እንዳለው ውዳጅነት ያለመሥራቱን አሁም አንተ ሁሉንም እንደምታስተካክል ተስፋ እንዳላቸው ነገሩን።

«ከዚህ በኋላ ሠፈራችን እንድንመለስ ተነገረን። በሠፈራችንም ምንም ነገር እንዳይጐድልብን አስፈላጊያችን ሁሉ እንዲደረግልን ሣሙኤል አዘዙት። እኛም ‹ንጉሥ ሆይ በእርስዎ ታላቅ ቸርነት በምግብ በኩል ምንም የጐደለብን ነገር የለም። ነገር ግን የምንጠብቀው በታላቁ ቸርነትዎ መልሱን ሰጥተውን ወደ ምፅዋ እንድትመለስ እንዲያደርጉን ነው› አልናቸው። እሳቸውም መንገዱ አስቸጋሪ መሆኑና ይህንንም ለማስተካከል በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ትግሬ እንደሚዘምቱና እኛም ጥቂት እንድንቆይ ቆንሲሉንም እንደሚፈቱ ነገሩን። እኛም ስንላክ በአርባ ቀን እንደምንመለስ ተስፋ ሰጥተን ነበር። ከዚህ የበለተም መቆየት አንፈልግም አልናቸው።

«እሳቸውም ሳቅ አሉና በፈገግታ ‹የእንግሊዙ ወኪል በእርግጥ ወደዚህ ለመምጣት ፈልጐ እንደሆነ እንዴት አድርጎ በሸፈተው አገር ውስጥ ሊያልፍ ይችላል?› ሲሉ ሳሙኤል በዚያው ነበርና ጣልቃ ገብቶ በመተማ በኩል

መልካም (ሰላማዊ) መንገድ መኖሩን ተናገረ። ንጉሱም በአሳቡ ተስማሙ። እኛንም አሁን ሂዱና ነገ እንድትመጡ አሉን።

«በማግስቱ ማለዳ ጁላይ 5 (ሰኔ 28) ቀን ንጉሱም እኛንም ሣሙኤልንም የአማርኛና የአረብኛ ፀሐፊዎቻቸውንም አስጠሩን። የአረብኛውን ቋንቋ ደብዳቤ ሙአሊም ማታ ጻፈው። የአማርኛው ደብዳቤ ደግሞ በአንድ ፀሐፊ ተጻፈ። ለእኛም አጃቢ እንደሚሰጡንና እነሱም መተማ ድረስ እንደሚሸኙን ነገሩን። አንተም እዚያ በምትደርስበት ጊዜ ተቀባይና አጃቢ ሳይልኩልህ አይቀርም። ከምፅዋ ስትነሳም እንድትጽፍላቸው ነግረውናል። ይህም መተማ ያለው እንደራሴያችወ እንዲቀበልህ ለማዘዝ ነው።

«ከዚህ በኋላ ካንተ የላኩትን የበፊተኞቹ መልክተኞች ሁሉ ከኛ ጋር አብረውን እንዲመለሱ እንዲነግራቸው አዘዙ። ለእያንዳንዳቸው 5 ብር አምስት ብር እንዲሰጣቸው ተናገሩ። ለኛ ግን ምንም አልሰጡንም። ነገር ግን ካንተ ጋር ተመልሰን በምንሔድበት ጊዜ እንደሚሸልሙን ተስፋ ሰጥተውናል። ወደ አንተ የተላከውን ደብዳቤ እንዳልፈረሙበትና ማህተምም እንዳልተደረገበት ነግረውናል። ምክንያቱም በቆንሲል በጣም ስለተናደዱ ነው። እሱንም እኛ ከሔድን በኋላ እንደሚፈቱት ነገሩን። እኛም ‹ንጉሥ ሆይ ታላቁን ደግነትዎን የምንለምነው ለላከንም ለአቶ ራሳም ቆንሲል ተፈትቶ አየነው ብለን ለመንገር እንድንችል ከመሔዳችን በፊት ቆንሲሉን ፈትተው ልባችንን በደስታ እንዲሞሉን ነው። አልናቸው። እሳቸውም ይሁንላቸው። ለአቶ ራሳም ወዳጅነትና ስለ እናንተም መቸገር ቆንሲል ተለቆ ታዩታላችሁ› አሉን።

«ከዚህ በኋላ አቶ ሣሙኤልንና ዋናውን የጦር አዛዣቸውን ራስ እንግዳን አዘው እኛ ከእነሱ ጋር እንድንሔድና ቆንሲሉን ከፊታች እንዲፈታ ከእኛ መፈታቱን ማየታችንን ላንተ እንድንነግር አዘዙን። ቆንሲሉ ከፊታችን ከተፈታ በኋላ ላንተ የሚላክ ደብዳቤ እንዲሰጠን ጠየቅነው። ሣሙኤል ግን ንጉሱ ካላዘዙ በስተቀር ይሄ ነገር ፈጽሞ አይቻልም አለን። እኛም ጉዞ በጀመርንበት ጊዜ ቆንሲሉ ተፈትቶ ነበር። ይህንንም ታላቅ ቸርነታቸውን ተመልሰን ለማመስገን አስበን ፈርተን አልሔድንም። ከዚህ በኋላ ጉዞአችንን ቀጥለን በ12ኛው ቀናችን ምፅዋ ገባን። የቆየነውም በመንገዱ ፀጥታ ማጣት ነው።

እነኝህ መልዕክተኞች በራሳም መጽሐፍ በመጀመሪያው ቮልዩም ላይ ይገኛሉ።


በመጨረሻምው እነራሳም ምፅዋ በገቡ በዓመቱ በነሐሴ ወር 1857 ዓ.ም የፈቃዱ ደብዳቤ ከቴዎድሮስ ዘንድ መጣላቸው። ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ለሚስተር ራሳም የተጻፈው ደብዳቤ ቀጥሎ ያለው ነው።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ስሚን
አንዳልጥፍልህ አቡነ ሰላማ ኮከብ የሚባል  ፈላሽ
ቁንሲል በላችሁ የሰዳችሁቱ ከምሮን ከገባ ከተማየ
በእግዚአብሔር ኃይል በፍቅር አስቀምጫቸው ሳለሁ
ሰይቡኝ የእንግሊዝን ንግሥት ፍቅር ስፈልግ ቡላዲን
ዮሐንስ ሚባሉ የእንግሊዝ ሰዎች። ካገሬ ቢደብደቡ።
በእግዚአብሔር ኃይል የነዚያን ደም ብመልስ
እብዚኸውም ነፍሰ ገዳይ ብለው ሰደቡኝ ቁንሱሉ
ኬምሮን የሚባለው የንግሥት ሎሌ ነኝ ቢለኝ ያገሬን
ጌጥ ሸልሜ ሥንቁን ሰጥቼ ከንግሥት ወዳጅ አድርገኝ
ብዬ ብሰደው ከቱርኮች ጋራ ስንብቶ ተመልሶ መጣ።
ደብዳቤየሳ ብለው አልተመለሰልኝም አለኝ። ምን
ባደረግሁ ጠሉኛ ብየ በጌታዬ ኃይል ዝም አልሁ።

ይድረስ ከሀርዝ ራሳም አሁንም ትግሬ ሸፍታ
ወጥቶአልና። በእግዚአብሔር ኃይል ዙረህ በመተማ ና
መተማ ስትደርስ ላክብኝ በእግዚአብሔር ኃይል ተቀባይ
እሰድልሀለሁ።
ሰኔ  በባታ በ፳፱ ቀን ረቡ ተጣፈ።




ደብዳቤውም ማህተም አልነበረውም። ለራሳም የተጻፈበት ደብዳቤ ከዚህ በላይ ያነበብነው አምርኛው ብቻ ሳይሆን ይህ የአማርኛው ደብዳቤ በአረብኛ ተተርጉሞ በአንድነት ከማአርኛው ጋር ተልኮለታል። ምናልባትም ለአንባቢዎች ወይም ለተመራማሪዎች ጠቃሚ ይሆን እንደ ሆነ በማለት እንደ አማርኛው ሁሉ ማህተም የሌለበትን አረብኛ ደብዳቤ ፎቶ ኮፒ ከዚህ ቀጥሎ አስገብቼዋለሁ


بسم الاب والابن والروح القدس الاله الواحد لم يحل الى الاباد امين

ራሳም ይህ ማህተም የሌለበት የፈቃድ እንደደረሰው ከምፅዋ ወደ መተማ ለመሔድ ያለበትን ችግር ሁሉ ያወጣና ያወርድ ጀመር። ክረምት ስለገባ ከምፅዋ መተማ ለመድረስ የተዘጋጀ መንገድ በሌለበት አገር የማይታሰብ መሆኑን አወቀ። ሁለተኛው ነገር ደግሞ በዚያው ጊዜ ሱዳን ውስጥ ኃይለኛ በሽታ ገብቶ ሕዝቡን ይጨርስ ስለነበረ በቀጥታ ሄዶ ከዚያ በሽታ ገብቶ ሕዝቡን ይጨርስ ስለነበረ በቀጥታ ሄዶ ከዚያ በሽታ ውስጥ መግባትም አስፈራው። ስለዚህ እንደገና ወደ አጤ ቴዎድሮስ ችግሩን ገልጾን አስፈራው። ስለዚህ እንደገና ወደ አጤ ቴዎድሮስ ችግሩን ገልጾ ደብዳቤ ጻፈላቸው «ጃንሆይ።.......አንድ ነገር እንድገልጽልዎት እለምናለሁ። በከሰላና

እባካባቢው በገባው በሽታ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ እርስዎ እንዳሉኝ በመተማ ዞሬ ለመምጣት የማይቻል ነው……» ብሎ አሳወቀ።

ራሳም ይህን ደብዳቤ ከጻፈ በኋላ የክረምቱን ወራት ካይሮ ላይ ለማሳለፍ በመርከብ ተሳፍሮ ወደ ካይሮ ሔደ። ወደ ካይሮ የሔደበት ዋናው ነገር ክረምቱን በዚያ ለማሳለፍ ብቻ ሳይሆን የእንግሊዝ መንግሥት በራሳም ምትክል ፖልግራብ የተባለውን ሾሞ ምፅዋ ድረስ ሰዶ ስለ ነበረ ስለዚሁ ጉዳይ በቴሌግራም ለመጠየቅና ለመነጋገር ነው። ካይሮ ደርሶ የቴዎድሮስን የፈቃድ ደብዳቤ መድረሱንና ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ይመከራቸው የነበረው ካሜሮንም አሁን ግቡ የሚለው የንጉሱ ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ ቢቀሩ በእስረኞቹ ላይ አደጋ እንደሚደርስ ገልጾ የጻፈለትንም ጨምሮ ለእንግሊዝ መንግሥት በቴሌግራፍ አስታወቀ። የእንግሊዝ መንግሥት ጉዳዩ እስከዚህ ደረጃ ከደረሰ በራሳም ምትክ ወደ ቴዎድሮስ እንዲሔድ ታዞ የመጣው ፖልግረብ ባለው በዚያው በካይሮ እንዲቆይ ሆኖ ራሳም ግን በደረሰው የፈቃድ ደብዳቤ መሰረት ከነተከታዮቹ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ የሚል ትእዛዝ አሳለፈ። ከዚህ በኋላ ራሳም ከእንግሊዝ አገር ሲነሳ ለአጤ ቴዎድሮስ የሚሰጥ የያዘው ስጦታ አጥጋቢ መስሎ ስላልታየው አንዳንድ ስጦታዎችን ገዛ። እስከ መስከረም ድረስ ካይሮ ከቆዩ በኋላ ምስከረም 28 ቀን 1858 ዓ.ም ተመልሰው ምፅዋ ገቡ።



የጥንታዊት አዱሊስ ከተማ

እነራሳም ምፅዋ እንደገቡ ጊዜ ሳያጠፉ ጥቅምት 6 ቀን 1858 ጓዛቸውን በተከራዩዋቸው ስልሳ ግመሎች ላይ ጭነው በቀጠሯቸው በብዙ ሰዎች ታጅበው የመተማ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ከምጽዋ መተማ ድረስ ያለውን ረጅም ጉዞ በመሬት በመጓዝ 704 ኪሎ ሜትር ተጉዘው ከምጽዋ በተነሱ በወር ከሰባት ቀናቸው ሕዳር 12 ቀን መተማ ገቡ። ጐንደር ለመድረ ግን ግና 160 ኪሎ ሜትር ያህል መንገድ ይቀራቸዋል።

መተማ ድረስ ስለነበረው የጉዞ ሁኔታ ብላንክ ሲጽፍ «......በሠፈርንበት ቦታ ሁሉ የአንበሶቹ ጩኸት ጆሮአችንን ያደነቁረው ነበር። የአገሩ ሙቀት ከመጠ በላይ ኃይለኛ አሰቃቂ ስለነበረ የቀኑን ሐሩር ለመሸሽ ስንል በጧት እየተንሳን መጓዝን እንወድ ነበር። ከሁሉም ይልቅ ማታ ማታ ጨረቃ ቢኖርም ባይኖርም ከቀኑ ሐሩር ይሻላል በማለት መጓዝን እንመርጣለን። እንደዚህ ካለ ካበዳ ሁኔታ የምንገሰግሰው የመንግሥታችንን ትእዛዝ ለማክበርና በሰንሰለት የታሠሩት ወገኖቻችን ወደሚገኙበት አገር በመድረስ ተግባራችንን ለመፈጸም ግዴታችን ስለነአብረ ነበር። የምንጠጣው ውሃ በፍየል አቅማዳ የተያዘውን


ሙቅና ቆሻሻ ውሃስ ለ ነበር በፀሐይ የተቃጠለውን አካላታችንን ለማለስለስና ድካማችንንም ለማውጣት ለመንገድ አልነበረንም። የደረሰብንን መጐሳቆል በሱዳን ላይ ለማቋረጥ የገጠመን ችግርና መከራ ከባድ ቢሆንም በጥንቃቄ አንድ ሰው በሞት ሳይለየን በሰላም ደረስን። አብረውን የተጓዙት የአገሬው ሰዎችና ተከታዮቻችን ሚስተር ራሳምም ሳይቀር በወባ በሽታ መሰቃየታቸው ባይቀርም ሁሉም በሕይወታቸው ላይ አደጋ ሳይደርስባቸው ድነዋል.......» ብሏል።

መተማ እንደደረሱ ቴዎድሮስ መተማ ስትደርስ ላከብኝ ባሉት መሠረት ራሳም ወደ አጤ ቴዎድሮስ መተማ መድረሱን በደብዳቤ ጻፈላቸው። አጤ ቴዎድሮስም የፍቃድ ደብዳቤ ተቀባይና አጃቢም ለኩላቸው። ለመተማው ገዢ ለሸህ ጁማ አጤ ቴዎድሮስ በጻፉለት ደብዳቤውም «........የምወደው ወዳጄ አቶ ኸርሙዝድ ራሳም የሚባል የእንግሊዝ ሰው አሁን አንተጋ መተማ አለ። እሱንም አጅበህና በደህና አድርገህ ጭልጋ እንድታደርሰው ይሁን። ከዚያም የኔ ሰዎች ይቀበሉታል። በዚህ ጉዳይ እንድትበረታበት። ምክንያቱም የምወደው ወዳጄ ነውና። እንድታከብረውም ይሁን።.......» ይላል።

እነ ራሳም እንደ ቴዎድሮስ ትእዛዝ ሁሉ ታጅበው ጭልጋ ሲደርሱ 1400 የሚሆኑ ከአጤ ቴዎድሮስ የተላኩ ተቀባዮች ተቀብለዋቸው ይጓዙ ጀመር። ጥር 20 ቀን 1858 ዓ.ም በጌምድርንና ብዙ ሰው ይዘው ከሚያዋስነው ቦታ እኩለ ቀን ላይ ሲድደርሱ ራስ እንግዳ ብዙ ሰው ይዘው አቀባበል አደረጉላቸው። ከዚህ ቦታ አጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ለመድረስ የሚቀራቸው መንገድ ሃያ ደቂቃ ያህል የሚያስኬድ ነው።

በዚያ ቦታ ስለ ነበረው አቀባበል አብሮ ይጓዝ የነበረው ዶክተር ብላንክ ሲገልጽ «......ተራራማ ቦታ ላይ የአጤ ቴዎድሮስ ወታደሮች የጦር መሣሪያና ጦር በያዙ...... ባጌጡ ሰዎች ተሞልቶ ነበር።......ቁጥራቸው አስር ሺህ የሚሆኑ ሰዎች በሁለት ረድፍ ተሰልፈው ስለጠበቁን በመካከላቸው ስናፍል በቀኝ በኩል የተሰለፉት እብተንቆጠቆጠ ልብስ አጊጠው በብር ያጌጠ ጋሻና ጦር ይዘው ፈረሶቻቸው ባማረ መሣሪያ ተሸላልሞ የንጉሠ ነገሥቱ መኮንኖችና የቤት አሽከሮች በሚያማምሩት ፈረሶቻቸው ላይ በንቃት ተቀምጠው ነበር። በግራ በኩል የተሰለፈው ፈረሰኛ ሠራዊት ጥቅጥቅ ባለ ሁኔታ በብዛት የቆመ ሲሆን የቀኙ ክፍል ደግሞ የተለየ ነበር።.......» ብሏል።

ከዚህ አቀባበል በኋላ ለራሳም መሔጃ ከአጤ ቴዎድሮስ በተላከች ውብ ሆና ባጌጠች በቅሎ ራሳም ተቀምጦ በደመቀ አጀብ ከቴዎድሮስ ሠፈር ደረሱ። ከሠሩም የመንገደኞቹ ድንኳን እስቲተከል ድረስ ለመቀበያ ተብሎ ከተከለው ከአጤ ቴዎድሮስ የግል ቀይ ድንኳን ውስጥ ገብተው አረፉ። ግብር ገብቶላቸው በሚዝናኑበት ጊዜ ከአጤ ቴዎድሮስ በአረብኛ የተጻፈ ደብዳቤ ስለራሳም ደረሰው።



بسم الآب والابن والروح القدس إله واحد
آمين
من الإمبراطور تيودروس بقوة الله الوصول
إلى صديقي
من هرمز الذي يريد ان نكون اصدقاء.

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ አሜን

ከንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ በእግዚአብሔር ኃይል ይድረስ ከወዳጄ ወዳጅነት ከሚፈልገው ህርሙዝ ራሳም።

የዛሬውን ሌሊት አርፈህ ብታሳልፈው የተሻለ ይሆንልህ ነበር። ነገ ጧት ብንገናኝም ጡር ነበር። ነገር ግን እኔ በዚህ አገር አይንተን መምጣት ስጠባበቅ ብዙ ቆይቻለሁ። ስንቅ በማለቱ ምክንያት ወታደሩ ምግብ ፍለጋ ነው። በዚህ ምክንያት በኔና መሀል የሚደረገው ንግግር ዛሬ ቢጀመር መልካም ነው። ነገ ጧት ጉዞ እንጀምራለንና አሁን መጥተህ እንገናኝ።»

ከዚህ በኋላ ራሳም እንግዳ እየተመሩ ከንጉሡ ድንኳን አካባቢ ሲደርሱ በሩምታ ጥይታ ተተኩሶ አቀባበል ተደረገላቸው። ከድንኳኑ ውስጥ ሲገቡም አጤ ቴዎድሮስ በዙፋናቸው ተቀምጠው በግራና በቀኝ ሹማምንቶቻቸው ቆመው ነበር። ቴዎድሮስ የለበሱት ያገር ልብስ ሲሆን ራሳቸውን ተከናንበዋል። በአፍንቻቸውም ላይ የኩታቸውን ጠርዝ አድርገዋል። እነ ራሳም ገብተው ከተጻፈ ዓመት ከመንፈቅ የሆነውን የመንግሥት ቪክቶሪያን ደብዳቤ ለመስጠት ራሳም ሲጠጋ ከንብንባቸውን አወረዱ።

ራሳም የንግሥቲቱን ደብዳቤ ለአጤ ቴዎድሮስ ከሰጠ በኋላ ከዚያው ከፊታቸው ቆሞ «እጅግ በጣም ከተከበሩት የእንግሊዝ ንግስት የተጻፈውን ይህን ደብዳቤ ለግርማዊነትዎ ሳቀርብ ታላቅ ክብር ይሰማኛል» በማለት ንግግር አደረገ። ቴዎድሮስም «ደብዳቤውን የምቀበለው በደስታ ነው። አንተንም በደህና በማየቴ ተደስቻለሁ» ብለው መልስ ሰጡ። ደብዳቤውንም በሶስተኛው ካለው መከዳ ላይ አስቀመጡት። ወደ ተነጠፈው ሥጋጃ እያሳዩም «ተቀመጡ» አሏቸውና ተቀመጡ።

ከንግሥቲቱ በእንግሊዝኛ የተጻፈውን ደብዳቤ ወደ አማርኛ ለመተርጐም አስተርጓሚ አቶ ወልደ ገብርኤል ቀረቡ። አቶ ወልደ ገብርኤል ትውልዳቸው ሸዋ በመሆኑ ለሸዋው ንጉሥ ለምኒልክ ረድተው ነገር ያበላሻሉ ብለው አጤ ቴዎድሮስ ውጣ በልው ከድንኳኑ አስወጧቸው። ስለዚህ ደብዳቤውን በቀጥታ ወደ አማርኛ የሚተርጐመው ስላልተገኘ ራሳም ወደ አረብኛ እየተረጐመ አቶ ሣሙኤል ደግሞ ከአረብኛ ወደ አማርኛ ቃል በቃል ይተረጉመው ጀመር።

ከንግሥቲቱ በተጻፈው ደብዳቤ ላይ «......ግርምዊነትዎ ሚስተር ራሳምን በመልካም እንደሚቀበሉት ስለምናምን ስለኛም የሚነገርዎትን ሁሉ ዋጋ እንደሚሰጡት አምናለሁ።...... «የሚለውን አረፍተ ነገር አቶ ሣሙኤል ሲያስተረጉሙ «........ሚስተር ራሳም የሚፈልጉትን ሁሉ ያደርጋል» የሚለውን የተሳሳተ ትርጉም የሰሙት ቴዎድሮስ በጣም ደስ አላቸው። «.......ከእንግዲህ ወዲህም እንዲህ ያለ ሰው ካገኘሁ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መሀል ያለው የቆየ ወዳጅነት እንደገና ይታደሳል። ከእነኝያ ኤሮፓውያን እስረኞች ሁሉ ይህ ሰው የበለጠ ነውና ወዳጄ ሚስተር ራሳም ከኔ ጋር የሚቆይ ከሆነ እነኝያ ወደፈለጉበት ይሂዱ። ልቀቋቸው.......» አሉ።

በዚህ በአጤ ቴዎድሮስ መልስ ራሳም ተደሰተ። ራሳም እንደ መሰለው አጤ ቴዎድሮስ እስረኞቹ እንዲፈቱ ያዘዙት ከንግሥቲቱ በመጣው ደብዳቤ ተደስተው መስለው እንጂ «ከኔ ጋር የሚቆይ ከሆነ» የሚለውን አረፍተ ነገር አላጤነውም። ከዚህ በኋላ በተደረገው ጭውውት ቴዎድሮስ ለራሳም ኤሮፓውያን እንዴት እንዳስቀየሙዋቸው፥ በተለይ አቡነ ሰላማ ቆንሲል ካሜሩንና ቄስ እስተርን አንድነት ሆነው የበደሏቸውን ሁሉ ነገሩት። ካሜሩን የሰጡትን ለእንግሊዝ ንግሥት የጻፉትን ደብዳቤ ይዞ ምፅዋ በመሔድ ፈንታ ወደ ከሰላ ሔዶ ከጠላቶቻቸው ከቱርኮች ጋር ሲማከር መቆአይቱን ከቱርኮችም ጋር በተገናኘ ጊዜ በተደረገለት የእራት ግብዣ ላይ ይዞ የሔደውን የአበሻ አሽከር እየሸለለ እንዲፎክር ቢያዘውና እምቢ ቢለው አስገድዶ ማሸለሉን ቱርኮችም እየሳቁ «ትልቁ ንጉሣችሁ ወታደሮች የሚያዋጋው እንደዚህ ነው» እያሉ ማላገጣቸውን ሁሉ ነገሩት።

እስተርንም አቡነ ሰላማ የነገሩትን ይዞ የኮሶ ሻጭ ልጅ ብሎ መጻፉንና እሳቸው ያደረጉትን ውለታ ሁሉ ለራሳም አጫወቱት። ድካማቸውም አገሪቱን በአድን ንጉሥ የምትገዛ ሰላማዊ አገር ለማድረግ መነሳታቸውን ሁሉ አጫወቱት። «.......ወደ ደቡብ ስሔድ በሰሜን ያለው ሕዝብ ይሸፍታል። ወደ ምዕራብ በምሔድበት ጊዜ ደግሞ በምሥራቅ ያሉት ይሸፍታሉ......» ኣይሉ ነገሩት። ቱርኮች በሱዳን በኩል ገብተው ከኢትዮጵያ ግዛት ስናርን ቆርሰው መውሰዳቸውንና በአሁኑም ጊዜ ለጦርነት መዘጋጀታቸውን ሁሉ ነገሩት። ራሳምም የሚነጉርትን ሁሉ በጥሞና አዳመጠ። በመጨረሻውም አጤ ቴዎድሮስ ለነሚስተር ራሳም ባልደረባ እንዲሆናቸው ፀሐፊያቸውን አቶ

ሣሙኤልን ሰጡዋቸው። እነ ራሳምም ባልደረባቸውን ከተቀበሉ በኋላ ከቴዎድሮስ ድንኳን ጥቂት ራቅ ብሎ ከተተከላቸው የማረፊያ ድንኳን ውስጥ ገቡ።

ለነሚስተር ራሳም ለሚያስፈልጋቸው ወጭ አጤ ቴዎድሮስ 10000 (1500 የሚሉም አሉ) ሰጡዋቸው። በየቀኑም አንድ ሺ እንጀራ ሁለት የቀንድ ከብት ሃያ ዶሮ 500 እንቁላል አስር ገንቦ ወተትና አሥር ገንቦ ማር እንዲሰጣቸው ድርጎ አዘዙላቸው። መቅደላ ያሉት እስረኞችም ተፈትተው ለነራሳም እንዲሰጡ ተፈቅዶ መልክተኛ ወደ መቅደላ ተላከ።

## ምዕራፍ 12

# እስረኞች ተፈትተው ታሠሩ

አጤ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የሚላክ የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፈው እስረኞቹ ወደ አገራቸው በሔዱበት ጊዜ እንዲላክ አዘዙ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ የእግዚአብሔር ፍጡር ባርያው የዳዊት የሰሎሞን ልጅ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ለእግዚአብሔር ሰው ሁሉ መርጦ አልቆ ከነገሠ ሃይማኖት ፍቅር ከሚወዱ የተጠቃ ደሀ ከሚጠብቁ ዕንግሊዝ ንግሥት ከቢክቶርያ ሕርምዝ ርስአምን በኬምሮን ጉዳይ ሠድጄዋለሁ ያሉኝን እንኳን እርስዎ የባርያዎ ባርያ ቢልክብኝ እምቢ እላለሁ እሺ ሰድጄልዎ አለሁ እኒያ ግን ጳጳስ ነኝ ብሎ ከመጣ ግብጥ ጋር ሁነው ያደረጉኝን እግዚአብሔርን ከሚፈራ ሰው ጠይቀው ያግኙት እኔ ከታላቂቱ ከርስዎ ጋራ መላላክ ተገብቶኝ አይደለም ዳሩ ግን ተሳቅ ሰውና ባሕር አንድ ነው ሁሉን ይችላል እኔን የኢትዮጵያን ደንቆሮ ስለ እግዚአብሔር ብለው ብለው ይቻሉኝ አስሬአቸው የነበርሁ ሰዎች ያዋረዱኝ የሰደቡኝ ጋሉ ገዝቶ የእስራኤል ልጅ ጠፍቶ እኮ አምኖ ነበረ ያንዲቱ የእስራኤል ልጅ ጠናቸው ልጅ እኔ ነኝ እግዚአብሔር ግን ያባቴን መንግሥት ኃይል ሠጥቶኝ መለሰልኝ። የኢትዮጵያ ሰዎች ድንቁርነታቸውን ዕውርናታችነን ሳይሰሙት አይቀሩም። ያማረ መስሎኝ ደፍሬ የላክሁብዎን ከፍቶብኝ ቢገኝ ይሞክሩኝ እንጂ አይከፉብኝ እግዚአብሔር የመረጠዎ ንግሥት ዓይንዎ የበራ ነዎና።

ዓለም በተፈጠረ በ፯ሽህ ከ፫፻፶፰ አመት በጥር በ፳፪ ቀን ተጣፈ ጌታ ከተወለደ በሽ ከ፰፻፶፰ ዓመት



ይህም ለንግሥት ቪክቶሪያ የተጻፈ ደብዳቤ ወደ እንግሊዝ ከተተረጐመው ጋር ሲተያይ አንዳንድ ስህተቶች አሉበት። ይህም የሆነው ከተርጓሚው ብዛት ይመስላል። አማርኛው በአቶ ሣሙኤል ወደ አረብኛ ከተተረጐመ በኋላ ራሳም ራሱ ከአረብኛ ወደ እንግሊዝኛ ስለተረጐመው ነው። ወይም ደግሞ ራሳም በእንግሊዝኛ አተረጓጐም ላይ የፈለገውን ቃል ጨምሮ ይሆናል ራሳም ስለተርጓሚው አቶ ሣሙኤል በመጽሐፉ እንደጻፈው «አቶ ሳሙኤል አረብኛና አማርኛ በጥሩ ሁኔታ ያውቃሉ……» ይላል። አቶ ሣሙኤል ግን የሰናፌ ሰው በመሆኑ አማርኛ 2ኛው ቋንቋው እንጅ የራሱ ቋንቋ አይደለም። ለምሳስሌ «…….በኬምሮን ጉዳይ ሰድጄዋለሁ……» የሚለው አማርኛው አረፍተ እንገር በእንግሊዝኛው ላይ «…….በሁሉም ኤሮፓውያን ጉዳይ…….» የሚል ተጨምሮበታል። በአማርኛው።…….ስለ እግዚአብሔር ብለው ይቻሉኝ «…….በስህተቴ ይቅርታ ያድርጉልኝ በተረጐመው እንግሊዘኛ ላይ «…….በስህተቴ ይቅርታ ያድርጉልኝ…….» ይላል። በውጫሌው ውል በትርጉም ስህተት ኢጣሊያኖች እንደመጡ ሁሉ በቴዎድሮስም ዘመን በትርጉም ስህተት እንግሊዞች መጡ። በቴዎድሮስ ደብዳቤ ላይ «……ጋላ ገዝቶ……» ያሉት እነ ራስ አሊን ነው።

እነ ራሳም ጥቂት ቀናት እረፍት ካደረጉ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ወደ ጣና አካባቢ ለመሔድ እነራሳም አገር እንዲያዩና እንዲላመዱ ብለው አብረው ይዘዋቸው ሔዱ። ጣና ሐይቅ ሲደርሱም ራሳም መቅደላ ያሉት እስረኞች ተፈትተው እስኪመጡ ድረስ ዘጌ ደሴት ላይ ሆኖ እንዲጠባበቅ ትተውት አጤ ቴዎድሮስ ወደ ሜጫ ሔዱ። ከሜጫም ራሳምን ለማስደስት ብለው ወታደሮች ከጫካ የያዙዋቸውን ሁለት የአንበሳ ግልገሎች በልጅ ካሣና በልጅ አብተው ላኩለት። የአንበሳ ግልገሎቹን በላኩለት ጊዜም የሚከተለውን የሰላምታ ደብዳቤ ጻፉለት።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ካቶ ሕምርዝ ርስአም እንዴት ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ወንድሞችኽንም እነሀኪምን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ በፈጣሪየ ሃህይል ካንተ ከተለይሁ ያንበሣ ግልገሎች። ዕየወረቦ ልጅ ማርኬ ሠድጄልሃለሁ የናንተን ደህና መግባት አዳምጣለሁ ብዬ ሜጫ ከሚባል አገር ላይ መጥቸ ሠፍሬአለሁ እግዚአብሔር ቢል እንገናኛለን በታንኳ መሻገር አምሮኛል።



የአንበሳ ግልገሎቹና ይህ የአጤ ቴዎድሮስ ደብዳቤ እንደደረሰው ራሳም የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፈላቸው «........ትናንት የተከበረ ደብዳቤዎን ስቀበል ክብር ተሰምቶኛል።......በደብዳቤው ላይም የግርማዊነትዎን ጤንነት በማወቄ በጣም ተደሰትሁ። እግዚአብሔር በረከቱን እንዳሳደረብዎት ሁሉ ወደ ፊትም እንዲሁ እንዲቀጥል እፀልያለሁ።......የላኩልኝን የአንበሳ ግልገሎቹና ሚዳቋ በደህና ደረሱኝ። ስለዚህና በአገርዎ ከገቡ ጀምሮ ስለተደረገልኝ አክብሮት ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በደግነትዎ ከዋንጂ ተነስተን በሐይቅ ላይ አድርገን ባለፈው ሐሙስ ከዚህ ስንደርስ አቶ ካሣና አቶ ወንዴ ከፍተኛ አቀባበል አደረጉልን። እስካሁንም ያለነው ከእነሱ ቤት ነው። .......»

እስረኞቹ ቀስ በቀስ እያሉ ራሳም ዘንድ ቆራጣ ከተባለው መንደር ተሰባሰቡ። እነኝህም ለመጀመሪያ ጊዜ ራሳም ዘንድ የመጡት የፖለቲካ እስረኝኖች ሳይሆኑ ሚስዮናውያኖቹና ሌላዎቹ አገር ለመጐብኘትና ለጥናት የመጡት ነበሩ። ራሳም ለቴዎድሮስ በጻፈው የሰላምታ ደብዳቤም ላይ የሌሎቹን እስረኞች ከሱ ዘንድ መድረስ ጠቅሶ የምቅደላ እስረኞች ያለመድረሳቸውን ደብዳቤ ጽፈው በልጅ አብተውና በከንቲባ ኃይሉ እጅ ላኩለት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ
ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ከአቶ ሕርምዝ
ረስአም እንዴት ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር
ይመስገን ደህን ነኝ ሐኪም ብሎግናን አቶ ጥራይን
ወንድሞችህን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ ደህና
መግባታችሁን ቆራጥ መድረሳችሁን ሰምቸ
በፈጣሪአችን ኃይል እጅግ ደስ አለኝ። አሁንም
አይዞአችሁ አጋፋሪ ጐለምን ሠድጀዋለሁ እስሮችን
አስፈትተህ ና ብየ በቶሎ አገራችሁን እሠዳችኋለሁ።
፲ቱን ፯ ፯ት አፍ ተራዛሚዎች። ፳ቱን ፪ ፪ አፍ
የወገብ ጠበጆች ከነማፍሰሻቸው የሰጠኸኝን። አቶ
ቢርሳ እኔ ከወንድሜ ልኬ ላንተ በረከት ያስመጣሁት
ነው ብሎ አለኝ እኔም ለአቶ ቢርሳ ፲ሽህ ብር
ዳረግሁት ከትግሬው ነጋድራስ። አቶ ምስንጂር
አጥብቆ ይወድሃል ብለህ የነገርኸኝን የፍቅር በረከት
ስትሄድ የምሠድለትን የሚወደውን ላክብኝ
በእግዚአብሔር ኃይል አስቤ እንድቆይ



ራሳም ከመጣም በኋላ የፈረንጆች ቅጥፈት ቴዎድሮስን ያስገርማቸው ጀመር። ራሳም ለቴዎድሮስ አራት ባለ 2 አፈሙዝ ጠመንጃዎችን (እንደረሽ ያሉ) እና በዘመኑ ምርጥ የተባሉት ሁለት አፈሙዝ ያላቸው ስምንት ሽጉጦችን በስጦታ መልክ ሰጠ። ራሳም ከቴዎድሮስ አጠገብ ሲርቅ ሙሴ ቡርጋድ የተባለው ፈረንሳዊ ጠመንጃ ሠሪ እኔ ከወንድሜ ዘንድ ልኬ ያስመጣሁሎት ነው ብሎ ከቴዎድሮስ 4.000 ብር ተቀብሎ አሁን በዚህ ደብዳቤ እንዳነበብነው ቴዎድሮስ ጠመንጃዎችንና ሽጉጦቹን ራሳም እንዳልሰጣቸውና እሳቸው መግዛታቸውን እንዲያውቁ ለራሳም በደብዳቤ ገለፁለት። ይህ ደብዳቤ ለራስም የካቲት 11 ቀን ሲደርሰውም ደነገጠ።

በደብዳቤውያቸው ላይ የጠቀሱት ምዚንጀር የስዊስ ተወላጅ ነው። እሱም እ.ኤ.አ. በ1864 በምፅዋ የፈረንሳይ ተጠባባቂ ቆንሲል ሆኖ ነበር። በኋላም በምፅዋ የፈረንሳይ ተጠባባቂ ቆንሲል ሆኖ ነበር። በኋላም በምፅዋ እየንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ሆኖ ተሾመ። ይህ ሰው ወደፊት እንደምናነበው የእንግሊዝን ጦር እየመራ መቅደላ ያደረሰ ነው። ከቴዎድሮስም በኋላ አጤ ዮሐንስንና ንጉሥ ምኒልክን ሲያጣላ የኖረ ነው። በመጨረሻው በ1867 ዓ.ም ኢትዮጵያ ውስጥ አፋሮች ገደሉት።

አጤ ቴዎድሮስ እስረኞቹን በሙሉ አስፈትተው እምጋቢት 3 ቀን ከራሳም ዘንድ ከተሰበሰቡ በኋላ አሁን ወደ ራሳቸው ጉዳይ ተመልሰው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ለሚስተር ራሳም ጻፉለት።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ካቶ ህርምዝረ ስአም እንዴት ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ሀኪም ብሎግንና አቶ ጥሪዩን ወንድሞችኽን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ በእግዚአብሔር ቸርነት በኔና በንግሥቲቱ በቢክቶርያ ሀብት ወዳጀ ፍታልኝ ያሉኝን ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል ደህና መምጣታቸውን ከናንት መገናኘታቸውን ሰምቸ እጅግ ደስ አለኝ እኔ ወዳጅ ንግሥቲቱ የላኩብኝ ፈቃድዎን አደረግሁ በእግዚአብሔር ኃይል አሁንም ወዳጅ ንግሥቲቱ የሠደዱልኝ ደብዳቤ እንዲህ ይላል አቶ ሕርምዝ ረስአምን የአደን ሹም የነበረውን አማኛ ሎሌየን ወዳጁን ሠድጄዋለሁና ከኛ የምትፈልገውን ሁሉ ጉዳይ ከርሱ ጋር ተማከር እርሱ ያረግልሃል ብለውኛል አሁንም እኔ የምፈልገው እውር ነኝና ዓይኔ እንዲበራ ጥበብ ነው። አሁንም አንተን ደስ እንዳለህ እኔም ደስ እንዲለኝ በእግዚአብሔር ኃይል ብልህ ልከህ አስመጣልኝ የንግሥቲቱንም ቃል ገልብጠህ የሠጠኸኝን ሠድጃለሁ እንድትሰሙ ት ብዬ እኒህን ያስፈታሀቸውን ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል እውነት አዋረዳችሁትን አላዋረዳችሁትም ብለህ ጠይቃቸው ወንድሞችኽን ይዘህ እነ አቶ ዋልድ ማየርን ጨምረህ

ዓለም ከተፈጠረ በ፯ሽ ከ፫፻፶፰ ዓመት ጌታ ከተወለደ በሽ ከ፰፻፶፰ ዓመት በዘመነ ማርቆስ በወርሀ መጋቢት በ፮ ቀን ተጣፈ።



ይህ ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ ራሳም በጣም ደነገጠ። በተጻፈለት ደብዳቤ ላይ «ወዳጄን» የሚለውን ቃል በቅንፍ ከቦ የኤክስ ምልክት አደረገበት። ምክንያቱም ንግስቲቱ ራሳምን «ወዳጅጄን» ብለው እንዳልጻፉና ሊሉትም እንደማይገባእው ስለሚያውቅ ነው። ቀጥሎ «ከኛ የምትፈልገውን ሁሉ ጉዳይ ከርሱ ጋር ተማከር። እሱ ያረግሃል» የሚለውንም አረፍተ ነገር እንደዚሁ በቅንፍ ከብቦ ከደብዳቤው ሕዳግ ላይ (NO INSTRUCTION THUS) የሚል ጽፎ ከርሙዝ ራሳም ለማየት H.R ጻፈበት። ይህም አረፍተ ነገር ንግሥቲቱ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ስላልነበረ ታላቅ የትርጉም ስህተት መፈጠሩ ገባው።

ራሳም የተፈቱትን እስረኞች በድንኳኑ ውስጥ ሰብስቦ ከቴዎድሮስ የተጻፈውን ደብዳቤ አነበበላቸው። የተፈቱትም ሰዎች ምንም ጥፋት እንዳልሠሩ ተናግረው በመጨረሻው ለንጉሱ ክብር ሲባል ብቻ ጥፋታኞች ነን እንዲሉ ተደርጐ ራሳም ይህንኑ በደህናው ጥፋተኛነታቸውን ብቻ ገልሶ ለቴዎድሮስ ጻፈ። አጤ ቴዎድሮስም የተበደሉት በደል በዝርዝር ባለመነገሩ አዝነው የተበደሉበት ሁኔታ ለራሳም ለማስረዳት የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉለት።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ካቶ ህርምዝ ርስአም እንዴት ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ሀኪም ብሎግናን አቶ ጥረዶን ወንድሞችኽን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ። ኵንሱል ነኝ ብሎ ያለው የኬምሮንም ነገር እንዲህ ነው። ባርደልን ወኪል አድርጎ እርሱ አይተናኝ ሁኖ የንግሥት መልክተኞች መጥተናልና ተቀበልኝ ብሎ ላከብኝ እኔም በእግዚአብሔር ኃይል ደስ ብሎኝ ምጥዋ ድረስ ሰው ሰድጄ አስመጣሁት ሜጫ ደብረ መይ ከሚባል ሠፍሬ ቢደርስ መኳንንቶች ወጥተው ተቀበሉት መድፍ አስተኮስሁ እንደ አገሬ ሥራት አንጥፌ ተገናኚሁት በእግዚአብሔር ኃይል። የንግሥት ደብዳቤ ነው ብሎ ሰጠኝ ደብዳቤውን ባነበው ፸ አፍ ተራዛሚ ፩ ነፍጥ ፪ት ፪ ፪ት አፍ የወገብ ጠበንጃ የንግሥት በረከት ነው ብሎ ሠጠኝ እግዚአብሔር ይሥጥልኝ ብዬ እጅ ነስቸ ተቀብያለሁ። በቀረ ግን የደብዳቤው ቃል ወዳጅ አንሁን ዘመድ እንሁን አንተም እንዳፈቀርኽን እንደወደድኽን ሰምተናል በነቡላዲን ነገር ካገርህ ሰው ጋራ የተዳረግኸውን ጥንትም ኢትዮጵያና እንግሊዝ አንድ ነው ፍቅር ነው ዛሬም እኛ ቈንስል ካንተ አገር እንዲቀመጥ አዳኝ እንዲአድን ነጋዴ እንዲነግድ እንዲመላለስ የኛ ሰው ያንተ ሰው ነውና ጠብቅልነ እለኝ። ያንተም ኵንሱል ከኛ አገር መጥቶ እንዲቀመጥ አዳኝህ እንዲአድን ነጋዴህ እንዲነግድ በእግዚአብሔር ኃይል እንጠብቅልሃለን ብሎ አለኝ እሺ ብዬ ደስ ብሎኝ እንዳገሬ ሥራት ደስ የሚለኝን ሁሉ አድርጌለት ለባርደልም ለርሱም ቱርኮች አገሬን ይዘውብኝ ባለጋራ ሁነውኛልና መርከብ የለኝ በባህር አልችላቸውም በእግዚአብሔር ኃይል የምሠደውን በረከት ሎሌየን የሚቀበለኝ ሰው ይስደዱልኝ ብዬ የፍቅር ደብዳቤ ሠጥቸ ሰደድሁት ከወዲያ ተላክሁ ብሎ የመጣህበትን ከዚህ ተማክሮኝ የሄደበትን ጉድይ ትቶ ከቱርኮች ከማይወዱኝ ሰዎች ሂዶ ሲአዋርደኝ ሢንቀኝ ሰንብቶ መጣ የሠጠሁህ የፍቅር ደብዳቤ ምላሹ የት አለ ምን ይዘህ መጣህ ብዬ ብጠይቀው እንጃ አላውቅም አለኝ እንግዲያ የወዳጅም ሎሌ አይደለህ ብዬ በፈጣሪየ ኃይል አሠርሁት። ይኸን አሉ ቢልህ በቃሉ ጠይቀው።

የባርደልሞ ነገር ከፈረንሲስ ንጉሥ ላስተዋውቅህ ብሎኝ እሺ ብየ ብሠደው እስከልክሎ እምቢ ብሎ ሠደደኝ ብሎ መጣ ብሻው እግዚአብሔር አለኝ ብዬ ዝም ብየ ተቀምጬ ሣለ ፈረንሲስ ነውና መክረርን ፍታ አለኝ ከወዲያ ላስተዋውቅህ ብለህ ሂደህ አስከልክሎ ሠደደልኝ አልህ የማን ወዳጅ ብየ ነው የምፈታው አይሆንም አልሁት በዚህ ተቆጥቶ ካደባባይ ሸማዉን ታጥቆ የነበረውን ፈትቶ ተከናነበ በዚህ ተቆጥቸ አሠርሁት በጌታየ ኃይል አሉ ቢልህ ጠይቀው። ይህን ሁሉ አይደለም እወዳቸው አቆላምጣቸው ነበርና ወዳጅ ጋሻ ነውና በመከቱልኝ በእግዚአብሔር ኃይል ብየ ነው የጠላኋቸው አሁንም በእግዚአብሔር ኃይል ንግሥትን የአገርዎን ሰው እናንተ እየወደድሁ እኒህን እንደገና ተመልሼ የምጠላቸው ነኝ ካንጀት አስታርቁኝ በድየ እንደሆነ እዩብኝና ልካስ ተበድዬ እንደሆነ የፍቅር ካሣ አስክሱኝ።




ከዚህ ደብዳቤ በኋላ እስረኞቹ በሙሉ ጥፋተኛነታቸውን ነማመናቸው ቴዎድሮስ ተደሰቱ ራሳምም ጥፋት እከስረኞች እንጅ ከቴዎድሮስ ዘንድ ያለመኖሩን በደብዳቤ ገለፀላቸው። አጤ ቴዎድሮስም ከራሳም ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ ለእስረኞቹም ሙሉ ምህረት ማድረጋቸውን በሚከተለው ደብዳቤ ለራሳም አሳወቁ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ካቶ ሕርምዝ ጊስአም እንዴት ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ሀኪም ብሎግን አቶ ፕሪዶን ወንድሞችኽን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ የነኬምሮንንም ነገር ወዳጆች ብዬ ሣቆላምጣቸው በድለውኝ መገኘታቸውን እንኳ እናንተ ታውቃላችሁልን እንጂ ከእግዚአብሔር በታች ሡለታላቂቱ ንግሥት ሡለወዳጆ ሡለ ቢክቶርያ ይቅር ምንተ እዚአብሔር ታርቄአለሁ። በእግዚአብሔር ኃይል ደስ አሠኝተህ የላክህብኝን ቃል እጅኽን እግርኽን ዝቅ ብዬ የምሥምህ ነኝና መጥታችሁ ተገናኙኝ እንድንመካከር። የነኬምሮን ታስረውየነበሩት እናንት ምሽት ዘመዶች አልቅሠው የላኩብኝን በእግዚአብሔር ኃይል ሡለታላቂቱ ንግሥት ሡለወዳጅ ሡለ ቢክቶርያ ታርቂላቸዋለሁ ሁሉንም በፈጣሪአችን ኃይል ሡንገናኝ እንመካከራለን

በመጋቢት ፲ ቀን እሁድ ተጣፈ።




አጤ ቴዎድሮስ ምህረት ማድረጋቸውን በዚህ ደብዳቤ ብቻ ላያቆሙ እንግሊዝ አገር ላሉት ለእስረኞቹ ቤተሰቦች የሚላክም የሚቀጥለውን ደብዳቤ ጽፈው ለራሳም ላኩለት።



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ካዝንተኞች ሁሉ እንዴት ሰነበታችሁ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ።
ያዘንተኞች መቅደስ ታሠሩን ያላችሁቱ በእግዚአብሔር ኃይል በንግሥቲቱ በቢክቶርያ ወዳጅነት ፈትቸ ለአቶ ህርምዝ ረስአም ሠጠሁላችሁ ደስ ይበላችሁ።


አጤ ቴዎድሮስ ዘጌ ከመጡ በኋላ የተለቀቁትን እስረኞች ለስንብት ዘጌ ድረስ የሚያመጣቸው ጀልባዎች ላኩላቸው። በከንቲባ ኃይሉ የሚታዘዙት ጀልባዎች እንደደረሱ ራሳም እስረኞቹ የነበሩትን ሁሉ ይዞ ወደ እሳቸው እንዲመጣ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጻፉለት።



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ካቶ ህርምዝ ረስአም እንዴት ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ሀኪም ብሎግንና አቶ ፕሪዶን ወንድሞችኽን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ በእግዚአብሔር ኃይል በደኅና ተመልሼ ከቤቴ ገባሁ ፈረሶችን ካገር የነበሩትን ልቀበል ሂጀ ነበረ አሁንም እግዚአብሔር ጤና ከወዳጆች ከናንተ ጋራ ለመገናኘት ይብቃ ፊት ለማልወዳቸው አስሬአቸው። ለነበርሁ ሰዎች ከናንት እስቲገናኙልኝ ድረስ ከፈጣሪአችን ጤና ሠጥተህ አድርሥልኝ እያልሁ እለምን ነበረ ዛሬ ግን ከላይ ለንግሥቲቱ ለወዳጀ ከዚህ የደሥታ አበባ ለያዛችሁልኝ ለናንተ እድሜና ጤና ይስጥልኝ እያልሁ እለምናለሁ እኔን የሚወዱበት ልቦና ሥጥልኝ እያልሁ እለምናለሁ ፈጣሪያችነን እኔ ግን እንግሊዞችን እወዳችሁም እጠላችሁም በዮሐንስ በቡላንዲን ጠይቃችሁ አግኙት። እብተቻለኝ እንዳገሬ እንዳቅሜ ማቆላመጤን መውዴን አልተውሁም ነበረ። እኒያን መውደዴን ማቆላመጤ የንግሥቲቱን የአንተን ፍቅር አገኝ ሥል ነው አሁንም ወትሮ እፈልገው የነበረ ፍቅራችሁ ተገኘልኝ መስሎኝ በፈጣሪአችን ሠድጀላችኋለሁ። በቃ እንግዳ ጋራ ኑና እንድንማከር እነከንባም እናንተም።

በመጋቢት በ፲፭ ቀን ዓርብ ተጣፈ።

እስካሁን ባነበብናቸው ደብዳቤዎች ሁሉ አጤ ቴዎድሮስ ስም ሲጠሩ ብሎግና የሚሉት ብላንክን ፕሪዶን የሚሉት ፕሪዲውክስን ነው። በኋላም የመጡትን እንግሊዞች የበፊተኞቹም እስረኞች ጭምር በተላላኩባቸው ጆላብዎች ሆነው ወደ ዘጌ ሔዱ። ቴዎድሮስ ከእስረኞቹ ጋር ከእስረኞቹ ጋር እንሰነባበት ያሉትን ሀሳብ ራሳም አልወደደውም። ምክንያቱም ቴዎድሮስ የሚጠሉዋቸውን ሰዎች ሲያዩ ምናልባት ይናደዱና ነገር ይበላሻል ብሎ ነው። ራሳም በዚህ ሐሳብ ላይ እያለ ከቴዎድሮስ የተጻፈ ደብዳቤ ደረሰው።



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ካቶ ህርምዝ ረስአም። እንዴት ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ሀኪም ብሎግን። አቶ ፕሪዶን ወንድሞቾኽን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ ስልስትና ደህና መግባታችሁን የሚጠይቅ ደብዳቤ ሠድጄ ነእብረ ኋላ ግን እነ ልጅ አባተ ደህና መግባታችሁን መጥተው ነገሩኝ በእግዚአብሔር ኃይል እጅግ ደስ አለኝ። የነከንቲባ ጉዳይ ያዘዝኋቸው ተሰናድታችሁ ቆዩ በእግዚአብሔር ኃይል

በመጋቢት በ፳፪ ቀን አርብ ተጣፈ።

ይህ ደብዳቤ እንደ ደረሰው የተጨነቀው ራሳም ለመለማመጥና በቴዎድሮስ ዘንድ ያለውን ፍቅር ላለማጣት ብሎ ካለችው ቅርስ እጅ ጠባብ ለቴዎድሮስ ላከ። የራሳም ጭንቀት የቴዎድሮስ ጠባይ ተለዋዋጭ መሆኑን እስረኞቹ ነግረውታል። አሁንም በመፈታታቸውም እርግጠኛ ሆነው አልተደሰቱም። ምክንያቱም ቴዎድሮስ ከፋ ባላቸው ቀን መልሰው እንደሚያስሯቸው ስለሚያውቁ ነው። ራሳም ይህን ሁሉ ለሚነግሩት እስረኞች ምንም አደጋ እንደማይደርስ ቢነግራቸውም እስረኞቹ አላመኑም ነበር። ስለዚህ የራሳም ሥጋት እየበዛ በመሔዱ ለመለማመጥ ብሎ እስረኞቹ የሰጧቸውን እጀጠባቦች በሥጦታ መልክ አቀረበ። አጤ ቴዎድሮስም ለተደረገላቸው ስጦታ ምስጋና ሲያቀርቡ እንዲህ ብለው ጻፉ።

በስመ አብ ወወልድ መንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ከአቶ ህረምዝ ረስአም እንዴት ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ሀኪም ብሎንግን አቶ ፕሪዶን ወንድሞችኽን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ የሠደድህልኝ እጀ ጠባብ በወና ሞሀመድ እጅ ደረሠልኝ እግዚአብሔር ይሥጥህ ምነው ዛሬማ የኔ እንግዳ አይደለኽም በተቻለኝ እኔ ልጨነቅልህ እንጂ አንተ ለምን ታሥለህ። እግዚአብሔር ቢረዳህ በምፈልገው ጉዳይ ተጨነቅልኝ እንጂ እንግዴህ በገንዘብ አትጨንቅልኝ አደራኽን ወንድሜ ወገራ ጫፍ አምባጫራ ላይ መልክተኞች ሢመጡ የኔ ሰዎች ይዘው ደብዳቤአቸው ቀምተው ሰዎቹን አስረው ደብዳቤውን ስደዱልኝ ባየው የፈረንጅ ማኅተም ሆነ ያንት እንደ ሆነ ብየ ልፍታ ሠድጀልሃለሁ ያንተ የሆነ እንደ ሆነ ሰውየውን የሚአስፈታ ሠድጀልሃለሁ ያንት ያለሆነ እንደ ሆነ ደብዳቤውንም መልሰህ ሥደድልኝ እስሩንም ወደኔ እንዲ አመጡት አረጋለሁ። የናንተ ፋሢካ ወደፊት መሆኑን ሣላውቅ አንደኛው ፋሢካ ምነው መስሎኝ ፍሪዳ ሥጡ ብዬ ልኬ ነበረ ባውቅሁኝ የፋሢካችሁ ለት አንድታከብሩ አረግ ነበረ ይል በገዛ ቤትህ በገዛ ወዳጅህ በገዛ ወንድምህ

መጋቢት ፳፩ ቀን ሰኞ ተጣፈ።



በደብዳቤው ላይ ራሳም የላከው አንድ እጀ ጠባበ ይመስላል ራሳም እንደሚገልጸው ግን 12 ያህል እጀ ጠባቦችና ሸሚዞችን ነው የላከላቸው። መጋቢት ወር አልቆ ሚያዝያ እስቲገባ ማንኛውንም ነገር በሰላምና በፍቅር ሲካሔድ ቆየ። በሚያዝያ ወር እስረኞቹ የነበሩት በሙሉ ወደ አገራቸው እንዲሄድ ተወስኖ ነበር። ኤሮፓውያኖቹም ወደ አገራቸው ለመመለስ ጓጉተዋል። ዘመዶቻቸውንም ለመገናኘት ናፍቀዋል። የበፊተኛውን ብላንክ ሲጽፍ «........በውስጣዊ መንገድ የነበረውን ሁኔታ ስላልተረዳነው ማንኛውንም ችግርና እንቅፋት የተወገደልን መስሎን ፍርሃታችንን ቀንሰን በአየር ላይ ግንብ መሥራት ጀመርን። በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ አገራችን ተመልሰን ዘመድ ወዳጆቻችንን ለመገናኘት ጓጉተን ሱዳን በሪሃ ስናልፍ የሚገጥመንን ድካም ስንፈራ በድንገት ፕሮግራማችንና ፍላጎታችን በጭካኔ ተደምስሶ ሁኔታው ተለወጠ» ይላል። ብላንክ እንዳለው ሁኔታው ተለውጧል። የሁኔታውንም መለወጥ ያጠራጠራቸው አጤ ቴዎድሮስ በድንገት የጻፉላቸው ደብዳቤ ነበር።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ የእግዚአብሔር ፍጡር ባርያው የዳዊት የሰሎሞን ልጅ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ከንግሊዝ ንግሥት ሎሌ ከወዳጆ ከማካሪየ ካቶ ህምርዝ ረስአም የምፈልገው የምትልክልኝ መድፍ ሠሪ ነፍጥ ሠሪ ብረት አቅላጬ ቡምባ ተኳሽ መድፍ ተኳሽ እኒህ ሁሉ ሠራተኞች አሣይተኝ እንዲያመለሱ ከነመሣሪያቸው ይምጡልኝ በእግዚአብሔር ኃይል ይህን ጥፈህ ላክልኝ በእግዚአብሔር ኃይል።



አጤ ቴዎድሮስ እንደገና የሠራተኞቹን ጉዳይ ካነሱ ሠራተኞቹ እስቲመጡ ድረስ እነኝንና እንደመያዣ ሆነው እንሚቆዩ ገባቸው። አንዳንዶቹም ምህረት ተደርጐልን ስለተለቀቅንና እንድንሔድም ስለተፈቀደልን የደብዳቤው ጥያቄ ከሔድን በኋላ የሚፈፀመውን ነው በማለት ተናገሩ።

ለእስረኞች የተፈቀደላቸው የመሔጃ ጊዜ ስለደረሰ እስረኞቹ የነበሩትን ሰዎች በሙሉ ከቴዎድሮስ ሳይሰናበቱ ጉዞ እንዲጀምሩ አድርጐ ራሳም ግን ቴዎድሮስን ተሰናብቶ እንደሚደርስባቸው ገለፀና ሌሎቹ ጉዞአቸውን ጀመሩ። ራሳምና አብረውት የመጡት የኋለኛው ጊዜ መልክተኞች ግን ለመሰናበት ከቴዎድሮስ ፈቃድ ጠይቀውና ተቀብለው ወደ ዘጌ ሔዱ።

አርብ ዕለት ዘጌ ሲደርሱ ከፍ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው። ራስ እንግዳ ከሌሎች መኳንንቶችና ሠራዊት ጋር ሆነው በዘጌ ወደብ ተቀበሉዋቸው። ከዚያም ምርጥ በሆነ ዕቃ ባጌጡ በቅሎዎች ተቀምጠው ወደ ንጉሡ ሠፈር ሔዱ። ከቴዎድሮስ አዳራሽ ደርሰው ሲገቡ በአዳራሹ ውስጥ ብዙ ወታደሮች ቆመዋል። ቴዎድሮስ አዳራሽ ደርሰው ሲገቡ በአዳራሹ ውስጥ ብዙ ወታደሮችና መኳንንት ቆመዋል። ቴዎድሮስ ግን የሉም። እየተነባበረ እነራሳምን እያነቀ ያዛቸው። ታጥቀውት የነበረውንም ዝናርና ጐራዴ ፈትተው ወሰዱባቸው። ልብሳቸውም ተቀዳደደ። ከመሬት ላይ አስተኝተው ያዙዋቸው። ከጥቂት ጊዜ ሽብር በኋላ ይቀመጡ ተብለው እጅ እጃቸውን ከያዛቸው ወታደር ጋር ከመሬት ከተነጠፈው ምንጣፍ ላይ ተቀመጡ።

ይህ ከሆነ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ መጥተው ከዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው «እስረኞቹ የታሉ? ለምን ወደኔ አልመጡም? እኔ ሳልፈቅድ መሰደድ አይገባችሁም» እያሉ ጠያይቀው በመጨረሻው «ወንድሞቻችሁን ለማስመጣት ልኬአለሁና እነሱ ከመጡ በኋላ የሚደረገውን እነግራችኋለሁ» አሉዋቸውና ጥቂት እልፍ ብሎ ከተተከለላቸው ድንኳን ውስጥ እንዲገቡ አዘዙላቸው።

ወዲያውኑም ሌሎቹ እስረኞቹ የነበሩት ኤሮፓውያን ተይዘው እንዲመጡ ለቢትወደድ ተድላ ደብዳቤ ተጻፈላቸው። ደብዳቤውም በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ከቢትወደድ ተድላ። እንዴት ከርመሃል። እኛ ደህና ነን። ከወዳጆቻችንና ወደ አገራችን እንሔዳለን ካሉት አይሮጳውያን ጋራ ተቀያይመናል። እሱም ገና እርቅ

ባለማረጋችን ነው። በነገሩ መክረን የምናደርገውን እስከ ወሰንን ድረስ ሰዎቹን ያዟቸው። ግን ጉዳት እንዳይደርስባቸውና እንዳይፈሩ ይሁን» የሚል ነበር።

እስረኞቹ የነበሩት እንደ ገና ተይዘው ሚያዝያ 9 ቀን 1858 ዓ.ም ሰኞ ዕለት ዘጌ ደረሱ። እንደደረሱም ሁሉም በአንድነት ሆነው ከቴዎድሮስ ችሎት ቀረቡ። አጤ ቴዎድሮስም «እኔን ለምን ሳትሰናበቱና ሳታስፈቅዱኝ ከአገሬ ለመውጣት ሞከራችሁ?» ብለው ጠየቁ። እስረኞቹም ግርማዊነትዎ ለሚስተር ራሳም ስለሰጡን ሚስተር ራሳም ባዘዘን መሠረት ነው የሔድነው ብለው መለሱ።

«ታዲያ ለምንድነው ረምህዝ ወደኔ አምጥቶ እንዲያስታርቃችሁና እንዳያሰናብታችሁ ያልጠየቃችሁት?» ብለው ወደ ራሳም ዞር አሉና «ይህ ከሆነ ጥፋቱ ያንተ ነው። ከነዚህ ሰዎች ጋር እንድታስታርቀኝ ነግሬህ አልነበረምን? ለምንድነው በዚህ መሠረት ያልፈፀምከው?» በለው ጠየቁት። ራሳምም «ከእነዚህ ሰዎች ፍርድ በኋላ በላኩልኝ የይቅርታ መጠየቂያ ደብዳቤ እርቁ የተፈፀመ መስሎኝ ነው» አላቸው።

አጤ ቴዎድሮስም «ለእነዚህ ሰዎች መጓጓዣ የሚሆን በቅሎና ለስንቃቸውም ገንዘብ ልስጣቸው ብልህ በቅሎም ገዝቼላቸዋለሁ። ለስንቃቸውም በቂ ገንዘብ አለ አላልከኝም? እነዚህን ሰዎች ከአበሻ አገር በልዩ መንገድ ለማውጣት ፈልገህ ከነገርከኝ ቀን ጀምሮ ባንተ ላይ ጥርጣሬ አድሮብኛል። አገርህ ስትገባ እነዚህን ሰዎች በሰላም አስፈትተህ የወሰድካቸው መሆኑን ትተህ በተንኮልና በዘዴ እንዳወጣሃቸው አድርገህ ለመፎከር መሰለኝ።......» አሉትና ያለ ምንም ውሳኔ የተሰበሰበውን ጉባኤ በትነው ተነሱ።

በማግስቱ ሁሉም የታሰሩበት ሰንሰለት እንዲወልቅላቸው ተደርጎ ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ቀረቡ። በዚህኛው ችሎት አጤ ቴዎድሮስ ፈረንጆቹን ሁሉ ቀረብ በሉ ብለው እንዲቀመጡ ከፈቀዱላቸው በኋላ «......በእናንተ ላይ እንድናደድና በፕላውዴ ጊዜ በኔና ነእንግሊዝ መሀል የነበረውን መልካም ወዳጅነት እንዲበላሽ የሚያደርገው ሰይጣን ነው። ከልጅነቴ ጀምሮ ኤሮፓውያኖችን እወዳለሁ። በተለይንም እንግሊዞችን። እግዚአብሔር በሚያስቀው ከጧት እስከ ማታ የማስበው ከእንግሊዝ ሕዝብ ጋር ያለኝን

ወዳጅነት ለማጠንከር ነው። የማይካደው ነገር ቱርኮችን እዋጋለሁ። ነገር ግን እንግሊዞችን ለመዋጋት ፈፅሞም በአእምሮዬ የለም። የምመኘው እንዲወዱኝና ወዳጆቼ እንዲሆኑ ነው።

«አቶ ኮከብ (እስተርን) የዋህ ገራገር ሰው ነህ። አንተ አይደለህም የሰደብከኝ። የሰደበኝ እሱ ነው። አቶ ፍላድም እግዚአብሔር በሚያውቀው በሱ ላይ መጥፎ ሐሳብ የለኝም። ከኔ ጋር የሚቀያይመው አንድም መጥፎ ነገር አልሠራም። አቶ ራሳም በሕይወቴ ካጋጠሙኝ ጥሩ ሰዎች አንዱ አንተ ነህ። እንድቆጣ ከሚያደገግ ምንም የሠራኸው ነገር የለም። እርግጥ አንድ ቀን በነገርህ ግልፍ ብሎኛል። ይህንንም ያደረገው ሰይጣን ነው። አሁን እንግዲህ ሰላም እንመሠርታለን። ያለፈውን እንርሳው። በፍቅር ወዳጅነታችንን እናድሳለን»…….ብለው ተናገሩ።

አጤ ቴዎድሮስ ይህን ንግግር ካደረጉ በኋላ ከዙፋናቸው ተነስተው ይቅርታ ጠየቁ። እስረኞቹም ተጠያቂዎች ሳይሆን እነርሱ ይቅርታ እንዲደረግላቸው ለመኑ። አጤ ቴዎድሮስ ግን ኤሮፓውያኖቹ ይቅርታ እንዲያደርጉላቸው ወጥረው ስለያዙ ፈረንጆቹ እንደ አገራችን ባህል «ለእግዚአብሔር ብለን ይቅር ብለናል» ብለው ተናገሩ። ይህንንም ብለው ወዲያው ሁሉም ተንበርክከው ለሠሩት በደል አጤ ቴዎድሮስ ይቅርታ እንዳያደርጉላቸው ለመኑ። እሳቸውም «ለእግዚአብሔ ብዬ ይቅር ብያለሁ» አሉና ተቀመጡ አሏቸው።

ከዚህ በኋላ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥት የሚላከውን ደብዳቤ መጻፍ ጀመሩ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ የእግዚአብሔር ፍጡር ባርያው የዳዊት የሰሎሞን ልጅ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ እግዚአብሔር ከሰው ሁሉ መርጦ አልቆ ካነገሠዎ ሃይማኖት ፍቅር ከሚወዱ የተጠቃ ድሀ ከሚጠብቁ ከእንግሊዝ ንግሥት ከቢክቶርያ። አቶ ህርምዝ ረስአምን ሎሌዎን በኬምሮን ጉዳይ ሰድጄዋለሁ ያሉሻን እንኳ እርስዎ የባርያዎ ባርያ ቢልክብኝ። እምቢ እላለሁ። እሺ እነሆ በእግዚአብሔር ኃይል አቶ ኬምሮንን ፈትቸ ለሎሌዋ ለአቶ ህርምዝ ረስአም ሰጠሁ። የአይሮጳን ሰዎች ሁሉ የታሰሩትን ፍታልኝ ይሉሻን በእግዚአብሔር ኃይል ፈትቸ ባንድ ሠጠሁ የአይሮጳን ሰው ሁሉ ወደ አገሩ መመለስ የሚአምረውን በእግዚአብሔር ኃይል እሺ ሠጠሁ አቶ ህርምዝ ረስአምን ሎሌዎን ያሰነበትሁት ከኛ የምትፈልገውን ሁሉ ጉዳይ ከርሱ ጋር ተማከር ባሉኝ ረገድ ከርሱ ጋራ እየተማከርሁ እልክብዎ ብየ ነው። የኢትዮጵያ ሰዎች እውር ነን ዓይናችነን ያብሩልን። እግዚአብሔር በሰማይ ያብራለዎ። በ፯ሺ ተ፫፻፶፰ ዘመን። ዓለም ከተፈጠረ።

ክርስቶስ በተወለደ በሽ ተ፰፻፶፰ ዘመን በዘመነ ማርቆስ በወርኃ ሚያዝያ በ፲ ቀን ዘጌ ላይ ተጣፈ።



በደብዳቤው እንዳየነው አጤ ቴዎድሮስ ራሳምን ለማስቀረት ወስነው። «.......እውር ነንና ዓይናችንን ያብሩልነ....... » ባሉት መሠረት ኢትዮጵያውያን በዘመኑ ከዓለም ሥልጣኔና ጥበብ ተለይተው ሳያዩም ሳይሰሙም ይኖሩ ስለ ነበረ በዓለም ያለውን ጥበብ በራስም አማካይነት በእንግሊዝ መንግሥት ረዳትነት ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት አስበው ነው። ሆኖም ይህ ድርጊት ወይም የራሳም በኢትዮጵያ መቅረት በትርጉም ስህተት የመጣ እንጂ ንግሥት ቢክቶርያ በጻፉት ደብዳቤ ራሳም በኢትዮጵያ ቀርቶ ጉዳይ ፈፃሚ ይሁን አላሉም። ራሳምም ቢሆን የሚያውቀው የንግሥቷን ደብዳቤ አድርሶና እስረኞቹን አስፈትቶ መመለስ እንጂ የመቅረቱን ጉዳይ በውኑም በሕልሙም አላሰበውም። አጤ ቴዎድሮስም ከበፊቱ እንዲህ ዓይነቱን የመቅረት ነገር አንስተውበት ቢሆን ምናልባትም አንድ ስምምነት ወይም የመግባቢያ ቋንቋ ሊፈጠር በቻለ ነበር።

አጤ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቢክቶሪያ ደብዳቤ የጻፉ ዕለት ራሳምም ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አንድ ደብዳቤ ጻፈ። አፕሪል 18 (በኛ ሚያዝያ 10) ቀን 1866 (በኛ 1858) ዓ.ም ራሳም የጻፈው ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነበር።

«......ከዶክተር ብላክና ከሚስተር ፕሬደውክስ ጋር ሆነን ጃንዋሪ 28 ከአበሻው ንጉሥ ነገሥት ዘንድ ደረስን እንደደረስንም ንጉሥ ነገሥቱ በታላቅ ክብር ተቀበሉን። በመንከባከብና በቸርነትም አቆዩን። የንግሥትንም ደብዳቤ በአክብሮት ተቀብለው የከበረ መልስም ጽፈዋል።......» ብሎ የተደረገውን አቀባበልና መስተንግዶ ከገለፀ በኋላ «........ንጉሥ ነገሥቱ ስለ ጉዞዬ ወጭ 10.000 ብር ሰጡኝ። በደግነትና በእንክብካቤም ይዘውኛል።......የልውላኖች በቅሎ ኮርቻ ጋሻ የተለያዩ ጎራዴና ጦር ሰጥተውኛል። አብረውኝ ላሉትም ጋሻ ጦርና የተለያዩ ሥጦታዎች ሰጥተውኛል። አብረውኝ ላሉትም ጋሻ ጦርና የተለያዩ ሥጦታዎችን ሰጥተዋቸዋል። በተጨማሪም አምስት በቅሎዎች ሰጥተውናል።.........

«ንጉሥ ነገሥቱ ከጥቂት ዓመትታት በፊት ጀምሮ ጠቢባን ሰዎችን ከእንግሊዝ አገር ለማስመጣት ይፈልጋሉ። ትናንትናም ስንነጋገር ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች እንዲመጡላቸውና መድፍ ጠመጃና ጥይት አንዲት እንደሚሠራ ብረት አንዲት እንደሚቀልጥ ሰዎቻችችሁን እንዲያስተምሩላቸው

መፈለጋቸውን ነገሩ። እንዳሉም፣ እነኚህ ሰዎች ሲመጡ የሚያስፈልገውን ዕቃና መሣሪያቸውን ሁሉ ይዘው እንዲመጡና ሰዎቻቸውን ካስተማሩ በኋላ በደህና ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ነገሩኝ።.......ለክብርነትዎ የማሳስበው........ከዚች አገር ጋር ለወደፊቱ ጥሩ ወዳጅነት እንድንመሠርት ነው።

«የግርማዊት ንግሥት መንግሥት ፈቃዱ ሆኖ አንድ መቶ ሺ የተለያዩ ጥይቶች ጥቂት ባለ ሁለት አፍ ጠመንጃዎች ሽጉጦች፥ ንጉሱ በባሕሮች ላይ የሚሔዱበት አንድ ጀልባና የሚሆነውን ነገር ሁሉ ይህን ደብዳቤ ባመጣው በሚስተር ፍላድ እጅ እንዲላክልኝ አሳስባለሁ።

«የግርማዊት መንግስት ጠቢባኖቹን ለመላክ ፈቃዱ ከሆነ ሰዎቹ እዚህ በሚመጡበት የንጉሠ ነገሥቱ ሠራተኛ ሆነው ቢያንስ አንድ ዓመት እንደሚቆዩ.......ቢነገራቸው መልካም ነው......የሚል ነበር።

ይህንና አጤ ቴዎድሮስ ለንግስት ቪክቶሪያ የጻፉትን ደብዳቤ አቶ ፍላድ እንዲያደርስ መልሱን ይዞ እንዲመጣ ተመርጧል። ፍላድ ደብዳቤዎችን ይዞ ከመሔዱ በፊት ከንጉሱ ለመሰናበት ከራሳም ጋር ሆነው ወደ አጤ ቴዎድሮስ ድንገት ሳይታሰቡ ከራሳም ዘንድ መጡ። እንደመጡም ከራሳም ድንኳን ሲገቡ የራሳም ድንኳን ምንጣፍ የሌለበት ስለነበረ በአስቸኳይ ምንጣፍ እንዲመጣ አዘዙ። ምንጣፍ እንደ መጣም ከራስ እንግዳና ከአቶ ሳሙኤል ጋር ሆነው ራሳቸው ቴዎድሮስ ምንጣፎቹን አነጠፉ። ምን ያህል ትሁት ንጉሱ መሆናቸውንም ለፈረንጆቹ አሳዩ። የብላንክና የፕሪዲውክስ ድንኳኖችም እንዲነጠፉ አዘዙ። ጥቂት ተጨዋውተውና ፍላድን ተሰናብተው ሊሔድ ሲነሱ ራሳም ቀረብ ብሎ እስከ ቤታቸው ለመሸኘት እንዲፈቅዱለት ለመናቸው። ቴዎድሮስም «ማለፊያ ነው በልና» ብለው እጅ ለእጅ ተያይዘው ይጓዝ ጀመረ።

ከራሳም ጋር እጅ ለጅ ተያይዘው እየተጫወቱ ሲሔዱ ከፈረንጆች ሠፈር ሊወጡ ሲሉ የፈረንጆቹን ጠባቂ ራስ ወልደ ማርያምን ቆመው አገኙዋቸው። ቴዎድሮስም ቆም አሉን «ምን ታደርጋለህ? » ብለው ጠየቋቸው። ራስ ወልደ ማርያምም «እየጠበቅሁህ ነኝ» ብለው መለሱ። ቴዎድሮስ ይህን መስል እንደሰሙ ቆጣ ብለው «ምን! ወዳጄን ራሳምን ነው የምትጠብቀው? በል አሁን ከዚህ ሂድ። እሱን የምፈራበት ምንም ነገር የለኝም «ብለው በእጃቸው

ወደራሳቸው አፍ እየጠቆሙ» እየው። እዚህ ውስጥ የሸጉጥ አፈሙዝ ቢያስገኝ እንኳ አልጠረጥረውም» አሏቸው። ጥበቃው ግን ላላ እንጂ ጨርሶ አልተነሳም።

አቶ ፍላድ እንግሊዝ አገር ሔዶ መልሱን ይዞ እስኪመጣ ድረስ ኤሮፓውያኖቹ በሙሉ በመያዣ ስም እንደሚቆዩ ተነግሮአቸው። ፍላድም ቀደም ብለን ያነበብናቸውን ደብዳቤዎች ይዞ ሚያዝያ 20 ቀን 1858 ዓ.ም የእንግሊዝ አገር ጉዞውን ጀመረ። መጀመሪያ ወደ ኤደን ሔደ። በዚያም ሲመካከር ከቆየ በሐምሌ ወር እንግሊዝ አገር ገባ።

የዚያን ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ከከባድ ችግር ላይ የወደቀበት ዘመን ነበር። የፑርሲያና የኦስትሪያ ጦርነት በመነሳቱ የእንግሊዝ መንግሥት ተወጥሯል። በእንግሊዝ አገር ላይም በደረሰው የገንዘብ ችግር ከከባድ ፈተና ወድቋል። ይህ ብቻ ሳይሆን እንግሊዝ አገር ከባድ የከብት እልቂት የደረሰበት ነበር። በእነዚህ ሁሉ ችግሮች ለተዘፈቀችው እንግሊዝ ከቴዎድሮስ የተላከው አቶ ፍላድ ተመልካችም ሆነ ጉዳዩ ክብደት አጣ። ቢሆንም ፍላድ ጣልቃ እየገባ ራሳምም ሆነ ሌሎቹ እስረኞች ተለቀው በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ እያስረዳ እንደገና ነገሩ ከመበላሸቱ በፊት የቴዎድሮስ ጥያቄ እንዲሟላ ይወተውት ጀመር። በመጨረሻውም የእንግሊዝ መንግስት መሪ የሆነው ሎርድ ደርቤይ በቴዎድሮስ የጠቢባን መላክ ጥያቄ ተስማምቶ በንግሥቲቱ ስም ደብዳቤ እንዲፃፍና ቴዎድሮስ የጠየቋቸውም የጅ ሥራ አዋቂዎች እንዲላኩላቸው ወሰነ።

ፍላድ በውሳኔው ተደስቶ የመመለሻ ጉዞውን በሚያዘጋጅበት ጊዜ ተለቀው የነበሩት እስረኞች እንደገና ደብረ ታቦር ላይ በሙሉ ታሰሩ የሚል ወሬ እንግሊዝ አገር ደረሰ። ይህም ወሬ ደህና አዝማሚያ የያዘውን የፍላድን ጉዳይ አደፈረሰው። ኤሮፓውያኖቹም ተመልሰው እንደገና በቴዎድሮስ መታሰራቸው ወሬ ሳይሆን እርግጥ የፍላድ ነበር።

አጤ ቴዎድሮስ ፈረንጆቹን መልሰው ያሠሩበት ምክንያት ኢየሩሳሌም ደርሰው የሚመለሱም ሆነ በዚያው በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች በሚልኩላቸው መልዕክት ወይም በሚነግሩዋቸው ዜና «የእንግሊዞች ከሷኪን ከሰላ ድረስ የባቡር ሐዲድ እየዘረጉ ናችው። ይህም እንግሊዞች ከቱርኮች ጋር መስማማታቸውንና ወዳጅነታቸውን ያሳያል። ተባብረውም ሊወጉዎት ነው»

እያሉ ይነግሩዋችው ነበር። ከዚህም ሌላ ምፅዋ የሚኖረው ወዳጃቸው የሆነው ፈረንጅ «አቶ ራሳም እላከሁ የሚለው ውሸት ነው እንጂ እውነት አይደለም። እንግሊዞችም ቢሆኑ የሚፈልጉት የተያዙባቸው ሰዎች እንዲለቀቁላቸው ነው እንጂ ስለእርሱ ጉዳይ ሐሳብም የላቸው» ብሎ ስለጻፈላቸው ነበር።

ተለቀው የነበሩት እስረኞችም ፍላድ እስኪመለስ ድረስ በሰላምና በፍቅር እንዲያውም በቅሎ ከነኮርቻቸውና ሌላም ሽልማት ተሸልመው በሰላም ጋፋት ሔደው መኖር ሲጀምሩ ቴዎድሮስ እንዲህ ያለ ወሬ በመስማታቸው ሰኔ 18 ቀን 1858 ፈረንጆቹን ከጋፋት ወደ ደብረ ታቦር ጠሩዋቸው። ደብረ ታቦርም ከአጤ ቴዎድሮስ ሠፈር እንደደረሱ በአንድ ድንኳን ውስጥ እንዲያርፉ ተደረገ። ጥቂት ቆይቶም ራስ እንግዳ ከንቲባ ኃይሉና አቶ ሣሙኤል ወደ ፈረንጆች ዘንድ ተልከው መጥተው የቴዎድሮስን የመልዕክት ጥያቄ አቀረቡ። ጥያቄውም «ቱርክ በእንግሊዝና በፈረሲስ መንሥት እየተረዳች አገሬን ለመውጋት አስባ በሱዳን በኩል የባቡር ሐዲድ የተዘረጋው በእንግሊዞች እጅ አይደለምን። ቆንሲል ኪምሮን ለእንግሊዝ ንግሥት እንዲያደርሱኝ የጻፍኩትን ደብዳቤ ከሰጠሁት በኋላ መልስ ሳይዝልኝ ተመልሶ የመጣውስ በዚያው አይደለምን? ከጻፍኩትም ደብዳቤ የእንግሊዝ መንግሥት የሳቀበት መሆኑን አቶ ሮዚንታል ነግሮኛል። ስለዚህ እኔ ወዳጅነታችሁን ስፈልግ እናንተ ጠላቴ እየሆናችሁ ከጠላቶቼ ጋር ከተባበራችሁ በእጃችሁ ያለውን የጦር መሣሪያ ስጡና ከዚሁ እንድትቆዩ ብለዋቸኋል» ብለው ነገሩዋቸው። ፈረንጆቹ ደብረ ታቦር ላይ በእስር ስም እንዲቆዩ ተደረገ። ስሙ እስር ይባል እንጂ የደብረ ታቦሮቹ እስከ ጋፋት ድረስ እየሔደ ጋፋት ከቀሩት ፈረንጆች ጋር ሲጫወቱ እንዲውሉ ተፈቅዶላቸው ነበር። በኋላ ግን በአመላቸው ጠበቀባቸው።

አንድ ቀን በሰኔ ወር ማለቂያ ገደማ አጤ ቴዎድሮስ በጋፋት የሚሠራውን ሥራ ለማየት ወደ ጋፋት ሔዱ። በጋፋት ያለውንም ብረት ማቅለጫ ሲጐበኙ ፈረንጆቹም አጅበው እየተከተሉ ይሔዱ ነበር። ፈረንጆቹ በሙሉ ባርኔጣቸውን አውልቀው በእጃቸው ይዘው ሲጓዙ ሁለቱ ፈረንጆች ግን ባርኔጣቸውን እንዳደረጉ ይከተሉ ነበር። ቴዎድሮስም ፈንረጆቹ ስለ ጤንነታቸው ሁሉ እየጠየቁ ተጓዙ። ከብረት ማቅለጫው ቤት ሲገቡ በዚያው ያሉትን ሁሉ እጅ ሲነሱ ሮዜንታል እጅ ሳይነሳ ቀረ። ይህን ሁሉ ድርጊት ቴዎድሮስ ያላዩ መስለው አይተዋል። ግን ምንም አልተናገሩም።

የብረት ማቅለጫውን ጐብኝተው ሲወጡ አንድ ሰው «ጃንሆይ። እነኝህ ፈረንጆች ጌቶች ሁል ጊዜ ይረዱኛል። ደጐች ናቸው። እርስዎም ካለሁበት ችግር እንድትወጣ ይርዱኝ» ብሎ ለመናቸው። የዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ ከፉኛ ተቆጥተው «እንዴት ከኔ ሌላ ሌሎችንም ሰዎች ጌቶች ይላል? በሞቴ በልልኝ» ብለው ያን ደሃ አስደበደቡት። ከዚያም ጥቂት እርምጃዎች ሔድ ብለው በድንገትት ቆሙና ወደ ሮዜንታል ዞር ብለው ያዘው» ሲሉ ወታደሮቹ ሮዜንታልን ተረባርበው ያዙት። ሌሎች ደግሞ በዚያው በአጠገባቸው ያገኙትን ዶክተር ብላንክን ወጥረው ያዙት።

አጤ ቴዎድሮስ ወደ ሮዜንታል እየተመለከቱ «አንተ አህያ ለምንድነው የድሃ ሴት ልጅ ነው ያልከኝ» ብለው በቁጣ ጠየቁት። ሮዜንታልም በፍርሃት እየተንቀጠቀጠና የውጥር እንደተያዘ «ጃንሆይ። እርስዎን በድየና አዋርጄ ከሆነ ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ እለምናለሁ።» አለ። ሮዜንታል ፈርቶ የሚንቀጠቀጥበት ምክንያት ቴዎድሮስ ጥያቄ ባቀረቡበት ጊዜ ጦራቸውን በእጃቸው ይሰብቁ (ይነቀንቁ) ስለ ነበረ ነው።

ሮዜንታልን ከጠየቁና የሚለውን ከሰሙ በኋላ ወደ ሌሎቹ ኤሮፓውያን ዞር ብለው «እናንት ባሮች። በገንዘቤ አልገዛኋችሁም። ኧረ እናንተ እነማን ናችሁ ጌቶች ተብላችሁ የምትጠሩት። ተጠንቀቁ» አሏቸው። ከዚያም ባርኔጣ አድርገው ወደ ተከተሏቸው ፈረንጆች ዞረ ብለው «ኩራት አልተሰማችሁምን። ባሮች ሴቶች አህያዎች። ከኔ ጋር እየሔዳችሁ ባርኔጣችሁን ታደርጋላችሁ? እኔ አብሬአችሁ እንዳለሁ አላያችሁምን ደግሞስ ሐኪሙ (ዶክተር ብላክን ነው) ባርኔጣውን በእጁ ይዞ ሲያጅብ አላያችሁምን።

እኔ አይደለሁም እንዴ ሀብታም ያደረግኋችሁ። እናንተማ ድሆች አልነበራችሁም?» ብለው ከወቀሷቸው በኋላ ሁሉም በወታደር እንደተያዙ እየተገፉና እየተጐተቱ ጉዞው ወደ ደብረ ታቦር ቀጠለ። ባርኔጣውን በእጁ ይዞ ላጀባቸው ለዶክተር ብላንክ ግን የከንቲባ ኃይሉን በቅሎ አስጥተው በማዕረግ እንዲከተላቸው አደረጉ።

ደብረ ታቦር እንደ ገቡ አቶ ራሳምና ከዚያ የነበሩት ኤሮፓውያኖች ከሜዳ ላይ እንዲሰበሰቡም አድርገው እሳቸውም ከአንድ ድንጋይ ላይ ቁጭ አሉ።

ዙሪያውንም በመኳንንትና በወታደሮቻቸው ተከበው። አጤ ቴዎድሮስም በያዙት ጦር ጀንፎ (እጀታ) ድንጋዩን እየደበደቡና እየሰባበሩ ወደ እስተርን እየተመለከቱ «የክርስቲያንን የአረመኔ ወይስ የይሁዲ ባህል ነው እንድትሰድበኝ የሚፈቅድልህ? ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሆነ በየትኛው ሥፍራ መጽሐፉን ስትፅፍ ፈቃድ የሰጠህ ማነው? ኧረ እንዲያው ማነው! ይህን እኔ የሚያንቋሽሽ ታሪክ የነገረህ? በል ንገረኝ» አሉ። እስተርን ለመመለስ ሲዘጋጅ ቴዎድሮስ ወደ ራሳም ዞር አሉና «አንተም ብትሆን በድለኸኛል» ብለው ሊነግሩት ሲጀምሩ ራሳም ከፉኛ ደንግጦ ንግግራቸው መሀል መሀል ገባና «እኔ? ጃንሆይ እኔ» አላቸው።

አጤ ቴዎድሮስም «አዎን አንተ አንተው ራስህ። ያውም የበደልከኝ አራት ጊዜ ነው። ስማኝ ልንገርህ። መጀመሪያ ነገር አቶ ኮከቤ እኔን ሰድቦና አዋርዶ የጻፈውን መጽሐፍ አነበብከው። ሁለተኛው ነገር ከእስረኞቹ ጋር ሳታስታርቀኝ ከአገር እንዲወጡ አድርገህ ልታስወጣቸው ነበር። ሶስተኛው በደል ያንተ አገር መንግሥት ኢየሩሳሌም ቱርኮች እንደተያዘች እንድትቆይ ፈቃዱ ሆነ አራተኛው ምን ነበር? ይሁን ብቻ አሁን ረስቸዋለሁ። ግን የምልህ ኢየሩሳሌም የኔ መሆኗን ታውቃለህ በዚያም ያለው ጽላት በቱርኮች መያዙንም ታውቃለህ? ወይስ አላውቅም ልትል ነው።» ብለው ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉ።

ከዚያም አስተርጓሚውንና ፀሐፊያቸውን አቶ ሣሙኤልን «እነዚህን ወዳጆችህን ባስራቸው ምን ታስባለህ» ብለው ጠየቁት። አቶ ሣሙኤልም «ጃንሆይ። እርስዎ ያውቃሉ እንጂ እኔ ደግሞ ምን አውቃለሁ። ምንስ አስባለሁ። አዛዣችን እርስዎ አይደሉምን» ብሎ መለሰ። ከዚህ በኋላ ማሰሪያውን አምጣልኝ ብለው እግር ብረትና ሰንሰለት ቀረበ። ከቀረበ በኋላ ወደ አንዱ የጦር መኰንናቸው ዞር ብለው «እነኝህን ሰዎች በድንኳናቸው ውስጥ ሆነው ልትጠብቃቸው ትችላለህ ወይስ አትችልም።» ብለው ጠእይቁት። ሰውየውም «ጃንሆይ። ከድንኳን ይልቅ በቤት ውስጥ ሆነው ቢጠበቁ ይሻላል» ብሎ ስመለስ «መልካም ነው» ብለው ወዲያው ካንድ ከቤተ መንግሥቱ ቅርብ ከሆነ ቤት ተወስደው እንዲታሠሩ አዘዙ።

የታሥሩበት ቤት አየር መግቢያ መስኮት እንኳ የሌለው ስለ ነበረ አቶ ራሳም ተበሳጭቶ አንድ መልክተኛ ወደ አጤ ቴዎድሮስ ሲልክ «በጃንሆይና በእንግሊዝ መንግሥት መካከል ወዳጅነት እንዲፈጠር ለማድረግ በቻልኩት ሁሉ ደከሜአለሁ። አሁን ግን በኛ በኛ ላይ የደረሰውን በደል የእንግሊዝ መንግሥት በሚያውቅበት ጊዜ በሚመጣው ነገር ጃንሆይ እንዳይወቅሱኝ ብለህ ንገራቸው» ብሎ ላከ። አጤ ቴዎድሮስም ለራሳም መልስ ሲልኩ «በመጥፎም ሆነ በመልካም ብይዛችሁ እንግሊዞች ጠላቶቼ በመሆናቸው አጉላላቸው ማለታቸው አይቀርምና ምንም አይደለም አርፈህ ተቀመጥ» ብለው ላኩበት።

የቴዎድሮስ ጠባይ ተለዋዋጭ ነው ተብሏል። በጠባያቸው መለዋወጥም እጅግ በጣም ክፉ የሆኑት ሰው የዚያንኑ ያህል ደግሞ እጅግ በጣም ደግ ሰው ሆነው ይገኛሉ። እንዲያ ተጣልተውና ሰድበው ካሠሩዋቸው ፈረጆች ዘንድ አንድ ቀን ማታ ጠጅና አረቄ አስይዘው እስረኞቹ ካሉበት ቤት ገቡ። ከዚያም ተቀምጠው ጠጅና አረቄው እየተጠጣ ሲጫወቱ «ሚስቴ እንኳ በአሁኑ ጊዜ ከቤት እንዳልወጣ አጥብቃ ብትነግረኝም እናንተ በእንደዚህ ያለ ኃዘንና ችግር ላይ ጥያችሁ ለመቅረት ደስ ስላለኝ አብሬአችሁ ለመጠጣትና ለመጫወትና ለመጫወት መጣሁ» አሏቸው።

ከራሳም ጋር ሲጫወቱ ራሳም በእንግሊዝ አገር ስላለው የቀረጥ አቀራረጥ ጉዳይ አጫወታቸው። ቴዎድሮስ በእንግሊዝ አገር ስላለው ከነጋዴው ስለሚቀረጠው ቀረጥ ሰምተው ከት ብለው ሳቁና «ስማኝ እንጂ ራሳም። የአግሬ ሰው በገንዘቡ እንደመነገድ ከመሬት ውስጥ ይቀብረዋል። ይህን የሚያደርገውም ለኔ የሚገባኝን ቀረጥ ላለመክፈል ሲል ነው» አሉት። እንደገና ራሳም በፈረስና በበቅሎ በቤት ሠራተኛም ስለሚቀረጠው ቀረጥ ቢያጫውታቸው «አይ አቶ ራሳም። አንተኮ የአበሾችን ነገር አታውቅም። አሁን እኔ በበቅሎው በፈረሱ በእንስሳው ቀረጥ ልቀበልህ ብለው ማንም ሰው ፈረስና በቅሎ የሚኖረው የለም። በአሽከርህ ቀረጥ ክፈል። ብለውም የየራሱን አሽከር ይሆናል» አሉት። ይህን የመሳሰለውን ሲጫወቱ ቆይተው ለመሔድ ሲነሱ «........ፊቴን ሳያዩና ሰውም የሚናገረውን ሰምታችሁ ሳትገምቱት በልቤ ውስጥ ያለውን ስሜት ብትመለከቱት ለአገሬ ጥሩ አላማ ያለኝ ሰው ነኝ» ብለዋቸው ሔዱ።

አንድ ቀን ደግሞ ከደብረ ታቦር ወደ ጋፋት መጥተው ሥራውን ከጐበኙ በኋላ ከውጭ መቀመጥ ፈልገው ቀይ ሐር የተነጠፈበት ወንበር ተደርጐላቸው ተቀመጡ። ራሳም በአጫዋወቱ ያስደስታቸው ነበርና የንግስት ሳባን ታሪክ አጫወቱት። ቀጥሎም አንድ ጊዜ የጐንደር ከንቲባ ሆነው ተሹመው የነበሩት ከንቲባ ኃይሉ የአሌክሳንደርን (እስክንድርን) ታሪክ እንዲናገሩ አዘዋቸው ያወሩ ጀመር። ታላቁ አሌክሳንደር ከኢትዮጵያ ልዕልት ልጅ ማስወለዱ እስከ ገነት (መንግስት ሰማያት) ድረስ ሔዶ መመለሱን ሁሉ ከንቲባ ኃይሌ መጽሐፍ ይዘው ስዕሉን እያሳዩ ለራሳም ተረኩለት።

ራሳም ባፉ ባይናገርም በነገሩ አላመነም። በታሪክ መጨረሻ ላይ ቴዎድሮስ ወደ ራሳም ዞር ብለው «የእስክንድርን ታሪክ ወደድከው ወይም ጠላኸው?» ብለው ጠየቁት። ራሳምም «ጃንሆይ እውነቱን ለመናገር እሌክሳንደር ወደ ገነት ለመሔድ በመመኘቱና በመሔዱ በጣም ብልህ ሰው ነው ወደ መሬት ተመልሶ በመምጣቱ ግን በጣም ሞኝ ሰው ነው። እኔ በሱ ቦታ ብሆን ኖሮ አንድ ጊዜ ተፈቅዶልኝ መንግሥተ ሰማያት ከገባሁ ከዚያው እቀር ነበር «ሲላቸው ከተቀመጡበት ከትንሿ ወንበር ተፈንግለው እስኪያዘሙ ድረስ ሳቁ ሲበቃቸውም ወደ እራሳቸው እያዩ «እኔ በእንዲህ ዓይነቱ ግብስብስ ነገር ሁሉ የማምን ይመስልሃል?» ቢሉት «አይመስለኝም ጃንሆይ። ግርማዊነትዎ የበለጠ እውቀት እንዳለዎ እርግጠኛ ነኝ።» በዚችም ቦታ ተቀምተው ሁለት ሰዓት ያህል ሲጫወቱ መቆየታቸውን ራሱ ራሳም ፅፎታል።

ኤሮፓውያኖቹ በሙሉ መቅደላ ተወስደው እንዲታሠሩ በታዘዘው መሠረት ፈረንጆቹ በሙሉ የመቅደላውን የእስራት ዘመናቸውን ለጀመጀመር ሐምሌ 5 ቀን 1858 ዓ.ም መቅደላ ገቡ።



ካፒቴን ትሪስትራም ቻርልስ ሶየር ስፒዲ

# ምዕራፍ 13

# የእስረኞች የመቅደላ ኑሮ

ማርክሃም ስለ መቅደላ ተራራ ሲፅፍ «.......በዓለም ካሉ ቦታዎች ሁሉ ጤናማ አየር ያለበት ሥፍራ ነው።......» ይለዋል። መቅደላ ተራራ ዙሪያውን ሙጥጥ ያለ ገደል ነው። ከአናቱ ለመድረስ ያለው መንገድና በር አንድ ብቻ ነው። ከላዩ ላይ ከተወጣ በኋላ ግን እጅግ በጣም ሰፊ የሆነ ሜዳ ነው። መቅደላ ተራራ በተፈጥሮ አቀማመጡ አመች በመሆኑ ከጥንት ጀምሮ የእስረኞች ማስቀመጫ ነበር። አጤ ቴዎድሮስም የመቅደላን ተራራ ለእስረኞች ማኖሪያ ብቻ ሳይሆን የንብረታቸውም ማስቀመጫ አድርገውት ነበር።

ጭልጋ ውስጥ ሣር አምባ ከተባለ ቦታ የነበሩት የፖለቲካ እስረኞች ወደ መቅደላ ከተዛወሩ በኋላ በመቅደላ አምባ ዘጠኝ ሹሞች ተሾሙበት። ከዚያ በፊት ግን የአምባው ሹም አንድ ሰው ብቻ ነበር። በዚያም የሚሾመው የእስረኞች ጠባቂ ማዕርጉ ደጃዝማች ነበር። ኤሮፓውያኖቹ እስረኞች ወደ መቅደላ ከተወሰዱ በኋላ ግን የአምባው አዛዥ ማዕረግ ከደጃዝማችነት ወደ ራስነት ከፍ አለ። ዋናው አዛዥ ራስ ሲባል የሌላዎቹ ዘጠኝ ሹማምንት ማዕረግ ግን ቢትወደድ ነበር።


ፈረንጆቹ መቅደላ የገቡ ጊዜ ዋናው የአምባው አዛዥ የበጌምድሩ ተወላጅ ራስ ኪዳነ ማርያም ነበሩ። ራስ ኪዳነ ማርያም በራስ አሊ ዘመነ መንግሥትም ያገለገሉ ታላቅ ሰው ናቸው። በጠባያቸውም ጨዋ፥ አዛኝ እውነተኛ፥ ስለ ነበሩ ፈረንጆቹ ይወዱዋቸው ነበር። ራስ ኪዳነ ማርያም ያለ ንጉሥ ትእዛዝ ምንም ዓይነት መጥፎ ነገር እንዳይደረግ የሚቆጣጠሩና የማይፈልጉም ሰው ነበሩ። ምኒልክ ከመቅደላ ካመለጡ በኋላ ራስ ኪዳነ ማርያም ግንኙነት አላቸው ተብለው በሰንሰለት ታሠሩ። የተረፈ ዘመናቸውንምን በሰንሰለት እንደታሠሩ ደብረ ታቦር ጨረሱት።

መቅደላ በሸሎ እና ጀዳ በተባሉ ወንዞች መሀል የሚገኝ ተራራ ነው። በተራራው ወገን ላይ ያለው ሰላምጌ የሚባለው ቦታ ሰፊ በመሆኑ በዚያን ጊዜ በዚያ ቦታ በእርሻ ተግባር የሚኖሩ ብዙ ሰዎች ነበሩት። አራሾቹም የሚያርሱት ለንጉሱና ለመቅደላ ሹማምንት ነበር። ይህ ብቻ ሳይሆን በተራራው ጫፍ የታሰሩት የታላላቅ ሰዎች አሽከሮች በዚያው በሰላምጌ ቦታ እየተሰጣቸው ቤት

ሠርተው ከብት እያረቡ ስንቅ በማቀበል የሚኖሩም ነበሩበት። ከሰላምጌ ጐን ወደ ሥላሴ እየተባለ የሚጠራ ሜዳ አለ። ሜዳው ሥላሴ የተባለበት የሥላሴ ቤተ ክርስትያን ስላለበት ነው። በዚያም በየሳምንቱ ቅዳሜ የገበያ ቀን ስለሆነ ብዙ ህዝብ ይሰበሰብበት ነበር።

በመቅደላ ተራራ ላይ ስላሉት ቤቶች ዶክተር ብላክን ሲገልፅ «.......የአፄ ቴዎድሮስ ቤትና ጐተራ የተሠራው ከአምባው ማዕከላዊ ቦታ ላይ ነው። ከቤቱ ፊት ለፊት ሰፊ ለአዳባባይነት እንዲያገለግል ክፍት ቦታ ያለው ሲሆን በጀርባ በኩል የንጉሥ ነገሥት መኮንኖች መኖሪያ ሠፈር ይሆንና በስተቀኝ በኩል ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑ እሥር ቤቱና የወታደሮች ሠፈር....... (አለ) መቅደላ ላይ ያሉት የአጼ ቴዎድሮስ ቤቶች ሰፋ ባለ ሁኔታ እንደሌሎቹ የአበሻ ቤቶች የተሠሩ ናቸው አጤ ቴዎድሮስ ግን በጠቅላላው በቤት ውስጥ ከመኖር በድንኳን መኖርን ስለሚወዱ በአምባውም ውስጥ ገብተው መዘጋትን ስለማይፈልጉ ሲመጡ ሰላምጌ ላይ ድንኳናቸውን አስጥለው ይሰነብታሉ። በእነዚህ ቤቶች ብዙም ኑረውባቸው አያውቁም።.......» ብሏል።

ስለ እስር ቤቶቹ ሁኔታ ሲገልፅ ደግሞ «......የፖለቲካ ነፍስ ገዳይና ሌቦችም የሚታሰሩባቸው አምስት ትልልቅ ቤቶች ነበሩ። በዙሪያቸው የብታሞቹ እስረኞች አሽከሮችና ዘበኞች ይኖራሉ። ቤቶቹ በጥብቅ አጥር የተከበብቡ ናቸው። እኛ በተያዝን ጊዜ በነዚህ ቤቶች ውስጥ ቁጥራቸው 600 የሚሆኑ እስረኞች ይገኙበት ነበር። በዚሁም ውስጥ 80 በትኩሳት በሽታ ሲሞቱ 175 ተፈቱ።.......307 ተገደሉ። የእሥር ቤቱ አጠባበቅ በአንድ በኩል በጣም ጥብቅ ሲሆን ባንድ በኩል ደግሞ ልል መስሎ ይታያል። ፀሐይ ስትጠልቅ እስረኛው ሁሉ ወደ እሥር ቤቱ አጥር ግቢ እንዲገባ ይታዘዝና ሲገባ አንድ ባንድ እየተቆጠረ ሰንሰለቱም ግቢ እንዲገባ ይታዘዝና ሲገባ አንድ ባንድ እየተቆጠረ ሰንሰለቱም ያልተፈታ መሆኑን ከበራፉ ላይ ዘበኞች ቁመው ይፈትሻሉ።



ደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለም

«ከዚህ ቀደም ሴቶቹ እስረኞች ከወንድ እስረኛ ጋር በአንድ ቤት ውስጥ ይታሠሩ ስለነበር ኋላ ግን ተሻሽሎ ለብቻቸው ቤት ተሰጥቷቸዋል። እስር ቤቱ በጣም ሞልቶ ብዙ መጨናነቅና መታፈግ ስላለ አበሻዎችንም ያሳዝናቸው እንደ ነበር ይገልፃሉ። ወንበዴው፤ ከብዙ የጦር ግንባር ድል የተጐናፀፈው ጀግና ጠቅላይ ገዢው ልዑሉ በጣም በጠቅላላው የተለየ ቦታ ሳይኖራቸው እጃቸውና እግራቸው በሰንሰለት ተፈድኖ በዚያች ጠባብ ቦታ ላይ ጐን ለጐን እየተጋፉ ይተኛሉ። ከእስር ቤቱ መካከል ላይ ዘበኞቹ እሳታቸውን እየሞቁና እየተጫወቱ ሲጠብቁ ያድሩና ከጧቱ 12 ሰዓት ላይ እስር ቤቱን ከፍተው እስረኛውን ስለሚያስወጡት በችግር የተጐዳው እስረኛ የእለት ምግቡን ለመለመን ወይም የታደልና አሽከሮቹ ሀብቱን ይዘው በዙሪያው የሚጠብቁት ከሆነ ስንቁን በመቀበል በጠቅላላው ምግብ ለማግኘት ሲጥር ይውላል። …….» በማለት ጽፈዋል። (ትርጉም ዳኜ ወ/ሥ)

ራስ ኪዳነ ማርያም የመቅደላ ሹም የነበሩት ጊዜ እስረኞቹ ፈረንጆች መቅደላ ገቡ። ከመቅደላ እንዴት ተደርገው በእግር ብረት እንደታሠሩ ዶክተር ብላክን ሲጽፍ «…….እግረ ሙቁ ቀርቦ ተራ በተራ እየቀረብን የመታሰሩ ተግባር ተጀመረ። የፊተኞቹ ኤሮፓውያን በከባድ እግረሙቅ ቀድመው ታሠሩ። በመጨረሻው የኔው ተራ ደረሰና እንድቀመጥ ከተደረገ በኋላ ሱሪየን ከፍ ከፍ አድርገው ቀኝ እግሬን ከአንድ ለዚሁ ተግባር ከቀረበ ድንጋይ ላይ አስቀመጡት። የሰንሰለቱን ቀለበት ከቀኝ ቁርጭምጭምቴ በላይ ካጠለቀ በኋላ ሰንሰለቱን ለመግጠም ሲሉ በመዶሻ መደብደብ ያዙ። ብረቱን ሲደበድቡ መዶሻው በትክክል ስለማይመታ ለሰውነቴ ሁሉ አሰቃቂ የሆኑ ጉዳት ተሰማኝ። የመጀመሪያዋን ቀለበት ለአምስጥለቅ አሥር ደቂቃ ጊዜ ወሰደባቸው። በዚሁ ሁኔታ ከግራ እግሬ ላይ ሰንሰለቱን አጠለቀልኝ። የእስራቱ ሁኔታ በሚከናወንበት ጊዜ ሰንስለቱን የሚያጠብቋቸው ቀጥቃጭ ብረቱን ስቶ እግሬን ያነኩተዋል በማለት ከባድ ሰቀቅን ጥሎብኝ ነበር። የግራውን እግረሙቅ አጥብቀው ወደ መጨረሱ ገደማ ሳሉ ቀለበቱ ስለተሰበረ ሰውነቴ በድንጋጤ አረገደ። በዚህም ምክንያት ሥራው እንደገና ተጀምሮ በሚገባ ስለ ተፈፀመ ቀጥቃጩና የወህኒ ቤቱ አዛዥ ተደሰቱ።……..» ይላል (ትርጉም ዳኜ ወ/ሥ)

የእሥረኞቹ የእስራት ዘመን እንዴት እንደ ተፈፀመ ከማወቃችን በፊት እስረኞቹ መቅደላ ተራራ ላይ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ሲቆዩ እንዴት ይኖሩ እንደ ነበረ ማወቅ ይጠቅም መሰለኝ። ራሳም በሁለተኛው ቮሊዩም መጽሐፍ ሲገልጥ «.......የእምቅደላ መሬት ለአትክልት ተስማሚ ነው። ችግሩ በድርቅ የወራት ውሃ በመስኖ ለማጠጣት ውሃ ያለማግኘቱ ብቻ ነው። መቅደላ እንደ ደረስን ከግብፅ አገር የያዝኩት የቲማቲም ዘር ነበረኝና ከጐጆዬ ፊት ለፊት ተከተልኩት። በወሩ ልክ እንደ ወይን ሐረግ አደገ። ከጥቂት ተጨማሪ ሳምንታት በኋላ በብዛት አድጐ በሥሩ 6 ሰዎች ያህል የሚያስቀምጥ ዳስ (መጠለያ) ሆነ። የቤቱንም መግቢያ ሁሉ ከላይ አለበሰው። ዓመቱን ሙሉ ፍሬው ባለማቋረጡ የቲማቲም ወጥና ኮቴሌት እየሠራን ለመብላት ቻልን። ጥቂት ፍሬዎችም ዘራሁና ችግኙ እንደ ደረሰ ለአገሬው ሰው ሁሉ አደልኩ። የእንግሊዝ ጦር መጥቶ እስከንወስን ድረስ ቲማቲም አላጣንም ነበር። አንድ ጊዜ አንዱን የቲማቲም ሐረግ ለከቼው ርዝመቱ 18 ጫማ ከግማሽ ሆነ። .......» ብሏል። ቲማቲም ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተክሎችንም ይከተሉ ነበር። ይህ የቲማቲም ተክል በኢትዮጵያ የመጀመሪያው እንደሆነ ይገመታል።

ራሳም ጊዜውን የሚያሳልፈው በአትክልት ተከላ ብቻ አልነበረም። ብዙ የዱር ወፎችን አላምዶ ቤቱ ነፃ በተለቀቁ ወፎች የተመላ ነእብር። አጤ ቴዎድሮስ በዚህ በወፍ ማላመዱ እየተደሰቱ ያደንቁለት ነበር። የሰላምታ ደብዳቤ በሚፅፉለት ጊዜ «.......ልጆችህስ እንዴት ናቸው.......» ለለ ወፎቹ ይጠይቁት ነበር። ከራሳም ዘንድ የመጣ ሰው ሲያገኙም «የራሳም ልጆች እንዴት ናቸው?» እያሉ መጠየቃቸውን ራሳም ጽፏል።

ራሳም ስለ መቅደላ ኑሮአቸው ሲገልፅ «......ዳቦ እንጋግራለን። የምንመገብበት ጠረጴዛችን ሁልጊዜ ልብስ አለው። አንዳንዴም የአፍ መጥረጊያ ፎጣ (ናፕኪን) ይኖራል።.......ምግብ የምንመገበው ከሾርባ ጀምረን ነው። አንዳንዴም አሣ እናገኛለን።.......እውነቱን ለመናገር አንድ ባለሚሊዮን ብር ጌታ ከኛ የተሻለ ኑሮ አይኖርም።.......ትንሽ ምቾታችንን የምትበላሽብን የታሰርንባት ሰንሰለት ብቻ ናት።........ሌላው ደግሞ በክር ጫፍ ስለተንጠለጠለችው ሕይወታችን እንሰጋለን።

«የሚጠይቁን ከአምባው ብዙ ሰዎች ይመጣሉ።......እንደ ደንብ አድርጌም ለሚመጣው እንግዳ አንድ ሲኒ ቡና አንድ ወይም ሁለት መለኪያ አረቂ እሰጣለሁ። ጠጅ ግን በቤቴም እንዲገባ አልፈቅድም ነበር። ........ከሹማምንቱ ጋር ሁሉ ስንጫዋወት እናመሻለን። እኔም ሳስቃቸው አመሻለሁ።....... አንዳንዴም ሹማምንቶቹ የሚማከሩትና ስብሰባቸውን የሚያካሒዱት ከኔ ቤት ነው።......የማታ ጐብኝዎቼ ብዙውን ጊዜ ሴቶች ናቸው። እነኝህም ባሎቻቸው በፖለቲካ የታሠሩባቸው ናቸው። እነሱም የባሎቻቸውን ወሬ ይዘው ይመጡና ስንጫወት እናመሻለን።......ድምፃቸውን ሲሰሙት ግሩም ቃና ያለው ነው። የአበሻ ሴቶች ሲናገሩ ሳይጮሁና ረጋ ብለው ነው።......ያዝኑልኛል የፅናኑኛልም። የእግዚአብሔርን ምሕረት እንድጠብቅ ይነግሩኛል።......ሲያፅናኑኝም ያንተንና የጓደኞችህን አስተሳሰር ከኛ ባሎች ጋር ብታስተያየው የእናንተ ሰንሰለት መታሰር አይባልም። እነሱ እኮ እጃቸውንና እግራቸውን ባንድነት በሰንሰለት ታስረው ነው ያሉት። አንተ ከመምጣትህ በፊት ከኛ ሰዎች ጋር ታስረው የነበሩትን ወንድሞችህን እስቲ ጠይቃቸው። ይነግሩሃል። ያኔ ያንተን እስርና የኛን ባሎች አስተሳሰር ልታመዛዝን ትችላለህ ይሉኛል።

«......አንድ የፎቶግራፍ አልቡም ነበረኝና እሱን እያገላበጡ ማየት ይወዳሉ። ወደየቤታቸው ከተመለሱም በኋላ ላክልን እያሉ ያስወስዱታል። ለሌሎች ለማሳየት እያሉ ነው። አንዳንዴም ሳይመልሱልኝ እስከ 15 ቀን ድረስ ይቆያል።.......አንድ ጊዜ ከእንግሊዝ አገር የአንዲት ወዳጄ ስዕል ካርድ ደረሰኝ። ይህ አዲስ ስዕል እንደ ደረሰኝ ለሁሉም እንግዳ ሆነባቸው አንዳንዶቹ የሚስቴ ወይም የወዳጄ ይመስላቸዋል። እነኚያ ቅዱሳን ነፍሳት ስዕሉን እያዩ ያለቅሳሉ። ስዕሉን እየሳሙም «አቶ ራሳም እንዲህ በሰንሰለት መታሰሩን ስትሰሚ አላለቀሽም? እግዚአብሔር ብርታቱን ይስጥሽ› ይላሉ።.......ብሏል።

ከመቅደላ የጥበቃ ኃላፊነት ራስ ኪዳነ ማርያም ከተነሱ በኋላ ምክትል አዛዥ የነበሩት ቢትወደድ ቢሰውር ራስ ተብለው የመቅደላ ሹም ሆኑ። ቢሰውር በደምቢያና በበጌምድር መሀል ያለው የእንፍራንዝ ተወላጅ ናቸው። አባታቸውም የእንፍራንዝ ገዥ ነበሩ። አባትዬው የቴዎድሮስን አክስት አግብተው ቢሰውርን ወለዱ፥ በዚህ ምክንያት ቢሰውር ዘንድ የሚታመኑ ሰው ነበሩ። ራስ ቢሰውር በእርሻና በከብት እርባታ የታውቁ ሀብታም ነበሩ።

በውይን ተክልም በኩል በብዛት ስለነበራቸው በጐንደርና በሌላም በሌላ አገር እየተላከ ይሸጣል። ቴዎድሮስ ራስ ቢሰውርን ስለሚያምኗቸውና ስለሚመኩባቸውም ቁባቶቻቸውን እንኳ የሚያስጠብቁት ራስ ቢሰውርን ነበር። በኋላ ግን የቴዎድሮስ አመራር እየተለወጠና ግራ እየገባቸው ስለሄደ ፈርተው ከመቅደላ ጠፍተው ከዱ።

ይህ የፈረንጆቹ እንደገና መታሰር እንግሊዝ ውስጥ በተሰማ ጊዜ ታላቅ ውዝግብ ፈጠረ። በሰላም ሊያልቅ የነበረው ጉዳይም እንደገና እስር ገብቶ ክርክር አስነሳ። ኮሎኔል ሜርዌዘር በክርክሩ መሀል ገብቶ «የሚሻለው ጦር ማወጅ እንጂ ከእንግዲህ ወዲያ መለማመጡ የእንግሊዝን መንግሥት ማዋረድ ነው» የሚል አሳብ አቀረበ። ቢሆንም ጉዳዩ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲጠና ስለታዘዘ ምክር ቤቱ ጉዳዩን በዝርዝር አጥንቶ አጤ ቴዎድሮስ ለጻፉት ደብዳቤ ጥያቄ መልስ ሰጥቶ ቢሞክር ይሻላል በሚለው ሐሳብ ላይ ረጋ። ወሰነ።

ከዚህ በኋላ ታልቦት የሚባል ሲቢል ኢንጅነርና ስድስት የጅ ሥራ አዋቂዎች ከነመሣሪያቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲሔዱ ለፍላድ ተሰጡት። ለንጉሡ የሚሆን ስጦታ ይዞ በጥቅምት ወር 1859 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ጉዞውን ጀመረ። በታህሣሥ ወር ምፅዋ ገብተው ለአጤ ቴዎድሮስ ምፅዋ መግባቱን የሚገልፅ ደብዳቤ ላከ። ፍላድ ከእንግሊዝ አገር ከመነሳቱ በፊት ምፅዋ ሲደርስ መድረሱን ለቴዎድሮስ አሳውቅ እስረኞቹ ተልከውለት ምፅዋ ላይ ሳይረከባቸው የጅ ሥራ አዋቂዎችን እንዳይልክ ወይም ይዞአቸው እንዳይገባ ታዞ ነበርና ይህንኑ ገልጾ ለቴዎድሮስ ጻፈ።

ፍላድ ለአጤ ቴዎድሮስ ከጻፈው የራሱ ደብዳቤ ጋር ከእንግሊዝ ንግሥት የተላከላቸውንም የደብዳቤ ትርጉም ጨምሮ ልኮት ነበር። ደብዳቤውም «ለመልካም ወዳጃችን» በሚል አድራሻ ይጀምርና «.......ግርማዊነትዎ እንደጠየቁት ሁሉ በአበሻ ውስጥ እንዲሠሩ የሚያስፈልጓቸውን ጠቢባን ሰዎች ልከንልዎ ፍላድ ይዞ ሊመጣልዎት ሲል ለአሽከራችን ለራሳም ያደረጉለትን መልካም ድርጊት ሁሉ ትተው ከአሽከራችን ከካሜሮንና ከሌሎቹ ኤሮፓውያን ጋር እንደ ገና ማሠርዎን ሰማን። ከግርማዊነትዎ ግን ይህ የሆነበትን ምክንያት የሚያስረዳ ምንም ነገር አላገኘንም።

«ይህም ቢሆን ፍላድን እንዲያው በከንቱ በማቆየት ጊዜ አናጠፋም ብለን ለግርማዊነትዎ የጻፍነውን ደብዳቤ ሰጥተን ላክነው። ግርማዊነትዎም የገቡትን የተስፋ ቃል እንደሚፈጽሙ እየተማመን የታሠሩትን እስረኞች አሽከራችንን ራሳምን ከአሽከራችን ከካሜሮንና ከሌሎቹ ኤሮፓውያን ጋር እንደሚለቁዋቸው ተስፋ እናደርጋለን።.......ወዳጅነታችን ላይ የጋረደው ጥቁር ደመና ፍላድ እርስዎ ዘንድ በደረሰ ጊዜ ተገፎ እንደሚጠፋ ሙሉ እምነት አለን......» የሚል ረጅም ደብዳቤ ነበር።

አጤ ቴዎድሮስም ከዚህ ደብዳቤ ጋር ከፍላድ የተጻፈው ማስታወሻ ከደረሳቸው በኋላ መልሱን ለፍላድ በመጻፍ ፈንታ መቅደላ ላይ በእስር ላለው ለራሳም ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጻፉለት።

በስመ አብ ወወልድ መንፈስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት
እንዴት ሰነብትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ
ሃኪም ብሎንግን አቶ ፕሪዶን እነአቶ ኬምሮንን እነ ኮከብን
እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ አሽከርህን እምተማ
ስደድልኝ ያልኸኝን ሠደድሁልህ። እስተውህኒ በግመል ከዚያ
ወዲህ በሰው ተሸክማሁ አምጡልኝ ብዬ አዛዥ ሰድጃለሁ
በእግዚአብሔር ኃይል። አቶ ፍላፕ መልስ መጥጦ ምጥዋ
ላይ ሁኖ ይህነን ደብዳቤ ሠዶልኛል አይተህ አንብበህ ቆየኝ
እኔም በእግዚአብሔር ኃይል ልመጣ ነኝ ተማክረን ምላሹን
እንድንልክ።



ይህ ደብዳቤ ታህሣሥ 21 ቀን 1859 ዓ.ም መቅደላ ላለው ለራሳም ደረሰው። በዚያ ያሉት ኤሮፓውያን እስረኞች ሁሉ የፍላድን መመለስና መጥዋ መድረስ በመስማታቸው ከፍተኛ ደስታ አደረጉ። የቴዎድሮስ ደብዳቤ ራሳም ጉዳዩን እንዲያጠናው የተላከ እንጂ መልስ መጻፍ ስለሚያስፈልገው ራሳም ደብዳቤውን ይዞ ጉዳዩን እያጠና ቆዩ።

ፍላድ ለጻፈው ደብዳቤ መልስ ሳያገኝ ስለዘገየበት እንደገና ያንኑ የመጀመሪያውን ደብዳቤ ግልባጭ ጽፎ መልሱ የዘገየበት መሆኑንም ገልጾ ለአጤ ከምጥዋ ጻፈላቸው። አሁንም አጤ ቴዎድሮስ ለፍላድ መልስ በመስጠት ፈንታ ስለሁለተኛውም ደብዳቤ ሁኔታ ለስረኛው ለራሳም ጻፉለት። ደብዳቤውም ቀጥሎ ያለው ነው።

በስመ አብ ወወልድ መንፈስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ከአቶ ረስአም እንዴት ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ሀኪም ብሎንግን አቶ ፐሪዶን አቶ ኬምሮንን እነአቶ ኮከብን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ። ደግሞ አሁን ኊልተኛ አቶ ፍላፐ ላከብኝ ላንተም የሠደደውን ደብዳቤ ሠድጀልሃለሁ። አሁንም የውነት የናንትና የኔ ዝምድና መገኘቱ ምልክት እኒህ የመጡ ሠራተኞች ብልሆችም በመተማ ካቶ ፍላፐ ጋር እንዲመጡ አርገህ ላክልኝ ከዚያ ወዲያ ጠላቴን ጠላት ወዳጆን ወዳጅ ካደረጋችሁልኝ በኋላ የናንተን ዝምድና የጠላሁ እንደሆነ የዳዊት ልጅ ታላቁ ንጉሥ የእግዚአብሔር ፍጥረት የእግዚአብሔር ባርያ ቤተ መቅደስ ሲሠራ እጅግ ችግሮት ነበረ ከኪሮስ ንጉሥ ከኪራም አቆላምጦ ከጫምው ወድቆ ለምኖ ቤተ መቅደስን ብልህ ተቀብሎ አምጥቶ አሠራ አሁንም እኔ ከታላቂቱ ከእንግሊዝ ንግሥት ከመኳንንቶችዎ ሁሉ ከእንግሊዝ ንግሥት ከመኳንንቶችም ሁሉ ተአገርዎ ሰው ከሠራዊትዎ ሁሉ ከጫማው ወድቄ እየታጠቅሁ እየፈታሁ ሣቆላምጥ እነአቶ ኮከብ ሠድበውኝ አዋርደውኝ አባኘውሁ። ቀጥሎ አቶ ከኢርምሮን ከእንግሊዝ ንግሥት ከታላቂቱ ሃይማኖትና የተጠቃ ደሀ ከሚተብቁ ከእግዚአብሔር ወዳጅ ከእግዚአብሔር ባለመዋል ከቢክቶርያ የፍቅር ደብዳቤ ብሠድ ምላሽ ነሳኛ አንተ አቶ ረሳአም ቀጥለህ ከንግሥቲቱ ተልኬአለሁ ብለህ መጣህ እሺ ብዬ በተቻለኝ ጉልበቴ በፍቅር ተቀበልሁህ የሠጠኸኝን ደብዳቤ ባይ ያውሮጳን ሰዎች ሁሉ የተጣላሃቸውን ያሠርሃቸውን ፍታልኝ ማርልኝ የሚል ቃል አገኘሁኝ እኔም ካንተ ፊት ፩ ቀን ሣላድር እሺ ብዬ ልኬ አስፈትቸ አመጣሁልህ በፈጣሪአችን ኃይል ከኔ ሣይደርሱ አስመጥቸ ላንተ ሰጠሁህ ወዳጀን ንግሥቲቱን ከነመኳንንቶችዎ ደስ ይበልዎ ብዬ አንተ ግን ምንስ በድላችሁ ነው የታሠራችሁ ብለህ ሣትጠይቃቸው በድዬ ተገኝቸ እንደሆነ ሣልክስ ተበድዬ ተገኝቸ እንደሆነ ከንግሥቲቱ ወረታየን እንዳገኝ ሣታገኝ ከኔ ሣታገናኝ ሠድደሃቸው ቀጥሎ እንግሊዝና ቱርክ ፩ ሁነው ጠሉህ ብለው ሰማሁ በዚህ አዝኜ ዝም ብዬ ተቀምጬ ሣለሁ አቶ ፍላፐ የደስታ የፍቅር ደብዳቤ ላከብኝ አሁንም ሰሎሞን በፍቅር በኪራም ጫማ እንደ ወደቀ እኔም ከእግዚአብሔር በታች ከንግሥቲቱ ከመኳንንቶችዎ ከወዳጆችዎ ሁሉ ጫማ ወድቄአለሁ የጥበብ ብልሃት እንዲአሣዩኝ በመተማ እንዲመጡልኝ አርገህ ላክ። ይህ ከሆነ በኋላ ደስ አሠርኝቸ አሸኝቼ እሰዳችኋለሁ በእግዚአብሔር ኃይል።

ዘመነ ሉቃስ በወርኃ ታኅሣሥ በ፳፰ ቀን ተጣፈ።



በዚህ ደብዳቤ ላይ እዳነበብነው ታላቁ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሊያሠራ ባሰበ ጊዜ ከኪሮስ ጫማ ወድቆ ለመነ ብለዋል። ይህን ማለታቸው በዘመኑ ከሁሉ ታላቅ የነበረው የሰሎሞን የሚፈልገው ጉዳይ እስቲሟላለት ከበታቹ ከበታቹ ከኪሮስ እግር ላይ ወደቀ። እኔም ጉዳዩ እስኪሞላልኝ ድረስ ብቻ የማይገባኝን ከንግሥቲቱ ጫማ ወድቄ እለምናለሁ ማለታቸው ነው። የሚለማመጡት ጉዳያችወ እስኪፈጸምላቸው ድረስ ብቻ መሆኑን መግለጣቸው ነው። የንቀት አጻጻፍ ነው።

ዋናው ቁም ነገር በቴዎድሮስ ሁለት ደብዳቤዎች ላይ እንዳየነው እስረኞቹ ከመለቀቃቸው በፊት ፍላድ ጥበበኞቹን ይዞ ይምጣ ይላሉ። ራሳምም በዚህ ሐሳብ ተስማምቶ ለፍላድ እንዲፅፍለት ጠይቀዋል። ምጥዋ ያለው ፍላድ ግን ማንም ቢጥፍለት እስረኞቹ ተለቀዋል ምጥዋ ላይ በእጁ እስኪገቡ የመጡትን ጥበበኞች ወደ ቴዎድሮስ የሚልክ ሰው አይደለም። ምክንያቱም ከዚህ በፊት እንዳነበብነው እስረኞቹን ሳይቀበል ጥበበኞቹን እንዳይልክ ከእንግሊዝ መንግሥት ታዟልና ነው። ደግሞም የቴዎድሮስ ጠባይ ተለዋዋጭ መሆኑን ስለሚያውቅ ሥጋትም አለበት። ፍላድ በሁለቱ መንግሥታት መሀል ባለው የመልክተኛነት ጉዳይ ከአጣብቂኝ ውስጥ የገባ ሰው ነው። የእንግሊዝ መንግሥት የራሱ መንግሥት ስለሆነ የመንግሥቱን ትእዛዝ መቀበልና ማክበር ግዴታ ነው። ምጥዋ ላይ ባለበት ባሁኑ ጊዜ እጁን ከቴዎድሮስ እጅ ያላለቀ ቢሆንም ቴዎድሮስ ሚስቱን በመያዣነት የያዙበት በመሆኑ ስለ ሚስቱ ሕይወት ያስባል ይጨነቃልም።

አጤ ቴዎድሮስ ለራሳም የጻፉት ደብዳቤ እንደደረሰው ራሳም በንጉሱ ሐሳብ እንደሚስማማ ገልጦ ለንጉስ ጻፈላቸው። አጤ ቴዎድሮስም የራሳም ደብዳቤ ሲነበብላቸው በጣም ተደሰቱ። ደብዳቤውንም ላመጣው ሰው አንድ በቅሎ ከነሙሉ ዕቃው ሸለሙት። እነ ራሳምም ሆኑ ሌሎቹ ኤሮፓውያንን እስረኞች የእርቁን ጉዳይ እያስመሰሉ ከፍላድ ጋር ምጥዋ ላለው ለኰሎኔል ሜርዌዘር የሚፅፉለት ጉዳይ በጦር ኃይል መፍትሔ እንዲያገኝ እያሉ ነበር። የእንግሊዝ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ቢመጣ ቴዎድሮስ እንደሚፈጁዋቸው እስረኞቹ ያውቃሉ። ግን በእስር መጉላላቱ ሰልችቷቸው ስለነበረ ከዚያ ኑሮ መሞታቸውን መርጠው ነው። ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ከአቶ ረስአም እንዴት ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ሀኪም ብሎንግን አቶ ፐሪዶን እነአቶ ኬምሮንን እነአቶ ኮከብን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ አቶ ፍላፐ እንዲህ ብሎ ላከብኝ ቀድሞ አቶ ረስአምን ከነኬምሮን ነገር ወዳንተ በላክነው ጊዜ በመልካም ዓይን በፍቅር ተቀበልኸው በልው ሰማነ እኛም ያልኸነን ሁሉ እሺ ብለን እልፍጥሰጠን ሠደን ነበረ ኋላ ግን የወትሮው ፍቅሩ ተለወጠበት ብሎ ወሬ ሰማነ ዳሩ ግን ይህን ሥለሰማነ ያንተና የኛ ፍቅር ይለወጣል ያለማለት ተስፋ አለነ ብለው ላኩብኝ እኔም እንዲህ ብዬ ምላሽ የምልክ ነኝ ጥንት እንግሊዝ ለኢትዮጵያ ወዳጅ ዘመድ ነበረ አሉ። ዕኔም የጥንቱን ነገር እየሰማሁ እጅግ አጥብቄ እወዳችኋለሁ ዛሬ ግን ከቱርክ ጋራ አሙህ ጠሉህ ብለው ቢነግሩኝ ውነትን ይሆን ብየ ልቤ አወላወለብኝ። ዳሩ ግን በዕንግሊዝና በኢትዮጵያ ማካከል መከፋፋት አለ አይመስለኝም ተስፋ አለኝ ፍቅር እንዲሆን እንግሊዝን የሚአማ የሚጠላ እኛ አንወድም እናንተም ኢትዮጵያን የሚያማን የሚጠላን አትወዱብነ እነአቶ ረስአምን ወደኔ የላካችኋቸውን መቅደስ ከቤቴ ከከተማዬ መልካም አርጌ አስቀምጫቸዋለሁ የናንተን ወዳጅነትና ፍቅር እስታገኘው ብዬ የኔን ቃል እንዲህ ብዬ እምልክነኝ ካቶ ፍላድ ድረስ አንተም ዝምድናችሁን ወዳጅነታችሁን እንዳገኘው አርገህ እንዳላላክህ ላክልኝ በእግዚአብሔር ኃይል የምትሰደው ሰው ደብዳቤኸን ጨምረህ ቶሎ ከኔ ድረስ ስደድልኝ። አቶ ፍላድን ቶሎ ይዞት እንዲያደርስ።



አጤ ቴዎድሮስ መልስ በመስጠት ፈንታ አዲሱን የፍላድን ትእዛዝ ካልታዘዘውና ሊሽርም ከማይችለው ከራሳም ጋር ሲፃፃፉ ቆዩ። ፍላድም አራት ጊዜ ለአጤ ቴዎድሮስ ፅፎ ከእሳቸው መልስ ባላማግኘቱና እንደታዘዘው እስረኞቹ ተለቀው ምፅዋ ባለመግባታቸው ፍላድ አብረውት የመጡትን የጅ ሥራ አዋቂዎች ወደ አገራቸው መልሶ ደምቢያ ላይ ከቴዎድሮስ ጋር ተገናኘ።

ፍላድ ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር እንደተናኘ «ሠራተኞቹ የታሉ» ብለው ጠየቁት። ፍላድም ከእንግሊዝ መንግሥት የታዘዘውን ትእዛዝ ነግሮ «ጃንሆይ እስረኞቹን ለቅቀው ምፅዋ ድረስ ባለመላክዎ በትእዛዙ መሠረት መልሼ ወደ አገራቸው ሰደድኋቸው» ብሎ ተናገረ። ቴዎድሮስም «ለመሆኑ ከንግሥቲቱ ጋር ተገናኘህ» ብለው ጠየቁት «አዎን ጃንሆይ ተገናኝቻለሁ። እንዲያውም የቃል መልክትም ልከውልኛል» ብሎ መለሰ።

«ምንድነው መልዕክቱ» አሉት።

«የእንግሊዝ ንግሥት ለግርማዊነትዎ እንዳደርስ ያዘዙኝ መልክት እነዚህን በአገርዎ ውስጥ ያለ ፈቃዳቸው ያስቀመጧቸውን ሰዎች በሚያስቸኩል ከአገርዎ አስወጥተው ካላኳቸው ለወደፊቱ ከእኛ ጋር በወዳጅነት ለመኖር የማይቻል ነው ብለዋል» አለ።

አጤ ቴዎድሮስም ለጥቂት ጊዜ በፀጥታ ቆይተው አሰቡና «ስማ። የወዳጅነት ምልክት እንዲያሳዩኝ ጠይቄ መልስ አልስተሰጠኝም። መጥተው መዋጋት ከፈለጉ ይምጡ። ድል ባላደርጋቸው ደግሞ ሴት ብለህ ጥራኝ» ብለው አሰናበቱት።

በማግሥቱ ፍላድ ከእንግሊዝ ንግሥት የተላከውን ስጦታ አቀረበ። በስጦታው መሀል የሩቅ ማያ መነጥር (ቴሌስኮፕ) ነበረበት። ይህም መነጥር በዘመኑ ከነበሩት ምርጥ መነጥሮች አንደኛው ነበር። አጤ ቴዎድሮስ መነጥሩን ተቀብለው አዩበትና «......መጥፎ መነጥር ነው የተላከልኝ። በዚህም ምንም ነገር ለማየት አልቻልኩም። እንካ እስቲ አንተ እይበት» ብለው ላንዱ ወታደራቸው ሰጡት ወታደሩም አይቶበት ጥሩ የሚያሳይ መነጥር መሆኑን ተናገረ።

አጤ ቴዎድሮስም ወታደሩን «ወይድልኝ ወዲያ። ከጥቂት ዓመታት በፊት ሙቶ አለቃ ፈጠነ (እስፒዲ) አንዲት ትንሽ ቁራጭ ምንጣፍ ቢጤ ባቶ ኬሬንስ እጅ ላከልኝ። በእግዚአብሔር ኃይል ያቺን ምንጣፍ ያመጣልኝን ሰው አሠርኩት። አሁንም ይሄ መነጥር ያመጣልኝ ለደህና ነገር አይደለም። ስለዚህ ባለፈው ጊዜ እንዳደረግሁት የመሰለ ነገር ባምጪው ላይ አደርጋለሁ።» አሉት።

ፍላድም ነገሩን ለመለወጥና ለማብረድ ሲል «ጃንሆይ። እነኚህን እስረኞች ካለቀቁ ከእንግሊዝ መንግስት ጋር ወዳጅነት ያለ አይመስለኝም። ነገሩም እየከረረ መሔዱ ነው።» አላቸው።

«ይምጡ ብየሃለሁ» አሉት። ቴዎድሮስ «በኃይሌ አልመካም። ኃይሌን ያደረግሁት በእግዚአብሐኢር ላይ ነው። የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ያለው ተራራዎችን ማዘዝ ይችላል» አሉት። ፍላድ ይለቀቁ እያለ የሚከራከርላቸው እስረኞች በዚህ ጊዜ 61 ሰዎች ነበሩ። ይህም ቁጥር የኤሮፓውያኖችን ሚስትና ልጆች ጨምሮ ነው። ከፍላድ ክርክር በኋላ ግን የእስረኞቹ ብዛት 62 ሆነ። ይህን ቁጥር ያበዛው የራሱ የፍላድ መታሰር ነው።

ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ መካ የሚሔዱ ኢትዮጵያውያን ምዕመናን በየደረሱበት አገር የአበሻ ንጉስ የእንግሊዝን ንግሥት አሽከሮች በሰንሰለት አስሮ ካስቀመጣቸው አራት ዓመት አለፈ እያሉ በማውራታቸው ውሬው እየተዛመተ በመላው ዓለም ተዳረሰ። የእንግሊዝ መንግሥትም ሆነ ይህ ወሬ እንዳይሰማ ቢደብቅም ወሬው እየተስፋፋና እየገነነ ሔደ። ሄንሪ ዱፍተን እንደጻፈው «.......ከጅዳ እስከ ቻይና ግንብ ከኬፕ ጋርዳፊ እስከ ጐልድ ኮስት ተዳረሰ......» ይላል። ያኔ እንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር ይተዳደሩ የነበሩት ሕንዶች ይህን ወሬ ሰምተው የእንግሊዝን መንግሥት ደካማ ነው እያሉ እንግሊዞች በየደረሱበት ሁሉ ይሰደቡና ይናቁ ጀመር። በያሉበትና በየደረሱበትም በማፌር አንገታቸውን ያቀረቅሩ ጀመር። በእነዚህ እስረኞች ምክንያት ኢትዮጵያ በማትታወቅበት አገር ሁሉ ዝነኛ ሆነች። እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያ በኤሮፓውያኖች ምክንያት በመላው ዓለም ላይ ስሟ የተጠራው ሁለት ጊዜ ነው። አንደኛው የቴዎድሮስ ኤሮፓውያኖችን ማሠር ሲሆን ሁለተኛው

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በኤሮፓውያን ላይ አድዋ መንደር ውስጥ ያስገኙት ድል ነው።

የእንግሊዝ መንግሥት ከቴዎድሮስ ጋር ያለውን ግንኙነት በሰላም ለመጨረስ እንደማይቻል ካወቀ በኋላ የጦር አዋጅ አወጀ። የጦሩ አዋጅ ቢወሰንም እስረኞቹን በደህና ለማስለቀቅ እንዴት ይቻላል የሚለው ጥያቄ ክርክር አስነሳ። በምክር ቤቱ ካሉት አማካሪዎች መሀል ሰር ኸንሪ ቡልወር እናስ እር ሳሙኤል ቤከር ባቀረቡት አሳብ የእንግሊዝ መንግሥት ከግብጾች ጋር ተስማምቶ ቴዎድሮስን ቢያጠቃ ይሻላል አሉ። በተለይ ሰር ኸንሪ ቡልወር የተባሉት ፓል ማል ጋዜጣ ላይ ሲፅፉ «.......ዘመናዊ የሆነው የእንግልዚና የሴፓይ (የሕንድ ፈረሰኛ) ጦር ባንድነት ሆኖ ከግብፅ ጦር ጋር ተባብሮ ቢጋጠም ዛሬ ቴዎድሮስ ዜጎቻችንን ባሠረበት ሰንሰለት ነገ እሱን እንሰቅልበታለን ሲሉ የግብፅ ገዥ ነግሮኛል.......» ብለው አወጡ። ሐሳቡ የእንግሊዝና የሴፓይ ጦር በቀይ ባህር በኩል ገብቶ ወደ መቅደላ ሲጓዝ የግብፅ ጦር ደግሞ በመተማ በኩል ቢገባ የኢትዮጵያን ኃይል ከፋፍሎ በመውጋት የመሀል ግንኙነታቸውን ጥሩ ወጤት ይሰጣል የሚል ነው። ለዚህ አስተሳሰብ መልስ ተገኘለት። መልሱም የአበሻ ሰው ደርቡሾች የሚላቸውን በአገሩ ላይ ካየ እንኳን ስንቅ ማቀበል ቀርቶ ከንጉሱ ይተጣላው ሸፍታም ቢሆን ይዋጋል የሚል ነበር። በዚህም ምክንያት አሳቡ ወደቀ።

ኰሎኔል ሜርዌዘር ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ያጠናውን ጥናት አቀረበ። የሜርዌዘር ጣንት የአገሪቱን ለምለምነት ገልጾ የኢትዮጵያ ሕዝብም ከዳር እስከ ዳር በንጉሱ ላይ ሸፍቶ መነሳቱን አስረድቶ አገሪቱ ብትወረር ሕዝቡ እንግሊዞችን በደስታ ይቀበላል ብሎ አሳመነ። በዚሁ ላይም ኢጣሊያዊው አባ ማስያስ ከቴዎድሮስ ተነጋግረው እስረኞቹን እንደማይገሉ ቃል የገቡላቸው መሆኑን የሚያስረዳ የጻፉለትን ደብዳቤ አሳየ።

ሜርዌዘር ያቀረበው አሳብና ጥናት ትክክለኛ ነበር። አለቃ ተክለ ኢየሱስ በዚያን ዘመን ስለነበረው የአገር መናወጥ ሁኔታ ሲገልጡ «......ደብረ ታቦርን ከተማ ካደረገ በኋላ ታቦቱ መድኃኔ ዓለም ተከለና ቤተ ክርስትያኑን አሳምሮ ሠርቶ ባጡን በብረት ማገረው። ሥራውን ከጨረሰ በኋላ የእስር ቤት አደረገው። ከዚህ በኋላ የቤጌምድር ሰው ይሄስ የደህንነትም አይደል እያለ አመል አወጣ። አገር ተናወጠ። ንጉሡን ተጣላው። በተራራ ላይ

እየቆመ.......ተሳደበ።.......ንጉስም ሕዝቡ እንደ ጠላው አውቆ ጠላት ገብቶ እንዳይገድለው ከተማውን በእሾህ አጥር ዙሪያውን እያሳጠረ ይሠፈር ጀመር። ባላገርና ወታደርም በከተማ እርስ በርሱ ይጋደል ጀመር። ረሀብም ሆነ። እመጫት ልጅዋን እስክትጥል ድረስ። ያንጊዜም ረሃብ የሆነበት ምክንያት.........አጤ ቴዎድሮስ የበጌምድርን እህል ዘርፎ ደብረ ታቦር አስገብቶ ለፈረስ ለበቅሎ ለአህያ ቀለብ ይሁን። ለከብት ሣር አትስጡ ብሎ አውጆ ነግሮ ነበርና ነው። ያን ጊኤ ያን ሶስት ወር ሙሉ ከብት እንደ ሰው እህል ሲበላ ባጀ። አንድ ቀን ቁና እህል አንድ ብር ተሸመተ።.......ከአጤ ፋሲል ጀምሮ ጥንት ከተማ የነእብረውን ጐንደርን እንቅፎ ዘረፈው።......ከቤተ ክርስትያንም እየወጣ የጉልላት መስቀል እያወረደ ወሰደ......ሁሉንም በዘበዘ።........» በማለት ያዩትን ፅፈዋል።

የወሎዋ ገዥ ወይዘሮ መስተዋት ከጐበዜ ጋር ተስማምታ የመቅደላን አምባ ደምስሳ ለመያዝ አቅዳለች። መቅደላ ላይ ያለውን የቴዎድሮስን ሠራዎት በረሃብ ለማዳከም ለመፍጀት ከመቅደላ አምባ ሥር በየሳምንቱ አንድ ቀን ከሚውለው ገበያ ማንኛውንም የሱዋ ሰው የሆነ የወሎ ኦሮሞ ገበያው ላይ ምንም ዓይነት ሸቀጥ ይዞ እንዳይሔድ በአዋጅ አስከለከላለች። በደላንታ በዳሞት የሚገኘው ሠራዊትም እያደፈጠ ይሁን በግልፅ የቴዎድሮስን ሠራዊት እንዲያጠቃ አዛለች። እንዲያውም የሸዋው ምኒልክ ለባለንጣዋ ለወርቂት አግዘው የመስትዋትን ሠራዊት ባይወጉ ኖሮ መቅደላን ከቴዎድሮስ ሠራዊት አላቃ ለመያዝ ቀላል ሆኖላት ነበር።

የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ መቅደላን ወርረው ለመያዝ ዘምተው ከመቅደላ አካባቢ ከደረሱ በኋላ የጊዜውን ሁኔታና ያላቸውን ኃይል ገምተው ተመልሰዋል። ምኒልክ ከራሳም ጋራ በምስጢር ባደረጉት ስምምነት መሠረት እስረኞቹን ከመቅደላ ማስፈታት ቢችሉ ኖሮ የእንግሊዝ መንግሥት እየሳቸውን ንጉስነት ሊያውቅላቸው እንደሚችል ቃል ተገብቶላቸው ነበር። ምንም እንኳ ምኒልክ መቅደላ ትይዩ ድረስ ቢዘምቱም በጊዜው ቴዎድሮስ መቅደላ አልነበሩምና እቴጌ ጥሩነሽ ሊከዳቸው የነበረውን የቴዎድሮስን ሠራዊት እንዲመለስ በማድረጋቸው መቅደላ ሳይያዝና እስረኞቹ ሳይፈቱ ቀሩ።

ሌላው የቴዎድሮስን ኃይል የቀሰቀሰውና ብዙ ተከታይ ያገኘው የዋግሹም ጐበዜ መሸፈት ነበር። የዋግሹም ጐበዜ አባት ዋግሹም ገብረ መድኅን ለአጤ

ቴዎድሮስ ተወዳጅ ባለሟል ነበሩ። አጤ ቴዎድሮስ አንድ ቀን ተቆጥተው እንዲገደሉ አዘዙ። የዚያን ጊዜ ጳጳሱ አቡነ ሰላማ ነበሩና ማልደው ዋግሹም ገብረ መድኅን ከመገደል አዳኑዋቸው። ዋግሹም ገብረ መድኅንና ልጃቸ ወጣቱ ጐበዜ ጊዜ ጠብቀው ሲመቻው ከቴዎድሮስ ከድተው ትውልድ አገራቸው ላስታ ገቡ። በላስታም ሆነ ላስታ ከቴዎድሮስ የተለየ ራሱን የቻለ ግዛት ነው ብለው አወጁ።

ዋግሹም ገብረ መድኅን ሸፍተው ላስታ ገብተው ማወጃቸውን የሰሙት አጤ ቴዎድሮስ የዋግሹም ገብረ መድኅንን ወንድም ተፈሪን ዋግሹም ብለው ሾመው ላስታ ሰደዱዋቸው። ዋግሹም ተፈሪም ላስታ ዘምተው ወንድማቸውን ዋግሹም ገብረ መድኅን በጦር ኃይል ድል አድርገውና ማርከው አምጥተው ላጤ ቴዎድሮስ ሰጡ። በዚያን ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ዋድላ ላይ ነበሩና ምርኮኛው ዋግሹም ገብረ መድኅን እንደደረሷቸው ሡራዊቱን እንዲያያቸው ከድንኳንቸው ፊት ለፊት ካለ ዛፍ ላይ አሰቀሉዋቸው።

ጐበዜ ምንም እንኳ ከአባታቸው ጋር ቢማረኩም ጠፍተው ከቴዎድሮስ እጅ አመለጡ። ከዚያም ተደብቀው ሲኖሩ በአሁኑ ጊዜ የቴዎድሮስ ኃይል መዳከሙንና ሕዝቡ ጠልቶ መሸፈቱን ሲሰሙ ከተደበቁበት ወጡ። የአባታቸውን አሽከሮች አሰባስበው «በደልህን ልወጣልህ ተነስቻለሁና ተከተለኝ» ብለው አወጁ። የላታም ሕዝብ አዋጃቸውን በደታ ስለ ተቀበለው ላስታ ከቴዎድሮስ ሥልጣን ሥር ወጣ። እንዲያውም የጐበዜ ኃይል በመርታቱ እስከ ትግራይ ድረስ ዘምተውና አስገብረው ግዛቱን ለሚስታቸው ወንድም ለደጃዝማች ካሣ (በኋላ አጤ ዮሐንስ ለተባሉት) ሰጥተው ተመለሱ።

ዋግሹም ጐበዜ ከራሳም ጋር ግንኙነት ስለ ነበራቸው በሚስጥ ባደረጉት ስምምነት ጐበዜ መቅደላን ቢይዙና እስረኞቹን ቢያስፈቱ የእንግሊዝ መንግሥት የአበሻ ንጉስነታቸውን እንደሚያውቅላቸው ስለተነጋገሩ በ1859 ዓ.ም አጋማሽ ላይ መቅደላን ለመያዝ አስበው ነበረ። ነገር ግን በመጀመሪያ የሚሻላቸው ቴዎድሮስን መውጋት መሆኑን አምነውበት የመቅደላን መያዝ ተውት። ወደ አጤ ቴዎድሮስም ቢዘምቱ የቴዎድሮስ ታማኝ የሆኑት ተስማ እንግዳ የተባሉት የጋይንት ባላባትና ገዥ ድል አደረጓቸው። በትግራይ የሾሙዋቸው ደጃች ካሣ ጐበዜን ከድተዋቸው ነፃነታቸውን አወጁ። እንዲህ ዓይነቱ መከፋፈል ባይኖር ኖሮ ቴዎድሮስ በእንግሊዝ ጦር አይደፈሩም ነበር።

ቴዎድሮስ አብዛኛው ሠራዊታቸው ይከዳቸው ጀመር። ዕለት ዕለትም የሠራዊታቸው ብዛት እየቀነሰ ሔደ። ከጦር አዛዦቻቸው መሀል የታወቁት ራስ ዕድሉ የተባሉት ቀን በቀን ከቴዎድሮስ ከድተው ሠራዊታቸውን አስከትለው ሔዱ። ቴዎድሮስም በመላከተኛ ጦር ለማስወጋት ፈልገው መላከተኛውም ጦር አብሮ እንዳይከዳ ብለው ተውት።

የጋይንቱ ባላባትና ጀግናው የሠራዊቱ መሪ ዘለለው የተባለው ከቴዎድሮስ ከድቶ 200 ያህል ፈረሰኞች አስከትሎ አገሩ ጋይንት ገባ። የጋይትንም ሕዝብ ብስሩ ሰብስቦ ቴዎድሮስ ቢመጡ ለመዋጋት ተዘጋጅቶ ተቀመጠ። የዳሞትና የደላንታም ሕዝብ በዚያ ይቀለብ የነበረውን የቴዎድሮስን ሠራዊት ፈረስና በቅሎ ማርኮ ሸፈተ ብላክን እንደሚለው «.......በሰኔ ወር 1859 ዓ.ም ያለግዛት ንጉሥ ያለ ጦር ሠራዊት ጄኔራል ሆኑ።......» ለመቅደላ አቅራቢያ የሆኑትን አንዳንድ መንደሮች ባሏቸው ወታደሮች ወግተው ለመያዝ ሲዘምቱ ሕዝቡ ጠንክሮ በመዋጋቱ በለው እያሉ ሠራዊታቸውን ያበረታቱ የነበሩትን ቴዎድሮስ ሠራዊታቸውን ሽሽ ከማለት ደረጃ ደረሱ።

1859 ዓ.ም ለቴዎድሮስ የመከራ ዘመን ነበር። ይህንንም መከራ ያመጣባቸው ጭካኔያቸውና በኃይል እገዛለሁ ማለታቸው ነበር። የሸፈተባቸው መኳንንት ቀርቶ ተራው ሸፍታ ሁሉ ቴዎድሮስ በሠፈሩበት አካባቢ እየመጣ አደጋ ይጥልባቸው ጀመረ። ሠራዊታችውም በየቀኑ እየከዳቸው በመሔዱ ቴዎድሮስ ሠፈራቸውን በአጥር እያሳጠሩ ሠራዊቱን ያስጠብቁ ጀመር። ይህም ሁሉ ሆኖ ቴዎድሮስ ርህራሄ አላሳዩም። የሚማረከውንም ሽፍታ ሆነ ታማኝ ወታደራቸውን በየጥቃቅኑ ጥፋት ሁኑ እጅና እግር ማስቆረጣቸውና እበሳት ማቃጠላቸውን አልተው አሉ። በዚያን ጊዜ ለቴዎድሮስ መጠነኛ እርዳታ ያደረገው የባላገሩ ሕዝብ ነበር። ይሄውም የቴዎድሮስ ሠራዊት እየከዳ በሚሔድበት ጊዜ ብድሩን ለመመለስ እያለ ባላገሩ ይፈጀው ጀመር። ስለዚህ የቴዎድሮስ ሠራዊት ቢከዳ ባላገሩ እንደሚገድለው በማወቁ ከዳቱ ጋብ አለ። ቢሆንም ከሙቶ ሺህ በላይ ወታደር ያስከትሉ የነበሩት ቴዎድሮስ በአሁኑ ጊዜ የቀሩዋቸው ስድስት ሰባት ሺ የሚሆን ወታደሮች ብቻ ናቸው።

አንድ ቀን ብስጭትጭት ያሉት ቴዎድሮስ ከቀሩዋቸው ሠራዊታቸው መሀል ሆነው «ሁላችሁም እንደጠላችሁኝና ለመከዳትም እንደምትፈልጉ

አውቄአለሁ። ከዚህ ሁሉ ነገር ለምን እኔን አትገድሉኝም? ብለው ተናግረው በፀጥታ ቆሙ። ከወታደሩም ምንም መልስ ስላላገኙ «መልካም ነው እናንተ የማትገድሉኝ ከሆነ እኔ ሁላችሁንም አንድ ባንድ እያልኩ እገላችኋለሁ» አሉ።

ይህን የመሳሰለውን ሁሉ ነው ሜርዌዘር አጥንቶ ለእንግሊዝ መንግስት ያቀረበው። የሜርዌዘርም ሐሳብና ሪፖርት በእንግሊዝ መንግሥት ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ በቴዎድሮስ ላይ የጦር አዋጅ ታወጀ።

# ምዕራፍ 14

# ጦር መጣ

እንግሊዞች በኢትዮጵያ ላይ የጦር አዋጅ ካወጁ በኋላ ዘማቹ ጦር የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የነበረው የሕንድ ጦር እንዲሆን ተመረጠ። የሕንድ ጦር የተመረጠበት ምክንያት ለእንዲህ ዓይነቱ መንገድና ለሌላውም ጦርነት ልምድ ያለው ሠራዊት በመሆኑና በቀላሉም ቀይ ባሕር ለመድረስ ስለሚችል ነው።

ስለዚህ ለሚዘምተው ጦር መሪም አዝማቹ ጄኔራል ናፒር እንዲሆን ተወሰነ። ጄኔራል ናፒር ለዚህ ውጊያ አዝማችነት የተምረጠበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። ናፒር በትምህርቱ ላቅ ያለውን ሥፍራ የያዘው በኢንጂኔርነቱ ነው። በሕንድ ጦር ሠራዊት ውስጥ እያለ በሕንድ አገር ብዙ መንገዶች (በዮች) ድልድዮችና የመሳሰሉት ሁሉ በሱ ኢንጂኔርነት ተሠርተዋል። በጦር ሜዳም ቢሆን በማዋጋት ብቻ ሳይሆን በመዋጋትም ጭምር የታወቀ ሰው ነው። ሁለት ጊዜ የተቀመጠበት ፈረስ ከስሩ እየተገደለበት በተአምር የዳነ ሰው ነው። ብዙ ጊዜ በጦር ሜዳ ላይ ቆስሎ ለቁስሉ ሳይጨነቅ ወይምጥግ ሳይዝ ወይም ወደ ኋላ ሳይመለስ ትኩስ ቁስሉን እንደ ያዘ ብዙ ጊዜ የተዋጋና ያዋጋ ሰው ነው። የእንግሊዞች ጦር ቻይናን በወረረ ጊዜ ናፒር በድል አድራጊነት ቀድሞ ፔኪንግ የተባው እሱ ነው። ከዚያም ተመልሶ በሕንድ አገር ያለው የቦምቤይ ጦር ሠራዊት አዛዥ ሆነ። በጨዋታው በቀልደኛነቱ፥ በደግነቱ፥ በፍርድ አሰጣጡ ወታደሩ ሁሉ ይወደዋል። ያከብረዋልም ይህ የሱ ጦር ሁሉ ኢትዮጵያ እንዲዘምቱ የተወሰነው።

ናፒር ወደ ኢትዮጵያ ለሚዘምተው ጦር አዝማች መሆኑ ከተነገረው ቀን ጀምሮ ስለ ኢትዮጵያ ማጥናት ያዘ። ኢንጅነሮቹንና የጦር መኰንኖቹን ሰብስቦ ከጀምስ ብሩስ ጀምሮ ስለ ኢትዮጵያ የተጻፉትን መጽሐፍት ሰብስበው እንዲያነቡና ስለ ኢትዮጵያ እውቀት እንዲኖራቸው አዘዘ። ይህም ብቻ ሳይሆን በዚያ ዘመን በሕይወት የሚገኙትን ስለ ኢትዮጵያ የሚያውቁ ሚስዮናውያንና ሌሎችም ለንደን ተሰብስበው ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን አንድ ጥናት እንዲያቀርቡ አደረገ። ይህ በዚህ እንዳለ በኤደን የፖለቲካ ኃላፊ የሆነው ሜርዌዘር ቀይ ባህርን ተሻግሮ ለእንግሊዝ ጦር ማረፊያ የሚሆን ቦታ መርጦ እንዲያዘጋጅ አዘዘው።



ጀኔራል ሮቤርት ናፒየር

በአገሪቱና በሕዝቡ አጠናን በኩል ይህን ካደላደለ በኋላ እሱ ደግሞ በ1859 ዓ.ም በነሐሰ መግቢያ ላይ የሚያስፈልገውን የወታደር ብዛትና መሣሪያ ለእንግሊዝ መንግሥት አቀረበ። ባቀረበውም መጠይቅ 12.000

ተዋጊ ወታደሮች 20.000 በቅሎዎችና የማጓጓዣ እንስሶች በያይነቱ በተለይ ከፍተኛ የተራራ መድፎች ጦሩን የሚያጓጉዝበት 280 መርከቦችና ከብት የሚነዱ ተራ ሰዎች እንዲሰጠው ጠየቀ።

ለውጊያ የሚያስፈልገውን መጠይቅ ጽፎ ከጨረሰ በኋላ ለጦር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ደግሞ በዝርዝር አቀረበ። ይህም ያቀረበው መጠይቅ ከባዶቹን መድፎች የሚሸከሙ 44 ዝሆኖች በኢትዮጵያ ምድር ከገቡ በኋላ ከወደቡ ጀምሮ የሚዘረጋ 32 ኪሎ ሜትር ወይም ሃያ ማይልስ ርቀት የሚሆን የባቡር ሐዲድ መስመር የባቡሩ ጋሪዎችና ጐታቾች ወደብ ላይ የሚተከሉ ታላላቅ ባውዛ መብራቶች ለመጋዘን መሥሪያ የሚሆን የተለያዩ ዕቃዎች የባህሩን የጨው ውሃ ጨውን ለይተው የሚያጣሩና ንፁህ ውሃ የሚያስገኙ ሁለት ኮንዴንሰሮች ብዙ መቶ ማይል ርዝማኔ ያለው የቴሌግራፍ ሽቦ በጠቅላላው ይዞታቸው ሆስፒታል የሆኑ ሶስት መርከቦች ከበረዶ መሥሪያ ዕቃዎቻቸው ጋር ሆነው የተሟላ የሕክምና መሣሪያ ያላቸወ እንዲሰጡት ጠየቀ። ይህም ብቻ ሳይሆን በዘመኑ በኢትዮጵያ መገበያያ የነበረው ማርትሬዚያ ብር 500.000 እንዲዘጋጅለት አሳሰበ።


ለወታደሩም ለእያንዳንዱም ነጭ ወታደር ሁለት ሁለት ተለዋጭ ቦት ጫማ አንድ የብረት ቆብ አንድ ከሐር የተሠራ ቀበቶ አንድ ጥንት የጅ ሹራብ (ጓንት) ለእያንዳንዱ የበላይ መኰንን ሁለት ሕንዳዊ አሽከሮች እንዲሰጡትና አንዱ ለሰውዬው ሲያገለገል ሌላው ለፈረስ ጠባቂነትና ቀላቢነት የሚሆን ሕንዳዊ ለሆኑት ወታደሮች ደግሞ ለእያንዳንዱ ወታደር ለውር 5.833 ሩፒ ወይም 580 ፓውንድ ሂሳብ ወጭ እንዲሆን ሲጠይቅ በምግብ በኩል ደግሞ 50.000 ቶን የሚመዝን የተለያየ ምግብና 30.000 ጋሎን ሩም የተባለው መጠጥ እንዲሰጠው ጠየቀ።

ናፒር ይህ ሁሉ እንዲሰጠው ከጠየቀ በኋላ በአስቸኳይ በመንግሥት በኩል እንዲጠና ታዞ ጣናቱ ተፈፀመ። በተጠናለትም መሠረት 13.000 ተዋጊ ወታደሮች እነዚህም 4.000 ኤሮፓውያን 9.000 ሕንዳውያን እንዲሆኑ 19.000 አሽከሮችና ከብት ነጂዎች በጠቅላላው በሰው በኩል 32.000 ኃይል እንዲሰጠው ተወሰነ። ለዕቃና መሣሪያ ተሸካሚነት በጠቅላላው 55.000 እንስሳት እንዲዘጋጅለት ታዘዘ። የጠየቃቸውም መርከቦች በሙሉ

እንዲሰጡትና ለእነዚህም መርከቦች ኪራይ የሚከፍል ግማሽ ሚሊዮን ፓውንድ ተፈቀደለት።

የኪራይ መርከቦቹ ከካልካታ ከቦይምቤይ ከሊቨርፑል ከለንደንና ከሌላም ቦታ ሁሉ ተሰበሰቡ። መድፍ ይሸከማሉ የተባሉት ዝሆኖች በመርከቦቹ ግድግዳ ዙሪያ እየታሠሩ ተጫኑ። ሌላው ዕቃና የጦር መሣሪያ ሁሉ ሲጫን ከረመ። ወደ ኢትዮጵያ ጠረፍ ተልኮ የማረፊያ ቦታ እንዲጠና የታዘዘው ኰሎኔል ሜርዌዘር እስቲመለስና ጥናቱን እስቲያቀርብ ጓዙ አይነሳም ነበርና ሜርዌዘር ጥናቱን ፈፅሞ ገባ።

ሜርዌዘር ጥናቱን ፈፅሞ ናፒር እንድ እንደደረሰ ለጓዙ ወይም ለጦሩ ማሳረፊያ የተመረጠው ቦታ ወደ ዙላ መሆኑን ተናገረ። ዙላ የተመረጠበትም ምክንያት ከጥንቱ የኢትዮጵያ ወደብ ከአዶሊስ አቅራቢያ በመሆኑና ወደ መሀል አገር ለሚደረገውም ጉዞ የጥንት ግሪካውያን ነጋዴዎች ከአዶሊስ ወደ አክሱም ይጓዙበት በነበረው መንገድ ለመጓዝ አመቺ መሆኑ ስለታመነበት ነው። ሌላው ለምርጫ ያበቃው ደግሞ ያን ጊዜ ዙላ በግብፆች እጅ የተያዘ በመሆኑ በዚያ ያሉ ግብፃውያን ሹማምንት የእንግሊዝን ጦር ለመርዳት ቃል ስለገቡም ነው። ሌላው ደግሞ አባ ዘካርያስ የሚባል ኢትዮጵያዊ ሮም የተማረ የካቶሊክ እምነት ተከታይ «ከዙላ በሰነዓፌ በኩል ሲታለፍ መንገዱ በጣም ቀና ነው» ብሎ ስላማከራቸውም ጭምር ነበር። ዙላ ከመመረጡ በፊት በኰሎኔል ሜርዌዘር የሚመራው አጥኚ ቡድን እስከ ታጁራ ድረስ በመሔድ ብዙ ወደቦችን አጥንተው ነበር።




የአምባአላጌ ተራራ

የወደቦቹ ጥናት በሚካሔድበት ጊዜ ከአጥኚው ቡድን ጋር አብሮ የነበረው ጋር አብሮ የመነው ሙዚንጀር እስከ ታጁራ ድረስ በመሄድ አጥንቷል። ሐንፊላ ደሴት ለቅርበቱ ለወደብነቱም ተመርጦ ነበር። ግን በጉዞ ጊዜ የጨው መሬት ስላለው ለእግረኛው ወታደር አስቸጋሪ መሆኑ ታስቦ ቀረ። ምጥዋ ጥሩ ወደብ ሆኖ ሳለ በገዥው ግብጻዊ ያለ መስማማት ምክንያት ቀረ። ታጁራ ተመርጦ ከወደቡ በኋላ 200 ማይልስ ያህል የሚርቅ ውሃ የሌለበት የበረሃ መንገድ ስላለው ቀረ።

የመጀመሪያው ቀዳሚ ጦር 10ኛው የቦምቤይ ተወላጆች እግረኛ ጦር የሚባለው ጥቅምት 11 ቀን 1860 ዓ.ም ዙላ አጠገብ ሙልቅጦ ከተባለችው ባህር ዳርቻ ወረደ። ይህ በመሐንዲሶችና በሠራተኞች የተመላው ቀዳሚዊ ዘማች ከሙልቅጦ እንደወረደ ወዲያውኑ ሥራውን ጀመረ። ሥራውም በወደቡ አካቢና እስከ ዙላ ድረስ ለሚመጣው ጦር ማረፊያ ማዘጋጀት ነበረ።

በጥቅምት ወር መጨረሻ ገደማ ከባህሩ ውስጥ እስከ መሬት ድረስ ያለ የመርከቦች ማስጠጊያ እና የዕቃ ማራገፊያው ጄቲ (ግንብ) ተሠርቶ አለቀ። በግምቡ (በጄቲው) ላይም የባቡር መሔጃ ሐዲድ ከባህሩ መሃል እስከ ምድር ድረስ ተዘረጋ። ይህ ግንብ ባባህር ላይ የመጡት መርከቦች ይጠጉትና ጭነቱ የሚራገፍበት ነው። ይህም የሚሠራው መርከቦቹ ከመሬቱ ዳርቻ ድረስ ለመውጣት ስለማይችሉ ነው። ይህም ጄቲ እስከነሐዲዱ ፈራርሶ ሐዲዱም ዝጐ አይቼዋለሁ።

ጊዜያዊ ቤቶችም በባህሩ ዳርቻ ተሠሩ። ሠራተኞቹም ህድኖቹ ርዴያኖች፥ ግብጾችና፥ ኢትዮጵያውያኖች በሠፈሩ በመብዛታቸው ያ ውድማ የነበረው ሜዳ ከተማ መሰለ። እኔ እንዳየሁትም ዛሬም ተመልሶ ውድማ ቢሆንም አንድ ከግንብ የተሠራ ሕንፃ ከባሕሩ ዳርቻ አጠገብ ቆሞ በመጠኑ ቢፈራርስም ለመታሰቢያነት ያህል ይታያል።



27ኛው የቦምቤይ እግረኛ ወታደር

በባሕር ማለቂያ ሌላው ሁለተኛው የመርከብ ማስጠጊያ ጄቲ ተሠርቶ አለቀ። የዚህኛው ጄቴ እይባህር ውስጥ ርዝመት 3000 ሜትር ያህል ነበር። በሱም ላይ የባቡር ሐዲድ ተዘርግቶ ስላለቀ ባቡር መመላለስ ጀመረ። ከዚህ ለባቡር መስመር መዘርጋት ሥራ በሞያው ጥሩ ችሎታ ያላቸው 176 ቻይናውያን መጥተው ስለ ነበረ እነሱ ናቸው የሠሩት። በዚያ አካባቢና ዙላ ድረስ (ዙላ ከወደቡ ትንሽ ራቅ ይላል) ተመላላሹ ሠራተኛ በመባቱ ሰዎች አንዳንድ ሱቆች መከፈት ጀመሩ።

ሆስፒታሎች ተሠሩ። ታላላቅ መጋዘኖችና በጣም ሰፋፊ እይሆኑ የእንስሳ በረቶች ተበጁ። ከባህሩ ጫፍ ከጄቴው መነሻ አጠገብ የተተከሉ ሁለቱ የውሃ ማጣሪያ ኮንዴንሰሮች በቀን 160 ቶን ከጨው የተጣራ ውሃ ማውጣት ጀመሩ። ይህም ድጋፍ በየቀኑ በመርከብ ከኤደን እየተጓዘ ለተጠራቀመው በሚሊዮን ቶን ለሚገመተው የተጣራ ውሃ ድጋ ሰጭ ሆነ።

ሥራው እያለቀ በመሔድም ጦሩና የጦር መሣሪያዎቹ መግባት ጀመሩ። ከግብፅ አገር የተገዙት 11.000 ፈረሶች በቅሎዎች አህያዎችና ግመሎች ገቡ። ከህንድ የሚነሳው ጦርም በየቀኑ ከመርከብ እየወረደ ይሠፈር ጀመር። በዚህ መሀል በዙላ በሠፈረው ሠራዊት ላይ ያልታሰበ ድንገተኛ አደጋ መጣበት። የከብት ወረርሽኝ በሽታ ገባ። በበሽታው የተለከፉ ፈረሶችና በቅሎዎች በየቀኑ በመቶ የሚቆጠሩ ያልቁ ጀመር። ከእንስሶቹ ማለቅ ሌላ ደምን ሬሳቸው ከባሕሩ ዳርቻ ይጣል ስለ ነበር ከባድ በሽታ ያመጣል ተብሎ አሰጋ ዙላ አገሩ ቆላ በመሆኑ ሜርዌዘር አሉ ያላቸው የውሃ ጓድጓዶች ሁሉ ስለደረቁ የውሃ እጥረት የሚያሰጋ ሆነ። የኮንዴንሰሮቹም ማጣራት በየቀኑ ከሚገባው ሰውና እንስሳ ጋር አልመጣጠን አለ። ይህ ከሆነ በኋላ ጦሩ ተከፍሎ ቀዳሚ ጦር ወደ ሰነአፌ እንዲሄድ ታዘዘ። ሰነአፌ ዋናው ጦር ከሠፈረበት ከባህሩ ዳርቻ 40 ማይልስ ያህል ይርቃል። የቀደመው ጦርም በመሀንዲሶች የተሞላ ስለ ነበረ የሚጓዘው ለተከታዩ ጦር መንገድ በመሥራት ነበር።

ይህ ቀዳሚ ጦር ከግብጾች የመሬት ይዞታ ወጥቶ ከደጃዝማች ካሣ (በኋላ አጤ ዮሐንስ ከሆኑት) ግዛት ሲገባ ጦሩን የሚመራው ሜርዌዘር ለደጃዝማች ካሣ ደብዳቤ ፅፎ የማለፊያ ፈቃድ ጠየቀ። በጻፈውም ደብዳቤ የሚጓዘው በመቅደላ ያሉትን ኤሮፓውያን እስረኞች ለማስፈታት ብቻ መሆኑን ገልጾ በሰላም እንዲያስላፉት የሚጠይቅ ነበር። ሜርዌዘር ለጻፈው ደብዳቤም ደጃች ካሣ መልሱን በፅሁፍ አሳወቁት። ደጃች ካሣ በጻፉት ደብዳቤ ከራስ ወልደ ሥላሴና ከሰባጋዲስ ጋር እንግሊዞች የነበራቸውን ወዳጅነት እሳቸውም እንደሚፈልጉት ገልፀው ይህንንም ወዳጅነት ለማደስ ሁኔታውን ለመነጋገር መርጫ ወርቄን መላካቸውን የሚገልፅ ነበር።

መርጫ ወርቄ ከደጃች ካሣ የተላከውን ደብዳቤ ለሜርዌዘር ሰጥቶ ሲጨዋወቱ ሜርዌዘር «የመጣነው እስረኞች ወገኖቻችን ከመቅደላ ለማስፈታት ነው። ሕዝቡን ለመንካት ወይም አገሪቱን ለመውረር አልመጣንም.....» አለው። መርጫ ወርቄም የቴዎድሮስን መሸነፍ እነሱም እንዲፈልጉት ገልጾ ከዚያ በኋላ አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ በሚለው ሐሳብ ሁለቱንም ወገኖች ተስማምተው ተለያዩ።



# የዙላ ሰፈርና ወደብ

ሜርዌዘር ከደጃዝማች ካሣ የማለፊያውን ፈቃድ ካገኘ በኋላ ከካሣ ግዛት ሲወጣ የሚጠብቀው የዋግሹም ጎበዜ ግዛት በመሆኑ ለእሳቸውም ያንኑ የመሰለ ቃል ፅፎ ላከላቸው። ዋግሹም ጎበዜም በስጡት መልስ የቴዎድሮስን መውደቅ እንደሚፈልጉ ገልፀው ለዚህ ጉዳይ ብቻ ከሆነ የማይቃወሙ መሆናቸውን ጻፉለት። የሸዋው ምኒልክ በጦሩ መንገድ ላይ ምንም ግዛት ስለሌላቸው ሜርዌዘር በአሁኑ ጊዜ ደብዳቤ አልጻፈላቸውም። ኤደን በነበረ ጊዜ ምንም ተቃውሞ እንዳያነሱ ፅፎላቸው ተስማምተዋል። ሜርዌዘር ሰነአፌ ላይ ሆኖ ከታላላቆቹ ገዢዎች ጋር በቃልም በፅሁፍም የመጓዣውን መንገድ ጥርጊያ አሳመረ።



ናፒየር ከሹማምንቶቹ ጋር

ሜርዌዘር ይህን ካደረገና ካጠናቀቀ በኋላ ለአጤ ቴዎድሮስ በናፒር ስም ደብዳቤ ጻፈላቸው።

ለቴዎድሮስ

የአበሻ ንጉሥ

«በእንግሊዝ ንግሥት ትእዛዝ በእጅዎ ያለ ምክንያት የተያዙትን እስረኞች ለማስለቀቅ መጥቻለሁና እስረኞቹን በሙሉ ለቀው እንግሊዝ ሠፈር ከደረስንበት ድረስ እንዲልኳቸው ይሁን። ግርማዊነትዎ ይህን ትእዛዝ የማይስማሙበት ቢሆን ግን ከግርማዊነትዎ ግዛት በኃይል እንድገባ ታዝዤአለሁ። ይህንንም የመጣሁበትን እስክፈፅም ምንም የሚያቆመኝ ኃይል የለም።

«በግዛትዎ ውስጥ የማደርገውም ሆነ የምፈልገው ነገር የለኝም ሥልጣንዎንም አልቀናንም። ዋናው ጉዳይ የተያዙት ሰዎች እንዲለቀቁ መሆኑ አሳውቆታል።

«ግርማዊነትዎ ይህን የመጣውን አደጋ እስረኞቹን ቶሎ በመልቀቅ ሊመልሱት ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን እስረኞቹ በሰላም እጄ ካልገቡ ቢጉላሉ፥ ወይም አንዳንድ ጉዳት ቢደርስባቸውም ኃላፊነቱን የሚወስዱት በግል ግርማዊነትዎ ብቻ ነዎት። ይህ ከሆነም ለወደፊቱ ምንም ዓይነት ወዳጅነት አይኖረንም።

አር. ናፒር ሌ/ጄኔራል

የቦምቤይ ጦር ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ።

ይህን ደብዳቤ ይዞ የሚሔደውን ሰው ከመንገድ ላይ ሽፍቶች አግኝተው ያዙት። መልእክተኛውም የቴዎድሮስን ስም እንዳይጠራ ፈርቶ እንግሊዞች ለራሳም የጻፉትን ደብዳቤ ይዞ እንደሚሄድ ገለፀ። ሽፍቶቹም በራሳቸው መልእክተኛ ደብዳቤውን ለራሳም ላኩለት። ራሳምም ደብዳቤው እንደደረሰው አንብቦ ለቴዎድሮስ በመድረስ ፈንታ ሲሉ በመድረሱ በጣም ተደሰተ። ለቴዎድሮስ ደርሶ ቢሆን ኖሮ በራሳም አስተሳሰብ እስረኞች የተባሉትንሁሉ እንደሚፈጅዋቸው ስለገባው ደብዳቤውን ደብቆ አስቀመጠው።

ይህ ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ የእንግሊዝ ጦር ዋና አዛዥ ጄኔራል ናፒር ወደ ኢትዮጵያ ገና አልመጣም ነበር። ናፒር ጦሩንና ጓዙን በሙሉ አስቀድሞ ከላከ በኋላ በታኅሣሥ 25 ቀን ሙልቅጦ ገባ። ጄኔራል ናፒር ከቦምቤይ ወደብ ኦክታቪያ በተባለች መርከብ ከተከታዮቹ መኰንኖች ጋር ሆኖ ውልቅጦ ወደብ አካባቢ መርከቧ ስትደርስ ያሉዋት መድፎች በሙሉ ተተኩሶ። ከመሬት ለአቀባበርሉ የተዘጋጁት የጦር መድፎችም አጠፋውን በመተኮስ መለሱ።

መርከቢቱ ከተዘጋጀው ጄቲ አጠገቡ ቆመች። ጄኔራል ናፒር ከመርከቧ ብቅ ሲል የተሰለፈው ጦር ሙዚቀኞች የወታደር ማርሽ ማሰማት ጀመሩ። ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቁ የወታደር ሙዚቃ በሚሰማበት ጊዜ ለወሬ የተሰበሰበው የዙላና የአካባቢው ሕዝብ ሴቱ በእልልታ ወንዱ በሆታ በባህሩ ማዕበል ጋር መሬቲቱን በጩኸት አደበላለቋት። በቀይ ኮት ያጌጠውንና የተሰለፈው የክብር ዘብም በብረት ሰላምታ ሰጠ። ናፒር የመጣው ወደ ኋላ ከቀሩት 19 ዝሆኖች ጋር ስለነበረ የዝሆኖቹ በሰልፈኛው መሀል ማንጐማለል ለሰልፉ የበለጠ ድምቀት ሰጠው። እነኝህ ለመቅደላ ጦርነት የመጡት

ለማዳዎቹ የኤስያ ዝሆኖች ከታላቁ አሌክሳንደር በሃኡአል ለአፍሪካ ምድር የመጀመሪያዎኡ ዝሆኖች ነበሩ። ናፒርም ለሶስት ሳምንታት ያህል በዙላ የተሠራውን በመመልከትና የጐደለውንም በማሟላት ቆይቶ ዘማቹንና ከወደቡ የሚቀረውን ጦር ካደላደለ በኋላ ጥር 17 ቀን ወደ ሰነአፌ ሔዱ።

ናፒ አስቀድሞ የላከውና በኋላም ይዞት የመጣው ስንቅ 32.062 የሰው ኃይልና 27.747 የጭነትና የምግብ እንስሳት ነበሩ። ዝርዝሩን ለማወቅ ካስፈለገ እንደሚከተለው ነው።

10.231 እግረኛ ወታደር

983 መድፈኛ ወታደር

2.064 ፈረሰኛ ወታደር

2.306 ረዳት ዕቃ ያዥ ወታደር በጠቅላላው 16.189 ተዋጊ ወታደሮች ሲሆኑ ከብት ነጅና ጠባቂው ደግሞ 12.640 ሰዎች ነበሩ። ለመኮንኖች ተከታይ የሆኑ አሽከሮች ደግሞ ብዛታቸው 3.233 ነበር።

ይህ ሁሉ ሠራዊትና ጓዝ የመጣው በ669 መርከቦች ነው። ለመርከቦቹም የተከፈለው የኪራይ ገንዘብ 433.028 ፓውንድ ነበር። በጓዝ በኩልም መርከቦቹ ጭነው ያጋዙት 306.524 ቶን የሚከብድ ዕቃና መሣሪያ ነበር። በእንስሳት በኩል ሙልቅጦ የገባው።

4.189 ፈረስ

16.022 በቅሎ

1759 አህያ

5.733 ግመል

44 ዝሆን ሲሆን ለወታደሩ ስንቅና ቀለብ እንዲሆኑ የገቡት የሥጋ ከብቶች ደግሞ 7.071 በሬና 12.839 በጐች ነበሩ።

ጄኔራል ናፒር ይህን ይህን ሁሉ ጓዝና ሠራዊት አስቀድሞ እሱ ኢትዮጵያ ምድር ከገባ በኋላ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚነገር አንድ አዋጅ አወጣ።

«ለገዥዎች፥ ለባላባቶች፥ ለሃይማኖት መሪዎችና ለአበሻ ሕዝቦች በሙሉ።

«የአበሻው ንጉሥ ቴዎድሮስ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል የሆነውን ካሜሮንን የእንግሊዝ ንግሥት መልክተኛ ራሳምንና ሌሎችንም ብዙዎችን ኤሮፓውያኖች ከሰለጠነው ዓለም ሕግ ውጭ አስረው መያዛቸውን ሁላችሁም ታውቃላችሁ። እንዲለቋቸውም በወዳጅነት የተደረገው ድካም ሁሉ አልሆነም። በዚህም ምክንያት መንግሥቴ አንድ ጦር እንድመራና እስረኞቼን እንዳስለቅቅ አዞኛል።

«ለእስረኞቹ ወዳጅ የሚሆነው ሁሉ ወይም ነፃነታቸውን እንዲያገኙ የሚያደርግ ሁሉ ይሸለማል። አንዲጎዱ የሚያደርጉ ግን ያእል ምህረት ይቀጣል።

«የእንግሊዝ ጦር ሠራዊት በአገራችሁ ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ አሳውሱ የአበሻ ሕዝብ ሆይ። የእንግሊዝ መንግሥት ከእናንተ ጋር ጠላትነት የላቸውም። የአገራችሁንም ሆነ ነፃነታችሁን ለማጥፋት ምኞትም የላቸው። ሃይማኖታችሁ እንደተመሠረተ ሰዎቻችሁና ሀብታችሁ ሁሉ በጥንቃቄ ይጠበቃል። ለወታደሮቼ የምታቀርቡት ምግብ ሁሉ ዋጋው ይከፈልበታል።

«የእንልግሊዝ መንግሥት ኃይል ወደ አበሻ ምድር የመጣው የግርማዊት ንግሥት አሽከሮችና ሌሎችም ያለ ፍርድ የተያዙትን ኤሮፓውያኖች ለማስለቀቅና ነፃነታቸውን ለማስገኘት ነው። ይህ ከሆነ በኋላ በተቻለ ፍጥነት አገሪቱን ለቀን እንወጣለን። ከአበሻ ምድር ውስጥ ምንም ዓይነት ግዛት ለመፈለግ ወይም በአገራችን የመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ ልንገባ አልመጣንም»

ናፒር በጉዞው ላይ መጀመሪያ ከሚያገኛቸው ከደጃች ካሣ ጋር በቃል መነጋገሩ ጠቃሚ መሆኑን አወቀ። በዚህም ምክንያት ይህንኑ ግንኙነታቸውን የሚያዘጋጁና የሚያገናኙትንም ቦታ የሚያስወስኑ መልክተኞች ከሰነአፌ ወደ ደጃች ካሣ ተላኩ። በኰሎኔልነት ሲያገለግል የኖረው አሁን ብርጋዲየር ጄኔራል ሆኖ የተሾመው እና የኢትዮጵያን መኳንንት እስከ አጤ ዮሐንስ ዘመን ሲያበጣብጥ የኖረው ሙዚንጀርም አብሮ ነበር። በጠቅላልው 13 መልክተኞች ያሉበት ቡድን ጥር 18 ቀን ከሜጀር ጄኔራል ናፒር ተልኮ ወደ ደጃች ካሣ ሔደ። ጥር 23 ቀንም ከደጃች ካሣ ዋና ከተማ አድዋ ገባ።

መልከተኞቹ አድዋ እንደደረሱም በመርጫ ወርቄ ወንድም በገብሩ ባልደረባነት በገቡ በማግሥቱ ከደጃች ካሣ ጋር ተገናኙ። ገብሩ ወርቄ ከሕድን አገር ቦምቤይ የተማረ በመሆኑ እንግሊዝኛ በሚገባ ይችላል። ለባልደረብነት የተመረጠውም በዚሁ ምክንያት ነበር።

ደጃች ካሣ የሽሬውን ገዥ ጉግሣን አማካሪያቸውን የፀረ ገብረ ሚካኤል የሰላዋውን ገዥ ኃይለ ማርያምን የገራልታውን ሐጐስን የአክሱሙን ንቡረዕድ ውበትን ሹም ተምቤን አኑንን ሹመው አጋሜ ጥርሶን የሰባጋዲስን ልጅና ሌሎችንም መኳንንት ይዘው ተቀበሉዋቸው። መልእክተኞቹም የመጡበትን ጉዳይ ሳይሆን የወዳጅ ሰላምታ ከተለዋወቱ በኋላ ታላቅ ግብር ተደረገ። በማግስቱ የመጡበት ጉዳይ ንግግር ተጀምሮ ከናፒር የተጻፈውን ደብዳቤ መልእክተኞቹ ለደጃች ካሣ ሰጡ። ደብዳቤው ተነቦና ተተርጉሞ እንዳበቃም ደጃች ካሣ ሲናገሩ «.......አባቶቼ ከእንግሊዝ ጋር ወዳጅነት እንዳበጁ ሁሉ እኔም ወዳጅ በመሆን ከብትና አህል በማቅረብ እረዳለሁ........» አሉ።



ራስ ካህሣይ በአዲግራት ከእንግሊዝ ሰፈር ሲደርሡ

በዚህና ከናፒር ስለሚገናኙበትም ቦታና ጊዜ ተስማምተውና ወስነው የናፒር መልእክተኞች ጥር 27 ቀን ከአድዋ ተነስተው ጉዞአቸውን ጀመሩ። ከመልክተኞቹም ጋር ሊቀ መኳስ ይልማ አብረ እንዲሔዱ ተደርጐ ነበር። ሊቀ መኳስ የአድዋ አዋሳኝ የጐንደብታ ገዢ ናቸው። እናታቸው የሰባጋዲስ ልጅ ሲሆኑ አባታቸው ሊቀ መኳስ ደስታ ይባላሉ። ደስታ ደግሞ የጐንደብታው የፊታውራሪ ገብረ አምላክ ልጅ ናቸው። ከመልእክተኞቹ ጋር ሊቀ መኳስ ይልማ ዋና ሆነው አብረው እንዲሔዱ ይላኩ እንጂ እሳውስት አርባ ያህል ጦር የያዙና ሃያ ጠመንጃ የያዙ ተከታዮች አብረው ነበሩ።

እነኘህ መልእክተኞች ከናፒር ሠፈር መድረሳቸው እንደተሰማ ናፒር ከፍተኛ አቀባበል እንዲደረግላቸው አዘዘ። ከዚያም የመልክተኞቹ የሁለቱም ወገን ቡድን ከናፒር ጋራ ተገናኝተው በሰፊው ከተነጋገሩ በኋላ በማግስቱ

ኢትዮጵያውያኖቹ መልእክተኞች አንድ ወጥ ልብስ (ዩኒፎርም) በለበሱ ወታደሮች አጃቢነት ተሸኝትወ ወደ አድዋ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ሁለቱም ወገኖች የተስማሙት የትግራዩ ገዥ ደጃች ካሣ የእንግሊዙ ጦር አዛዥ ሌተና ጄኔራል ናፒር ሐራማት ውስጥ ማይ አደብ ከተባለው ቦታ እንዲገናኙ ተወስኖ ነበር።

በቀነ ቀጠሮው ናፒር በ450 ወታደሮች ታጅቦ የካቲት 18 ቀን ማይ አደብ ሲደርስ ደጃች ካሣ አራት ሺህ ከሚሆኑ ጠመንጃና ጦር ከያዙ ወታደሮቻቸው ጋር በዚያው ሠፍረው ነበር። ቀይ መልክ ያለው ካሣ ድንኳን ተተክሏል። ከካሣ ሠፈር ማዶ ከትይዩ ቦታ የናፒር ሠፈር ሆኖ ድንኳኑ ተተከለ። የድንኳኑ ተከላ ሥራ አልቆ ጥቂት ከቆየ በኋላ ካሣ በወታደሮቻቸው ታጅበው ናፒርን ለመገናኘት ወደ ናፒር ሠፈር ሔዱ። ካሣ በአሥፈሪ ግራም ታጅበዋል። የተቀመጡባት በቅሎ ግራጫ (ነጭ) ነች። ካሣ በራሳቸው ላይ ያሠሩት ታላቅ ጐፈር ግርማ ሞገስ ሰጧቸዋል። ታላቅ ዣንጥላ በረጅም ሰው ተይዞላቸው ከበፊታቸው ነጋሪቱ እየተጐሰመ እምቢልታ እየተነፋ የኢትዮጵያን ባንዴራ ቀይ ቢጫ አረንጓዴ የሆነውን (ያኔ እንዲህ ነበር።) አስቀድመው በ400 ወታደሮች ታጅበው ሔዱ።



ብርጋዴር ጀነራል ሜርዌዘር ከካህሣይ ጋር ተቀምጠው

የካሣ መምታት እንደታወቀ ለቀባበውሉ የክብር ዘብ ተሰልፎ ራሱ ናፒር ባጌጠ ዝሆን ተቀምጦና ቀያይ ልብስ በለበሱ ዝሆን ተቀማጮች ታጅቦ ታላቅ አቀባበል አደረገላቸው። ከዚያም ከአቀባበሉ ሥርዓት በኋላ ለመገናኘት ከተዘጋጀው ድንኳን ይዞአቸው ገባ። ጥቂት ረፍት እንዳደረጉ የወይን ጠጅ ቀረበ። ወይን ጠጅ ለደጃች ካሣ ሲሰጥ በውስጡ መርዝ ወይም መጥፎ እንገር ያለመኖሩን ለመግለፅ ናፒር ራሱ የካሣን ብርጭቆ ተቀብሎ ቀመሰ።

በንግግሩም ወቅት እንግሊዞች ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ቀደም ብለው የሚያቁት ሙዝኒጀር እንደሚያዘጋጅላቸው ካሣ ተናግረው በእሳቸው በኩል ደግሞ ያለውን ችግር የዋግሹም ጉበዜና በአጋሜ የራስ ባርያው መሸፈት መሆኑን አስረዱ። ናፒርም ሲመልስ በጋራችሁ የውስጥ ጉዳይ አንገባም። መሣሪያ ግን እንረዳዎታለን ብሎ በዚህ አሳብ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተው አንገባም ማለቱ የጨዋነት መልስ ቢሆንም ዋናው ቁም ነገር ግን ናፒር ከትግራይ ከደጃች ካሣ ግዛት ሲወጣ የሚያጋጥመው ወይም

የሚገባበት የዋግሹም ጐበዜ ግዛትና ዋግሹም ጐበዜ በመሆናቸው ናቸው ነው።

ደጃች ካሣ ከናፒር ከመለየታቸው በፊት ናፒር ወደ ሠፈራቸው እንዲመጣ ጋብዘውት ስለነበረ በዚያው ዕለት ከተሰያት በኋላ ናፒር ወደ ደጃች ካሣ ሠፈር ሔደ። ከካሣ ሠፈር ሲደርስም የካሣ ወታደሮች ተሰልፈው እርምታ በመተኰስ ተቀበሉት። ናፒርም ምርጥ የሆኑትን የካሣን ወታደሮች በማየቱ መደሰቱን ለደጃች ካሣ ገለጠላቸው። ከዚያም ከካሣ ጋር ተያዘው ለማረፊያ ወደ ተዘጋጅተው ድንኳን ገቡ።



ራስ ካህሣይ ከናፒየር ጋር ተቀምጠው ሲጨዋወቱ

ከድንኳኑ እንደገቡም የትግራይ ቆነጃጅት ሴቶች እያሳለፉ በትልቅ ውብ ዋንቻ ጠጅ እየተቀዳ ተሰጣቸው። ግብር ቀርቦ ምግብ ከተበላ በኋላ እምቢልታ ነፊዎችና ማሲንቆ መቺዎች ገብተው ጨዋታ ተጀመረ። ካሣም ለጄኔራል ናፒር በራሱ ላይ የአንበሳ ጐፈር አሠሩለት። በእጁም ጦርና ጋሻ


በማስያዝ ሽለሙት ከዚህ በኋላ ናፒር ለመሔድ በሚነሳበት ጊዜ ከድንኳኑ በራፍ ሲደርስ በወርቅ መረሸት ያጌጠች ግራጫ በቅሎ ቀርባ ለመጓጓዣው የተሰጠችው መሆኑ ተነገረች። መልካም አቀባበል እንደተደረለት የተሰጠችው እምሆኑ ተነገረው። መልካም አቀባበል እንደተደረገለት ሁሉ እምቢልታና መለከት ነፊዎች ቀድመው ሙዚቃ እያሰሙ መልካም አሸኛኘት ተደረገለት። ናፒር ጐፈሩን አስሮ ጐራዴውን ታጥቆ በተሸለማት ግራጫ በቅሎ ተቀምጦ ከሠፈሩ ሲገባ እንኳን ወታደሮቹ የሆኑት የእንግሊዝ መኰንኖች እንኳ ናፒር መሆኑን አላወቁም ነበር።

ከዚህ በኋላ የእንግሊዝ ጦር የመቅደላ ጉዞውን ቀጠለ። የእንግሊዝ ጦር በሚጓዝበት ጊዜ በየደረሰበት ሁሉ ሕዝቡ እየወጣ በማድነቅ ይመለከተው ነበር። ጉዞው ላይ ፈረሰኞች ይቀድማሉ። ፈረሰኞቹም አረንጓዴ ልብስ ለብሰው ውብ ባርኔጣ ያደረጉ ናችው። መኰንኖቹ ግን ብርማ መልክ ያለው የብረት ባርኔጣ አድርገዋቸል። ከፈረሰኞቹ ቀጥሎ የሚጓዘው እግረኛው ወታደር ነው። ከእግረኛው ወታደር መሀል የሆኑት ሕንዳዊ ወታደር ከጉልበታቸው የሚደርስ አረንጓዴ ቁምጣ ታጥቀዋል። ቀይ ኮት ደርበዋል። አረንጓዴ ጥምጥም ጠምጥመዋል። ሕንዳዊ ያልሆኑት ወታደሮች ደግሞ ሱሪያቸው ተመሳሳይ ሲሆን ነጭ ኮፍያ (መለዮ) አድርገው ይጓዛሉ። ይህ ሁሉ ታይቶ ያልታወቀ የአለባበስና የሰልፍ ሂደት ሕዝቡ እያየ ቢያደንቅም የበለጠ ግን የሚደነቀው ታላላቆቹን መድፎች የተጫኑት ዝሆኖች በየራሳቸው ላይ ሰው ተቀምጦባቸው ሲጓዙ ማየቱ ነበር።

በጉዞው ላይ ናፒር በየደረሰበት ሠፈርና መንደር ሁሉ ከሠፈሩ ሹም ጋር ሰላማዊ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ ከብሪትሽ ሙዝየም ለቅርሳዊ ዕቃዎች ፍለጋ ከጦሩ ጋር የመጣው ሪቻርድ ሆልምስ ደግሞ በየቤተ ክርስትያኑ እየገባ ለሙዚየም የሚሆን ዕቃዎችን ይፈልግ ነበር።

ከደጃዝማች ካሣ ግዛት ጨርሰው ከመውጣታቸው በፊት ቀጥሎ ካለው አገር ከላስታ ገዥ ከዋግሹም ጐበዜ ጋር በሰላም ለማለፍ መነጋገር ያስፈልግ ነበር። ይህንኑ ጉዳይ እንዲነጋገር ሙዚንጀር ተልኮ ቀድሞ ሔደ። በዚያን ጊዜ ዋግሹም ጐበዜ ወደ በጌምድር ሔደው ነበር። በቦታቸው ግን አጐታቸውና የጐበዜ ጦር ዋና አዛዥ ለሆኑ ደጃች መሸሻ ስለ ነበሩ በተከዜ ሸለቆ ዛጐል ዛፍ ከሚባል ሥፍራ ከሙዚንጀር ጋር ተገናኙ። ካናፒር በተላከው መልዕክት

መሠረት ደጃች መሸሻ ተስማምተው የእንግሊዝን ጦር እየመሩና እየጠበቁ ያለ ምንም ችግር ኮችታ ደላንታ ደረሱ።



የእንግሊዝ ወታደር መቅደላ አፋፍ ሲወጣ

የእንግሊዝ ጦር ደላንታ ላይ የስንዴ በተባለ ቦታ ሠፈር ሳለ ናፒር ራሱ ለአጤ ቴዎድሮስ የመጀመሪያውን ደብዳቤ ጻፈ ደብዳቤውም «.........በእንግሊዝ ንግሥት ትእዛዝ ከጦር ሠራዊቴ ጋር መቅደላ አጠገብ ደርሻለሁ። የታዘዝኩትም በእርሶ እጅ የሚገኙትን መልክተኛዎን ራሳምን ቆንሲል ካሜሮንን ሐኪም ብላክንና ሙቶ አለቃ ፕሪዲውክስን እና ሌሎቹንም አሁን በግርማዊነትዎ ኃይል ሥር ያሉትን ኤሮፓውያኖቹን ለማስለቀቅ ነው ግርማዊነትዎን የምጠይቀው እነኝህን ሰዎች በተቻለ ፍጥነትና ሰላማዊ ሰፈሬ ድረስ እንዲልኩልኝ ነው........» የሚል ነበር።

የእንግሊዝ ጦር በዚያው የስንዴ በተባለው ቦታ እንደ ሠፈሩ ለቴዎድሮስ በተጻፈው ደብዳቤ መልሱ እስኪመጣ ድረስ ከዋግ ጐበዜ እንጀራ አባት ከዋድላው ገዥ ከደጃች ወልደ ቂርቆስ (ኪሮስ) ከደላንታው ባላባት ልጅ አበጋዝ ጋር ተገናኝተው በመመካከር 20.000 ኪሎ ግራም ስንዴ 15.000 ኪሎ ግራም ዱቄት 50.000 ኪሎ ግራም ገብስ ከዋድላ ከደላንታና ከዳውንት ሕዝብ ቀርቦላቸው ገዙ። መጋቢት 29 ቀን የወሎዋ ንግሥት የወይዘሮ መስተዋት ልጅ ኢማም አህመድ ከጐናቸው እንደሚሰለፍና ቴዎድሮስን ለመጣል እንዲበረቱ የሚያበረታታ ደብዳቤ በእናቱና በሱ ስም ጽፎ ለናፒር ላከ። ናፒርም ለደረሰው ደብዳቤ በእናቱና በሱ ስም ለናፒር ላከ። ናፒርም ለደረሰው ደብዳቤ መልስ በእንግሊዞች በኩል ምንም የሚያውክ ነገር እንደሌለና ቴዎድሮስ ግን በሌላ በኩል ከመቅደላ አምልጠው እንዳይወጡ ሠራዊታቸውን ጠባቂ እንዲያደርጉ ጽፎ ለአረብኛ ቋንቋ አስተርጓሚነት ጠባቂ እንዲያደርጉ ጽፎ ለአረብኛ ቋንቋ አስተርጓሚነት አብሮአቸው በነበረው በአክበር አሊ እጅ ላከላቸው። በፊት የመቅደላ ገዥ የነበሩትና ቴዎድሮስ ከድተው የወጡት ቢትወደድ ኃይሉ ከእንግሊዝ ጦር ዘንድ መጥተው የመቅደላን ምሽግ ሁኔታ መድፎቹ የተጠመዱበትን ቦታ ሁሉ ዝርዝር መረጃ ሰጡ።

እስካሁንም ድረስ ለቴዎድሮስ የተጻፈው ደብዳቤ መልሱ አልመጣላቸውም ነበር። ቀዳሚው የእንግሊዝ ጦርም ተከዜ ወንዝ ደረሰ። መቅደላ ለመድረስም የቀረው 65 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ነው። በዚህ ጊዜ ራሳም ይገልጻል።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት
ቴዎድሮስ ይድረስ ከአቶ ህርምዝ ረስአም ሰነበትህ እኔ እግዚአብሔር
ይመስገን ደህና ነኝ ሀኪም ብሎንግን አቶ ፕሪዩን እነአቶ ኬምሮንን እነ
አቶ ኮከብን ወንድሞችሽን እንዴት ሰነበታችሁ አለ በልልኝ እኔ ካንተ
ከወዳጀ ጠብ የለኝም ቂም የለኝም ቀድሞም መቅደላ የሰደድሁህ ጊዜ
ጠብቁ ብየ ብልክ ፈርቶን አሰርነው ብለው መልሰው ላኩብኝ አሁንም
እኔን ወዳጅህን እግዚአብሔር ካመጣልህ ሠንሰለቱ ይውጣል ተፈታ
የጌቶችኽን ሁነታ እስትናይ ድረስ ባንዲራው እንጠብቅሃለን አቶ ፍላፕ
ካገርህ ስንቅህን አምጥቶ ሰጥቶኝ ነበረ አገር ሸፍቶብኝ ተሸካሚ አጥቸ
ተበላሸብኝ ባቶ ፍላፕ ባለቃ እንግዳ በሻለቃ ልይህ እጅ ሁለት ሽ ብር
ሰድጀልሃለሁ ተቀበል ገንዘብህ ሰለተበላሸ መቶ በግ አምሳ ፍሪዳ
ሰድጄልሃለሁ ተቀበል በእግዚአብሔር ኃይል ደህና ለመድረስ ቢአበቃኝ
ዓይን ላይን ተያይተን እንጫወታለን አይዞህ።



ራሳም በቴዎድሮስ የደብዳቤ ትእዛዝ መሠረት ከታሰረበት ሰንሰለት ተፈታ። ቴዎድሮስም ወደ መቅደላ ሔደው ከመቅደላ ተራራ ግርጌ ከሰላምጌ ሠፈሩ። ሚስዮናውያኖች እስረኞች ያሉት ሰላምጌ ሲሆን የፖለቲካ እስረኞቹ ግን ከሰላምጌ በላይ ከአፋፍ ከመቅደላ ነው። አንድ ቀን ቴዎድሮስ ከሰላምጌ እንደሆኑ ዎልድሜርን ጠሩትና....... «ወደ መቅደላ እንሔዳለን። ቢጤዎችህንም ከዚህ ያሉትን ጥራቸውና አብረን እንሄዳለን.......» አሉት። ዎልድሜየርም ትእዛዛቸውን ተቀብሎ ለጓደኞቹ ለእስረኞቹ ፈረንጆች መልክቱን በነገራቸው ጊዜ ደነገጡ። ምክንያቱም ቴዎድሮስ ሰውን ከነሕይወቱ ገደል የሚጨምሩበት 135 ሜትር ያህል ርዝማኔ ያለው ገደል ላይ ስለሆነ በዚያ ገደል ይጥሉናል ብለው ፈርተው ነው። ቢፈሩም የሚቀር ነገር የለምና ቴዎድሮስን ተከትለው ወደ መቅደላ ወጡ።

ቴዎድሮስ ከመቅደላ አፋፍ እንደወጡ እስካሁን ድረስ በሰንሰለት የታሠሩበት እነ ካሜሮንን በታሠሩ በአራተኛው ዓመታቸው በሰንሰለት በታሠሩ በሁለተኛው ዓእምታቸው ሰንሰለታቸው እንዲፈታላቸው አዘዙ። እስረኞቹ በሙሉ ከሰንሰለት እስራት ተፈቱ። እስረኞቹ ሁሉ ከሰንሰለት እስራቸው ከተፈቱ በኋላ ከእስተርንና ከሮዜንታል በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ እንዲመጡ አስጠሩዋቸው።

ፈረንጆቹ እስረኞች ከመምጣታቸው በፊትም ከሜዳ ላይ ብዙ ምንጣፎች ተነጥፈው ነበር። ፈረንጆቹም መጥተው ከዚያ እንደደረሱ ቴዎድሮስም ወጥተው ሁሉም ከምንጣፍ ላይ ተቀመጡ። ከራሳም ጋር ከተገናኙ ሁለት ዓእምት አልፏቸው ነበርና እጁን ጨብጠው ሰላምታ ሰጥተውት ተቀመጡ። ለራሳምም የአስር ዓመት ያህል ዕድሜ የጨመሩ ሰው መስለው ነው የታዩት። ምክንያቱም ቴዎድሮስ በዚህ ጊዜ ሸብተዋል ከስተዋል። ተጐሳቁለዋልም። ከዚያም ባንድነት ሆነው በሰላምና በወዳጅነት ይጨዋወቱ ጀመር።

ሲጫወቱም «.......ስማ ራሳም። ባንተ እተማመንብሃለሁ። ይኸውና ልጄን ልዑል ዓለማየሁን አደራ ሰጥቼሃለሁ። ጠብቀው። አባትህም ሁነው። እንደማውቀው የመጨረሻዬ ቀን ተቃርቧል። ሬሳዬ አጠገብም የምትቆምበት ቀን ደርሷል። ያኔም ‹አ ንጉሥ ቴዎድሮስ ኃጢአትህ ምንኛ የበዛ ነው› ትሉ ይሆናል። ግን እባካችሁ በኔ እንዳትፈርዱ። ምክንያቱም በእያንዳንዳችን ላይ የሚፈርደው እግዚአብሔር ነው። እኔ እንደ ንጉሥነቴ እፈርዳለሁ። አንተም

እንደመልከተኛነትህ ትፈርዳለህ። ዎልድሜየርም እንደሚስዮናዊነቱ ይፈርዳል። ድሆች ለማኞችም እንደ ድህንታቸው ይፈርዳሉ። እግዚአብሔር በሰማይ ምስክሬ ነው። በምድርም ዎልድሜየርና ጓደኞቹ ሁሉ ወዳጅቸው እንደበርኩ ይመሰክራሉ። እግዚአብሔር የሚያደርገውን ካደረገ በኋላ እንገናኝ ይሆናል።........ተመልከተኝ ራሳም። ከተለያየን ጀምሮ እንዴት እንደሸበትሁ እየኝ «ብለው ራሳቸውን አሳዩት። ራሳምም በትህትና «ግርማዊነትዎ ቢሸብቱም ምንም አያስደነቅም በጋብቻ ላይ ስለሆኑ የጋብቻ ዘመንዎን በደስታ ያሳልፋሉ» አላቸው።

ቴዎድሮስም በራሳም አነጋገር ስቀው በእጃቸው ጉንጫውን እያሻሹ «ወዳጄ ራሳም። አሁን ገና ደህና አድርገህ ደበደብኸኝ።......አንድ ቀንም ሞቼ ታየኝ ይሆናል። ከሬሳዬ አጠገብም ትቆም...... ‹ይሄን ደካማ ሰውዬ አትቅበሩት። ሬሳው ከመሬት ላይ እንደቀደቀ ይቅር› ብለህ ትናገር ይሆናል። እኔ ግን በጨዋነትህ እተማመናለሁ» ቢሉት ራሳም እንዲህ ያለ ነገር እንዳይናገሩ ለመናቸው። ከዚያም ቴዎድሮስ ለራሳም ጤንነት ብለው ጠጅ የተቀዳበትን ዋንጫቸውን አንስተው ጠጡ። ራሳም አጤ ቴዎድሮስ ለናፒር ደብዳቤ ጽፈው ነገሩን በሰላም እንዲጨርሱ ነግሮአቸው ነበር። ቴዎድሮስ ግን ሰምተው እንዳልሰሙ ዝም አሉት።

ሚያዝያ 2 ቀን ጧት በ12 ሰዓት ቴዎድሮስ ዎልድ ሜየርን አስጠተውት ሔደ። ዎልድሜየር እንደደረሰም አዝነውና ተክዘው አገኛቸው።። ዎልድሜየርም ጥቂት ጊዜ ቆሞ እንደጠበቀ ቴዎድሮስ ከተቀመጡበት ተነስተው ራሳም ከነጓደኞቹ እንዲጠራ አዘው ወደ ውስጥ ገቡ። ራሳምና ሌሎቹ ተጠርተው ሲገቡ ቴዎድሮስ የንጉሥነት ማዕረግ ልብሳቸውን ለብሰው ወጡ። ራሳምንም «ለዚያን ሰውየ ወረቀት እንድፅፍለት ትፈልጋለህ? አይሆንም። አላደርገውም። አንዲት ሴት ለላከችው ሰው ምንም የማደርገው ነገር የለም።» ብለው ተቆጡ። ዎልድሜየርም ነገሩን ለማብረድ ብሎ «ጃንሆይ ከእንግሊዝ ጦር አዛዥ የተላከ ደብዳቤ ያመጣ ሰው አለ» አላቸው። እሳቸውም። «ተወው። ደብዳቤው በመልከተኛው ኮሮጆ ይቀመጥ። ቢፈልግም ወደ ላከው ጌታው ተመልሶ ሊሔድ ይችላል። ምክንያቱም እስከ ጭራሹም ስለማልቀበለው ነው። ሐሳቤንም ሊለውተው ስለማይችል ነው። አንተም ራሳም ከእንግሊዞች ጋር ግንኙነት ብትፈጥር ከኔ ጋር ያለህ ወዳጅነት ይጨረሳል። የመልከተኛህም ደም በራስህ ላይ ይሆናልና ተጠንቀቅ።

«........ካሉት በኋላ ወደ ዎልድሜየር ዞር ብለው «ሒድ ተሰናብተህ ና። ዛሬ ከንጉሥ ጋር የክብር ሞት ትሞታለህ» አሉትና ሁሉንም አሰናበቷቸው።

ቴዎድሮስ ሚያዝያ 2 ቀን ስረኞቹን ፈረንጆች ጠርተው በሚያነጋግሩበት ጊዜ በዚሁ ቀን የእንግሊዝ ጦር በበሸሎ በወርቅ፥ ውሃ ሸለቆ፥ ከፉላ ተራራ ሥር በእሮጌ በአፍንጮ ጦሩን ሲያሰልፍና ሲያደራጅ ዋለ።



የበሸሎ ወንዝ አጠገብ

ቴዎድሮስም ዎልድሜየርን ቤተሰብህን ተሰናብተህ ና ካሉት በኋላ ዎልድሜየር ከልጁና ከሚስቱ ጋር ተላቅሶና ተሳስሞ ከቴዎድሮስ ዘንድ ሲመለስ ንጉሡ ከተሰበሰበው ሠራዊታቸው ፊት ለፊት ከፈረስ ላይ ተቀምጠው እንደ ቆሙ አያቸው። የተሰበሰውበው ሰባት ሺ ያህል ሰው ይሆናል። ቴዎድሮስም ለሠራዊቱ ንግግር ያደርጉ ጀመር።

«.......ልጆቼ። እነህኝን የመጡትን የእንግሊዝ ወታደሮች አትፍሩዋቸው። እነሱ ዳዊትን እንደተጋጠሙት እንደ ፍልስጤማውያን ናቸው። ዳዊት ግን በእግዚአብሔ ኃይል አሸንፋቸዋለሁ ብሎ ገጠመ። እኔ የዳዊት የሰሎሞን ልጅ አይደለሁምን። እግዚአብሔር እኔን የኢትዮጵያ ንጉሥ አድርጐ አልቀባኝምን። በጦርነትስ ላይ የማልነካ ሁሉን የማስፈራ የእሳት ምሰሶ እየሆንኩ ያረጀሁበት ጀግና አይደለሁምን።.......እግዚአብሔር በድል ላይ ድል እየጨመረ አልሰጠኝምን። ዛሬ የእንግሊዝን ጦር አበሻ ምድር ድረስ እንዳስመጣሁት ድል ሳደርገው ደግሞ ታያላችሁ። እንደ ሕጋችን ወደ ጦርነት የሚሔደውን ሰው እግዚአብሔር ይፍታ እንዳይሉ ጳጳሱ አቡነ ሰላማ ሞተዋል። በእሳቸው ቦታ ሆኜም እኔ እፈታችኋለሁ። በእግዚአብሔር በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ማንኛውም ወታደር የኤሮፓውያን ጦር ተቃውሞ የሚዋጋውን ሁሉ በጦር ሜዳ ሕይወቱን ቢያጣ እግዚአብሔር ይፍታው ብለው ንግግራቸውን ሲጨርሱ ወታደሩን እየሸለለና እየፎከረ የእንግሊዝ ጦር ወደ መሽገበት ወደ አሮጌ ወረደ።

## ምዕራፍ 15

# ጦርነቱ ተጀመረ


ሚያዝያ 2 ቀን ከቀኑ ለአሥራ አንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የቴዎድሮስ ሠራዊት በእንግሊዞች ላይ ተኩስ ከፈቱ። ቴዎድሮስም ፏላ ኮረብታ ላይ ሆነው መድፎቻቸውን እንዲተኮሱ አዘዙ። የሚተኮሱትም የመድፍ ጥይቶች በእንግሊዞች ሠፈር ሠራዊት ላይ ምንም ጉዳት አላደረሱም። እግረኛው ሠራዊትም በብዛት እየተመመ ወደ እንግሊዞች ሠፈር ይጓዝ ጀመር። ይህንንም የቴዎድሮስን ሠራዊት ብርጌድ ተኩስ እንዲጀምር ታዘዘ።

በፊታውራሪ ገብርዬ የሚመራው 5000 ያህል የሚሆነው የቴዎድሮስ ሠራዊት በብዛትና ባንድነት ሆኖ በመጓዙ ለእንግሊዞቹ ተኩስ ተመቸ። ብዙ ሰውም አለቀ። የተረፈውም እየተፏከረ ለማጥቃት ቢሞክር ምሽግ ይዞና ተኝቶ የሚተኩሰው የእንግሊዝ ጦር አልበገር አለ። እነፊታውራሪ ገብርየና ብዙ

መኳንንቶችም በጀግንነት እየተዋጉ ሞቱ። የተረፈው ሠራዊትም መሸሽ ጀመረ።

ፉላ ላይ ሆነው መድፍ የሚያስተኩሱት ቴዎድሮስ የሠራዊታቸውን መሸሽ እንዳዩ ጋፋት ያሠሩት ትልቁ መድፋቸው እንዲተኮስ አዘዙ። ሚስዮኖቹን አላምን ብለው መድፉን እንዲተኩሱ የተመደቡት ኢትዮጵያውያን ነበሩ። መድፉ አንድ ጊዜ የሚጐርሰው የጥይቱ ክብደት 17 ኪሎ ግራም ያህል ነበር። ኢትዮጵያውያኖች ተኳሾች ግን ባንድ ጊዜ ሁለት ጥይቶች አጉርሰው በመተኮሳቸው መድፉ ከበስተኋላው በኩል ተሰነጠቀ። ከአገልግሎት ውጭ ሆነ።

መድፉ እንዲተኮስ በታዘዘበት ጊዜ ሠሪዎቹ ሚስዮናውያኖች ከመድፉ 3 ሜትር ያህል ሩቅ ብለው ቆመው ነበር። ቴዎድሮስም ከእነሱው አጠገብ ነበሩ። ቴዎድሮስ የመድፉን መሰንጠቅ እና ከአገልግሎት ውጭ መሆኑን ሲያውቁ ተበሳጩ። በንዴታቸው ብዛት ጥርሳቸውን ሲቀረጥሙ ድምፁ አጠገባቸው ለነበሩት ሁሉ ይሰማ ነበር። ቴዎድሮስ እንዲያ እንደተናደዱ መድፉን በሠሩት ፈረንጆች ላይ አንዳችም ርምጃ አልወሰዱም። በክፉ አስተያየት እንኳ አልገላመጡዋቸውም። ምክንያቱም የሠሩዋቸው ሌሎቹ ትናንሽ መድፎች በሚገባ ወደ እንግሊዝ ጦር ይተኩሱ ነበርና ነው። ግን ጥይቶቹ ባዶ ሜዳ ላይ ከመውደቅ በስተቀር ፋይዳ አልሠሩም። ወዲያውም ነጐድጓድማ ዝናብ በመዝነቡ ጦርነቱን ቅጥ አሳጣው።



# የንጉሡ ቤት ሲቃጠል


ከጀርባ የተኩስ ሽፋን ወይም ድጋፍ የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ከእንግሊዞች ምሽግ አምሳና ስልሳ ሜትር ርቀት ድረስ እየተጠጉ ቢዋጉም ለእንግሊዞች ጥይት ተመቹ እንጂ ውጤት ሊያገኙ አልቻሉም። በተለይ ደግሞ አብዛኛው የቴዎድሮስ ሠራዊት የሚዋጋው በጦርና በጐራዴ በመሆኑ ከማለቅ በስተቀር መጨረስ አልቻሉም። ጦርነቱም ከሶስት ሰዓት ውጊያ በኋላ ምሽት ሲሆን ቆመ። እንግሊዞች ምንም ጉዳት ባይደርስባቸው ሃያ ወታደሮች ያህል ቆሰሉባቸው። ከኢትዮጵያውያን ወገን ግን 700 ያህል ሰዎች ሲሞቱ 1200 ያህል ወታደሮች ቆሰሉ።

አጤ ቴዎድሮስም ቢሆኑ በዚህ ውጊያ ጊዜ ሊገደሉ ነበር። እንግሊዞቹ ከሠፈራቸው ሆነው ወደ ፉላ ኮረብታ ከተኮሱዋቸው የመድፍ ጥይቶች

አንደኛው ቴዎድሮስን ጥቂት ስቷቸው አጠገባቸው የቆመውን ሰው ገደለው። ከዚህም በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ጦራቸውን ያዋጉ የነበሩት ጋሻቸውን ይዘውና መከታ አድርገው ነበር። በኋላም መልክተኛ ልከው ከሥራቸው ያለው የሚዋጋው ሠራዊታቸው በሙሉ መገደላቸውን ነገራቸው። አጤ ቴዎድሮስም አዝነው ማታውኑ የማዋጊያ ቦታቸውን ከፉላ ወደ ሰላምጌ አዛወሩ። በዕለቱ ውጊያ የተረፈውም ሠራዊታቸው ቴዎድሮስን እየከዳ ወደየቤቱ ሔደ። አንዳንዶቹም ቁስለኞችን ሲያነሱና ሲያግዙ አመሹ። በዚያን ዕለት ውጊያ እንግሊዞች 18000 የጠመንጃ ጥይትና 219 ልዩ ልዩ የመድፍና ጥይት ተኩሰዋል። በዚያን ዘመን ስናድር ጠመንጃ ገና መፈልሰፉ ስለ ነበረ ለመጀመሪያ ጊዜ በጦር ሜዳ ላይ የዋለው በዚህ በመቅደላ የአሮጌ ጦርነት ነው።

ለሊት ፍላድ እና ዎልድሜየር ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ተጠሩ። ሌሎቹ ፈረንጆች እስረኞችና ተጠሪዎችም ልንገደል ነው ብለው ደንግጠው ነበር። ፍላድና ዎልድሜየር ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ እንደደረሱ «......ተዘጋጁ። ወደ ራሳም የምልካችሁ መልክት አለ «አሉና» እንዲህ በሉት። እኔ የኢትዮጵያ ንጉሥ ባገሬ ያለሁት ጉበዝ እኔ ብቻ ነኝ እል ነበር። አሁን ግን እግዚአብሔር ከኔ የተሻሉና ጠንካራ ሰዎች መኖራቸውን አሳየኝ። አሁን የምጠይቀው ምክር በኔና በእንግሊዝ ጦር አዛዥ መሀል እርቅ እንዲሆን ነው። «አሉዋቸው። እነሱም ወደ መቅደላ አፋፍ ወጥተው መልክቱን ለራሳም ተናገሩ። ራሳምም ሐሳባቸውን ደግፎ «የሰላም መልክተኞች ቢላኩ ጥሩ ነው» ብሎ መለሰላቸው። መልክተኞቹም ይህንኑ ለአጤ ቴዎድሮስ ነገሩ። ቴዎድሮስም ይህን እንደ ሰሙ «.......ወደ እንግሊዝ ለመላክ የሚያስቸኩል አይደለም። እግዚአብሔር ደስ የሚለውን ያድርግ። አሁን ሒዱና ተኙ።» ብለው አሰናበትዋቸው።

ከለሊቱ አስር ሰዓት ሲሆን ቴዎድሮስ እንደ ገና አስጠሩዋቸው እሰላሙ ጉዳይ እንዴት ሊሆን እንደሚችልም ጠየቁዋቸው። እነሱም ራሳም ያቀረበው ሐሳብ ጥሩ መሆኑን ነገሩዋቸው። በዚህም ስብሰባ ደጃዝማች ዓለሜ ሚስተር ፍላድና ፕሪዲውክስ የሰላም መልክተኞች ሆነው ወደ እንግሊዝ ጦር እንዲላኩ ተወሰነ። በማግስቱ ማለት ሚያዝያ ፫ ቀን እነኝህ መልእክተኞች በየበቅሎ ሆነው ነጭ ባንዲራ አስቀድመው ወደ እንግሊዞች ሠፈር ሔዱ።



# የአሮጌው ጦርነት

አጤ ቴዎድሮስ መልክተኞቹን ከላኩ በኋላ በመነጥር ቁልቁል የእንግሊዞችን የጦር ሠፈር አዩና «.......አቤት በአበሻ ምድር ምን ዓይነት የሚያስገርም ነገር ይታይ ጀመር? በዛሬው ቀን የእንግሊዝ ጦር በሙሉ በአበሻ ምድር ላይ ሠፈሯል።.......» ብለው ተናገሩ። ከዚያም በኋላ እነደጃች ዓለሜ የሚመጡትን መስል ሲጠባበቁ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ቆዩ። ደጃች ዓለሜ ከቴዎድሮስ ጋር አብረው ያደጉ ጓደኛ ሲሆኑ የአጤ ቴዎድሮስ ቁባት የሆኑት የወይዘሮ የተመኙን ልጅ አግብተው ጓደኝነታቸውን የጠና ሆነዋል።

እነደጃች ዓለሜ ከእንግሊዞች ጦር ሠፈር ሲደርሱ በእንግሊዞች ሠፈር ነጮ በመታየታቸው ጭፍራና ሁካታ ሆነ። ሠራዊታቸው የጨፈረው እስረኞቹ ተለቀው የመጡ መስሎት ነው። የእንግሊዝ ሠራዊት ከብቦ እየታያቸውና እያወካ ከናፒር ድንኳን ድረስ አደረሳቸው መልእክተኞችም የተላኩትን የሰላም መልእክት ለናፒር ነገሩ። ናፒርም በጉዳዩ ተስማምቶ ለአጤ ቴዎድሮስ

የሚላከው ደብዳቤ እስኪዘጋጅ ድረስ ደጃች ዓለሜ የእንግሊዝን ጦር ዝሆኖችንና ታላልቆቹን መድፎች እንዲጐበኙ ተደረገ። አስጐብኝውም «ትናንት የተኮስናቸው መድፎች ትናንሾችን ነው። እነኝህ ግን አንዱ መድፍ ላንድ ጦርነት በቂ ነው» እያለ ታላላቆቹን መድፎች አሳያቸው። ከዚያም በኋላ የተጻፈው ደብዳቤ ተሰጥቷቸው መልክተኞች በሙሉ ተመለሱ።

ደጃች ዓለሜ መልክቱን ይዘው ከመመለሳቸው በፊት በትናንቱ ውጊያ ላይ የሞቱትን የፊታውራሪ ገብርዬን ሬሳ እንዲፈልጉ አስፈቅደው ነበር። መልእክተኞቹ ሲመለሱ እግረ መንገዳቸውን የፊታውራሪ ገብርዬን ሬሳ ፈልገው አገኙት። ፊታውራሪ ገብርዬ የሞቱት በሰናድር ጠመንጃ ጥይት ግንባራቸውን ተመትተው ነው። ጐፈርና ለምድ ለብሰው ያዋጉ ስለነእብረም እንግሊዞቹ በመጀመሪያ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ የሚያዋጉ መስሏቸው ነበር አሁንም የወደቁት ከነማዕረግ ልብሳቸው ነው። ማርክሃም ስለ ገብርዬ ሬሳ አገኛኘት ሲገልጥ «......በጀርባቸው ተንጋለው ወድቀዋል። እጆቻቸው ተዘረጋግተዋል። ልብሳቸው ለበዓል ቀን የሚለበሰው በወርቀ ዘቦ ዝምዝም ያጌጠ ሐር ቀሚስ ነው። ፈረሳቸው ከእሳቸው አሥር እርምጃ ያህል ራቅ ብሎ ሞቶ ወድቋል። ጠጉራቸው ሽበት የበዛበት ነው።.......» ይላል። መልክተኞቹም የፊታውራሪ ገብርዬን ሬሳ ይዘው ወደ መቅደላ ወጡ።

ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ደረሱ። ንጉሡም ፊታቸውን ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስትያን አድርገው ድንጋይ ላይ ተቀምጠው አለቃ እንግዳን ደብዳቤ ያጽፉ ነበር። የሚያጽፉትም ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነበር።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ። በሶስትነት ባንድነት በክርስቶስ ያመነው ካሣ። መቼም ያገሬ ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል እኔ ካልወረድሁላችሁ ሸሽታችሁን አትተውም። ክርስቲያኑን ሁሉ ጉልበት አለኝ መስሎኝ ካረመኔ አገር አግብቼው ወንድ የሌላት ቆንጆ አለች ወንድ የነበራት ቆንጆ ነበረች። ትላንትማ የሞተባት ትኖራለች። ሽማግሌ ልጅ የሌለው ባልቴት ልጅ የሌላት እኔ የምጠራቸው ብዙ በከተማዬ አሉ። እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ፍቀዱዋቸው። ያረመኔ አገር ነውና ያገሬ ሰው ገብር ሥርዓት ግባ ብዬ አቸነፋችሁኝ። እኔን ወደውኝ የተከተሉኝ ሰዎች አድን እርሳስ ፈርተው ጥለውኝ ሸሹ።» ከሚለው ፅሁፍ ላይ ሲደርሱ እነ ደጃች ዓለሜ መጡ።

መልክተኞቹም ከናፒር የተላከውን ደብዳቤ ሰጡአቸው። ደብዳቤው የተጻፈው በእንግሊዝኛ ስለ ነበር በዎልድሜየር አስተርጓሚነት ይነበብ ጀመር።

ለግርማዊ ንጉሥ ቴዎድሮስ

ግርማዊነትዎ ትናንትና እንደ አንድ ጀግና ተዋግተዋል። ግን በኛ ጥበብና ኃይል ድል ሆነዋል። እንደ ገና ደግሞ በመሀከላችን ደም እንደማይፈስ እናምናለን። ግርማዊነትዎ የእንግሊዝን ንግሥት ከተቀበሉ በግርማዊነትዎ እጅ ያሉትን ኤሮፓውያን እስረኞችን በሙሉ በዛሬው ቀን በሰላም ከእንግሊዝ ጦር ሠፈር ድረሰንዲልኩዋቸው። ይህ ከሆነ ለግርማዊነትዎና ለመላው የግርማዊነትዎ ቤተሰቦች ሁሉ በክብር መልካም አያያዝ እንደሚያደርግ ቃል እገባለሁ።

ጠቅላይ አዛዥ

ሮበርት ናፒር

ቴዎድሮስ ደብዳቤው ሲነበብ በጥሞና አዳምጠው ንባቡ ሲያልቅ «........ያልገባኝ ነገር አለ። ይህ በክብር መልካም አያያዝ የሚለው ነገር ምንድነው» ብለው ጠየቁ። መልሰውም ራሳቸው «......እንደ እረኛ ተይዤ ነው ይዞታው? ወይስ ኧሪኡትን ከሽፍታ ሊያነጡልኝ ነው?......አውቀዋለሁ። በእስረኛነት አድርጎ እንዴት እንደሚይዘኝ ማለቱ ነው። እኔ ቴዎድሮስ! እኔ ነኝ እስረኛ የምሆነው? የማይሆን ነገር ነው።.......ሂዱ ከዚህ ከአጠገቤ» ብለው ሲጮሁ ሁሉም አምሳ ሜትር ያህል ርቀዋቸው ቆሙ።

አጤ ቴዎድሮስ ያፅፉት የነበረውን ደብዳቤ ለማስጨረስ ወደ ፀሐፊው ወደ አለቃ እንግዳ ዞር አሉ። በዚያው በተጀመረው ላይ ሲያስቀጥሉ «.......ብታሮጡአቸው ከሮጡ ሰዎች ጋር አልነበርሁም። ጌታ ነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ስታገል ውዬ ነው። ያገሬ ሰው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዞአል አስልሚል እያለ አስሩን ምክንያት ይሰጠኝ ነበረ። እኔ ከከፋሁበት እግዚአብሔር መልካም ይስጠው። እንደ ወደደ ይሁን። እግዚአብሔር ቢሰጠኝ ሁሉን ልገዛ አሳብ ነበረኝ እግዚአብሔር ቢነሳኝ ልሞት ሐሳቤ ይህ ነበር። ከተወለድሁኝ እስታሁን ወንድ እጄን ጨብጦት አያውቅም ነበረ። ሰዎች ሲሸሹ ተነስቼ ማራጋት ልማድ ነበረኝ። ጨለማ ከለከለኝ። ትላንትና በደስታ

ያደራችሁ ሰዎች እግዚአብሔር እንደኔ አያድርጋችሁ። እንኳን የሀበሻ ጠላቴን ኢየሩሳሌም ዘምቼ ቱርኮችን አስለቅቃለሁ መስሎኝ ነበር። ወንድ ያቀፈው ወንድ ተመልሶ አይታቀፍም።

ይህን ደብዳቤ አፅፈው ከጨረሱ በኋላ ምንም ሳይናገሩ ለብዙ ጊዜ ተቀምጠው እያሰቡ ቆዩ። ይህንንም ደብዳቤ ለናፒር እንዲያደርሱለት ለመልክተኞቹ ሰጧቸው። ጊዜው ቢመሽም መልክተኞቹ እጅ ነስተው ሔዱ።

አጤ ቴዎድሮስ በአጠገባቸው ያሉትን ሰዎች ራቅ በሉ ብለው ብቻቸውን እንደ ተቀመጡ ተክዘው ቆዩ። ተነስተውም። ግንባራቸውን መሬት እያስነኩ ሶስት ጊዜ ሰገዱ። ከስግደቱ ሶስት ጊዜ አማተቡና የታጠቁትን ባለ ሁለት አፈ ሙዝ የሆነውን ሽጉጣቸውን መዘው ራሳቸው ላይ ደገኑ።

ይህን ሽጉጥ መደገናቸውን ያየው ራቅ ብሎ የሚመለከተው ሠራዊት ተሯሩጦ ደርሶ ግማሹ ወገባቸውን ተጠምጥሞ ሲይዝ ሌላዎቹ ደግሞ ሽጉጥ የያዘውን እጃቸውን ይጐትቱ ጀመር። በዚህ ትንንቅ መሀል ሁሉም ባንድነት ወደቁ። አጤ ቴዎድሮስም ከያዟቸው ሰዎች ለማምለጥ ከመሬት ላይ ይከባለላሉ ጀመር። ከዚህም መተናነቅ መሐል የቴዎድሮስ ሽጉጥ አብርቆ ጥይቱ የቴዎድሮስን ጆሮ በመጠኑ አቆሰላቸው።

ቴዎድሮስ ወጥረው ከያዙዋቸው አሽከሮቻቸው ጋር መሬት ላይ እየተንከባለሉ ከቆዩ በኋላ ሽጉጣቸውን ሰጥተው ለቀቁዋቸው ሲነሱም «የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆን ነው» ብለው ተናገሩ። አጤ ቴዎድሮስ መጀመሪያውን ሽጉጣቸውን ራሳቸው ላይ ባነጣጠሩ ጊዜ ራሳቸውን ይገድሉ ነበር። በዚያች ደቂቃ ያልሞቱበት ምክንያት ወታደሮቻቸውን ተሯሩጠው ስለያዙዋቸው ብቻ አይደለም። ቴዎድሮስም የሽጉጡን ምላጭ ወዲያውኑ ሳይስቡት ቀርተው አይደለም። የዚያን ዘመኑ ባለ ሁለት አፈ ሙዝ ሽጉጥም ሆነ ጠመንጃ ለመተኮስ ሁለት ምላጭ (መሳቢያ) አለው። የቴዎድሮስ ሽጉት የተቀበለው በአንደኛው አፈሙዝ ሲሆን ሌላው አፈሙዝ ባዶ ነበር። ቴዎድሮስ ራሳቸውን ለመግደል የሳቡት ምላጭ የባለ ባዶውን እንጅ ጥይት ያለበትን አልነበረም። ስለዚህ የተሳበው አፈሙዝ ጥይት የሌለበት ስለነእብር ራሳቸውን ሳይገሉ ቀሩ። በትንንቁ ጊዜ ግን የሌላውን የጐረሰውን አፈ ሙዝ ምላጭ በመሳባቸው ጥይቱ ሊተኮስ ቻለ።

ሁሉም ነገር ሰላማዊ መሰለ። ቴዎድሮስም ቤተሰባቸውን ከመቅደላ ወደ ሰላምጌ አስጠሩ። አምስቱ ልጆቻቸው ቁባታቸው ወይዘሮ የተመኙ ሳይቀሩ ከእቴጌ ጥሩነሽ ጋር ሰላምጌ መጡ። በሜዳ ላይም ስብሰባ ተደረገ። ታላቁ ጀግና ራስ እንግዳ ደጃች አቦዬ ባሻ አብተው አለቃ እንግዳ ወርቅ አሳላፊ ከንቲባና ሌሎችም ሆነው ተሰበሰቡ። በተያዙበትም ምክር በእስረኝነት የተያዙትን እስረኞች እንግደላቸው የሚል አሳብ ቀረበ። አንደኛው ተናጋሪ «ሁሉንም ባንድነት ለመያዝ የሚችል ትልቅ የእንጨት አዳራሽ ቤት ስላለ ከዚያ አጉረን ከነሕይወታቸው እናቃጥላቸው» አለ። ሌላው ተናጋሪ ደግሞ «የለም። እጅና እግራቸውን እየቆራረጥን እንጣላቸውና እንግሊዞቹ ሲመጡ ያንሷቸው» አለ።

ባሻ አብተው በቀረበው ሐሳብ ተለዩ። «እነዚህ እስረኞቹ ቢገደሉ በአገሪቱ ላይ ከባድ መከራ ይደርሳል። ስለዚህ የሚያዋጣው ነገር እስረኞቹን በነፃ መልቀቅ ነው» አሉ። በሕዝቡ መሀል ቆመው ይህን የሕዝብ ፍርድ የሚያዳምጡት ፈረንጆች ደንግጠው የቴዎድሮስን የመጨረሻ ውሳኔ ይጠባበቁ ነበር። የደነገጡትን ፈረንጆች የተመለከቱት ቴዎድሮስም ወደ ፈረንጆቹ ዞር ብለው «አይዟችሁ ተቀመጡ። አትፍሩ። ሁላችሁንም እንገድላችሁ ተመክሬአለሁ። እናንተ ግን በኔ ላይ ምንም መጥፎ ነገር አላደረጋችሁም። ስለዚህ አልገድላችሁም። የኔ ሞት ግን ያለው በእጄ ላይ ነው ከኔ ቀድማችሁ እንድትሄዱ አልፈልግም። በእግዚአብሔር ዘንድ ታስጠይቁኛላችሁ። ሒዱ ወዳጆቻችሁን ሁሉ ይዛችሁ ወደ እንግሊዞች ሠፈር ሂዱ» ብለው አሰናበቷቸው።

የተሰናበቱትም ፈረንጆች ወደ ሠፈር ሔደው የመለቀቃቸውን ዜና በሠፈር ለነበሩት ነገሩ በፈረንጆቹም ላይ ሁለት ነገር ተለዋዋጭ በመሀኑ ምናልባት ተለቀናል ብለው ሲሔዱ ሊገድሉዋቸው የሚችሉ ተጠራጠሩ። በማንኛውም መንገድ ቢሆን ሒዱ የሚለውን ትእዛዝ ለመፈጸም ተሰባስበው ቴዎድሮስ ወዳሉበት አቅጣጫ ተጓዙ። ከዚህ በፊት ሳይሰናበቱኝ ሔዱ ብለው እንዳሠሩዋቸው ያውቁ ነበርና የሚቻል ቢሆን ቴዎድሮስን ለመሰናበት ሔዱ። ከንጉሱ ሠፈር ሲደርሱ ቴዎድሮስ ድንኳናቸው ውስጥ ያለመኖራቸውንና ወደ እንግሊዝ ጦር ሠፈር ከሚወስደው መንገድ ላይ እንደሚጠብቁዋቸው ነገሩዋቸው።

ፈረንጆቹ ተሰባስበው ሲመጡ ቴዎድሮስ አዩዋቸው። ወዲያውኑም «እባካችሁ ያን ጠላቴን ኮከብን (እስተርን) አታሳዩኝ» አሉ። ይህን የሰማው ዎልድሜየር ሮጦ ሔዶ ዶክተር እስተርንን እንዲደብቀው ለራሳም ነገረው። ከዚህ በኋላ ሌሎቹ ተሰባስበው ቴዎድሮስ ዘንድ ደረሱ። ቴዎድሮስ ሃያ ያህል ከሚሆኑ ሰዎች ጋር ቆመው አገኙዋቸው።

አጤ ቴዎድሮስ ራሳምን ወደ አጠገባቸው ጠሩና «ደህና ያግባህ። ወዳጄ ዳግመኛ በሕይወት አንተያይም። ከሞት በኋላ እንገናኝ ይሆናል። እንደሌሎቹ ወዳጆቼ ሁሉ አንተንም አምንሃለሁ።......ከእንግዲህ ወዲያ የምትሰማው መሞቴን ወይም መመንኮሴን ነው።» አሉትና ቀና በልው የጀምበርዋን ሁኔታ ተመለከቱ።

ቴዎድሮስ ፀሐይዋ ልትጠልቅ ማሽቆልቆዋን ካዩ በኋላ «ወደ እናንተ ሠፈር አሁን ለመሔድ ያልመሸ ይመስልሃል? አሁኑኑ ትሔዱ ወይስ ለሊቱን ከኔ ጋር አድራችሁ ጧት በማለዳ ወደ ሰዎቻችሁ ልላካችሁ?» ብለው ራሳምን ጠየቁት። ራሳምም «ጃንሆይ። እርስዎስ ደስ እንደሚልዎት ይሁን» አላቸው። ቴዎድሮስም «መልካም። አሁኑኑ ብትሔዱ ይሻላል። ግን አንድ ጊዜ ቁጭ በልና ከመሔድህ በፊት ጥቂት እንጫወት» አሉት። ሁለቱም አብረው ተቀመጡ። «ታውቃለህ አቶ ራሳም። እኔና አንተ ሁልጊዜ በመልካም ሁኔታ ላይ ነበርን። የልብህን አክብሮት አለኝ። ባንተ ላይም መጥፎ ነገር ማድረጌ እውነት ነው። ያንንም ያደረግሁት በመጥፎ ሰዎች ግፊት ነው። አሁን ያለፈውን ማንሳት ምንም አይጠቅመንም። እኔ አሁን ያለፈውን ማንሳት ምንም አይጠቅመንም። እኔ የማምነው ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደተደረገ ነው። ያለፈውን ከአእምሮ እንድታጠፈው እፈልጋለሁ....... ራሴን እገድላለሁ ወይም እመነኩሳለሁ። አሁነ ንግዲህ በል ደህና ሁን። ከቻልክ ነገ መጥተህ እንድታየኝ» አሉት።

ራሳምም ስለ ደግነታቸው አመስግኖ «ከተቻለ መጥቼ ጃንሆይን አይዎታለሁ» ሲላችው ንግግሩን አቋረጡትና «እውን ነገ ትመጣለህ?» ብለው ጠየቁት። ራሳምም ሁሉም ነገር በጦር አዛዡ ውሳኔ የሚፈፀም መሆኑን ነግሮ ሁለቱም ከተቀመጠበት ተነሱ። ቴዎድሮስም የራሳምን እጅ ጨብጠው ይዘው

እንባ እየተናነቃቸው «በል ደህና ያግባህ። መሽቷልና እየገሰገሳችሁ ሒዱ» አሉት።

ራሳም ከቴዎድሮስ ተሰናብቶ እጃቸውን ስሞ ሲለያቸው ሌሎቹ ፈረንጆች ካሜሮንን ጨምሮ ከሩቅ ከመንገድ ላይ ቆመው ይጠብቁት ነበር። ራሳምም እየተጠራጠረ አከሁን አሁን በኋላዬ አስተኩሰው ገደሉኝ እያለ ወደ ፊቱ ሔደ። ጥቂት እንደሔደ ቆም ብሎ ወደ ኋላው መለስ አለና «ጃንሆይ ስለርኅራሄዎ አመሰግንዎታለሁ። ብለህ ብትሔድ ይሻልሃል» አሉት። ራሳም እጅ ነስቶ ቀጥታ ተጓዘ አሁን ጥቂት እንደሔደ ቆም አለና ዞር ብሎ ወደ ቴዎድሮስ አየ አጤ ቴዎድሮስም ጠመንጃ በያዙ ሰዎች እንደታጀቡ ናቸው። እሳቸውም ሁለት ጐራሽ ሽጉጣቸውን እያወዛወዙ ቆመዋል። የራሳምን መቆም እንዳዩ እንዲሔድ በጃቸው ምልክት ሰጡት። እሱም መንገዱን ቀጥሎ ዞር እያለ ሲያይ ጓደኞቹ ቁልቁለቱን እየወረዱ ሲመጡ አየ።

በዚህ ጊዜ የተለቀቁት ወይም የሔዱት እስረኞች በሙሉ አይደሉም። ሆኖም እነኝህ በደጃች ዓለሜና ባቶ ሳሙኤል ሽኝነት ለመጀመሪያ ጊዜ የተለቀቁት እስረኞች ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ከእንግሊዞች ጦር ሠፈር ደረሱ። በዚያም ትልቅ የደስታ አቀባበል ተደረገላቸው። ዘጠኝ ኤሮፓውያን እስረኞችና አሁን የተለቀቁት ፈረንጆች ቤተሰቦች በቴዎድሮስ እጅ ቀርተው ስለነበረ ስለነሱ ሲመከር ታደረ።

በማግስቱ የፋሲካ በዓል ስለሆነ አጤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ጦር አንድ ሺህ የቀንድ ከብትናና 500 በጎችን በፀሐፊያቸው በአቶ ሳሙኤል በጀርመናዊው ቤንደር እጅ የሚከተለውን ደብዳቤ ጨምረው ላኩ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ። ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ከታላቂቷ ከእንግሊዝ ንግሥት ወዳጅ ከሎሌዎ ልኬብዎ አለሁ። ስምዎን እከሌ ብዬ እንዳልጠፍ ባላሰብሁት ጉዳይ ድንገት ተገናኘን። ትላንትና ለነአቶ ፍላፐ የሰደድሁት ደብዳቤ ከእናንተ ከወዳጆቼ ጋር በመጣላቴ ለነአቶ ፍላፐ የሰደድሁትን ደብዳቤ ከእናንተ ከወዳጆቼ ጋር በመጣላቴ ሁለተኛ የወጊያችሁን ያገራችሁን ሥራት በማየቴ ያገሬ ሰው ከትእዛዝ መውጣቱን አይቼ ብገለው ብቀጣው አልመሰለልኝ ቢል ቢነደኝ ብቀና በገዛ ጠመጃዬ እሞታለሁ ብዬ ሰይጣን አሳብ አሳደረብኝ። አይ ይህን ሁሉ ሠራዊት ዋቢ አልቢ ትቼው አልሒህድም እግዚአብሔር ይጣላኛል ብዬ አጣዳፊ

ከእርስዎ ሰደድሁት። እኔ ስሞት ሲድበለበል ቃሌ ሳይደርስዎ ይቀራል ብዬ ከሰደድሁልዎ በኋላ ግን የጠመንጃዬን ቃታ ከፍቼ ካፌ አፉሼ ብስበው ብስበው እምቢ አለኝ። ሰዎች ሩጠው መጥተው ካፌስ ሲመዙት ተተኩሶ እግዚአብሔር አትሙት ካለኝ ግን ብተወውና ልብዎ ይሻቅላል አቶ ርስአምን ሰድጀው አደርሁ። ዛሬ ትንሣኤ ነውና ፍሪዳ እንድሰድልዎ ይፍቀዱልኝ። ደብዳቤዎንም መልሼ የሰደድሁት በሰማይ እንጂ በምድር እንገናኛለን ኣላልሁም ነበር።

ፊታውራሪ ገብርዬን የኔን ወዳጅ ሳላስነሳው ያደርሁ ከሞትሁ (እኔንም) አብረው ይቀበሩን ብዬ ነበር። ከዋልሁ ግን (ልቅበረው) ይፍቀዱልኝ።.......

ይህ እውነተኛው ደብዳቤ ወደ መጨረሻው ገደማ ፅሁፍ የጠፋ ስለሆነ የማይነበብ ነው። በቅንፍ ውስጥ ሆኖ ከሥሩ መሰመር ያደረግሁበት ከደብዳቤው ላይ ይመስላሉ ብዬ ያነበብኳቸው ናቸው። ከውጭ ቋንቋ ትርጉም እንደሚታወቀው ግን የደብዳቤው መጨረሻ ኤሮፓውያኑን መለቀቃቸውን የጅ ባለሙያዎች እንዲላኩላቸው መጠየቃቸውን የሚገልጽ ነው።

ደብዳቤውን ይዘው የሔዱት መልክተኞች ከናፒር ዘንድ ቀርበው አቶ ሳሙኤል ወደ አረብኛ ራሳም ደግሞ አረብኛውን ወደ እንግሊዝኛ እየተረጐሙ ለናፒር ተነበበ። ናፒርም በራሳም አስተርጓሚነት በቃሉ ለአቶ ሳሙኤል የከብቶቹን ስጦታ መቀበሉን ነግሮ በቴዎድሮስ እጅ የቀሩትን እስረኞችና የሁሉም ቤተሰቦች እንዲላኩለት የሚለውን መልእክት እንዲያደርስ ቤንደርን ፍላንድ፥ ማየርን፥ ሳልሙለርን፥ እና ዎልድሜየርን ቤተሰቦቻቸውን እንዲያመጡ አቶ ሳሙኤል ከአቶ ሳሙኤል ጋር ላካቸው።

እነ አቶ ሳሙኤል ተመልሰው ሥላሴ ከነበሩት ከአጤ ቴዎድሮስ ዘንድ እንደደረሱ ቴዎድሮስ ቃል «ሥጦታውን ተቀበለ ወይስ አልተቀበሉም? » ብለው ጠየቁ። አቶ ሳሙኤልም እጅ ነስተው «የእንግሊዙ ራስ የላኩት መልክት ስጦታዎን ተቀብያለሁ። ድሩን እግዚአብሔር ይክፈልዎት ብለዋል» አሉ። ቴዎድሮስም ሰላም በመውረዱ ደስ አላቸው። ወዲያውም የቀሩት ፈረንጆችና የሌሎችም ሚስቶች ልጆች ሁሉ ከነጓዛቸው ጭምር እንዲሔዱ ፈቀዱላቸው።

የፈረንጆቹ ጓዝና ቤተሰብ ተጠቃሎ ለመሔድ ወጣ። ዎልድሜየር ሊሰናበታቸው ንጉሡ ሔደ። ቴዎድሮስም ወልድሜየርን ሲያዩት እንባቸው አቅርሮ «በል ደህና ያግባህ። ወዳጄ ነህ። ቤልን እንደምወደው ነበር አንተን የምወድህ» ብለው አሰናበቱት። እነኝህም ለመጨረሻ ጊዜ የተለቀቁት ኤሮፓውያን ከተስያት በኋላ በ9 ሰዓት ከእንግሊዞች ጦር ሠፈር ደረሱ። በጠቅላላው ከቴዎድሮስ እጅ የተለቀቁት እስረኞችና ቤተሰቦቻቸው 67 ናቸው። እነሱም ሲዘረዝሩ እንደሚከተለው ነበር ብዛታቸው።


| | | |
|---|---|---|
| ካሜሮን ከፖርቱጋላዊ ሠራተኛው ጋር | | 2 |
| ራሳም ከህንድ ፖርቱጋላዊና ከሁለት ሕንዳዊ አሽከሮችጋር | | 4 |
| ዶክተር ብላንክ ከሁለት ፖርቱጋላዊ አሽከሮች ጋር | | 3 |
| ሙቶ አለቃ ሪዲውክስ | | 1 |
| ቄስ ሮዜንታል ከሚስቱና ከልጁ ጋር | | 3 |
| ቄስ እስተርን | 1 | |
| ኪራንስ | 1 | |
| ዳቪድ ፔትሮ ከክልስ ልጁ ጋር | | 2 |
| ሪቻርድ ማክ ኪልቪ | | 1 |
| ፍላድ ከሚስቱና ከሶስት ልጆቹ ጋር | 5 | |
| ቤንደር ከሚስቱና ከሶስት ልጆቹ ጋር | | 5 |
| የሚች የኬንዚሊን ሚስት | 1 | |
| ዎልድሜየር ከሚስትና ከልጁ ጋር | 3 | |
| አሊጋዝ ቤል | 1 | |
| ሜየር ከሚስቱና ከሶስት ልጆቹ ጋር | 5 | |
| ሳልሙለር ከሚስቱና ከልጁ ጋር | 3 | |
| ወይዘሪት ሉስያ ቤል | | 1 |
| ሞርዝ ሐል ከሚስቱና ከሁለት ልጆቹ ጋር | 4 | |
| ቡርጋውድ ከሚስቱና ከአምስት ልጆቹ ጋር | 7 | |
| ዛንደር ከሚስቱና ከአራት ልጆቹ ጋር | | 6 |
| ዶክተር ቪመፐር ከሴትና ወንድ ልጆቹ ጋር | 3 | |

| | |
|---|---|
| ማክረር | 1 |
| ብራንዲስ | 1 |
| እስቴይገር | 1 |
| ቢለር | 1 |
| ኢስለር | 1 |

አጤ ቴዎድሮስ እስረኞቹን ካሰናበቱ በኋላ ከአንድ ትልቅ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው በሁለት እጆቻቸው ራሳቸውን ተደግፈው ሲተክዙ ቆዩ። በአጠገባቸው የነበሩት ራስ እንግዳ ቀረብ ብለው «ጃንሆይ። ለምን ያዝናሉ? እነዚህን ነጮ መልሰን እናምጣና ገድለናቸው እንሽሽ። ወይም ተዋግተን እንሙት» አሏቸው። አጤ ቴዎድሮስም በቁጣ «አንተ አህያ። ባልፈው ሁለት ቀን ውስጥ ያስፈጀሁት ሰው አይበቃምን። እነዚህን ነጮች አንድገድልና አበሻን በደም እንዳጥባት ነው የምትፈልገው?» አሏቸው። ማታውኑ ደግሞ በሰው ገዳይነታቸው የታወቁት አጋፋሪ መሸሻ ከቴዎድሮስ ዘንድ ቀርበው «የእንግሊዙ ራስ የላኩላቸውን ከበቶች ተቀበሉ የተባለው በውሸት ነው። ከሠፈራቸው እንኳን እንዳይገቡ ብሎ ከሠፈር ውጭ ያስጠብቁዋቸዋል።» ብለው ሲናገሩ ቴዎድሮስ የበለጠ ተበሳጩ። ተናደዱ። «እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉትን አግኝተዋል። አሁን የሚፈልጉት እኔን ለመግደል ነው እንጅ» አሉ።

ቴዎድሮስ እንደተናደዱ ወደ ሰላምጌ ሔዱ። ከሰላምጌም መሬት ላይ ቁጭ ሲሉ ዙርያቸውን ጦር ተተክሎ ሽማ ተጋረደላቸው። እዚያም ሆነው «የምትወዱኝ ጦረኞች ተዘጋጁ። ሁሉን ነገር ትታችሁ መሣሪያችሁን ብቻ ይዛችሁ ተከተሉኝ። ሌላ ቤት የምንፈልግበት ጊዜው ደረሰ» ብለው ተናገሩ። ከተራራው ላይም ወርደው ለማምለጥ ቢያስቡም የተራራው ዙርያ በሙሉ በወሎ ኦሮሞዎች ስለተከበበ ፈፅሞ የማያዋጣ ሆነ። ወታደሩም አብዛኛው እየከዳቸው ሔደ። ከጦር አለቆቻቸውም አንዳንዶቹ ቴዎድሮስ እንደገና እዋጋለሁ ወይም አመልጣለሁ ቡሉ እጃቸውን ይዘው ለእንግሊዝ ጦር ለመስጠት ተማከሩባቸው። ግን እጃቸን የሚይዘው ደፋሩ ማነው? ከሰላምጌ ወደ መቅደላ አፋፍ ሲወጡም የተከተሏቸው አራት የጦር አለቆችና ጥቂት ወታደሮ ብቻ ነበሩ። ቴዎድሮስ መቅደላ አፋር ወጥተው በዚያ ያለውን

ወታደራቸውን ሲያዘጋጁ አመሹ። እንደገናም ወደ ሥላሴ ወርደው በዚያም ያላቸውን ወታደሮች ሰብስበው «እንደገና አንድ ጊዜ ከእንግሊዝ ወታደር እየከዳ የሥላሴን ቁልቁለት ይወርድ ጀመር። ጥቂት ወታደሮች ብቻ በአሳባቸው ተስማምተው ከአጠገባቸው ቀሩ።



የመቅደላ ሠፈር (መንደር)

ሚያዝያ 6 ቀን ጧት 3 ሰዓት ገደማ ፀሐይዋ ዙርያዋን በጥቁር ክበብ ተከባ አዩና «ይህ ነገር የደም መፍሰስ ምልክት ነው» ብለው ተናገሩ። በዚህ ጊዜም ቴዎድሮስ ከመቅደላ ተራራ አምልጠው ለመውጣት አስበው ነበር። ነገር ግን እየከዱዋቸው ወደ እንግሊዞች ጦር የገቡት የጦር አለቆቻቸው ቴዎድሮስን አምልጠው ለመጥፋት ማሰባቸውን ለእንግሊዞች ስለተናገሩ እንግሊዞች የወሎን አጋምሽ የምትገዛው የወርቂትን የጦር አለቆች ሰብስበው ቴዎድሮስን በሕይወት ወይም ሬሳቸውንም ቢሆን ላመጣ ሰው ታላቅ ሽልማት

እንደሚሸለም አወጁ። ቴዎድሮስም ከአምባቸው አምልጠው ለመጥፋት ማሰባቸውም ተነገረ።

ከዚህ በኋላ የፋሲካ ሰኞ ዕለት የእንግሊዝ ብርጌድ ጦር ወደ ፉላና ሰላምጌ ተላከ። ቴዎድሮስም መቅደላ አፋፍ ላይ እንደ ሆኑ የእንግሊዞች ጦር ሲመጣ ተመለከቱ። ከዚያም ከፈረሳቸው ላይ ወጥተው በመቅደላ ተራራ ሜዳ ላይ እየጋለቡ ሽጉጣቸውን ወደ ሰማይ ይተኩሱ ጀመር። ከጥቂት ጊዜም በኋላ ከፈረሳቸው ወርደው እንግሊዞች ወደ መቅደላ አምባ እንዳይገቡ ይቋቲትን በር በታላቅ ድንጋይ ያዘጉ ጀመር። ውጊያው ከተስያት በኋላ ተጀመረ። የእንሊዞች መድፍ የመቅደላን ተራራ ይደበድቡ ጀመር። በኮሎኔል ፊልድ የሚመራው እስረኛው የእግረኛው ብርጌድ ፋላ ኮረብታን ያዘ። ሌላው ብርጌድ ደግሞ ሥላሴ ኮረብታን ያዘ። በሁለቱም አምባዎች ላይ ያለው ሠራዊት ጠመንጃቸውንም ሆነ ጦሩን ጋሻውንም ሆነ ጐራዴውን ከመሬት እያስቀመጠ የእንግሊዝን ጦር በሰላም ተቀበለ። ሴቶችም ዕቃቸውንም እያዘጋጁና እያዘሉ ወደ አሮጌ ይጓዙ ጀመር።

በዚህ እምህል ነገረኛ እወደድ ባይ ሰው ከናፒር ዘንድ ቀርቦ «ቴዎድሮስ አመለጡ» ብሎ ተናገረ። ናፒርም ተናደደ። ማህደረ ቃል የሚባለው ኢትዮጵያዊ የቴዎድሮስን የማምለጥና ያለማምለጥን ሁኔታ አጣርቶ ቴዎድሮስ ያለማምለጣቸውን ለሙዚንጀር ነገረው። ሙዚንጀርም ለናፒር ተናገረ። ከዚህ በኋላ ናፒር የመቅደላ ተራራ በኃይል እንዲደበደቡ አዘዘ። ከቋቲት በር አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀው የተጠመዱት መድፎችና ሞርታሮች ያለማቋረጥ ይተኮሱ ጀመር። የመቅደላ ሜዳ በሙሉ ይደበደብ ጀመር። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ አጠገብ የነበረ ጋሻዣግሬአቸው አቶ አማረ «ጃንሆይ። እጃችንን እንስጥ» ቢያማክራቸው «የለም በሰዎች እጅ ከመውደቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻላል» አሉት።

ከእርስዎ ሳንለይ አብረን እንሞታለን ብለው ከቴዎድሮስ አጠገብ ያልተለዩት አማካሪያቸውና ጓደኛቸው ራስ እንግዳ የራስ እንግዳ ወንድም የመድፈኞች አለቃ የሆኑት ራስ ፀጋ ቢትወደድ በቀለ መድፈኛው የአባ መርሳ ልጅ አቶ እንግዳ ወርቅ የጐጃሙ ራስ መብረቁ ባሻ ቢሰውር የቋራው ቢትወደድ ዳማሽ ግምጃ ቤታቸው ቢትወደድ ባህሪ አሳላፊ ከንቲባ ደጃች

አልዩ ደጃች መሸሻ የመቅደላው ገዥ ቢትወደድ አሰኔ ጋሻ ዣግሬአቸው አቶ አማኒ እና አሽከራቸው ወልደ ጋብር ብቻ ነበሩ።



ማህደረ ቃል (በኢትዮጵያና በኤሮፓ አለባበስ)

አጤ ቴዎድሮስ ውብ የሆነ የወርቅ ዘቦ ዝምዝም ያጌጠ ሐር ልብስ ለብሰዋል። በላዩም የአንበሳ ለምድ ደርበዋል። በወገባቸው ጐራዴና ሽጉጥ ታጥቀዋል። ካንድ ድንጋይ ላይም ቁጭ ብለው የእንግሊዝን ጦር ሁኔታ በመነጥር ይመለከታሉ። አንለይዎትም ያሏቸውም ሰዎች ዙሪያቸውን ከበው ቆመዋል። በዚህ ሁኔታ እንዳሉ አንድ የመድፍ ጥይት በቴዎድሮስ ራስ በኩል ለጥቂት ስቷቸው አልፎ ሁለት ላሞችን ገደለ። ይህ ከሆነ በኋላ ተኩሱ የተተኮሰው በልብሳቸው ምልክት መሆኑ ታውቆ ቴዎድሮስ ልብሳቸውን ለውጠው ተራ ልስብ ለበሱ። ከጥጥ የተሠራ ሱሪያቸውን ታጥቀው ሐር ሸሚዝ ለበሱ። ነጭ ሸማም ደረቡበት በወገባቸውም ሽጉጣቸውን ታጠቁ። እንዲህ ከለበሱ በኋላ እንደገና በመነጥራቸው የጦሩን ሁኔታ ይመለከቱ ጀመር። እሳትና ጭስ እያሳየ እየሚመጣባቸውን ጥይት ራሳቸውን ዝቅ እያደረጉ ያሳልፉት ጀመር። ከታማኝ ወዳጆቻቸው አጠገባቸው ካሉት መሀልም እየተመቱና እየሞቱ ይወድቁ ጀመር። ታማኞቻቸው አማካሪያቸው ራስ እንግዳ ከወንድማቸው ጋር በአንዲት ጥይት ሞቱ። ተኩሱ እየበረከተ ሲሔድም

አንዳንድ ታማኞቻቸው እየሸሹ ሔዱ። በቴዎድሮስ አጠገብ ቢትወደድ አሰኔ እንግዳ፥ ወርቅና ኢጋፋሪ መሸሻ ብቻ ቀሩ።



## መቅደላ ሲቃጠል

አጤ ቴዎድሮስ በቋቲት በር ያለውን ወታደር ለማበረታት ወደ ቋቲት በር ወረዱ። በዚያም አንድም ሰው አላገኙም። ለመቅደላ ተከላካይነት በበሩ የቀሩትንም ወታደሮች አሥር ሰዎች ያህል ብቻ መሆናቸውን አዩ። በዚያም እንዳሉ ባሻ እንግዳአን ጋሻ ሻግሬአቸው አማኒ ከእንግሊዝ ጦር በተተኮሰ ጥይት ተገደሉ። ጠመንጃ ያዥያቸው ወልደጋብር ጠመንጃቸውን አቀባብሎ ለአጤ ቴዎድሮስ ሰጣቸው። እሳቸውና የቀሩት ታማኞቻቸው በቋቲት በር ሳንቃ ቀዳዳ እያሾለኩ ይተኩሱ ጀመር። ተስፋ የሌለው አተኳኮስ ነበር። ስለዚህ ሁሉም ያን ቦታ ትተው ወደ ላይ ወደ መቅደላ ወጡ።

መጠነኛ ከፍታ ያላትን ገደል ወጥተው 30 ሜትር ያህል በሜዳው ላይ እንደሔዱ ቴዎድሮስ ቆም አሉና ከታማኛቸው ከወልደጋብር በስተቀር ሌላዎቹ «.......ሽሹ። ቃል ከገባችሁልኝ መሀላ ፈትቻችኋለሁ። እኔ ግን በጠላቴን እጅ ፈፅሜ አልወድቅም» አሏቸው። እነኻያም እያለቀሱና እያዘኑ ተለይተዋቸው ሔዱ። እንደ ሔዱላቸውም ወደ ወልደ ጋብር ዞር ብለው «አለቀ። በእነሱ እጅ ከመውደቅ ራሴን እገድላለሁ» አሉትና ሽጉጣቸውን አፋቸው ውስጥ ከተቱና ተኮሱ። ወደቁ። ጥይቷም በላንቃቸው አልፋ በማጅራታቸው በኩል ወጣች። ይህ የሆነው ወይም ቴዎድሮስ ራሳቸውን የገደሉት ከቀኑ 10 ሰዓት ከ10 ደቂቃ ሲሆን ነው።

ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ የእንግሊዝ ጦር መቅደላ ኮረብታ ላይ ወጥቶ ነበር። በድንጋይ የተዘጋው ቋቲት በር ባንድ መድፍ ጥይት ብትንትኗ ወጥቶ በሩ ተከፈተ። የእንግሊዝ ጦርም ግማሹ በመሰላል ሌላውም በገመድ እየተጐተተ የመቅደላን ገደል ወጣው። ውጊያው የተጀመረው ከቀኑ በ8 ሰዓት ሲሆን በ10 ሰዓት የእንግሊዝ ጦር መቅደላ አፋፍ ገባ። ኃይለኛ ዝናብ ይዘንብ ነበርና ቴዎድሮስ ከሞቱ ከአምስት ደቂቃ በኋላ መላው መቅደላ ተራራ በእንግሊዞች ጦር እጅ ሆነ።

ቴዎድሮስ ራሳቸውን ገድለው እንደወደቁ አሽከራቸው ወልደ ጋብር ቀበቶአቸውንና ሸማቸውን ይዞ ሔደ። ከተሰባሰቡት 15 ያህል ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ሸሽተው እየሮጡ ሊያመልጡ ሲሉ የተራራው ዙሪያ በኦሮሞዎች ስለተያዘ መውጫ አጥተው ዋሻ ውስጥ ተደብቀው ተቀመጡ። በማግስቱ ወደ መቅደላ ተመለሱ።

ቴዎድሮስ ራሳቸውን የገደሉበት ጥይት ስትጮህ የሰሙ ሁለት የአይርሽ ወታደር የተኩስ ድምፅ ወደሰሙበት ቦታ ሔዱ። ከዚያም ሲደርሱ ቴዎድሮስ በጀርባቸው ተንጋለው ወድቀው አገኙዋቸው። ቴዎድሮስ ሕይወታቸ ገና ፈፅማ አላለፈችም ነበር። እነኻያም የአይርሽ ወታደሮች የቴዎድሮስን ሽጉጣቸውን ከወሰዱ በኋላ ከወርቅ የተሠራው የአንገት ሀብላቸውንና የጣት ቀለበታቸውንም ሰርቀው ወሰዱባቸው። እግራቸውንም እየጐተቱ ካንገላቷቸው ከጥቂት ሴከንዶች በኋላ ሕይወታቸው ጨርሳ አለፈች። ይህ የተወሰደባቸው የቴዎድሮስ የአንገት ሀብል ዛሬ በእንግሊዝ አገር ባንድ ወታደር

ቤተሰብ እጅ ሲገኝ የጣት ቀለበታቸው ግን በእንግሊዝ አገር ኮልጌት ቸርች ላንካስተር ተብሎ በሚጠራው ሥፍራ ይገኛል።



የቴዎድሮስ ሞት (ራሳቸውን ሲገሉ)

በወቅቱ በሥፍራው የነበረው አሜሪካዊው ጋዜጠኛ «.......ራቅ ብዬ ስመለከት ብዙ አፊሰሮች እንግሊዛውያን ሲቪሎች በደም የተበከለውን የቴዎድሮስን ሸሚዝ ለኔ ይገባል በማለት ሲጓተቱትና ሲጣሉበት አየሁ......» ይላል። ይህ በደም የተለወሰው የቴዎድሮስ ሸሚዝ ዛሬ በእንግሊዝ አገር ባንክ ፊልድ ሙዚየም ውስጥ ይገኛል። ያው ጋዜጠኛ..... «ሬሳቸው ተዘርዝሮ ጠጉራቸው ተሸልቶ ልብሳቸው ተገፎ በከፊል እርቃነ ሥጋቸውን አየኋቸው......» ሲል ጽፏል። ይህ ተሸለተ የተባለው ጠጉራቸው ዛሬ ሙዚየም ኦፍማን ካይንድ ተብሎ በሚጠራው ለንደን ሙዚየም ውስጥ ተቀምጦ ለሕዝብ ይታያል።

ቻርልስ እንታቪሌይ መቅደላ ተራራ ላይ እንደወጣ አንድ ወታደር እየሮጠ ሄዶ የንጉሡ ሬሳ ወድቆ መገኘቱን ነገረው። እሱም ሬሳቸውን በቃሬዛ ላይ አድርጐ እስረኞቹ የነበሩበትና ቴዎድሮስን በሕይወታቸው ዘመን የሚያውቋቸው አይተው የቴዎድሮስ ሬሳ መሆኑን እንዲያረጋግጡ አደረገ። ከእስረኞቹ መሀል አንዱ የቴዎድሮስን እጅ አንስቶ የተሰበረች ጣታቸውን አየና የቴዎድሮስ ሬሳ መሆኑን አረጋገጠ።

ጣታቸው የተሰበረችው በወጣትነታቸው ጊዜ በጦርነት ላይ በጥይት ተመትተው ነው። ቻርልስም የቴዎድሮስ ሬሳ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ከሬሳው አጠገብ ዞር ሲል በዚያ የነበረው ሕዝብ ሁሉ እያወካና እየጮኸ የቴዎድሮስን ሬሳ ደበደበ። ፍፁም ራቁት እስቲሆን ድረስም ልብሳቸውን ሁሉ ቀዳደደው ቴዎድሮስም በተወለዱ በ50 ዓመታቸው በነገሱ በ15ኛው የግዛት ዘመናቸው ሞቱ ማርከሃም ሲተች «.......አስፈሪው ጊዜ አልፏልና ያ አስፈሪው ሰው እንደሞተ ቀበሮ ሆነ.......» ይላል።

የቴዎድሮስ ሬሳ ወደ ኢጣሊያዊው ወደ ዴቪድ ፒየትሮ ጐጆ ተወሰደ። ራሳም ያ የተናገሩት ሬሳዬ አጠገብ ሆነህ አትቅበሩት ይቀምጥ ትለኛለህ ያሉት ትዝ አለውና ሬሳቸውን አሰልብሶ በአልጋ አስደርጎ እንዲወሰድ አደረገ።

በማግስቱ የእንግሊዝ መልዕክተኞች ወደ እቴጌ ጥሩ ወርቅ ዘንድ ሔደው የቴዎድሮስን ሬሳ ታላቅ ክብር ተደርጐለት በእንግሊዞች እጅ ይቀበር? ወይስ ለእርስዎ ሰጥተን እንደ አገራችሁ ባህል ትቀብሩ? ብለው ጠየቋቸው። ንግሥቲቱም በአገሬ ቄሶች በፀጥታ ቢቀበር ይሻላል አሉ። እቴጌይቱ ሬሳው

እንዲሰጣቸው በመጠየቃቸው ላምስዴን ዶክተር ብላንክ እና ከኢትዮጵያውያኖች በኩል አቶ ሣሙኤል ባሉበት እንዲመረመር እንዲሰጣቸው ታዘዘ።

የቴዎድሮስ ሬሳ ይመርመር የተባለበት ምክንያት «ራሳቸውን ገደሉ? ወይስ ሌላ ሰው ገደላቸው?» ለሚለው መጠይቅ መልስ እንዲገኝ ነበር። መርማሪዎቹ በአፋቸው የገባችው ጥይት በማጅራታቸው በኩል መውጣቷን ጥይቱም የሸጉጡን አፈ ሙዝ አፋቸው ውስጥ ከትተው በመሆኑ አፋቸው ውስጡ በሙሉ በባሩዱ ጭስ በመጥቆሩ ተረጋገጠ። ቴዎድሮስ የሞቱት ራሳቸውን ገድለው እንጂ ሌላ ሰው እንዳልገደላቸው ከተረጋገጠ በኋላ ሬሳቸው ተሰጠ።



## አጤ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ገድለው እንደወደቁ

ሬሳቸው በመጀመሪያ በጥሩ የጥጥ ልብስ ተጠቀለለ። በዚያ ላይ ወርቀ ዘቦ ክር የተዘመዘመ ሐር ለበሰ። በመጨረሻ ውብ የሆነ ባለ አበባ ተደረገበት። መቃብራቸው ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከገረገራ (ከግቢ) ውጭ ተቆፈረ። መሬቱ ጠጣር ስለነበረም ቁፋሮው ብዙ ጊዜ ቆየ። በቀብሩም ሥርዓት ላይ ማንም ሰው መካፈል እንደሚችል መፈቀዱን ለፋፊ እየዞረ ተናገረ። ከጥቂት ሰዎች በስተቀር ግን የመጣ አልነበረም። ምናልባት ጥቂት ቀደም ብሎ ነጐድጓዳማ ዝናብ ዘንቦ ስለነበረ ቀባሪ በብዛት ያልወጣው በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችል ይሆናል። ምናልባትም በጥላቻ ወይም ደግሞ በፍራቻ ሊሆንም ይችላል።



# የቴዎድሮስ ሬሳ ያረፈበት ቤት በዘብ ሲጠበቅ

ሬሳቸው ባንድ አሮጌ የጠፍር አልጋ ላይ ተደረገ። ሬሳቸው እስቲቀበር ድረስ ለፀጥታው ጥበቃ የታዘዘው ከ33ኛው ብርጌድ የተውጣጡ ወታደሮች መጡ። ከዚያም በኋላ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥም ተከተተ። በላዩም ላይ ድንጋይ ተረበረበ። ከድንጋዩም በላይ ድቅድቅ እየተደቀደቀ ተደረገበት። አቀባበሩ ፍትሐትም ሆነ ደንበኛ የቀብር ሥርዓት አልተፈፀመበትም። ጥቂት ቄሶች ብቻ መጠነኛ ፀሎት አደረሱ። ቀብሩ እንደተፈፀመም ታላቅ ነጐድጓዳማ ዝናብ ዘነበ።

እንግሊዞች መቅደላን ከያዙ በኋላ በዚያ አምባ የታሠሩትን እስረኞች በሙሉ እየፈቱ ለቀቁዋቸው። ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

15 ዓመታት የታሠሩ

የጐጃሙ ደጃች ብሩ ጐሹ ከሁለት ወንድሞቻቸው ጋር።

14 ዓመት የታሠሩ

የየጁው ባላባት ፋሪስ አሊ

የደጃች ውቤ ልጅ ካሣ ውቤ

የኢዱ ልጅ ዳንጉል።

13 ዓመት የታሠሩ

የንደርታው ባልገዳ አርአያ

10 ዓመት የታሠሩ

የሜጫው ባላባት ባሻ ኃይሌ

7 ዓመት የታሠሩ

የአጋሜው ሹም አጋሜ አረጋዊ

5 ዓመት የታሠሩ

የሐራማቱ ደጃዝማች ሣህሉ

የሐራማቱ አዛዥ ንጉሤ

የጠራው ባልገዳ ሙሮ

የኢዱ ሣህሌ

የሰለዋው ሹም ስለዋ ሕዝቅያስ

4 ዓመት የታሠሩ

የዋጉ የዋግሹም ተፈሪ

የበለሳው ጐሸን ወንድየ

3 ዓመት የታሠሩ

የሰሜኑ አካሉ ደረሶ

አዛዥ ጋረድ

የሸዋው ራስ ልቤ

2 ዓመት የታሠሩ

የሸዋው ገርማሜ

የሸዋው ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ

1 ዓመት የታሠሩ

የበጌምድሩ ራስ ወልደ ማርያም

ራስ ገብሬ

ራስ ዋህድ ተድላ

ቢትወደድ ተድላ ከሁለት ወንድሞቻቸው ጋር

የበጌምድሩ አዛዥ ወንዴ

አዛዥ ገብረ ሥላሴ

አቶ ሠርጌ ደረሶ

የቋራው ባላባት ወሰን ይልማ

አቶ ወሰን ዳርዬ

የትግራዩ ጠለፋ እንግዳ ናቸው።

እነኚህ ለጊዜው እየተመዘገቡ የወጡት እንጂ ብዙዎች ሳይመዘገቡ በግርግሩ መሀል ወጥተዋል።

የአጤ ቴዎድሮስ የቀብር ሥነ ሥርዓት ከተፈፀመ በኋላ እንግሊዞች እቴጌ ጥሩወርቅ ከሚኖሩበት ቤት በራፍ ላይ ዘብ አቆሙ። ዘብ ያቆሙበት ምክንያት

ማንም ሰው ገብቶ እንዳሰድባቸው ወይም እንዳያጉላላቸው እንዲጠብቃቸው ነው። ሜርዌይዘር እቴጌ ጥሩወርቅ ካሉበት ድረስ ሔዶ ከቤታቸው ውጭ ተቀምጦ በአስተርጓሚው በአቶ ሳሙኤል አማካይነት እቴጌ ጥሩ ወርቅ ምን ሐሳብ እናላቸው ተጠየቁ። እቴጌይቱም ፍላጐታቸው ወደ ትውልድ አገራቸው ወደ ሰሜን ለመሔድ መሆኑን ነግረው ስለ ልጃቸው ስለ ዓለማየሁ ግን አባትዬው አጤ ቴዎድሮስ በመጨረሻ ጊዜ እንደተናገሩት ወደ እንግሊዝ አገር ይሂድ አሉ። ከዚህ በኋላ እቴጌይቱ ከልጃቸው ከዓለማየሁ ቴዎድሮስና የቴዎድሮስ ቁባት ከነበሩት ከወይዘሮ የተመኙ ጋር ወደ እንግሊዝ ጦር ሠፈር ወርደው በዚያ ቆይተው የእንግሊዝ ጦር በሚመለስበት ጊዜ እስተአገራቸው መንገድ ድረስ እንዲሸኛቸው ተወሰነ። እነሱም በዎልድሜየር አጃቢነት ወደ እንግሊዞች ጦር ሠፈር ተወሰዱ።

ሚያዝያ 16 ቀን ወደ ማታ ገደማ ከወሎ የኦሮሞ ባላባቶች አንደኛዋ ወይዘሮ ወርቂት መምጣታቸው በእንግሊዞች ሠፈር ተነገረ። እንግሊዞችም በክብር ተቀብለው ከሰር ሮበርት ናፒየር ጋር አገናኙዋቸው። ወይዘሮ ወርቂት ከሰር ሮበርት ናፔር ጋር ተገናኝተው በአስተርጓሚው ሲጨዋወቱ «..........የቻልነውን ያህል ከቴዎድሮስ ስንዋጋ ኖርን። ግን ኃያልነቱ እያለብን ብዙ ጊዜ ልንዋጋውና ልናሸንፈው አልቻልንም። ልጄን በጥሩ ሁኔታ አሳድገዋለሁ ብሎ ወስዶ ከሰው ልጅ ርህራሄ ውጭ በሆነ ሁኔታ ቆራርጦ መቅደላ ገደል ጣለው። አሁን እኔ የመጣሁት የጠላቴን የቴዎድሮስን መቃብርና ልጄ የተጣለበትን የመቅደላን ገደል ለማየት ነው........» ብለው ተናገሩ።

ሰር ሮበርት ናፒርም በሌላዋ የወሎ ኦሮሞ ባላባት በሆኑት በወይዘሮ መስተዋትና በእሳቸው መሀል ያለው ልዩነት ቀርቶ ሰላም እንዲመሠርቱ ቢጠይቋቸው «.......ሁለት ሰዎች ለመንገስ ሲተናነቁ በነሱ መሀል እንዴት ሰላም ሊኖር ይችላል? መስተዋት ከኔ ጋር ወዳጅ ለመሆን በእናንተ ፊት ዛሬውኑ ቃል ብትገባ ነገ ጠብዋን ትጀምራለች.......» አሉ። ይህን በሚነጋገሩበት ጊዜ የሰር ናፒር ወታደር ገብቶ የወይዘሮ መስተዋትን መምጣት ተናገረ። ናፒርም ለወይዘሮ ወርቂት ስጦታ ሰጥቶ ተሰነባበቱ። ወይዘሮ ወርቂት «ልጄን ገደለብኝ» ያሉት ምኒልክ ያመለጡ ጊዜ ወርቂት ምኒልክን በወሎ በኩል አሳልፈዋል በማለት ቴዎድሮስ ተናደው 24 የወሎ መኳንንትን ገደል እየጨመሩ ካስገደሉዋቸው መሀል አንዱ የወርቂት ልጅ ነበር።

በዚያን ጊዜ በቦታው የነበረው ማርከሃም ስለ ወይዘሮ ወርቂት ሲፅፍ «.......ጀግናይቱ ወርቂት ለብዙ ጊዜ በቴዎድሮስ ላይ አምጣ ቆይታለች። የነበራትም አንድ ልጅ ተገድሎባታል። አሁን አርጅታለች። ልጅም የላትም። የነበራትም ኃይል በአሁኑ ጊዜ በርዷል። የሚደጋግፋትም የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ብቻ ነው።.......ትውልዷ ከታላላቅ ባላባቶች ነው። ባልዋም አህመድ በሽር ከታላላቅ የወሎ ባላባቶች ዝርያ የሚወለድ ነው። በመጨረሻም አብዛኛው የወሎ ጋላ ሌላይቱን ባላባታቸውን ወይዘሮ መስተዋትን በመደገፍ ላይ ነው።....... ወርቂት ሁሉን ነገር የተወችው ልጅዋ ከሞተ በኋላ ነው........» ብሏል።

ሌላዋ የወሎ አሮሞ ባላባት ወይዘሮ መስተዋት ነበሩ። እሳቸውም ወደ እንግሊዞች ጦር ሠፈር የመጡት ከልጃቸው ከኢማም አህመድ ጋር ነው። ወይዘሮ መስተዋት የአህመድ በሽር አጐት የሊበን ሚስት ነበሩ። ባላቸው ሊበን ስለሞቱ መስተዋትም እንደ ወርቂት ሁሉ ዓለም በቃኝ ብለው ግዛታቸውን የሚያስተዳድረው ልጃቸው ኢማም አህመድ ነው። ወደ እንግሊዞች ጦር ሠፈር የመጡትም በጦር አዛዣቸው በአክበር አሊና በወታደሮች ታጅበው ነው። የመጡ ዕለትም የወይዘሮ ወርቂት ሠራዊት ከእንግሊዝ ጦር ሠፈር ለቆ እስቲወጣና እረፍትም ለማድረግ በአቅራቢያ አደሩ። በማግስቱ ሚያዝያ 17 ቀን ከእንግሊዞች ጦር ሠፈር ሲገቡ ለጄኔራል ናፒር «ታላቅዋ የወሎ ባላባት ከደላንታ መጡ» ብሎ ተነገረ።



ወርቂቱ (የወሎ ንግስት)

ወይዘሮ መስተዋት የሚኖሩት ከመቅደላ ተራራ 10 ኪሎ ሜትር ያህል ከሚርቅ ከደላንታ ጐን ከበሽሎ አጠገብ ሉጉድ ከሚባል ኮረብታ ላይ ነው እንግሊዞች ወደ መቅደላ በሚመጡበት ጊዜ ሁኔታውን በመፍራት ከሉጉድ ለቀው ሰወር ብለው ነበር። የእንግሊዞች ሁኔታ ካለቀ በኋላ አክበር አሊ ወይዘሮ መስተዋትን አፅናንቶና ጉዳዩን አስረድቶ ባያፅናናቸው ኖሮ ወይዘሮ መስተዋት ከእንግሊዞች ዘንድ አይደርሱም ነበር።

እንግሊዞች የመቅደላን ጦርነት ከመጀመራቸው በፊት አክበር አሊ ከእንግሊዞች ጋር ተወዳጅቷል ከእንግሊዞች ጋር ባደረገው ምክክርና በታዘዘው ትእዛዝ መሠረት ከወይዘሮ መስተዋት ዘንድ ሔዶ ሁሉንም ነገር አስረድቶ ወታደሮቻቸው ቃፊር በርንና የመቅደላን ዙርያ ቴዎድሮስ እንዳያመልጡ እንዲጠብቁ ያስደረገ አክበር አሊ ነው። ከመቅደላ ተራራ የሚወርድ ማንኛውም ሰው ወደ ኋላ እንዲመለስ እንጅ ተራራውን እንዳይወርድ የሚወርድ ወይም በኃይል የሚጠቀም ካለም በኃይል እንዲመለስ ትእዛዝ የሰጠ አክበር አሊ ነው። አጤ ቴዎድሮስ በመጨረሻው ሰዓት ከመቅደላ ባንደኛው በኩል ለማምለጥ ሞክረው በኃይል የመለሱዋቸው እነኝህ ጥብቅ ትእዛዝ የተቀበሉት የመስተዋት ሰዎች ናቸው። በኋላ ግን የታዘዙት የወይዘሮ መስተዋት ወታደሮች የታዘዙትን ትእዛዝ ትተው ዘረፋ ስለ ጀመሩ የአጤ ቴዎድሮስ ልጅ ደጃች መሸሻ ሳይቀሩ በቃፊር በር በኩል እየወጡ ሔዱ።

ወይዘሮ መስተዋት ወደ እንግሊዞች ጦር ሠፈር የመጡት በቴዎድሮስ ሞት በታም ሰለ ተደሰቱ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት ጭምር ነበር። ከናፒር ዘንድ ገብተው ይህንኑ ደስታቸውን ገለጡ። ናፒርም አጤ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ የተሳለውን ስዕላቸው ለወይዘሮ መስትዋት አሳይቶ «እኝህ አይደሉሞይ የምጠያቸው ቴዎድሮስ?» ብሎ ጠየቀ። ወይዘሮ መስተዋትም «እኔ እንዴት አውቀዋለሁ? ያየውስ የተጠጋውስ ማነው?» ብለው መለሱ።

ወይዘሮ መስተዋት በኢትዮጵያ ውስጥ በጦርኝነት ከታወቁት ሴቶች አንደኛዋ ናቸው። ወይዘሮ መስተዋት በአፍላነታቸው ዘመን እንደ ወንድ የጦር መሣሪያ እየያዙ ከወንዶች እኩል የሚዋጉ ሴት ነበሩ። ከአረጁ በኋላ እንኳ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክና የጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እምባቦ ላይ በተዋጉ ጊዜ ወይዘሮ መስተዋት ለንጉስ ምኒልክ ረድተው ጐጃሞችን

ወግተዋል። በዘመኑና በጦርነቱ የነበሩ የጐጃምና የሸዋ ሰዎች ሁሉ የወይዘሮ መስተዋትን ጀግንነትና ውጊያ አድንቀዋል።

እቴጌ ጥሩ ወርቅ ልዑል ዓለማየሁና ወይዘሮ የተመኙ እንግሊዞች ጦር ሠፈር ገብተው ጥቂት ከቆዩ በኋላ የእንግሊዝ ጦር መመለሻ ስለደረሰ የቴዎድሮስ ቤተሰቦችና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ከእንግሊዞች ጦር ጋር አብረው ለመጓዝ ተነሱ። ምንም ዓይነት ክብር ባልጐደለበት ጉዞ እየተጓዙ ዋድላ ሲደርሱ የተከዜን ወንዝ ሳያቋርጥ ሳንጠራ ላይ ወይዘሮ የተመኙ ተለይተው የተሰጣቸውን ስጦታ ይዘው ወደ ትልውድ አገራቸው ወደ የጁ ሔዱ።

ወይዘሮ የተመኙ አጤ ቴዎድሮስ ከነበሩዋቸው ቁባቶች ሁሉ የሚወዷቸው ሴት ነበሩ። ቴዎድሮስ የተመኙን የያዙት ገና እቴጌ ተዋበች ሳይሞቱ በፊት ጀምሮ ነው። የተዋበችን ሞተው ጥሩ ወርቅን ካገቡ በኋላ እቴጌ ጥሩወርቅ የቴዎድሮስን ቁባቶች ሁሉ ማየት እንደማይፈልጉ ነግረዋቸው አጤ ቴዎድሮስ ቁባቶቻቸውን ሁሉ ሲያባርሩ ወይዘሮ የተመኙን ግን አላባረሩም ነበር። ቴዎድሮስ በወይዘሮ የተመኙ ላይ የነበራቸው ፍቅር የተለየ ነበር። አጤ ቴዎድሮስ ራቅ ካለ ቦታ በሚሔዱበት ጊዜ ከሚስታቸው ይልቅ ለወይዘሮ የተመኙ የፍቅር ደብዳቤ ይፅፉላቸው ነበር። በደብዳቤያቸውም ላይ «እህቴ የእናቴ ልጅ አትባቢ አይዞሽ። በቅርቡ አይሻለሁ።........» እያሉ ይፅፉላቸው ነበር።

ራሳም እንደፃፈው «.......የተመኙ ቴዎድሮስ የሚወዷቸው እቴጌ ናቸው። ........ የአንድ የየጁ ጋላ ሚስት ነበረች። ውብ ነበረችና ውበቷን (ቴዎድሮስ) ሰሙ። ከዚያም በኋላ አስመጥተው ክርስትና አስነሱዋት።........» ይላል። ወይዘሮ የተመኙ ወፍራምና ውብ ሴት ነበሩ።

ወይዘሮ ጥሩ ወርቅ ወደ ትውልድ አገራቸው የሚታጠፉበት አካባቢ ሲደርሱ ሆዳቸው ባባ። ትንሹን የሰባት ዓመት ልጃቸውን ዓለማየሁን ለእንግሊዞች ትተው መለየቱ አባባቸው። በፊት የተናገሩትንም ከልጃቸው ተለይተው ወደ ትውልድ አገራቸው የመመለሳቸውን ሐሳብ ለውጠው ከልጃቸው ሳይለዩ ልጃቸው ከሚደርስበት አገር አብረው ለመጓዝ መወሰናቸውን ለእንግሊዞቹ ነገሩ። እንግሊዞቹም በአዲሱም ሐሳባቸው ተስማምተው ወደ ፊት ጉዞአቸውን ቀጠሉ። መቅደላ ላይ ታስረው የነበሩት

ሁለቱ ወንድሞቻቸው ካሳ ውቤና ጓንጉል ውቤ ግን እህታቸውንና እንግሊዞቹን ተሰናብተው ወደ ትውልድ አገራቸው ሔዱ።

እቴጌ ጥሩ ወርቅ ውቤ ልጃቸውን አለማየሁን ተከትለተው ከእንግሊዞች ጦር ጋር ጉዞአቸውን ቀጠሉ። እቴጌ ጥሩ ወርቅ መቅደላን ከለቀቁ ጀምሮ ሕመማቸው እየጠና ጤነኛ አልነበሩም። አንጣሎ አጠገብ ሐይቅ ሐላጥ ከሚባል ሥፍራ ሲደርሱ መከረኛይቱ እቴጌ ጥሩ ወርቅ ሞቱ። ሬሳቸውም ጨለቆት ባለው ሥላሴ ቤተ ክርስትያን ከታላቁ ከራስ ወልደ ሥላሴ መቃብር አጠገብ ተቀበሩ።



ጨለቅት ከተማ (አዲግራት)

አባቱ የሞቱበት ሕፃን ዓለማየሁ ቴዎድሮስ አሁን ደግሞ እናቱ እቴጌ ጥሩ ወርቅ ሞቱ። ቴዎድሮስ ከመሞታቸው በፊት ራሳምን አስጠርተው «.......አምንሃለሁ ልጄን ልዑል ዓለማየሁን አደራ እሰጥሃለሁ። ተጠንቅቀህ ያዝ። አባትም ሁነው። የመጨረሻ ጊዜዬ እንደቀረበ ታውቆኛል.......» ያሉትን በማስታወስ ራሳም ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ኤሮፓውያን ጭምር አለማየሁን በእንክብካቤና በአባትነት ያዙት።

# ምዕራፍ 16

# እቴጌ ጥሩ ወርቅ ውቤ - ልጅ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ

እቴጌ ጥሩ ወርቅ የሰሜን ገዥ የነበሩት የደጃች ውቤ ልጅ ናቸው። ራሳም እንደጻፈው ቴዎድሮስ ጥሩወርቅን ያገቡዋቸው ገና የ12 ዓመት ልጅ ሳሉ ነው ይላል። ከእቴጌ ተዋበች በኋላ ያገቡዋቸው ሁለተኛ ሕጋዊ ሚስታቸው መሆናቸው ነው።

አጤ ቴዎድሮስ በዚህ ጋብቻ መልካም ምርጫ አላደረጉም። በውበቷ ተደንቀው ወደው ማግባታቸው ጥሩ ነው። ልጅቱ ግን በግዴታ እንጂ በውዴታ በፍቅር ልታገባቸው አትችልም። ቴዎድሮስ አባትዋን በጥብቅ አስረዋቸዋል። አባትዋ ብቻ ሳይሆን ሁለት ታላላቅ ወንድሞቿንም ካሣ ውቤንና ጓንጉል ውቤንም አስረውባታል። ጥሩነሽ በአባትዋ በወንድሞችዋ መታሰር በቤተሰቡ መፍረስ ያዘነች በወጣትነት ዕድሜዋ ለመመንኮስ ያሰበች ናት።

ጥሩነሽ ከጧት ጀምራ እስከ ማታው ውሎዋ ከቤተ ክርስቲያን ነበር። ለአጤ ቴዎድሮስ ቆንጆ ልጅ አየሁ ብሎ የተናገረውም ወታደር ልጅነቱን ያየው ከቤተ ክርስትያን ስትፀልይ ነው። በተጠራችም ጊዜ በግደታ ተወሰደች እንጂ በደስታና በውዴታ አልነበረም። ይህን ሁሉ ብናልፈው እንኳ ቴዎድድሮስ ሚስታችወን ለማስደሰትና ኑሮአቸውን በሚገባ ለመመሥረት ከፈለጉ ወንድሞችዋንም ሆነ አባትውና ሊፈቱላት ይገባ ነበር። ታሳሪዎቹ የሚፈሩና የሚጠረጠሩ ቢሆኑ እንኳ በአጠገባቸው አስቀምጠው በዓይነ ቁራኛ ሊያስጠብቋቸው ይችሉ ነበር። ይህ ባለመሆኑ ሚስቲቱ ሚስት ሊሆኑ አልቻሉም የግዴታ እንጂ የደስታ ሚስት አልነበሩም። ስለዚህ በቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ገብታ እስረኛ የሆነችው ጥሩነሽ ቴዎድሮስ እንደሰየሟት ጥሩ ወርርቅ መሆንዋን ቀርቶ ጥሩ አናዳጅ ሆነችባቸው።

ቴዎድሮስ ሚስታቸውን ለማስደሰት ስላልፈለጉ እቴጌ ጥሩወርቅም ባላቸውን ለማስደሰት አልፈለጉም። ሌላው ቀርቶ ቴዎድሮስ ከውጭ ጥሩ ወርቅ ካሉበት እልፍኝ ሲገቡ እንኳ በባህላችን መሠረት ከተቀመጡበት ብድግ አይሉላቸውም ነበር። እነዚህን በመሳሰሉት ሁኔታዎች ሁሉ የቴዎድሮስ ኑሮ በውጭም በውስጥም ብስጭት የበዛበት ሆነ።

ለቴዎድሮስ የቅርብ ወዳጅ የነበረው ዎልድሜየር ስለዚሁ ጉዳይ ሲጽፍ «.......አዲስዋ እቴጌ እንደፊተኛዋ አልሆን አሉ። በዚህ ምክንያት ንጉሱ ይበሳጩ ጀመር። ከብስጭት የተነሳም ብዙ አስካሪ መጠጥ መጠጣት ጀመሩ። ሌሎች ሴቶችንም በየቦታው ማስቀመጥና መሔድ አበዙ።.......» ይላል ዎልድሜየር እንደጻፈው ቴዎድሮስ በመቅደላ ተራራ ላይ ብቻ 28 ቁባቶች አስቀምጠው ነበር። በዚህ ምክንያትም በአባት እንጂ በእናት የማይገናኙ ብዙ ልጆች ነበሩዋቸው።

ዶክተር ብላክን ስለ ወይዘሮ ጥሩ ወርቅ ጋብቻ ጉዳይ በጻፈው ታሪክ «.......ወጣትዋ ቤተ ክርስትያን ለማገልገል ስትል ገዳም ለመግባት ማቀድዋን ገልጻ ጥያቄያቸውን ሳትቀበል ቀረች። አጤ ቴዎድሮስ ሐሳባቸውን ከፍጻሜ ሳያደርሱ የማይቀሩ ብርቱና ኃይለኛ ሰው ስለሆኑ ደጃዝማች ውቤን ይህችን ልጃችወን በሚስትነት ቢድሩላቸው ከእስር ቤት አውጥተው በሠፈራቸው የክብር እንግዳ ሆነው እንዲቀመጡ የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸው በበኩላቸው ልጃቸውን እንዲያሸንፉ አሳብ ስላቀረቡ በመጨረሻ ጥሩነሽ ለሽማግሌ አባትዋ ደህንነት ራስዋን ሰውታ ልትወዳቸው የመትችለውን ሰው ለማግባት ተስማማች። አጤ ቴዎድሮስ ባለመታደላቸው ሁለተኛ ሚስታቸው እንደሚቿ በእርሳቸው ፍቅር የተነደፈች ፍጹም የሆነ ፍቅር ያላት ሳትሆንላቸው በመቅረቷ ከፍ ያለ ሃዘን ደረሰባቸው። ወይዘሮ ጥሩነሽ በጣም ኩሩ ሴት ስለ ነበሩ ባላቸውን እንደ አንድ ዝቅተኛ ሰው አድርገው እየተመለከቱ እንዲያከብሯቸውና እንዲጨነቁላቸው የነበራቸው ፍላጎት በግልጽ ከማሳየት አልተመለሱም። አጤ ቴዎድሮስ እንደልማቸው ከሰዓት (ከተስያት) በኋላ የድደከመውን ሰውነታቸውን ለማሳረፍ ወደ ንግሥቲቱ ድንኳን ሲሔዱ አስደሳች አቀባበል ስለማያገኙና እንዲያውም በቀዝቃዛና ኩራት በተመላ መንፈስ እየተቀበሉና የተለመደውን ለንጉሠ ነገሥት ባላቸው ማሳየት የሚገባቸውን ትህትናና የክብር ሰላምታ እንኳ ይነፍጓቸው ጀመር። አንድ ቀን ወደ ድንኳናቸው ሲገቡ ያላዩዋቸው መስለው ከመቀመጫቸው ላይ ሳይነሱላቸውና ስለ ጤናቸውም ሲጠይቋቸው መልስ ሳይሰጡ በእጃቸው የያዙትን ዳዊት እየተመለከቱ ዝም በማለታቸው ለምን መልስ እንዳልሰጧቸው ቢጠይቋቸው «ከእርስዎ ከበለጠና ከሚሻል ሰው ጋር በመነጋገር ላይ ስለሆንኩ ነው።.......አሏቸው። ይባላል......» ይላል። አጤ ቴዎድሮስ በገቡት ቃል መሠረት የሚስታቸውን አባት አልፈቱላቸውም። ሽማግሌው ውቤ ከእስር

የተፈቱት ከሞቱ በኋላ ሬሳቸው ነው። ወንዶች ልጆቻቸውን የእቴጌ ጥሩ ወርቅ ወንድሞችም የተፈቱት የእንግሊዝ ጦር መቅደላን ከያዘ በኋላ ነው። በዚህ ሁሉ ምክንያት የጥሩ ወርቅ ኑሮ የኀዘን ነበር።

ዶክተር ብላክን በጻፈው ታሪክ እቴጌ ጥሩ ኑሮአቸው እንዴት እንደነበር ሲገልጽ «.......የዓለማየሁ እናት ወይዘሮ ጥሩነሽ የተበደሉና የተገፉ ቢሆንም ምንም ቅያሜ ሳያሳዩ ለባላቸው ታማኝ ሆነው ይኖሩ ነበር። ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት ልጃቸውን ከጐን አስቀምጠው ብቻቸውን መዝሙረ ዳዊት የመላእክትንና የሰማዕትን መልካ መልክ የሐዋርያትንና እጅግ በጣም የሚወዷትን የቅድስት ማርያም በማንበብ ነበር። ምንም እንኳን ባላቸው ቴዎድሮስ ምን ጊዜም ቢሆን ወደዋቸው የሚያውቁ ቢሆንም በመከራቸው ጊዜ በድፍረት አብረዋቸው ተሰልፈው የስቃያቸው ተካፋይ ሆነዋል።........አጤ ቴዎድሮስ ሊሞቱ ሁለት ቀን ሲቀራቸው ለብዙ ዓመታት የተለዩዋቸውን ሚስታቸውን አስጠርተው ከሰዓት በኋላ ከእርሳቸውና ከልጃቸው ጋር ሲጫወቱ ዋሉ።........» ብሏል። (ትርጉም ዳኜ ወ/ሥ)

ምኒልክ ሸዋ ገብተው ራሳቸውን ንጉሥ ካሉ በኋላ አንዳንድ የመቅደላ እስረኞችና መኳንንት ጋር ተማክረው የመቅደላን አምባ ለመያዝ በመጡ ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ ዶክተር ብላንክ በመጽሐፉ ሲገልጽ «.......በዚህ ጊዜ ማድረግ የሚገባትን ፈጸመች። በልጅ ዓለማየሁ ጋባዥነት በአምባው ውስጥ ለሚገኙት የጦር አለቆች ምንም እንኳ ቀኑ ጾም ቢሆንም በጾም ወጥ ግብር አግብታ የጦር አለቆችና ወታደሮቹ ታማኝነታቸው ለቴዎድሮስ መሆኑን እንዲያረጋግጡ ስለጠየቀችና ከሐዲም ቢኖር ቅጣቱን ለመስጠት መሰናዳቷ ስለታወቀ ምኒልክን እንረዳለን በማለት ውስጥ ውስጡን ቃል የገቡ ሁሉ ፍርሃት አደረባቸውና ሁላቸውም ታማኝነታቸውን ለቴዎድሮስ ለማድረግ ቃል እየገቡ ወጡ። በዚህ ስብሰባ እንዳንድ የጦር አለቆች ከምኒልክ ጋር የነበራቸውን ስምምነት መሠረት በማድረግ ሳይገኙ በመቅረታቸውና ምኒልክንም በግልጽ የሚደግፉ ብዙ ሰዎች ባለመገኘታቸው ተጠርተው ምክንያታቸውን ሲጠየቁ የሚያዛልቃቸውን መልስ በመስጠታቸው ምክንያቱን ለጊዜው ተቀብላ የቤተ መንግሥቱን አጥር እንዲያጥሩ ቀላል ቅጣት ሰጥታ ቃል ከገቡ በኋላ አሰናበተች።....... ውስጥ ውስጡን ከድቶ የነበረው የጦር አለቃ

ሁሉ ለቴዎድሮስ ታማኝነቱን በቃል አጋኖ እየተነገረና ምኒልክንም «ወፍራም ልጅ» በሚል ቅፅል ስም ይሰድቡ ጀመር።.......» ብሏል።

## ዓለማየሁ ቴዎድሮስ

አጤ ቴዎድሮስ ስድስት ልጆች ቢኖሩዋቸውም ከሕጋዊ ሚስት የተወለደው ግን ዓለማየሁ ብቻ ነው። ዓለማየሁ ደብረ ታቦር ከተማ በ1853 ዓ.ም ሚያዝያ 5 ቀን በተወለደ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ተደስተው መድፍና ጠመንጃ አስተኩሰዋል። 500 ያህል እስረኞችም ፈተዋል። ያ ቴዎድሮስ ከዓለማየሁ ጋር ሲጫወቱ መውላ በጣም ያስደስታቸዋል። ተናድው ተበሳጭተው በሚመለሱበት ጊዜ እንኳ ዓለማየሁን ታቅፈው ሲስሙ ንዴታቸውም ሆነ ብስጭታቸው ይጠፉላቸው ነበር ይባላል።



አለማየሁ ቴዎድሮስ በሕፃንነቱ

ቴዎድሮስ አንድ ቀን ከመኳንንቶቻቸው ጋር ሲጫወቱ በድንገት በጨዋታው መሀል «በዓለም ላይ ካለ ነገር ሁሉ ሽታው እጅግ ደስ የሚልና ልብ የሚመስጥ ምንድነው? ብለው ጠየቁ መኳንንቱም ሁሉም የሚያውቀውን የሽቶ ዘርና ሌላም ሁሉ ተናገረ። ቴዎድሮስም ሁሉንም አላወቃችሁም ካሉ በኋላ «የሕፃን ልጅ ጠረን ነው» ብለው መለሱ ይባላል።

የቴዎድሮስ ልጅ ውብ ዓለማየሁ በእንግሊዞች እጅ ገብቶ ኤሮፓውያኖቹ በሙሉ ቢያዝኑለትና ቢንከባከቡትም ኃላፊ የሚሆነው ሰው የሚያስፈልገው ሆነ። በዚህ ምክንያት ጄኔራል ናፒር ካፒቴን እስፒዲን ለዓለማየሁ ሞግዚትነትና አላፊ አድርጎ ሾመው። ካፒቴን እስፒዲ የተመረጠበት ዋናው ምክንያት አማርኛ ቋንቋ ደህና አድርጎ መናገር ስለሚችል ነው። እስፒዲ ብቻ ሳይሆን ሁለት ኢትዮጵያውያን ሞግዚቶችና አጫዋቾችም ተመረጡለት። እነሱም አንደኣኘው በቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት የታወቁት አለቃ ዝርአት ሲሆኑ ሌላው አቶ ገብረ መድኅን ይባላሉ።

እቴጌ ጥሩ ወርቅ ሊሞቱ አቅራቢያ ካፒቴን እስፒዲን አስጠርተው እጁን ይዘው «ልጄ አባት የለውም። እኔም እናቱ ልሞት ነው። በሚሔድበትም አገር ዘመድ ስለሌለው አንተ ዘመንድ ሁነው። አባት ስለሌለው አንተ አባት ሁነው። ያልኩህን ሁሉ እንደ ምታደርግለት በእግዚአብሔር ማልልኝ። አሉት። እስፒዲ በኋላ ጊዜ እንደጻፈው «.......ከሞት አፋፍ ላሉት ለዓለማየሁ እናት የጠየቁኝን ሁሉ እፈጽማለሁ ብዬ ማልኩላቸው........» ይላል።

ዓለማየሁ ከአዲስ አሳዳጊ ከእስፒዲ ጋር ፌሬዝ በተባለች መርከብ ላይ ሰኔ 4 ቀን 1860 ዓ.ም ተሳፈረ። በመርከቧም ላይ ለእስፒዲና ለዓለማየሁ ለብቻቸው አንድ ክፍል ተሰጣቸው። ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ሞግዚቶችም አብረውት ሆኑ። አባቱም እናቱም የሞቱበት የትናንቱ የንጉሠ ነገሥት ልጅ ከሞዚቱ ከእስፒዲ ጋር ፍቅሩን መሠረት። እስፒዲ በመርከቧ ላይ ላንዳንድ ሥራ ሲታዘዝ ዓለማየሁ ሳየለየው አብሮት ይሂዳል። ዓለማየሁ ከአንድ ቦታ ብቅ ሲል ከኋላአው እስፒዲ አለ ማለት ነው። ካፒቴን እስፒዲ ብቅ ሲል ቀጥሎ የሚመጣው ዓለማየሁ ነው። የሁለቱን መፋቀር ያየው የመርከቧ ላይ ሠራዊት ካፒቴን እስፒዲ ምንም ዓይነት ሥራ እንዳይታዘዝ አደረጉ።

በመርከቧ ሲጓዙ ሰኔ 8 ቀን ስለደረሰው ሁኔታ እስፒዲ እንዲህ ይላል። «……የሚጮህ ድምፅ ሰማሁ። አጯጯሁና ድምፁ አማርኛ ስለሆነብኝ ዓለማየሁ ይሆናል ብዬ ደነገጥሁ። ዓለማየሁ ከኔ ተለይቶ መርከቧ ሜዳ ይጫወት ነበር። ወደ ልጁ እየሮጥሁ ስሔድ ከናፒር የተላከ መልዕክተኛ አጋጠመኝና ቶሎ ና ትባላለህ አለኝ።፡ ስደርስ አለማየሁን ናፒር ታቅፎታል። ዓለማየሁ ይወራጫል እናት አባቱ የሞቱበት ያን ሕፃን ከአዛዦችን ከናፒር እጅ ስቀበል አከቃ ዝርአት ልጁ የሚጮኸው ቡዳ በልቶት ነው አሉን። ምስኪን ዓለማየሁ የያዝንለትን ኢትዮጵያውያን ሞግዚቶቹን ጠልቶ እኔን ሲያይ ከኔ አንገት ላይ ጥምጥም አለ……» ብሏል።

ዓለማየሁ ጉዞው አልተማማውም። በተለይ ኢትዮጵያውያን ሞግዚቶቹን ሲያይ አምርሮ ያለቅሳል ስለዚህ ጉዳይ እስፒዲ እንዲህ ይላል። «……ናፒር ጠራኝና በልጁ ላይ ያለውን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ አንተ ያዝ። ከአበሾቹ ይልቅ ልጁ አንተን እዶሃል። አበሾቹን ሲያይ የሚያወራጨውና የሚያበሳጨው ነገር ስላለ እነሱ ሲዊዝ ስንደርስ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ አለኝ…….» ይላል።

መርከብዋ ስዊዝ ስትደርስ ዓለማየሁ የተያዙት ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ሞግዚቶች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ወደ ቦምባሳ (ኬንያ) በሚሔድ መርከብ አሳፈው ላኩዋቸው። ከዚያ በኋላ ስላለው ሁኔታ እስፒዲ ሲገልጽ «……እኔንም ቢሆን ዓለማየሁ አስቸገረኝ። ከኔ በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር አልለምድ አለ። ሲተኛ እንኳን ክንዴን ካላንተራስኩትና እብብቴ ውስጥ ሽጉት ካላለ እንቅፍ አይወስደውም። የአበሻ ሞግዚቶቹ ስለ አባቱና እናቱ አሟሟት የነገሩት የሚያስፈራራ ነገር ከአእምሮው አልወጣ አለ። ተኝቶ ይባንንና ይነቃል። ምን ሆንክ ስለው ፈራሁ ይለኛል። ሽጉጥ አድርጌ እብብቴ ሥር እይዘውና አይዞህ እኔ እያለሁ አትፍራ። ተኛ ስለው ያን ምስኪን እንቅፍል መልሶ ያሸልበዋል። እንቅልፍ ድብን አድርጎ እስኪወስደው ድረስም ራሱን ከክንዴ ላይ አላነሳም። ለዓለማየሁ ያለሁት እኔ ብቻ ነኝ። ሶስት ወር ሙሉ በእንዲህ ያለ ችግር ከረምን…….» ይላል።

ዓለማየሁ እንግሊዝ አገር ከደረሱ በኋላ ከእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ጋር ተገናኘ። ንግሥቲቱ ለዓለማየሁ ማነኛውም ጥንቃቄ እንዲደረግለት አዘዙ። የፍርሀቱን ነገር ከአእምሮው እንዲጠፋ ሐኪሞች ሁሉ ተባብረው እንዲያድኑት ንግሥት ቪክቶሪያ አዘዙለት። ዛሬ በእንግሊዝ ቤተ መንግሥት በሚገኘው

የንግሥት ቪክቶሪያ የዕለት አጀንዳ ወይም ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ንግሥት ቪክቶሪያ ሲጽፉ «.......ምስኪኑ ልጅ (ፑር ቻይልድ) አሁንም ፍርሃቱ አለቀቀውም። መቅደላ በተያዘ ጊዜ በዚያ ነበረውን እልቂትና የአባቱን ሞት ስላየ ያ ነገር በአእምሮው ይመጣበታል......» የሚል ቃል ፅፈዋል።



አለማየሁ ቴዎድሮስ እንግሊዝ አገር በተወሰደ ጊዜ

ዓለማየሁ ሐምሌ 11 ቀን 1868 እ.ኤ.አ. እንግሊዝ አገር ከደረሰ በኋላ እስፒዲ በአሰሌ ውስጥ ፍሬሽወተር ከሚገኘው ቤቱ ይዞት ገባ። በዚያም እንግሊዝኛ ያስተምረው ጀመር። ንግሥት ቪክቶሪያ የዓለማየሁን ሁኔታ ይቆጣጠሩ ስለ ነበር እስፒዲ እየወሰደው ብዙ ጊዜ ከንግሥቲቱ ጋር ይገናኛል። ልጁን እንዳይጐዳውም በእስፒዲ ላይ ልዩ ተቆጣጣሪ አቋቁመውበታል። ሐምሌ 10 ቀን ንግሥት ቪክቶሪያ ዓለማየሁን ባነጋገሩበት ጊዜ ንግሥቲቱ በዕለት ሁኔታ መመዝገቢያ ደብተራቸው ላይ ስለ ዓለማየሁ ከጻፉት «.......ጨዋና ውብ ልጅ ነው። ኬክ መብላት ይወዳል። የሰጠሁትን ኬክ ሁሉ በላ። የምሰጠውንም ኬኮች ደስ እያለው በፈገግታ እየተቀበለኝ በላ........» የሚል አረፍተ ነገር አለበት።

ጁላይ (ሐምሌ) 25 ቀን ደግሞ ንግሥቲቱ በዕለት ሁኔታ ደብተራቸው ላይ «.......ዛሬ ከዓለማየሁ ጋር አብረን ምሳ በላን ዓለማየሁ ከኔ ዘንድ የሚመጣው የአገሩን የአበሻ ልብስ ለብሶና ከአገሩ የተያዘለትን ጌጣ ጌጦች አጊጦ ነው። ምሳ በልተን ከጨረስን በኋላ ለዚህ ለተከበረ ትንሽ ልጅ (ዲር ሊትል ቦይ) በእጁ ላይ ሰዓት አሠርኩለት። በወገቡም ላይ የወርቅ ሰንሰለት አስታጠቅሁት......» ብለው ጽፈዋል።

ዓለማየሁ ከንግሥት ቪክቶሪያ ጋር ተወዳጅቷል። በዓለማየሁ ሰበብ እስፒዲም የንግሥት ባለሟል ሆነዋል። ብዙ ጊዜም ንግሥት ቪክቶሪያ «ለዚህ እናት ለሌለው ሕፃን እናቱ እኔ ነኝ» እያሉ ይናገራሉ። ስለ ትምህርቱ ይጠይቁታል። ስለ ጤንነቱ ያጫውቱታል ዓለማየሁ። በቤተ መንግሥቱ ታላቅ የብስኩት ግብዣ እየተደረገለት ከልዑላንና ልዕልታት ልጆች ጋር ሲጫወት ቢውልም አምኖት የሔደውን እስፒዲን አይረሳም። ግብዣ ላይ እስፒዲ ከሌለ አይበላም። መብላት ቀርቶ ከእስፒዲ ተለይቶ ከቤተ መንግሥት አይገባም። በጨዋታ ቦታ እስፒዲ ቁጭ ካላለ ዓለማየሁ አይጫወትም ያለ እስፒዲ ምንም ነገር አያደርግም።

እስፒዲ ወታደር ነው። የወታደር ድልድሉ ደምኅ ሕንድ ውስጥ ነው። በሥራው ላይ ባለመገኘቱ ደብዳቤ ይጻፍለት ጀመር። እስፒዲ ጥቅምት 10 ቀን ለሕንድ ዋና አዛዥ ደብዳቤ ጻፈ። በሳፈውም ደብዳቤ «........እርግጥ ልጁ ጤነኛ ነው። ባባሕር ዳር እየተዘዋወረ ከባሕር የሚነሳውን አየር መቀበልና

በባሕሩ ውስጥ መንቦራጨቅ ይወዳል። በሥራዬም ላይ ያልተገኘሁት ልጁን ውሃ መዋኘት እያስተማርኩት ነኝ። ልጁ አሁን እየተላመደ ሔድዋል። ማፈርና መሽኮርመሙን ትቷል። በሱ ዕድሜ ካሉ ልጆች ሁሉ የተለየ ጨዋ ልጅ ነው። በእንግሊዝኛ ችሎታውም ገፍቷል።» በማለት ሪፖርት አቀረበ።

እስፒዲ ለዓለማየሁ ሕይወቱን ሰጥቷል። እስፒዲና ዓለማየሁ የሚበሉት አብረው ነው። የሚተኙትም አብረው ነው። ዓለማየሁ የእስፒዲን ክንድ ካልተንተራሰ እንቅልፍ አይወስደውም እስፒዲም ከዓለማየሁ መለየት አይፈልግም። ግን ሥራው ወታደርነት ስለሆነ የወታደር ግዴታውን መፈጸም አለበት። እስፒዲ ሚስት ስለሌለው ዓለማየሁን የሚያሳድገው ብቻውን ነው። እንዲህ አይነቱ ኑሮ የማያዛልቅ በመሆኑ እስፒዲ ሚስት ለማግባት ወሰነ። «ዓለማየሁን እንደ ልጇ አድርጋ የምታሳድግ ሚስት የት ትገኛለች?» ይል ጀመር። ልጅ የሌላትና ልጅ የምትወድ ባልቴት ያፈላልግ ጀመር። ወይዘሮ ኮታም ተገኘችና ከሷ ጋር ተጋባ። ኮታም ከዓለማየሁ ጋር ተላመዱ። እንደምትወደው ዓለማየሁም ወደዳት። ዓለማየሁ ከወይዘሮ ኮታም ጋር ብቻ ሳይሆን ከወይዘሮ ኮታ እናት ጋር ተዋደደ።

ታኅሣሥ 26 ቀን ንግሥት ቪክቶሪያ በዕለት ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ «.......ዛሬ ምሣ ከመብላታችን በፊት ዓለማየሁ መጥቶ ነበር። ዓለማየሁ ደህና ሆንዋል። ቁመቱም አድጓል። ካፒቴን እስፒዲ ከአዲሷ ሚስቱ ጋር የሙሽርነት ሽርሽር ስለሔደ ልጁን ይዛ የመጣችው የካፒቴን እስፒዲ ሚስት እናት ናት.......» ብለው ጽፈዋል።

ያን ጊዜ ሕንድ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር ስለ ነበረች የሕንዱ አገረ ገዥ የእስፒዲ አለቃ ስር እስታፎርድ ኖርዝኮት አንድ ውሳኔ አሳለፉ። በውሳኔያቸውም ላይ «......ካፒቴን እስፒዲ ከዓለማየሁ መለየት የለበትም። ቢያንስ ዓለማየሁ ራሱን እስኪችልና በደንብ እስኪላመድ አብሮት መቆየት አለበት። እስፒዲ የአለማየሁን ቋንቋ ይችላል። ከዚህም ሌላ የዓለማየሁ እናት ሊሞቱ ሲሉ ልጃቸውን ዓለማየሁንና እስፒዲን እጅ ለእጅ አጨባብጠው ለእስፒዲ አደራ መስጠታቸውንና መሞታቸውን ዓለማየሁ ያስታውሳል። የአባትና የእናቱ ተከታትሎ መሞት ከልጁ አእምሮ ውስጥ ያልጠፋ ስለሆነ ያለ እስፒዲ የሚያምነውና የሚወደው ሰው ስለሌለ እስፒዲ ከዓለማየሁ ጋር እንዲቆይ ወስኛለሁ። ለልጁ ማሳደጊያ መደጐሚያ እንዲሆንም ባመት 300

ፓውንድ ለልጁ ልብስና መጫወቻ መግዣ ደግሞ ባመት 400 ፓውንድ በጠቅላላው ባመት 700 ፓውንድ እንዲሰጠው ወስኛለሁ......» በማለት አስታወቁ። ይህ የተወሰነው ገንዘብ በዘመኑ ከፍ ያለ ገንዘብ ነበር። አሁን ለዓለማየሁ በእንግሊዝ አገር ኑሮ አንድ ዓመት ሆነው።

1861 ዓ.ም በሕንድ አገር አድ ውስጥ ባለው ሱታፑር ለሚባለው ቀበሌ የፖሊስ ኮሚሽነር ሆኖ ተሾመ። እስፒዴ እ.ኤ.አ. ጁላይ 4 (በኛ ሰኞ 27) ቀን የምስንት ዓመቱ ዓለማየሁና ሚስቱን ይዞ ወደ ተሾመበት አገር ሔደ። እስፒዲ ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ዓለማየሁን እንዲያሳድግ ተፈቅዶለት ነበር። እስፒዲ በየጊዜው የልጁን ሁኔታ ሪፖርት ማቅረብ ስለነበረበት ከሔደ የመጀመሪያ ሪፖርቱ እንዲህ የሚል ነበር። «......ዓለማየሁ በትምህርቱ ጐብዟል። ከትምህርቱ ሌላ የውጭ እስፖርት ይወዳል። በተለይ ፈረስ ግልቢያ በጣም ይወዳል። የአእምሮ ሕመሙ አንዳንዴ ይነሳበታል። ዓለማየሁ ለሚጠይቀኝ ሁሉ ሳልደብቅ እውነተኛውን እነግረዋለሁ.......» ብሏል።

የዓለማየሁ የመከራ ዘመን የተጀመረው የሊብራሉ መንግሥት ቻንስለር ኦፍ ኤክስቼከርስ ሰር ሮበርት ሉዊ ስለ ዓለማየሁ ሐሳብ ካቀረቡ በኋላ ነው። ቻንስለሩ ጁን 5 ቀን 1870 (በኛ ግንቦት 28 ቀን 1962) ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ያቀረቡት አሳብ «......እኔ እንደማስበውና ለልጁም ይጠቅመዋል የምለው በወታደርነት ትምህርቱን እንዲቀጥል ነው። የኢሮፓ መኮንኖች በፈረስ ግልቢያ ከሚሰለጥኑበት ቢገባ ጥሩ ይሆናል።.......» የሚል አሳብ አቀረቡ። አሳቡ ለክፋት አልነበረም። ራሱን ችሎ የሚኖር ለማድረግ ነበር። ዓለማየሁ ከእስፒዲ ጥገኝነት እንዲወጣ ለማድረግ ነበር።

ዓለማየሁ ከእስፒዲ የሚለይበት ቀን ደረሰ። እስፒዲ ለሁለት ዓመት ብቻ ከዓለማየሁ ጋር እንዲሆን የተወሰነው ቀንም ደረሰ። የወተሰነው ጊዜ ኦገስት (ነሐሴ) 1 ቀን ከመድረሱ በፊት በየካቲት ወር 1871 እስፒዲ ሪፖርት አቀረበ። በሪፖርቱም «.......በሚመጣው ሚያዝያ ወር የዓለማየሁ እድሜ አሥር ዓመት ይሆናል። አሁን የዓለማየሁ ቁመት 4 ጫማ ከ6 ኢንች ሆንዋል። ጨዋታ ይወዳል። በተለይ ከእንስሳት ጋር መዋልን ያፈቅራል። ዓለማየሁ ደብተሮቹን ከማዝረክረኩ ሌላ በጥሩ ሁኔታ አድጓል። በዚህ አለማችን (ዩኒቨርስ) ካሉ ልጆች ጥሩው ልጅ ዓለማየሁ ነው።......ዓለማየሁ ልባችንን

የሚነካ ልጅ ነው። ስለኛ ወላጆች ይጠቀንና ወላጆች እንደሌሉን ስንነግረው እኔም ወላጆች ስለለሉኝ እኩል ነን ይልና ኩራት ይሰማዋል። የዚህ የሕንድ አገር ኑሮአችን ለዓለማየሁ አልተመቸውም። ምክንያቱም ደህና ትምህርት ቤት ስለሌለ ነው።.......» የሚል ሪፖርት አሳለፈ።

የእንግሊዝ መንግሥትም ዓለማየሁ ከእስፒዲ ሞግዚትነት ሥር ወጥቶ በመንግሥት ቁጥጥር እንዲሆን ወሰነ። በ1863 ዓ.ም እስፒዲ ወደ ፔናንግ እንዲዛወር ሲታዘዝ ዓለማየሁ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመለስ ተወሰነ። ዓለማየሁ አለቀሰ። እስፒዲ አንገት ላይ ተጠምጥሞ «......አባቴ አንተ ነህ ያለ አንተ መኖር አልችልም። እባክህ ከአንተ አትለየኝ ወደምትሔድበት ሁሉ አብሬህ ልሂድ። ያለዚያ እሞትብሃለሁ.......» አለው። በዚህ ንግግር ልቡ የተነካው እስፒዲ ከዓለማየሁ ላለመለየት ደብዳቤ ጻፈ። የእስፒዲ ማመልከቻ ከተጠና በኋላ የሲንጋፑር አዛዥ የነበሩት ሎርድ ኮምበርሌይ በኮሚቴው ስም የሚከተለውን ውሳኔ አስተላለፉ።

«......ካፒቴን እስፒዲና ዓለማየሁ አብረው አይተናቸዋል። ካፒቴን እስፒዲ ለዓለማየሁ እንደ አባቱ ነው። ካፒቴን እስፒዲ ልጅ ስለሌለው ሚስቱም እሱም ዓለማየሁን እንደ ልጃቸው ያዩታል። የካፒቴን እስፒዲ ሚስት ከእንግሊዝ አገር ሆና ለዓለማየሁ በቂ ጥንቃቄ ማድረግ ስለምትችል ካፒቴን እስፒዲ ወደ ተዛወረበት አገር እንዲሔድና ዓለማየሁ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመለስ ይሁን......»

ብዙ ክርክር ተነሳ። የዓለማየሁ የመከራ ዘመን ተጀመረ። ካፒቴን እስፒዲና ሚስቱ ዓለማየሁን ላመመስጠት ሙግት ጀመሩ። መሟገቻ አንደበትና እውቀት የሌለው ዓለማየሁም ከካፒቴን እስፒዲ ላለመለየት በእንባው ተቃውሞውን ይገልጽ ጀመር። የእስፒዲን አንገት አቅፎ እየያዘም «አባ አባዬ፥ እባክህ ካንተ አትለየኝ። እባክህ አብረን እንሁን።» ይለው ጀመር። የእስፒዲ ሚስትም የንግሥት ቪክቶሪያ የግቢ ሚኒስቴር ለሆኑት ለሰር ጆን ከቄል ደብዳ ጻፈች። «.......ከልጁ ጋር ለመለየት የተወሰነው ውሳኔ ከፍተኛ ኀዘን አሳድሮብናል......... በየቀኑ የየቀኑ ሁኔታ የሚከታተሉና ከሚወዱት ፍቅረኛቸው የተለያዩ ሰዎች ብቻ ይህን ነገር ያውቁታል ለዓለማየሁ ጥቅም ነው የሚወሰደው ከተባለ የምንናገረው ነገር ግን ይህ ነገር እጅግ በጣም አጠራጣሪ ነው ብላ ጻፈች።

የአርጊል ዱክ በጉዳዩ ገብተው ኖቨምበር 11 ቀን 1881 ለግላንድ እስቶን በጻፉት ደብዳቤ ልጁ ከእስፒዲ ጋር ቢኖር እስማማለሁ ብለው አሳወቁ። ለዚህ ሐሳብ የኤክስቼከር ቻንስለር ሮበርት ሎዊ በደብዳቤ ሲመልሱ «........ነገሩ የተወሰነው በጠቅላላው አስተሳሰብ ነው።........ልጁን ማየት ያለብን እንደ ልጃችን አድርገን ነው። ማንም ወላጅ ቢሆን ልጁን ሕንድ ውስጥ ለማሳደግ ይፈልጋል ቢባል ቅጥፈት ነው።........በዚህም አገር የሚቆይ ከሆነ መጨረሻው የማያምር ይሆናል።........እኔ አሁን ከኬልተንሃም ኮሌጅ ከጄክስ ብላኬ ጋር ተነጋግሬአለሁ። የተነጋገርኩትም ልጁን በግል ቤታቸው እንዲያኖሩት ነው። ብዙ ቤተስብ ያላቸው ሰው ስለሆኑ ልጁ ብቸኝነት አይሰማውም።.......ምናልባትም ልጁ አንድ ቀን ከአገሩ ከአበሻ የሚገባበት ጊዜ ይመጣ ይሆናል።.......ስለዚህ ይህ ልጅ የኤሮፓን ባሕ ብቻ ጠቅሎ መያዝ የለበትም........» አሉ። ጃክስ ብላኬ የኬልተንሃም ኮሌጅ ፕሬዘዳንት ናቸው። ሌሎችም ብዙ ትምህርት ቤቶች አሏቸው። ቄስ በመሆናእውም በደግነታቸው የታወቁ ሰው ናቸው። የወለዷቸውም ብዙ ልጆች ቢኖሩዋቸውም ሌሎች ልጆችም የሚያሳድጉ የብዙ ቤተሰብ አባት ናቸው።

ንግሥት ቪክቶሪያም ይህን ውስኔ እንደሰሙ ከእስፒዲ ይለይ በሚለው አሳብ አልተደሰቱም። በጻፉትም ደብዳቤ በአሳቡ ያለመስማማታቸን ገልጸው «........ቢሆንም መፈጸም ያላበቸው ሁለት ነገሮች አሉ። መጀመሪያ የሕክምና አዋቂዎች ልጁን እንዲመረምሩትና እንዲያጠኑት ያፈልጋል። ከሚወዳቸውና ከሚያውቃቸው ሲለይ በአእምሮው ላይ የሚያመጣው ለውጥ መጠናት አለበት ሁለተኛ የሐኪሞች ሰብሳቢና የበላይ ወሳኝ ሰር ጄነር እንዲሆን........» የሚል አሳብ አቀረቡ። ሮበርት ሎዊ ደግሞ «........የዓለማየሁ የወደፊት ሕይወቱ የሚመራው ካሁኑ በሚመሠረተው ሥነ ሥርዓት ነው። እውር ዕድል እንዲኖረው አያስፈልግም። በቅኝ ግዛታችን በሕንድ ቆይቶ አሁን ደግሞ እንዴት ወደ ፔናንግ ይሂድ እንላለን። በ700 ፓውንድ ወጭስ ምን ዓይነት ኑሮ ሊኖር ይችላል። በምሥራቅ አገሮች ሆኖ የምሥራቅ አገር ትምህርት ይማር የሚባል ከሆነ እኔ እንደማስበው ልጁ ለሕንድ ገዢ መሰጠት አለበት። ግን እኛ ለትምህርት የምንከፍለው ገንዘብ ልጁ በሚጠቀምበት ሁኔታ ላይ መዋል አለበት። ስለዚህ እኔ የማቀርበው አሳብ ልጁ ወደ እንግሊዝ አገር መጥቶ በጥሩ ሁኔታ ማደግ አለበት......» አሉ።

በመጨረሻው ዓለማየሁ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመጣ የሚለው አሳብ ተወሰነ። ጃክስ ብላኬ ልጁን ለመቀበለ እንዲዘጋጁ ተነገራቸው። እሳቸውም ልጁን በደስታ እንደሚቀበሉት ሲገልጹ «........ምናልባትም የሚፈልገው ከሁሉ በፊት ርህራሄንና ሥነ ሥርዓት ያላቸውን ልጆች ይሆናል።.......እኛ ዘንድ ከመጣ ከወርና ከሁለት ወር በኋላ ሁሉም ነገር ይታወቃል። እንደ ወዳጃችን ልጅ አድርገን እንይዘዋለን። እናስተምረዋለን። ግልገል ፈረሱንም እንዲጋልብ እናደርጋለን። የሚጠይቀንን ሁሉ እንፈጽማለን።.......» በማለት ለዓለማየሁ በኃላፊነት ለመቀበል ተስማሙ። ከዚህ በኋላ እስፒዲ ዓለማየሁን ይዞ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመጣ ታዘዘ። እስፒዲም ዓለማየሁን ይዞ ታኅሣሥ 21 ቀን 1863 ዓ.ም (ዲሴምበር 30 /1871) እንግሊዝ አገር ሳውዝ አምተን ገባ። ወዲያውም ከቤታቸው ፍሬሽወተር ይዞት ሔደ። እስፒዲ የተጻፈለት ደብዳቤ አልደረሰውም እንጂ ዓለማየሁን ይዞ ሲመጣ የት እንዲያርፉና ለአቀባበሉም ፕሮግራም መውጣቱ ተጽፎለት ነበር። እስፒዱ ግን ደብዳቤው ስላልደረሰው ዓለማየሁን ይዞ ከቤቱ ሔደ።

የዓለማየሁ እንግሊዝ አገር መግባት እንደ ተሰማ በንግሥት ቪክቶሪያ ስም ቶማስ ቢደልፍ አንድ ደብዳቤ ለሉዊ ጻፈ። ደብዳቤውም «........ንግሥቲቱ በልጁ ላይ ትልቅ ሥሜት አላቸው። እስፒዲ ልጁ ይዞ መምጣቱን ሰምተዋል። ቢያንስ እንኳ የልጁን መድረስ ለንግሥቲቱ ሪፖርት ማቅረብ ነበረበት። .......ንግሥቲቱ ያዘዙት ትእዛዝ አለ። የልጁ ጤንነት በሚገባ እንዲመረመርና የእንግሊዝ አገር አየርም ለኑሮውም ይስማማው እንደሆነ በአስቸኳይ እንዲጠና አዘዋል። ለዚህም ጉዳይ ንግሥቲቱ አሳብ ሲያቀርቡ ሰንጄነር እንዲያዩትና ስለ ጤንነቱም ሆነ አእምሮውን ስለሚያውከው ሕመም ሪፖርት ይቀረብልኝ ብለዋል።........ልጁ አሁን የት እንዳለ እኔ አላውቅም። .......በፕሮግራሙ መሠረት ግን እንግሊዝ አገር በገባ በአራት ቀኑ ለጅጄክስ ብላኬ እንዲሰጥና ትምህርት ቤት እንዲገባ ነበር። እስፒዲ ንግ አልሰጠውም። .......» የሚል ነበር። ለዚህ ደብዳቤም ሉዊ ሲመልሱ ልጁ በደህና እንግሊዝ አገር መድረሱን ስለ ልጁም ማንኛውንም ነገር ማዘጋጀታቸውን ገለጹ። ወዲያውም እስፒዲ አለማየሁን ወደ ብሪንግተን ባለፈው ሮብ ዕለት ወስደህ ለቄስ ብላኬ እንድታስረክብ ብለው አልታዘዘልኝም።........» ሲሉ አስታወቁ።

የንግሥት ቪክቶሪያ ፀሐፊ ለእስፒዲ በላኩት ቴሌግራም ልጁን ብሪንግተን ወስዶ ከጄክስ ብላኬ ጋር እንዲያገናኝና እንዲያስተዋውቃቸው የሚቀጥል ትእዛዝ እስኪደርሰው ግን ልጁ ከሱ ጋር እንዲቆይ የሚል ትእዛዝ ላኩለት። እስፒዲ ይህ ቴሌግራም እንደደረሰው ወዲያው ተከታትሎ ሌላ ቴሌግራም ደረሰው። ይህን ለሁለተኛ ጊዜ የደረሰው ቴሌግራም አለማየሁ ንግሥቲቱ ሊያዩት ስለሚፈልጉ እሮብ ለት ልጁን ይዘህ ወደ ወኢንዲሰር አንድትመጣ የሚል ነእብር።

ንግሥት ቪክቶሪያ ዓለማየሁ ባንድ ጊዜ ከሚወደው ከእስፒዲ መለያየቱን አልፈለጉም። ከቄስ ጄክስ ብላኬ ዘንድ ሆኖ ደግሞ እንዲማር ይፈልጋሉ። ስለዚህ ዓለማየሁ ከቄስ ብላኬ ዘንድ ገብቶ ከልጆቹ ጋር እስኪለማመድ ድረስ እስፒዲ ለአንድ ዓመት በእንግሊዝ አገር ሆኖ እየተመላለሰ እየጠየቀ እንዲያለማምደው አዘዙ። ዓለማየሁ ከቄስ ብላኬ ዘንድ በሚገባበትም ጊዜ የፈለገውን ነገር በደብዳቤ እየጻፈ ለእስፒዲ እንዲልክ የሚፅፈውንም ደብዳቤ ከመላኩ በፊት ማንም ሰው እንዳያነበው በኋላ ግን የተጻፈውን ደብዳቤ በሚስጥር እየታየ የሚፈልገውን ሁሉ እንነገር እንዲያደርግለት አዘዙ።

ዓለማየሁ የካቲት 25 ቀን 1864 ዓ፣ም ለቄስ ብላኬ ተሰጠ። እስፒዲ ለቄስ ብላኬ ሊሰጠው ይዞት ሲሔድ ዓለማየሁ ባባ። እስፒዲም ጥሩ ቤት መሆኑን እሱም እንደማይለየው በቤቱም ብዙ ልጆች ስላሉ ከትምህርት መስል ብዙ ጨዋታ እንደሚጫወቱ እየነገረ ወሰደው። ቄስ ብላኬ ዘንድ ሲደርሱም ለዓለማየሁ ከፍተኛና ደስ የሚያሰኝ አቀባበል ተደረገለት። የምሣ ሰዓት ሲደርስም እስፒዲ ባለበት አብረውት ከቤተሰቡ ጋር ምሳቸውን በሉ። እስፒዲ ለዚያች ዕለት ካረፈበት ሆቴል ከዓለማየሁ ጋር ለመጨረሻ ጊዜ አበው እንዲያድሩ ቀኤስ ብላኬን ለመናቸው። ቄሱ ግን አይቻልም አሉ። እስፒዲ «እኔ በማይመቸኝም ጊዜ ባለቤቴ እየመጣች እንድታየው እንዲፈቀድላት ይሁን» ብሎ ቢጠይቃቸውም ቄሱ መልስ ሳይሰጡ እያጉረመረሙ ዝም አሉ።

በዚይ የተበሳጨው እስፒዲ ጉዳይን ለንግሥት ቪክቶሪያ አሳወቀ። ንግሥቲቱም ማንኛውም የተጠየቀው ነገር ሁሉ በትክክል እንዲፈጸም አዘዙ። ሉዊ ሁኔታው ሁሉ መስተካከሉን ካዩ በኋላ በየካቲት ወር መጨረሻ ማርች 1 ቀን ለቢድልፍ በጻፉት ደብዳቤ «........አሁን የዓለማየሁ የታሪክ ምዕራፍ

ስለተዘጋ በጣም ደስ ብሎኛል። የንግሥታችን ምኞትና ሐሳብ ካፒቴን እስፒዲና ቤተሰቦቹን እንዲጐበኙት የሚለው ሁሉ ተሳካ......» ብለዋል።

የካቲት 29 ቀን (ማርች 8) የተሰበሰውበው የእንግሊዝ ምክር ቤት የዓለማየሁን ጉዳይ አነሳው። በምክር ቤቱ አባል የሆኑት እስታፎርድ ኖርዝኮት ዓለማየሁ ከካፒቴን እስፒዲ ለምን እንደተለየ ጠየቁ ለዚህም ጉዳይ ሉዊ ሲመልሱ «.......ልጁ አሁን 11 ዓመቱ ነው። በዚህ ዕድሜ መሠረታዊ እውነት እንኳ አላገኘም.......በዚህም ምክንያት የመኳንንት ልጆች ካሉበት ትምህርት ቤት ከእኩዮቹ ጋር ሊማር አልቻለም። መጻፍና ማንበብ እንደማይችልም አምናለሁ።.......ለዚህ ብለን ነው.......» አሉ። እስፒዲም ከንግሥት ቪክቶሪያ ዘንድ ቀርቦ እስካሁን ድረስ ለዓለማየሁ ባደረጉለት ጥበቃና እንክብካቤ የመታሰቢያ ሰዓትና ሌላም ሽልማት ተሰጠው። ወዲያውም እይሱ ሞግዚትነት በማብቃቱ በመንግሥት ትእዛዝ አዲስ ወደ ተሾመበት አገር እንዲሄድ ተብሎ ወደ ፔናንግ ሔደ።

በዚህ ዘመን በግንቦት ወር ለዓለማየሁ ከአገሩ ከኢትዮጵያ የተጻፈ አንድ ደብዳቤ ደረሰው። ደብዳቤው የተጻፈው በአማርኛ ስለ ነበር የሚያነበው ሰው እንዲፈለግ ጄክስ ብላኬ ጉዳዩን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለሎርድ ኢንፊልድ አሳውቁ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዎልድሜየርን አፈላልጎ አገኘው። ዎልድሜየርም ደብዳቤውን እንዲተረጉም ተደረገ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሎርድ ኢንፊልድ ቅዳሜ ቀን ዎልድሜየርን ለማነጋገር ፈልገው ከቢሮአቸው ሆነው ስለደባቤው ይዞታ ተነጋገሩ። ዎልድሜየርም ደብዳቤው ከዓለማየሁ አያት ከእቴጌ ጥሩ ወርቅ እናት የተጻፈ መሆኑን ገለጡ። ደብዳቤው የሚለው አለማየሁ ለምን ወረቀት እንደማይጻፍላቸው የአበሻ ሕዝብም የእሱን መመለስ በጉጉት እንደሚጠብቅ የሚናገር መሆኑን አስረዱ። ኢንፊልድም ይህን ደብዳቤ ትርጉም ለሉዊ ላኩት። ከዚያ በኋላ ምን እንደ ሆነ አይታወቅም።

የዓለማየሁ ሞግዚቶችና ባለ አደራዎቹ ሥራ እንዲሠራ ወሰኑበት። በወጣለትም የሥራ ፕሮግራም መሠረት በሳምንት 31 ሰዓት ተኩል ማንኛውንም ሥራ ይሠራ ጀመር። የእስፒዲ ሚስት ይህን ተቃውማ ለቢዱልፍ አመለከተጭ። ቢዱልፍም ለሉዊ በጻፉት ደብዳቤ «.......ዓለማየሁ አንዳንድ ቀን እደ እስፒዲ ሚስት ዘንድ እየሐኢዱ እንዲውል ጄክሲ ብላኬን ብታዘው

ንግሥቲቱ ያዘዙት ትእዛዝ በመፈጸሙ ደስ ይላቸዋል። በዚህም በሚመጣው የበጋ ወራት የእስፒዲ ሚስት ወደ ምዕራብ ከመሔድዋ በፊት ከእሷ ጋር እንዲከርም አድርግ.......» ብለው ላኩበት።

በትእዛዙ መሠረት የእስፒዲ ሚስት እንድትጐበኘው ተፈቀደላት። እሱማ ካለበት ድረስ ሔዳ ዓለማየሁን ካየችውና ሲጫወቱ ከዋሉ በኋላ ለቢዱልፍ በጻፈችው ሪፖርት «........ማደጉን ቁመቱ አድጓል። መልኩ ግን ገርጥጧል። አካላቱም ከስቷል። ዝምተኛና ጭምትም ሆንዋል ከወንዶች ልጆች ጋርም እንዳይገናኝ ከእኩዮቹ እንዳይጫወት ተደርጓል። ከውጭ እየወጣም እንዳይዛለል ታግዷል። ብዙ ጊኤም እየደጋገመ የምጫወታቸው ወንዶች ልጆች አጣሁ። ቅዳሜና እሁድ ብቻ ከሌሎች ሁለት ልጆች ጋር መነጋገር ይፈቀድልኛል። እነኝም ሊያጫውቱኝ የሚመጡት ሁለት ልጆች ሁልጊዜ እነሱው ብቻ መሆናቸው ተሰላችተናል። በሌላ ቀን ግን የሌሎች ወንድ ልጆች እጅ እንኳ ጨብጬ አላውቅም ብሎ አጫውቶኛል ይህን የመሳሰሉት ነገሮች ያበሳጩታል።.......እኔም ብሆን ይህን የሚበሳጭበትን ለማስተው ጓደአ ልፈጥርለት አልቻልኩም። እየደጋገመ የነገረኝን ወንዶች ልጆች እፈልጋለሁ። የበለጠ እንድዛለልም እፈልጋለሁ።........እያለ ነው። በምግብ አበላሉ በኩልስ እንዴት ነህ ብዬ ብጠይቀው ምግብ አሁን አይበላልኝም ምክንያቱም ውጭ ወጥቼ ስለማልዛለልና ሰለማልጫወት አይርበኝም። የምበላው በትንሹ ነው ብሎ መለሰልኝ። እኔ እንደማስበው ዓለማየሁ ደስተኛና በሚደረግለት የረካ ልጅ አይደለም......» ብላ አመለከተች።

ቄስ ብላኬ ዘጠኝ ሴት ልጆች አሏቸው። ዓለማየሁ የሚኖረው ከእነኝህ ዘጠኝ ሴት ልጆች ጋር ነው። የቄስ ብላኬ ሚስት ሴቶች ልጆች የሴት ስራ እንዲሠሩ ስታስገድድ ዓለማየሁ ያለ ጓደኛ ይቀራል። ለዚያውም ቢሆን ወንድ ልጅ ብቻውን ከሴቶች ጋር መጭወቱ አይጣጣሙም። ሴቶቹም ቢሆኑ ከወንድ ጋር መጫወቱ አያግባባቸውም። ወንዱ እየሮጠ መዝለል ሲፈልግ የሴቶቹ ፍላጐት ቁጭ ብሎ የጨዋታ ወጥ መስራትና አሻንጉሊት ማሳመር ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ያለመገጣጠም ነው ዓለማየሁ አላስደስት ያለው።

የእስፒዲ ሚስት የጻፈችው ሪፖርት ከንግሥት ቪክቶሪያ ዘንድ ደረሰ። ንግሥቲቱም ስለዚህ ጉዳይ ሌዲ ኢሊይ አንድ ደብዳቤ ለቢዱፍ እንዲጽፍ አዘው ልዲይቱ በጻፉት ደብዳቤ «.......ትንሹ ልዑል በጥሩ ሁኔታ ሊጭወት

የሚችልበትና የሚያስደስተውን ዝላይ ሁሉ እንዲዛለል ጓደኞች እንዲዘጋጁለት ንግሥት አዘዋል።.......» ብለው ትእዛዝ አሳለፉ። በዚህ ምክንያት ዓለማየሁ ለሶስት ሳምንት እደ እስፒዲ ሚስት ዘንድ ተወሰደ። በዚያም የድሮ ጓደኖቹንና የሚወዳቸውንም ሰዎች ሁሉ አገኘ። የእስፒዲ ሚስትም ኦገስት 1 ቀን ለቢዱልፍ በጻፈችው ሪፖርት ዓለማየሁ በጥሩ ጤንነት በደስተኛ መንፈስ እንደሚገኝና በንባብ በጽሕፈትም እንደተሻሻለ አሳወቀች። ዓለማየሁንም የተለያዩ ፎቶ ግራፎች አንስታ ንግሥቲቱ ደስ እንዲላቸው ሁለቱን ፎቶ ግራፍ ለንግሥት ቪክቶሪያ ላከች።

በእስፒዲ ቤት የተፈቀደለትን የእረፍት ጊዜውን ከጨረሰ በኋላ እንደ ገና ደግሞ በቢብዱልፍ ቤት የሶስት ሳምንት ረፍት ለማድረግ ተወሰደ። ቢዱልፍ በዚህ ጊዜ በያዙት ማስታወሻ «......ይህ ምስኪን ልጅ የእረፍት ጊዜውን አጋማሽ ከኔ ጋር አሳልፏል። ጨዋ ልጅ ነው። ቢሆንም የዘሮቹ ኃይለኛነት አለበት።» በለዋል በዚያው በቢዱልፍ ቤት በከረመበት ጊዜ የቢዱልፍ ሚስት ዓለማየሁን ወደ ንግሥት ቪክቶሪያ ዘንድ ወስደውት ነበር። ንግሥቲቱ ሴፕቴምበር 6 በሚለው ማስታወሻቸው ላይ «.......ሜሪ ቢዱልፍ ትንሹን ዓለማየሁን ይዛው መጥታ ነበር። የሚወደድ የተከበረ ልጅ ነው። ጥቂት ጌጣጌጦችና አንድ የእኔን ፎቶ ግራፍ ሰጠሁት» ብለው ጽፈዋል።

ዓለማየሁ በሁሉም ዘንድ ያለውን የእረፍት ጊዜውን ጨርሶ ወደ ቦታው ተመለሰ። በቢዱልፍ ቤት በነበረበት ጊዜ ከሌዲ ቢዱልፍ ጋር በጣም ተዋደው ነበር። ከትምህርት ቤቱ ከተመለሰ በኋላ ለሌዲ ቢዱልፍ አንድ ደብዳቤ ጻፈ። ዛሬ ከዓለማየሁ ደብዳቤዎች በሚገባ ተቀምጦ የሚገኘው ይህ ለሌዲ ቢዱልፍ የጻፈው ብቻ ነው። ደባቤው እንዲህ ይላል። «.......በጣም ደህና እንደሆንሽ ተስፋ አለኝ። ይህን በመናገሬ አዝናለሁ እኒ አቶ ጄክሲ ብላኬ ግጥሚያውን ለማየት እንድመጣ አልፈቀዱልኝም። ከካፒቴን እስፒዲ የተጻፈ ደባቤም ድርሶኛል። እሱም እንዳለኝ ከጒበዝ ሰዎች ጋር ወደ ሕንድ መሔዱን ገልጾልኛል። ከቻይናዎቹ ጋር ከመዋጋታቸው በፊት ሰላም ይፈልጉ እንደሆነ የካሩትራጋ እንዲጠይቃቸው መደረጉን እነሱ ግን ይህን ነገር ሊሰሙትም እንደማይፈልጉ መናገራቸውን ሁሉ ገለጸልኝ። ራጋውም ለካፒቴን እስፒዲ ሲያጫውተው ሔደው ምሽጋቸውን እንዲይዙ በነገራቸው መሠረት ካፒቴን እስፒዲ መቶ ሰዎች ይዞ ሐኢደ ስድስት ምሽጐቻቸውን ወሰደባቸው። ካፒቴን

እስፒዲ እንደሚለው ቻይናዎቹ እንደ ጦር የሾለ ቀርከሃዎች ጫፋቸውን ደግሞ መርዝ እያደረጉ በመትከላቸ የማለያ ሰዎች ወደ ምሽጉ መትጋት ፈርተው ነበር። ሕንዶቹ ግን አልፈሩም። ምክንያቱም ቦት ጫማ ስላደረጉ ነው። ሰር እስታፎርድ ኖርዝኮት ስለኔ ጉዳይ ምን አደረገ። አሁን ክፍል ተዛውሬአለሁ። በክፍሌም ጥሩ ውጤቶች አገኛለሁ። በኃይል ስለምሠራም ሽልማት እንደማገኝ ተስፋ አለኝ። በቸልተንሃም ከቆየሁ እድገቴን አገኛለሁ። ግን ለማወቅ የምፈልገው ሰር እስታንፎድ ኖርዝኮት ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላል?»

በ1867 ዓ.ም ወደ ዓለማየሁ ወደ ራግቢ ትምህርት ቤት ተዛወረ። የተዛወረው ወደ ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ከቄስ ጀኢክሲ ብላኬ ቤት ወጥቶ ኪሊ ዋርነር ቤት እንዲኖር ተደረገ። በዚያም ስላልተደሰተ በቀጠለው ዓመት በዚያው ወር ሚስተር ድራፐር ቤት እንዲኖር ተደረገ። ወደዚህ የዞረው የዓለማየሁ እኩዮች የሆኑት አስር ያህል ተማሪ ልጆች ስላሉ ነው። ዓለማየሁ ወደ ራግቢ ትምህርት ቤት የገባው ቄስ ጄክሲ ብላኬ ወደዚያ ትምህርት ቤት ስለተዛወሩ እሱም አብሯቸው መዛወሩ ነበር። ዓለማየሁ በኑሮው ከቄስ ጄክሲ ጋር ባይገናኝም በትምህርት በኢት ግን ይገናኛሉ።

በ1886 ዓ.ም /1876 እ.ኤ.አ./ በግንቦት ወር ጄክሲ ብላኪ አንድ ሪፖርት ለቢዱልፍ አስተላልፈው ነበር። ሪፖርታቸውም «.......እኔ እንደምመኘው ያህል በትምህርቱ አልገፋም። እሱ ግን ጮሌ ነው........እንደማስበው ከሌላው የኑሮ ሕይወት ይልቅ ለውትድርና ተግባር የሚስማማ ነው። በወታደርነት ጥሩ ትምህርት ሊሰጠው ይገባል። በጨዋታም በጣም ጥሩ ውጤት የሚያመጣ ልጅ ነው። በተለይ በእግር ኳስ ጨዋታ በጣም ጉበዝ ነው። ምንጊዜም ቢሆን በመልካም ጠባይ ውጭ ሆኖ አላየሁትም.......» ብለዋል። በዚህ ሪፖርት መሠረት እንደ ኤሮፓ አቆጣጠር በሴፕቴምበር ወር 1878 ዓ.ም ያለ ምንም ፈተና ሳንድኸርት የወታደር ትምህርት ቤት እንዲገባ ተደረገ። በዚያን ዘመን በፓሪስ ከተማ የዓለም ኤግዚቪሽን ይታይ ስለነበረ ዓለማየሁ ባልደረባ ተሰጥቶት ፓሪስ ሔደ ኤግዚቪሽኑን እንዲያዩ ተደረገ። ከዚያም ተመልሶ ትምህርት ቤት ገባ።

አንድ ጊዜ ለእረፍት ወደ ዲቮንሻየር መጥቶ ሶስት ሳምንት ያህል በኖርዝኮት ቤት ሰንብቶ ነበር። ከዚያ ከርሞ በተመለሰበት ጊዜ ኖርዝኮት እ.ኤ.አ. ጥቅምት 20 ቀን ለሌዲ ቢዱልፍ በጻፉት ደብዳቤ «........ልጁ

በትውልድ አገሩ ላይ ማተኮርና ማሰብ ጀምሯል። በአገሩም ሁለት አክስቶችና አንድ ወንድም እንዳለው ይናገራል እኔም ወደ አበሻ የመመለስህ ጉዳይ የማይታሰብ ነው ብየዋለሁ። በእንግሊዝ አገር እኮ እንደ አቶ ራንስም የሚያስደስተኝና ሁሉን ነገር የሚያደርግልኝ ሰው አንድም የለም ይላል ወደ እሱም እንድ ለመሔድ ይፈልጋል።.......» ብለው ነበር።

በዚያው ዘመን ወደ ሊድስ ሔደ በጠየቀው መሠረት በሚስተር ሰሪል ራምሶን ቤት ተቀምጦ ሳለ በጥቅምት ወር ታመመ። ኖርዝ ኮትም ስለ ዓለማየሁ ሐመም ለሌዲ ቢዱልፍ ደብዳቤ ጻፉ «......አደገኛ የሆነ ሕመመ መታመኡን እንድታውቁ ይሁን። ምንም ጥረት ብናደርግ ሕመሙ እየጠናበት ሔደ። .......ሕመሙ አደገኛ በመሆኑና በጣም ስለጠናበትም........አሁን ምግብ አይበላም መድኃኒትም አይወስድም።.......»


አለማየሁ ቴዎድሮስ

ሐኪሙ ዶክተር ክሊፎርድ ከሎች ሐኪሞች ጋር ሆነው ያክሙታል። ሰር ዊላይም ጉር እና ጀምስ ፖርት ከአጠገቡ እንዳይለዩና አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርጉለት ታዘዋል። ንግሥት ቪክቶሪያም መታመሙን እንደሰሙ ሌዲ ቢዱልፍ ሔደው አይተውት ሁኔታውን እንዲነግሩዋቸው በስልክ ታዘዙ። ንግሥቲቱ በጠና መታመሙን ሲነገራቸው ለዓለማየሁ አንድ የማጽናኛ ደብዳቤ ጽፈው ላኩለት። ዓለማየሁ የንግሥቲቱ ደብዳቤ እንደደረሰው «.......ከየት የመጣ ነው ብሎ ጠየቀና ከንግሥቲቱ መስመሮችን አነበበ። ግን ሐምሙ ስላስቸገረው ጨርሶ ሊያነበው አልቻለም። እኔንም ጠራኝና ደብዳቤውን ሊያየው ከሚችልበት ቦታ እንዳስቀምጥለት ጠየቀኝ። በዚያም ባስቀመጥኩለት ቦታ ሳይነሳ እስከ መጨረሻ ድረስ ቆየ።........» በማለት የንግሥቲቱ መልዕክተኛ ሰር ጀን ኮዌል ጽፈዋል።

ለዓለማየሁ አልጋ አጠገብ የቄስ ጀክስ ብላክኢ ሚስትና ራንሶም ተቀምጠዋል። አለማየሁ የሁለቱንም እጆች እንደያዘ ሕዳር 5 ቀን 1872 ዓ.ም ኖቬምበር 14 1879 ከጧቱ በሶስት ሰዓት ተሩብ በተወለደ በ19 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። በንግሥት ቪክቶሪያ ትእዛዝ ዊንድሰር ባለው የነገሥታት መቀበሪያ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ። በመቃብሩም ላይ

የአበሻው ልዑል ዓለማየሁ


አፕሪል 13.1861 ተወለደ

ኖቨምበር 14. 1879 አረፈ። የሚል አረፍተ ነገር ተጻፈበት። ንግሥት ቪክቶሪያ ግን ከዚህ ጽሑፍ በታች «እንግዳ ሆኜ መጣሁ ተቀበላችሁኝም» የሚለው የወንጌል ቃል እንዲጻፍበት አዘው ተጻፈበት።

# ዋቢ መጻሕፍት


| | |
|---|---|
| ሐንሪ ብላንክ (ዶክተር) | የአሥራት ዘመን በአበሻ አገር ትርጉም ዳኘው ወልደሥላሴ |
| ተክለ ኢየሱስ (አለቃ) | የኢትዮጵያ ታሪክ ያልታተመ |
| ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ( አለታ) | ሃይማኖተ አበው ቀደምት |
| ወልደ ማርያም ( አለቃ) | የዳግማዊ ቴዎድሮስ ታሪክ |
| ዘነበ (ደብተራ) | የቴዎድሮክ ታሪክ |
| ገሪማ ታፈረ | አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ |
| ALAN MOOREMEAD | THE BLUE NILE |
| GIRMA SELASSIE ASFAW & DAVID LAPPLE YARD | THE AMHARIC LETTERS OF EMPEROR THEODORE OF ETHIOPIA |
| HENRY DUFTON | NARRATIVE OF A JOURENY THROUGH ABYSSINIA |
| MARKHAM, CR | HISTORY OF ABYSSINIA EXPEDITION |
| PLOWDEN, W.C. | TRAVELS IN ABYSSINIA |
| POLSON NEWMANN | ETHIOPIAN REALITIES |
| RASSAM NORMUZD | NARRATIVE OF THE BRITISH MISSION TO THEOOORE KING OF ETHIOPIA VOL. 1, 2 |
| STANLEY, H.M. | COOMASSIE AND MAGDALA |
| SYEN. RUBENSON | 1) KING OF KINGS TEWOOROS OF ETHIOPIA |

| | |
|---|---|
| | 2) THE SURVIVAL OF ETHIOPIAN INDEPENDENCE |
| WALDMEIER, T | TEN-YEARS LIFE IN ABYSSINIA |



## ስለደራሲው በጥቂቱ

ደራሲ ጳውሎስ ኞኞ ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ቁልቢ አካባቢ ተወልደው ድሬዳዋ ከተማ አደጉ። በጣሊያን ወረራ ምክንያት ትምህርታቸውን ከ4ኛ ክፍል በላይ ለመቀጠል አልቻሉም ነበር። ብልህ አዕምሮና የፈጠራ ችሎታ የነበራቸው ሰው ስለነበሩ፤ በልጅነታቸው የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ጣሊያንን ሲገድሉ ወይንም ሲማርኩ ሥዕል በመሣል ያሳዩ ነበር። ጳውሎስ ካላቸው የጽሑፍ ጥማት የተነሳ የ«ድምጽ ጋዜጣ» አዘጋጅ በመሆን የብዕር ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር። ጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሠርተዋል። በተለይ «አንድ ጥያቄ አለኝ» በሚለው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምዳቸው ላይ ብዙ ታዋቂነትን አግኝተዋል። አቶ ጳውሎስ ኞኞ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ዕድገት የነበራቸውን ተሰጥኦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያዋሉ እውቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበሩ። እኚህ ታዋቂ ሰው በተወለዱ በ58 ዓመታቸው አረፉ።

ከጋዜጠኝነታቸው ጎን ለጎን በድርሰትና በታሪክ ጸሐፊነታቸውም ፲፱ መጻሕፍት የታተመላቸው ሲሆን ሁለቱ ካረፉ በኋላ የታተሙ ናቸው። ለሕዝብ የሚሆኑ ዕውቀት ተኮር መጻሕፍት በማቅረብ ይታወቁ የነበሩት አቶ ጳውሎስ ኞኞ ካረፉ ከ፳ ዓመታት በኋላ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸውንና ወደውጭ አገር የላኳቸውን ደብዳቤዎች የሚያሳዩት ሁለት መጻሕፍት በአስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት አማካይነት ታትመዋል።

<u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. ከሴቶቹ አምባ (**ልብወለድ**)
2. የአራዳው ታደሰ (**ልብወለድ**)
3. የጌታቸው ሚስቶች (**ልብወለድ**)
4. ድብልቅልቅ (**ልብወለድ**)

5. የኔዎቹ ገረዶች (**ልብወለድ**)
6. አጤ ቴዎድሮስ (**ታሪክ**)
7. አጤ ምኒልክ (**ታሪክ**)
8. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት (**ታሪክ**)
9. አስደናቂ ታሪኮች (**ታሪክ**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY